# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣

## የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓቶች ክዋኔ ትንተና፤ በአፋር ክልል፣ ዞን ሶስት፣ አርጐባ ልዩ ወረዳ

**በ**

**እታገኘሁ አስረስ**

**የካቲት፣ 2017 ዓ.ም.**

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣
የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የአርጎባ ብሄረሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓቶች ክዋኔ ትንተና፤ በአፋር ክልል፣ ዞን ሶስት፣ አርጎባ ልዩ ወረዳ

በ
እታገኘሁ አስረስ

የካቲት፣ 2017 ዓ.ም.

# የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓቶች ክዋኔ ትንተና፤ በአፋር ክልል፣ ዞን ሶስት፣ አርጐባ ልዩ ወረዳ


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ

ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣


የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

በፎክሎር የዶክትሬት ዲግሪ ከፊል ማሟያ ጥናት


በ

እታገኘሁ አስረስ

አማካሪዎች

ዘሪሁን አስፋው (ተባባሪ ፕሮፌሰር)

የኔዓለም አረዶ (ዶ/ር)

መሐመድ አሊ (ዶ/ር)



የካቲት፣ 2017 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓቶች ክዋኔ ትንተና፤ በአፋር ክልል፣ ዞን ሶስት፣ አርጐባ ልዩ ወረዳ

በ

እታገኘሁ አስረስ

የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም ______________________ ፊርማ ________________

______________________ ፊርማ ________________

የውስጥ ፈታኝ ስም ______________________ ፊርማ ________________

የውጭ ፈታኝ ስም ______________________ ፊርማ ________________

## ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና ........................................................................................ i
ሙዳየ ቃላት ........................................................................................ iii
አጠቃሎ ........................................................................................ vi
**ምዕራፍ አንድ መግቢያ**........................................................................................ 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ........................................................................................ 1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........................................................................................ 2
1.3. የጥናቱ ዓላማ ........................................................................................ 3
1.3.1. ዓቢይ ዓላማ ........................................................................................ 3
1.3.2. ዝርዝር ዓላማዎች ........................................................................................ 3
1.4. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች ........................................................................................ 4
1.5. የጥናቱ ወሰን ........................................................................................ 4
1.6. የጥናቱ ጠቀሜታ ........................................................................................ 5
1.7. የጥናቱ አደረጃጀት ........................................................................................ 6
**ምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳናት** ........................................................................................ 7
2.1. የጽንሰ ሀሳብ ማብራሪያ ........................................................................................ 7
2.1.1. የስነ ስርዓት ምንነት ........................................................................................ 7
2.1.2. የስነ ስርዓት ምድቦች........................................................................................ 9
2.1.3. የስነ ስርዓት ባህርያት ........................................................................................ 9
2.1.4. የስነ ስርዓት ተግባራት ........................................................................................ 10
2.1.5. የስነ ስርዓት ለውጥና ቀጣይነት ........................................................................................ 12
2.1.6. የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓት ምንነት ........................................................................................ 12
2.1.6.1. ወሊድ ........................................................................................ 13
2.1.6.2. ጋብቻ ........................................................................................ 14
2.1.6.3. ሞትና ሀዘን ........................................................................................ 15
2.2. የንድፈ ሀሳብ ማሕቀፍ ........................................................................................ 15

2.2.1. የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ ........................................................ 15
2.2.2. መዋቅራዊ ንድፈ ሀሳብ .............................................. 17
2.2.3. ትዕምርታዊ ንድፈ ሀሳብ ........................................... 20
2.2.4. ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ............................................... 21
2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ................................................... 23
ምዕራፍ ሶስት የጥናቱ ስነ-ዘዴ ............................................................ 28
3.1. የጥናቱ ንድፍ ................................................................... 28
3.2. የጥናት ቦታና የመረጃ ሰጪዎች መረጣ ..................................... 28
3.2.1. የጥናት ቦታ መረጣ........................................................ 28
3.2.2. የመረጃ ሰጪዎች መረጣ .................................................. 29
3.3. መረጃ የተሰበሰበባቸው መቼቶች ............................................. 30
3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች .................................................. 30
3.4.1. ሰነድ ፍተሻ ................................................................ 31
3.4.2. ምልከታ ...................................................................... 31
3.4.3. ቃለመጠይቅ ................................................................. 33
3.4.4. ቡድን ተኮር ውይይት .................................................... 35
3.5. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ......................................................... 37
3.6. የመረጃ መተንተኛ አንፃር...................................................... 37
3.7. የመቅረጫ መሳሪያዎች ምንነትና አጠቃቀም .............................. 38
3.8. ትራንስክሪፕሽን ................................................................ 40
3.9. የጥናትና ምርምር ስነ ምግባር .............................................. 40
3.10 የመስክ ስራ ክንውን ሂደት................................................. 41
ምዕራፍ አራት የአርጐባ ብሄረሰብ መግለጫ........................................... 45
4.1. ብሄረሰቡ የሚኖርበት መልክዓ ምድር ገጽታ.............................. 45
4.2. የብሄረሰቡ ስያሜ............................................................... 48
4.3. ታሪክና አመጣጥ............................................................... 49
4.4. ማህበራዊ መዋቅር.............................................................. 52
4.5. ቋንቋ ............................................................................... 53

4.6. ሀይማኖት/ እምነት ....................................................................55
4.7. ኢኮኖሚ ..................................................................................... 55
4.8. አመጋገብ ...............................................................................57
4.9. ባህላዊ ስነ ህንፃ......................................................................57

ምዕራፍ አምስት የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ ስነ ስርዓት ........................................ 58
5.1. የልጅ መውለድ እሳቤ በአርጐባ..............................................................58
5.2. የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ ስነ ስርዓት፤ ክዋኔው፣ መዋቅሩና
ትዕምርቱ ........................................................................................60
5.2.1. መለየት ........................................................................ 61
የቅምሻ ስነ ስርዓት..........................................................62
5.2.2. ሽግግር..........................................................................62
5.2.2.1. ለነፍሰጡር የሚደረግ እንክብካቤ...............................63
5.2.2.2. ለነፍሰጡር የሚከለከሉ ነገሮች..................................66
5.2.2.3. ለነፍሰጡር የሚሰጥ ምክር.......................................67
5.2.2.4. የአምሮት ስነ ስርዓት..............................................67
5.2.2.5. የወሊድ ዝግጅት.....................................................82
5.2.2.6. የወሊድ ስነ ስርዓት............................................ 87
5.2.2.7. ላንቃ ማንሳት..................................................... 100
5.2.2.8. የደም ዶሮ እርድ.................................................. 101
5.2.2.9. የልጅ ጓሮ ቀበሩ.............................................. 102
5.2.2.10. የአራስ ቤት ገጽታና እንክብካቤ ..........................103
5.2.2.11. አራስ ጠያቂዎች.............................................. 109
5.2.2.12. የሰባት ቀን እጥበት ስነ ስርዓት.......................... 110
5.2.3. መቀላቀል.......................................................................119
5.2.3.1 የአርባ ቀን እጥበት ስነ ስርዓት............................ 119
5.2.3.2. የማዘየሪያ ስነ ስርዓት...........................................120
5.2.3.3. የቁንጮ መጣያ............................................... 121
5.3. የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ ፋይዳ ........................ 122

5.4. የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ ለውጥና ቀጣይነት........... 124
5.4.1. የተከሰቱ ለውጦች ከለውጥ ምክንያቶቻቸው አንፃር...................124
5.4.1.1. ዘመናዊነት ያስከተለው ለውጥ ..............................124
5.4.1.2. የኢኰኖሚ ጫና ያስከተለው ለውጥ ..........................128
5.4.2. ያልተለወጡ ጉዳዮች.............................................. 128

ምዕራፍ ስድስት የአርጐባ ብሄረሰብ የጋብቻ ስነ ስርዓት .................................. 129
6.1. የጋብቻ እሳቤ በአርጐባ..............................................................129
6.2. የጋብቻ ዓይነቶችና የጋብቻ እድሜ...............................................130
6.3. የትዳር አጋርን የመምረጫ መስፈርቶች.........................................131
6.4. የአርጐባ ብሄረሰብ የጋብቻ ስነ ስርዓት፤ ክዋኔው፣ መዋቅሩና ትዕምርቱ ............................................................................ 133
6.4.1. ቅድመ መለየት ክዋኔዎች ............................................ 133
6.4.1.1. የማጨት ሂደት................................................... 134
6.4.1.2. የስለላ ስነ ስርዓት............................................ 135
6.4.2. መለየት ............................................................. 136
የቆዳ ማንጠፊያ ስነ ስርዓት.............................................136
6.4.3. ሽግግር...........................................................................143
6.4.3.1 የነገር መፍጃ ስነ ስርዓት.........................................143
6.4.3.2 የሰርግ ስነ ስርዓት ዝግጅት.......................................148
ሀ. ከሰርጉ ቀን ቀደም ተብሎ የሚደረጉ ዝግጅቶች......... 149
ለ. ሰርጉ ሲቀርብ የሚደረጉ ዝግጅቶች........................ 153
6.4.4. መቀላቀል.............................................................. 158
6.4.4.1 የሰርግ ስነ ስርዓት............................................. 158
6.4.4.1.1. የሰርግ ስነ ስርዓት ክዋኔ ...................... 159
6.4.4.1.2. የሰርግ ስነ ስርዓት ክዋኔ በሙሽራው ቤተሰብ ቤት........................................... 164
6.4.4.1.3. የሰርግ ስነ ስርዓት ክዋኔ በሙሽራዋ ቤተሰብ ቤት..................................... 166

ሀ. የሙሽራዋ፣ የሚዜዎቿና አጃቢዎቿ የጋራ
ቆይታ.............................................. 166
ለ. የጉፍታ መጫን ስነ ስርዓት..........................168
ሐ. የኒካህ ማሰር ስነ ስርዓት............................ 171
መ. የወግ ማስረከብ ስነ ስርዓት......................... 173
ሠ. የገበታ ስነ ስርዓት.................................... 177
ረ. የሙሽሮች አወጣጥ ስነ ስርዓት....................... 178
6.4.4.1.4. የጫጉላ ቤት ስነ ስርዓትና ለድንግልና
የሚሰጥ ዋጋ........................................... 182
6.4.4.2 የባዱሼህ ስነ ስርዓት........................................ 184
6.4.4.3. የደመቅሁ ስነ ስርዓት........................................ 187
6.4.4.4. የመልስ ስነ ስርዓት............................................ 189
6.4.4.5. የጐጆ መውጫ ስነ ስርዓት.................................... 193
6.5. የአርጐባ ብሄረሰብ የጋብቻ ስነ ስርዓት ክዋኔ ፋይዳ....................... 197
6.6. የአርጐባ ብሄረሰብ የጋብቻ ስነ ስርዓት ክዋኔ ለውጥና ቀጣይነት......... 199
6.6.1.የክዋኔ ለውጦች ........................................................... 199
6.6.1.1. ቀጥተኛ ለውጦች ............................................. 199
6.6.1.2. ዘመናዊነት ያስከተለው ለውጥ.................................. 204
6.6.1.3. የሌላን ባህል ተቀብሎ በመከወን ምክንያት የተከሰቱ
ለውጦች ......................................................208
6.6.1.4. ኢኰኖሚያዊ ጫና ያስከተለው ለውጥ..................... 209
6.6.1.5. ሆን ተብሎ የተደረጉ ለውጦች ............................ 209
6.6.2. የመዋቅር ለውጥ ...........................................................210
6.6.3. ያልተለወጡ ጉዳዮች ....................................................... 210
ምዕራፍ ሰባት የአርጐባ ብሄረሰብ የሀዘን ስነ ስርዓት...................................... 212
7.1. የሞት እሳቤ በአርጐባ.......................................................................... 212
7.2. የአርጐባ ብሄረሰብ የሀዘን ስነ ስርዓት፣ ክዋኔው፣ መዋቅሩና
ትዕምርቱ ........................................................................................ 214
7.2.1. መለየት ........................................................................... 214

7.2.2. ሽግግር…………………………………………………………… 218
ሀ. ጥሪ ማድረግ……………………………………………… 218
ለ. ዳስ መጣል……………………………………………. 220
ሐ. መሸኛ ማዘጋጀት………………………………….…. 220
መ. የመቃብር ጉድጓድ መቆፈር……………….………….. 221
ሠ. አስከሬን ማለስለስ…………………………………….. 224
ረ. አስከሬን ማጠብና መገነዝ ……………………….….. 226
ሰ. የአለቃቀስ ስነ ስርዓት፣ ለቅሶ የመድረስና
የመረዳዳት ልማድ……………………………..……232
ሸ. ሀዘን ደራሾችን በምግብ ማስተናገድ……………………235
ቀ. አስከሬን ከቤት ሲወጣ የሚከወን ስነ ስርዓት………… 236
በ. የቀብር ስነ ስርዓት……………………………………. 239
ተ. በቀብር ቀን ከቀብር መልስ የሚከወን ስነ ስርዓት……..242
ቸ. የሀፊሻ ስነ ስርዓት ………………………………………243
7.2.3. መቀላቀል……………………………………………………….. 245
7.2.3.1. የቆዳ ማጠፊያ ስነ ስርዓት……………………….…. 249
7.2.3.2. የወር መታሰቢያ ስነ ስርዓት……………………….…. 253
7.2.3.3. የዓግል መፍቻ ስነ ስርዓት…………………….…….. 253
7.2.3.4. ጠም ቆሎ…………………………………………….. 255
7.2.3.5. የክረምት ዚያራ……………………………………… 256
7.2.3.6. ዚያራ…………………………………………………… 257
7.3. የአርጐባ ብሄረሰብ የሀዘን ስነ ስርዓት ክዋኔ ፋይዳ……………………… 259
7.4. የአርጐባ ብሄረሰብ የሀዘን ስነ ስርዓት ክዋኔ ለውጥና ቀጣይነት………… 260
7.4.1. የተከሰቱ ለውጦች ከለውጥ ምክንያቶቻቸው አንፃር……………………….. 260
7.4.1.1. ቀጥተኛ ለውጦች ……………………………………………….. 261
7.4.1.2. ዘመናዊነት ያስከተለው ለውጥ…………………………………… 261
7.4.1.3. ሆን ተብሎ የተደረጉ ለውጦች……………………………….… 262
7.4.2. ያልተለወጡ ጉዳዮች………………………………………………….. 262

**ምዕራፍ ስምንት ማጠቃለያ፣ ግኝት እና ይሁንታ** ........................................ 263

የዋቢ መጻሕፍትና ጽሁፎች ዝርዝር ..................................................271

አባሪ

አባሪ 1. መሰረታዊ የምልከታ ጥያቄዎች

አባሪ 2. ምልከታ የተከናወነባቸው ስነ ስርዓቶች

አባሪ 3. ለመረጃ ሰጪዎች የቀረቡ መሰረታዊ ጥያቄዎች

አባሪ 4. የመረጃ ሰጪዎች ዝርዝር

አባሪ 5. የተደረጉ መደበኛ ቡድን ተኮር ውይይቶች ዝርዝር

አባሪ 6. የአፋር ክልልና የአርጐባ ልዩ ወረዳ ካርታ

## ምስጋና

የጥናት ጽሁ□ን በተደጋጋሚ በማረም፣ በማቃናት፣ ሀሳብ በመስጠት እንዲሁም መጻሕፍት በመስጠት ትልቅ እገዛ ላደረጋችሁልኝ አማካሪዎቼ ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስፋው፣ ዶ/ር መሐመድ ዓሊ እና ዶ/ር የኔዓለም አረዶ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ ሲያማክሩኝ ቆይተው ድንገት በህይወት ያጣነዎ ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስፋው ነፍስዎ በሰላም ትረፍ!

ትምህርቱን እንድማር የፈቀደልኝን የኢትዮ□ያ ቅርስ ባለስልጣን መ/ቤት አመሰግናለሁ፡፡

የአርጎባ ተወላጅ የሆኑት አቶ መሐመድ አቡበከር በመስክ ስራዬ ወቅት መረጃ በመስጠት፣ መረጃ ሰጪዎችንና የጥናት ናሙና ቦታዎችን በመጠቆም፣ በማስተባበር፣ በመምከርና አቅጣጫ በመጠቆም፣ ማረፊያ በመስጠት፣ በየተዘዋወርኩባቸው ሩቅ የገጠር ቀበሌዎች ሁሉ አብረውኝ በመጓዝ፣ ሰዎችን በማስተዋወቅና የመረጃ መሰብሰብ ስራውን በማመቻቸት አብረውኝ ደክመዋል፡፡ እርስዎ አጠገቤ ባይሆኑ የመስክ ስራው ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አልችልም፡፡ ላደረጉልኝ ሁሉ አመሰግንዎታለሁ፤ አላህ ውለታዎን ይክፈል!

በመስክ ስራ ወቅት መረጃ በመስጠት የደከማችሁልኝን መረጃ ሰጪዎቼን በሙሉ አመሰግናለሁ፡፡ በተለይ ቁልፍ መረጃ ሰጪዎቼ የነበራችሁት ወ/ሮ ሲቲ ፋጡማ መሐመድ፣ ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ ወ/ሮ እመይ መሐመድ ነጋሽ፣ አቶ አህመድ ሲራጅ፣ ወ/ሮ ሶህሊየት ባቢ፣ አቶ ኑርዬ በሽር፣ ወ/ሮ ሷቢራ ኡመር፣ ወ/ሮ አይኔ ይማሙ፣ አቶ አደም መሐመድ፣ አቶ ፋንታዬ መሐመድ ኑርና ሌሎቻችሁም ከፍ ያለ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ! ከመረጃ መሰብሰብ ስራው በኋላ በህይወት የተለዩን መረጃ ሰጪዬ ወ/ሮ ሳሱየ አሊየ (የነፊሳ እናት) አላህ ነፍሳቸውን ይማርልን፡፡

የአርጎባ ልዩ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት ለጥናቱ የሚሆን የገንዘብና የተሽከርካሪ ድጋፍ ስላደረገልኝ እጅግ በጣም አመሰግናለሁ፡ ለተደረገልኝ ድጋፍ አቶ ፊቂ አህመድን እና አቶ ሙጎ ቡሽራን አመሰግናለሁ፡፡ አቶ መሐመድ አሚን ኢብራሂም እና አቶ ኻሊድ በድሩ ወደ ገጠር ቀበሌዎች ባደረግሁት ጉዞ ከመልካም ባህርይ ጋር የሹፍርና አገልግሎት ስለሰጣችሁኝ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

በወቅቱ የአርጐባ ልዩ ወረዳ የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሀላፊ የነበረው አቶ ሁጤል፣ የ"ማደግ በጋር" የባህል ቡድን መሪ አቶ ዩሱፍ መሐመድ (አባዬ) እና የቡድኑ አባላት በመስክ መረጃ የመሰብሰብ ስራ ወቅት ላደረጋችሁልኝ ትብብር በጣም አመሰግናችኋለሁ፡፡

የአቶ መሐመድ አቡበከር ባለቤት ወ/ሮ ነፊሳ እንደ እህት ሆነሽ ሀሳብ በመስጠትና በማማከር ከጐኔ ስለነበርሽ፣ ቤትሽ ማረፊያ እንዲሆነኝ ስላደረግሽ፣ የእንግዳነት ስሜት እንዳይሰማኝ አድርገሽ ራሴን እንደ ቤተሰቡ አባል እንዳስብ ስላደረግሽኝ፣ በገጠር ቀበሌዎች በቆየሁባቸው ጊዜያትና ከተደጋጋሚው የመስክ ስራ በኋላም ሁሉ እየደወልሽ ምን ደረስሽ እያልሽ በሀሳብ ከእኔ ጋር ስለነበርሽ በጣም አመሰግንሻለሁ፡፡

በሄድኩባቸው የገጠር ቀበሌዎች ቤታችሁን ማረፊያ አድርጋችሁ፣ እየጋበዛችሁ በእንግዳ አቀባበል ደንብ በቤታችሁ የተቀበላችሁኝና ያስተናገዳችሁኝ ወ/ሮ አይሻ አብዱልጀሊልና ባለቤቷ አቶ አህመድ መሐመድ ሼህ ዩሱፍ፣ ወ/ሮ ሷቢራ ኡመር፣ አቶ ኑርዬ በሽር እና ወ/ት አይሻ አህመድ አላህ ውለታችሁን ይክፈላችሁ!

በመስክ እህትና ወንድም የሆናችሁኝ ወ/ሮ ጀሚላ አህመድ እና አቶ ኑርሁሴን መሐመድ አጠገቤ ሰው አለ ብዬ እንዳስብ ያደረጋችሁኝና በፍቅር ያስተናገዳችሁኝ ናችሁና ክበሩልኝ፡፡ አላህ ውለታችሁን ይክፈላችሁ! በተጨማሪም አይዞሽ ብላችሁ አጋርነታችሁን ላሳያችሁኝና የመስክ ስራው እንዳይስተጓጐል ለረዳችሁኝ አቶ ሱልጧን መሐመድ፣ ወ/ሮ ሩቅያ አሙ፣ አቶ አብዱሰላም አወል፣ አቶ ሙስጠፋ ሽሁ እና አቶ መሐመድ ሷሊህ አላህ አለሁ ይበላችሁ!

አስፈላጊ ዶክመንቶችን በማዋስና በርቺ በማለት ጉልበት ለሆንከኝ ዶ/ር ታከለ መርዕድ ምስጋናዬ ይድረስህ፡፡

አቶ ኡመር መሐመድ እና ወ/ሮ ሲቲና አሚኖ የቁርዓን አንቀፆችን በማመላከት ላደረጋችሁልኝ ትብብር በጣም አመሰግናለሁ፡፡

## ሙዳየ ቃላት[1]

| አካባቢያዊ ቃል | አቻ የአማርኛ ፍች |
|---|---|
| ሀጃ | ጉዳይ |
| ለኸድ | አስከሬን የሚያርፍበት የመቃብር ክፍል፣ ኪስ |
| ሉሀ | ሰሌዳ |
| ላዚም | የአንገት ጌጥ |
| መርሀባ | መቀበልን፣ መስማማትን መግለጫ |
| መሸለል | የሺሎ ጨዋታን መጫወት |
| መዋስ | የተለፋ የከብት ቆዳ |
| መዘየር/መዚያየር | ሰላምታ መስጠት፣ መጠየቅ፣ መገናኘት |
| መደሳት | መደሰት |
| መጀን | ይሁንብህ ማለት፣ መለመን፣ መማለድ |
| ሙራድ | ሀሳብ፣ ምኞት፣ ፍላጎት |
| ሙሰሪፍ | ጠባቂ አምላክ |
| ሩሀ | ነፍስ |
| ርዚቅ | ሲሳይ፣ የፈጣሪ ስጦታ |
| ሰለዋት | የእስልምና ሐይማኖት ፀሎትና ስግደት |
| ሰለዋት ጂናዛ | ለሙት የሚደረግ ስግደት |
| ሰብር/መሶበር | መታገስ፣ መበርታት |
| ሱቢሀ | ጎህ ሲቀድ ጀምሮ እስከ ጀምበር መውጣት ያለው ጊዜ |
| ሶደቃ | በሀዘን ስነ ስርዓቶች ላይ ተዘጋጅቶ የሚቀርብ ምግብና መጠጥ፣ ለተቸገሩ ሰዎች የሚሰጥ ምጽዋት |
| ሶፈር | የወር ስም፣ በጨረቃ አቆጣጠር መሰረት |
| ሸፍዓ | መማለድ/ አማላጅ |
| ቁጥብ | ዋና ተመላኪ እንደሆነ የሚታመንበት፣ አምላክ |
| ቂብላ | የስግደት አቅጣጫ |

[1] ሙዳየ ቃላት ለአንባቢ ግልጽ ሆኖ እንዲቀርብ ሲባል በሰንጠረዥ ተደራጅቶ ቀርቧል፡፡

| | |
|---|---|
| በረካ | የተባረከ |
| ባጤል | የተበላሸ፣ ያልተገባ፣ ሀይማኖታዊ ትዕዛዝን የሚቃረን ስራ ሁሉ |
| ባዲሼህ | አካባቢውን ይጠብቃል፣ ከፈጣሪ ያማልዳል ተብሎ የሚታመንበት ወልይ |
| ተአብ | ችግር፣ ጣጣ |
| ታዕዚያ | የሀዘን ቤት |
| ንይት/መነየት | ግዴታን ለመወጣት በሀሳብ ቀድሞ ማሰብ፣ ማቀድ |
| አሊም | አዋቂ ሰው |
| አሊጣጦ | በስሱ የሚጋገር ቂጣ |
| አማን | ሰላም |
| አርሂብ | መቀበል |
| አሱር | ከአስር ሰዓት ጀምሮ እስከ ጀምበር መጥለቂያ ያለው ጊዜ |
| አብሱማ | የልጅ ልጅ፣ በአፋር ከሴት የቤተሰብ አባል የሚወለድ ልጅ ሁሉ ነው፡፡ |
| አጐበር | ከመቃ የሚሰራ ልብስን ጭስ ለማሞቅ የሚያገለግል |
| አዛን | ፀሎትን በዜማ ማሰማት |
| አፋት | ድንገት የሚመጣ መጥፎ ነገር፣ መዓት፣ አጥፊ ነገር |
| ኸሊፋ | ተተኪ ሆኖ ዚያራ የሚመራ ልጅ ወይም ዝርያ |
| ኸቲማ/አቂማ | መጨረሻ |
| ኸይር | መልካም፣ በጐ |
| ወስያ | ኑዛዜ |
| ወቃሊሞ | ደቅቆ የተከተፈ፣ በቅመም ተለውሶ በአንጀት ውስጥ የሚቀመጥ ስጋ፣ ባህላዊ የአርጐባዎች ምግብ |
| ወይባ | ጭሱ የሚሞቅ እንጨት |
| ዉዱእ | አላህን ለማምለክ ታስቦ አራት አካሎችን (ፊት፣ ራስ፣ እጆችና እግሮችን) በውሃ ማጽዳት |
| ደረሳ | የሀይማኖት ትምህርት ተማሪ |

| | |
|---|---|
| ደገሳ | መዘጋጀት |
| ዱንያ | ጠፊው ዓለም፣ ገህዱ ዓለም፣ |
| ዱዓ | ምርቃት፣ ፀሎት |
| ጀሀነም | ገሀነብ |
| ጀነት | ገነት |
| ጂኒ | እርኩስ መንፈስ |
| ጂናዛ | አስከሬን |
| ጡሀራ | ንፁህ |
| ጭልጭሌ | የጆሮ ጌጥ |
| ፈረጀ | መገላገል፣ እፎይ ማለት |
| ፈጫ | የውሃ መውረጃ ቦታ፣ ደረቅ ወንዝ |

## አጠቃሎ

*የፎክሎር አንድ ክፍል የሆነው ሀገረሰባዊ ልማድ ከሚይዛቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ስነ ስርዓት (Ritual) ነው፡፡ ከስነ ስርዓት ዓይነቶች መካከል ደግሞ የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች ይገኛሉ፡፡ ይህ ጥናት በህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች ላይ ትኩረት ያደረገ ሲሆን "የአርጎባ ብሄረሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓቶች ክዋኔ ትንተና፤ በአፋር ክልል፣ ዞን ሶስት፣ አርጎባ ልዩ ወረዳ" በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ በአፋር ክልል ከሚኖረው የአርጎባ ብሄረሰብ የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች መካከል የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓቶችን ክዋኔ መተንተን ነው፡፡ በአፋር ክልል የሚኖረውን የአርጎባ ብሄረሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓቶች ለመተንተን የክዋኔ፣ መዋቅራዊ፣ ትዕምርታዊና ተግባራዊ ንድፈ ሀሳቦች ጥቅም ላይ የዋሉ ሲሆን የጥናቱን ዓላማ ለማሳካትና የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ ካልዓይና ቀዳማይ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ካልዓይ መረጃ ከጽሁፍ ሰነዶች፣ ቀዳማይ መረጃ ደግሞ የመስክ ስራ በማከናወን የተሰበሰበ ሲሆን በመስክ መረጃን ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ የዋሉ ምልከታ፣ ቃለመጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይት ዘዴዎች ናቸው፡፡ የጥናት ቦታና የመረጃ ሰጪ መረጣ የተከናወነው በአላማ ተኮርና በጠቋሚ የንሞና ዘዴ ነው፡፡ መረጃ የተሰበሰበባቸው አውዶች ተፈጥሯዊና አርቴፊሻል አውዶች ሲሆኑ መረጃው ከዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ውስጥ ኢትኖግራፊ የጥናት ሞዴልን በመጠቀም ተተንትኗል፡፡ የሜታ ፎክሎር ምርመራም በመረጃ መተንተኛነት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የጥናቱ ግኝት እንደሚያሳየው በአፋር ክልል የሚኖረው የአርጎባ ብሄረሰብ የጋብቻ ስነ ስርዓት ክዋኔ መዋቅር በቅድመ መለየት፣ መለየት፣ ሽግግርና መቀላቀል ደረጃዎች ሊከፈል የሚችል ሲሆን የወሊድና የሀዘን ስነ ስርዓቶች ክዋኔዎች ደግሞ በመለየት፣ ሽግግርና መቀላቀል ደረጃዎች ሊከፈሉ የሚችሉ ናቸው፡፡ በብሄረሰቡ የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ ስነቃል (ዱዓዎች፣ ዝኪሮች)፣ ቁሳዊ ባህል (ሽታ፣ አዝጋሮ፣ ወይባ፣ አልባሳት) እና ሀገረሰባዊ ልማድ (እምነቶች፣ ባህላዊ ሕክምና፣ ጭስ መሞቅ) ፎክሎሮች ተለይተዋል፡፡ በጋብቻ ስነ ስርዓት ክዋኔ ስነቃል (ቃል ማሰሪያዎች፣ መወከያዎች፣ ዱዓዎች)፣ ቁሳዊ ባህል (ወይደል፣ ምግብና መጠጥ፣ አልባሳት፣ ጌጣጌጥ፣ ጉፍታ)፣ ሀገረሰባዊ ልማድ (እምነቶች፣ ጭስ መሞቅ) እና ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት (ሺሎ፣ ዘፈኖች) ፎክሎሮች ተለይተዋል፡፡ በሀዘን ስነ ስርዓት ክዋኔም ስነቃል (ዱዓ፣ ማጽናኛዎች፣ መሰናበቻዎች)፣ ቁሳዊ ባህል (ምግብና መጠጥ፣ የከፈን ጨርቅ፣ ማግ፣ መዋስ) እና ሀገረሰባዊ ልማድ (ባህላዊ ህክምና፣ እምነት) ፎክሎሮች ተለይተዋል፡፡ በብሄረሰቡ በወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ ውስጥ ያሉ ቃላዊ (የዱዓ ቃላት)፣ ቁሳዊና (ማር) ድርጊታዊ (ጣትን በገበታ ዙሪያ ማድረግ፣ ገበታን ከፍ ማድረግ፣ ድፍን ቅል አልጋ ላይ ማድረግ)፣ በጋብቻ ስነ ስርዓት ክዋኔ ውስጥ ያሉ ቃላዊ (የዱዓ ቃላት)፣ ቁሳዊ (የወይደል ቀለም፣ ጉፍታ) እና ድርጊታዊ (ለሙሽራ ጉፍታ የምትጭን ሴት አግብታ ያልፈታች መሆኗ) እና በሀዘን ስነ ስርዓት ክዋኔ ውስጥ ያሉ ድርጊታዊና (ጥልፍ መተርተር፣ ውሀ ማርከፍከፍና እርጥብ ቅጠል መጎዝጎዝ፣ መዋስን በጠዋት ውሀ አርከፍክፎ ማጠፍ፣ እጅንና ፊትን በቀዝቃዛ ውሃ መታጠብ) ቁሳዊ (ውሀ፣ መዋስ) ትዕምርቶች ተለይተዋል፡፡ የብሄረሰቡ የወሊድ ስነ ስርዓት ማህበራዊና (ወላድ መንከባከብ፣ አራስ መጠየቅ) ስነ ልቡናዊ (ባህላዊ ህክምናና የአምሮት ስነ ስርዓት) ፋይዳዎች አሉት፡፡ የብሄረሰቡ የጋብቻ ስነ ስርዓት የአሻጋሪነት (ትዳር የሌለውን ሰው ወደ ባለትዳርነት)፣ ማህበራዊ (ሰዎችን በአንድ ያገናኛል)፣ ኢኮኖሚያዊ (ስጦታዎች)፣ ስነ ልቡናዊና (ዱዓና ባዱሼህ) የተግባቦትና የማዝናናት (ዘፈኖች) ፋይዳዎች አሉት፡፡ የብሄረሰቡ የሀዘን ስነ ስርዓት ተግባቦታዊና ማህበራዊ (ለቅሶ መድረስ)፣ ኢኰኖሚያዊና (ሀፊሻ) ስነ ልቡናዊ (በጋራ ማልቀስና ሶደቃ) ፋይዳዎች አሉት፡፡ ለውጥን ተቋቁመው የቀጠሉ ክዋኔዎች ቢኖሩም በብሄረሰቡ የወሊድና የሀዘን ስነ ስርዓቶች ላይ የክዋኔ ለውጦች፤ በብሄረሰቡ የጋብቻ ስነ ስርዓት ላይ ደግሞ የክዋኔና የመዋቅር ለውጦች ታይተዋል፡፡ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ተለይተው የሜታ ፎክሎር ምርመራም ተደርጎባቸዋል፡፡ በጋቸኔ ጤና ጣቢያ የተሰራው ባህላዊ ጎጆ ለታሰበለት ዓላማ ቢውል፣ የነፍሰጡር የምግብ ክልክሎችና ከነፍሰጡሯ ጤና አንፃር ጉዳት ያለው መሆኑና አለመሆኑ ቢጠና፣ በወሊድ ጊዜ የሚከወኑ አንዳንድ ክዋኔዎች ለምሳሌ፣ መነቅነቅ የሚያስከትሏቸው የጤና ጉዳቶች ካሉ በጥናት ቢለዩ፣ ሀፊሻን ከዘመናዊ የመረዳጃ ተቋማት ጋር ማስተሳሰር ቢቻል፣ ዚያራ በዝርዝር ቢጠና ጥሩ ነው፡፡*

## ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

ይህ ክፍል ለጥናቱ መንደርደሪያ የሚሆኑ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓቢይና ዝርዝር ዓላማዎች፣ ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ወሰንና የጥናቱ ጠቀሜታ የቀረቡበት ነው፡፡

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

የፎክሎር ክፍል የሆነው ሀገረሰባዊ ልማድ ከሚይዛቸው የፎክሎር ጉዳዮች መካከል አንዱ ስነ ስርዓት (Ritual) ነው፡፡ ተመራማሪዎችና ምሁራን ስነ ስርዓት የሚለውን ቃል በተለያየ መልኩ ያቀረቡ ቢሆንም "A *ritual* is a patterned, repetitive, and symbolic enactment of a cultural belief or value; its primary purpose is transformation." (Davis-Floyd qtd.[1] in Grimes 24) የሚለው ብያኔ ግን ብዙዎቹ ያነሷቸውን ነጥቦች የያዘ ነው፡፡ ብያኔው ስነ ስርዓት ከዋና ዋና መገለጫ ባህርያቱ አንፃር የተገለፀበትና ዋና ዓላማው ሰዎችን ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ ማሻገር መሆኑም የተገለፀበት ነው፡፡ የስነ ስርዓት ዓይነቶች በርካታ ቢሆኑም ይህ ጥናት የስነ ስርዓት አንድ ፈርጅ በሆኑ የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡

የዚህ ጥናት ዋና ማተኮሪያ የሆኑት የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች የወሊድ፣ የጋብቻና የሞት/ሀዘን ስነ ስርዓቶች ናቸው፡፡ ወሊድ የሰው ልጆች ዘር ማስቀጠያ የሆነ መሰረታዊ የህይወት ሽግግር ሲሆን በተለያዩ ባህሎች ውስጥ ወሊድን በተመለከተ የሚከናወኑ ስነ ስርዓቶች አሉ፡፡ ስነ ስርዓቶቹ በነፍሰጡርነት ጊዜ የሚጀምሩና ከወሊድ በኋላም የሚቀጥሉ ናቸው (Bell, *Ritual* 95)፡፡ ጋብቻ የዘርን ቀጣይነት የሚያስገኝ፣ የተጋቢዎች ብቻ ሳይሆን የቤተሰቦቻቸውም ግንኙነት ነው (Cooke and Macy 28)፡፡ ሞትን በተመለከተም ከሞት በፊት ለሞት ያደርሰዋል ተብሎ በሚታሰብ ህመም ላይ ላለ ሰውና ከሞት በኋላም የሚከወኑ በርካታ ስነ ስርዓቶች አሉ (Cooke and Macy 156)፡፡ እነዚህን የህይወት ሽግግሮች በተመለከተ ያለ እምነት ሽግግሮቹን ተከትለው የሚከወኑ ስነ ስርዓቶች እንዲኖሩ

[1] በሁለተኛነት ስሙ የተጠቀሰው ፀሐፊ መረጃውን ስሙ መጀመሪያ ከተጠቀሰው ፀሐፊ የወሰደው መሆኑን ለማመላከት ጥቅም ለይ የዋለ አጽርኦተ ቃል ነው፡፡

አድርጓል፡፡ ይህ ጥናትም እነዚህ ሶስት የህይወት ሽግግሮችን ተከትለው በሚከወኑ ስነ ስርዓቶች ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡

ይህ ጥናት የተከናወነው በአርጐባ ብሄረሰብ ላይ ነው፡፡ የአርጐባ ብሄረሰብ በኢትዮጵያ አራት ክልሎች ማለትም በሐረሪ፣ በኦሮሚያ፣ በአማራና በአፋር ክልሎች ውስጥ የሚኖር ሲሆን ይህ ጥናት በአፋር ክልል በሚኖረው የአርጐባ ብሄረሰብ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ በአፋር ክልል የሚኖረው የአርጐባ ብሄረሰብ በክልሉ ዞን ሶስት፣ የአርጐባ ልዩ ወረዳ ውስጥ ይኖራል፡፡ የአርጐባ ልዩ ወረዳ የአፋር ክልል 29ኛ ወረዳ ሲሆን የተቋቋመው በ1988 ዓ.ም. ነው፡፡ በወቅቱ በወረዳውና በአካባቢው የሚኖሩ አርጐቦች የአርጐባ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ የሚል የፖለቲካ ፓርቲ በማቋቋም ጥያቄ አንስተዋል፡፡ የእንቅስቃሴው ዓላማ በራሳቸው በአርጐቦች የሚመራ ልዩ ወረዳ ማቋቋም ነበር፡፡ ጥያቄው በአፋር ክልልና በተወካዮች ምክር ቤት ተቀባይነት አግኝቶ የአርጐባ ልዩ ወረዳ በ1988 ዓ.ም. ተቋቁሟል (የአርጐባ ልዩ ወረዳ የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት 1-2)፡፡

ይህ "የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓቶች ክዋኔ ትንተና፤ በአፋር ክልል፣ ዞን ሶስት፣ አርጐባ ልዩ ወረዳ" በሚል ርዕስ የተከናወነ ጥናት በአፋር ክልል የሚኖረው የአርጐባ ብሄረሰብ ከወሊድ፣ ከጋብቻና ከሞት ጋር ተያይዞ የሚከውናቸው ስነ ስርዓቶች ጥናት ነው፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የጥናቱ ትኩረት የሆነውን ብሄረሰብ እና ርዕሰ ጉዳይ ለመምረጥ ምክንያት የሆነኝ የመጀመሪያው ጉዳይ ከብሄረሰቡ አባላት ጋር ከነበረኝ ትውውቅ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ከዚህ በፊት ወደ አካባቢው ለጥናት በሄድኩበት ጊዜ ከብሄረሰቡ አባላት ጋር ጥሩ ትውውቅና ወዳጅነትን ለመመስረት ችያለሁ፡፡ በዚህ ምክንያትም በወቅቱ ከነበረኝ የአጥኚነት ሚና ባሻገር የብሄረሰቡ አባላት በሚከውኗቸው የተወሰኑ የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች መገለጫ በሆኑ ክዋኔዎች ላይ እገኝ የነበረ መሆኑና ይህም ክዋኔዎቹን ለማጥናት ያነሳሳኝ በመሆኑ የብሄረሰቡን የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች ለዚህ መሰሉ ጥናት መርጫቸዋለሁ፡፡

ሁለተኛው ጉዳይ በተለያዩ አጋጣሚዎች የብሄረሰቡ ባህል በሌላ ባህል የተዋጠና ብሄረሰቡ በመጥፋት ላይ ያለ ተደርጐ ሲቀርብ (ለምሳሌ፣ Aklilu 173) ከመመልከቴ ጋር ይያያዛል፡፡ ብሄረሰቡ በመጥፋት ላይ ያለ ተደርጐ መታሰቡ ደግሞ በትክክል የብሄረሰቡ ቋንቋ

በመጥፋት አደጋ ላይ ከመሆኑ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ነገር ግን የቋንቋ መጥፋት ወይም ውሰት በትክክል የሌላው የባህል መገለጫ (ማሂጃው ቋንቋ በመሆኑ ስነ ቃልን ሳይጨምር) መጥፋት ወይም ውሰት ማለት አይደለም፡፡ በአካባቢው በነበረኝ ቆይታ ይህን ለመመልከት ችያለሁ፡፡ በብሄረሰቡ ባህል የለውጥና ቀጣይነት ጉዳይ እንዳለ ሆኖ የብሄረሰቡ ቋንቋ የደረሰበትን አይነት የመጥፋት አደጋ በሌሎቹ የብሄረሰቡ የባህል እሴቶች፣ ሀይማኖትና ሀገረሰባዊ ልማዶች ላይ አልደረሰም፡፡ ሀገረሰባዊ ልማዶች በየመከወኛ አጋጣሚዎቻቸው ይከወናሉ፡፡ እነዚህ መገለጫዎች ናቸው የአርጐባነት መመዘኛ ሆነው የተመለከትኩት፡፡ አርጐቦች የሌላውን ብሄር/ብሄረሰብ ቋንቋ በመናገራቸው ሌላውን ብሄር/ብሄረሰብ አልሆኑም፡፡ በመሆኑም ያነበብኩትና የሰማሁት በቦታው ሆኖ ከተመለከትኩት ጋር የተለያየ በመሆኑ ይህን ለማሳየት ብሄረሰቡን ለጥናት መርጩዋለሁ፡፡

ሶስተኛው ምክንያት የአርጐባ ብሄረሰብን የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች በተመለከተ የተከናወነ ጥናት ያጋጠመኝ ካለመሆኑ ጋር የተያያዘ ሲሆን የስነ ስርዓቶቹ አለመጠናት ስነ ስርዓቶቹን ለጥናት እንድመርጣቸው አነሳስቶኛል፡፡

### 1.3. የጥናቱ ዓላማ

ጥናቱ የሚከተሉት ዓቢይና ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

#### 1.3.1. ዓቢይ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማ በአፋር ክልል ከሚኖረው የአርጐባ ብሄረሰብ የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች መካከል የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓቶችን ክዋኔ መተንተን ነው፡፡

#### 1.3.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- በአፋር ክልል የሚኖረውን የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓት ክዋኔዎችን መግለጽ፣
- የስነ ስርዓቶቹን መዋቅር መለየት፣
- በክዋኔዎቹ ውስጥ ያሉ ሌሎች የፎክሎር አህዶችን መለየት፣
- በስነ ስርዓቶቹ ውስጥ ያሉ ትዕምርታዊ ጉዳዮችን መፈከር፣
- ስነ ስርዓቶቹ ለብሄረሰቡ አባላት ያላቸውን ፋይዳ መግለጽ፣

- ክዋኔዎቹ ቀደም ባለው ጊዜ የሚከወኑበትን መልክና አሁን የሚከወኑበትን ሁኔታ በማነፃፀር ለውጥ ተከስቶ ከሆነ ይህንኑ ለውጥና የለውጡን መንስኤ ማብራራት፣
- የህይወት ሽግግሮቹንና ሽግግሮቹን ተከትለው የሚከወኑ ስነ ስርዓቶችን መነሻ የሚያደርጉ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን መለየት፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮቹ የያዟቸውን መልዕክቶች መተንተን፡፡

## 1.4. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች

ጥናቱ የሚመልሳቸው የምርምር ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- በአፋር ክልል የሚኖረው የአርጐባ ብሄረሰብ በወሊድ፣ በጋብቻና በሀዘን ጊዜ የሚከውናቸው ስነ ስርዓቶች ምን ምን ናቸው? እንዴትስ ይከወናሉ?
- በአፋር ክልል የሚኖረው የአርጐባ ብሄረሰብ የሚከውናቸው የሕይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች መዋቅር ምን መልክ አለው?
- በክዋኔዎቹ ውስጥ ያሉ ሌሎች የፎክሎር አሀዶች ምን ምን ናቸው?
- በስነ ስርዓቶቹ ውስጥ ያሉ ትዕምርቶች ምን ምን ናቸው? ፍካሬያዊ ትርጉማቸውስ ምንድን ነው?
- ስነ ስርዓቶቹ ለከዋኞቻቸው የሚሰጡት ግለሰባዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ምንድን ነው?
- የስነ ስርዓቶቹ ክዋኔ ቀደም ካለው ጊዜ ክዋኔ ጋር ያለው ልዩነትና ተመሳስሎ ምንድን ነው?
- መነሻቸው ወሊድ፣ ጋብቻና ሞት እንዲሁም የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶቹ የሆኑ ምሳሌያዊ አነጋገሮች የትኞቹ ናቸው? የሚያስተላልፏቸው መልዕክቶች ምንድን ናቸው?

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በአፋር ክልል ከሚኖረው የአርጐባ ብሄረሰብ የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች መካከል በወሊድ፣ በጋብቻና በሀዘን ስነ ስርዓቶች ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ ከሰው ልጅ የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶት መካከል እነዚህ ስነ ስርዓቶች ዋና ዋና ሽግግሮችን ተከትለው የሚከወኑ በመሆናቸው ስነ ስርዓቶቹ ለጥናት የተመረጡትም በዚያው አግባብ

ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ በአፋር ክልል የሚኖረው የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓቶች ክዋኔ፣ መዋቅር፣ ትዕምርት፣ ፋይዳ፣ ለውጥና ቀጣይነት እና የህይወት ሽግግሮቹንና እነዚህን ስነ ስርዓቶች የሚያነሱ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ይዘት የተተነተኑበት ነው፡፡

ጥናቱ በቦታ የተወሰነ ነው፡፡ የአርጐባ ብሄረሰብ በሀገሪቱ የተለያዩ ክልሎች ማለትም በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በሀረሪና በአፋር ክልሎች ውስጥ የሚኖር ሲሆን የዚህ ጥናት ትኩረት ግን በአፋር ክልል የሚኖረው የአርጐባ ብሄረሰብ ነው፡፡ በጥናቱ ውስጥ የአርጐባ ብሄረሰብ ተብሎ የተገለፀው በአፋር ክልል የሚኖረውን የአርጐባ ብሄረሰብ ነው፡፡ ይህን መሰል ጥናት ለማድረግ ጥናት የተደረገበትን ማህበረሰብ በተመለከተ ቀደም ያለ እውቀት መኖሩ የሚያስገኘው ጠቀሜታ አለ፡፡ የጥናት ማህበረሰቡን ለጥናት ዓላማ እንደ አዲስ ከማወቅም ይሁን ከመተዋወቅ ይልቅ ቀድሞ የነበረ ቅርበትና ትውውቅ መረጃን ከመሰብሰብ ሂደት አንፃር (ለምሳሌ በመረጃ ሰጪዎች መረጣ ላይ) የሚያስገኘው ጠቀሜታ አለ፡፡ ከዚህ አንፃር በዚህ ጥናት የአፋሩ አርጐባ ለጥናት ተመርጧል፡፡ በትውውቅ ምክንያት የሚኖርን አድሏዊነት ለመቆጣጠር የተደራጀ የጥናት ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል፣ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች መሪ እንዳይሆኑ ጥንቃቄ ተደርጓል፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በጥምረት በመጠቀም መረጃን የማጥራት ስራ ተከናውኗል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት፣

1. በአፋር ክልል የሚኖረው የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶችን ክዋኔ በተመለከተ የሚሰጠው እውቀት ያለው በመሆኑ ለፎክሎር መስክ ጥናት መዳበር የሚሰጠው አስተዋጽኦ በቅድሚያ የሚጠቀስ ጠቀሜታው ነው፡፡
2. የብሄረሰቡን ባህል ለመሰነድ ያስችላል፡፡
3. ዘመናዊ የህክምና ተቋማት በተለይ ወሊድን በተመለከተ ዓላማቸውን ለማሳካት የሚያግዛቸውን እውቀት ሊሰጥ ይችላል፡፡
4. በተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ ወይም በብሄረሰቡ ባህል ላይ ለሚሰሩ ጥናቶች መነሻ ሀሳብ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 1.7. የጥናቱ አደረጃጀት

ጥናቱ በስምንት ምዕራፎች የተዋቀረ ነው፡፡ አስቀድሞ የጥናቱን ምንነት ማስተዋወቅ አስፈላጊ በመሆኑ የመጀመሪያው የጥናቱ ምዕራፍ የጥናቱ መግቢያና ጥናቱን ከርዕሰ ጉዳይና ከቦታ፣ ጥናቱን ለማከናወን ምክንያት ከሆነ ጉዳይ፣ ከዓላማ፣ ጥናቱ ከሚመልሳቸው ጥያቄዎች፣ ከጥናቱ ወሰንና ጠቀሜታ አንፃር የሚያስተዋውቅ ነው፡፡ ምዕራፍ ሁለት የተከናወነ የክለሳ ድርሳናት ስራ የቀረበበት ሲሆን የጥናቱ ርዕሰ ጉዳይና ጥናቱ የተተነተነበት ንድፈ ሀሳብ ምንነት የቀረቡበት፣ ከጥናቱ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ቀደምት ጥናቶች የተቃኙበትና ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ልዩነት የቀረበበት ነው፡፡ ምዕራፍ ሶስት የጥናቱ ስነ ዘዴ የቀረበበት ሲሆን ከጥናት ዘዴ አንፃር ጥናቱ የተከናወነበትን አግባብ የሚያስተዋውቅ ነው፡፡ ምዕራፍ አራት የአርጐባ ብሄረሰብ መግለጫ የቀረበበት ሲሆን ብሄረሰቡን ከሚኖርበት መልክዓ ምድር፣ ከስያሜ፣ ከታሪክና አመጣጥ፣ ከማህበራዊ መዋቅር፣ ከቋንቋ፣ ከሀይማኖት/እምነት፣ ከኢኮኖሚ፣ ከአመጋገብና ከባህላዊ ስነ ህንፃ አንፃር የተዋወቀበት ነው፡፡ ከምዕራፍ አምስት ጀምሮ እስከ ምዕራፍ ስምንት ያሉት የጥናቱ የትንተና ክፍሎች ሲሆኑ ምዕራፍ አምስት፣ ምዕራፍ ስድስትና ምዕራፍ ሰባት በቅደም ተከተል በአፋር ክልል የሚኖረው የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓቶች ክዋኔ፣ የየክዋኔዎቹ መዋቅር፣ ትዕምርት፣ ፋይዳ እና ለውጥና ቀጣይነት የቀረበባቸው ናቸው፡፡ ምዕራፍ ስምንት የጥናቱ ማጠቃለያ፣ ግኝት እና ይሁንታ የቀረቡበት ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

ይህ ክፍል የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ ምንነት ለመግለጽ የሚያስችል የጽንሰ ሀሳብ ማብራሪያ፣ መረጃ የሚተነተንበት ንድፈ ሀሳባዊ ማሕቀፍ እና የቀደምት ተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት የቀረበበት ነው፡፡

### 2.1. የጽንሰ ሀሳብ ማብራሪያ

ይህ ክፍል የጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ምንነት የቀረበበት ነው፡፡ በመሆኑም የስነ ስርዓት ምንነት፣ የስነ ስርዓት ምድቦች፣ የስነ ስርዓት ባህርያት፣ የስነ ስርዓት ተግባራት፣ የስነ ስርዓት ለውጥና ቀጣይነት፣ የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓት ምንነትና በተለይ የጥናቱ ትኩረቶች የሆኑት ወሊድን፣ ጋብቻና ሞትን ተከትለው የሚከወኑ የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች ምንነት ቀርቧል፡፡

#### 2.1.1. የስነ ስርዓት ምንነት

ፎክሎር በአራት ዋና ዋና ክፍሎች የሚከፈል ሲሆን እነርሱም ስነቃል፣ ቁሳዊ ባህል፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት እና ሀገረሰባዊ ልማድ ናቸው፡፡ ይህ ጥናት በሀገረሰባዊ ልማድ ስር ከሚጠኑ የፎክሎር ጉዳዮች መካከል አንዱ በሆነው በስነ ስርዓት ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡

*Ritual* (ስነ ስርዓት[2]) የሚለው ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የጥናት መደበኛ ቃል ተደርጎ ጥቅም ላይ የዋለው በ19ኛው ክ/ዘመን ሲሆን ከዚያ በኋላ በነበሩ ምሁራዊ ጥረቶች ቃሉ በርካታ ብያኔዎች ተሰጥተውታል (Bell, *Ritual theory* 14)፡፡

---

[2] አማርኛ ቋንቋን በመጠቀም በርዕሰ ጉዳዩ ጥናት ያደረጉ ሰዎች *Ritual* ለሚለው የእንግሊዝኛ ቃል የአማርኛ አቻ እንዲሆን ስራዬ እንዳለው፣ ድርብወርቅ ብፁ፣ አበባ አማረ፣ ደስታ አማረና ፍሬህይወት ባዩ እና ደስታ አማረ ስርዓት የሚለውን ቃል የተጠቀሙ ሲሆን አፀደ ተፈራ ስነ ስርዓት የሚለውን ቃል ተጠቅመዋል፡፡ Leslau ባዘጋጁት መዝገበ ቃላት *Ritual* የሚለው ቃል "ስነ ስርዓት" የሚል የአማርኛ አቻ ቃል ተሰጥቶታል (*English-Amharic Context Dictionary* 1087)፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ ባዘጋጀው *ኣማርኛ መዝገበ ቃላት* ስርዓት የሚለው ቃል "1. አንድ ነገር የሚሰራበት ወይም የሚከናወንበት ደንብ፣ ህግ 2. ወግ፣ ባህል፡፡" የሚል ትርጉም የተሰጠውና (137) ስነ ስርዓት የሚለው ቃል ደግሞ "አንድን ድርጊት በተመለከተ የተለመደ ስርኣትን ወይም ደንብን ተከትሎ የሚሄድ ክንውን" የሚል ብያኔ ተሰጥቶታል (አጽንኦቱ የእኔ ነው) (138)፡፡ በዚህ መሰረት ስርዓት አጠቃላይ ደንብ፣ ስነ ስርዓት ደግሞ ደንብን ተከትሎ የሚከወን ክዋኔ መሆኑ

*Ritual* (ስነ ስርዓት) ለሚለው ቃል የተሰጡ አብዛኛዎቹ ብያኔዎች ስነ ስርዓቶች በአብዛኛው ትዕምርቶችን፣ እንቅስቃሴዎችና ድግግሞሾችን የሚይዙ፣ ጅማሯቸውንና ፍፃሜያቸውን የሚያሳዩ ቅንብሮችና የተለየ የመከወኛ ቦታና ጊዜ ያሏቸው፣ ወጥ በሆኑ ድርጊቶች የተገነቡ፣ ቀዳሚ ዓላማቸው ማሻገር የሆነ፣ ድራማዊ መዋቅር ያላቸው፣ ከቴክኖሎጂ የተለዩ፣ ማህበረ ሀይማኖታዊ ባህርይ ያላቸው፣ በማህበራዊ ህግ የሚመሩና የጋራ የሆኑ ክዋኔዎች ናቸው የሚሉ ዋና ዋና ሀሳቦችን የያዙ ናቸው (Davis-Floyd qtd. in Grimes 24; Turner, *From Ritual to Theatre* 79, 81; Pentikäinen 1104-1105)፡፡

Gluckman (7) ስነ ስርዓቶች የሰዎችን ሚና ለዋጮች መሆናቸውን አጽንኦት በመስጠት ስነ ስርዓት የሚለውን ቃል "Rituals are acts aiming to change the relationship between the ME 1 and ME 2" በማለት በይነዋል፡፡

ስነ ስርዓትና ሀይማኖት ያላቸውን ግንኙነት በተመለከተ ተመራማሪዎች የተለያዩ ሀሳቦችን አቅርበዋል፡፡[3] ከፊሉ ስነ ስርዓትን በብዙ መጠን ወደ ሀይማኖት ጉዳይ አስጠግተዋል፣ ከፊሉ ስነ ስርዓት በእኩል መጠን መንፈሳዊም ዓለማዊም ሊሆን ይችላል ያሉ ሲሆን ከፊሉ ስነ ስርዓትን ከነገረ ሀይማኖት ውጭ በማድረግ ነፃ አድርገውታል፡፡ ከመጀመሪያዎቹ መካከል Shujaa (575), Eriksen (215) እና Lan (12) ተጠቃሾች ናቸው፡፡ Bell (*RITUAL* 91, 164) እና Pickering (78) ሀይማኖት፣ ዓለማዊው አቅጣጫና ስነ ስርዓት የተመጣጠነ ግንኙነት አላቸው የሚል ሀሳብ ያላቸውን ብያኔዎች ያቀረቡ ሲሆን Gruenwald (ix, 2-3) ስነ ስርዓት ከሀይማኖት ጉዳይ ነፃ ነው ብለዋል፡፡

ስነ ስርዓትና ዘመናዊነት ያላቸውን ግንኙነት በተመለከተም ተመራማሪዎች ሀሳቦቻቸውን አቅርበዋል፡፡ ከፊሉ (ለምሳሌ፣ McWhorter 76, 93) ስነ ስርዓትንና ዘመናዊነትን በሁለት የተለያዩ ጐራዎች በመክፈል ዘመናዊነት እየተስፋፋና የአመለካከት ለውጥ እያስከተለ በሄደ መጠን ስነ ስርዓት ዋጋ እያጣና ክዋኔው እየቀነሰ ይሄዳል የሚል አቋም ያላቸው ሲሆን ከፊሉ ደግሞ (ለምሳሌ፣ Koster 222; Grimes 177; Navon 521) ስነ ስርዓት የኋላ ቀርነት መገለጫ ሳይሆን የዘመናዊውም ሰው የአኗኗር መንገድ ነው የሚል አቋም አላቸው፡፡

---

ተቀምጧል፡፡ በመሆኑ Ritual ለሚለው ቃል ገላጭ የአማርኛ አቻ ይሆናል ተብሎ የታመነበት ስነ ስርዓት የሚለው ቃል በመሆኑ በዚህ ጥናት ለእንግሊዝኛው Ritual ስነ ስርዓት የሚል የአማርኛ አቻ ተሰጥቶታል፡፡

[3] በዚህ ጥናት ወደ ፊት እንደተመለከተው የአርጐባዎች አንዳንድ የስነ ስርዓት ክዋኔዎች ሀይማኖታዊ መነሻዎች አሏቸው፡፡

### 2.1.2. የስነ ስርዓት ምድቦች

ተመራማሪዎች ስነ ስርዓትን በተለያየ መንገድ ከፍለዋል፡፡ Turner ("Symbols in African Ritual" 1100) ስነ ስርዓቶችን ወቅታዊና ድንገተኛ በማለት በሁለት መሰረታዊ ክፍሎች ከከፈሉ በኋላ ድንገተኛ ስነ ስርዓቶችን የህይወት ቀውስ ስነ ስርዓቶችና የመከራ ጊዜ ስነ ስርዓቶች በማለት እንደገና በሁለት ክፍሎች ከፍለዋል፡፡ Shujaa (576) ወቅታዊ ስነ ስርዓት፣ የህይወት ኡደት ስነ ስርዓትና ከንጉሳውያንነት ጋር የተያያዙ ስነ ስርዓቶች በማለት በሶስት ክፍሎች እና Sims and Stephens (114) የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች፣ የጉልምስና ስነ ስርዓቶች (Coming of age rituals)፣ ለአቅመ አዳም/ሄዋን መድረስን የሚያጅቡ ስነ ስርዓቶች (Initiation rituals) እና የስም ማውጣት ስነ ስርዓቶች በማለት በአራት ክፍሎች ከፍለዋል፡፡ ከዚህ ዓይነቱ ስነ ስርዓትን የመከፈያ መንገድ በተለየ ደግሞ Grimes ስነ ስርዓቶችን በ16 ክፍሎች ከፍለዋል (Bell, *Ritual Perspectives and Dimensions* 93-94)፡፡

ነገር ግን Bell (*RITUAL* 102-129) የተሻለ መንገድ ነው ያሉትን የመከፈያ መንገድ አቅርበዋል፡፡ Bell ስነ ስርዓቶችን በስድስት ዋና ዋና ክፍሎች የከፈሉ ሲሆን እነርሱም ወቅታዊና የመታሰቢያ ስነ ስርዓቶች (Calendrical Rites)፣ የልውውጥ (ስዕለት) እና የትስስር ስነ ስርዓቶች (Rites of Exchange and Communion)፣ የመከራ ጊዜ ስነ ስርዓቶች (Rites of Affliction)፣ የግብዣ፣ የፆምና የበዓላት ስነ ስርዓቶች (Feasting, Fasting and Festivals)፣ የፖለቲካ ስነ ስርዓቶች (Political Rites) እና የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች (Rites of Passage) ናቸው፡፡

ከፊሉ የስነ ስርዓት ዓይነቶችን በአንድ አጭቀው ልዩነታቸውን የሸፈኑ በመሆናቸውና ከፊሉ ደግሞ የበዛና በማይመች ዝርዝር የስነ ስርዓት ምድቦችን ያበዙ በመሆናቸው፤ ነገር ግን Bell የተጠቀሙበት ስነ ስርዓቶችን የመመደቢያ መንገድ አማካይና የተሻለ ነው የሚል ግንዛቤ በመውሰድ የBell አመዳደብ ጥቅም ላይ ውሏል።

### 2.1.3. የስነ ስርዓት ባህርያት

Bell (*RITUAL* 139-159) እንደገለፁት መደበኛነት፣ ልማዳዊነት፣ ወጥነት፣ በህግ መመራት፣ መንፈሳዊ ትዕምርታዊነት እና ተከዋኝነት የስነ ስርዓት ባህርያት ናቸው፡፡ ከዚህ በታች የእነዚህ ባህርያት ምንነት ቀርቧል፡፡

**መደበኛነት፣** Bell (*RITUAL* 139-144) እንደሚሉት መደበኛነት ውሱንና የማይለዋወጥ ገለፃን መጠቀም ሲሆን ትኩረቱ ቅርጽ ነው፡፡ የስነ ስርዓት መደበኛነት ባህርይ ለስነ ስርዓቱ ውበት ይሰጣል፤ ስነ ስርዓት ከሌሎች እንቅስቃሴዎች የተለየ መሆኑንም ይገልፃል፡፡

**ልማዳዊነት፣** ልማዳዊነት እንቅስቃሴዎች ቀደም ያለውን የባህል ገጽታ እንዲመስሉ ማድረግ ሲሆን ጥንታዊ የባህል መገለጫዎችን ጠብቆ ማቆየት መገለጫው ነው (Bell, *RITUAL* 145-150)፡፡

**ወጥነት፣** Bell (*RITUAL* 150) እንደሚሉት ስነ ስርዓት ወጥ በሆኑ ድርጊቶች የተገነባ ነው፡፡ ነገር ግን Rappaport (“Ritual” 250)፣ Grimes (190-191, 209)፣ Kowalzig (34, 40, 41)፣ Brown (6)፣ Langer et al. (1) እና Frobish (361-362) ስነ ስርዓት ለለውጥ የተጋለጠ እንጂ ወጥ አይደለም የሚል ጠንካራ ሀሳብ አቅርበዋል፡፡

**በህግ መመራት፣** ስነ ስርዓቶች ከዋኞች በክዋኔ ወቅት የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ቅቡል የሆነ ብቻ እንዲሆን በሚወስን ደንብ የሚገዙ ናቸው (Bell, *RITUAL* 155; Schechner 13)፡፡

**መንፈሳዊ ትዕምርታዊነት፣** ስነ ስርዓቶች ገሀዱን ዓለም የሚሻገሩ ሀሳቦችንም ይይዛሉ (Bell, *RITUAL* 155-159)፡፡

**ተከዋኝነት፣** ስነ ስርዓት ከሌላው የቀን ተቀን ድርጊት የተለየ መሆኑን የሚወስን የራሱ ቅንብብ ያለው ሲሆን የስነ ስርዓት የተከዋኝነት ገጽታ ለስነ ስርዓት ጉልበት የሚሰጥ ዋና ጉዳይ ነው (Rappaport, *Ritual and Religion* 37-38; Bauman, *Folklore, Cultural performances, and popular Entertainments* 46)፡፡

### 2.1.4. የስነ ስርዓት ተግባራት

ስነ ስርዓቶች ያላቸውን ፋይዳ ወይም ጠቀሜታ በተመለከተ ተመራማሪዎች በሁለት ጐራ ተከፍለዋል፡፡ ከፊሉ ስነ ስርዓቶች አንድ ግብ ላይ ለመድረስ ውጤታማ መሳሪያዎች ናቸው ሲሉ ከፊሉ ደግሞ ስነ ስርዓቶች ምንም አይነት ፋይዳ የላቸውም ባዮች ናቸው (Sax 8; McClymond 9)፡፡ ከዚህ በታች የቀረቡት ስነ ስርዓቶች ፋይዳ አላቸው የሚሉ ተመራማሪዎች ያቀረቧቸው የስነ ስርዓት ተግባራት ናቸው፡፡

- **መግባቢያነት፣** ስነ ስርዓቶች ሁኔታዎችን በማሳየትና ትዕምርታዊ ትርጉሞችን በመያዝ በተለያየ ደረጃ ተግባቦት እንዲኖር ያደርጋሉ (Harris 35-36; Alcorta and Sosis 330-332; Frobish 361, 362)፡፡
- **አሻጋሪነት፣** ስነ ስርዓቶች በህይወት ሽግግሮች የሚገኝን ለውጥ በማጀብ ለውጡን የማስረገጥ ሚና አላቸው (Dissanayake 13; Mwandayi 54)፡፡
- **ማህበራዊ ግንኙነትን ማጠናከር፣** ስነ ስርዓቶች ማህበራዊ ግንኙነትን የማጠናከርና ዝምድናን የመፍጠር ሚና አላቸው፡፡ ስነ ስርዓቶች ያላቸው ማህበራዊ ግንኙነትን የማጠናከር ተግባር ሁለት ገጽታ አለው፡፡ የመጀመሪያው ገጽታ በአንድ ባህል ውስጥ ያሉ ሰዎችን በየጊዜው እንዲገናኙ በማድረግ የማህበረሰብን አንድነት መጠበቅ ሲሆን ሁለተኛው ገጽታ በጋራ ለመኖር የማያስችሉ ችግሮችን መፍታት የሚያስችል እውቀትን ማስገኘት ነው (Al-Krenawi and Graham 163; Briggs 345-347)፡፡ Turner (*The Ritual Process* 179) ያመጡት የcommunitas እሳቤ ስነ ስርዓቶች ላላቸው ማህበራዊ ግንኙነትን የማጠናከር ፋይዳ በማሳያነት መቅረብ የሚችል ነው፡፡
- **መቆጣጠር፣** ስነ ስርዓቶች ማህበረሰብን የመቆጣጠሪያ መንገዶች ናቸው፡፡ Sutlive (362-363) እንደሚሉት ስነ ስርዓቶች ያላቸው የቁጥጥር ሚና ማህበረሰብን እንደ ማህበረሰብ እንዲፀና የሚያደርግ ነው፡፡
- **እምነትን ማጽናት፣** ስነ ስርዓቶች መንፈሳዊ ጉዳዮችንም የሚይዙ በመሆናቸው እምነቶችን ያፀናሉ (Sutlive 365; Kleinig 100-131; Farbod 59)፡፡
- **እሴቶችን መትከል፣** ስነ ስርዓቶች በማህበረሰብ ቅቡልነት ያላቸውን እሴቶችና ልማዶች በማጠናከርና ተቀባይነት የሌላቸውን በማራቅ የባህልን ቀጣይነት ያስገኛሉ (Al-Krenawi and Graham 163; Toit 45)፡፡
- **ማስተማር/ በስነ ምግባር መግራት፣** ስነ ስርዓቶች የከዋኞቻቸውን ቡድን የስነ ምግባር ደንቦች ይገልፃሉ፡፡ Rappaport (*Ritual and Religion* 24) እንደሚሉት ስነ ስርዓቶች የሰውን ልጅ ማህበራዊ ማንነት የሚቀርፁ ናቸው፡፡
- **ጉዳትን ማከም፣** ስነ ስርዓቶች በከዋኞቻቸው ተቀባይነት ያላቸው በመሆኑ ቀደም ሲል በተከሰተ ጉዳይ አእምሮ ላይ የደረሰን ጉዳት የመፈወስ አቅም አላቸው (Gordon-Lennox 16)፡፡

➢ **በሽግግር ጊዜ የሚከሰት መረበሽን መቀነስ፣** ስነ ስርዓቶች በሽግግር ምክንያት የሚደርስን ቀውስና መረበሽ የመቀነስ ጠቀሜታ አላቸው (Brana-Shute and Gary Brana-Shute 78)፡፡

### 2.1.5. የስነ ስርዓት ለውጥና ቀጣይነት

ለውጥና ቀጣይነት የስነ ስርዓቶች መገለጫ ሲሆን ለውጥ በነባሩ የባህል እሴት ላይ አዳዲስ መገለጫዎች መከሰት፤ ቀጣይነትም ለውጥን ተቋቁሞ መቆየት ማለት ነው፡፡ Rappaport ("Ritual" 24) ስነ ስርዓት የሚለውን ቃል "I take the term "ritual" to denote the performance of <u>more or less invariant</u> sequences of formal acts and utterances not entirely encoded by the performers" (አጽንኦቱ የእኔ ነው) ብለው በመበየን ስነ ስርዓት ለውጥ ሊከሰትበት የሚችል መሆኑን የገለፁ ሲሆን በተጨማሪም Kowalzig (34, 40, 41) Brown (6) Langer et al. (1) Reimers (163-164) እና Frobish (361-362) ተመሳሳይ ሀሳቦችን አንስተዋል፡፡

Rappaport (*Ritual and Religion* 36) የከዋኞች እውቀት ውሱን መሆን፣ የጊዜና የቦታ ለውጥ እና ሆን ተብሎ የሚደረግ ለውጥ የስነ ስርዓትን ክዋኔ ለለውጥ የሚዳርጉ ጉዳዮች ናቸው ያሉ ሲሆን Eller (272-288) ደግሞ ፈጠራ፣ የባህል መጥፋት፣ የውጭ ባህል መቀበልና ቀጥተኛ ለውጥ (በባህል ግንኙነት ሳይሆን ባህል ራሱ ሂደት በመሆኑ ምክንያት የሚከሰት ለውጥ) የባህል ለውጥ መንስኤዎች ናቸው ብለዋል፡፡

### 2.1.6. የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓት[4] ምንነት

የህይወት ሽግግር ጽንሰ ሀሳብ ለመጀመሪያ ጊዜ ትኩረት የተሰጠው በፈረንሳዊው የስነ ሰብዕ ተመራማሪ Van Gennep ሲሆን ከዚያ በኋላ በእንግሊዝ የስነ ሰብዓ ምሁራን ስራ ውስጥ ዋና ጉዳይ ለመሆን በቅቷል፡፡

የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች ከእርግዝናና ወሊድ ጀምሮ እስከ ሞት ድረስ ያሉ ዋና ዋና የሰው ልጅ ህይወት ሽግግሮችን ማለትም ወሊድን፣ ስም ማውጣትን፣ ግርዛትን፣ ትምህርት ማጠናቀቅን፣ ጋብቻን፣ ማዕረግ ማግኘትን፣ በስራ ዘርፍ የተለየ ባለሙያ መሆንን፣

[4] Van Gennep የህይወት ሽግግሮችን ለማጀብ የሚከወኑ ስነ ስርዓቶችን *Rites of passage* በማለት ጠርተዋቸዋል፡፡ በዚህ ጥናት *Rites of passage* የሚለው ቃል *የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች* በሚል የአማርኛ አቻ ስያሜ ቀርቧል፡፡

ሽምግልናን፣ ሞትን፣ ወዘተ ተከትለው የሚመጡ ለውጦችን የሚያጅቡ ስነ ስርዓቶች ናቸው (Barnard and Spencer 737; Gennep 3; Simpson and Roud 214)፡፡

Pickering (72) እንደሚሉት የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች ለተሻጋሪዎች አዲስ ማንነትን የሚሰጡና በመለየት፣ በሽግግርና በመቀላቀል ሶስት ደረጃዎች የሚያልፉ በመሆናቸው ውጥረትና መሸበርን ያስከትላሉ፡፡

በዚህ ጥናት ከህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች መካከል ትኩረት የተደረገባቸው የተመረጡ የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓቶች በመሆናቸው ከዚህ በታች የእነዚህ ስነ ስርዓቶች ምንነት ቀርቧል፡፡

#### 2.1.6.1. ወሊድ

Pentikäinen (788) እንደገለፁት ወሊድ ከተወለደው ህፃንም ሆነ ከወላጇ አንፃር ሲታይ ዋና ሊባል የሚችል ሽግግር ነው፡፡ ከህፃኑ አንፃር አዲስ ህፃን ወደ ዓለም የሚመጣበት በመሆኑ፤ ከወላጇ አንፃር ደግሞ ለወላጇ የእናትነት ሚናን የሚጨምር በመሆኑ ትልቅ ቦታ አለው፡፡

Watts (67) እና Grimes (36-37) እንደሚሉት ደግሞ ይህ በመሆኑ ምክንያት እርግዝናና ወሊድ ከሌሎች የህይወት ሽግግሮች በበለጠ ፎክሎራዊ ክዋኔዎች ይከወንባቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ የሚከወኑ የፎክሎር ክዋኔዎች ወላጇ በእርግዝና ጊዜ፣ በወሊድና ከወሊድ በኋላም ያለው ጊዜዋ ጥሩ እንዲሆን፤ ህፃኑም ከተወለደ በኋላ ጥሩ እንዲገጥመው ከመመኘት ጋር የተያያዙ እምነቶች፣ ልማዶችና ተግባራት ናቸው፡፡

Longhurst (77-78) እንደሚሉት የእርግዝና ወቅት ትኩረት የሚሰጠው ጊዜ በመሆኑ ነፍሰጡሯ ከወሊድ በፊትም ሆነ ከወሊድ በኋላ ማድረግ ስለሚኖርባት ጉዳይ ምክር ይሰጣታል፡፡ Han (2) በበኩላቸው እንደሚሉትም በወሊድ ጊዜና ከወሊድ በኋላም ለእናቲቱ ትኩረት የሚሰጥ ሲሆን በዚህ ጊዜ ምጥ፣ የልምድ አዋላጆች ሚና፣ ለእናቲቱና ለህፃኑ የሚደረግ እንክብካቤና የመንፃት ስነ ስርዓት ዋና ዋና ጉዳዮች ናቸው፡፡

የዘመናዊ ቴክኖሎጂ መስፋፋትን ተከትሎ ወሊድ በዘመናዊ የህክምና ሂደት ውስጥ እንዲያልፍ ሆኗል፡፡ Grimes (34) ይህን ሁኔታ በተመለከተ የሚከተለውን ሀሳባቸውን አቅርበዋል፡፡

> In my view, if no middle path is found or created between birth rites and biomedicine, indigenous ritual traditions are more likely to suffer the crash fatally. Ritual is an endangered species of action. It will not suffer well or for long the heavy tread of medicalization.

የGrimes ሀሳብ ከሀገር በቀሉ ስነ ስርዓትና ከዘመናዊው የህክምና ስርዓት የሚገኙ ጥቅሞችን በአንድ አስተሳስሮ የለዘበ አማካይ ቦታ መፍጠር መቻል ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችል አማራጭ በመፍጠር የባህላዊውን የወሊድ ስነ ስርዓት ተከዋኝነት ማስቀጠል ይቻላል የሚል ነው፡፡

#### 2.1.6.2. ጋብቻ

የጋብቻ ምንነትን በተመለከተ የተለያዩ ተመራማሪዎች ስነ ህይወታዊ፣ ህጋዊና ማህበራዊ አቅጣጫን በመያዝ ሀሳቦቻቸውን አቅርበዋል፡፡ ስነ ህይወታዊ ብያኔዎችን ከሰጡት መካከል Stone (qtd. in Wimalasena 166-167), Tambiah (qtd. in Wimalasena 167) እና Shujaa (577) ይገኙበታል፡፡ Sills (qtd. in Wimalasena 168), Leach (qtd. in Wimalasena 168) እና Dillingham and Isaac (qtd. in Grimes 61) ደግሞ ጋብቻን ከመብትና ግዴታ አንፃር በመመልከት ህግ ተኮር ሀሳቦችን አቅርበዋል፡፡ ከዚህ በታች የቀረቡ ሀሳቦች የማህበራዊ ግንኙነትን ፈርጅ በመያዝ የተሰጡ ናቸው ለማለት ይቻላል፡፡

Grimes (161-162) የጋብቻን ምንነት በተመለከተ የሚሰጡ ብያኔዎች አብዛኛውን ጊዜ ህግ ተኮር እንጂ የፍቅር ጉዳይን ከግምት ያላስገቡ ናቸው በማለት ከፍቅር ውጭ ያሉ ሌሎች የጋብቻ ጉዳዮች ቅድሚያ ሊሰጣቸው አይገባም ብለዋል፡፡ ተመሳሳይ ሀሳብ ያላቸው Eriksen (108) እንደሚሉት ደግሞ በብዙ ማህበረሰቦች ውስጥ ለመልካም ትዳር መፈጠር ፍቅር መሰረታዊ ጉዳይ ተደርጎ ስለማይታሰብ የጋብቻ ምርጫ በተጋቢዎቹ ዘመዶች ይወሰናል፡፡

የሰርግ ስነ ስርዓት ተጋቢዎች ከነበራቸው ማንነትና ደረጃ ወደተለየ ማንነትና ደረጃ መሻገራቸውን ይፋ ማድረጊያ ሲሆን (Pentikäinen 788; Kalmijn 23) ማህበራዊ ጉዳይም ነው (Cooke and Macy 62-63)፡፡

### 2.1.6.3. ሞትና ሀዘን

ሞት በተለያየ ቦታ፣ ጊዜና ሁኔታ የተለያየ አረዳድ አለው፡፡ Gerhart (1) እንደሚሉት ሞት መነጠል ሲሆን በገሀዱና በማይታየው ዓለም መካከል ሆኖ ሁለቱን ዓለማት የሚለይ ክስተት ነው፡፡ Barnard et al. (226-229) እንደሚሉት ሞት በአንዳንድ ማህበረሰቦች ዘንድ የህይወት የአንዴ መቋረጥ ብቻ ተደርጎ ሲታሰብ በአንዳንድ ማህበረሰቦች ደግሞ ረዥም ሒደት ነው፡፡

Lobar et al. (44) እና Gerhart (15) እንደሚሉት የሀዘን ስነ ስርዓቶችን ክዋኔ የሚያመጣው የማህበረሰብ እምነትና ልማድ ነው፡፡ Gerhart (1) እና Grimes (219-220, 236-237) የሞት መከሰትን ተከትለው የሚከወኑ ስነ ስርዓቶች ሟችን ለመሸኘትና በሀዘኑ የተጎዳን ቤተሰብ ለማጽናናት ዓላማ ሲባል የሚከወኑ ናቸው ያሉ ሲሆን Farbod (58) ደግሞ ሞት ለሀዘን ስነ ስርዓት መፈጠር ምክንያት እንዲሆን የሚያደርጉ ናቸው ያሏቸውን ጉዳዮች "1. Fear of dead body of the deceased person 2. Afraid of ghosts and spirits of the deceased person 3. Love and interest for the deceased person 4. Aversion of inanimate body of the deceased person 5. Disgust of death and to fight with it." በማለት ዘርዝረዋቸዋል፡፡

## 2.2. የንድፈ ሀሳብ ማሕቀፍ

የስነ ስርዓቶች ጥናት ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በየጊዜው እያደገ መምጣቱ ስነ ስርዓቶችን በተለያዩ የመተንተኛ ንድፈ ሀሳቦች እንዲመረመሩ አድርጓል፡፡ ንድፈ ሀሳቦች የአንድን ስነ ስርዓት የተለያዩ መልኮች ለመለየት ያስችላሉ፡፡ የአርጎባ ብሄረሰብን የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓቶች ለመተንተን የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ፣ መዋቅራዊ ንድፈ ሀሳብ፣ ትዕምርታዊ ንድፈ ሀሳብና ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

### 2.2.1. የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ

Performance (ክዋኔ) የሚለው ቃል ከጥንቱ የእንግሊዝኛ ቃል parfournir የመጣ ሲሆን ቀጥተኛ ትርጓሜውም ሙሉ በሙሉ ወይም በዝርዝር ማቅረብ ማለት ነው፡፡ በመሆኑም መከወን ማለት አንድን ነገር ማምጣት ወይም መፈፀም ማለት ነው (Turner, *From Ritual to Theatre* 79)፡፡ ክዋኔ ከሌሎች እንቅስቃሴዎች የተለየ መሆኑን የሚገልጽ መግቢያና

ማጠቃለያ ያለው ድርጊት ሲሆን የመግባቢያነት ትልቅ ሚና ያለውና በባህል ጥናት ቅድሚያ ተሰጥቶት የተጠና ነው (Hufford 531-532; Bronner 90)፡፡

በፎክሎር መስክ ክዋኔ የተግባቦት ስልት ሲሆን የክዋኔ ጥናት ከሚደረግባቸው የፎክሎር ጉዳዮች መካከል አንዱ ስነ ስርዓት ነው (Bauman, "Verbal Art as Performance" 293; Ben-Amos, "Performance" 630-634)፡፡

የክዋኔ ገለፃ በክዋኔ አላባውያን ምንነትና የእርስ በርስ ግንኙነት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ የከዋኞች ባህርይ፣ የክዋኔ ጊዜ፣ ቦታና አደረጃጀት የክዋኔ አላባውያን ሲሆኑ የተለያዩ ክዋኔዎች እንዲኖሩ የሚያደርጉ ጉዳዮች ናቸው (Finnegan 89-91, 95, 97-101)፡፡ በተጨማሪም የክዋኔ ዘዴዎች ማለትም የድምጽ ክዋኔ፣ ቁሳዊ ነገሮች፣ አካላዊ ገለፃዎችና ባህላዊ ደንቦች የክዋኔ ክፍሎች ናቸው (Bauman, "Performance" 101)፡፡

Finnegan (88) የክዋኔ ጥናት ሲከናወን የሚከተሉት መረጃዎች ሊካተቱ ይገባል ብለዋል፡፡

> (1) Meaning and artistry emerge in performance: this means attention not just to words but also to how they are delivered: such elements as intonation, speed, rhythm, tone, dramatisation, rhetorical devices, and performance techniques generally. (2) … interaction with, or behaviour of, all the participants, including the audience and its expectations, perhaps the researcher too … (3) … non-verbal features such as music, gesture, dance or visual attributes like costume … (4) … The interaction of individual artistry and cultural conventions … (5) The context of the performance (including the organisation of the event and the participants within it) … .

በመሆኑም የክዋኔ ጥናት ሲደረግ ከላይ የተዘረዘሩት የክዋኔ ጉዳዮች መታየታቸው ጥናቱን ምሉዕ ያደርጋል፡፡

የፎክሎርን ትርጉም ለማግኘት ከክዋኔ በተጨማሪ አውድ መሰረታዊ ጉዳይ መሆኑን Hufford (528) እና Ben-Amos ("Toward a Definition of Folklore in Context" 4-5) ይገልፃሉ፡፡

Ben-Amos (“"Context" in Context” 209, 210, 212) እንደሚሉት በፎክሎር መስክ አውድ የመግለጽ ሳይሆን የመፈከር ተግባር ነው፡፡

ተመራማሪዎች አውድን በተለያየ መልኩ ከፍለዋል፡፡ Bauman (qtd. in Ben-Amos, “"Context" in Context” 215) አውድን በስድስት ዋና ዋና ክፍሎች የከፈሉ ሲሆን እነርሱም (1) የትርጉም አውድ፣ (2) ተቋማዊ አውድ፣ (3) የተግባቦት ስርዓት አውድ፣ (4) ማህበራዊ መሰረት፣ (5) ግላዊ አውድና (6) የሁኔታ አውድ ናቸው፡፡ Ben-Amos (“"Context" in Context” 215, 216, 218) አውድን የባህል አውድና የሁኔታ አውድ በማለት፤ Sims and Stephens (334) ደግሞ አካላዊና ማህበራዊ በማለት በሁለት ከፍለውታል፡፡

የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓቶችን አከዋወን ለመተንተን ይቻል ዘንድ የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን የትንተናውን ምሉዕነት ለማግኘት ትንተናው አውድ ተኮር እንዲሆን ተደርጓል፡፡

### 2.2.2. መዋቅራዊ ንድፈ ሀሳብ

መዋቅራዊ ንድፈ ሀሳብ (structuralism) ቅርጽ ላይ ትኩረት የሚያደርግ ሲሆን የነገሮችን መዋቅርና የመዋቅሩ ንዑሳን ክፍሎች እርስ በርስ ያላቸውን ግንኙነት ይመለከታል (Storey 128-129, 330)፡፡ Dundes (qtd. in Bronner 123) መዋቅራዊ ንድፈ ሀሳብን ወደ ፎክሎር በማምጣት ሲበይኑት "[Structuralism is the] study of the interrelationships or organization of the component parts of an item of folklore" ብለዋል፡፡ በዚህ ብያኔ የፎክሎር መዋቅር ጥናት በፎክሎር ክፍሎች ላይ ትኩረት የሚያደርግ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

Gennep ስነ ስርዓቶችን በአግባቡ ለመረዳት ስነ ስርዓቶቹ የሚከወኑበትን መቼት መረዳት አስፈላጊ መሆኑን አበክረው በመግለጽ የስነ ስርዓቶች ትክክለኛ አውድ ስነ ስርዓቶቹ የሚከወኑበት ቅደም ተከተል ነው ብለዋል (Bell, *RITUAL* 36)፡፡ በተጨማሪም Gennep (191) የሚከተለውን ማለታቸው ስራቸው መዋቅራዊ ጥናት መሆኑን ይናገራል፡፡

> The purpose of this book is altogether different. Our interest lies not in the particular rites but in their essential significance and their relative positions within ceremonial wholes—that is, their order. … The underlying arrangement is always the same. Beneath a

multiplicity of forms, either consciously expressed or merely implied, a typical pattern always recurs: *the pattern of the rites of passage*.

Gennep ባቀረቡት የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶችን ለመረዳት የሚያስችል ሂደትን መሰረት ያደረገ ሞዴል የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች በሶስት ዋና ዋና የሽግግር ደረጃዎች ያልፋሉ ብለዋል፡፡ እነዚህ ደረጃዎች Separation (መለየት)፣ Transition (ሽግግር) እና Incorporation (መቀላቀል) ናቸው፡፡

- **መለየት፣**

የመለየት ደረጃ ተሻጋሪው ግለሰብ ወይም ቡድን ቀደም ሲል ከማህበረሰቡ አባላት ጋር ከነበረው ማህበራዊ ግንኙነት የሚለይበትና ወደሚቀጥለው ደረጃ የሚሄድበት ነው፡፡ መለየት ተሻጋሪው ግለሰብ ወይም ቡድን በተወሰነ ሁኔታው ልዩ የሚሆንበት፣ ሊያልፋቸው የሚገቡ ሙከራዎች ወይም ፈተናዎች ያሉበት፣ ማዕቀብ የሚጣልበትና በራሱ ፈቃድ የሚያደርጋቸው ጉዳዮች ጥቂት ብቻ የሚሆኑበት ነው (Daniel 160-161)፡፡

Van Gennep በወሊድ፣ በጋብቻና በሀዘን ስነ ስርዓቶች ክዋኔ ላይ ያለውን የመለየት ደረጃ ለይቶ አስቀምጧል፡፡ Gennep (41) እንደሚለው በነፍሰጡርነት ጊዜ የሚከወን የመጀመሪያው ስነ ስርዓት ነፍሰጡርን ከማህበረሰብና ከቤተሰብ ይለያል፡፡ የጋብቻ ስነ ስርዓት የመለየት ጊዜ በእጮኝነት ጊዜ ላይ የሚበቅል ሲሆን (Gennep 116) የሀዘን ስነ ስርዓት የሽግግር ጊዜ የተለየ የሀዘን ጊዜ በመሆኑ (Gennep 147) የመለየት ደረጃ የሞት መከሰት ነው፡፡

- **ሽግግር፣**

የሽግግር ደረጃ ከነባሩም ሆነ ከአዲሱ ማንነት የማይኮንበት የመካከለኛው ጊዜ ነው፡፡ ግለሰቡ ወይም ቡድኑ ከነባሩ ደረጃው ተለይቷል፤ ነገር ግን አዲሱን ማንነት የማግኛውም ጊዜ አልደረሰም ማለት ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ይህ ደረጃ የተለየ ማንነትን የማይሰጥና ደብዛዛ ነው፡፡ ግለሰቡ ወይም ቡድኑ ለፈተናዎች እንዲዘጋጅ የሚደረግበትና ነገሮችን በትዕግስት የሚያልፍበት ጊዜ ነው፡፡ አዲሱን ማንነት እስኪያገኝ የሚከፍላቸው መስዋዕትነቶች ይኖራሉ (Turner, “Liminal to Liminoid” 58-60, 79; Sims and Stephens 105)፡፡

በዚህ ደረጃ ተሳታፊዎች የተለየ ባህርይ ሊያሳዩ፣ መረበሽና ፍርሃት ሊያድርባቸው ይችላሉ፡፡ የሽግግር ጊዜ አጭር ወይም ረዥም፣ ቦታውም አንድ ውሱን ወይም ሰፊ ቦታ ሊሆኑ ይችላሉ (Pentikäinen 791-792; Thomassen 16)፡፡

Turner (*The Ritual Process* 96, 126, 128-129, 131-132) በGennep የተጀመረውን የሶስት ደረጃ ሞዴል በመቀበልና ደረጃዎቹን በቅደም ተከተል preliminal/ቅድመ ሽግግር፣ liminal/ሽግግር እና postliminal/ድህረ ሽግግር በማለት ለመካከለኛው liminal/ሽግግር ደረጃ ትኩረት ሰጥተው አስፋፍተው አቅርበውታል፡፡ Turner የሽግግር ደረጃ የእኩልነት መገለጫ ነው የሚል ሀሳብ ያቀረቡ ሲሆን በዚህ ደረጃ ያለን ማህበራዊ አንድነት ከመደበኛው የአኗኗር ስርዓት ካለ ማህበራዊ ግንኙነት ለይተው ለመግለጽ community ከሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ይልቅ communitas የሚለውን የላቲን ቃል ለመጠቀም መምረጣቸውንም ይገልፃሉ፡፡ Turner እንዳስቀመጡት Communitas የሽግግር ደረጃ ማህበራዊ ገጽታ ሲሆን ለጊዜውም ቢሆን ሰዎች ከተለመደው ማህበራዊ ስርዓት ውጭ የሚሆኑበትና በማህበራዊ መዋቅር መኖር ምክንያት የሚከሰቱ እንደ ማግለልና የበታችነት መልኮች የማይኖሩበት ነው፡፡

Gennep (41) እንደሚለው ወሊድን በተመለከተ የተለያዩ ስነ ስርዓቶች የሚከወንበት የእርግዝና ጊዜ የወላዷ የሽግግር ጊዜ ነው፡፡ Gennep (43) Plossን ጠቅሶ እንደሚለው በወሊድ የምግብና ፆታዊ ግንኙነት ክልክሎች፣ መገለልና ከኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መታቀብ ያሉበት የእርግዝና ጊዜ የሽግግር ጊዜ ነው፡፡ ጋብቻን በተመለከተ የእጮኝነት ጊዜ ከመለየት ደረጃ ባሻገር የሽግግር ደረጃንም ይይዛል (Gennep 116)፡፡ Gennep (147) እንደገለፀው በሀዘን ስነ ስርዓት ክዋኔ የሀዘን ጊዜ ለቋሚዎች የሽግግር ጊዜ ሲሆን የሀዘን ጊዜ ማብቂያ ወይም የሀዘን ደንቦች መነሳት ደግሞ የሽግግር ጊዜያቸው የሚያበቃበትና መቀላቀያ ጊዜያቸው የሚጀምርበት ነው፡፡ እርሱ እንደሚለው አንዳንድ ጊዜ የቋሚዎች የሽግግር ጊዜ የሚችም የሽግግር ጊዜ ይሆንና የቋሚዎች የሽግግር ጊዜ ማብቂያ የሚች ነፍስም ወደማይታየው ዓለም የምትቀላቀልበትና የሚችም የሽግግር ጊዜ ማብቂያ ይሆናል፡፡ የሽግግር ጊዜ አስከሬን በቤት ውስጥ የሚቆይበትን ጊዜ የሚሸፍን ሲሆን ይህ ጊዜ የሙት መታሰቢያ እስከሚከወንበት ጊዜ ድረስ ሊረዝምም የሚችል ነው (Gennep 149)፡፡

- **መቀላቀል፣**

ይህ የመጨረሻው የመቀላቀል ደረጃ ተሻጋሪው ሙሉ በሙሉ አዲስ በሆነ ማንነት ወደ ማህበረሰቡ የሚመለስበት ነው፡፡ ግለሰቡ ወይም ቡድኑ አዲስ ህይወት የሚጀምርበትና በአዲስ ማንነቱ ከሌሎች የማህበረሰቡ አባላት ጋር አዲስ ማህበራዊ ግንኙነትን የሚመሰርትበት ነው (Daniel 161-162)፡፡

Gennep እንደገለፀው ወሊድ ወላዷን ወደነበረችበት ቡድን የሚያቀላቅል ቢሆንም (41) ቆይታው ከማህበረሰብ ማህበረሰብ የሚለያይ በመሆኑ በአንዳንድ ማህበረሰቦች ዘንድ የሽግግር ጊዜ ከወሊድ በኋላም የሚቆይ ነው (43)፡፡ Gennep እንደሚለው በአንዳንድ ማህበረሰቦች ዘንድ በመንፃት ስነ ስርዓት ክዋኔ የመቀላቀያ ጊዜ የሚጀምር ሲሆን (41) ጋብቻን በተመለከተ የሰርግ ስነ ስርዓት ክዋኔ ዋና የመቀላቀያ ስነ ስርዓት ነው (117)፡፡ በሀዘን ስነ ስርዓት ክዋኔ የመቀላቀያ ጊዜ ቋሚዎች ወደነበረው ህይወታቸው የሚመለሱበትን (Gennep 149) እና ሟችም ወደ ሙታን ዓለም የሚቀላቀልበትን ጊዜ የሚመለከት ነው (Gennep 165)፡፡ Gennep የሽግግር ደረጃ እስከ ሙት መታሰቢያ ስነ ስርዓት ክዋኔ ሊረዝም እንደሚችል በመግለጽ (149) የመታሰቢያ ስነ ስርዓት ክዋኔ የመቀላቀያ ደረጃ የሚጀምርበት ሊሆን እንደሚችል አሳይቷል፡፡ በመታሰቢያ ስነ ስርዓቶች ላይ የሚቀርብ ምግብም የመቀላቀል ደረጃ መገለጫ ነው (Gennep 164)፡፡

ይህ ባለ ሶስት ደረጃ የስነ ስርዓቶች ጥናት ሞዴል የዚህ ጥናት ትኩረት የሆኑትን የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓቶችን ክዋኔ ከመዋቅር አንፃር ለመተንተን ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

### 2.2.3. ትዕምርታዊ ንድፈ ሀሳብ

Cohen (qtd. in Turner, “Symbolic Studies” 145) እና Geertz (qtd. in Turner, “Symbolic Studies” 145) ትዕምርት (symbol) የሚለውን ቃል በቅደም ተከተል "[Symbols are] objects, acts, concepts, or linguistic formations that stand *ambiguously* for a multiplicity of disperate meanings, evoke sentiments and emotions, and impel men to action" እና "any object, act, event, quality, or relation which serves as a vehicle for a conception" በማለት በይነውታል፡፡ በመሆኑም በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ ትዕምርቶች መልዕክትን በተመሳስሎ መንገድ የሚያስተላልፉ ነገሮች ናቸው፡፡

በስነ ስርዓቶች ጥናት ትዕምርት ቁልፍ ጉዳይ ሲሆን በስነ ስርዓት የትዕምርቶች ጥናት ትዕምርቶችን ከመለየት ባሻገር ትርጉማቸውንም መለየት አስፈላጊ ነው (Seligman et al. 4)፡፡ Turner (“Liminal to Liminoid” 55) በስነ ስርዓት ውስጥ የሚገኙ ትዕምርቶች ከአንድ በላይ ትርጉም ሊይዙ የሚችሉና ተለዋዋጭ መሆናቸውን በመግለጽ ሊተረጐሙ የሚገባው እርስ በርስ ባላቸው ግንኙነት መሰረት እንዳሉበት ሁኔታ ነው ብለዋል፡፡

Turner (“Symbolic Studies” 166, 176) የስነ ስርዓት ትዕምርት ፍቺ ሰው በመጠየቅ፣ ምልከታ በማድረግና አንድ ትዕምርት ከሌላው ትዕምርት ጋር ያለውን ግንኙነት በመለየት መረዳት ይቻላል ብለዋል፡፡ በተጨማሪም የትዕምርቱ ስያሜ፣ አካላዊና ስነ ህይወታዊ ምንነትና ቁሳዊ ገጽታ ትርጓሜን ለማግኘት ይረዳሉ፡፡

በአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓቶች ክዋኔ ውስጥ ያሉ ትዕምርታዊ ቁሶች፣ እንቅስቃሴዎች፣ ድርጊቶች፣ ሀሳቦች፣ ቃላትና ግንኙነቶች ተለይተው የተተነተኑ ሲሆን ይህን ለማድረግ ትዕምርታዊ ንድፈ ሀሳብ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

### 2.2.4.ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ

ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ (Functionalism) በ1930ዎቹ የመጣ ንድፈ ሀሳብ ሲሆን በፎክሎር ጥናት እያንዳንዱ የፎክሎር አሀድ ተግባር ሊኖረው ይገባል የሚል መነሻ ያለው ነው (Malinowski 159; Bell, *RITUAL* 23)፡፡

ንድፈ ሀሳቡ ትችቶች ተሰንዝረውበታል፡፡ ትችቶቹ ንድፈ ሀሳቡ ለታሪክ ትኩረት አይሰጥም፣ ማህበረሰብን በእኩል ደረጃ ያስቀምጣል፣ ማህበራዊ ለውጦችን ለመመርመር አያስችልም፣ አንድ ንድፈ ሀሳብ በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ ይሰራል የሚል እሳቤ አለው፣ እሴቱን በሚያከብር ማህበረሰብ ላይ ብቻ ትኩረት ያደረገ ነው፣ ከምክንያት ይልቅ ግብ ላይ ትኩረት ያደርጋል፣ የከዋኞቹ ግንዛቤ አስፈላጊ እንዳልሆነ ሁሉ ወደ አንድ መደምደሚያ ይሄዳል የሚሉ ናቸው (Price 241; Bascom 343-346)፡፡ ንድፈ ሀሳቡን በተመለከተ የቀረቡትን ትችቶች አስመልክተው Srivastava (28) ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ የታሪክና የለውጥ ጉዳዮችን ከማንሳት የሚያግደው ነገር የለም፣ Radcliffe-Brown (185) የንድፈ ሀሳቡ ትኩረት ተቋማት በማህበራዊ ስርዓት ውስጥ ያላቸውን ፋይዳ መለየት እንጂ በጊዜ ሂደት ያላቸውን ለውጥ መመርመር አይደለም፣ Davis (766-767) የተወሰኑ ተግባራውያን ንድፈ ሀሳቡን የማይቀበሉ ሰዎች ካከናወኗቸው ጥናቶች ጋር መሰረታዊ ልዩነት የሌላቸው የማህበራዊ ለውጥ

ትንታኔዎች ማድረጋቸውን እና Sims and Stephens (177) ንድፈ ሀሳቡ በአንድ ቡድን የሚተገበሩ የፎክሎር ዓይነቶችን ፋይዳና ትርጉም ለመለየት ከዋለ ጠቃሚ ነው በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ለተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ትልቁን ሚና የተወጡት እንግሊዛውያኑ Malinowski እና Radcliffe-Brown ናቸው[5]፡፡ Malinowski እና Radcliffe-Brown የዘመናዊ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ መስራቾች ቢሆኑም አካሄዳቸው የተለያየ ነው፡፡ Malinowski ከግለሰብና ለመኖር ከሚያስፈልጉት መሰረታዊ ፍላጐቶች የሚነሱ ሲሆን Radcliffe-Brown ከማህበረሰብና ለመኖር አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች ይነሳሉ፡፡ የMalinowski ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ መሰረት ያደረገው የሰው ልጅን ስነ ህይወትና ስነ ልቡና ሲሆን ምግብ፣ ዘር መተካት፣ አካላዊ ምቾት፣ ደህንነት፣ ግንኙነት፣ እንቅስቃሴና እድገት የማግኘት ሰባት የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጐቶች ድምር ነው፣ በባህል ውስጥ ያለ ማንኛውም ማህበራዊ ተቋምና ልማድ እነዚህን ፍላጐቶች ለማሟላት የቆመ ነው የሚል መሰረት አላቸው፡፡ Radcliffe-Brown መዋቅራዊ ተግባራዊ መንገድን የሚከተሉ (Structural functionalist) ናቸው፡፡ Radcliffe-Brown በማህበራዊ መዋቅር ላይ ትኩረት በማድረግ ማህበረሰብ የግንኙነቶች ስርዓት ሲሆን የማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ሀይማኖታዊ ተቋማት ተግባር ማህበረሰብን እንደ ስርዓት መጠበቅ ነው፣ ተቋማቱ የግለሰብን መሰረታዊ ፍላጐት የሚያሟሉ ሳይሆኑ ማህበራዊ መዋቅርን የሚጠብቁ ናቸው የሚል አካሄድ አላቸው (Malinowski 155-157, 171; Radcliffe-Brown 178-184)፡፡

ነገር ግን ሁለቱ ንድፈ ሀሳባውያን ትኩረት ያደረጉባቸውን ጉዳዮች ማጣመር ትንተናን ምሉዕ ያደርጋል፡፡ Oring (69-70) የሚከተለውን በማለት የMalinowski እና የRadcliffe-Brown አካሄድ ተደጋጋፊ እንጂ የሚጣረስ አለመሆኑን ይገልፃሉ፡፡

---

[5] Malinowski እና Radcliffe-Brown ይህን ንድፈ ሀሳብ በተመለከተ ወጥ የሆነ ስራ ከመስራታቸው በፊት የተለያዩ ምሁራን ለዚህ የጥናት አቅጣጫ መዳበር አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ ከምሁራኑ መካከል Fustel de Coulanges, Tylor, Smith, Sumner, Durkheim, Bucher, Webster, Schurtz ተጠቃሾች ናቸው (Bell, *RITUAL* 23-24; Malinowski 148)፡፡

> Despite their different emphases, both theorists must acknowledge the importance of both the social and psychological levels of analysis. Radcliffe-Brown cannot discern the functions of social patterns without taking into account their psychological implications, and Malinowski cannot account for the collective nature of psycho-physiological need satisfactions without suggesting the social consequences of these satisfactions.

በመሆኑም በተግባራዊ ትንታኔ የሚጠናው ፎክሎር በግለሰብ ደረጃ ያለውን ስነ ህይወታዊና ስነ ልቡናዊ ፋይዳ እንዲሁም ፎክሎሩ ያለውን ማህበራዊ ፋይዳ አጣምሮ በአንድነት ማቅረብ ተገቢና እርስ በእርስ የማይጣረስ ነው ማለት ነው፡፡

በዚህ ጥናት የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓቶች ለከዋኞቻቸው ግለሰቦችና በአጠቃላይ ለማህበረሰቡም ምን አይነት ስነ ልቡናዊ፣ ስነ ህይወታዊና ማህበራዊ ፋይዳዎች እኗቸው የሚለውን ለመመርመር የሁለቱ ንድፈ ሀሳባውያን አቅጣጫ የተጣመረበት ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

### 2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ከዚህ ቀደም በአርጐባ ብሄረሰብ የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች ላይ የተደረገ ጥናት አላጋጠመኝም፡፡ ነገር ግን በጥናት አካባቢውና በርዕሰ ጉዳዩ ላይ በተናጠል የተደረጉ ጥናቶች አሉ፡፡ በዚህ ክፍል ቅኝት የተደረገባቸው አስራ አንድ ጥናቶች ሲሆኑ ጥናቶቹ ሰባት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ፣ ኋላም በአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለመጀመሪያ ዲግሪ፣ ለማስተርስ ዲግሪና ለፒ. ኤች. ዲ. የተከናወኑ፣ አንድ በስነ ልሳን ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ የተከናወነ፣ ሁለት በጆርናል ላይ የታተሙና አንድ በአውደ ጥናት ላይ ቀርቦ በፕሮሲዲንግ ላይ የታተመ ጥናቶች ናቸው፡፡ ይህ ክፍል እነዚህ ጥናቶች የተለዩበትና ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ተመሳስሎና ልዩነት የቀረበበት ነው፡፡

አዲሱ ጴጥሮስ "የአርጐባ ማህበረሰብ የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ትንተና" በሚል ርዕስ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አድርገዋል፡፡ አዲሱ በዋናነት ከብሄረሰቡ ስያሜ፣ አመጣጥ፣ የትውልድ ሐረግና አሰፋፈር ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮችና ከጋብቻ አመሰራረት፣ ከሽምግልና ስርዓት፣ ከጥበበ ዕድ ሙያ ጋርና ከጀግንነት ጋር በተያያዘ የሚነገሩ ተረኮች

ላይ ትኩረት በማድረግ ያደረጉት ጥናት ዓላማ በብሄረሰቡ የሚነገሩ ተረኮች የብሄረሰቡን ማንነት ለመገንባት ያላቸውን ፋይዳ ማሳየት ነው፡፡ የአዲሱ ጥናታዊ ጽሁፍ የተከናወነው በአርጐባ ብሄረሰብ ላይ መሆኑ (ምንም እንኳን ከእኔ ጥናት በተለየ በአማራ ክልል በሚኖረው አርጐባ ላይ የተከናወነ ቢሆንም)፣ የነገረ ጋብቻና ሀዘን ጉዳይን ማንሳቱ እና ከጋብቻ ጋር በተያያዘ የሚነገሩ ተረኮችን የሚያነሳ መሆኑ ጥናቱን በመጠኑ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ ነገር ግን ከዓላማና ከግኝት አኳያ በጥናቱና በእኔ ጥናት መካከል ልዩነት አለ፡፡

ዐቢዩ አስማማው "የአርጎባ ብሄረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች፣ በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን፣ አርጎባ ልዩ ወረዳ" በሚል ርዕስ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አድርገዋል፡፡ የዐቢዩ ጥናት ዓላማ የብሄረሰቡን ማንነት ከቁሳዊ ባህሎቹ አንፃር ማጥናት ነው፡፡ ጥናቱ በአርጐባ ብሄረሰብ ላይ የተከናወነ መሆኑ (ምንም እንኳን ከእኔ ጥናት በተለየ በአማራ ክልል በሚኖረው አርጐባ ላይ የተከናወነ ቢሆንም)፣ የብሄረሰቡን ዳራዊ መግለጫ ለመስጠትም ቢሆን የወሊድና የጋብቻ ጉዳዮች የተነሱበት መሆኑ ጥናቱን ከእኔ ጥናት ጋር በመጠኑ ያመሳስለዋል፡፡ ነገር ግን በጥናቱና በእኔ ጥናት መካከል የዓላማ ልዩነት አለ፡፡

Seid Muhie "Documentation and Description of the Rekebot Traditional Conflict Resolution System of the Argoba Community" በሚል ርዕስ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናታቸውን በአማራ ክልል በሚገኘው የአርጐባ ብሄረሰብ ላይ አድርገዋል፡፡ የሰይድ ጥናት ዓላማ የአርጐባ ብሄረሰብን ረከቦት ባህላዊ የግጭት አፈታት ስነ ስርዓት መግለጽና በድምፅ፣ በምስልና በጽሁፍ መሰነድ ነው፡፡ ምንም እንኳን የሰይድ ጥናት በአማራ ክልል በሚኖረው የአርጐባ ብሄረሰብ ላይ የተከናወነ ቢሆንም በአጠቃላይ በብሄረሰቡ ላይ መከናወኑ ጥናቱን ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ጉዳይ ነው፡፡ ብሄረሰቡን ለማስተዋወቅ ያክል በመጠኑ የነገረ ጋብቻና ሀዘን ስነ ስርዓቶችን ጉዳይ ያነሳ መሆኑም ጥናቱን በመጠኑ ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ ነገር ግን የጥናቱ ዓላማ የብሄረሰቡን የግጭት አፈታት ስነ ስርዓት መሰነድ ላይ ብቻ የተወሰነ በመሆኑ በሰይድ ጥናትና በዚህ ጥናት መካከል የዓላማ ልዩነት አለ፡፡

የዚህ ጥናት አቅራቢ እታገኘሁ አስረስ "የአርጐባ ብሄረሰብ አፋዊ ትውፊቶችና መገለጫዎች ጥበቃ ጥናት" በሚል ርዕስ ያደረገችውና በአውደ ጥናት ላይ ቀርቦ በፕሮሲዲንግ የታተመ ጥናት የጥበቃ (safeguarding) ጥናት ሲሆን ዓላማው የመጥፋት አደጋ

የተጋረጠባቸውን የብሄረሰቡን ስነ ቃሎች ከጥፋት ለመመለስ የሚያስችሉ ስልቶችን ማሳየት ነው፡፡ ጥናቱ በብሄረሰቡ ላይ ይከናወን እንጂ ከዚህ ጥናት ጋር የዓላማ ልዩነት አለው፡፡

Tesfaye Hailu "History and Culture of the Argobba: recent investigations" በሚል ርዕስ ያደረጉትና በአካዳሚክ ጆርናል ላይ የታተመ ጥናት የብሄረሰቡ የባህል መገለጫዎች በዳሰሳ ደረጃ የቀረቡበት ሲሆን ከእኔ ጥናት ጋር የዓላማና የርዕሰ ጉዳይ ልዩነት አለው፡፡

አበባ አማረ፣ ደስታ አማረና ፍሬህይወት ባዩ በጋራ በመሆን "የሕይወት ዑደት ባህላዊ ክዋኔና ሥርዓት በስልጤ" በሚል ርዕስ ያከናወኑት በአካዳሚክ ጆርናል ላይ የታተመ ጥናታዊ ጽሁፍ እንደ እኔ ጥናት ሁሉ በህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች ላይ ትኩረት ያደረገ መሆኑ፣ ከዓላማ አንፃርም የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶችን ከክዋኔ፣ ከመዋቅር፣ ከትዕምርትና ከፋይዳ አንፃር የሚተነትን መሆኑ በእኔ ጥናትና በጥናቱ መካከል ያለ ተመሳስሎ ነው፡፡ ነገር ግን የእኔ ጥናት ከጥናቱ በተለየ ከጥናት ዘዴ አንፃር ቡድን ተኮር ውይይት በመረጃ መሰብሰቢያነት ጥቅም ላይ የዋለበት መሆኑ፣ ከእነ አበባ ጥናት በተለየ የለውጥና ቀጣይነት ጽንሰ ሀሳባዊ ምንነት የቀረበበት መሆኑ እንዲሁም የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔን በለውጥና ቀጣይነት መነጽር የተመለከተ መሆኑ የእኔ ጥናት ከጥናቱ የተለየ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

ስራዬ እንዳለው "የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ስርዓተ ክዋኔ በፍኖተ ሰላም አካባቢ ከፎክሎር ክዋኔ ንድፈ ሀሳብ አንፃር" በሚል ርዕስ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አድርገዋል፡፡ የስራዬ ጥናት የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች ከክዋኔ አንፃር የተተነተኑበት ነው፡፡ ጥናቱ የስነ ስርዓቶቹ አውዳዊ ክዋኔና መዋቅር ትንተና የተደረገበት መሆኑ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ ነገር ግን የእኔ ጥናት ስነ ስርዓቶቹን ከክዋኔ፣ ከመዋቅር፣ ከትዕምርትና ከተግባር አንፃር የመተንተን ዓላማ ያለው በመሆኑ ከስራዬ ጥናት የሚሰፋ ዓላማና ግኝት አለው ማለት ነው፡፡

ድርብወርቅ ብፁ "የጉምዝ ብሄረሰብ ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ሥርዓት በማንዱራ ወረዳ" በሚል ርዕስ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት ያደረጉ ሲሆን የጥናቱ ዋና ዓላማ በጉሙዝ ብሄረሰብ የሚከወኑ ዋና ዋና የህይወት ሽግግር ደረጃዎች ከሚከወኑባቸው አውድ አንፃር ያላቸውን ፋይዳ መለየት የሚል ነው፡፡ ጥናቱ የህይወት

ሽግግር ስነ ስርዓቶች አውድ ተኮር ጥናት ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም መዋቅራዊ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ በመረጃ መተንተኛነት ጥቅም ላይ የዋለበትና ስነ ስርዓቶቹ የከዋኞቻቸውን ማህበረሰብ መዋቅር ጠብቆ ከማቆየት አንፃር ያላቸው አስተዋጽኦ የቀረበበት ነው፡፡ በመሆኑም የድርብወርቅ ጥናት በእነዚህ ሁለት ጉዳዮች ምክንያት ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰል ሲሆን ነገር ግን የእኔ ጥናት የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች ከእነዚህ ጉዳዮች በተጨማሪ ከክዋኔ፣ ከመዋቅርና ከትዕምርት አንፃር የተፈተሸበት መሆኑ በዚህ ጥናትና በድርብወርቅ ጥናት መካከል ያለ ልዩነት ነው፡፡

አፀደ ተፈራ "የዋግኽምራ የወሊድ የጋብቻ እና የሞት ሥነ-ሥርዓት ፋይዳ ትንተና" በሚል ርዕስ፣ ደስታ አማረ "የህይወት ኡደት (የወሊድ፣ የጋብቻና የሞት) ስርዓቶች ክዋኔ ትንተና በወሊሶ ሊበን ኦሮሞ" በሚል ርዕስ እና ለማ ንጋቱ "የለቅሶ ሥርዓት ክወና በደቡብ ጎንደር ዞን" በሚል ርዕስ የፒ. ኤች ዲ ጥናት አድርገዋል፡፡

በአፀደ ጥናት መረጃን ለመተንተን ጥቅም ላይ ከዋሉ አራት ንድፈ ሀሳቦች ውስጥ አንዱ መዋቅራዊ ፋይዳዊነት ነው፡፡ የመዋቅራዊ ፋይዳዊነት ዋና ሀሳብ ማንኛውም ፎክሎር የከዋኙን ማህበረሰብ መዋቅር ጠብቆ ከማቆየት አንፃር ፋይዳ ሊኖረው ይገባል የሚልና ትኩረቱም የማህበረሰብ መዋቅር ሆኖ ሳለ (Radcliffe-Brown 178) በጥናቱ ውስጥ ንድፈ ሀሳቡ "መዋቅራዊነት" እና "ፋይዳዊነት" ተብሎ በሁለት ተከፍሎ "መዋቅራዊነት" ለብቻው የGennepን ባለ ሶስት ደረጃ ሞዴል የያዘ እሳቤ እንዲይዝ ተደርጎ ቀርቧል፡፡ "ፋይዳዊነት" በሚለው ርዕስ ስርም የተለያዩ ምንጮች ተጠቅሰው የፎክሎር ፋይዳ ቀርቧል፡፡ በመረጃ ትንተና ክፍልም "መዋቅራዊነት" በሚል ርዕስ ስር የስነ ስርዓቶቹ ክዋኔ ከGennep የመለየት፣ የሽግግርና የመቀላቀል ደረጃዎች አንፃር ያላቸው ገጽታ የቀረበ ሲሆን "ፋይዳዊነት" በሚል ርዕስ ደግሞ ክዋኔዎቹ አስገኝተዋቸዋል የተባሉ ግለሰባዊና ማህበረሰባዊ ፋይዳዎች ቀርበዋል፡፡

በመሆኑም በጥናቱ ውስጥ የመዋቅራዊ ፋይዳዊነት (structural functional) ንድፈ ሀሳብ በአግባቡ አልተተረጎመም፡፡ በRadcliffe-Brown እና Gennep የተነሱት ንድፈ ሀሳቦች የየራሳቸው ሀሳብ ያላቸው ሲሆኑ በጥናቱ ውስጥ ግን አንዱ በአንዱ ስር ቀርቧል፤ ወይም ሁለቱ ንድፈ ሀሳቦች የተዛመዱበት ሁኔታ አልቀረበም፡፡ ሌላው ጉዳይ የ Radcliffe-Brown ንድፈሀሳብ ትኩረት ማህበረሰባዊ ጉዳይ ሲሆን በጥናቱ ግለሰባዊ ፋይዳዎችም ተነስተዋል፡፡ የእኔ ጥናት የመዋቅርን እና የፋይዳን ጉዳይ በተናጠል በመመልከት የጥናት ትኩረት የሆኑ ስነ ስርዓቶች መዋቅር ከ Gennep የሶስት ደረጃ ሞዴል አንፃር የቀረቡ ሲሆን የMalinowski እና

የRadcliffe-Brown ንድፈሀሳቦችን በማቀናጀት ክዋኔዎቹ ለግለሰብና ለማህበረሰብ ያላቸው ፋይዳ ተመርምሯል፡፡

ሌላው ጉዳይ የአፀደ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ በጥናቱ የውይይት መድረክ እንደ መረጃ መሰብሰቢያ ጥቅም ላይ የዋለ መሆኑ የተገለፀ ሲሆን በመድረኩ ላይ ተሳታፊ የነበሩት የወረዳ ተወካዮችና የባህልና ቱሪዝም ሰራተኞች መሆናቸውም ተገልጿል፡፡ የተሳተፉት ሰዎች የተመረጡት በተቋም ሰራተኛነታቸው እንጂ ባላቸው የፎክሎር እውቀት አይመስልም፡፡ ለዚህ አይነቱ ጥናት መረጃ የሚሰበሰበው በዋነኛነት ከእውቀቱ ባለቤት ማህበረሰብ እንጂ በተቋም ደረጃ ተልከው ከሚመጡ ሰዎች አይደለም፡፡ በመሆኑም አጥኚዋ ክፍተት እሞላበታለሁ ብለው የመረጡት የውይይት መድረክ ውጤታማነት ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ነው፡፡

የለማ ጥናት ዋና ዓላማ በደቡብ ጐንደር ዞን የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ማህበረሰብ ሞት ሲያጋጥመው የሚከውናቸውን ስነ ስርዓቶች ክዋኔ መግለጽ ነው፡፡ ጥናቱ በህይወት ሽግግር ስነ ስርዓት ላይ የተከናወነና በንዑስ ዓላማነት የክዋኔዎቹን ትዕምርቶች የመፈከርና የመታሰቢያ ስነ ስርዓቶችን ማህበራዊ ፋይዳ የመግለጽ ዓላማ ያለው መሆኑ በጥናቱና በዚህ ጥናት መካከል ያለ ተመሳስሎ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ጥናት ከለማ ጥናት በተለየ የስነ ስርዓት ክዋኔ መዋቅርና ፋይዳ የተለየበትና የተተነተነበት መሆኑ በዚህ ጥናትና በለማ ጥናት መካከል ያለ ልዩነት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ይህ ጥናት የወሊድና የጋብቻ ስነ ስርዓቶችንም የሚመለከት መሆኑ በዚህ ጥናትና በለማ ጥናት መካከል ያለ ልዩነት ነው፡፡

የፒ. ኤች ዲ ጥናቶቹ በህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች ላይ የተከናወኑ መሆናቸው፣ የአፀደና የደስታ ጥናቶች ዓላማቸው ስነ ስርዓቶቹን ከክዋኔ፣ ከመዋቅር፣ ከትዕምርትና ከፋይዳ አንፃር መተንተን መሆኑ በእኔ ጥናትና በጥናቶቹ መካከል ያለ ተመሳስሎ ነው፡፡ ነገር ግን የእኔ ጥናት ከጥናቶቹ በተለየ የሜታ ፎክሎር ምርመራ በመተንተኛነት ጥቅም ላይ የዋለበት መሆኑ በእኔ ጥናትና በጥናቶቹ መካከል ያለ ልዩነት ነው፡፡

በተከናወነው የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት በአርጐባ ብሄረሰብ የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች ላይ የተከናወነ ጥናት አላጋጠመም። በመሆኑም ይህን የእውቀት ክፍተት ለመሙላት ይህ ጥናት ተከናውኗል። ቅኝት የተደረገባቸው ጥናቶችም ለዚህ ውሳኔ ያበቁ በመሆናቸው ለጥናቱ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

## ምዕራፍ ሶስት

## የጥናቱ ስነ-ዘዴ

ይህ ክፍል ጥናቱን ለማከናወን የሚያስችል የአጠናን ዘዴ የቀረበበት ነው፡፡ የጥናቱ ንድፍ፣ የጥናት ቦታና የመረጃ ሰጪዎች መረጣ፣ መረጃ የተሰበሰበባቸው መቼቶች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ፣ የመረጃ መተንተኛ አንፃር፣ የመቅረጫ መሳሪያዎች ምንነትና አጠቃቀም፣ ትራንስክሪፕሽን እና የጥናትና ምርምር ስነ ምግባር በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

### 3.1. የጥናቱ ንድፍ

የኢትኖራፊ ጥናት ቅደም ተከተል ወደ መስክ መሄድ፣ መረጃ ሰጪዎችን መምረጥ፣ ከማህበረሰቡ ጋር መተዋወቅና መቀላቀል፣ ተሳታፊ ምልከታ ማድረግ፣ ቃለ መጠይቅ ማድረግ፣ ሌሎች የመረጃ ምንጮችን መጠቀም፣ መረጃን ማጣራትና ማደራጀት እና የመረጃ ትንተና ማድረግ ነው በማለት Fetterman (*Ethnography step-by-step* 7-10) አጠቃልለው ያቀረቡ ሲሆን ይህ ጥናት የፎክሎር ጥናት በመሆኑ ከመስክ ስራ በፊት የጽሁፍ ሰነዶችን በመመልከት መረጃ መሰብሰብን በማስቀደም Fetterman ያቀረቡትን ሂደት የተከተለ ነው፡፡

### 3.2. የጥናት ቦታና የመረጃ ሰጪዎች መረጣ

ለጥናቱ መረጃ ለመሰብሰብ የተመረጡ ቦታዎችና መረጃ ሰጪዎችን ለመምረጥ ጥቅም ላይ የዋሉ የንሞና ዘዴዎች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

#### 3.2.1. የጥናት ቦታ መረጣ

የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው የአርጎባ ብሄረሰብ በአፋር ክልል አርጎባ ልዩ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ አስራ ሶስት ቀበሌዎች ውስጥ ማለትም በጋቸኔ፣ ደብረኮ፣ ወርካምባ፣ ኮካ፣ ጉዜ፣ ገበሮች፣ ጨኖ፣ አባሊ፣ ሱፊ ሃገር፣ ላይ መጠቅለያ፣ ታች መጠቅለያ፣ ቢሉ እና ጪሳ ቀበሌዎች ውስጥ ይኖራል፡፡ ብሄረሰቡ የሚኖርበት መልክዓ ምድር ሰፊና የተራራቀ በመሆኑና ጥናቱን በእነዚያ ቦታዎች ሁሉ ማከናወን ከሚጠይቀው ጊዜና ወጪ አንፃር አስቸጋሪ በመሆኑ ወካይ ቦታዎችን መምረጥ አስፈላጊ ሆኗል፡፡ በመሆኑም ጥናቱ በወረዳው በተመረጡ ስድስት ቀበሌዎች ማለትም በጋቸኔ፣ በገበሮች፣ በላይ መጠቅለያ፣ በጨኖ፣

በአባሊና በጐዜ ቀበሌዎች ተከናውኗል፡፡ ቀበሌዎቹ የተመረጡት በአላማ ተኮር የንሞና ዘዴ የተመረጡ መረጃ ሰጪዎች የሚኖሩባቸው በመሆናቸው፣ ከሌሎቹ ቀበሌዎች በተሻለ የብሄረሰቡ አባላት ሰብሰብ ብለው የሚኖሩባቸው በመሆናቸውና አካባቢውን በአግባቡ የሚያውቁና በጥናቱ መረጃ ሰጪ የነበሩ አቶ መሐመድ አቡበከር (17/11/2010፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) ቀበሌዎቹ የሚጐራበቱት በዚያው ወረዳ ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ቀበሌዎች ጋር መሆኑንና ከሌላው አካባቢ የተሻለ የብሄረሰቡ ባህላዊ ክዋኔዎች የሚከወኑባቸው መሆናቸውን በመጠቆማቸውና በማስረዳታቸው ምክንያት ነው፡፡ ቀበሌዎቹ በዚያው ወረዳ ውስጥ ከሚገኙ የተለያዩ ቀበሌዎች ጋር የሚዋሰኑ መሆናቸው ከአጐራባች ማህበረሰቦች ጋር አብሮ በመኖር ምክንያት የሚከሰትባቸው የባህል ንክኪ አነስተኛ የሆነ ክዋኔዎችን ለማግኘት ያስችላል፡፡

### 3.2.2. የመረጃ ሰጪዎች መረጣ

ናሙና ከብዙ ተጠኚ ቡድን ውስጥ አነስተኛ ወካይ ቡድንን መምረጥና ወካይ ቡድኑ የሰፊውን ቡድን መረጃና ሁኔታ ለመገመትና ለማመልከት መሰረት እንዲሆን ማድረግ ማለት ነው፡፡ ናሙና ከሚወሰድባቸው ዘዴዎች ውስጥ አንዱ እድል የማይሰጥ ናሙና ሲሆን በዚህ የንሞና ዘዴ ውስጥ ከሚመደቡ የንሞና አይነቶች መካከል ዓላማ ተኮርና ጠቋሚ የንሞና ዘዴዎች ይገኙበታል (Kumar 153)፡፡

ዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ የጥናትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችል መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ሰዎችን በመወሰን የሚደረግ የመረጣ አይነት ነው፡፡ በዚህ የንሞና ዘዴ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃ ሰጪዎችን ቁጥር የሚወስን የንሞና አሰራር የለም፤ አጥኚው ማግኘት የቻለውን ያህል መረጃ ሰጪዎችን ይወስዳል፡፡ ጠቋሚ የንሞና ዘዴ በተመራማሪው የሚፈለገው መረጃ ያላቸውን ሰዎች በሚያውቁ ሰዎች ጥቆማ ማግኘት የሚያስችል ንሞና ሲሆን ሰዎቹን ለማግኘት አስቸጋሪ ሲሆን (ምሳሌ፣ ሰዎቹ በሰፊ ቦታ የሚገኙ ጥቂት ሰዎች ሲሆኑ) ይህ የንሞና ዘዴ ጥቅም ላይ ይውላል (Schensul et al. 72)፡፡

በዚህ ጥናት ዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ እና ጠቋሚ የንሞና ዘዴ መረጃ ሰጪዎችን ለመምረጥ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ መረጃ ሰጪዎች ያላቸው እውቀት መሰረታዊ ጉዳይ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ጥናቱ ከሚያነሳው ርዕሰ ጉዳይ አንፃር የፆታ፣ የእድሜ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ደረጃ ልዩነት ተገቢና ወሳኝ መረጃዎችን ለማግኘት ያስችላል ተብሎ

በመታመኑ ምክንያት መረጃ ሰጪዎች ከተለያየ ፆታ፣ እድሜ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደረጃ አኳያ እንዲመረጡም ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ለባህልና ለጤና ባለሙያዎች ቃለ መጠይቅ በማድረግ መረጃ ተሰብስቧል፡፡

3.3. መረጃ የተሰበሰበባቸው መቼቶች

Goldstein (80-82) አውድን በሶስት መንገድ ለማየት ይቻላል ብለዋል፡፡ Goldstein ያቀረቧቸው ሶስት የአውድ አይነቶች ተፈጥሯዊ አውድ፣ ቅንብር ተፈጥሯዊ አውድ እና አርቴፊሻል አውድ ናቸው፡፡ ተፈጥሯዊ አውድ በማህበረሰብ ውስጥ ፎክሎር የሚከወንበት አውድ ነው፡፡ ቅንብር ተፈጥሯዊ አውድ በውሱን ጊዜ ተፈጥሯዊው አውድ በማይገኝበት ሁኔታ ተፈጥሯዊውን አውድ በተመለከተ መረጃ ለማግኘት የሚቀናበር አውድ ሲሆን አርቴፊሻል አውድ ፎክሎር በአጥኚው አነሳሽነት የሚከወንበት አውድ ነው፡፡

በዚህ ጥናት የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓቶችን በተመለከተ መረጃ የተሰበሰበባቸው አውዶች ተፈጥሯዊና አርቴፊሻል አውዶች ናቸው፡፡ በተፈጥሮ አውዶቻቸው መረጃ የተሰበሰበባቸው ክዋኔዎች የወሊድ ስነ ስርዓትን በተመለከተ የአራስ ቤት ገጽታ፣ የሰባት ቀን እጥበት፣ የአርባ ቀን እጥበት፣ የአምሮት ዋዜማ ዝግጅት፣ የአምሮት ስነ ስርዓት፣ ዘመናዊ የእርግዝና ክትትልና የወሊድ አገልግሎት፤ የጋብቻ ስነ ስርዓትን በተመለከተ የጉፍታ ስነ ስርዓት፣ የሰርግ ስነ ስርዓት፣ የጐጆ መውጫ ስነ ስርዓት ዝግጅት፣ የጐጆ መውጫ ስነ ስርዓት፣ የመልስ ስነ ስርዓት፤ እንዲሁም የሀዘን ስነ ስርዓትን በተመለከተ የሀፊሻ ስነ ስርዓት፣ የመሸኛ ዝግጅት፣ የአለቃቀስ ስነ ስርዓት፣ መተጋገዝ፣ የስራ ክፍፍል፣ ወዘተ (የቀብር ቀን ስነ ስርዓቶች)፣ የወር መታሰቢያ ስነ ስርዓት፣ የቆዳ ማጠፊያ ስነ ስርዓት እና የዓግል መፍቻ ስነ ስርዓት ሲሆኑ በአርቴፊሻል አውድ የተሰበሰቡ መረጃዎች የተፈጥሮ አውዶቻቸው ባልገጠሙኝ ባህላዊ የወሊድ (ምጥ) እና ባዷሼህ ስነ ስርዓቶች ላይ የሚከወኑ ዱዓዎች ናቸው፡፡

3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ጥናቱን ለማከናወን ካልዓይና ቀዳማይ መረጃዎች የተሰበሰቡ ሲሆን ከዚህ በታች እነዚህን መረጃዎች ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ የዋሉ ዘዴዎች ምንነት ቀርቧል፡፡

### 3.4.1. ሰነድ ፍተሻ

የጥናት ዓላማን ለማሳካት ጠቃሚ የሚሆን ካልዓይ መረጃ መሰብሰብ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም የመስክ ስራ ከማከናወን አስቀድሞ ጥናት የሚከናወንበትን ርዕሰ ጉዳይ እና አካባቢ የሚመለከቱ ዶክመንቶችን ማንበብና ግንዛቤ ማግኘት ወሳኝ ጉዳይ ነው (ፈቃደ 124-125)፡፡ በመሆኑም በቤተ መጻሕፍትና ሌሎች ተቋማት የሚገኙ የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶችን በተመለከተ ጽንሰ ሀሳባዊና ንድፈ ሀሳባዊ ትንታኔን፣ የአጠናን ዘዴን፣ ወዘተ በተመለከተ መረጃ የሚሰጡ መጻሕፍትን፣ የጆርናል አርቲክሎችን፣ ያልታተሙ ጽሁፎችን፣ መዝገበ ቃላትን፣ ከመረጃ መረብ የተገኙ ጽሁፎችን፣ ወዘተ በመመልከት ካልዓይ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች እና በአርጐባ ብሄረሰብ ላይ የተከናወኑ ቀደምት ጥናቶችን በመፈተሽም ጥናቶቹ ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ልዩነትና ተመሳስሎ ተለይቷል፡፡

### 3.4.2. ምልከታ

Goldstein (77) የምልከታ ቴክኒክ መስከኛው በመመልከት መረጃ የሚያገኝበትና ሁኔታዎችን ባየበት መልኩ የሚገልጽበት ነው በማለት እና ያለው (188) የምልከታ ዘዴ መረጃ ሰብሳቢው ሰው መረጃ ለመሰብሰብ ከሚፈልግባቸው ሰዎች ጋር በመሆን የሚያደርጉትን እያየና የሚናገሩትን እየሰማ በመመዝገብ መረጃ የሚሰበስብበት ዘዴ ነው በማለት ገልፀውታል፡፡

ምልከታ ተሳትፎ ያለበትና ተሳትፎ የሌለበት ነው፡፡ Flick (216, 220) እንደሚሉት ተሳትፎ የሌለበት ምልከታ ተመራማሪው ምልከታ ከሚያደርግበት ሁነት ራቅ ብሎ ምልከታውን የሚያደርግበት ሲሆን ተሳትፎ የሚደረግበት ምልከታ ደግሞ ሁለት አንፃር አለው፡፡ አንደኛው የተመራማሪው በሰዎቹ የቀን ተቀን ህይወት ተሳታፊ መሆንን የሚመለከት ሲሆን ሌላው ደግሞ ተመራማሪው የምርምሩን ጥያቄዎች ለመመለስ በሚያስችለው የተወሰነ ጉዳይ ላይ የሚያደርገውን ተሳትፎ ይመለከታል፡፡

ተሳትፎ የሌለበትን ምልከታ በተመለከተ Bechhofer and Paterson (93) የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> The researcher does not interact with those observed, nor influence events in any way. It would be naive to imagine that being observed has no effect at all on those observed, but it is well established in practice that after a while people come to ignore an observer, and the researcher will have very little impact on what happens.

በመሆኑም ተሳትፎ የሌለበት ምልከታ የሚያደርግ አጥኚ በመኖሩ ምክንያት እየሆነ ባለው ነገር ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ በጣም ትንሽ ነው ማለት ነው፡፡

በዚህ ጥናት የምልከታ ዘዴ በመስክ መረጃ ስብሰባ ስራ ጊዜ በዋና የመረጃ መሰብሰቢያነት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ይህ ዘዴ ጥቅም ላይ መዋሉ የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓቶች እንዴት እንደሚከወኑ በተግባር ለመመልከት አስችሏል፡፡ የሰዎችን ሀሳብና አመለካከት ሳይጨመርበት ነገሮች ያላቸውን ትክክለኛ ገጽታ ለማወቅ አስችሏል፡፡ ያደረግሁት ምልከታ ክዋኔዎች የሚከወኑበትን ቦታ፣ በአካባቢው ያሉ ሰዎችን፣ ቁጥራቸውን፣ የሚያደርጓቸውን እንቅስቃሴዎች፣ የስራ ክፍፍላቸውን፣ ስሜታቸውን፣ ዋና ዋና ድርጊቶችን፣ ቁሶችን፣ የሚከወኑ ሌሎች የፎክሎር ዓይነቶችን፣ የክዋኔውን ሰዓት፣ የክዋኔውን ዓላማ፣ ትዕምርታዊ ጉዳዮችን፣ ወዘተ ለመለየት ያስቻለ ነው፡፡

በመሆኑም በወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ የአምሮት ዋዜማ ዝግጅትንና ስነ ስርዓቱን፣ የአራስ ቤትን ገጽታን፣ የሰባትና የአርባ ቀን እጥበትን፣ በዘመናዊ የህክምና ተቋማት የሚሰጠውን የእርግዝና ክትትልና የወሊድ አገልግሎት ገጽታን፤ በጋብቻ ስነ ስርዓት ክዋኔ የጉፍታ ስነ ስርዓትን፣ የሰርግ ዝግጅት ዋዜማንና ስነ ስርዓቱን፣ የጐጆ መውጫ ዝግጅትንና ስነ ስርዓቱን፣ የመልስ ስነ ስርዓትን፤ በሀዘን ስነ ስርዓት ክዋኔ የሀፊሻ ስነ ስርዓትን፣ በቀብር ቀን የሚከናወኑ የመሸኛ ዝግጅትን፣ የስራ ክፍፍልን፣ የአለቃቀስ ስነ ስርዓትን፣ ወዘተ፣ የቆዳ ማጠፊያ፣ የወርና የዓግል መፍቻ ስነ ስርዓቶችን ተመልክቻለሁ፡፡ በዚሁ መሰረት 11 የወሊድ ስነ ስርዓቶችን፣ 16 የጋብቻ ስነ ስርዓቶችን እና 6 የሀዘን ስነ ስርዓቶችን ተመልክቼ መረጃ ሰብስቤያለሁ፡፡

ምልከታ ሳደርግ የተሳተፍኩባቸውና ያልተሳተፍኩባቸው ክዋኔዎች ነበሩ፡፡ ተሳትፎን በተመለከተ ከዚህ ቀደም ከብሄረሰቡ የተወሰኑ አባላት ጋር እውቂያና ጥሩ ወዳጅነት ያለኝ በመሆኑና በአካባቢው በነበረኝ ቆይታ በማህበረሰቡ የቀን ተቀን ህይወት ውስጥ እሳተፍ

የነበረ በመሆኑ በዚህ ጥናት የመረጃ ስብሰባ ወቅትም ከማህበረሰቡ ጋር የነበረኝ ወዳጅነት ተጠናክሮ ቀጥሎ ነበር፡፡ በማህበረሰቡ ኑሮና ባህል ውስጥ በመሳተፍ ከማህበረሰቡ ጋር የነበረኝን ወዳጅነት ያጠናከርኩት ግን የአጥኚነት ሚናዬ እንዳለ ሆኖ ወይም እየተሳተፍኩ እየታዘብኩም ነው፡፡ ያደረግሁት የተሳትፎ መጠን እንደየሁኔታው የተለያየ ቢሆንም በብሄረሰቡ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓቶች ላይም ተሳትፎ በማድረግ መረጃ ሰብስቤያለሁ፡፡ ያደረግሁት ተሳትፎ በወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ ላይ በአምሮት ስነ ስርዓት ዝግጅት ላይ በስራው በመሳተፍና አብሮ በመብላትና በመጠጣት፣ ለአምሮት ስነ ስርዓቱ ጥሪ ከሚያደርጉ ሰዎች ጋር አብሬ በመሄድ፣ በስነ ስርዓቱም ላይ አብሮ በመብላትና በመጠጣት፣ አራስ በመጠየቅና ለእንግዳ የሚቀርበውን ምግብ በመመገብ፣ በዱዓዎች ላይ በመቀበልና በዝኪሮቹ ክዋኔ ላይም በመሳተፍ፣ በጐጆ መውጫ ስነ ስርዓት ዝግጅት ላይ ስራ በማገዝ፣ በሰርግ፣ በመልስና በጐጆ መውጫ ስነ ስርዓቶች ላይ አብሮ በመብላትና በመጠጣት፣ ለጐጆ መውጫ ስነ ስርዓት ጥሪ ከሚያደርጉ ሰዎች ጋር አብሬ በመሄድና በመሳተፍ፤ በሀዘን ስነ ስርዓት ክዋኔ ላይም ለአስከሬን ማጠቢያ የሚሆነውን የቁርቁራ ውሀ ከሌሎቹ ሴቶች ጋር በመሆንና በማዘጋጀት፣ ለቅሶ በመድረስና አብሮ በመብላትና በመጠጣት፣ ወዘተ ምልከታ በማድረግ መረጃ ሰብስቤያለሁ፡፡ ልዩ እውቀትን በሚሹ ክዋኔዎች ላይ ደግሞ ከመመልከት ባለፈ ተሳትፎ አላደረግሁም፡፡

ምልከታ ያላደረግሁባቸው ክዋኔዎች ነበሩ፡፡ በመስክ ስራ ወቅት የቤት ውስጥ ወሊድ ክዋኔ ያላጋጠመኝ በመሆኑና የባዲሼህ ስነ ስርዓት ክዋኔን ለመመልከት በነበረው የመኪና እጥረት ምክንያት በቦታው ቆይቶ ለመመልከት ባለመቻሌ ምልከታውን ለማድረግ አልቻልኩም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሴት በቀብር ስነ ስርዓት ላይ እንድትገኝ የማይፈቀድ በመሆኑ በቀብር ስነ ስርዓት ላይ በመገኘት ምልከታ ለማድረግ አልቻልኩም፡፡ ይህ በመሆኑ ምክንያት ክዋኔዎቹን በተመለከተ የመረጃ ክፍተት እንዳይኖር የቃለመጠይቅ ዘዴን ተጠቅሜያለሁ፡፡

### 3.4.3. ቃለ መጠይቅ

Gray (213) ቃለ መጠይቅን "An interview is a conversation between people in which one person has the role of researcher" ብለው በመበየን ቃለ መጠይቅ ለምርምር ዓላማ ሲባል የሚከናወን መሆኑን ገልፀዋል፡፡ Goldstein (104) በበኩላቸው እንደገለፁት ደግሞ በቃለመጠይቅ የሚገኝ መረጃ የመላሹን ሰው እውቀት፣ እምነት፣ ሀሳብ፣ ፍላጐትና ድርጊት ይይዛል፡፡

የጥያቄዎችን ዓይነት መሰረት በማድረግ የቃለመጠይቅ አይነቶች ውሱን ቃለ መጠይቅ (structured interview)፣ ከፊል ነፃ ቃለ መጠይቅ (semi-structured interview) እና ነፃ ቃለ መጠይቅ (unstructured interview) ተብለው በሶስት ይከፈላሉ፡፡ ውሱን ቃለ መጠይቅ ጥያቄዎቹ ቀድመው የተዘጋጁና ምንም የማይጨመርበት ሲሆን ዝግ ጥያቄዎችን ይይዛል፡፡ ከፊል ነፃ ቃለ መጠይቅ በጠያቂውና በመላሹ መካከል የተሻለ ወይም ለዘብ ያለ ግንኙነት የሚታይበት፣ መላሹ ሀሳብ የሚሰጥበት ነገር ግን የግል ሀሳቡን እንዳይገልጽ ማዕቀብ የሚደረግበት ነው፡፡ ነፃ ቃለ መጠይቅ መደበኛ የሆነ የጥያቄና መልስ ቅርጽ የሌለው፣ ጠያቂው እየተሳተፈ በሚያደረገው ምልከታ የሚያነሳው፣ ባነሳው ጉዳይ ዙሪያ መረጃ ያስገኙልኛል ብሎ የሚያስባቸውን ጥያቄዎች በፈለገውና ለተጠያቂው ይመቻል ብሎ ባሰበው መንገድ ማቅረብ የሚችልበት፣ ተጠያቂው ደግሞ ነፃና መልስ ይሆናል ብሎ የሚገምተውንና ያመነውን መረጃ የሚሰጥበት ነው (Fife 93-95, 101-102)፡፡

በዚህ ጥናት ቃለ መጠይቅ በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በኢትኖግራፊ ጥናት ውሱን ቃለ መጠይቅ በማድረግ መረጃ የሚሰጡ ሰዎች ራሳቸውን እንዲገልፁ ወይም የሚፈለግን መረጃ እንዲሰጡ ማድረግ የሚያስኬድ ባለመሆኑ በዚህ ጥናት ጥቅም ላይ የዋሉ የቃለመጠይቅ ዓይነቶች ከፊል ነፃ እና ነፃ ቃለመጠይቆች ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት የብሂረሰቡ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓት ክዋኔዎችን፣ በስነ ስርዓቶቹ ውስጥ ያሉ ትዕምርታዊ ጉዳዮችን፣ በየስነ ስርዓቱ ክዋኔዎች ያሉ የፎክሎር ዓይነቶችን፣ ማህበረሰቡ ለስነ ስርዓቶቹ ያለውን አመለካከት፣ የብሂረሰቡ አባላት በስነ ስርዓቶቹ ክዋኔ ላይ ያላቸውን ተሳትፎ እና የስነ ስርዓቶቹን ለውጥና ቀጣይነት በተመለከተ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ከፊል ነፃ ቃለ መጠይቅ ለማድረግ መነሻ የሆኑ ጥያቄዎች የተዘጋጁት ወይም የተገኙት የመስክ ስራ ከመከናወኑ አስቀድሞ በተደረገ ንባብ ነው፡፡

ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው ክዋኔዎቹን በተመለከተ እውቀት ያላቸው ሰዎች ሆነው የወሊድ ስነ ስርዓትን በተመለከተ የልጆች እናቶችና አባቶች፣ የልምድ አዋላጆች፣ በጤና ተቋማት የእርግዝና ክትትል እያደረጉ ያሉና ክትትል የሌላቸው ነፍሰጡሮች፣ ለወሊድ ጤና ተቋም የገቡ ሴቶች፣ በጤና ተቋምና በቤት ውስጥ የወለዱ አራሶች፣ አዋላጅ ነርሶች፣ የባህል ህክምና እውቀት ያላቸው ሰዎች፣ የሀይማኖት አባትና ተማሪ፤ የጋብቻ ስነ ስርዓትን በተመለከተ ሽምግልና ተልከው የሚያውቁ አባቶች፣ ስለላ ሄዳ የምታውቅ ሴት፣ ጉፍታ

ጭና የምታውቅ ሴት፣ የሙሽራ ተከታይ ሆና የሄደች ሴት፣ ሙሽሮች፣ ከተጋቡ ጥቂት ጊዜ የሆናቸው ጥንዶች፣ የሰርግ ስነ ስርዓት ላይ የሙሽራውና የሙሽራዋ ሚዜዎች ሆነው ያገኘኋቸው ወጣቶች፤ እና የሀዘን ስነ ስርዓት ክዋኔን በተመለከተ እውቀት ያላቸው ሰዎች፣ አስከሬን የመገነዝ እውቀት ያላቸው ወንዶችና ሴቶች፣ የእድር ዳኛ ሲሆኑ የመረጃ ሰጪዎችን ቁጥር በተመለከተም 78 ለሚሆኑ ሰዎች ቃለ መጠይቅ ተደርጎ መረጃ ተሰብስቧል፡፡



ፎቶግራፍ 1. አጥኚዋ በቃለ መጠይቅ ጊዜ

### 3.4.4. ቡድን ተኮር ውይይት

ቡድን ተኮር ውይይት በጥናት ጉዳዩ ዙሪያ በቂ መረጃ አላቸው ተብለው የሚታሰቡ ሰዎችን በመውሰድና ጥያቄ በመጠየቅ በቡድን ሆነው በነፃነት በመወያየት መረጃ እንዲሰጡ የማድረጊያ ዘዴ ሲሆን ጥልቅና ዝርዝር መረጃ ለማግኘት የሚረዳ ዘዴ ነው (ያለው 197፣ 198)፡፡ ቡድን ተኮር ውይይት መደበኛና መደበኛ ያልሆነ ገጽታም ሊኖረው የሚችል ነው፡፡ ታቅዶበት የሚዘጋጅ መደበኛ ቡድን ተኮር ውይይት እንዳለ ሁሉ ጥናት የሚደረግበት ማህበረሰብ አባላት ተገናኝተው እየተዋዙ ሀሳብ የሚለዋወጡባቸውን አጋጣሚዎች አግኝቶ መጠቀምም ውጤት ያስገኛል (Schensul et al. 51, 54)፡፡

መደበኛ ቡድን ተኮር ውይይት ጊዜ ተወስኖለት፣ በታቀደ ሁኔታ፣ ወካይ ግለሰቦችን በመምረጥ የሚከናወን፣ ጥያቄ በቀጥታ ተጠይቆ የሚመለስበትና በመላሾች መካከል እንጂ በአጥኚውና በመላሾች መካከል ተጽዕኖ የሚያሳድር ንግግር የማይደረግበት፣ የተወያዮች ቁጥር የሚወሰንበት፣ ክፍያ የሚፈፀምበት፣ ጥያቄዎቹ ቀድመው የሚዘጋጁ ነው፡፡ መደበኛ

ያልሆነ ቡድን ተኮር ውይይት ግን በአጋጣሚና በተሳታፊዎቹ በሚመረጥ የተፈጥሮ መቼት የሚሆን፣ የተለመደ ቃለምልልስና ተፅዕኖ ያለበት፣ የተወያዮቹ ቁጥር በአጥኚው ቁጥጥር የማይደረግበት፣ መላሾች ራሳቸውን የሚመርጡበት፣ ማበረታቻ የሌለው፣ ጥቂት ጥያቄዎች ብቻ ቀድመው የተዘጋጁና አጥኚው ከማህበረሰቡ ጋር ቀድሞዉንም የተገነባ ግንኙነት ያለው ነው (Schensul et al. 51, 56, 57, 59)፡፡

በአንድ መደበኛ ቡድን ተኮር ውይይት ላይ የሚሳተፉ ሰዎች ቁጥርና ውይይቱ የሚወስደው ጊዜ የውይይቱን ጥራት ዝቅ ሊያደርግ በሚችል ሁኔታ መብዛትና ማነስም የለበትም፡፡ ይህን በተመለከተ Patton (qtd. in Flick 190) ከስድስት እስከ ስምንት ሰዎችና ከ1½ - 2 ሰዓት፣ Schensul et al. (53, 60) ከ5-15 ሰዎችና ከ45 ደቂቃ እስከ 1½ ሰዓት እና Kumar (101) ከ8-10 ሰዎች በማለት ሀሳቦችን አቅርበዋል፡፡

በዚህ ጥናት መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ ቡድን ተኮር ውይይቶች በመረጃ መሰብሰቢያነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በመደበኛው ቡድን ተኮር ውይይት ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው መረጃ ሰጪዎች መካከል የጥናት ርዕሰ ጉዳዩን በተመለከተ የተሻለ እውቀት አላቸው ተብለው የተለዩና ፆታን፣ ዕድሜንና ማህበራዊ ደረጃን መሰረት በማድረግ በቡድን የተደረጉ መረጃ ሰጪዎች የተካተቱባቸው፣ በእያንዳንዳቸው ከ5-10[6] ተወያዮች የተሳተፉባቸው አምስት ቡድን ተኮር ውይይቶች ተደርገዋል፡፡ አራቱ ውይይቶች በጋቸኔ፣ ጨኖ፣ ገበሮችና ጉዜ ቀበሌዎች የተከናወኑ ናቸው፡፡ አምስተኛው ውይይት በላይ መጠቅለያ ቀበሌ የተከናወነ ሲሆን የአባሊ ቀበሌ ለላይ መጠቅለያ ቀበሌ ጉረቤት በመሆኑና ከአባሊ ቀበሌ ለጥናት ርዕሰ ጉዳዩ ባላቸው እውቀት የተመረጡ መረጃ ሰጪዎች ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ ላይ መጠቅለያ በተከናወነው ውይይት ላይ በአንድነት እንዲወያዩ ተደርጓል፡፡ በተደረጉ ውይይቶች የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓቶችን ክዋኔ በተመለከተ መረጃ ተሰብስቧል፣ መረጃዎች ጠርተዋል፣ ተጠናክረዋል፡፡ በተጨማሪም አጥኚዋ ከማህበረሰቡ አባላት ጋር በነበረኝ ቆይታ በተገኘሁባቸው ውይይቶች የጥናት ርዕሰ ጉዳዬ የሆኑ ነጥቦች ሲነሱና ሆን ብሎ በማንሳትም በአካባቢው ያሉ ሰዎች ሀሳባቸውን እንዲሰጡ በማመቻቸት መደበኛ ባልሆነ ቡድን ተኮር ውይይት መረጃ ሰብስቤያለሁ፡፡

[6] በአጥኚዋ አማካይ የተሳታፊዎች ቁጥር እንደሆነ ስለታመነበት

በቃለመጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት ጊዜ መረጃ የተሰበሰበው በአማርኛ ቋንቋ ነው፡፡ በብሄረሰቡ ዘንድ አርጐብኛው ለቀን ተቀን መግባቢያነት ጥቅም ላይ እየዋለ ባለመሆኑና በዚህ ምክንያትም በስነቃል ክዋኔው ላይም ተጽእኖ ያደረ በመሆኑ የብሄረሰቡ አባላት ምሳሌያዊ አነጋገሮችን የሚናገሩት ለቀን ተቀን መግባቢያነት በሚጠቀሙበት አማርኛ ቋንቋ ነው፡፡

3.5. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

ዓይነታዊ የመረጃ ትንተና የሚደረገው የተሰበሰበው መረጃ ከቁጥር ይልቅ በቃላትና በገለፃዎች የተገለፀ ሲሆን ነው (ያለው 426)፡፡ ኢትኖግራፊ የጥናት ሞዴል ደግሞ ለተወሰነ ጊዜ በመስክ በመቆየት፣ ምልከታ በማድረግና መረጃ ሰብስቦ በመተርጐም የማህበረሰቦችን ባህርይ ለማጥናት የሚያስችል ሞዴል ነው (Denzin et al. qtd. in Naidoo 1)፡፡ በዚህ ጥናት ዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴና በዚህ ስር ያለው ኢትኖግራፊ የጥናት ሞዴል ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

የሜታ ፎክሎርን (Metafolklore) ጽንሰ ሀሳብ ለመጀመሪያ ጊዜ ያቀረቡት Dundes ሲሆኑ (Shenhar 55) ሜታ ፎክሎር ስነቃሎች ሌሎቹን የፎክሎር ዓይነቶች በተመለከተ የሚይዙትና የሚያስተላልፉት መልዕክት ማለት ነው፤ ከዋኙ ቡድን ሀሳቡን ለመግለጽ የሚጠቀምበት መንገድ ነው፡፡ በዚህ ጥናት የአርጐባ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ወሊድ፣ ጋብቻና ሞትን እና የጥናቱ ትኩረት የሆኑትን እነዚህን ሽግግሮች ተከትለው የሚከወኑ ስነ ስርዓቶችን በተመለከተ የያዟቸውንና ማህበረሰቡ ለማስተላለፍ የሚፈልጋቸውን መልዕክቶች ለመተንተን የሜታ ፎክሎር ምርመራ ተደርጓል፡፡ ከስነቃል ዘርፎች ውስጥ ምሳሌያዊ አነጋገሮች የተመረጡት በመስክ መረጃ የመሰብሰብ ስራ ወቅት መረጃ ሰጪዎች በሚሰጧቸው ምላሾቻቸውና ንግግሮቻቸው ውስጥ ትኩረታቸው የጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ የሆኑ ምሳሌያዊ ንግግሮች ይበዙ የነበረ በመሆኑ የጥናቱ ትኩረት የሆኑ ጉዳዮችን በተመለከተ ከሌሎቹ የስነቃል ዘርፎች በተለየ የብሄረሰቡ ምሳሌያዊ አነጋገሮች የያዟቸው መልዕክቶች መኖራቸውን በመገንዘብ ነው፡፡

3.6. የመረጃ መተንተኛ አንፃር

በዓይነታዊ የጥናት ትንታኔ ሁለት አይነት የመረጃ መተንተኛ አንፃሮች ያሉ ሲሆን እነርሱም ውስጣዊ አንፃር (Emic point of view) እና ውጪያዊ አንፃር (Etic point of view)

ናቸው፡፡ ውስጣዊ አንፃር አጥኚው ባህልን ከባለቤቶቹ አንፃር ለመረዳት ጥረት የሚያደርግበት አንፃር ነው፡፡ ውስጣዊ አንፃርን እውን ለማድረግ ደግሞ ምላሽን የሚያቅፍ ኢትኖራግፊ (Reciprocal Ethnography) ዘዴን መተግበር ያስፈልጋል፡፡ ይህ ዘዴ የመረጃ ትንተና ከተከናወነ በኋላ ወደ መረጃ ሰጪዎች በመመለስ መረጃው ተገቢ ትርጉም የተሰጠው መሆኑን ማረጋገጫ ነው፡፡ ውጪያዊ አንፃር ማህበረሰብን ከማህበረሰቡ ውጪ ከሆነ ሌላ ጉዳይ አንፃር መመልከቻ ሳይንሳዊ ዕይታ ነው (Fetterman, "Emic/Etic Distinction" 249; Morris et al. 781-783; Underberg 303)፡፡

በዚህ ጥናት ውስጣዊና ውጪያዊ አንፃሮች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ በመገኘት መረጃ ስሰበስብ መረጃውን ባየሁበትና በሰማሁበት መንገድ፣ የማህበረሰቡን እውነታ ከራሱ ከማህበረሰቡ አንፃር ማህበረሰቡ እንዳለው ያቀረብሁ በመሆኑ ውስጣዊ አንፃርን ተጠቅሚያለሁ፡፡ መረጃው በትክክል ከማህበረሰቡ አንፃር መገለፁን እርግጠኛ ለመሆን ደግሞ ከመረጃ ትንተና ስራው በኋላ ሰነዱን ይዤ ወደ ማህበረሰቡ በመመለስና በማቅረብ መረጃ ሰጪዎች መረጃው በትክክል መተርጐሙን እንዲያረጋግጡልኝ አድርጌያለሁ፡፡ ከማህበረሰቡ የሰበሰብኩትን መረጃ ከሳይንሳዊ ጽንሰ ሀሳቦችና ንድፈ ሀሳቦች አንፃር ስተነትንና የጥናት ጽሁፉን ስጽፍ ደግሞ ውጪያዊ አንፃርን ተጠቅሚያለሁ፡፡

3.7. የመቅረጫ መሳሪያዎች ምንነትና አጠቃቀም

በመስክ የተሰበሰበውን መረጃ ለመቅረጽ ጥቅም ላይ የዋሉ የመቅረጫ መሳሪያዎች መቅረፀ ድምጽ፣ የመስክ ማስታወሻ፣ የቪዲዮና የፎቶግራፍ ካሜራ ናቸው፡፡

መቅረፀ ድምጽ በቃል የሚገኝን መረጃ ለመቅረጽ፤ የመስክ ማስታወሻ ደግሞ አውድን ለመመዝገብ ያስችላሉ (Goldstein 119-120; Gray 227, 244)፡፡ Schensul et al. (96)፣ Bernard (389-398) እና ፈቃደ (93-95, 102-104) የተሻሉ ናቸው ያሏቸውን የማስታወሻ አወሳሰድ መንገዶችን አቅርበዋል፡፡ ነገር ግን የመስክ ማስታወሻ አያያዝንና መልክን የሚገዛ መመሪያ ባለመኖሩ ተመራማሪው ይመቸኛል ባለው መልኩ የመስክ ማስታወሻዎቹን ዓይነትና የማስታወሻ አያያዙን ማስተካከል ይችላል፡፡

የቪዲዮ ካሜራ ምስልንና ድምጽን ለመቅረጽና ያልተቆራረጡ እንቅስቃሴዎችን ለማግኘት ያስችላል፡፡ የፎቶግራፍ ካሜራም የባህል መገለጫዎችን ለመሰብሰብና ለመረዳት ጠቃሚ መሳሪያ ነው (Collier and Malcolm Collier 77, 82-83, 145)፡፡

ባደረግሁት የመስክ ስራ መቅረፀ ድምጽን በምልከታ፣ በቃለመጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት ጊዜ በመቅረጫ መሳሪያነት ተጠቅሜያለሁ፡፡ በምልከታ ወቅት መቅረፀ ድምጽ የተጠቀምኩት በተለያዩ ክዋኔዎች ላይ የሚከወኑ ቃላዊ መረጃዎችንና ስነቃሎችን በቀላሉ ለመቅዳት ስለሚያስችለኝ ነው፡፡ በቃለመጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት ጊዜም መረጃ በዋናነት የሚገኘው ከንግግር በመሆኑ ይህን መረጃ በቀላሉ ለመያዝ መቅረፀ ድምጽ ተጠቅሜያለሁ፡፡ መቅረፀ ድምጽ የተጠቀምኩት የመረጃ ሰጪዎችን ፈቃድ በመጠየቅ ወይም የማሳመን ስራ በመስራት ነው፡፡ በመቅረፀ ድምጽ የተቀዱ መረጃዎችን በየእለቱ ወደ ኮምፒውተር በመገልበጥ መረጃው የተገኘበትን ቦታና ቀን መዝግቤያለሁ፡፡

በምልከታ፣ በቃለመጠይቅና መደበኛና መደበኛ ባልሆነ ቡድን ተኮር ውይይት ጊዜ ቁልፍ ቃላትንና ሀረጋትን በመጠቀም የጥናቱ ትኩረት የሆኑ ዋና ዋና መረጃዎችን በማስታወሻ መዝግቤያለሁ፡፡ ያደረግሁትን ምልከታ በድምጽ፣ በቪዲዮና በፎቶግራፍ ብቀርጽም የጥናቱን ጉዳይ፣ ክዋኔውንና አውዱን በተመለከተ በማየትና በመስማት የማገኘውን መረጃ በመስክ ማስታወሻ አስፍሬያለሁ፡፡ የክዋኔ አውዱንና ተሳታፊዎችን እንዳይረብሽ በምልከታ ጊዜ ምዝገባውን ያደረግሁትን ከክዋኔ ቦታው ዞር በማለት ነው፡፡ ጥናት የማደርግ መሆኑን የሚያውቁ ቢሆንም እንኳ በእያንዳንዱ ክዋኔ እንደ ተሳታፊ እንጂ ከወረቀት ጋር ብቻ የሚያዩኝ አጥኚ እንድሆን አላደረግሁም፡፡ በተለይ የሀዘን ስነ ስርዓት ክዋኔን ስመለከት በተሳታፊዎችና በሀዘንተኞች ፊት ጽሁፍ መፃፍ አግባብ ስላልመሰለኝ ይህንን አላደረግሁም፣ ምልከታውን እንደጨረስኩ ወይም በመካከል በመካከል ከክዋኔው ቦታ በትንሹ ራቅ በማለት ማስታወሻውን በመፃፍ እመለስ ነበር፡፡ በመስክ ውሎዬ መጨረሻ ጊዜ በመስጠት እነዚህን ጭምቅ ማስታወሻዎች በተብራራ መልኩ በሌላ ማስታወሻ አብራርቼ በመፃፍና ማስታወሻ የተያዘበትን ቦታና ቀን በመመዝገብ የመረጃውን ይዘት በሚጠቁም አንድ ቃል አደራጅቻለሁ፡፡ በየቀኑ የመስክ ውሎዬ ያጋጠሙኝን ሁኔታዎች በአንድ በተለየ ማስታወሻ ያሰፈርኩ ሲሆን የመስክ የጊዜና የበጀት አጠቃቀሜን የምገመግምበት፣ እቅድና ተግባሬን የማነፃጽርበት ማስታወሻም ነበረኝ፡፡ በመሆኑም አራት የመስክ ማስታወሻ አይነቶች ተጠቅሜያለሁ፡፡

የቪዲዮና የፎቶግራፍ ካሜራዎችም በመስክ መረጃን የቀረጽኩባቸው መሳሪያዎች ናቸው፡፡ እነዚህ መሳሪያዎች የመረጃ ሰጪዎችን ፈቃድ በመጠየቅ በምልከታ፣ በቃለመጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት ጊዜ መረጃን ለመቅረጽ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ እነዚህ መሳሪያዎች

በመኖራቸው የሚያስከትሉት አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳለ ሆኖ (ለምሳሌ፣ የከዋኞችን ሀሳብ በመረበሽ የክዋኔን ተፈጥሯዊ አካሄድ ሊያዛቡ የሚችሉባቸው አጋጣሚዎች መኖራቸው) ክዋኔዎችን ከነአውዳቸው እንድቀርጽና ደጋግሜ በመመልከት ጥሩ መረጃ እንዲኖረኝ ረድተውኛል፡፡ በቪዲዮና በፎቶግራፍ ካሜራዎች የተቀረፁ መረጃዎችን በየእለቱ ወደ ኮምፒውተር በመገልበጥ መረጃው የተገኘበትን ቦታና ቀን መዝግቤያለሁ፡፡ መረጃው ወደ ጽሁፍ የተገለበጠ ሲሆን የመረጃ ክፍተትን ሞልቷል፣ አጠናክሯል፡፡

## 3.8. ትራንስክሪፕሽን

አብዛኛው ትንተና በጽሁፍ በቀረበ መረጃ ላይ የሚደረግ በመሆኑ በኦዲዮ-ቪዥዋል የተቀረፀን መረጃ በጽሁፍ ማስፈር መሰረታዊ ስራ ነው፡፡ መረጃን ወደ ጽሁፍ የመገልበጥ ስራ በተለያየ መንገድ ሊከናወን ይችላል፡፡ ሙሉ መረጃን ወደ ጽሁፍ መቀየር ሲፈለግ በመቅረፀ ድምጽ የተቀዱ ሙሉ ንግግሮችን እና በቪዲዮ ደግሞ ቃላዊ ያልሆኑ ተግባቦቶችንና አውዱንም ወደ ጽሁፍ መቀየር ያስፈልጋል፡፡ ይህን በተመለከተ Schensul et al. (16-17) "Transcribing entire audiotapes or videotapes is a labor intensive and time-intensive endeavor, but it yields a level of detail that permits close and repeated analysis of the data" በማለት ሙሉ መረጃን ወደ ጽሁፍ መቀየር ዝርዝር መረጃ ለማግኘት የሚያስችል መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በዚህ ጥናት ከፍ ሲል በተገለፁ የመረጃ መቅረጫ መሳሪያዎች የተቀረፁ መረጃዎች ሙሉ መረጃ በርዕስ ኮድ እየተሰጠው ወደ ጽሁፍ ተቀይሯል፡፡

## 3.9. የጥናትና ምርምር ስነ ምግባር

በመስክ መረጃ የሚሰበስብ ሰው ሊጠብቃቸው የሚገባው የስነ ምግባር ደንቦች የመረጃ ሰጪዎች ተሳትፎ በፈቃደኛነት ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይገባል፣ መረጃ ሰጪዎችንና ባህላቸውን ማክበር፣ ተሳታፊዎች የጥናቱ ተሳታፊዎች በመሆናቸው ምክንያት ሊደርስባቸው የሚችልን ጉዳት መቀነስ፣ የመረጃ ሰጪዎችን ምስጢር መጠበቅና መረጃ ሰጪዎችን ተጠቃሚ ማድረግ ያስፈልጋል የሚሉ ናቸው (Walliman 49; Gray 235, 239, 252, 258-259)፡፡ Creswell (107-108) እንደሚሉት ደግሞ በመረጃ ትንተና ጊዜ አድልዎን ማስቀረት የሚያስፈልግ ሲሆን የምርምር ጽሁፉን በመፃፍ ጊዜ ደግሞ ባለቤትነትን፣ ማስረጃን፣ መረጃንና ግኝትን በአግባቡ መግለጽ፣ መረጃ ሰጪዎችን የሚጐዳን መረጃ ማስወገድ እና ግልጽና ተገቢ ቋንቋን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

ይህ ጥናት ሲከናወን ከፍ ሲል የተገለፁ የጥናትና ምርምር ስነ ምግባር ደንቦችንና እያንዳንዳቸው የሚይዟቸውን ዝርዝር ሁኔታዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡ በመስክ ስራ ወቅት የመረጃ መሰብሰብ ስራውን ያከናወንኩት መረጃ ሰጪዎች የጥናቱን ዓላማ፣ ጥናቱ የሚከናወንበትን ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ እንዲያውቁ ካደረግሁ በኋላና መልካም ፈቃዳቸውን ከጠየቅሁ በኋላ ነው፤ የመቅረጫ መሳሪያዎችን የተጠቀምኩት ፈቃድ በመጠየቅና በማስረዳት ነው፤ ባህሉን አክብሬያለሁ፣ በመስክ ቆይታዬ በሙሉ የአካባቢውን የአለባበስ መንገድ ተከትያለሁ፣ በተቻለ መጠን ወዳጅነትን ለማጠናከር ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ በመረጃ ትንተና ወቅትም የተሰበሰበው መረጃ ሳይዛባ ምንጭ እየጠቀስኩ ተንትኛለሁ፡፡

## 3.10 የመስክ ስራ ክንውን ሂደት

ይህን የጥናት ስራ ለማከናወን በመስክ በቆየሁባቸው ጊዜዎች አብሮነታቸው ያልተለየኝ አቶ መሐመድ አቡበከር ናቸው፡፡ አቶ መሐመድ አቡበከር በወረዳው የባህል ጽ/ቤት የቅርስ ጥናት ባለሙያ ሲሆኑ አርጐባዎች ባህልን በተመለከተ እርሱ ይናገርልን የሚሏቸው፣ በወረዳው አስራ ሶስቱም ቀበሌዎች እውቅናና ተሰሚነት ያላቸው የሚከበሩ ሰው ናቸው፡፡ እኚህን ሰው ያወቅኋቸው ከዚህ ጥናት በፊት ለሌላ ጥናት ወደ አካባቢው በሄድኩበት ጊዜ ሲሆን በቀዳሚው ጥናት እገዛቸውን አግኝቼ ነበር፡፡ አቶ መሐመድ በመስክ ስራ ጊዜ መረጃ የሰጡ፣ በጥናት ርዕሰ ጉዳዩ ላይ እውቀት ያላቸውን ሌሎች ሰዎች የጠቆሙ፣ የመረጃ መሰብሰብ ስራውን ያስተባበሩ፣ የትኛው ቀበሌ ላይ ምን እንዳለ የሚያውቁ በመሆኑ መረጃ የተሰበሰበባቸው ቀበሌዎች መረጣ ላይ ትልቅ አስተዋጽኦ የነበራቸው፣ በናሙና ወደተመረጡ የገጠር ቀበሌዎች አብረውኝ በመሄድ መንገድ የመሩ፣ ወረዳው በገንዘብና በመኪና እንዲያግዘኝ ጥረት ያደረጉ ሰው ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በመስክ ስራ ወቅት ሁሉ ማረፊያዬን ያዘጋጁልኝ ሰው ናቸው፡፡ በወረዳው ምንም አይነት የማረፊያ አገልግሎት የሌለ በመሆኑ ጋቸኔ በቆየሁባቸው ጊዜ ሁሉ የማርፈው በአቶ መሐመድ ቤት፤ ከቤተሰባቸው ጋር በአንድነት ሲሆን በገጠር ቀበሌዎች በነበረኝ ቆይታም አቶ መሐመድ በሚያውቋቸው ሰዎች ቤት እያረፍኩ የመስክ ስራውን አከናውኛለሁ፡፡ ይህን እንደ መነሻ በማድረግ የመስክ ስራ ያከናወንኩበትን ሁኔታ አቀርባለሁ፡፡

የመስክ ስራ ያከናወንኩበትን ጊዜ በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ከፍሎ መመልከት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው የመስክ ስራ የጥናት ርዕሱን ለትምህርት ክፍሉ ከመስጠቴ በፊት የነበረኝ

የአምስት ቀን የመስክ ቆይታ ነው፡፡ ይህን የመስክ ስራ ያከናወንኩበት ዋና ዓላማ በርዕሱ ለመግፋት እንድወስን የሚያደርገኝን መረጃ ማግኘትና ከእነ አቶ መሐመድ ጋር በስራው ዙሪያ መወያየት ነበረና ይህንኑ አድርጌያለሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ወደፊት ጥናቱ ሊከናወን የሚችልባቸው ናሙና ቦታዎችንና የተወሰኑ መረጃ ሰጪዎችን የመለየት ስራ ተሰርቷል፡፡

ሁለተኛው ክፍል የመስክ ስራ የጥናት ርዕሱ ከፀደቀና ትልመ ጥናት ካዘጋጀሁ በኋላ የተከናወነ ሲሆን በዋናነት የጥናቴ ትኩረት የሆኑትን የብሄረሰቡን የወሊድና የሀዘን ስነ ስርዓቶች ክዋኔዎችን ለመመልከት ዓላማ የተደረገ ነው፡፡ ይህ የመስክ ስራ ከ1/10/2012 ዓ.ም. እስከ ከ30/12/2012 ዓ.ም. ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ በመመላለስ ያከናወንኩት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ በወሊድና በሀዘን ስነ ስርዓቶች ክዋኔ ላይ ምልከታ በማድረግ መረጃ የሰበሰብኩ ሲሆን ወቅቱ ጋብቻ የሚደረግበት ባለመሆኑ ምክንያት የጋብቻ ስነ ስርዓት ክዋኔን ምልከታ ያደረግሁት በጥር እና የካቲት/2013 ዓ.ም. ነው፡፡

ሶስተኛው የመስክ ክፍል ከ1/2/2013 ዓ.ም. እስከ 30/7/2013 ዓ.ም. ያለውን ጊዜ የሚሸፍንና በመካከል መመላለስ የነበረበት የመስክ ጊዜ ነው፡፡ በዚህ የመስክ ጊዜ በዋናነት በጋብቻ ስነ ስርዓት ክዋኔ ላይና ባጋጠሙ የወሊድና የሀዘን ስነ ስርዓቶች ክዋኔዎች ላይ ምልከታ የተደረገበትና መረጃ የተሰበሰበበት፣ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓቶች ክዋኔን በተመለከተ በቃለመጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት መረጃ የተሰበሰበበት፣ በመቅረፀ ድምጽ፣ በፎቶግራፍና በቪዲዮ የተሰበሰቡ መረጃዎች ተደራጅተው ወደ ኮምፒውተር የተገለበጡበት፣ በአጭሩ የተወሰደ የመስክ ማስታወሻ ተብራርቶ የተፃፈበት፣ የትራንስክሪፕሽንና መረጃን የማደራጀት ስራ የተጀመረበት ነው፡፡

በዚህ የመስክ ክፍል በቅድሚያ ከትምህርት ክፍሉ የተሰጠኝን ትብብር እንዲደረግልኝ የሚጠይቅ ደብዳቤ ይዤ ከአቶ መሐመድና ከሌሎች ቀደም ሲል ከማውቃቸው ወዳጆቼ ጋር በመሆን ወደ ወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት ሄድኩ፡፡ ደብዳቤውን በመስጠት የመጣሁበትን ዓላማና ላከናውናቸው ያሰብኳቸውን ስራዎች ለሀላፊዎቹ አስረዳሁ፡፡ ሀላፊዎቹ ዓላማዬን በመረዳት ለጥናቱ ተሸከርካሪ በማዋስና መጠነኛ የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ እንደሚያግዙኝ ቃል ገቡልኝ፡፡ ከዚያ በኋላ የመስክ ስራው ተከናውኗል፡፡

በዚህ የመስክ ስራ ክፍል መልካም አጋጣሚዎችና ያጋጠሙ ችግሮችም ነበሩበት፡፡ እንደ መልካም አጋጣሚ የምቆጥራቸው ዋና ዋና ጉዳዮች ከጥናቱ በፊት አካባቢውን ማወቄና የተወሰኑም ቢሆኑ ከብሄረሰቡ አባላት ጋር ወዳጅነት መፍጠሬ፣ በመስክ ስራው አብረውኝ የነበሩት ሰው ታዋቂና ተሰሚነት ያላቸው መሆናቸውና የወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት የገንዘብና የተሽከርካሪ እገዛ ያደረገልኝ መሆኑ ናቸው፡፡

ቀደም ሲል በአካባቢው ባደረግሁት ሌላ የጥናት ስራ ምክንያት ሰዎችን ማወቄና ወዳጅነትን መፍጠሬ በዚህ ጥናት ላደረግሁት የመስክ ስራ ምቹ ሁኔታን እንደፈጠረልኝ አስባለሁ፡፡ ከተመረጡ የመረጃ ሰጪዎችና ከታወቁ ክዋኔዎች በተጨማሪ ማን እና ምን የት ቦታ እንዳለ መረጃ እሰበስብ የነበረው በማውቃቸው ሰዎች ቤት በነፃነት በመሄድና በመወያየት ነበር፡፡ ሰዎች በቤታቸው እየተቀበሉና እየጋበዙ እንደ ወዳጅ ማየታቸው በየመንደሩ በነፃነት እየተንቀሳቀስኩ የፈለግሁትን መረጃ እንዳገኝ ረድቶኛል፡፡ በመስክ ስራ በአካባቢው ታዋቂና ተሰሚነት ያላቸውን ሰው ይዤ መንቀሳቀሴ ቀደም ሲል በማላውቃቸው የገጠር ቀበሌዎች ጭምር በተወሰነ መጠን መታመንንና ተቀባይነትን ያስገኘልኝ በመሆኑ ለመረጃ መሰብሰብ ስራው ቀና መንገድ ፈጥሮልኛል፡፡ የወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት ያደረገልኝ የገንዘብ ድጋፍና መኪናና ሾፌር በመመደብ ያደረገልኝ እገዛ ለመስክ ስራው ትልቅ አቅም ሆኖኝ ነበር፡፡ የመኪና እገዛ ባላገኝ ምንም አይነት የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በሌለባቸው፣ በሩቅ ኪሎ ሜትሮች በሚራራቁ፣ አየሩ በረሀማና መንገዱም በአለቶች የተሞላ ገደል፣ ከፍታና ዝቅታ በሞላባቸው የተመረጡ ቀበሌዎች የታሰበው ስራ ምን ሊሆን እንደሚችል ማሰብ ከባድ ነው፡፡

በመስክ ስራ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ፎቶ ለመነሳት ፈቃደኛ አለመሆን፣ በክዋኔ ወቅት ተሳታፊዎች ትኩረታቸው እኔ ላይ መሆንና አውዱ ላይ መጠነኛ ለውጥ ማስከተል፣ በጥርጣሬ አይን ማየት፣ በመኪና እጥረት ምክንያት ባቀድኩት ጊዜ ወደ ገጠር ቀበሌዎች ለመሄድ አለመቻል ሲሆኑ ላጋጠሙ ችግሮች በቅደም ተከተል ዓላማውን በመንገር ፎቶግራፍ እንዲነሱ የማሳመን ስራ በመስራት፣ በተቻለ መጠን በክዋኔዎች ላይ አጥኚ መሆኔ ጎልቶ እንዳይወጣ ጥረት በማድረግ፣ በዚያ ቦታ የተገኘሁበትን ዓላማ ለማስረዳት ጥረት በማድረግ እና ወደ ገጠር ቀበሌዎች የሚደረገውን ጉዞ ከጽ/ቤቱ የስራ ጉዞ ጋር እንዲጣጣም በማድረግና አብሮ በመሄድ ችግሩን ለመፍታት ጥረት ተደርጓል፡፡ በሀገሪቱ

የኮሮና ወረርሽኝ ተንሰራፍቶ በነበረባቸው ጊዜዎች የተከናወኑ የመስክ ስራዎች ቢኖሩም በዚህ ምክንያት የገጠመ ችግር የለም፡፡

አራተኛው የጥናት ጽሁፉ ከተዘጋጀ በኋላ የጥናት ጽሁፉን ይገፎ ወደ አካባቢው በመሄድና ለቁልፍ የመረጃ ሰጪዎች በማቅረብ መረጃዎች በትክክል መተርጐማቸውን ለማረጋገጥ ያደረግሁት የጥቂት ቀናት የመስክ ስራ ነው፡፡ በዚህ መልክ በመስክ ስራ የቆየሁበት ጊዜ ከስድስት ወር በላይ ነው፡፡

## ምዕራፍ አራት

## የአርጎባ ብሄረሰብ መግለጫ[7]

ይህ ክፍል የአርጎባ ብሄረሰብ የሚኖርበትን መልክዓ ምድር ገጽታ፣ የብሄረሰቡን ስያሜ፣ ታሪክና አመጣጥ፣ ማህበራዊ መዋቅር፣ ቋንቋ፣ ሀይማኖት፣ ኢኮኖሚ፣ አመጋገብ እና ባህላዊ ስነ ህንፃ ገጽታን በተመለከተ መረጃ የቀረበበትና ብሄረሰቡ የተዋወቀበት ነው፡፡

### 4.1. ብሄረሰቡ የሚኖርበት መልክዓ ምድር ገጽታ

የአርጎባ ብሄረሰብ በሀገሪቱ የተለያዩ ቦታዎች ላይ ተሰራጭቶ ይኖራል፡፡ የመኖሪያ አካባቢውን መሰረት በማድረግ ብሄረሰቡ ሰሜናዊ አርጎባ እና ደቡባዊ አርጎባ በማለት በሁለት ቡድን ተከፍሏል፡፡ Waldron (49-50) እ.አ.አ. በ1973 በሰሜናዊው አርጎባ ላይ የዳሰሳ ጥናት ያከናወኑትን Stitzን ጠቅሰው እንደሚሉት የሰሜናዊ አርጎባ ህዝብ ከአንኮበር እስከ ደሴ ከስምጥ ሸለቆ ተዳፋት በታች በከፍታማ ቦታዎች ላይ በሚገኙ መንደሮች ውስጥ ይኖራል፤ በምዕራብ ከአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ክርስቲያኖች ጋር የሚዋሰን ሲሆን በምስራቅ ከአፋሮች ጋር ይዋሰናል፡፡ የደቡቡ አርጎባ የሚገኘውም ከሀረር ከተማ ደቡብ ምስራቅ ነው፡፡ በተመሳሳይ Trimingham (223) ሰሜናዊው አርጎባ የቀድሞው የይፋት መንግስት ግዛት በነበረው አካባቢ ይኖራል፣ ደቡባዊው አርጎባ ደግሞ ከሀረር በስተደቡብ ባሉ ኮረብታዎች ላይ ይኖራል ብለዋል፡፡ በዚህ መልኩ ሰሜናዊ አርጎባ የተባለው በአፋርና በአማራ ክልል ውስጥ የሚገኘው አርጎባ ሲሆን ደቡባዊው አርጎባ ደግሞ በሀረሪና በኦሮሚያ ክልል የሚኖረው አርጎባ ነው፡፡

የአርጎባዎችን መገኛ በተመለከተ Abebe ("The dynamics of Ethnicity in a plural polity" 46, 49) እና አህመድ (161) በቅደም ተከተል የሚከተሉትን ብለዋል፡፡

> The Argobba occupy a series of heartland villages stretching in a long line along the foot of the eastern escarpment of the Great Rift Valley system, starting from the gorges of the Gą̈rfa and cą̈llą̈qqa rivers in the north to the area of the ką̈są̈m river in the south.

[7] በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ተሰራጭቶ የሚኖረው አርጎባ በቋንቋ [ከዘዬ ልዩነት በስተቀር]፣ በሀይማኖትና በታሪክ መነሻ አንድ በመሆኑ (Aklilu 183) በጽሁፉ የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነውን የአርጎባ ክፍል ብቻ የሚገልጽ ሆኖ ከቀረበ መረጃ ውጭ በዚህ ምዕራፍ የቀረበው የብሄረሰቡ መግለጫ የሁሉም አርጎባ መግለጫ ነው፡፡

የአርጐባ ህዝብ አገራችን በምትከተለው የፌደራል አወቃቀር መሰረት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ማለትም በሰሜን ሸዋ፣ በደቡብ ወሎ፣ በኦሮሚያ ልዩ ዞን፣ በደቡብ አፋር፣ በምስራቅና ምዕራብ ሐረርጌ ዞን፣ በሐረር ከተማና በዙሪያው የገጠር ቀበሌዎች ሰፍሮ ከሌሎች ህዝቦች ጋር በጋራ የሚኖር ሕዝብ ነው፡፡

አርጐባዎች በሀገሪቱ የተለያዩ ቦታዎች እንዲህ ተሰራጭተው መገኘታቸው በተለያዩ ምክንያቶች የተከሰተ ነው፡፡ Aklilu (182) ከእነዚህ ምክንያቶች መካከል ለንግድ ዓላማ የሚደረግ እንቅስቃሴ፣ የእርሻ ቦታ ፍለጋ፣ ሀይማኖትን የማስፋፋት ተግባር፣ ጦርነት፣ ኢኮኖሚያዊ ጫና እና ከብሄረሰቡ ውጭ የሚደረግ ጋብቻን ጠቅሰዋል፡፡

Waldronም (50-51) የአርጐባ ብሄረሰብ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ተሰራጭቶ የመኖሩ ምክንያት በሶስት ጉዳዮች ምክንያትነት ሳይሆን እንደማይቀር በመግለጽ መላምቶችን አቅርበዋል፡፡ የመጀመሪያው መላምት የአርጐባዎችን መነሻ ቤኒ አል ሁመያ የሚባል የአረብ ጐሳን በማድረግ ጐሳው በተለያዩ ጊዜያት ከአረቢያ ተነስቶ በፍልሰት ኢትዮጵያ እየገባ የተለያዩ ቦታዎች ላይ መስፈሩ ያስከተለው ውጤት ሳይሆን አይቀርም የሚል ነው፡፡ በሁለተኛነት የቀረበው መላምት ብሄረሰቡ ቀደም ሲል ከነበሩና ስማቸው ከአርጐባ ብሄረሰብ ጋር አብሮ ከሚነሳው የሙስሊም መንግስታት መሸናነፍ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ Waldron እንደሚሉት የሸዋ ስርወ መንግስትን አሸንፎ ስልጣን የያዘው የይፋት ስርወ መንግስት በተራው ከሰለሞናዊ ስርወ መንግስት ገዥዎች ጋር ባደረገው ጦርነት ጫና ደርሶበት መቀመጫውን ከምስራቅ ሸዋ ወደ ሀረርጌ እንዲያዛውር ተገድዷል፤ መጠሪያውም የአዳል ስርወ መንግስት ሆኗል፡፡ መላምቱ በሀረር የሚኖሩ አርጐባዎች የይፋት ስርወ መንግስት መሪዎችን በጦርነቱ ሲረዱና ወደ ሀረር ሲሄዱም ሲያጅቡ የነበሩ አርጐባዎች ሳይሆኑ አይቀሩም፤ ሰሜናዊ አርጐባዎችም የይፋት ስርወ መንግስት ወደ ሀረር ሲዛወር አብረው ያልሄዱና እዚያው የቀሩ የብሄረሰቡ አባላት ሳይሆኑ አይቀሩም የሚል ነው፡፡ ሶስተኛው መላምት ፍልሰት ነው፡፡ የአዳሉ ኢማም አህመድ ኢብራሂም (ግራኝ መሐመድ) በ1529 (እ.አ.አ.) በሀገሪቱ ደጋማ ክፍል ጅሃድ አውጀው ነበር፡፡ ነገር ግን ክርስቲያኖች ለጅሃዱ መልስ በመስጠት የአዳል ስርወ መንግስትን ጥለዋል፡፡ ከጅሃዱ መቀልበስ በኋላም በሀገሪቱ ዋና ዋና የህዝብ እንቅስቃሴና ፍልሰት ተከስቶ የነበረ ሲሆን መላምቱ አርጐባዎች በወቅቱ በሌሎች ህዝቦች እንቅስቃሴ በደረሰባቸው ጫና ምክንያት ከአንድ አካባቢ ወደ

ሌላው ያደረጉት ፍልሰት የብሄረሰቡን አባላት በተለያዩ አካባቢዎች እንዲኖሩ ሳያደርጋቸው አልቀረም የሚል ነው፡፡

የዚህ ጥናት ትኩረት በአፋር ብሄራዊ ክልል፣ በዞን 3፣ በአርጐባ ልዩ ወረዳ ውስጥ የሚኖረው የአርጐባ ብሄረሰብ ነው፡፡ የአርጐባ ልዩ ወረዳ የአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ከአፋር ክልል ጋር በሚገናኝበት ድንበር ቦታ ላይ የሚገኝ በመሆኑ በምዕራብ ሙሉ በሙሉ ከሰሜን ሸዋ ዞን የተለያዩ ወረዳዎች ጋር፤ በምስራቅ ደግሞ በአብዛኛው ከአፋር ክልል የተለያዩ ወረዳዎች ጋር ይዋሰናል፡፡ በመሆኑም ወረዳው በስተምስራቅ ከዱለቻ ወረዳ፣ በስተምዕራብ ከአንኮበር ወረዳ፣ በስተሰሜን ከጣርማ በር ወረዳ እና በስተደቡብ ከበረኸት ወረዳ ጋር ይዋሰናል፡፡ የወረዳው የቆዳ ስፋት 1200 ካሬ ኪሎ ሜትር ነው፡፡ አብዛኛው የወረዳው ክፍል ከባህር ጠለል በላይ ከ1780 እስከ 3200 ሜትር ከፍታ ላይ የሚገኝ ሲሆን ህዝቡ በዋናነት በመኸር ዝናብ፤ አልፎ አልፎ ደግሞ በበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ነው፡፡ ልዩ ወረዳው ከክልሉ ርዕሰ ከተማ ሰመራ 520 ኪሎ ሜትር፤ ከሀገሪቱ ርዕሰ ከተማ አዲስ አበባ ደግሞ 203 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል ("የአርጐባ ልዩ ወረዳ ገጽታ" 21)፡፡ የወረዳው የመሬት አቀማመጥ ተራራማና ተዳፋት የበዛበት[8] ሲሆን 95% የሚሆነው የወረዳው ክፍል ቆላ፣ 5% የሚሆነው ደግሞ ወይና ደጋ ነው፡፡ የወረዳው የሙቀት መጠን በአማካይ ከፍተኛው 29 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ሲሆን ዝቅተኛው ደግሞ 17 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ነው (የአርጐባ ልዩ ወረዳ የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት 1)፡፡ የሀገሪቱ የህዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ባወጣው የህዝብ ቆጠራ ሪፖርት መሰረት የወረዳው የህዝብ ብዛት 21,791 ያህል ነው (Federal Democratic Republic of Ethiopia Population Census Commission 59)፡፡ ወረዳው በአስራ ሶስት ቀበሌዎች የተከፋፈለ ነው፡፡ ቀበሌዎቹ ጋቸኔ፣ ደብረኮ፣ ወርካምባ፣ ኮካ፣ ጉዜ፣ ገበሮች፣ ጨዋ፣ አባሊ፣ ሱፊ ሃገር፣ ላይ መጠቅለያ፣ ታች መጠቅለያ፣ ቢሉ እና ጪሳ ሲሆኑ የወረዳው ርዕሰ ከተማ ጋቸኔ ነው፡፡

[8] የመስክ ስራ ክንውን ሂደት በቀረበበት ክፍል እንደገለጽኩት የአካባቢው መልክዓ ምድር ዳገትና ቁልቁለት የበዛበትና ለጉዞ የማይመች መሆኑን በመስክ ስራ ወቅት ለመገንዘብ ችያለሁ፡፡



ፎቶግራፍ 2. ብሄረሰቡ የሚኖርበት መልክዓ ምድር ገጽታ፣ ጨኖ ቀበሌ

### 4.2. የብሄረሰቡ ስያሜ

አርጐባ የሚለውን ስያሜ ምንነትና ብሄረሰቡ ይህን መጠሪያ ያገኘበትን ሁኔታ በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ሀሳቦችን አቅርበዋል፡፡

ከሣቴ ብርሃን (720) አርጐባ የሚለውን ቃል "በይፋት አውራጃ የሚገኝ ወረዳ፣ አርጐባ የሚባል የእስላም አገር" በማለት በይነውታል፡፡ በዚህም ቃሉ ለቦታ ወይም ለአካባቢ የተሰጠ ስያሜ ሆኖ ቦታውም የእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች የሚኖሩበት መሆኑ ተገልጿል፡፡ ደስታም (136) ቃሉን "ያገር ስም፣ ባዳል አዋሳኝ ያለ አገር" በማለት የተረጐሙት ሲሆን በዚያ የሚኖሩ ህዝቦችም አርጐባዎች እንደሚባሉ ገልፀዋል፡፡ Stitz (188, 192) ደግሞ አርጐባ የሚለው ቃል ለማህበረሰቡ የተሰጠ መጠሪያ ነው ብለዋል፡፡ በመሆኑም አርጐባ የሚለው ቃል ለብሄረሰቡ አባላት (ለሰዎቹ) እና ለመኖሪያ አካባቢያቸው የተሰጠ የጋራ ስያሜ ወይም መጠሪያ ሆኗል፡፡

በርካቶች ደግሞ አርጐባ የሚለውን ቃል ከብሄረሰቡ አመጣጥ ጋር በማያያዝና የሚነገሩ አፈ ታሪኮችን መሰረት በማድረግ ለቃሉ ፍቺ ወይም ትርጓሜ ይሰጣሉ፡፡ የመጀመሪያው አፈ ታሪክ አርጐባ የሚለው ቃል "አረብ ገባ" ማለት እንደሆነ ወይም ከዚያ የተገኘ እንደሆነ የሚገለጽበት ሲሆን የብሄረሰቡ መነሻ የሆኑ አረቦች ወደ ሀገሪቱ ሲገቡ ነባሮቹ ነዋሪዎች በመመልከታቸውና "አረብ ገባ" በማለታቸው ቃሉ በሂደት ተለውጦ አርጐባ ሆነና

ለብሄረሰቡ መጠሪያ ሆነ የሚል ነው፡፡ ይህም የብሄረሰቡ ዝርያ ከአረብ የሚመዘዝ እንደሆነ የሚገለጽበትም ነው፡፡ ሌላው ደግሞ አርጎባ የሚለው ቃል “ሀር ጉባ” ከሚለው የመጣ ነው የሚለው አካሄድ ነው፡፡ ይህም “ሀር ጉባ` ማለት የተራራ ላይ ሀር ወይም በተራራ ላይ የሚታይ ሀር ማለት ሲሆን በጥንት ጊዜ አርጎባዎች የሚኖሩት በተራራ ላይ በተሰራ የሀር ድንኳን ውስጥ የነበረ በመሆኑ ምክንያት ማህበረሰቡን ለመግለጽ “ሀር ጉባ” የሚለው ስያሜ ጥቅም ላይ እንደዋለ፤ በሂደትም ቃሉ አርጎባ ወደሚል መጠሪያ ቃል እንደተለወጠ የሚተረክበት አፈ ታሪክ ነው (Abebe, “The dynamics of Ethnicity in a plural polity” 80; Aklilu 174)፡፡

አህመድ (11) ብሄረሰቡ አርጎባ የሚለውን ስያሜ ከማግኘቱ በፊት ነገደ እስላም፣ ጀበርቲ፣ የይፋት ህዝብ ወላስሞች እና የይፋትና የሀረርጌ እስላማዊ ማህበረሰብ የሚሉ መጠሪያዎች እንደነበሩት ይገልፃሉ፡፡

## 4.3. ታሪክና አመጣጥ

አርጎባዎች ምንም እንኳን በሀገሪቱ የተለያዩ ቦታዎች በተበታተነ ሁኔታ የሚኖሩ ቢሆኑም አብዛኛዎቹ አርጎባዎች አንድ መነሻና የዘር ሀረግ እንዳላቸው ያምናሉ (Abebe, “The dynamics of Ethnicity in a plural polity” 82)፡፡

የአርጎባ ብሄረሰብን መነሻ በተመለከተ ቁርጥ ያለ መልስ የሚሰጥ ትንታኔ የለም፡፡ ነገር ግን መልስ የቀረበባቸው ሁለት ዋና ዋና መላምቶች አሉ፡፡ የመጀመሪያው መላምት የአርጎባ ብሄረሰብ መነሻ የአረብ ሀገር ነው የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የአርጎባ ብሄረሰብ የሀገሪቱ ነባር ሕዝብ ነው የሚል ነው፡፡ Abebe (“The dynamics of Ethnicity in a plural polity” 80) ይህን ሁኔታ አስመልክተው ″The Argobba think of themselves and are sometimes classified by their neighbors as ″Arab″ or decendents of ″Arabs″ and at other times considered indigenous people who received Islam sometime in the distant past″ በማለት የአርጎባዎችን መነሻ በተመለከተ መልስ ሆነው የሚቀርቡ ከአንድ በላይ መላምቶች እንዳሉ ገልፀዋል፡፡

የመጀመሪያው መላምት የብሄረሰቡ የዘር ሀረግ ከአረቢያ የሚመዘዝ መሆኑንና ለአሁኑ የአርጎባ ብሄረሰብ መነሻ የሆኑት ከአረቢያ ተነስተው ወደ ኢትዮጵያ የገቡ አረብ

ስደተኞች መሆናቸው የሚገለጽበት ሲሆን ይህን መንገድ የሚከተሉ የብሂረሰቡ አባላት ራሳቸውን ከሌሎች የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ ከሆኑ ቡድኖች የሚለዩበት ነው፡፡ ይህን በተመለከተ ምሁራን ሀሳቦቻቸውን ሰንዝረዋል፡፡ አለቃ ታየ (47 እና 48) ከመካ መዲና ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ አራት የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ ቡድኖች መካከል አርጐባዎች አንደኞቹ ናቸው ብለዋል፡፡ ተ/ፃድቅ (54) "መቼም ከመሐመድ ከነቢያቸው ጊዜ ዠምሮ እስላሞች [በይፋት ያሉ ሙስሊሞች] ከዓረብ አገር በደቡብ ወደዛሬው ሸዋ በሰሜንም ወደምጥዋ ወደ አርኪቆ በጠቅላላው ወደኤርትራ መግባታቸው የታወቀ ነው" ያሉ ሲሆን Aklilu (180) አርጐቦች በአመጣጣቸው አረቦች መሆናቸውን መቀበል እንደሚቻል ገልፀዋል፡፡

ይህ የመጀመሪያውና የብሂረሰቡ አመጣጥ ከአረቢያ እንደሆነ የሚገለጽበት መላምት ስደተኞቹ ከየትኛው የአረብ ጐሳ እንደሆኑ፣ መቼ፣ በየት አቅጣጫና በምን ምክንያት ወደ ሀገሪቱ እንደገቡ የሚገልፁባቸው መንገዶች የተለያዩ የሆኑ አቅጣጫዎችን የያዘ ነው፡፡ Tesfaye (197) የስደተኞቹ ማንነት ላይ ትኩረት የሚያደርጉና የብሂረሰቡን መነሻ የሚገልፁ አቅጣጫዎችን አቅርበዋል፡፡

> The data provided by knowledgeable elders in all the areas inhabited by the Argoba indicate that there are three different versions on the origin of this people. The first version holds that when the Arab clan known as Benew Imeya lost its ruling power to another clan 800 years ago and dispersed throughout the world, it came also to Ethiopia. The second version holds that when a dispute arose between the prophet Muhamed and the followers of other religions, eighty-two followers of the prophet came to Ethiopia to Ahmed Nejash carrying a letter asking him to accept Islam After having delivered the letter, they came to Yifat and settled there … .

Tesfaye ያቀረቧቸው አቅጣጫዎች የብሂረሰቡን መነሻ አረቢያ የሚያደርጉ ቢሆኑም የብሂረሰቡን የዘር ሀረግ በተመለከተ ግን የተለያዩ ሀሳቦች መኖራቸውን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በአለቃ ታየ (47-48) የቀረበውና የአርጐባዎችን አመጣጥና ማንነት የሚመለከት ታሪክ ደግሞ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የእስላሞች የመጀመሪያ ንጉስና ነቢይ መሐመድ በመዲና ነገሠ፡፡ መዲና ማለት በግዕዝና በዓረብ ቋንቋ ከተማ ማለት ነው፡፡ መሐመድ ፳፫ ዓመት ነገሠና ሞተ፡፡ … ከእርሱ ቀጥሎ ዓሊ የፋጢማ ባል ነገሠ፡፡ በእነርሱ ቁጥር ፴፬ ዓመት እርሱም ዓሊ በነገሠ ጊዜ ከነኸርዋን ኸዋርጅን የሚባሉ … ነበሩና ዓሊ ፈጃቸው፡፡ … ከነኸርዋን ቀጣሚት የምትባል አንዲት ሴት ነበረች፤ ከኸዋርጅዋን ነበሩና አባትዋንና ባልዋን ወንድሞችዋንም ዓሊ ፈጃቸው፡፡ እነዚህ ከዓሊ ሰይፍ ያመለጡ ሰዎች እናግባሽ አሉዋት፡፡ እርስዋም እኔን የሚያገባ ዓሊንና መዐውያንን አልአስን እነዚህን ሶስቱን የገደለ ነው፡፡ ያለዚያ ወንድ አለ ብዬ አላገባም አለቻቸው፡፡ እነዚህም ሶስቱ ሶስቱን ለመግደል በዕጣ ተካፈሉ፡፡ አንዱ ወደ መዐውያን ሄደ፡፡ መዐውያን ረኸዮም ነበረና ጉልበቱን አቁስሎ ሳይገድለው ተያዘና ተደብድቦ ሞተ፡፡ … ወደ አልአስ የሄደው ተሳስቶ ምስለኔውን ገደለና ተያዘ፤ በምስር ከተማ በካይሮ ተሰቀለ፡፡ … ወደ ዓሊ የሄደው በመስጊድ መንገድ ተሸምቆ ቆየውና በመርዛም ጦር ወጋውና በ፫ ቀን ሞተ፡፡ … የገዳዩም ስም አብዱረሑማን ነበር፡፡ እርሱም ተይዞ ተሰቀለ፡፡ በይፋት ያሉ አርጎቦች የዚህ የዓሊ ገዳይ የአብዱረሑማን ዘሮች ናቸው ስለዚህ ዓሊ ከሞተ በኋላ በዓረብ አገር ለመኖር የማይቻላቸው ሆነ፡፡ ዓሊ ከሞተ በኋላ ከሊፋነትን ማለት አልጋን በሻም አበጋዝ ለነበረው ለመዐውያን ሰጡት፤ እርሱም ከሊፋ ሆነ፡፡ ስለዚህም የአብዱረሑማን ዘሮች የዓሊን ደም በቀል ስለፈሩ በይፋት መጡ፤ ማለት በግልጥ ይፋት ማለት ነው፡፡ … ስማቸው ወይም አበጋዛቸው ወላስማ ነው፡፡

እዚህ በአለቃ ታዬ የቀረበን አንድ ዋና ጉዳይ መመልከት ይቻላል፡፡ ይህም የአርጐባ ብሄረሰብ መነሻ የሆኑት ከነብዩ መሐመድ ሲወርድ የመጣውን አልጋ ከወረሰው ከዓሊ ጋር ፀብ የነበራቸው ሌሎች ቡድኖች ናቸው የሚል ሀሳብ ነው፡፡

Aklilu (177) እንደሚሉት ደግሞ በአፄ ካሌብ ዘመነ መንግስት በአክሱም ውስጥ ገለብ የሚባል ጐሳ የነበረ ሲሆን ይህ ጐሳ በኋላ መጠሪያው የተቀየረው የአርጐባ ብሄረሰብ ሳይሆን አይቀርም፡፡

Abebe (“The dynamics of Ethnicity in a plural polity” 81) የብሄረሰቡን መነሻ አረብ ሀገር የሚያደርጉ ሰዎች የብሄረሰቡ የዘር ሀረግ የሚመዘዝበትን ጐሳ በተመለከተ የተለያዩ

ሀሳቦችን እንደሚያቀርቡ "some claim descent from the Beni al-Humaya, a Quraish Clan from Arabia: others traced and stressed a Hashamite Arabian origin: while still others fround the prophet Muhammad in their distant past genealogical reckoning" በማለት ገልፀዋል፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለውም የብሄረሰቡን ዝርያ ከፊሉ የቁረይሽ ጐሳ፣ ከፊሉ ሀሽማይት፣ ከፊሉ ደግሞ የነብዩ መሐመድ የዘር ግንድ ያደርጋሉ፡፡

ለብሄረሰቡ መነሻ የሆኑ ከአረቢያ የመጡ ስደተኞች ወደ ሀገሪቱ የገቡበትን አቅጣጫ በተመለከተ ደግሞ Aklilu (176) ሁለት አተያይ እንዳለ በመግለጽ የመጀመሪያው መልክ ብሄረሰቡ በሰሜን ኢትዮጵያ በኩል ገባ የሚል ሲሆን ሁለተኛው መልክ ደግሞ ብሄረሰቡ በሀገሪቱ ምስራቅ በር ገባ የሚል ነው ብለዋል፡፡

ስደተኞቹ ወደ ሀገሪቱ የገቡበትን ጊዜ በተመለከተም የተለያዩ አገላለፆች አሉ፡፡ Tesfaye (197) ከ800 ዓመት በፊት የሚል መላምት ያቀረቡ ሲሆን አህመድ (22) ስደተኞቹ ወደ ሀገሪቱ የገቡበትን ጊዜ ከ1400 ዓመት በፊት አድርገው አቅርበዋል፡፡ ስደተኞቹ ወደሀገሪቱ የገቡበትን ምክንያት በተመለከተ Tesfaye (197) ምክንያቱ ጦርነት መሆኑን የገለፁ ሲሆን Aklilu (176) ደግሞ ምክንያቱ ንግድ፣ ሀይማኖትን የማስፋፋት ስራ፣ ጦርነት ወይም በኢኮኖሚያዊ ጫና ምክንያት የተደረገ ስደት ሊሆን ይችላል ብለዋል፡፡

ሁለተኛው መንገድ የብሄረሰቡ የዘር ሀረግ ከአረቢያ የሚመዘዝ መሆኑን የማይቀበሉ ሰዎች የሚያነሱትና ብሄረሰቡ ጥንታዊና የሀገሪቱ ነባር ነዋሪ ነው የሚል ሀሳብ የሚሰነዘርበት ነው፡፡ በመስክ ስራ ወቅት ከብሄረሰቡ አባላት ጋር በተደረገ ውይይት ተወያዮች የአርጐባ የዘር ሀረግ ከአረቢያ የሚመዘዝ አለመሆኑንና ህዝቡ የሀገሪቱ ጥንታዊ ህዝብ መሆኑን እንደሚረዱ ገልፀዋል (17/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ መደበኛ ያልሆነ ቡድን ተኮር ውይይት)፡፡

### 4.4 ማህበራዊ መዋቅር

በአርጐባ ብሄረሰብ ዘንድ የዘር ሀረግ ማንነትንና የብሄረሰቡን አንድነት ለመግለጽ የሚያስችል መዋቅር የሚሰጥ ሲሆን በባህል ስርዓቱ ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው፡፡ ብሄረሰቡ አባዊ በመሆኑ የዝምድና ሀረግን የሚቆጥረው የወንድ ተወላጆችን መስመር ተከትሎ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ Abebe ("The dynamics of Ethnicity in a plural polity" 253-254) የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> The Argobba system of descent or reckoning of ancestry is embodied in a cognatically based descent group and expanded through successive births of males over the generations. Argobba descent can also refer to descendants of a known ancestor who are generally aware of their relationship to each other and of key male ancestors.

Trimingham (153) "… their women are unveiled, held in great honour, and enjoy considerable liberty" በማለት የብሄረሰቡን ሴቶች ነፃነት ገልፀዋል፡፡ በመስክ የመረጃ መሰብሰብ ስራ ወቅት በብሄረሰቡ አባላት የእለት ተእለት የኑሮ እንቅስቃሴ ውስጥ በነበረ ተሳትፎም ሴቶች ከባድና የሚያጐሳቁል ስራ እንዲሰሩ የማይደረጉ መሆኑንና ውሃ መቅዳት፣ ልብስ ማጠብ፣ የማገዶ እንጨት መስበርና ማምጣት የመሰሉ የጉልበት ስራዎችን በአብዛኛው ወንዶች የሚሰሩ መሆኑን ለመመልከት ተችሏል፡፡

የአርጐባ ብሄረሰብ አባላት አብዛኛውን ጊዜ የደም ዝምድናን መሰረት በማድረግ በአንድ መንደር ተሰባስበው ይኖራሉ፡፡ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ወንድ ልጅ ሲያገባ ሙሽራዋን ወደ ቤተሰቦቹ ቤት በማምጣት በአንድ ላይ ይኖራሉ (Abebe, “The dynamics of Ethnicity in a plural polity” 257)፡፡

### 4.5. ቋንቋ

የአርጐባ ብሄረሰብ ቋንቋ አርጐብኛ ሲሆን ከደቡባዊ የኢትዮ ሴማዊ የቋንቋ ቤተሰብ የሚመደብ ቋንቋ ነው (Bender et al. 33)፡፡ ቋንቋው ከሌሎች የኢትዮ ሴማዊ ቋንቋዎች ጋር በተለይም ከአማርኛ ቋንቋ ጋር የሚመሳሰል ሲሆን የብሄረሰብ አባላት በሀገሪቱ የተለያዩ ቦታዎች ተሰራጭተው የሚኖሩ መሆናቸውን ተከትሎ ቋንቋውም በሀገሪቱ የተለያዩ ቦታዎች ላይ ይነገራል፡፡

Leslau (*Argobba Vocabulary* 2), Zelalem (26) እና Bender et al. (30) አርጐብኛን የአማርኛ ቋንቋ ዘዬ አድርገው ያቀረቡ ቢሆንም Waldron (50)፣ Wetter (899, 906)፣ Getahun (“Argobba Verb Morphology and Syntax” 7, 312) እና Girma (“The Ethio-Semetic Languages” 68) ቋንቋው ከአማርኛ ቋንቋ የተለየና ራሱን የቻለ ቋንቋ ነው ብለዋል፡፡

የአርጐብኛ ቋንቋ እንደየሚነገርበት አካባቢ የሚለያዩ ዘዬዎች ያሉት ሲሆን የተለያዩ ምሁራን የዘዬዎቹን ዓይነት በተለያየ መንገድ ከፍለዋል፡፡ Leslau ("Classification of the Semitic Languages of Ethiopia" 5-6) ቋንቋው ሁለት ዘዬዎች ያሉት መሆኑን ገልፀው ቋንቋውን ከሚነገርበት መልክዓ ምድር አንፃር ሰሜን አርጐባና ደቡብ አርጐባ በማለት በሁለት ከፍለዋል፡፡ እርሳቸው እንደሚሉት ሰሜን አርጐባው በአንኮበር አካባቢ የሚነገረው አርጐብኛ ሲሆን ደቡብ አርጐባው ደግሞ በሀረር የሚነገረው አርጐብኛ ነው፡፡ Getahun ("Argobba Verb Morphology and Syntax" 8-11) ደግሞ በሰሜኑ አርጐባ ብቻ የሾንኬና የጋቾኔ ሁለት ዘዬዎችን እንዳገኙ ገልፀው በእነዚህ ዘዬዎች መካከል ያለውን ልዩነት አሳይተዋል፡፡ በሌላ መንገድ ደግሞ Wetter (906) በአልዩ አምባ አካባቢ የሚነገረውን አርጐብኛ ሰሜን አርጐባ፣ በሀረር የሚነገረውን ደግሞ ደቡብ አርጐባ በማድረግ የመክፈል አካሄድ ሊታረም ይገባል ብለዋል፡፡ እርሳቸው እንደሚሉት በአልዩ አምባና በሀረር የሚነገሩ የአርጐብኛ ዘዬዎች ሁለቱም የደቡብ አርጐባ ዘዬዎች ሲሆኑ የሰሜኑ አርጐባ ዘዬዎች ደግሞ የጦልሃ/ሾንኬ እና የሸዋ ሮቢት ዘዬዎች ናቸው፡፡ Mohammed et al. (434) እንደሚሉት ደግሞ ቋንቋው ሶስት ዘዬዎች ያሉት ሲሆን እነርሱም የአንኮበር-ቀዎት ዘዬ፣ የበረኸት-ምንጃር ዘዬና የጦልሀ-ሾንኬ ዘዬ ናቸው፡፡ Mohammed et al. በሀረር የሚነገረውን አርጐብኛ ዘዬ በተመለከተ ያሉት ነገር አለመኖሩን ልብ ይሏል፡፡ Voigt (331) ደግሞ የቋንቋውን ዘዬዎች አራት በማድረግ ዘዬዎቹ በሀረር፣ በአንኮበርና ጨኖ፣ በሸዋ ሮቢት እና በሾንኬ አካባቢ የሚነገሩ አራት ዘዬዎች ናቸው ብለዋል፡፡

አርጐብኛ ቋንቋ ተናጋሪ እያጣና እየተዳከመ የሚገኝ ቋንቋ ሲሆን የብሄረሰቡ አባላት ከአርጐብኛው ይልቅ እንደየሚኖሩበት አካባቢ አማርኛ፣ ኦሮምኛና አፋርኛ ቋንቋዎችን ይናገራሉ፡፡ Leslau (*Argobba Vocabulary* 1) ቋንቋው በአንኮበር አካባቢ፣ በአልዩ አምባና ጨኖ መንደሮች እንዲሁም በሀረር እንደሚነገር በመግለጽ በአልዩ አምባ ቋንቋው ጥቅም ላይ የሚውለው በእድሜ በገፉ ሰዎች ሲሆን ወጣቱ ትውልድ አማርኛን ይጠቀማል ብለዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በሀረር የሚኖሩ አርጐባዎችም ከአርጐብኛው ይልቅ የኦሮምኛ ቋንቋን የሚጠቀሙ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ ይህ ሁኔታ በቋንቋው ላይ የመጥፋት አደጋ የጋረጠና ቀጣይነቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የፈጠረ ቢሆንም Stitz (189)፣ Zelealem (26)፣ Getahun ("Definiteness in Argobba NPs" 201; "Argobba Verb Morphology and Syntax" 31, 312) እና ግርማ (*አርጎብኛ-አማርኛ መዝገበ ቃላት* 2) እንደሚሉት ደግሞ

ቋንቋው ሙሉ በሙሉ የጠፋ ባለመሆኑ ቋንቋውን ከመጥፋት የመታደግ ስራ ሊሰራ ይችላል፡፡

አረብኛ የእስልምና ሀይማኖት አስተምህሮ የሚተላለፍበት ቋንቋ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ብዙዎቹ የብሄረሰቡ አባላት የአረብኛ ቋንቋ እውቀት አላቸው (Abebe, “The Argobba of Ethiopia are not the Languages they speak” 13)፡፡

### 4.6. ሀይማኖት/ እምነት

የአርጎባ ብሄረሰብ የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ ነው፡፡ Abebe (“The Argobba of Ethiopia are not the Languages they speak” 19) "Argobba Islamic identity is … one of the several symbols of their ethnicity and cultural continuity. Argobba ethnicity is not therefore distinct from their religious identity" በማለት አርጎባነትና እስልምና ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

የአርጎባ ብሄረሰብ ታሪክ እስልምና ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ከመግባት ታሪክ ጋር የተገናኘ ነው፡፡ Aklilu (176) አህመድ (16) እና አለቃ ታዬ (70) አርጎባዎች በሀገሪቱ የመጀመሪያዎቹ የእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ ስርግው (181-185) እና Abbink (111) እንደሚሉትም እስልምናን ወደ ኢትዮጵያ ያስገቡ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ከላይ ለአርጎባ ብሄረሰብ መነሻ ናቸው ተብለው የተገለፁቱ ናቸው፡፡

አርጎባዎች በተለይ ቀደም ያለው ትውልድ ከእስልምና በፊት በነበሩ የዛር እምነት፣ በመንፈስ መያዝና ነፃ መውጣት እና በመሳሰሉ እምነቶች ያምናሉ፡፡ አስማት፣ ባህላዊ የእጽዋት ሕክምናና የመሳሰሉ ሀገር በቀል እውቀች ካለፈው ትውልድ ተወርሰው ይተገበራሉ (Abebe, “The Argobba of Ethiopia are not the languages they speak” 13)፡፡

### 4.7. ኢኮኖሚ

የአርጎባ ብሄረሰብ ዋና ዋና መተዳደሪያዎች ግብርና፣ ንግድ፣ የጥበበ ዕድ ስራና የሀይማኖት ትምህርት ማስተማር ናቸው፡፡ በብሄረሰቡ ዘንድ አብዛኛውን ጊዜ አንድ ሰው ከፊል አርብቶ አደር፣ የጥበበ ዕድ ባለሙያና ነጋዴም ነው፡፡

**ግብርና፣**

ከአርጎባ ልዩ ወረዳ የህዝብ ቁጥር 96.2% የሚሆነው ህዝብ በገጠር የሚኖር ሲሆን በጥምር ግብርና ይተዳደራል፡፡ በመሆኑም የብሄረሰቡ አባላት ተራራማ የሆነውን መልክዓ ምድራቸውን በእርከን በማስተካከልና የእርሻ ስራ በማከናወን እንደ ማሽላ፣ ጤፍ፣ በቆሎ፣ ቦሎቄ፣ ማሾ፣ ኑግ፣ ሱፍና ሰሊጥ የመሳሰሉ እህሎችን ያመርታሉ (Stitz 189)፡፡ ከእነዚህ ውስጥም ማሽላና ጤፍ በስፋት በመመረት ቀዳሚ ናቸው፡፡ የብሄረሰቡ አባላት ከቤት ፍጆታ የተረፈን ማሽላ፣ ጤፍ፣ በቆሎና ቦሎቄ ለገበያ የሚያቀርቡ ሲሆን በዋናነት ግን ማሾ፣ ኑግና ሰሊጥን ለገበያ ያቀርባሉ፡፡ ከእርሻ ስራ በተጓዳኝ ብሄረሰቡ በትንሹም ቢሆን የከብት እርባታ ያከናውናል ("የአርጎባ ልዩ ወረዳ ገጽታ" 21)፡፡

**ንግድ፣**

ብሄረሰቡ የግብርናና የጥበበ ዕድ ውጤቶቹን ለገበያ የሚያቀርብ ሲሆን ከሌላ አካባቢ የሚመጡትን ለቤት ውስጥ ፍጆታ የሚሆኑ ጥራጥሬ፣ ጨውና ዘይት ይገዛል (Abebe, "The Argobba of Ethiopia are not the languages they speak" 9)፡፡

የአርጎባ ብሄረሰብ አባላት ቀደም ባለው ጊዜ ጠንካራ የንግድ ስራ ተሳትፎ የነበራቸው ቢሆንም የአዲስ አበባ-ጅቡቲ የባቡር መስመር መዘርጋትና የንግድ ማዕከሎች ከአርጎባ ምድር ወደ ሌላ አካባቢ መዛወራቸው አርጎባዎች በንግዱ ስራ የነበራቸውን ተሳትፎ አሳጥቷቸዋል (Abebe, "The dynamics of Ethnicity in a plural polity" 60-61)፡፡

**ጥበበ እድ፣**

የብሄረሰቡ አባላት የባህል አልባሳትን፣ ጫማና ጌጣጌጦችን እና የሽመናና የእርሻ መሳሪያዎችን በማበጀትና ለገበያ በማቅረብም ይተዳደራሉ (Tesfaye 113)፡፡ በመስክ ምልከታ ወቅት የባህል አልባሳትን እየሰሩ ለገበያ በማቅረብ የሚተዳደሩ የብሄረሰቡ አባላት መኖራቸውን ለመመልከት ተችሏል፡፡

**ሀይማኖታዊ ትምህርት፣**

ሌላው የሀይማኖት ትምህርትን የሚያስተምሩ፣ ቁርዓን የሚያቀሩ ሰዎች የሚተዳደሩበት ነው፡፡ እነዚህ የሀይማኖት ትምህርት የሚያስተምሩ ሰዎች ደመወዝ በገንዘብ

አይከፈላቸውም፤ የአካባቢው ሰዎች የእርሻ መሬት ይሰጧቸውና በየተራ ያርሱላቸዋል፤ አረሙንም የሀይማኖት ተማሪዎቹ ያርሙታል፡፡ የሀይማኖት አስተማሪዎቹ በዚህ መልኩ የሚተዳደሩ ሲሆን አንድ መምህር ወደ ሌላ ቦታ በሚሄድ ጊዜ ግን መሬቱ እርሱን ተክቶ ለሚመጣው የሀይማኖት አስተማሪ ይሆናል ወይም በተመሳሳይ መልኩ እንዲጠቀምበት ይሰጠዋል፡፡

## 4.8. አመጋገብ

በአርጐባዎች ዘንድ ተዘውትሮ የሚዘጋጅ የምግብ አይነት ከማሽላና ጤፍ ወይም ከዘንጋዳና ጤፍ የሚዘጋጅ እንጀራና የምስር ወጥ ነው፡፡ በተጨማሪም በብሄረሰቡ ዘንድ ስንዴ፣ ገብስ፣ አጃ፣ አተርና ባቄላ ምግብ ለማዘጋጀነት ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ ከዶሮና ከከብት ስጋ የሚዘጋጁ ምግቦች በተለያዩ ስነ ስርዓቶች ጊዜ ይዘጋጃሉ (Abebe, “Food Familiarity and Novelty in a Condition of Socio-economic Transformation in North-Central Ethiopia” 453-455)፡፡

## 4.9. ባህላዊ ስነ ህንፃ

አርጐባዎች ለየት ያለ ባህላዊ ስነ ህንፃ አላቸው፡፡ የብሄረሰቡ አባላት የመኖሪያ ቤቶቻቸውን ግድግዳዎች በተጠረቡ ድንጋዮች፣ ጣሪያዎቻቸውን ደግሞ በእንጨት፣ በጠጠርና በአፈር፤ በአራት ማዕዘን ቅርጽ ያንፃሉ፡፡ አብዛኛዎቹ የብሄረሰቡ አባላት የባህላዊ ስነ ህንፃ እውቀት ያላቸው ሲሆን ቤቶቻቸውን የሚገነቡት በጋራ በመሆን ነው (Aklilu 181)፡፡



ፎቶግራፍ 3. ባህላዊ የቤት አሰራር

# ምዕራፍ አምስት

## የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ ስነ ስርዓት

ይህ ምዕራፍ የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ ስነ ስርዓት መረጃ የተተነተነበት ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ምዕራፍ በዋናነት የብሄረሰቡ የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ፣ የክዋኔው መዋቅር፣ ትዕምርት፣ ፋይዳና ለውጥና ቀጣይነት ቀርበዋል፡፡

### 5.1. የልጅ መውለድ እሳቤ በአርጐባ

በአርጐባዎች ዘንድ ልጅ መውለድ ትልቅ ዋጋ ይሰጠዋል፡፡ በብሄረሰቡ ዘንድ የወለደ ሰው በልጆቹ ይረዳል፣ ያርፋል፣ ይጦራል፣ ቢሞትም ስሙ ይጠራል፣ ይታወሳል፣ ይሶደቅለታል፤ በአንፃሩ ልጅ ያልወለደ ሰው ሲኖር ደስታና ጧሪ፣ ሲሞትም አስታዋሽ ያጣል ተብሎ ስለሚታሰብ ለልጅ መውለድ ትልቅ ዋጋ ይሰጣል፡፡ ልጅ መውለድ በተለያየ መልኩ ጥቅም ያለው መሆኑን ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም (11/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) እና ወ/ሮ ፏቢራ ኡመር (25/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) በቅደም ተከተል በሚከተለው መልኩ ገልፀዋል፡፡

> መውለድማ ደስታ ነው፡፡ ልጅ መውለድ ዘመድ ማፍራት ነው፡፡ መውለድ ጥቅም ያለው አትጐሳቆልም [ወላድ]፣ ልጅ አላት፣ በልጆቿ ትደሰታለች፣ ስታረግዝ ስትወልድ ብዙ ጥቅም አላት፡፡ ያቺ መሀኗ ምን አላት? ብቸኛ ነች፣ ከብቸኛነት ጋር ትበሳጫለች፣ አንድ ነች፣ ልፋቷም በሷ ይብሳል፣ ትለፋለች፡፡ ያው አንድ ነች፣ እሷዉ የሞተች ጊዜ በቃ ቀረ፣ ስሟም አይነሳ እንዲሁ ቀረች፣ ነበረች ሞተች በቃ! ልጅ ቢኖር በልጆች ዘርም ይቀጥላል፡፡ አማች ታገኛለች፣ ቤተሰብ ይዳብራል፣ ብዙ ቤተሰብ ታገኛለች፣ ወንድ ልጅ ይኖራል ምራት ያመጣል፣ ሴት ልጆቿ አግብተው ቢሄዱባት ደግሞ በምራቶቿ ታጅባ ትኖራለች፣ ትደሰታለች፣ ደስታዋ የዘላለም ይሆናል፡፡ ይቺ መሀኗ ስትጠፋ ጠፋች፣ ለመሀን ምን ቅጥ አለው? መውለድ መቼም በጣም ነው የሚጠቅመው፡፡
>
> እንዴ እናቴ! መውለድማ ጥሩ ነው፡፡ ያሸታል፣ ያሳምራል፡፡ በምን ያሳምራል ብለሽ ብትጠይቂኝ በእንክብካቤ እቀመጣለሁ፣ ፀሐይ እንዳያቃጥለኝ እሆናለሁ፣ ስወልድ

በደንብ እታረሳለሁ፣ አጥሚት ይደረግልኛል፣ ተልባ ይመታልኛል፣ ገንፎ ይገነፋልኛል፣ በፈሰሰው ደሜ እተካበታለሁ፡፡ … ዘመድ ታገኛለሽ፣ ሴት ልጅ ትወልጃለሽ፣ ጋብቻሽ ይረባል፣ ከጋብቻ ጋር ትደምቂያለሽ፣ ወንድ ልጅ ትወልጃለሽ፣ ወንድ ልጅ ደግሞ ጋብቻ ያመጣልሻል፣ በጋብቾችሽ ትከበሪያለሽ፣ መውለድ ያስከብራል፡፡

የአርጐባ ብሄረሰብ የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ እንደመሆኑ መጠን ልጅ መውለድ ከሀይማኖቱ አስተምህሮ አንፃር የሚሰጠውን ዋጋ በተመለከተ ሼህ ጧሂር ኑሬ (21/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) የሚከተለውን ብለዋል፡፡

ኒካህ የሚታሰረው ዘርን ለማብዛት ነው፡፡ መዋለድ አለብን፣ ዘራችንን ማብዛት አለብን፡፡ ሴት አግብታ በሰላም የምትወልድ ከሆነች ዘርን ማብዛት ነው የሚፈለገው፡፡ በእስልምናም ከቁርዓን አኳያ መውለድ ትልቅ ቦታ አለው፡፡ ምክንያቱም ቁርዓን የሚነበበው፣ ኢስላምም የሚስፋፋው ሰው በመወለዱና በመብዛቱ ነው፡፡ ነቢዩ ሙሀመድም ብዙ ሁኑ እኔ የኡመቴን መብዛት እፈልጋለሁ ብለዋል፡፡

ልጅ መውለድ ከሚሰጠው ዋጋ አንፃር የልጅ መኖር በአብዛኛው ፍቺን ያስቀራል፡፡ በባልና ሚስት መካከል ግጭት ቢፈጠር እንኳን ለልጆች ሲባል በተለይ ችግሩን ለመፍታት ጥረት ይደረጋል፡፡ ሽምጋዮች ልጆቻችሁን አንድ ላይ ሆናችሁ አሳድጉ ብለው ይሸመግላሉ፡፡ የተወለዱ ልጆች ብቻ ሳይሆኑ በሆድ ያለ ጽንስ እንኳን ለትዳር መጠናከር አስተዋጽኦ አለው፡፡ ሚስት ነፍሰጡር ሆና በእርሷና በባለቤቷ መካከል አለመግባባት ቢፈጠር ሽማግሌ “የፊቷ ወደ ጀርባዋ እስኪዞር ታገሱ” ብሎ ይሸመግላል፡፡ የፊቷ ወደ ጀርባዋ እስኪዞር ማለት ነፍሰጡሯ ወልዳ ልጇን በጀርባዋ ማዘል እስክትችል ድረስ ማለት ነው፡፡ ነፍሰጡሯ ወልዳ ልጇን በጀርባዋ እስክታዝል ድረስ ደግሞ በእርሷና በባለቤቷ መካከል ተከስቶ ፍቺን ያሳሰባቸው ጉዳይ መፍትሄ አግኝቶ ሰላም ሊወርድ ይችላል፡፡ በአንፃሩ ወ/ሮ አሚና ኢብራሂምና አቶ መሐመድ አቡበከር (30/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቡድን ተኮር ውይይት) ልጅ ባለመገኘቱ ምክንያት ለፍቺ የተዳረጉ በርካታ ትዳሮችን እንደሚያውቁ ገልፀዋል፡፡

አርጐባዎች ለልጅ መውለድ ትልቅ ቦታ የሚሰጡ መሆናቸውን የሚገልፁባቸው በርካታ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ያሏቸው ሲሆን የሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች በማሳያነት ቀርበዋል፡፡

- ብዙ ከሚወድ ተጨንቆ መውለድ (ወ/ሮ ሷቢራ ኡመር፣ 27/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቡድን ተኮር ውይይት)፡፡
- የማግባት ትርፉ ልጅ መውለድ ነው (ወ/ሮ ሷቢራ ኡመር፣ 27/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቡድን ተኮር ውይይት)፡፡
- ልጅ ያለው ሰው አስታዋሽ አያጣም (ወ/ሮ ሶህሊየት ኑሬ፣ 27/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቡድን ተኮር ውይይት)፡፡
- ልጅ ያላት ሴት ለአዳሯ ታስባለች (ወ/ሮ ሲቲ ፋጡማ መሐመድ፣ 30/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቡድን ተኮር ውይይት)፡፡
- ያላረባ አያርድም፣ ያልወለደ አያዝዝም (አቶ ፋንታዬ መሐመድ ኑር፣ 15/7/2013፣ ጉዜ ቀበሌ፣ ቡድን ተኮር ውይይት)፡፡

የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ምሳሌያዊ አነጋገሮች በቅደም ተከተል የብዙ ሰዎችን ፍቅር ከማግኘት በላይ መውለድ እንደሚበልጥና ጋብቻ የመመስረት እንኳን ዋና ጥቅም ልጅ ማግኘት መሆኑን በመግለጽ በብሄረሰቡ ዘንድ ልጅ መውለድ የሚሰጠውን ዋጋ የሚገልፁ ናቸው፡፡ ሶስተኛው፣ አራተኛውና አምስተኛው ምሳሌያዊ አነጋገሮች ልጅ መውለድ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ በመግለጽ ማህበረሰቡ ለልጅ መውለድ ያለውን ከፍ ያለ ቦታ ይገልፃሉ፡፡ ሶስተኛው ምሳሌያዊ አነጋገር ልጅ የወለደ ሰው በቁሙ ጧሪን፣ ሲሞትም ሶዳቂ የሚያገኝ መሆኑን፣ አራተኛው ልጅ መውለድ ስለ ኑሮ ማሰብን፣ መርጋትን የሚያስገኝ መሆኑን እና አምስተኛው ምሳሌያዊ አነጋገር የወለደ ሰው አጋዥ የሚያገኝ መሆኑን፣ ነገር ግን ልጅ የሌለው ሰው በተቃራኒው ያልወለደ ሰው ታዛዥና አጋዥ ማግኘት የሚቸግረው መሆኑን በመግለጽ የመውለድን ጥቅም ይገልፃል፡፡

### 5.2. የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ ስነ ስርዓት፤ ክዋኔው፣ መዋቅሩና ትዕምርቱ

በዚህ ክፍል የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ Gennep የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች ያልፉባቸዋል ካሏቸው የመለየት፣ የሽግግርና የመቀላቀል ደረጃዎች አንፃር እና በክዋኔው ውስጥ ያሉ ትዕምርታዊ ጉዳዮችና ፍካሬዎቻቸው ቀርበዋል፡፡

### 5.2.1. መለየት

በአርጐባዎች የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ የመለየት ደረጃ አንዲት ሴት ነፍሰጡር መሆኗን እርሷና በዙሪያዋ ያሉ ሌሎች ሰዎች ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ የመጀመሪያ የሆነው የቅምሻ ስነ ስርዓት እስከሚከወንበት ድረስ ያለውን ጊዜ ይይዛል፡፡ የነፍሰጡርነት መታወቅ የመለየት መጀመሪያ ወይም መግቢያ ሲሆን የቅምሻ ስነ ስርዓት መጠናቀቅ ለመለየት ጊዜ ማለቂያና ለሽግግር ጊዜ መቀበያ ነው፡፡ ይህ ጊዜ ነፍሰጡር በነፍሰጡርነቷ ምክንያት ከቤተሰቧ አባላት፣ ከፆታ አቻዎቿና ከማህበረሰቡ የምትለይበት ሲሆን ዋነኛ መገለጫው የቅምሻ ስነ ስርዓት ክዋኔ ነው፡፡

አንዲት ሴት ማርገዟን የምታውቅባቸው ዋና ዋና ምልክቶች የወር አበባ መቅረት፣ የማቅለሽለሽና የድካም ስሜት መኖር እና የምግብ ፍላጐት መቀነስ ናቸው፡፡ በአርጐባዎች ዘንድ እርግዝናን ይፋ ማድረግ ነውር ተደርጐ የሚታሰብ በመሆኑ ማርገዟን ያወቀች ሴት ወዲያውኑ አርግዣለሁ ብላ ለሰው አትነግርም፤ ምስጢር አድርጋ ትቆይና ቤተሰቦቿና ጐረቤቶቿ ነፍሰጡር መሆኗን የሚያውቁት እንደ ማቅለሽለሽና የድካም ስሜት የመሰሉ የእርግዝና ምልክቶችን ሲያዩባት ነው፡፡ ነፍሰጡር መሆኗን የጠረጠሩ ጐረቤቶች ያምራታል በማለት ምግብ ሰርተው፣ ይሸታታል በማለት ከሰሩት ቀንሰው ይወስዱላታል፡፡ ነፍሰጡሯ ምግብ ሲመጣላት "ምን ብላችሁ አመጣችሁ?" ብላ ትግደረደራለች እንጂ በይፋ ማርገዟን አትናገርም፤ እነርሱም "ቅመሺ ብቻ" ይሏታል እንጂ ነፍሰጡር ስለሆንሽ ነው አይሏትም (ወ/ሮ ሲቲ ፋጡማ መሐመድ፣ 7/2/2013፣ ጋቺኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

እርግዝናን ምስጢር በማድረጉ ልማድ ምክንያት የነፍሰጡሯ ቤተሰብ አባላት ልጃቸው ነፍሰጡር መሆኗን የሚያውቁት የእርግዝና ምልክቶችን ሲያዩባት ወይም የነፍሰጡሯ ጐረቤቶች ጥርጣሬያቸውን ሲነግሯቸው ነው፡፡ የነፍሰጡሯ እናት ወይም ሌላ የቤተሰቡ ሴት አባል ይህንን ሲሰሙ ሁኔታውን ለማረጋገጥና ከልጃቸው ጋር ለመወያየት ወደ ነፍሰጡሯ ቤት ይሄዳሉ፡፡ የሚሄዱትም ነፍሰጡሯ የምትቀምሰውን ምግብ ይዘው ሲሆን ስነ ስርዓቱ ቅምሻ ይባላል (ወ/ሮ ሲቲ ፋጡማ መሐመድ፣ 7/2/2013፣ ጋቺኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

## የቅምሻ ስነ ስርዓት

የቅምሻ ስነ ስርዓት ልጃቸው ነፍሰጡር መሆኗን የጠረጠሩ የነፍሰጡሯ እናትና አባት፣ እነርሱ በህይወት ከሌሉ ደግሞ ሌላ አንጋፋ የቤተሰቡ አባላት አነባበሮና በዶሮ ወጥ የተጠቀሰ አሊጣጦ ይዘው በመሄድ ልጃቸውን የሚያቀምሱበትና የሚወያዩበት ስነ ስርዓት ነው፡፡ በመሆኑም የነፍሰጡሯ ቤተሰብ አባላት ለመሄድ ባሰቡበት ቀን ማታ ያዘጋጁትን ምግብ ይዘው ወደ ልጃቸው ቤት ይሄዳሉ፡፡ እዚያ ከደረሱ በኋላ የነፍሰጡሯ እናት ወይም ሌላ የመጣች የቤተሰቡ አባል እርግዝናዋን በተመለከተ ከነፍሰጡሯ ጋር ይወያያሉ፣ ስንት ወር እንደሆናትና አምሮት[9] መቼ መደረግ እንዳለበትም ይነጋገራሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ይዘው ከሄዱት ምግብ ያቀምሷታል፣ አነባበሮውም ተቆርሶ ቅመሱ እየተባለ ለቅርብ ጐረቤቶች ይታደላል፡፡ የነፍሰጡሯ ቤተሰብ አባላት ቤት ባፈራው ይስተናገዱና አድረው ጠዋት ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 12/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የመለየት ጊዜ ነፍሰጡሯ ነፍሰጡር በመሆኗ ምክንያት ከማህበረሰቡ፣ ከቤተሰቧና የፆታ አቻዎቿ በስነልቡና የምትለይበት ነው፡፡ ነፍሰጡሯ ነፍሰጡርነቷን በምስጢር በመያዝ ብትቆይም በተለያዩ ምክንያቶች ነፍሰጡርነቷ ሲገለጥ ከነበረችበት ቡድን ተለይታ ትታያለች፡፡ የዚህ ደረጃ ዋና መገለጫ የቅምሻ ስነ ስርዓት ክዋኔ ነው፡፡

### 5.2.2. ሽግግር

በአርጐባ የወሊድ ስነ ስርዓት የሽግግር ጊዜ በዋናነት የእርግዝናን፣ የወሊድን እና የአራስነት ጊዜን በሙሉ ያጠቃልላል፡፡ በመሆኑም ይህ ጊዜ ከቅምሻ ስነ ስርዓት ክዋኔ ጀምሮ እስከ አርባ ቀን እጥበት ዋዜማ ድረስ ያለውን ጊዜ ይይዛል፡፡ የቅምሻ ስነ ስርዓት የመለየት ጊዜ ማብቂያና የሽግግር ጊዜ መግቢያ ሲሆን የአርባኛ ቀን ዋዜማ ደግሞ የሽግግር ደረጃ ማጠናቀቂያ ወይም መደምደሚያ ሆኖ በአርባኛ ቀን የመንፃት ስነ ስርዓት የሚጀምረውን የመቀላቀል ደረጃ የሚቀበል ነው፡፡

ይህ ጊዜ ዋና የሽግግር መገለጫ በሆነው በእርግዝና ወቅት የሚከወኑ ስነ ስርዓቶችን የሚይዝ ሲሆን በአርጐባ ለነፍሰጡር የሚደረግ እንክብካቤ፣ ለነፍሰጡር የሚከለከሉ ነገሮች፣ ለነፍሰጡር የሚሰጥ ምክር፣ የአምሮት ስነ ስርዓት ክዋኔ፣ ለወሊድ የሚደረግ ዝግጅት

[9] ለነፍሰጡር የሚከወን ስነ ስርዓት ሲሆን ምንነቱ በሰፊው ወደ ፊት የሚቀርብ ነው፡፡

መገለጫዎቹ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ከእርግዝና በኋላ ያሉ የወሊድ፣ የላንቃ ማንሳት፣ የደም ዶሮ እርድና የልጅ ጓሮ ቀበራ ስነ ስርዓቶች፣ የአራስ እንክብካቤና ጥየቃ እና የሰባት ቀን እጥበት ስነ ስርዓት የሚከወኑበት ነው፡፡

### 5.2.2.1. ለነፍሰጡር የሚደረግ እንክብካቤ

አንዲት ሴት ነፍሰጡር መሆኗ በዚህ ሁኔታ ከታወቀ በኋላ ሴት የቤተሰቧ አባላት፣ በስጋና በጋብቻ በሚዛመዷት ሴቶች እና ጐረቤቶቿ እንክብካቤ የሚደረግላት ሲሆን እንክብካቤው አንዲት ሴት ነፍሰጡር በሆነችባቸው ተደጋጋሚ ጊዜዎች ሁሉ የሚደረግ ነው፡፡ አንደኛው አይነት እንክብካቤ ነፍሰጡሯ ያማራትንና ያምራት ይሆናል ተብሎ የሚታሰብን ምግብ በማዘጋጀትና በመውሰድ እንድትመገብ ማድረግ ሲሆን ነፍሰጡሯን በስራ በማገዝ የሚደረግ የጉልበት እገዛ ሌላው እንክብካቤ ነው፡፡

የነፍሰጡሯ ቤተሰብ፣ ሴት ዘመዶቿና ጐረቤቶቿ ያምራታል በማለት እንደ አቅማቸው ለነፍሰጡር የሚሰራ ምግብ ሰርተው ይዘው በመሄድ ነፍሰጡሯን ይጠይቋታል፡፡ ነፍሰጡር ያምራታል ተብሎ ከሚዘጋጁ ምግቦች ውስጥ ጨጓራና ጉበት፣ ጭብጦና አሊጣጦ ዋናዎቹ ናቸው፡፡ የፍየል ወይም የከብት ጨጓራና ጉበት ነፍሰጡር ያምራታል ተብሎ የሚታሰብ ዋና ምግብ ሲሆን ተከትፎና በበርበሬ ታሽቶ ወይም እንዲሁ በእንጀራ ተሸፍኖ ለነፍሰጡር ይወሰዳል፡፡ ጭብጦው በሰሊጥ የሚጨበጥ ሲሆን አሊጣጦው በዶሮ መረቅ እየተነከረ ከዶሮ ስጋና እንቁላል ጋር ይቀርባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ነፍሰጡር ቤቷ ጥሩ ምግብ ቢኖርም የሰው ቤት ምግብ ይሸታታል፤ ትጓጓለች በሚል ምክንያት የነፍሰጡሯ ጐረቤቶች እንጀራ ቢጋግሩ ትኩሱን አጥፈው፣ በርበሬ ቢያስፈጩና ወጥ ቢሰሩ ቀንሰው ይወስዱላታል (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 13/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የነፍሰጡሯ ጐረቤቶች ነፍሰጡሯን በምግብ ከመንከባከብ በተጨማሪ ነፍሰጡርን ለህመም ይዳርጋሉ ተብለው የሚታሰቡና የጉልበት የሆኑ ስራዎችን በመስራት በጉልበትም ያግዟታል፡፡ ነፍሰጡሯ በተለይ ሆዷ ከገፋ በኋላ እንጀራ መጋገር፣ በርበሬ ማስፈጨት፣ ልብስ ማጠብና የመሳሰሉ ስራዎችን ይሰሩላታል፡፡ የቤተሰብ የጉልበት እገዛ የሚደረግላት በአብዛኛው ከወሊድ በኋላ ነው (ወ/ሮ እመይ መሐመድ ነጋሽ፣ 19/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ለነፍሰጡር የሚደረግ እንክብካቤ ነፍሰጡሯ ተጋላጭ ነች ተብሎ ከሚታሰቡ በሽታዎች እንድትጠበቅ ማድረግም ሲሆን ትጋለጥባቸዋለች ተብለው ከሚታሰቡ ህመሞች መካከል አንዱ የሰው ዓይን ህመም ነው፡፡ በአርጐባዎች እምነት መሰረት የሰው ዓይን በተወሰኑ ሰዎች ላይ የሚገኝና አንድን ሰው፣ እንስሳ ወይም ቁስ አይተው ከወደዱት እይታቸው የወደዱትን ነገር የሚጐዳ፤ ነፍስ ያለውም ነገር ከሆነ ለህመም የሚዳርግ የጤና ችግር ነው፡፡ የሰው ዓይን ህመም ያለባቸው ሰዎች የሚያሳዩት የህመሙ ምልክት መንጠራራት፣ ከወትሮው የተለየ መልዕክት የሌለው ነገር መለፍለፍ፣ መጮህ፣ ማልቀስ፣ መንጠራራት፣ ጥርስ ማፋጨት፣ ወዘተ ናቸው፡፡ የሰው ዓይን አብዝቶ የሚያጠቃቸው ወይም በቀላሉ በሰው ዓይን የሚታመሙ ሰዎች መልበስና መዋብ የሚወዱ ሰዎች፣ ሙሽራ፣ አራስ፣ ነፍሰጡርና ህፃናት ናቸው (ወ/ሮ ከድጃሺ ከማል 19/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የሰው ዓይን ህመም በነፍሰጡር ላይ ይበረታል፡፡ ነፍሰጡር በሰው ዓይን ከታመመች እርሷም ሆነች በማህፀኗ ያለው ጽንስ ጉዳት ላይ ይወድቃሉ፤ የጽንስ መጨናገፍ ሊከሰት ይችላል፤ በወሊድ ጊዜ ምጥ ይበረታል ተብሎ ይታመናል፡፡  በዚህም ምክንያት በመንገድ ላይ ነፍሰጡር ብታጋጥም በሙሉ ዓይን አትታይም፣ አይን ሰበር ተደርጐ ወደ መሬት እየታየ ሰላምታ ይሰጣታል፡፡ ሆዷ የገፋ ነፍሰጡር ስታጋጥም "እንትፍ እንትፍ" ይባላል (ወ/ሮ ከድጃሺ ከማል፣ 19/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ልብስ የሰው ዓይን መከላከያ ነው ተብሎ የሚታመን በመሆኑ ነፍሰጡር ሆዷ ገፍቶ እንዳይታይ በተቻለ መጠን መሸፈንና በጣም ሰፊ ልብስ መልበስ እንዳለባት ይታመናል፡፡ በተጨማሪም ነፍሰጡር የምትለብሰው ልብስ ውበቷን የሚያጐላና የሚያደምቃት ከሆነ በቀላሉ ለሰው ዓይን ትጋለጣለች ተብሎ ስለሚታሰብ ውበቷን የሚደብቅ ልብስ እንድትለብስ ትመከራለች፡፡ ነፍሰጡር ሆዷ ሲገፋ ከቤት ደጅ ስትንቀሳቀስ ለበሽታ የሚዳርግ እርኩስ መንፈስ እንዳያያት ተብሎ ቤቱ አጥር ከሌለው ዙሪያውን አጥር ይታጠራል፤ አጥር ካለውም በክትክታ[10] ሽምጥ እየተጠቀጠቀ ይታደሳል፡፡ በተጨማሪም ነፍሰጡር የሰው ዓይን መከላከያ እንዲሆናት እውቀቱ ባለው ሰው ጽህፈት ተጽፎ በአንገቷ ወይም በክንዷ ላይ ታስራለች፤ ከብር በተሰራ የአንገት ሀብል ላይ ተደግሞ ያንን ታደርጋለች (ወ/ሮ አይከዲጅ መሐመድ፣ 29/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ይህ የህመም መከላከያ መንገድ ሀገር በቀል እውቀት ሲሆን መንፈሳዊ የሆነ

[10] በአካባቢው ተዘውትሮ ለአጥር ስራ የሚውል የዛፍ አይነት ነው፡፡

መፍትሄ የቀረበበት ነው፡፡ ሀገር በቀል እውቀት በከዋኙ ማህበረሰብ ዘንድ ከሌላ አካባቢ ከሚመጣው ዘመናዊ መፍትሄ በተሻለ ተቀባይነት ያለው በመሆኑ በማህበረሰቡ ተመራጭ ነው፡፡

አንዲት ነፍሰጡር ከነፍሰጡርነቷ በፊትም ሆነ በነፍሰጡርነቷ ጊዜ ለሰው ዓይን ህመም ከተጋለጠች ህመሙ የከፋ ጉዳት እንዳያደርስ፣ እንዳይብስ ወይም እንዲጠፋ የሚያደርግ ህክምና እንድታገኝ ይደረጋል፡፡ ወ/ሮ ሷቢራ ኡመር (25/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) እንደገለፁት አንድ ሰው በሰው ዓይን ከተያዘ በኋላ እንዲታመም ያደረገው ሰው ባስታወሰው ቁጥር ህመም ይከሰትበታል ተብሎ የሚታመን በመሆኑ የሰው ዓይን ያለባት ነፍሰጡር ነጭ ዶሮ በሰውነቷ ላይ ደበስበስ አድርጋ ዶሮው ቤት ውስጥ ቢለቀቅ ለህመም የዳረጋት ሰው ቢያስባት እንኳን ሀሳቡ ወደ ዶሮው ስለሚሆን ነፍሰጡሯ በየጊዜው አትታመምም፤ ዶሮው በእርሷ ፈንታ ሊታመም ወይም ሊሞት ይችላል፤ ይህ ሲሆን ደግሞ በነፍሰጡሯ ላይ ይደርስ የነበረው ጉዳት በዶሮው ላይ ሆነ ተብሎ ይታመናል፡፡

በብሄረሰቡ ግንዛቤ መሰረት ውርጃ ከሚከሰትባቸው ምክንያቶች መካከል አንዱ ከቤተሰብ የተወረሰ፣ ግብር የለመደ ተመላኪ መኖርና የለመደው ግብር መቅረት ነው፡፡ አቶ መሐመድ አቡበከር (3/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) እንደገለፁት በዚህ ምክንያት አንዲት ሴት ተደጋጋሚ ውርጃ ሊከሰትባት ይችላል፡፡ ለዚህ አይነቱ ችግር መፍትሄ የሚሆን ነፍሰጡሯ በወገቧ ወይም በአንገቷ ላይ የምታስረው ጽህፈት ይሰራላታል፡፡ ሌላው የውርጃ መንስዔ የሰው ዓይን ነው፡፡ ይህን ችግር ለማስወገድ ቁርዓን ይቀራል፣ ጽህፈት ተዘጋጅቶ ነፍሰጡሯ ታስረዋለች፡፡ በዚህ ሁኔታ ነፍሰጡሯ አንድ ጊዜ ከህመሟ ከዳነች በኋላ ህመሙ እንዳይመለስ ህሙ የሚባል እንጨት ወይም የሽኮኮ ጐመን ቅጠል ጭስ እንድትታጠን ትደረጋለች፡፡ የባህል መድሀኒት እውቀት ያላቸው አቶ መሐመድ አቡበከር እንደገለፁት በሰው ዓይን የታመመችን ነፍሰጡር ከህመሟ ድና ነፃ ከሆነች በኋላ ህመሙ እንዳይመለስ ብቻ የሚጨስ መድኃኒት መጠቀም ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም፡፡ ነገር ግን ነፍሰጡሯን በሚጨስ መድኃኒት ለማዳን መሞከር ብዙ ጊዜ አስቸጋሪ ነው፤ በዚህ መልክ ነፍሰጡርን ለማዳን ሲሞከር ሊያንቃት ወይም ሊፈጠፍጣት ስለሚችል መጀመሪያ ወልዳ ነፃ ብትሆን ይመረጣል፡፡

### 5.2.2.2. ለነፍሰጡር የሚከለከሉ ነገሮች

የመውለጃ ጊዜዋ የቀረበ ነፍሰጡር በምግብና በድርጊት ክልክሎች አሉባት፡፡ ምግብን በተመለከተ ጥራጥሬ፣ አሬራ፣ ማር፣ ሽንኮራ፣ ፓፓዬ፣ ቃሪያና የሎሚ ጭማቂ ምግቧ ውስጥ እንዳይኖር ትከለከላለች፡፡ አሬራ መጠጣት ጽንሱ ጭንቅላት ላይ ቆሻሻ ሆኖ ይጋገራል፣ ማር መብላት ለጽንሱ ትንታ ያመጣበታል፣ ሽንኮራ መብላት ምጥ ያጠናል፣ ፓፓዬ መመገብ ጽንሱን እንዲፋፋ ስለሚያደርግ በወሊድ ጊዜ ምጥ ያጠናባታል፣ ቃሪያ ሲመገቡት እንደሚፋጅ ሁሉ ጽንሱም ላይ መፋጀት ያስከትላል፣ የሎሚ ጭማቂ ምጥ ያለጊዜው እንዲመጣ ያደርጋል (ወ/ሮ ሷቢራ ኡመር፣ 25/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) የሚሉ ምክንያቶች የክልከላዎቹ መነሻዎች ናቸው፡፡

ነፍሰጡር በጽንሱ አንገት ላይ እትብት ይጠመጠማል በሚል ምክንያት በመኝታ ጊዜ በጀርባዋ እንዳትተኛና ለመዞር ስትፈልግ ተነስታ መዞር ወደምትፈልግበት አቅጣጫ መዞር እንጂ እንደተኛች እንዳትዞር፣ ጽንሱ ቦታውን እንዲስት ያደርጋል በሚል ምክንያት ስትራመድ ፈጠን ፈጠን እንዳትል፣ በጽንሱ ላይ ጉዳት ያደርሳል በሚል ምክንያት በጣጣቴ[11] እንዳትታከም፣ የሽሉ አቅጣጫ ባልተገባ ሁኔታ እንዲሆንና ወደ ጐን እንዲሰነቀር ያደርጋል ይህ ደግሞ ነፍሰጡሯን አቅም ያሳጣታል ሽንትም ይከለክላታል በሚል ምክንያት እንዳትጠማዘዝና እግሮቿን አጣጥፋ ዝቅ ባለ መቀመጫ ላይ እንዳትቀመጥ፣ ጽንሱ ቦታውን እንዲስት ያደርጋል በሚል ምክንያት ብዙና እንደ ልብስ ማጠብ፣ ከድብኝት እቃ ማውጣት፣ ከጉድጓድ እህል መቀበል፣ እህል ማበጠርና መውቀጥን የመሰሉ ከባድ ስራዎችን እንዳትሰራ፣ ከባድ እቃ እንዳታነሳና እንዳትሸከም እና የወይባ ጭስ ሰውነት ያጠብቃል ተብሎ ስለሚታመን ሰውነቷ ጠብቆ ምጧ እንዳይጠና ወይባ እንዳትሞቅ ትከለከላለች (ወ/ሮ ሀይሀሊማ ሱለይማን፣ 16/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ነፍሰጡር ለበሽታ ተጋላጭ እንደሆነች ይታመናል፡፡ ከምትጋለጥባቸው ህመሞች መካከል ምችና የሰው ዓይን ህመሞች ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በመሆኑም ነፍሰጡር ምች ከሚያስመቷት ለምሳሌ ጋግራ ሳትታጠብ መውጣት፣ በፀሀይ መንቀሳቀስ፣ የተሰጣ እህል ማስጣጣት፣ በርበሬ ማስፈጨትና የመሳሰሉትን ድርጊቶች ራሷን መቆጠብ እንዳለባት ይታመናል፡፡ በአለባበስ ረገድም በተቻለ መጠን ሰፋ ሰፋ ያለና ሆዷን ሊሸፍን የሚችል ልብስ እንጂ

---

[11] ሸቦ በእሳት እየተጋለ የታመመን አካል በመተኮስ የሚከናወን ባህላዊ ህክምና ነው፡፡

ለሰው ዓይን ህመም የሚዳርጋትን ጠበብ ብሎ ሆዷን አጉልቶ የሚያሳይ ልብስ እንዳትለብስ ትከለከላለች (ወ/ሮ አይኔ ይማሙ፣ 3/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

### 5.2.2.3. ለነፍሰጡር የሚሰጥ ምክር

ነፍሰጡር በዙሪያዋ ባሉ ሰዎች ምክር ይሰጣታል፡፡ የምትመከረው ምክር በተለይ እንድታደርጋቸው የሚገቡትን እንድታደርግና ለነፍሰጡር ክልክል የሆኑ ነገሮችን ደግሞ እንዳታደርግ የሚነግሩ ናቸው፡፡ በመሆኑም እረፍት እንድታደርግ፣ በዶሮና በፍየል ስጋ የተዘጋጁ ጥሩ ጥሩ ምግቦችን እንድትመገብና ከፍ ሲል የተዘረዘሩ የምግብና የድርጊት ክልክሎችን እንድታከብር ትመከራለች፡፡ በተጨማሪም በእርግዝና ጊዜ ወላዷ ከወለደች በኋላ ለእርሷም ሆነ ለህፃኑ ልታደርግ የሚገባትን እንክብካቤ በተመለከተ ምክር ይሰጣታል፡፡ በመሆኑም ከወለደች በኋላ የእርሷንም ሆነ የህፃኑን ልብሶች በንጽህና መያዝ እንዳለባት፣ የመኝታ አካባቢዋን ንፁህ ማድረግና ጭስ ማጫጫስ እንዳለባት እንዲሁም በተቻለ መጠን ህፃኑን ማጥባት እንዳለባት ትመከራለች (ወ/ሮ አይኔ ይማሙ፣ 3/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

### 5.2.2.4. የአምሮት ስነ ስርዓት

የአምሮት ስነ ስርዓት ነፍሰጡር ሰባት ወይም ስምንት ወር ሲሆናት የሚከወን ስነ ስርዓት ሲሆን የነፍሰጡሯ ቤተሰብ የተለያዩ ምግቦችን አዘጋጅቶ በመሄድ ነፍሰጡሯን የሚጠይቅበት፣ ጐረቤት ተጠርቶ የሚጋበዝበትና ዱዓ የሚደረግበት ስነ ስርዓት ነው፡፡ የአምሮት ስነ ስርዓት የሚከወንበት ዋና ዓላማ ነፍሰጡሯ በሰላም እንድትገላገል፣ ምጧ እንዲገራ፣ ጭንቋ እንዲቀል፣ ጤነኛ ልጅ ወልዳ እንድትታቀፍ፣ መጥፎ ነገር ሁሉ ከእርሷ እንዲርቅና በአንፃሩ ጥሩ ነገር እንዲቀርባት ዱዓ እንዲደረግላት ማድረግ ነው (ወ/ሮ ሲቲ ፋጡማ መሐመድ፣ 8/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ነፍሰጡሯ ከመጥፎ ተከልላ ለጥሩ እንድትቀርብ ማድረጊያ ከሆነ ደግሞ የስነ ስርዓቱ ክዋኔ ነፍሰጡሯን የመጠበቅ ዓላማ ያለው ነው ማለት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ወ/ሮ እመይ መሐመድ ነጋሽ (19/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) እንደገለፁት ሰዎችን መመገብ ለነፍሰጡሯ በረከት ያስገኛል ተብሎ የሚታመን መሆኑ፣ ስነ ስርዓቱ የነፍሰጡሯ እናት ልጇ ልጅ ልታገኝና ዘር ልትቀጥል በመሆኑ ያገኘችውን ደስታ ማካፈያዋ መሆኑና ስነ ስርዓቱ ለነፍሰጡሯ ብቻ

ሳይሆን ለነፍሰጡሯ ቤተሰብ፣ ለሀገር፣ ለታመሙና ለተቸገሩ ሰዎች፣ ወዘተ ዱዓ የሚደረግበት መሆኑ የስነ ስርዓቱ ተጨማሪ የመከወኛ ምክንያቶች ናቸው፡፡

የአምሮት ስነ ስርዓት ሴቶች የሚያዘጋጁት በመሆኑ በዋናነት የነፍሰጡሯ እናት ኃላፊነት ነው፡፡ የነፍሰጡሯ እናት በህይወት ባትኖር እንኳን የቤተሰቡ ኃላፊነት ያለባት ሌላ ሴት፤ በቤተሰብ ውስጥ ሴት ከሌለች ደግሞ አክስት፣ የአጐት ሚስት፣ የወንድም ሚስት፣ ወዘተ ኃላፊነቱን በመውሰድ የአምሮት ስነ ስርዓቱን ዋና በመሆን ታዘጋጃለች፡፡ ስነ ስርዓቱ የሴቶች ነው ማለት ሴቶች በኃላፊነት ይከውኑታል ማለት እንጂ ወንዶች አይሳተፉበትም ማለት አይደለም፡፡ ወንዶች በምግብ ዝግጅት ላይ የማገዶ እንጨትን ፈልጦ ማቅረብን የመሰሉ የጉልበት ስራዎችን በመስራት፣ የተዘጋጀውን ምግብ ተሸክሞ ወደ ነፍሰጡሯ ቤት በመውሰድ፣ በስነ ስርዓቱ ላይ በመካፈል፣ ዱዓ በማድረግና በማስተናገድም አብረው ይሆናሉ (ወ/ሮ ሳሱየ አሊየ፣ 6/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የአምሮት ስነ ስርዓት የሚከወነው ነፍሰጡሯ ሰባት ወይም ስምንት ወር ሲሆናት የነፍሰጡሯ እናት ወይም ስነ ስርዓቱን በሀላፊነት የምታዘጋጀው ሴት በምትመረጠው ቀን ነው፡፡ እናት ወይም ሌላዋ ሴት ቀኑን ከወሰነች በኋላ በዚህ ቀን እንመጣለን በማለት ለነፍሰጡሯ ታሳውቃታለች፤ ለእህቶቿ፣ ለወንድሞቿና ለመላው ቤተሰቧ እንዲሁም ለቅርብ ጓደኞቿም በዚህ ቀን ልጄን ለማየት እሄዳለሁ ብላ ታሳውቃለች፤ ተከትለዋት የሚሄዱ ሰዎች የአቅማቸውን ያህል ጭነት እህል ያዘጋጃሉ (ወ/ሮ ሳሱየ አሊየ፣ 6/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የነፍሰጡሯ እናት ወይም ስነ ስርዓቱን የማዘጋጀት ሀላፊነት ያለባት ሌላ ሴት የአምሮት ስነ ስርዓት የሚከወንበት ቀን ሲቃረብ ለስነ ስርዓቱ ምግብ ማዘጋጃ እንዲሆን ገብስ ፈትጋና ቆልታ በማስፈጨት የገንፎ እህል ታዘጋጃለች፤ ሌሎቹ ምግቦች የሚዘጋጁት በአምሮቱ ቀን ዋዜማ በመሆኑ "በዚህ ቀን ልጄ ጋር ገንፎ ላበላ ነውና በዚህ ቀን ስራ እርዱኝ" በማለት ጐረቤቶቿን አስቀድማ ትጠራለች፡፡ በአምሮቱ ዋዜማ ስነ ስርዓቱን የማዘጋጀት ሀላፊነት ባለባት ሴት ቤት የቤተሰቡ አባላት ለስራ እገዛ ከተጠሩ ጐረቤቶች ጋር በመሆን ለአምሮት ወደ ነፍሰጡሯ ቤት የሚወሰዱ ምግቦችን ይዘጋጃሉ፡፡ ለአምሮት የሚወሰዱ ምግቦች ዳቦ፣ አነባበሮ፣ በዶሮ ወጥ የተነከረ አሊጣጦ፣ የጤፍ እንጀራ፣ ንጥር ቅቤና የተወቀጠ ሰሊጥ ሲሆኑ ነፍሰጡሯ ለአምሮቱ ለምትጠራቸው ጐረቤቶቿ መጥሪያና ማስተናገጃ ሊሆኑ በሚችሉበት መጠን ይዘጋጃሉ፡፡ የሚጋገረው ዳቦ፣ አነባበሮና እንጀራ

እያንዳንዱ ከአንድና ሁለት መሶብ አልፎ አራትና ከዚያ በላይ መሶብ ሊሆን ይችላል (ወ/ሮ ሳሱየ አሊየ፣ 6/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ የአርጐባዎች ማህበራዊ ኑሮ ጠንካራና ሰፊ በመሆኑ የሚዘጋጀው ምግብም ብዙ ይሆናል፡፡

ምግቡ ተዘጋጅቶ ካለቀ በኋላ ምግቡን ለመውሰድ የማዘጋጀት ስራ ይሰራል፡፡ በመሆኑም አሊጣጦው በተሰራው ዶሮ ተነክሮ ይዘጋጃል፡፡ የሚዘጋጀው አሊጣጦ ሶስት አይነት ነው፡፡ አንደኛው ለነፍሰጡሯና ለባለቤቷ፣ ሁለተኛው ለሌማት ከፋቾች እና ሶስተኛው ነፍሰጡሯ ለምትጠራቸው ጐረቤቶቿ የሚሆን ነው፡፡ ሌማት ከፋቾች ነፍሰጡሯ ቤተሰቧን እንዲቀበሉና ቤተሰቡ ይዞት የሚመጣውን ምግብ በተጠሪው ጐረቤት አባወራ ቁጥር ልክ አድርገው በመሸንሸን እንዲያዘጋጁላት የምትጠራቸው ጐረቤቶቿ የሆኑ አዛውንት ሴቶች ናቸው (17/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ምልከታ፤ 11/3/2013 እና 25/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡ ምግቡ የሚዘጋጀው ለሶስቱ አካላት በመሆኑ ወሳጅ የሆነው ቤተሰብ ከምግቡ አይመገብም፡፡

የአሊጣጦው አዘገጃጀትም የተሰራው ዶሮ ወጥ ስጋና እንቁላሉ በሙሉ ይወጣና በጣባ ይደረጋል፤ ከቅባቱና ከመረቁ ይቀነስና በሌላ ጣባ ይደረጋል፡፡ ከዚያ በኋላ የተጋገረው አሊጣጦ ቅባት በበዛበት የዶሮ መረቅ እየተነከረ በሌላ ጣባ ይደረግና ሲያልቅ በብዛት የዶሮው ስጋና እንቁላል ተደርጐበት ለነፍሰጡሯና ለባለቤቷ እንዲሆን ይዘጋጃል፡፡ ከዚያ በኋላ የተረፈው መረቅ ለሁለት ተከፍሎ በአሊጣጦ እየተነከረ ይዘጋጅና የተረፈ ስጋና እንቁላል ካለ ለሌማት ከፋቾች በተዘጋጀው አሊጣጦ ላይ ይደረጋል፡፡ ለጐረቤቶች የሚሄደው በዶሮው መረቅ የተነከረ አሊጣጦ ብቻ ይሆናል፡፡ አነባበሮው ቅቤና በርበሬ ተመትቶ ይለቀለቅና አይንና አይኑ እየተገጠመ በመሶብ ተደርጐ ይሸፈናል፤ ዳቦውና እንጀራው በመሶብ ተደርጐ ይሸፈናል፡፡ ምግቡ ሁሉ ተዘጋጅቶና ለጉዞ እንዲሆን ተቋጥሮ ካለቀ በኋላ ቡና ይፈላና የቡና ቁርስ ከተጋገረው አነባበሮ ይቀርባል፡፡ በስራው ላይ የተሳተፉ ሁሉ ይሰበሰቡና ዱዓ አድርገው ቡናውን ይጠጣሉ (17/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ምልከታ፤ 11/3/2013 እና 25/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡



ፎቶግራፍ 4. አሊጣጦ ስትጋግር

በመስከ ምልከታ ወቅት ለነፍሰጡሯ ለወ/ሮ ዘይነባ መሐመድ ጀማል ለሚዘጋጀው የአምሮት ስነ ስርዓት በዋዜማው በነፍሰጡሯ እናት በወ/ሮ ሀሊማ መሐመድ ሰኢድ ቤት ዝግጅቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ቡና ተፈልቶ ጀባ ሲባል በስራው ላይ ዋና ተሳታፊ በነበሩት በወ/ሮ በድሪያ መሐመድ አድራጊነትና ስራውን ሲሰሩ በነበሩና በቡናው ስነ ስርዓት ላይ ተሰብስበው በነበሩት ሴቶች ተቀባይነት ወይም አሜን ባይነት ዱዓ የተደረገ ሲሆን (16/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ) እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| <u>ዱዓ አድራጊ</u> | <u>ተቀባዮች</u> |
|---|---|
| ፈረጃሽን ቅርብ | አሜን |
| ደስታሽን ሰፊ | ” |
| አላህ ያርግልሽ | ” |
| አላህ ያክርምሽ | ” |
| ያገሩ ሼህ ከክፉም፣ ከጦስም፣ ተአፉትም፣ ተንቅፋትም | |
| ጥብቅ አላህ ያርግልሽ | ” |
| የበረካ ዛፍ አላህ ያርግሽ | ” |
| ሀረግሽም የሚሳብ አላህ ያርገው | ” |

አበባሽ የማይረግፍ ይሁን ”

ኖረሽ ከርመሽ ደግ ዕድል፣ ደግ ኸቲማ አላህ ይወፍቅሽ ”

አሏሁ መሰሊ ወሰሊም አላ ሰይድና መሐመድ ወአላ አሊ ሰይድና መሐመድ[12]

ዱዓው የተደረገው ለነፍሰጡሯ እናት ለወ/ሮ ሀሊማ መሐመድ ሲሆን እናቲቱ ደስተኛ ኑሮ እንዲኖራት፣ የአካባቢው ጠባቂ ነው ተብሎ የሚታመንበት በመንፈሳዊነቱ የበቃ ያገሩ ሼህ ከክፉው ሁሉ እንዲጠብቃት በመመኘት የተደረገ ነው፡፡ በዱዓው ውስጥ “የበረካ ዛፍ አላህ ያ[ድ]ርግሽ”፣ “ሀረግሽም የሚሳብ አላህ ያ[ድ]ርገው”፣ “አበባሽ የማይረግፍ ይሁን” የሚሉ የዱዓ ክፍሎች ያሉ ሲሆን ዛፍ፣ ሀረግና አበባ ትዕምርታዊ ናቸው፡፡ የእነዚህ ትዕምርቶች ፍች የሚገኘው ደግሞ የትዕምርቶቹን ስነ ህይወታዊ ምንነት በመለየት ነው፡፡ ዛፍ ቅርንጫፎቹ የሚሰፉና ለሰውም ሆነ ለእንስሳት ከፀሀይና ከዝናብ መጠለያ የሚሆን ነው፡፡ አበባ የውበት ጊዜና የፍሬ መሰረት ነው፤ አበባን ቀጥሎ የሚመጣው ፍሬ ነው፡፡ ሀረግም ቁመቱ የሚሳብና የሚረዝም ተክል ነው፡፡ ዱዓው የተደረገው ዱዓ የተደረገላት ሴት የእጽዋቱን መገለጫ ባህርያት እንድታገኝ፤ እንደ ዛፍ ለሰዎች መጠጊያ እንድትሆን፣ እንደ አበባ ፍሬ የማግኛ ጊዜዋ እንዲረዝም፣ እንደ ሀረግ ዘሯ የሚሳብ እንዲሆን ነው፡፡

የነፍሰጡሯ ቤት ራቅ ያለ ቦታ ከሆነ ስራው በጊዜ ተጠናቅቆ ጉዞ ይጀመራል፡፡ ነገር ግን የነፍሰጡሯ ቤት ብዙ የሚርቅ ካልሆነ ጉዞው ከመሸ በኋላ ይደረጋል፡፡ በመሆኑም ቤተሰቡ በሙሉ፣ የቅርብ የሆኑ ዘመዶች ማለትም አክስቶች፣ አጎቶች፣ የወንድም ሚስቶች የእህት ባሎች፣ ወዘተ እና በስራው ላይ የነበሩ ጐረቤቶች ምግቡን ይዘው ወደ ነፍሰጡሯ ቤት ይጓዛሉ፡፡ ከበድ ያለው እቃ በአህያ የሚጫን ሲሆን የማይጫነው በእጅ ይያዛል (ወ/ሮ ሳሱየ አሊየ፣ 6/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ነፍሰጡሯ ቤተሰቧ የሚመጣበት ቀን ተቆርጦ እንደተነገራት በእድሜ ከፍ ያሉ ጐረቤቶቿን ቤተሰቤ በዚህ ቀን ስለሚመጣ ተቀበሉልኝ ብላ ትጠራለች፡፡ ለመቀበያ የሚሆን ምግብና

---

[12] ዱዓ ተደርጐ ሲያበቃ ዱዓውን የሚመራው ሰው “አሏሁ መሰሊ” የሚል ሲሆን ትርጉሙ “አላህ ምህረትን አውርድ” የሚል ነው፡፡ ተቀባዮች ደግሞ “ወሰሊም አላ ሰይድና መሐመድ ወአላ አሊ ሰይድና መሐመድ” የሚሉ ሲሆን ትርጉሙ “በነቢዩ መሐመድና በቤተሰቦቻቸው ላይ ሰላምታን አውርድ” ማለት ነው (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 6/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ይህ የዱዓ መዝጊያ ነው፡፡ ከዱዓ በኋላም ዱዓ አድራጊዎች እርስ በእርስ ይዘያየራሉ ወይም ፊታቸውን አበስ ያደርጋሉ፡፡

መጠጥ በነፍሰጡሯ ቤት ይዘጋጃል፡፡ ቀኑ ሲቃረብ የአብሽ ውሀ ወይም ቀሪቦ የሚዘጋጅ ሲሆን ቤተሰቧ በሚሄድበት የአምሮቱ ዋዜማ ቀን ፍየል ታርዶ ምግብ ይዘጋጃል፡፡ አምሮት ወሳጆቹ በአምሮቱ ቀን ዋዜማ ምሽት በነፍሰጡሯ ቤት ሲደርሱ የነፍሰጡሯ ባለቤት ቤተሰብና ነፍሰጡሯ ተቀበሉልኝ ብላ የጠራቻቸው ሰዎች፤ ሴቶቹ ሴቶቹን፣ ወንዶቹ ደግሞ ወንዶቹን ይቀበሏቸዋል (ወ/ሮ ሳሱየ አሊየ፣ 6/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ በእስልምና ሀይማኖት አስተምህሮ መሰረት በዚህ አይነቱ ስብሰባ ወቅት ወንድና ሴት ተቀላቅሎ ስለማይቀመጥ (*The Quran*, Al-Ahzab[13] 33:53) ሴቶችና ወንዶች በየተዘጋጀላቸው ስፍራ ለየብቻ ይሆናሉ፡፡ የተለየ ክፍል ባይኖር እንኳን የሴቶቹና የወንዶቹ መቀመጫ ተከልሎ ወይም ተጋርዶ ይለያል፡፡ የነፍሰጡሯ እንግዶች ከገቡ በኋላ ለመቀበያ የተዘጋጀው ምግብና መጠጥ ይቀርብላቸዋል፤ ማርና ቅቤ ይቀዳላቸዋል፤ የአብሽ ውሀ[14] ወይም ቀሪቦ[15] ይቀርብላቸዋል፡፡ በአርጐባዎች ዘንድ ማርና ቅቤ የክብር ምግቦች ናቸው፡፡ ማርና የተነጠረ ቅቤ በተለያዩ ስነ ስርዓቶች ላይና የተለየ ክብር ለሚሰጠው እንግዳ ሲመጣ የሚቀርቡ ሲሆን በጣባ ቀርበው በእንጀራ እየተጠቀሱ ይበላሉ፡፡ የነፍሰጡሯ ቤተሰቦች የቀረበላቸውን ምግብ ጨርሰው አይበሉም፡፡ ገበታው ከእነርሱ በኋላ ለሌሎች የሚቀርብ በመሆኑ በተለይ ማሩና ቅቤውን በመጠኑ አጥቅሰው በመብላት እንዲተርፍ ያደርጋሉ፡፡ ገበታ ሲነሳ ቡና ተፈልቶ ዱዓ ከተደረገ በኋላ ይጠጣል፡፡ በዚህ መልኩ ወንዶቹና ሴቶቹ ለየብቻ ከተስተናገዱ በኋላ ወንዶቹ ዱዓ እያደረጉ ያመሻሉ (17/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ምልከታ፤ 11/3/2013 እና 25/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

---

[13] የቁርዓን ምዕራፎች እያንዳንዳቸው ስያሜ አላቸው፡፡ በMLA ምንጭ አጠቃቀስ መሰረት ደግሞ ቁርዓን በምንጭነት ሲጠቀስ አንባቢ የትኛው የቁርዓን ምዕራፍ መሆኑን በቀላሉ ለመረዳት እንዲችል የምዕራፉ ስያሜ የምዕራፉና አንቀፁ ቁጥር ከመገለፁ አስቀድሞ በዚህ ዓይነት መንገድ እንዲቀርብ ያዝዛል፡፡ ስለዚህ Al-Ahzab የምዕራፍ 33 ስያሜ በመሆኑ በዚህ መልክ ተጠቅሷል፡፡

[14] ከማሽላና ከአብሽ የሚዘጋጅ መጠጥ ሲሆን አዘገጃጀቱ ሁለት ወይም ሶስት እጅ ማሽላና አንድ እጅ አብሽ ለየብቻ ይታጠብና ከደረቀ በኋላ ለየብቻ ይቆላና ይከካል፡፡ ከዚያ በኋላ ተደባልቆ በፈላ ውሃ ይላግና ሲበርድ በርሜል ወይም ባሊ ታጥቦ፣ በወይራ ይታጠንና የበረደው እህል በዚያ ተደርጐ በእህሉ መጠን ውሃ ይሞላል፡፡ ከስምንት እስከ አስር ቀን ከፈላ በኋላ ታጥቦ በታጠነ እቃ ይቀዳና ዝንጅብል፣ ጥቁር አዝሙድ፣ ቀረፋና ማር ተጨምሮበት ለመጠጥነት ዝግጁ ይደረጋል፡፡

[15] ቀሪቦ ለማዘጋጀት መጀመሪያ ገብስ ይቆላና ይከካል፡፡ ከዚያ በውሃ ተበጥብጦ በእንስራ ይደረግና በውሀ ይሞላል፡፡ ከላይ የገብስ ብቅል ይደረግበትና ይከደናል፡፡ በሶስተኛው ቀን ተቀድቶ ሊጠጣ ይችላል፡፡

ከመስተንግዶው በኋላ የነፍሰጡሯ እናት ወይም አምሮቱን በኃላፊነት ይዛ የመጣችው ሌላ ሴት ለነፍሰጡሯና ለባለቤቷ ለብቻ ተዘጋጅቶ የመጣው አሊጣ ሲቀር የመጣውን ምግብ በሙሉ ለሌማት ከፋቾች ካቀረበች በኋላ ሌማት ከፋቾች ዳቦውን፣ አነባበሮውንና እንጀራውን ይቆጥራሉ፡፡ ከዚያ በኋላ በማግስቱ ጠዋት ለሚከወነው የገንፎ ስነ ስርዓት የሚጠራውን ጕረቤት ማንነትና ቁጥር በተመለከተ ተነጋግረው ይወስናሉ፡፡ በማግስቱ ለሚከወነው የገንፎ ስነ ስርዓት የሚመጣው ጕረቤት የሚጠራው የመጣው ዳቦና አነባበሮ እየታደለው በመሆኑ ዳቦው፣ አነባበሮውና እንጀራው በሚጠራው አባወራ ቁጥር ልክ እንዲደርስ ተደርጐ ይቆረሳል፤ ከስር አነባበሮው፣ ከላይ በቅደም ተከተል ዳቦውና አሊጣው ተደርጐ እየታጠፈ በሳፋ ላይ ይከመራል፤ አንዱ እጥፍ ለአንድ አባወራ ጥሪ የሚሆን ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ሁለት ሁለት ሴቶች፤ አንዷ ሳፋውን በጭንቅላቷ የምትሸከም፣ አንዷ የምታድል እየሆኑ ጥሪ የሚደረግበትን ጕጥ ተከፋፍለው ወደየምድባቸው ጕጥ የሚጠሩ ጕረቤቶች ቤት በመሄድ “ነገ ጠዋት እከሌ ቤት ቡና ጠጡ” እያሉ ምግቡን ያድላሉ፡፡ እደላው አልቆ አዳዮቹ ሲመለሱ ሌማት ከፋቾቹና አዳዮቹ ይቀመጡና ለሌማት ከፋች ተብሎ የመጣው አሊጣ ይቀርብላቸውና ይመገባሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ለመቀበያ ተብሎ በነፍሰጡሯ ቤት የተዘጋጀውና ከነፍሰጡሯ ቤተሰብ የተረፈው ምግብ ማርና ቅቤው ተጨምሮበት ቀርቦላቸው ይመገባሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ጕረቤቶች ወደየቤታቸው ሲሄዱ የነፍሰጡሯ ቤተሰብ እዚያው ያድራል፡፡ ጕረቤት ከተሸኘ በኋላ ነፍሰጡሯና ባለቤቷ ለብቻ የመጣላቸውን አሊጣ ይመገባሉ (17/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ፤ 11/3/2013 እና 25/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡ ጥንዶቹ በአንድነት ሆነው ለብቻ መመገባቸው ለብቻ ከመመገብ ድርጊት በላይ ትዕምርታዊ ሲሆን የአንድነት፣ የጥምረት መገለጫ የሆነ ድርጊት ነው፡፡ ነፍሰጡሯ እንግዶች ከተስተናገዱ በኋላ የምትስተናገድ በመሆኑ እንግዶች ከመምጣታቸው በፊት ቤቷ ከተዘጋጀው ምግብ ቀድማ ተመግባ ትቆያለች፡፡



**ፎቶግራፍ 5. የአምሮት ጥሪ**

ለአምሮት ስነ ስርዓት የሚዘጋጀው ብቸኛ ምግብ ገንፎ በመሆኑ በማግስቱ ጠዋት ገንፎ ይገነፋል፤ ለማባያ የሚሆነው የተወቀጠ ሰሊጥ ትንሽ ውሃና ስኳር ይጨመርበትና ተንተክትኮ ይዘጋጃል፡፡ ስራውን የሚሰሩት አምሮት ይዘው የሄዱ የነፍሰጡሯ የቤተሰብ አባላት፣ ተቀባይ ሆነው የቆዩ የነፍሰጡሯ ባል ሴት ዘመዶችና ጎረቤቶችም ናቸው (17/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ምልከታ፤ 11/3/2013 እና 25/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

ገንፎው እየተገነፋ የተጠሩ ጎረቤቶች ሲመጡ ሴቶች ለብቻ ወንዶች ለብቻ በመሆን ይቀመጣሉ፡፡ ቤት ቢጠብ እንኳን በውጭ አነስተኛ ዳስ እየተደረገ እንግዶች እዚያ ያርፋሉ፡፡ ቅድሚያ የሚስተናገዱት ወንዶች በመሆናቸው ገንፎ በቅቤና በሰሊጥ ለየብቻው ተደርጎ ለወንዶቹ ይቀርብና በቡድን ሆነው ይመገባሉ፤ ለቤተሰብ መቀበያ ከተዘጋጀው የአብሽ ውሀ ወይም ቀሪቦ ይቀርብላቸዋል፡፡ ገንፎው ተበልቶ እንዳበቃ ድፎ ዳቦ፣ የማሽላ ቆሎና ቡና ቀርቦ ዱዓ ከተደረገ በኋላ ቡናው ይጠጣል፡፡ ሴቶቹ ያዘጋጁትን ምግብ እየወሰዱ ወንዶችን የሚያስተናግዱት ወንዶች ናቸው፡፡



**ፎቶግራፍ 6. የአምሮት ገንፎ ሲያገነፉ**

ከወንዶቹ መስተንግዶ በኋላ ተጠርተው ነገር ግን በህመምና በአቅም መድከም ምክንያት መምጣት ላልቻሉ ሰዎች ገንፎ በጣባ እየተደረገ በየቤታቸው ይላክላቸውና በሴት አስተናጋጆች የሴቶቹ መስተንግዶ ይቀጥላል፡፡ ለሴቶቹ ተጠሪዎች ገንፎ ይቀርብና የነፍሰጡሯ እናት ቆማ "ቢስሚላሂ ራህማራ ራሂም ለሲቲና ፋጡማ" በማለት ገንፎውን ጀባ ትላለች፡፡ ፋጡማ የነብዩ መሐመድ ልጅ ሲሆኑ ወልደው የተባረከላቸው፣ ምጥን የሚያገሩ፣ ምጥን የሚያሳጥሩ፣ ጭንቅን የሚያቀሉ፣ ወላድን የሚቀርቡ፣ ወሊድን የሰላም የሚያደርጉ እንደሆኑ ይታመናል፡፡ የአምሮት ስነ ስርዓት ነፍሰጡሯ በሰላም እንድትወልድ በዋናነት ፋጡማ የሚለመኑበት በመሆኑ የነፍሰጡሯ እናት ገንፎው በፋጡማ ስም መዘጋጀቱን በመግለጽ ሰዎችን ለዱዓ ትጋብዛለች ማለት ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ሴቶቹ በገንፎው ዙሪያ በክብ በመቀመጥ የሁለት እጆቻቸውን ጣቶች በገበታው ክፈፍ ዙሪያ ላይ በማድረግ ዱዓ ያደርጋሉ (17/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ፤ 11/3/2013 እና 25/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡ ጣቶችን በገበታ ዙሪያ በማድረግ ገበታውን መያዝ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው፡፡ ገበታው ምጥን እንደሚያገሩ፣ ጭንቅን እንደሚያርቁ በሚታመንባቸው ስም የሚቀርብ በመሆኑ በአፍ ከሚደረገው ዱዓ በተጨማሪ ገበታውን መያዝ አጥብቆ መለመንን፣ መማፀንን የያዘ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው፡፡



**ፎቶግራፍ 7. ገንፎው ቀርቦ ዱዓ ሲደረግ**

ዱዓውን የሚያደርጉት ከተሰበሰቡት ሴቶች መካከል በእድሜ አንጋፋ የሆኑና ዱዓ ማድረግ የሚችሉ ናቸው፡፡ በመስክ ስራ ወቅት በተዘዋወርኩባቸው ቀበሌዎች ሁሉ ዱዓ በማድረግ የሚታወቁና "ያለእርሷ ዱዓ አይሆንም" የሚባልላቸው ሴቶች መኖራቸውን የተገነዘብኩ ሲሆን ከጋቸኔ ቀበሌ ወ/ሮ ሶህሊየት ባቢንና ከገበሮች ቀበሌ ወ/ሮ ብርቄን እንደምሳሌ ማንሳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጊዜም እነዚህን መሳይ ሴቶች ተመርጠው ዱዓ የሚያደርጉ ሲሆን የተሰበሰቡ ሴቶች "አሜን" እያሉ ዱዓውን ይቀበላሉ፡፡ የነፍሰጡሯ እናት ወይም አምሮቱን በኃላፊነት ያዘጋጀችው ሴት በየመራቂዎቹ ፊት ቆማ ጐንበስ በማለትና እጆቿን በመዘርጋት "አሜን" እያለች ዱዓውን ትቀበላለች (17/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ፤ 11/3/2013 እና 25/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

የሚከተሉት ዱዓዎች በምልከታ ወቅት ለወ/ሮ ዘይነባ መሐመድ ጀማል የተደረገ የአምሮት ስነ ስርዓት ላይ ገበታ ቀርቦ ከተደረጉ ዱዓዎች ውስጥ ለማሳያነት የተመረጡና በቅደም ተከተል በወ/ሮ አሚና ኢብራሂምና በወ/ሮ ሶህሊየት ባቢ መሪነት የተደረጉ ናቸው (17/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

ዱዓ 1፣

| <u>ዱዓ አድራጊ</u> | <u>ተቀባዮች</u> |
|---|---|
| በሙሉ አላህ ያውጣት | አሜን |
| ሙሉ ቀን አላህ ይግጠማት | " |
| የሰሊጥ ውቂያ አላህ ያድርግላት | " |
| ሙልጭ ሙልጭልጭ ያድርግላት | " |
| ቀሚሷ አይስማት | " |
| አማን ትውለድ | " |
| ልጁም ወንድ ይሁን | " |
| ምጡም ገር ይሁን | " |

አሏሁ መሰሊ ወሰሊም አላ ሰይድና መሐመድ ወአላ አሊ ሰይድና መሐመድ

በዚህ ዱዓ ላይ "በሙሉ አላህ ያውጣት"፣ "ሙሉ ቀን አላህ ይግጠማት"፣ "ልጁም ወንድ ይሁን" እና "የሰሊጥ ውቂያ አላህ ያድርግላት" የሚሉ የዱዓ ክፍሎች ትዕምርታዊ ናቸው፡፡ "በሙሉ አላህ ያውጣት" በተባለው ሙሉነት ከህመም፣ ከመጉደል፣ ይህ ቀረኝ ከማለት ተጠብቆ በሰላም መሻገርን የሚወክል ሲሆን በዚህና በሌሎች ዱዓዎች የሚታየው መውጣት የሚለው ቃል ነፍሰጡሯ ካለችበት የጭንቅ ጊዜ ቀለል ወዳለው ጊዜ ማለፏን፣ መሻገሯን፣ የሚወክል ነው፡፡ "ሙሉ ቀን አላህ ይግጠማት" በተባለው ደግሞ ሙሉ ቀን ችግር፣ ህመም፣ መከራ፣ ስቃይ የሌለበትና በአንፃሩ በገድ የተሞላ ቀንን ይወክላል፤ ነፍሰጡሯ በሚገጥማት ሙሉ ቀን ሙሉ ነገር እንዲገጥማት መመኘት ነው፡፡ "ልጁም ወንድ ይሁን" የሚለው የዱዓው ክፍል በአርጐባዎች ዘንድ ያለን የፆታ ምርጫ ጉዳይ በተመለከተ መረጃ የሚሰጥ ሲሆን በአርጐባዎች ልማድ ከሴት ልጅ ይልቅ የወንድ ልጅ መወለድ እንደሚመረጥ ያሳያል፡፡ የሰሊጥ ውቂያ ትዕምርታዊ ፍች የሚገኘው የትዕምርቱን ምንነት በመረዳት ነው፡፡ የሰሊጥ ውቂያ እንደሌላው እህል ውቂያ ብዙ ጉልበት አይፈልግም፡፡ አዝመራው ታጭዶና ታስሮ ይከመርና ሲደርቅ እስሩን ወደ ታች መዘቅዘቅና ማራገፍ ብቻ በቂ ነው፤ ምርቱ ይራገፋል፡፡ ምጡን የሰሊጥ ውቂያ ያድርገው ሲባልም ምጡ የሰሊጥ ውቂያን ያህል ይቅለል፣ ብዙ ጭንቅ አይኑረው ማለት ነው፡፡

ዱዓ 2፣

| <u>ዱዓ አድራጊ</u> | <u>ተቀባዮች</u> |
|---|---|
| አላህ ያስደስትሽ | አሚን |
| ምንም ሳይሰማብሽ | " |
| ሙልጭ ሙልጭልጭ | " |
| የተልባ ድጥ አላህ ያርግልሽ | " |
| ያቺንም ያቺንም [እህትማማች ነፍሰጡሮች አሉ] ይፍታቸው | " |
| ተቤት ሳይወጡ | " |
| በጓዳቸው የሚወልዱ | " |
| አላህ ያርግልሽ | " |

አሏሁ መሰሊ ወሰሊም አላ ሰይድና መሐመድ ወአላ አሊ ሰይድና መሐመድ

በዚህ ዱዓ ደግሞ “የተልባ ድጥ አላህ ያርግልሽ”፣ “ያቺንም ያቺንም ይፍታቸው” እና “ተቤት ሳይወጡ በጓዳቸው የሚወልዱ አላህ ያ[ድ]ርግልሽ” የሚሉ ክፍሎች ትዕምርታዊ ናቸው፡፡ የተልባ ድጥ ትዕምርታዊ ፍች የሚገኘው ትዕምርቱን በመረዳት ነው፡፡ ተልባ ከውሀ ጋር ሲደባለቅ የመዝለግለግና የማሟለጭ ባህርይ ያለው በመሆኑ በዱዓው ውስጥ “[ወሊዱን] የተልባ ድጥ አላህ ያርግልሽ” የተባለው የተልባ ድጥ የማያስጨንቅንና የፈጠነን ወሊድ እንዲወክል ሆኖ ነው፡፡ “ያቺንም ያቺንም ይፍታቸው” በሚለው ውስጥ መፈታት የሚለው ቃል መውለድን እንዲገልጽ የቆመ ነው፡፡ እርግዝናን ከመታሰርና ከመያዝ ጋር፣ መውለድን ደግሞ ከመፈታት ጋር በማመሳሰል ማሰብን ተከትሎ ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ነው፡፡ “ተቤት ሳይወጡ በጓዳቸው የሚወልዱ አላህ ያ[ድ]ርግልሽ” በሚለው የዱዓ ክፍል ከቤት ሳይወጡ መውለድ ማለት ከባድ የወሊድ ችግር ሳያጋጥምና ወደ ዘመናዊ የጤና ተቋም ሳይኬድ በቤት ውስጥ፣ በቀደመው ባህል፣ ከአያት በተወረሰው የወሊድ ስነ ስርዓት መውለድ ማለት ነው፡፡ ይህ የዱዓ ክፍል የአርጐባ እናቶች በዚህ መሰሉ መንገድ በቤታቸው መውለድ ምርጫቸው መሆኑን የሚነግር ነው፡፡

ዱዓው ካበቃ በኋላ ሁሉም ሴቶች ተዘያይረው ሲያበቁ ከገንፎው ሶስት ጊዜ ተቆንጥሮ በጣባ ይደረግና ነፍሰጡሯ እንድትበላው ይሰጣታል (17/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ፤ 11/3/2013 እና 25/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡ ማንም ሰው ከመቅመሱ በፊት ገንፎው ተቆንጥሮ ለነፍሰጡሯ የሚሰጣት ገንፎው ዱዓ የተደረገበት በመሆኑ ቀድማ መቅመሷ የዱዓውን በረከት ያስገኝላታል፤ ዱዓው እንዲደርስላት ያደርጋል ተብሎ የሚታመን በመሆኑ ምክንያት ሲሆን ሶስት ጊዜ መቆንጠሩም አርጐባዎች ነገር በሶስት ይፀናል ብለው ስለሚያምኑና ምርቃቱ እንዲሆንላት በመመኘት ነው፡፡

ገንፎው ተበልቶ ካበቃ በኋላም ሲጀመር በተደረገበት መንገድ ዱዓ ይደረጋል፡፡ ሴቶቹ የእጆቻቸውን ጣቶች በገበታው ክፈፍ ላይ በማድረግ የተመረጡ ሴቶች ዱዓ ሲያደርጉ ሌሎች “አሚን” ይላሉ፡፡ የነፍሰጡሯ እናት ወይም አምሮቱን በኃላፊነት ያዘጋጀችው ሴት እንደ መጀመሪያው ሁሉ በየዱዓ አድራጊዎቹ ፊት እየቆመች እጆቿን ዘርግታ “አሚን” እያለች ዱዓውን ትቀበላለች (17/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ፤ 11/3/2013 እና 25/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

ዱዓው ተደርጐ ካበቃ በኋላ አሁንም ሴቶቹ ይዘያየሩና ሁሉም ገበታውን ዙሪያውን በመያዝ እልል እያሉ ሁለት ጊዜ ወደላይ ከፍ ምልስ፣ ከፍ ምልስ በማድረግ በሶስተኛው

ከፍ አድርገው "ልጁ ተወለደ! ልጁ ተወለደ!" ብለው ገበታው በዚያው ወደ ጓዳ እንዲገባ ይደረጋል (17/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ፤ 11/3/2013 እና 25/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡ ከመረጃ ሰጪዎች አንዷ ወ/ሮ አይኔ ይማሙ (3/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) እንደገለፁት ገበታ ከፍ አድርጎ ወደ ጓዳ ከማስገባት ትዕምርታዊ ክዋኔ ጋር ተይዩ የሆነ ሌላ ክዋኔም አለ፡፡ ይህም ድፍን ቅል ይታጠብና እንደ ልጅ በጨርቅ ተጠቅልሎ "ወለደች! ወለደች!" ተብሎ አጣቢዋ ሴት ቅሉን ወስዳ አልጋ ላይ ታስተኛዋለች፡፡

ገበታን ሶስት ጊዜ ከፍ ማድረግ ትዕምርታዊ ድርጊት ሲሆን ገበታው የሚወለደውን ህፃን እንዲወክልና ገበታውን ከፍ ማድረግም ልጅ ተወልዶ ማንሳትን እንዲወክል የተደረገ ነው፡፡ ገበታው ከፍ የሚደረገው ሶስት ጊዜ መሆኑ አርጐባዎች ነገር በሶስት ይፀናል ብለው የሚያምኑ በመሆናቸው ምክንያት የህፃኑን በሰላም መወለድ ማጽናታቸው ነው፡፡ ገበታው ወደ ጓዳ እንዲገባ መደረጉም ልጅ ተወልዶ በጓዳ እንዲገኝ መመኘ ነው፡፡ በንግግር "ልጁ ተወለደ! ልጁ ተወለደ!" ማለትም የህፃኑን በሰላም መወለድ ማምሰያ ነው፡፡ በመሆኑም ሴቶቹ ይህን ድርጊት በማድረግ ነፍሰጡሯ በሰላም ወልዳ ልጁ በጓዳዋ እንዲሆን ያመስላሉ፡፡ በተመሳሳይ ድፍን ቅል አጥቦና በጨርቅ ጠቅልሎ "ወለደች! ወለደች!" በማለት በአልጋ ላይ ማድረግ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው፡፡ ቅሉ የሚወለደውን ህፃን እንዲወክል የተደረገ ሲሆን ተወለደ ብሎ ቅሉን እንደ ህፃን አጥቦና አልብሶ አልጋ ላይ ማድረግ ህፃኑ ተወልዶ በጓዳ እንዲገኝ የማምሰያ ትዕምርት ነው፡፡

ገበታ በመያዝ እልል እያሉ ከፍ የማድረግና ወደ ጓዳ የማስገባት፣ ድፍን ቅል አጥቦና አልብሶ እንደ ልጅ አልጋ ላይ የማድረግና ያልተወለደ ልጅን ተወለደ የማለት ትዕምርታዊ ድርጊቶችና ቃላት ነፍሰጡሯ በሰላም እንድትገላገል የማድረግ የክዋኔው ዓላማ ጋር ተሰናስለው የተደረጉና ፍችያቸውም በዚያው አግባብ የሚለይ ናቸው፡፡



ፎቶግራፍ 8. ገበታውን ከፍ ሲያደርጉ

ሴቶቹም ሆኑ ወንዶቹ ገንፎውን ከበሉ በኋላ እጃቸውን ይታጠቡና እጣቢው ወደ ጓዳ አልጋ ስር ይፈሳል እንጂ በደጅ አይፈስም፡፡ ገንፎው ዱዓ የተደረገበት በመሆኑ በረከት የሚያስገኝ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በረከት የሚያስገኝ ነገር ከነፍሰጡሯ ቤት ሳይወጣ እዚያው መቅረቱ ለነፍሰጡሯና ለቤተሰቧ በረከት ያስገኛል ተብሎ ስለሚታመን የተመጋቢዎቹ እጅ እጣቢ እንኳን ወደ ውጭ ወጥቶ ከመደፋት ይልቅ ጓዳ ውስጥ፣ አልጋ ስር እንዲፈስ ይደረጋል (ወ/ሮ ሳሱየ አሊየ፣ 6/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በዚህ መልኩ ገንፎው ተበልቶ ካበቃ በኋላ የቡና ቁርስ ድፎ ዳቦና የማሽላ ቆሎ ይቀርብና ቡና ይከተላል፡፡ ቡናው ሲቀርብ ቡናውን ያቀረበችው ሴት "አቦል ጀባ" ትላለች፤ ቡና መቅረቡን መግለጿ፣ ዱዓ እንዲደረግም ማመላከቷ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ አሁንም ዱዓ የምታደርግ ሴት ዱዓውን ስታደረግ ሌሎቹ እጆቻቸውን ዘርግተው "አሚን" እያሉ ይቀበላሉ፡፡ የነፍሰጡሯ እናት ወይም አምሮቱን በኃላፊነት ያዘጋጀችው ሴት አሁንም በተመሳሳይ መልኩ ቆማ "አሚን" እያለች ዱዓውን ትቀበላለች፡፡ ዱዓው ሲያልቅ ዳቦው ተቆርሶ ከቆሎው ጋር ይታደልና ቡናው ይቀዳል (17/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ፤ 11/3/2013 እና 25/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

በጋቸኔ ቀበሌ በተገኘሁበትና ምልከታ ባደረግሁበት የአምሮት ስነ ስርዓት ላይ ቡና ሲፈላ የተደረገው ዱዓ አቦል ቡና ፈልቶ ሲቀርብ አንድ ጊዜ ብቻ ነው (17/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡ ነገር ግን በላይ መጠቅለያ ቀበሌ በተመለከትኩት ለወ/ሮ ሩቅያ መሐመድ በተደረገ የአምሮት ስነ ስርዓት ላይ ግን ወ/ሮ መራኢና መሐመዱ ሶስት ጊዜ ማለትም አቦል (የመጀመሪያ ቡና)፣ ረጃ (ሁለተኛ ቡና) እና ጀሚ (ሶስተኛ ቡና) ፈልቶ በቀረበበት

ጊዜ ሁሉ ዱዓ አድርገዋል (11/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡ ወ/ሮ ከድጀሺ ከማል (14/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) እንደነገሩኝ ቡና ሲቀርብ በዚህ መልኩ አንድ ጊዜ ወይም ቡናው ፈልቶ በቀረበ ቁጥር ምርቃት ሊደረግ ይችላል፡፡

ቡናው ተጠጥቶ ካበቃ በኋላ ሴቶቹ ዝኪር ያደርጋሉ (17/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ፤ 11/3/2013 እና 25/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡ ዝኪር በአንድ አውራጅና ቁጥራቸው ብዙ በሆነ ተቀባዮች የሚከወን ማሞገሻና መማጠኛ ነው፡፡ የሚከወኑ ዝኪሮች በቅደም ተከተል የፋጢማ፣ የኑር ሁሴን፣ የእማ መዲናና ሼህ ጦሪቃ እና የነቢዩ ዝኪሮች ሲሆኑ በአምሮት ጊዜ ትኩረት ተሰጥቶት የሚከወነው የፋጢማ ዝኪር ነው፡፡ እማ መዲናና ሼህ ጦሪቃ ወልዮች ናቸው ተብሎ የሚታመንባቸው ናቸው፡፡ ሁለቱም በመቃብር ቦታቸው ላይ መስጊድ የተሰራ ሲሆን የእማ መዲና መስጊድ በወረዳው አባሊ ቀበሌ፣ የሼህ ጦሪቃ መስጊድ ደግሞ በጋቸኔ ቀበሌ ይገኛል፤ በየአመቱ በየመስጊዳቸው ይዘየራሉ (ወ/ሮ አይከዲጅ መሐመድ፣ 28/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ የሚከተለው ለማሳያነት የቀረበ የፋጢማ ዝኪር (17/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ) ነው፡፡

| <u>አውራጅ</u> | <u>ተቀባዮች</u> |
|---|---|
| አርሂብ አርሂብ ፋጢማ ነቢይ <u>አርሂብ</u> (2) | አርሂብ አርሂብ ፋጢማ ነቢይ <u>አርሂብ</u> (2) |
| አሰላም አሊኩም | አርሂብ አርሂብ |
| ብለው በሉልኝ | ” |
| እኔም እመጣለሁ | ” |
| አላህ ቢያሻልኝ | ” |
| አርሂብ አርሂብ ፋጢማ ነቢይ <u>አርሂብ</u> (2) | አርሂብ አርሂብ ፋጢማ ነቢይ <u>አርሂብ</u> (2) |
| እንዴት ያለው ነገር | አርሂብ አርሂብ |
| እንዴት ያለ አበሳ | ” |
| ሀቅን እየተዉ | ” |

ለባጤል ደገሳ ”

አርሂብ አርሂብ ፋጢማ ነቢይ <u>አርሂብ</u> (2) አርሂብ አርሂብ ፋጢማ ነቢይ <u>አርሂብ</u> (2)

ዝኪሮች የሚደረጉበት ዋና ዓላማ ፋጡማን፣ ኑር ሁሴንን፣ እማ መዲናን፣ ሼህ ጠሪቃን እና ነቢዩን ማሞገስ፣ መንፈሶቻቸው ነፍሰጡሯን እንዲቀርቧትና በሰላም እንድትወልድ እንዲረዷት መለመንና መማፀን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዝኪሮቹ በማህበራዊና መንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ ያሉ ህፀፆች የሚነሱባቸውና እርምቶች የሚሰነዘሩባቸው ናቸው፡፡ ዝኪሮቹ ከተከወኑ በኋላ የስነ ስርዓቱ ክዋኔ ማብቂያ በመሆኑ የመጨረሻ ዱዓ ተደርጎ ተጠሪዎች ወደየቤታቸው ይሄዳሉ፡፡

ከዚያ በኋላ የነፍሰጡሯ ቤተሰብ አባላት መሄድ የለባችሁም አድራችሁ ነው የምትሄዱት ተብለው ከተጋበዙ እዚያው ውለው ያድራሉ፡፡ ይህ ከሆነ የነፍሰጡሯ ባለቤት ሴት የቤተሰብ አባላት ሴቶቹን ገላቸውን አስታጥበው ቅቤና ሽቶ ይቀቧቸውና ሲጫወቱ ይውላሉ፡፡ ማታም ፀጉራቸውን አዝጋሮና ሽታ[16] እየሞቁ ያመሹና በማግስቱ ቁርስ በልተው ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ግን የነፍሰጡሯ እናት፤ እናት በህይወት ከሌለች እናትን ወክላ የመጣችው ሴት ነፍሰጡሯን በቀሪው የነፍሰጡርነት ጊዜዋ ለመንከባከብና ስትወልድም ለማረስ እዚያው ቤት ትቀራለች ወይም ነፍሰጡሯን ወደ ራሷ ቤት ይዛት ትሄዳለች (ወ/ሮ ሳሱየ አሊየ፣ 6/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

## 5.2.2.5. የወሊድ ዝግጅት

ነፍሰጡር የወሊድ ዝግጅት የምታደርገው ሰባት ወር ሲሆናት ጀምሮ ነው፡፡ የሚደረገውን ዝግጅት ለሁለት ከፍሎ መመልከት የሚቻል ሲሆን የመጀመሪያው ነፍሰጡሯ ሰባተኛ ወሯ እንደገባ ጀምራ የምታደርገው፣ ሁለተኛው ደግሞ ዘጠኝ ወሯ ከገባ ጀምራ የመውለጃዋ ቀን እስኪቀርብ ድረስ የምታደርገው ነው፡፡

ነፍሰጡሯ ሰባት ወር ሲሆናት ጀምራ ከምታደርጋቸው ዝግጅቶች መካከል አንዱና ዋናው የምግብ ግብዓቶችን ማዘጋጀት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ነፍሰጡሯ ወልዳ በምትተኛበት ጊዜ

---

[16] አዝጋሮና ሽታ ሁለቱም መልካም መዓዛ ያላቸው የጭስ አይነቶች ናቸው፡፡ አዝጋሮ እንጨት ሲሆን ሽታ የተለያዩ እጣኖችና ሰንደል ተደባልቀውና በሽቶ ተለውሰው የሚዘጋጅ ጭስ ነው፡፡

የምትመገበውና እንግዳ የሚሸኝበት የምግብ ግብዓት ይዘጋጃል፡፡ በመሆኑም ጤፍ፣ ማሽላ፣ ገብስ፣ ቅቤ፣ ማር፣ ዶሮ፣ በርበሬ፣ ሽሮና ተልባ ከገበያ የሚገዛው ተገዝቶ፤ ከቤት በግብርና ስራ የሚገኘውም ተዘጋጅቶ ለነፍሰጡሯ የአራስነት ጊዜ ተብሎ ይቀመጣል፡፡ ቅቤው ተነጥሮ፣ ሽሮና በርበሬው ተፈጭቶ፣ ገብሱ ተፈትጐና ደርቆ ይቀመጣል (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 12/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በአርጐባዎች ዘንድ የአራስ ሴት ዋና የመታረሻ ምግብ ከዶሮ ስጋ የሚዘጋጅ በመሆኑ ነፍሰጡሯ በነፍሰጡርነት ጊዜዋ ቀደም ብላ ዶሮ ማርባት ትጀምራለች ወይም ከገበያ ገዝታ እስከምትወልድበት ጊዜ ድረስ እየተንከባከበች ታቆያለች፡፡ ነፍሰጡሯ ለአውሊያ ግብር[17] ማድረግ ያስለመደች ከሆነም ያስለመደችውን አይነት ቀለም ያለው ዶሮ ገዝታ ግቢዋ ውስጥ ትለቃለች፡፡ የመገበሪያ ጊዜው ተጠብቆ ዶሮው የሚታረድ ሲሆን እስከዚያ ድረስ ግን ነፍሰጡሯ ዶሮውን ገዝታ በመልቀቋ ቀለል ይላታል፣ ጤና ታገኛለች ተብሎ ይታመናል፡፡ ከመውለዷ በፊት የመገበሪያ ጊዜው ከደረሰም ነፍሰጡሯ ያስለመደችውን ግብር መገበር ይኖርባታል፡፡ ነፍሰጡሯ ይህን በወቅቱ ካላደረገች "ልታዳፍን ትችላለች" ማለትም ምጥ ሳይመጣ ወሯ ሊያልፍ ይችላል ተብሎ ይታመናል (ወ/ሮ መራኢና መሐመዴ፣ 22/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ሌላው ዝግጅት ነፍሰጡሯ የምትወልድበትን ቤትና መኝታዋን የማሰናዳትና የማጽዳት ስራ ነው፡፡ የነፍሰጡር ቤት ብርሀን የሚያስገባ ቀዳዳ ካለው ቀዳዳው ሁሉ እየተጠቀጠቀ፤ ግድግዳውና ወለሉ በከብት አዛባ እየተለቀለቀ ይስተካከላል፡፡ ነፍሰጡር በቤት ውስጥ ስትወልድ የምትወልደው በጠፍር በተሰራ ድንክ አልጋ ላይ በመሆኑ ድንክ አልጋው በቤቷ ካላት አጽድታ ለመውለጃዋ አዘጋጅታ ታስቀምጠዋለች፡፡ ድንክ አልጋ በቤቷ ከሌለ ደግሞ ከጐረቤት ተውሳ አጽድታ ታስቀምጣለች፡፡ ከዚያ በኋላ ቤቷንና የምትወልድበትን ቦታ ታፀዳለች፤ ሽታ ታዘጋጃለች፤ ሽታ በማጨስ የምትወልድበት ቤትና አካባቢ ጥሩ መዓዛ እንዲኖረው ታደርጋለች፤ ልብሶቿ እንዲታጠቡና ንፁህ እንዲሆኑ፣ ከዚያም ሽታ እንዲሞቁ ታደርጋለች፡፡ ሽታ ሉባንጃ፣ ጭቃ ብርጉድ፣ አፈር ኮቸር፣ ሚስክ የሚባሉ ጥሩ ሽታ ያላቸው የእጣን ዓይነቶችና ሰንደል አንድ ላይ ተወቅጠውና በሽቶ ተለውሰው የሚዘጋጅ ባለ ጥሩ መዓዛ ጭስ ሲሆን ወይባ ከተሞቀ በኋላ የሚሞቁት፣ ልብስ ከታጠበ በኋላ በአጐበር

[17] አውሊያ የሚመለክ መንፈስ ሲሆን መንፈሱን የሚያመልኩ ሰዎች በተወሰነ ጊዜና በቋሚነት በመንፈሱ ስም ምግብና መጠጥ በማዘጋጀት፣ እርድም በማከናወን ይደግሳሉ፡፡ ግብር የተባለውም ይኸው ድግስ ነው፡፡

ተደርጐ የሚሞቅበትና ቤቱ ጥሩ ጠረን እንዲኖረው የሚጨስ ጭስ ነው፡፡ ሽታ በጣም ጠንካራ መዓዛ ያለው በመሆኑ ሲወቀጥና ሲጨስ ጐረቤት ድረስ ስለሚሸት ነፍሰጡር ቤት ሲሸት ሰዎች ነፍሰጡሯ ለመውለድ እንደደረሰች ይረዳሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ነፍሰጡሯ ከወለደች በኋላ የምትሞቀው የወይባና የአዝጋሮ ግንድ አስፈልጣ፣ ሳሙናና ሽቶ ገዝታ ታስቀምጣለች (ወ/ሮ ጠይባ ይማም፣ 5/10/2012፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡



ፎቶግራፍ 9. ሽታ

ነፍሰጡሯ ስትወልድና ወልዳ ስትተኛ የምትለብሰውን እና የህፃኑን ልብስም ታዘጋጃለች፡፡ ነፍሰጡሯ የምትወልድበትና ከወለደች በኋላ ታጥባ የምትለብሰው ሁለት ጐንደሬ ቀሚስ በቤቷ ካላት ታጥቦና ጭስ ተሞቆ ይቀመጣል፤ በቤቷ ከሌላት ደግሞ በሸማኔ አሰርታና አሰፍታ ካዘጋጀች በኋላ ታጥቦና ጭስ ተሞቆ ይቀመጣል፡፡ ጐንደሬ ቀሚስ ከጥጥ ፈትል የሚሰራና ከፊቱ በጥልፍ የሚጌጥ የአርጐባዎች ባህላዊ ቀሚስ ነው፡፡ ህፃኑ ሲወለድ ለማንሻና ለመጠቅለያ የሚሆን አዲስም ባይሆን ከቤት የተገኘ ጨርቅ ታጥቦና ሽታ ተሞቆ ይቀመጣል (ወ/ሮ ጠይባ ይማም፣ 5/10/2012፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡



**ፎቶግራፍ 10. ጐንደሬ ቀሚስ**

ነፍሰጡሯ ዘጠኝ ወሯ ከገባ በኋላ በዋናነት ቀደም ሲል የቀረቡ የምግብ ግብዓቶችን የማሰናዳት ስራ ይከናወናል፡፡ ተፈትጐ በተቀመጠው ገብስ የገንፎና የአጥሚት እህል[18] ይዘጋጅበታል፤ ተልባው ተወቅጦና ተነፍቶ፣ ከስኳር ጋር ተለውሶ ክዳን ባለው እቃ ይቀመጣል፤ የእንጀራ እህል ጤፍና ማሽላ ተቀላቅሎ ይፈጭና ይቀመጣል፤ የገብስ ቆሎ ተቆልቶ ይቀመጣል፡፡ ለህፃኑ ላንቃ ማንሻ የሚሆን ማር ተቆርጦ ወይም ተገዝቶ፤ የሚውጠው ለጋ ቅቤ ተንጦ ወይም ተገዝቶ ይቀመጣል (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 12/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ሌላው ዝግጅት በወሊድ ወቅት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን አዘጋጅቶ ማስቀመጥ ሲሆን ለእትብት መቁረጫ የሚሆን ምላጭ ተገዝቶና ማተቢያ ማግ ተፈትሎ በሙዳይ ይቀመጣል፡፡ ነፍሰጡሯ ከእነዚህ ከወሊድ በፊት የሚከናወኑ ስራዎች ውስጥ ቀለል ያሉትን የምታከናውን ሲሆን ሌሎች ስራዎችን ከአምሮት ስነ ስርዓት ክዋኔ በኋላ አጠገቧ የሆነችው እናቷ ወይም ሌላ የቤተሰቧ አባል የሆነች ሴት እና ጐረቤቶቿ ይሰሩላታል፡፡ በዚህ ጊዜ የባል ሚና በዋናነት በግብርና ስራ የሚገኙትን ማቅረብና የሚገዙትንም ገንዘብ በመስጠትና ገበያ ሂዶ በመግዛት እንዲሟሉ ማድረግ ነው (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 12/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

[18] ለገንፎ የሚሆነው ገብስ ተቀንሶ ይታመስና ማሽላም ሞቅ ሞቅ ተደርጐ ይደባለቅና ይፈጫል፡፡ ለአጥሚት የሚሆነውም ገብስ ከገንፎው ገብስ ትንሽ ገባ ተደርጐ ይታመስና ተልባ ሞቅ ምቅ ተደርጐ ተደባልቆበት ይፈጫል፡፡

ነፍሰጡሯ ዘጠኝ ወሯ ከገባ በኋላ ፀጉሯን ተሰርታ ትዘጋጃለች፡፡ ነፍሰጡር የመውለጃዋ ቀን ሲቃረብ ስጥቂት የሚባል የብሄረሰቡን ባህላዊ የፀጉር ስራት ትሰራለች፡፡ ስጥቂት ከመካከል ተከፍሎ ወደ ጐንና ወደ ኋላ ጥቅጥቅ ተደርጐ የሚሰራ የፀጉር ስሪት ነው፡፡ ነፍሰጡር አንድ ጊዜ ፀጉሯን በዚህ መልክ ከተሰራች በኋላ ወልዳ የአራስነት ጊዜዋን ጨርሳ በወለደች አርባኛ ቀን የግዴታ እጥበት እስከምታደርግበት አርባኛ ቀን ድረስ ፀጉሯን አትፈታም፤ አትታጠብምም፡፡ ነፍሰጡሯ ፀጉሯን ከተሰራች በኋላ በተደጋጋሚ ፀጉሯን ቅቤ እየተቀባች ፀጉሯ ጥሩ መዓዛ እንዲኖረው ማታ ማታ ፀጉሯን ብቻ አዝጋሮ ታሞቃለች (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 12/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ))፡፡



ፎቶግራፍ 11. ስጥቂት

ነፍሰጡር ሴት የመውለጃዋ ጊዜ ሲደርስ ፀጉሯን ሹሩባ መሰራቷና ሹሩባው ነፍሰጡሯ ከወለደችም በኋላ በአራስነት ጊዜዋ ሁሉ የሚቆይ መሆኑና በአርባኛ ቀን የሚፈታ መሆኑ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው፡፡ ፀጉር ሲሰራ መበጠሩ፣ መፍታታቱ፣ መናፈሱ ይቀርና በሹሩባ መልክ ይቋጠራል፤ ይታሰራል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ አራስ የአራስነት ጊዜዋ እንደ ፍላጐቷ የማትሆንበት፣ ከእለት ተእለት የስራ እንቅስቃሴዋ የምትለይበት፣ በፈለገችው ሰዓት ወደ ውጭ የማትወጣበት፣ ከነፋስና ከመገለጥ የምትጠበቅበት ጊዜ ነው፡፡ በተጨማሪም የአራስነት ጊዜ ማብቂያ ወላዷ በወለደች አርባኛ ቀን ሲሆን ወላዷ ከዚያ በኋላ የአራስነት ጊዜዋ አብቅቶ በመጠኑም ቢሆን ወደ እለት ተእለት ህይወቷ የምትመለስበት፣ ወደ ውጭ ለመውጣት በሰዓት የማትወሰንበት፣ ነፋስ ነካሽ የማትባልበትና ነፃ የምትሆንበት ጊዜ የሚጀምርበት ነው፡፡ ስለሆነም የፀጉር ስራው ወይም ሹሩባው አራስ ላለባት የመጠበቅና

እንደፈቀደች ያለመሆን ሁኔታ፣ የአራስነት ጊዜ ማብቃቱን ተከትሎ መፈታቱ ደግሞ የአራሷን መፈታትና ነፃ መሆንን በትይዩነት የሚያሳይ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው፡፡

ነፍሰጡር ሰባት ወር ከሆናት በኋላ ማታ ማታ ተልባ አዘውትራ እንድትጠጣ ይደረጋል፡፡ ዘጠኝ ወሯ ሲገባም የታመሰ ሱፍ ተወቅጦና ተፈልቶ፣ ወተት ተፈልቶ እንድትጠጣ ይደረጋል፡፡ ተልባ ሰውነትን ስለሚያፍታታ፣ በወሊድ ጊዜ "ምጧን ያገራዋል" ተብሎ ስለሚታመንና የሱፍ ውሃም ከምች ይከላከላል ተብሎ ስለሚታመን ነፍሰጡር በእነዚህ ጊዜዎች እንድታዘወትራቸው ይደረጋል (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 12/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በቅድመ ወሊድ ጊዜ የሀይማኖት አባቶች ዱዓ በማድረግ ትልቅ ሚና አላቸው፤ በአምሮት ስነ ስርዓት ላይ ዱዓ ያደርጋሉ፣ ምጥ በሚጠነክርበት ጊዜም ሰለዋት ይላሉ (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 2/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

### 5.2.2.6. የወሊድ ስነ ስርዓት

በአሁኑ ጊዜ በአካባቢው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለና እየተስፋፋ በመጣው ዘመናዊ የህክምና አገልግሎትና ይህን ተከትሎ ነፍሰጡሮችና ወላዶች በጤና ተቋማት እገዛ እንዲያገኙ በየጊዜው በሚደረገው የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ በቤት ውስጥ የመውለድ አማራጭ ብቻ የነበራቸው እናቶች ወደ ጤና ተቋማት በመሄድ ይወልዳሉ፤ ቅደመ ወሊድ ክትትልም ያደርጋሉ፡፡ በዚህ ጥናት ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው በጤና ተቋማት ቅድመ ወሊድ ክትትል ማድረግንና መውለድን የመረጡ ነፍሰጡሮችና ወላዶች ዘመናዊ ጤና ተቋምን የመረጡበትን ምክንያት አስረድተዋል፡፡ ወ/ሮ አሚና ዝይን ነፍሰጡር ሲሆኑ ቅድመ ወሊድ ክትትል ለማድረግ በሄዱበት በጋቸኔ ጤና ጣቢያ በመስክ ወቅት ወደ ጤና ተቋም ለመምጣት ምክንያት የሆናቸውን ነገር ሲገልጹ "እዚህ መምጣታችን ለሁሉ ነገር ይጠቅማል፡፡ ለደም ብዛት፣ ለደም ማነስ ይፈይዳል ብለን ነው ክትትል የምናደርገው" ብለዋል (21/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ነገር ግን ይህን የሚያደርጉት ሁሉም እናቶች አይደሉም፡፡ ዘመናዊውን የህክምና አገልግሎት ፈልገው የሚሄዱትን ያህል ከልምድ አዋላጆች አቅም በላይ የሆነ ችግር አጋጥሞ ወደ ጤና ተቋማት ለመሄድ ካልተገደዱ በስተቀር በቤታቸው በልምድ አዋላጅ እየታገዙ መውለድ የሚፈልጉ ብዙዎች መሆናቸውን ለማስተዋል ተችሏል፡፡ በመስክ ስራ

ወቅት ተዘዋውሬ ከጠየቅኋቸው ነፍሰጡሮችና እራሶች ብዙዎቹ በቤታቸው ውስጥ በልምድ አዋላጅ እየታገዙ መውለድን የሚመርጡና የመረጡ ናቸው፡፡ ሴቶቹ በቤታቸው መውለድን የመረጡባቸውን የተለያዩ ምክንያቶች የገለፁ ሲሆን ምክንያቶቹ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ሊመደቡ የሚችሉ ናቸው፡፡ አንደኛው ምድብ ሴቶቹ በአካባቢያቸው ያሉ ጤና ተቋማት አሉባቸው ባሏቸው ቀርነቶች ምክንያት በቤታቸው መቆየትንና መውለድን እንዲመርጡ ያደረጓቸውን ምክንያቶች የሚይዝ ሲሆን ሁለተኛው ምድብ ዘመናዊው ህክምና ከብሄረሰቡ ባህላዊ የወሊድ ስነ ስርዓት የተለየ በመሆኑ ምክንያት ሴቶቹ በለመዱት ባህል በቤታቸው መውለድን እንዲመርጡ ያደረጓቸው ምክንያቶች ስብስብ ነው፡፡ ወ/ሮ ጦይባ ይማም በመኖሪያ ቤታቸው የወለዱና በመኖሪያ ቤታቸው በመገኘት ቃለ መጠይቅ ያደረግሁላቸው እራስ ናቸው፡፡ ወ/ሮ ጦይባ በቤታቸው መውለድን የመረጡበትን ምክንያት እንደሚከተለው የገለፁ ሲሆን ምክንያታቸው ለአንደኛው ዓይነት ምድብ ማሳያ የሚሆን ነው፡፡

> ጤና ጣቢያ ሂዶ በህክምና እገዛው ተደስቶ የሚወልድ የለም፡፡ እንዲህ ሆንን እንዲህ ሆንን የሚለው ብዙ ነው፡፡ ከውሀ አቅም ከቤት ወስደው ነው የሚታጠቡት፡፡ ውሀ እንኳን ማግኘት አይቻልም፡፡ ከዚያ ከዚያ አንፃር ያስጠላናል፡፡ እኔ በበኩሌ እዚያ መውለድ አልፈልግም፡፡ እስከሚስተካከል ድረስ አላህ ያግራልኝ እቤቴ እወልዳለሁ፡፡ ያንን በሚል ሶስቱንም ቤቴ ነው የወለድኩት፡፡ … ለክትትልም አልመላለስም ነበር፡፡ አጠቃላይ ሁኔታቸው አይስበኝም ነበር (5/10/2012 ዓ.ም.፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ወላዶች በኖሩበት ባህላዊው የወሊድ ስነ ስርዓት ውስጥ ያሉ እሴቶችን መሻታቸውና ባህላዊውን የወሊድ ስነ ስርዓት ማብለጣቸው በዘመናዊ የህክምና ተቋም ከመውለድ ይልቅ በቤታቸው መውለድን እንዲመርጡ አድርጓቸዋል፡፡ ሌላዋ በቤታቸው የወለዱ እራስ ወ/ሮ ነፊሳ መሐመድ በቤታቸው ለመውለድ የመረጡበትን ምክንያት ሲገልፁ "እዚያ ሲወለድ ምጥ ላይ ተሆኖ እንኳን ሰው ያስገባሉ፤ ሰው ፊት ያጋልጡኛል፡፡ መሸፈን የለም" (12/4/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) ብለዋል፡፡ የወ/ሮ ነፊሳ ምክንያት ለሁለተኛው ምድብ ተጨባጭ የሆነ ማሳያ ነው፡፡ ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም የልምድ አዋላጅ ሲሆኑ ብዙ

ወላዶች በቤት ውስጥ መውለድ የሚፈልጉበትን ምክንያት በተመለከተ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> እዚያ መሄድ አይፈልጉም፡፡ ቤቷ ከሆነ ተጋርዶ፣ ጓዳ ውስጥ፣ ጭለማ ውስጥ ነው የምትወልደው፡፡ እዚያ ከሆነ በቃ ደጅ ነው፡፡ ያንን ነው የሚፈሩት፡፡ እንደገና ደግሞ "ስቲች" እንዳይደረጉ ይፈራሉ፡፡ ስለዚህ ነው ቤት መውለድ የሚፈልጉት፡፡ … እከሊት [የልምድ አዋላጅ የሆነች ሴት] ካለችኝ እቤቴ ነው የምወልደው አልሄድም! የምትል ሴት ሞልታለች፡፡ በዚያ ላይ አንድ አዋላጅ መጥታ ትንሽ ስትለምድ አንስተው ወደ ከተማ ይወስዷታል፡፡ በየጊዜው አዳዲስ ሰዎች ይመጣሉ፣ ሲለምዱ መሄድ ነው! ስለዚህ ወላዶች አይተማመኑም፡፡ ሌላው ደግሞ ወንድ አዋላጆች አሉ፡፡ የሚያውቁን ወንዶች ከሚያዋልዱን ይቅርብን ይላሉ፡፡ ከውርደት ነው የሚቆጥሩት (12/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ወ/ሮ አሚና ነፍሰጡሮች ለወሊድ ወደ ጤና ተቋም መሄድ የማይመርጡባቸውን ሶስት ምክንያቶች ገልፀዋል፡፡ ወ/ሮ አሚና "እዚያ በቃ ደጅ ነው" ማለታቸው በጤና ተቋማት ነፍሰጡሮች የሚወልዱበት ማዋለጃ ቦታ ሴቶቹ ከለመዱትና ሲወልዱበት ከኖሩበት የቤት ውስጥ የመውለጃ ቦታና ክዋኔ አንፃር ሲታይ ቦታው ከደጅ ይቆጠራል ማለታቸው ነው፡፡ ጨረር የሚያስገባ ቀዳዳ ተጠቅጥቆ፣ ስፍራው ጨለማ ተደርጎ፣ ተጋርዶና ቡና ተፈልቶ ወሊድ ከሚከናወንበት ባህላዊ የወሊድ ስነ ስርዓት ተነጥሎ ብርሀን አብዝቶ ባለበትና የቡና ድባብ በሌለበትና ባልተሟሟቀ የጤና ተቋማት ማዋለጃ መውለድ ነው በደጅ እንደመውለድ የተቆጠረው፡፡

ለዚህ ዓይነቱ ችግር መፍትሔ እንዲሆን ይመስላል በጋቸኔ ቀበሌ በሚገኘው ጤና ጣቢያ ለወላዶች ጊዜያዊ ማረፊያ ተብሎ በባህላዊ መንገድ የተሰራ ጐጆ ተመልክቻለሁ (23/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡ ሲ/ር አይሻ በድሩ እንደገለፁት ጐጆው ለወሊድ ወደ ጤና ጣቢያው የሚሄዱ እናቶች እስኪወልዱ ድረስ እንዲያርፉበት ታስቦ የተሰራ ሲሆን በባህላዊ መንገድ የተሰራው ወላዶች የመኖሪያ ቤታቸው ድባብ እንዲሆንላቸው ታስቦ ነው፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ጐጆ ቤቱ የታሰበለትን አገልግሎት እንዲሰጥ አልተደረገም፡፡

ጐጆው የእቃ ግምጃ ቤት ሆኗል፡፡ ጐጆውን ለተሰራበት ዓላማ ማዋል ያልተቻለው ለወላዶች በቆይታቸው የምግብ አቅርቦት ማድረግ ባለመቻሉ ምክንያት ነው (23/2/2013 ዓ.ም.፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡



ፎቶግራፍ 12. አገልግሎት ላይ ያልዋለው ጐጆ

ከዚህ በተጨማሪ በባህሉ ሴቶች እርግዝናቸውን ደብቀው ይይዛሉ እንጂ ይፋ እንዲሆንባቸው አይፈልጉም (ወ/ሮ ሲቲ ፋጡማ መሐመድ፣ 7/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ እርግዝና ሲከሰት ወደ ጤና ጣቢያ ሄደው ክትትል እንዳይጀምሩ የሚያደርግ አንድ ምክንያት ሆኗል፡፡

በመሆኑም ምርጫቸው በቤት ውስጥ መውለድ የሆነ ሴቶች አሁንም በባህላዊ መንገድ በልምድ አዋላጅ ታግዘው በቤት ውስጥ ይወልዳሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አጣዳፊ ምጥ ያጋጠማቸውና ጤና ተቋም መድረስ ያልቻሉ ወላዶች በተለይ በአካባቢው አምቡላንስ ከሌለና ቶሎ መድረስ ካልቻለ በቤት ውስጥ በልምድ አዋላጅ ይወልዳሉ፡፡ ወ/ሮ ፎዚያ ሰዒድ (3/4/2013 ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) በቤት ውስጥ የወለዱት በዚህ ምክንያት መሆኑን "ቤት የወለድኩት አጋጣሚ ነው፡፡ አመመኝና ወዲያው ተወለደ፡፡ ብዙ አልቆየም … ሲያመኝ ጐረቤት አዋላጅ ነበረች እሷ ተጠራች፡፡ ወደዛው ተወለደ ልጁ፡፡ … ክትትልም አልነበረኝም" በማለት ገልፀዋል፡፡ ከዚህ በታች የአርጐባዎች ባህላዊ የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ ቀርቧል፡፡

ነፍሰጡሯ የምትወልድበት ቀን ደርሶ የህመም ስሜት ሲሰማት በአካባቢው የምትገኝ የልምድ አዋላጅ ትጠራለች፡፡ ምጥ እግር አይወድም፣ ይመለሳል የሚል እምነት ያለ በመሆኑ ምክንያት የወሊድ ስነ ስርዓት በሚከናወንበት ቤት ውስጥ ከልምድ አዋላጅና ከቤተሰብ አባላት ውጭ ያሉ ሰዎች እንዲሰበሰቡና ሰው እንዲበዛ አይፈለግም፡፡ በመሆኑም ወደ ልምድ አዋላጇ በመሄድ ብቻ ቀለል ተደርጐ "ብቅ በይ" ብቻ ትባላለች፡፡ ለጐረቤት የሚነገረው ነፍሰጡሯ ከወለደች በኋላ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ጐረቤቶች የወሊድ ስነ ስርዓት ባለበት ቤት የሚገኙ ከሆነ ይህ በሁለት ምክንያቶች ሊሆን ይችላል፡፡ አንደኛው ምክንያት የወላዷን ምጥ የሰማች የቅርብ ጐረቤት ለሌሎች አሰምታ ከሆነ ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት የወላዷ ምጥ ሲጠነክር ሰዎች ዱዓ እንዲያደርጉ ተጠርተው ከሆነ ነው (ወ/ሮ ኢና ሙጋ፣ 10/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በአርጐባዎች ባህል መሰረት አንዲት ሴት የምትወልደው በጓዳ ውስጥ ሲሆን የምትኖርበት ቤት ክፍል አንድ ብቻ ከሆነ እዚያው ክፍል ውስጥ ተጋርዶ ትወልዳለች፡፡ የምትወልደው ፍራሽ በሌለው ድንክ አልጋ ላይ ሲሆን ስትወልድ የሚኖረው ፈሳሽና ስትታጠብ የሚፈሰው ውሃ ቤቱን እንዳያበላሽ ከአልጋው ስር ጉድጓድ ተቆፍሮ ይዘጋጅና ከወለደችና ከታጠበች በኋላ አፈሩ ተመልሶ ጉድጓዱ ይደፈናል (ወ/ሮ ኢና ሙጋ፣ 10/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በወሊድ ጊዜ ነፍሰጡሯ በሁለት መልኩ ልትሆን ትችላለች፡፡ አንደኛው በቀኝ ወይም በግራ ጐኗ ተኝታ፣ የልምድ አዋላጇ ደግሞ ከግርጌ ሆና እየረዳቻትና ከራስጌ አንድ ሌላ ሴት እየደገፈቻት፣ ስትወልድ ደግሞ ሌላ ሴት ከላይ ያለውን እግሯን ከጉልበቷ ከፍ በማድረግ ይዛ የምትወልድበት ሁኔታ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አልጋው ላይ ድንጋይ ተደርጐና እዚያ ላይ ጨርቅ ተደልድሎ ወላዷ እዚያ ላይ ቁጭ ብላ፣ የልምድ አዋላጇ ከግርጌ ሆና፣ ሌላ ሴት ከጀርባዋ በኩል ሆና ትከሻዋንና ወገቧን በመደገፍ የምትወልድበት ነው፡፡ በጀርባ መተኛት ጽንሱን ወደ ታች ከመምጣት ይልቅ ወደ ላይ ከፍ ያደርገዋል፣ እትብቱ በጽንሱ አንገት ላይ እንዲጠመጠም ያደርጋል ተብሎ ስለሚታመን ወላድ በጀርባዋ ተኝታ አትወልድም (ወ/ሮ ሞሚና መሐመድ፣ 19/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የልምድ አዋላጇ ከግርጌ ቁጭ በማለት የነፍሰጡሯን ሆድ ቅቤ እየቀባች የህመምና የምጥ ሁኔታዋን ትከታተላለች፣ ወላዷ ማድረግ ያለባትንና የሌለባትን እየነገረች ትመክራታለች፣ ወላዷ ትንፋሿን ወደ ውስጥ ማድረግ እንዳለባት፣ ወደላይ ወደላይ መተንፈስ እንደሌለባት፣

መጮህና መጠማዘዝ እንደሌለባት፣ ማማጥ በማይገባት ሰዓት ማማጥ እንደሌለባት ትነግራታለች፡፡ ወላዷ ከላይ በተገለፀው መንገድ ቁጭ ብላ የምታምጥ ከሆነ ድካም ሲሰማት ትንሽ ጊዜ በጐኗ እንድትተኛ ትደረጋለች፡፡ ወላዷ ምጧ ገና ከሆነና አቅም ካላት አልፎ አልፎ እየተነሳች ቤቱ ውስጥ እንድትንቀሳቀስ ትደረጋለች፡፡ ምጧ እየበረታ ሄዶ የእሽርት ውሃ ሲቃረብ ግን ከአልጋ ላይ እንዳትነሳ ትከለከላለች፡፡ የልምድ አዋላጆች የእንሽርት ውሃ መቅረቡን የጽንሱን ግፊት በማጤን ይለዩታል፡፡ ከዚያ በኋላ ወላዷ አልጋው ላይ በመሆን ታምጣለች፤ የልምድ አዋላጇ የህመሙ ስሜት ሲመጣ እንድታምጥና ወደ ታች እንድትጫን፣ ህመሙ ቀለል ሲል ደግሞ ትንፋሿን እንድትሰበስብ ትነግራታለች፡፡ ሌሎች ሴቶችም ድርሻቸውን ለመወጣት ይዘጋጃሉ፡፡ በወሊድ ጊዜ የአንድ የልምድ አዋላጅ መገኘት በቂ ሲሆን ከፍ ሲል እንደተገለፀው ወላዷን የሚደግፉና ወላዷ ከወለደችም በኋላ ወላዷንና ህፃኑን በማጠብ አዋላጇን የሚያግዙ ሁለት ወይም ሶስት ሴቶች ይኖራሉ (ወ/ሮ ሞሚና መሐመድ፣ 19/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የልምድ አዋላጆች የማዋለድንና ነፍሰጡርን የመርዳት እውቀትን ያገኙት ከዘመናዊ ትምህርት ሳይሆን ከአያት፣ ከእናት በተላለፈ እውቀትና በማየት፣ በመስማትና በመተግበር ልምድ ነው፡፡ ከመረጃ ሰጪዎች አንዷ ወ/ሮ አይከዷጅ መሐመድ የልምድ አዋላጅ ናቸው፡፡ ወ/ሮ አይከዷጅ ማዋለድ የጀመሩበት ጊዜ ከ40 ዓመት በፊት ጀምሮ መሆኑን በመግለጽ ማዋለድ የጀመሩት በአጋጣሚ መሆኑን ነግረውኛል፡፡ እርሳቸው እንደሚሉት ከ40 ዓመት በፊት በመንደራቸው አንዲት ሴት ምጥ ይይዛታል፡፡ በወቅቱ በአካባቢው የነበሩ አዋላጅ አንድ ብቻ የነበሩ ሲሆን በጊዜው ከመንደሩ ርቀው ሄደው ነበር፡፡ ነገሩ ጭንቅ ሲሆን ወላዷን ለመርዳት ገብተው ሲነገር የሰሙትን በመተግበር እንዳዋለዷትና ከዚያ በኋላ ማዋለድ እንደጀመሩ ገልፀዋል (28/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የልምድ አዋላጆች ነፍሰጡሮችንና ወላዶችን በመርዳት ትልቅ እገዛ ያደርጋሉ፡፡ ነፍሰጡር ከጽንሱ ጋር በተያያዘ እክል ወይም ህመም ሲያጋጥማት በአካባቢው የምትኖርን የልምድ አዋላጅ በመጥራት እርዳታ እንድታደርግላት ታደርጋለች፡፡ የልምድ አዋላጆች በእርግዝና ጊዜ ለእርዳታ ሲጠሩ በዋናነት ሁለት ነገሮችን ይመለከታሉ፡፡ አንደኛው የጽንሱን አቀማመጥ ሲሆን ሁለተኛው የጽንሱን እንቅስቃሴ ነው፡፡ የልምድ አዋላጆች በእጅ በመዳበስ እነዚህን ነገሮች ከተመለከቱ በኋላ ጽንሱ የተስተካከለ አቀማመጥ ከሌለው

አቀማመጡን ያስተካክላሉ፤ የጽንሱ እንቅስቃሴ ደካማ ነው ብለው ሲያስቡ ደግሞ ይህ የሆነው በነፍሰጡሯ አላግባብ የሆነ እንቅስቃሴ (ለምሳሌ፣ ሸክም ማብዛት) ምክንያት ከሆነ ለነፍሰጡሯ የተከለከሉ ነገሮችን እንዳታደርግ ይመክራሉ፤ ሁኔታው የከፋ ሲመስላቸው ግን ነፍሰጡሯ ወደ ጤና ተቋም እንድትሄድና እንድትመረመር ይመክራሉ፡፡ አሳሳቢ ችግር በማይኖርበት ጊዜም ለነፍሰጡሯ የህመም ስሜት አስከትሏል የሚሉትን ነገር በመግለጽ ነፍሰጡሯ በአመጋገብና በጠቅላላ እንቅስቃሴ ረገድ ማድረግ ያለባትንና የሌለባትን በመግለጽ ምክር ይሰጧታል (ወ/ሮ ሞሚና መሐመድ፣ 19/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በወሊድ ጊዜም የልምድ አዋላጆች ትልቅ ሚና አላቸው፡፡ በማዋለድ ስራ ችግር ከሌለበት ወሊድ ጀምሮ ከባድ ችግር እስካለበት ወሊድ ድረስ ወላዶችን ይረዳሉ፤ ነገር ግን ከአቅም በላይ የሆነ ነገር ሲገጥም ወላዷ ወደ ጤና ተቋም እንድትሄድ ያደርጋሉ፡፡ የልምድ አዋላጆች ከአቅማችን በላይ ነው ከሚሏቸው ሁኔታዎች ውስጥ ዋናው ከወሊድ በፊት የደም መፍሰስ ማጋጠም ነው፡፡ ችግሩ በወረዳው ጤና ተቋማት የሚፈታ ከሆነ አዋላጅ ነርሶች እገዛ ያደርጋሉ፤ ነገር ግን ችግሩ ከእነርሱም አቅም በላይ ከሆነ ወላዷ ወደ ደብረ ብርሃን ሪፌራል ሆስፒታል እንድትሄድ ያደርጋሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በጤና ተቋማት ለመውለድ የመረጡም ሆነ አጋጣሚ ያስገደዳቸው ወላዶች ወደ ጤና ተቋማቱ የሚሄዱት የልምድ አዋላጆችን አስከትለው ነው፡፡ በጤና ተቋማት ያሉ አዋላጅ ነርሶች የልምድ አዋላጆች በማዋለጃ ክፍል እንዲገኙ የሚፈቅዱ በመሆኑ የልምድ አዋላጆች ወላዷን ይደግፋሉ፤ አዋላጅ ነርሶችንም በማዋለድ ስራው ያግዛሉ (ወ/ሮ ሞሚና መሐመድ፣ 19/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የማዋለድ እውቀት ከአዋላጅ አዋላጅ የሚለያይ ቢሆንም ሙያውን በአግባቡ የሚያውቁ የልምድ አዋላጆች በእርግዝና ጊዜ የጽንሱ አቀማመጥ አለአግባብ ሲሆን ያስተካክላሉ፤ በወሊድ ጊዜ የጽንሱ አመጣጥ ያልተስተካከለ ከሆነ ጽንሱን መልሰውና አስተካክለው ያዋልዳሉ፤ ጽንሱ ላይ እትብት ተጠምጥሞ በወሊድ ጊዜ አስቸጋሪ ሁኔታ ቢገጥም እትብቱን አፍታተው እንዲወለድ ያደርጋሉ፤ በወሊድ ጊዜ የጽንሱ አመጣጥ አለአግባብ ሲሆን ወላዷን በጭንቅላቷ በመዘቅዘቅ ጽንሱ ተገልብጦ በትክክለኛው አመጣጥ እንዲመጣ ያደርጋሉ (ወ/ሮ ሞሚና መሐመድ፣ 19/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በአካባቢው የሚገኝ አንድ ግብረ ሰናይ ድርጅት ለልምድ አዋላጆች በጤና አጠባበቅና በማዋለድ ስራ ላይ ተከታታይነት ያለው ስልጠና ሰጥቷል፡፡ የልምድ አዋላጆች የሆኑ መረጃ ሰጪዎቼ (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 11/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) (ወ/ሮ ሞሚና መሐመድ፣ 19/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) እንደገለፁት በስልጠናው በማዋለድ ጊዜ የራስን ንጽህና ጠብቆ መገኘት እንደሚያስፈልግ፣ የእጅ ጓንት መጠቀም እንደሚያስፈልግ፣ የራሳቸውንና የወላዷን ጤና እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው፣ ወዘተ ስልጠናን አግኝተዋል፤ የተለያዩ የማዋለጃ ቁሳቁሶችንም አግኝተዋል፡፡ አዋላጆቹ የተሰጣቸውን ስልጠና ከራሳቸው እውቀት ጋር እያዛመዱ በተግባር ላይ እያዋሉ እንደሆነና የተሰጧቸውን የማዋለጃ ቁሳቁሶች እየተጠቀሙባቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በየስድስት ወሩ የሚሰጠው ስልጠና ግን ከጊዜ በኋላ እንደተቋረጠም ገልፀዋል፡፡

ነፍሰጡሯ በምታምጥበት ጊዜ በቤቱ ውስጥ የሞቀ ጨዋታና ጫጫታ እንዲኖር አይፈቀድም፡፡ ጨዋታ በሌለበት ሁኔታ ነፍሰጡሯ ምጧ እንዲገራና በሰላም እንድትገላገል የምጥ አግሪዎቹ ስም እየተጠራ ልመና ይደረጋል፡፡ በቤቱ ውስጥ የተሰበሰቡ ሴቶች “ጊስቴ ፋጡማዬ፣ ጊስቴ ፋጡማዬ፣ ያባዲገዝ፣ ያባዲገዝ እንተጋገዝ” እያሉ ይለምናሉ፡፡ ባዲገዝ ሀገሩን፣ አካባቢውን ከክፉ ሁሉ እንደሚጠብቅና መልካሙን እንደሚያመጣ የሚታመንበት መንፈሳዊ መሪ ሲሆን እንደየአካባቢው የተለያየ ባዲገዝ ይኖራል፡፡ ከዚያ በኋላ ዱዓ ለማድረግ ቡና ይፈላል፡፡ የሚፈላው ቡና ምጥን ያገራሉ ተብለው በሚታመንባቸው ስም ነፍሰጡሯ እስክትወልድ ድረስ እየተደጋገመ ይፈላል (ወ/ሮ ነፊሳ አህመድ፣ 16/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በቅድሚያ የሚፈላው ቡና የሲቲና ፋጡማ ቡና ተብሎ ነው፡፡ በመሆኑም የሚፈላውን ቡና መጀመሪያ ነፍሰጡሯ እንድትጨብጠው ይደረግና በሚቆላበት ምጣድ ላይ ተደርጎ ትንሽ ጊዜ እንዲቆይ ከተደረገ በኋላ ተቆልቶ ከነምጣዱ በወላዷ አልጋ ስር ይገባና ጭሱ እንዲጨስባት ይደረጋል፡፡ ምጥ ሲበረታ ወላዷ ግብር መገበር ያስለመደችው ነገር ግን ያሳለፈችበት አውሊያ ካለ ብር ትጨብጥና የአውሊያውን ስም ጠርታ ከጭንቋ እንዲገላግላት ትለምናለች (ወ/ሮ ነፊሳ አህመድ፣ 16/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ወላዷ ቡናውን እንድትጨብጠው ማድረጉና ቡናው ምጣድ ላይ ከተደረገም በኋላ ትንሽ ጊዜ መጠበቁ ትዕምርታዊ ድርጊቶች ናቸው፡፡ ወላዷ ቡናውን ጨብጣ መቆየቷ በስማቸው ቡና የተፈላላቸውን አማላጆች አማልዱኝ፣ እርዱኝ ማለት፣ መለመን፣

መማፀን ሲሆን ቡናውን በምጣድ ላይ አድርጐ መቆየት የአማላጆቹን ምልጃና እርዳታ የመጠበቅ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው፡፡ ወላዷ ጭሱ እንዲጨስባት የሚደረገው ቡናው የተፈላው በምጥ አግሪዋ በፋጡማ ስም በመሆኑ ጭሱ ወላዷ ቶሎ እንድትወልድ ይረዳታል በሚል እምነት ምክንያት ነው፡፡ ብሩን ጨብጣ መያዟም ቡናውን እንደመጨበጥ ሁሉ የመማፀን ድርጊት ነው፡፡

ቡናው ሲፈላ ዱዓ ይደረጋል፡፡ ይህን ለማድረግ ቡናው ፈልቶ እንደወረደ ቡናውን ያፈላችው ሴት "አቦል ጀባ" ትላለች፡፡ በዚህ ጊዜ ከተሰበሰቡት ሴቶች መካከል በዱዓ አድራጊነቷ የምትታወቅ ወይም በእድሜ ከፍ የምትል ሴት ዱዓውን ትጀምርና ሌሎቹ ሴቶች "አሚን" እያሉ ይቀበላሉ (ወ/ሮ ነፊሳ አህመድ፣ 16/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ቡናውን ያፈላችው ሴት "አቦል ጀባ" ማለቷ ቡናው መፍላቱን ማሳወቂያና ዱዓ እንዲደረግ መጋበዣም ነው፡፡ የሚከተለው ዱዓ በዚህ ጊዜ ከሚደረጉ ዱዓዎች ውስጥ ሲሆን በቡድን ተኮር ውይይት ጊዜ ወ/ሮ ሶህሊየት ባቢ የመሩትና ሌሎቹ ሴት ተወያዮች "አሚን" በማለት የተቀበሉት ነው (30/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቡድን ተኮር ውይይት)፡፡

| <u>ዱዓ አድራጊ</u> | <u>ተቀባዮች</u> |
|---|---|
| ሀጃዋን አላህ ያውጣው | አሚን |
| ከሙሰሪፍ | " |
| ተቁጥቡ | " |
| ግጥም አላህ ያርጋት | " |
| በደህና | " |
| የምትወጣ | " |
| አላህ ያርጋት | " |

አኋሁ መሰሊ ወሰሊም አላ ሰይድና መሐመድ ወአላ አሊ ሰይድና መሐመድ

ዱዓው ካለቀ በኋላ ሴቶቹ ይዘያየሩና ከቡናው መጀመሪያ ቀድተው ለወላዷ ያቀምሷታል፡፡ ቡናው የተፈላው በፋጡማ ስም በመሆኑ መጀመሪያ የተቀዳውን መቅመሷ ምጧን ያገራዋል፣ ቶሎ እንድትወልድ ይረዳታል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከዚያ በኋላ የቡና ቁርስ እንጀራ በበርበሬ ይቀርብና ቡናው ለሁሉም ተቀድቶ ሰለዋት የሚሉ ወንዶች ካሉ ከቁርሱም ተደርጐ ቡናው ይላክላቸዋል፤ የተሰበሰቡ ሴቶችም ቁርሱን ቀምሰው ቡናውን ይጠጣሉ፡፡ ከዚያ በኋላም ወላዷ እስክትወልድ ድረስ ቡና እየተፈላና መጀመሪያ የተቀዳው ለነፍሰጡሯ እየተሰጣት ይቆያል፡፡ ከዚህ ውጭ ነፍሰጡሯ ሞቅ ያለ ነገር ለምሳሌ፣ ተልባ ተሞቆ፣ አጥሚት በቅቤ ተደርጐ እንድትጠጣ ይደረጋል (ወ/ሮ ነፊሳ አህመድ፣ 16/2/2013፣ ጋቹኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በዚህ መልኩ ቡና እየተፈላና እየተለመነ ወላዷ በምትጠበቅበት ጊዜ የተወሰኑ የወላዷ ቤተሰብ አባላትና ጐረቤቶች ነፍሰጡሯ ከወለደች በኋላ ለሚመጡ ጠያቂዎች ማስተናገጃ የሚሆን ምግብ ያዘጋጃሉ፤ እንጀራ ይጋግራሉ፣ ወጥ ይሰራሉ (ወ/ሮ ነፊሳ አህመድ፣ 16/2/2013፣ ጋቹኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የወሊድ ስነ ስርዓት በሚከወንበት ቤት እንዲገቡ የማይፈቀድላቸው ወንዶች፣ የሰው ዓይን አለባቸው ተብለው የሚጠረጠሩ ሰዎችና ነፍሰጡሮች ናቸው፡፡ የወላዷን ባለቤት ጨምሮ ምናልባት የተሰበሰቡ ቤተሰብ ወይም ጐረቤት የሆኑ ወንዶች ካሉ የሚቀመጡት ከወሊዱ ቤት ውጭ ባለ ሌላ ክፍል ውስጥ ወይም ጥላ እንዲሆናቸው በደጅ አነስተኛ ዳስ በመጣል ነው፡፡ ነገር ግን ምናልባት ወላዷ የሰው ዓይን ኖሮባት በምጡ ጊዜ ህመሙ ተነስቶባት ከሆነና ምጧ ከበረታ ቁርዓን የሚቀራ ወንድ እንዲገባ ይደረጋል፡፡ የሰው ዓይን አለባቸው ተብለው የሚጠረጠሩ ሰዎች ከደጅ እንዲመለሱ ይደረጋሉ፡፡ ነፍሰጡሮች ወላዷ ስታምጥ ይጨነቃሉ ስለሚባል ወደ ቤት ውስጥ እንዲገቡ አይፈቀድላቸውም (ወ/ሮ አሚና ዝይን፣ 21/2/2013፣ ጋቹኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ምጥ ሲበረታ መፍትሄ ይሆናሉ ተብለው የሚታመንባቸው እምነታዊ ድርጊቶች የሚከወኑ ሲሆን ወንድ ሰው ይገባና የወላዷን እጅ ወይም ራስ ይዞ ቁርዓን ይቀራባታል፤ የተሰበሰቡ ወንዶች ዱዓ ያደርጋሉ፤ ሰለዋት ይላሉ፤ ዱዓ የተደረገበት ጫት ታሽቶ፣ ተጨምቆና በውሃ ተበጥብጦ ይርከፈከፍባታል፤ የቁርዓን ቃል በሉህ ላይ ተጽፎ ይታጠብና እንድትጠጣው ይደረጋል፤ ለጋ ቅቤ ቀርቦ ሁሉም "እንትፍትፍ" ይሉበትና ሆዷ ይቀባል፡፡ ምጥ የጠናው ወላዷ የሰው ዓይን ህመም ኖሮባትና በምጥ ጊዜ ተነስቶባት ነው ተብሎ ከታመነ ደግሞ

ቁርዓን ከመቅራት በተጨማሪ እውቀቱ ባለው ሰው ጽህፈት ተጽፎ በጭኗ ላይ ይታሰራል፤ በአካባቢው የባህላዊ መድኃኒት እውቀት ካላቸው ሰዎችና ከሌሎችም ዘንድ የሚገኝ ከሆነ የአንበሳ ፀጉር ወይም የጉማሬ ቆዳ ይጨሳል (አቶ አደም መሐመድ፣ 4/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በአካባቢው ፈቂ አህመድ፣ ጀሚል አውሊያና ጀይላኒ የሚባሉ አውሊያዎችን በየመገበሪያ ጊዜዎቻቸው የመገበር ልማድ ያለ ሲሆን ግብር ያስለመዱትን አውሊያ የለመደውን አለማድረግ ምጥን ያጠናል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ወላዷ በተወሰነ ጊዜ የምትገብርለት አውሊያ ኖሮ ሳትገብር ካሳለፈችና ምጡ የጠናው በዚያ ምክንያት ሊሆን ይችላል ተብሎ ሲታሰብ ነፍሰጡሯ ብር ትጨብጥና የአውሊያውን ስም በመጥራት "አንተ ገላግለኝ፣ አንተ ደግፈኝ፣ ያስለመድኩህን አደርጋለሁ" ብላ ሆዷን አባብሳበት ብሩ ይቀመጣል፡፡ የምትገባው ቃል ምጧን ያገራል ተብሎ ይታመናል፡፡ የሚቀመጠው ብርም ተጨምሮበት የመገበሪያ ጊዜው ሲደርስ ወላዷ የምታደርገውን ግብር ለማድረጊያነት የምትጠቀምበት ይሆናል (ወ/ሮ አይከዲጅ መሐመድ፣ 28/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ምጥ ሲጠነክር ከሚደረጉ እምነታዊ መሰረት ካላቸው ድርጊቶች በተጨማሪ ወላዷ ጽንሱን ወደ ታች መግፋት ያስችሏታል ተብለው የሚታሰቡ ልማዳዊ ድርጊቶች ይደረጋሉ፡፡ አንደኛው ነፍሰጡሯ ውስጡ ክፍት የሆነ የእሳት ማንደጃ ሸንበቆ ከአንድ በኩል በእጅ ተደፍኖ በትንፋሿ "እፍፍ" እንድትል ማድረግ ነው፡፡ ሁለተኛው ወላዷ እንዲያስነጥሳት ቀይ ሽንኩርት ተከትፎና በእንጀራ ተጠቅልሎ እንድትበላ ማድረግ ሲሆን ይህ የማያስነጥሳት ከሆነ በሶስተኛነት የሽንኩርቱ ልጣጭ እሳት ላይ ተደርጐ ጭሱን እንድትታጠንና እንዲያስነጥሳት ይደረጋል (ወ/ሮ አይከዲጅ መሐመድ፣ 28/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ምጥ ተፋፍሞ የእሽርት ውሀ ከፈሰሰ በኋላ ትንሽ ተጠብቆ ልጁ ይመጣል ተብሎ ይታመናል፡፡ የልምድ አዋላጇ ህፃኑን በጨርቅ ትቀበለውና አልጋው ላይ ታስቀምጠዋለች፤ ከዚያ በኋላ እትብቱን ትቆርጣለች፡፡ እትብት የሚቆረጠው መጀመሪያ ወደ ህፃኑ ሶስት ጣት ተትቶ በማግ ይቋጠርና ሁለት ጣት ታልፎ ከእናት በኩል እንደገና ይታሰርና መካከል ላይ በምላጭ ይቆረጣል፡፡ ከዚያ በኋላ አዋላጇ የእንግዴ ልጁ ተመልሶ ወደ ውስጥ እንዳይገባ ከእናት በኩል ያለውን እትብት በወላዷ ጭን ላይ በማግ ታስረዋለች፡፡ የእንግዴ

ልጁ እንዲወርድ ሆዷን እያሸቻት እስኪወርድ ድረስ ትጠብቃለች፡፡ ወላዷ እንደተገላገለች የተሰበሰቡ ሴቶች በሙሉ "አላህምዱሊላህ" እያሉ ይዘያየራሉ፡፡ የወላዷና የባለቤቷ ዘመዶች የተወለደው ልጅ ወንድ ከሆነ ብዙ ጥይት ይተኩሳሉ፤ ሴት ከሆነች ለወንድ ልጅ የሚተኮሰውን ጥይት ያህል ባይሆንም መተኮሳቸው ግን አይቀርም (ወ/ሮ አይከዲጅ መሐመድ፣ 28/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ህፃኑ እንደተወለደ ወላዷ ውሃ እንድትጠጣ ትደረጋለች፡፡ ውሀ የእንግዴ ልጁን "ይገድለውና" ቶሎ እንዲወርድ ያደርገዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ወላዷ ከወለደች በኋላ የእንግዴ ልጁ ከቆየ ወይም መነቅነቅ አስለምዳ ከሆነ ወንድ ሰው እንዲነቀንቃት ይደረጋል፡፡ መነቅነቅ ማለት ወላዷ መሬት ላይ ትወርድና ወገቧ ላይ የሙዳይ ክዳን ተደፍቶና የሚነቀንቃት ሰው ከኋላዋ በመሆን የሙዳዩን ክዳን በእግሩ አጣብቆ በመያዝና እጆቹን በእጅና በእጇ ስር በማስገባት በተደጋጋሚ ወላዷን በመጠኑ ብድግ በማድረግና በመነቅነቅ፤ ከዚያም ወላዷን ወደ መሬት በመልቀቅ የእንግዴ ልጁ እንዲወርድ ለማድረግ የሚተገበር ልማድ ነው (ወ/ሮ አይከዲጅ መሐመድ፣ 28/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የእንግዴ ልጅ ቢዘገይ ወላዷ የምትቀምሰውና የምታስረው ባህላዊ መድኃኒት ይሰጣታል፡፡ አቶ አደም መሐመድ እንደገለፁት የመጀመሪያው መድኃኒት የጋሜ ቅጠል ነው፡፡ የጋሜ ተክል ቅጠሉ ተጨምቆና በውሀ ተበጥብጦ እንድትጠጣ ይደረጋል፡፡ አቶ አደም እንደገለፁት (5/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) እንግዴ ልጅ እስኪወርድ ድረስ ህይወት ያለው በመሆኑ ወላዷ የጋሜ ቅጠል ጭማቂውን ስትጠጣ ወደታች መውረድ ሲገባው ወደላይ እየዘለለ የሚንፈራገጠውን የእንግዴ ልጅ ያደክመውና ወደታች እንዲመጣና እንዲወርድ ያደርገዋል፡፡ ሁለተኛው መድኃኒት መዥርጥ የሚባል ቅጠል ሲሆን በወላዷ ጭን ላይ ይታሰራል፡፡

የእንግዴ ልጁ ሲወርድ አዋላጇ በቅል ትቀበለውና እትብቱ የተቆረጠበት ምላጭ ከእንግዴ ልጁ ጋር አብሮ ስለሚቀበር ምላጩን እላዩ ላይ ታደርገዋለች፡፡ ከዚያ በኋላ ወላዷ ጭን ላይ የታሰረው ተፈትቶ የእንግዴ ልጁ እንዲቀበር ይላካል፡፡ አንዷ ሴት የእንግዴ ልጁን ለመቅበር ስትወስድ በቅደም ተከተል ህፃኑና ወላዷ በሳሙናና ለብ ባለ ውሃ እዚያው ድንክ አልጋው ላይ ታጥበው ገላቸውን ቅቤ ይቀባሉ፡፡ የሚያጥቧቸውና ቅቤ የሚቀቧቸው የልምድ አዋላጇና በወሊዱ ላይ ሲረዱ የነበሩ ሴቶች ናቸው፡፡ ከዚያ በኋላ ወላዷና ህፃኑ ታጥቦና

ተሞቆ የተዘጋጀውን ንፁህ ልብስ ይለብሳሉ፡፡ አልጋው እዚያው እንዳለ ይታጠብና ሲያበቃ ከአልጋው ስር ለፍሳሽ ተብሎ የተቆፈረው ጉድጓድ አፈሩ እየተመለሰ ተደፍኖ ወላዷ ከእነልጇ አልጋው ላይ ይተኛሉ፡፡ አዝጋሮ[19] በጋቻ ላይ ተደርጎ አልጋው ስር ይጨሳል፡፡ ከዚያ በኋላ አዋላጇ ራሷ ትታጠብና የወላዷ ዘመዶች ቅቤና ሽቶ ይቀቧታል፤ አዝጋሮ ያሞቋታል፡፡ ወላዷ የወለደችበት የቆሸሸ ጨርቅ ወደ ውጭ ይወጣና የወላዷ የቤተሰብ አባል ማለትም እናቷ፣ እህቷ ወይም ባለቤቷ ያጥቡታል (ወ/ሮ አይከዲጅ መሐመድ፣ 28/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በአርጎባዎች ዘንድ ከሴት ልጅ ይልቅ የወንድ ልጅ መወለድ ይመረጣል፡፡ የሚከተለው ምሳሌያዊ አነጋገር የብሄረሰቡ አባላትን የፆታ ምርጫ በተመለከተ የሚያስተላልፈው መልዕክት አለ፡፡

- ሴት በዛ ምን ረባ (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 29/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ መደበኛ ያልሆነ ቡድን ተኮር ውይይት)፡፡

በብሄረሰቡ የጋብቻ ስነ ስርዓት ሴት ልጅ ስታገባ ኑሮዋ የሚሆነው በትዳር አጋሯና በቤተሰቡ አካባቢ ነው፡፡ ወንድ ልጅ ደግሞ በቤተሰቦቹ አካባቢ ጎጆ ቀልሶ ቢያገባም ሚስቱን በማምጣት በቤተሰቡ አካባቢ ይኖራል፡፡ በቤተሰቡ አካባቢም ጋሻ ሆኖ ይኖራል፣ ቤተሰብን ይደግፋል፣ ይጦራል፣ ጥቃትን ይመከታል ተብሎም ይታመናል፡፡ በዚህ ምክንያት በብሄረሰቡ አባላት ዘንድ ልጅ ሲወለድ መኖሪያዋ በአማቾቿ አካባቢ ከሚሆነው ከሴት ልጅ ይልቅ እስከመጨረሻው የቤተሰቡን አካባቢ አስከብሮ የሚኖረው ወንድ ልጅ እንዲወለድ ይፈለጋል፡፡ ይህ ምሳሌያዊ አነጋገርም የሚገልፀው ይህንኑ ሀሳብ ነው፡፡

በመሆኑም ወንድ ልጅ ሲወለድ ብዙ ጥይት ይተኮሳል፤ በአንፃሩ የተወለደችው ሴት ከሆነች ወላዷ መውለዷን ይፋ ለማድረግ ብቻ ቁጥሩ ወንድ ልጅ ሲወለድ ከሚተኮሰው የጥይት መጠን ያነሰ ጥይት ይተኮሳል፡፡ ለወንድ ልጅ መወለድ ትልቅ ቦታ የሚሰጥ በመሆኑ ምክንያት በአምሮትና በጉፍታ[20] ስነ ስርዓት ክዋኔዎች ላይ የሚወለደው ልጅ ወንድ እንዲሆን የመሻት መሰረት ያላቸው ዱዓዎች ይደረጋሉ፡፡ በአምሮት ስነ ስርዓት ላይ

[19] ጥሩ ጠረን ያለው፣ ግንዱ ተፈልጦ ቤት ውስጥ የሚጨስ፣ ያገባች ሴት የምትሞቀውና ልብሷንም የምታሞቅበት ተክል

[20] በሰርግ ቀን ሙሽራዋ በራሷ ላይ የሚታሰርላትና ባለትዳር መሆኗን የሚገልጽ ሻሽ ሲሆን ስነ ስርዓቱ ይህን ሻሽ የማሰር ስነ ስርዓት ነው፡፡

“ልጁም ወንድ ይሁን ምጡም ገር ይሁን” (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 17/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ) እና “ወንዱን! ወንዱን! ወንዱን! ምጡ እማይጠናውን [ይስጣት]” (ወ/ሮ በድሪያ መሐመድ፣ 17/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ) ተብሎ ዱዓ ሲደረግና በጉፍታ ስነ ስርዓት ክዋኔ ላይም “የወንድ ልጅ እናት አላህ ያርጋት” (ወ/ሮ አይኔ ይማሙ፣ 23/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ምልከታ) ተብሎ ዱዓ ሲደረግ በምልከታ መታዘብ ተችሏል፡፡

5.2.2.7. ላንቃ ማንሳት

ህፃኑ ከተወለደ በኋላ ላንቃው ይነሳል፡፡ ላንቃ ማንሳት ማለት ህፃኑ ሲወለድ በጣት ትንሽ ማር በመቆንጠር የህፃኑን ላንቃ ወደ ላይ ማሸት ሲሆን ይህ የሚደረገው ህፃን ሲወለድ ላንቃው ወደ ታች የወረደ ነው ተብሎ የሚታመን በመሆኑ፤ በዚህ መልኩ ላንቃው ካልተነሳ ወደፊት ትንታ ያጠቃዋል፣ ሲያወራ ይነፋነፋል፣ ጥሩ ድምጽ አይኖረውም ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ የህፃኑን ላንቃ የምታነሳው አዋላጇ ነች፡፡ ህፃኑ ላንቃው ከተነሳ በኋላ ለጋ ቅቤ እንዲውጥና ጡት እንዲጠባ ተደርጎ እንዲተኛ ይደረጋል (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 12/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ማር ለላንቃ ማንሻነት የተመረጠው በዘፈቀደ አይመስልም፡፡ በአርጎባዎች የአነጋገር ልማድ ንግግሩ ጥሩ ያልሆነ ሰው ላንቃው የተነሳው በእርሾ ነው ይባላል፡፡ የማር ትዕምርታዊነት የሚወድቀው እዚህ ላይ ሲሆን ትዕምርታዊ ፍቸው የሚለየው ደግሞ የማርን ምንነት በመረዳትና ማር ማንፀሪያ ሆኖ ከቀረበው እርሾ ጋር ያለውን ግንኙነት በመለየት ነው፡፡ ማር ጣፋጭና መድኃኒትነት ያለው ተወዳጅ ምግብ ሲሆን በአንፃሩ እርሾ ኮምጣጣ በመሆኑ ሁለቱ የአንድ ጐራ ሳይሆኑ ተቃራኒ ነገሮች ናቸው ማለት ነው፡፡ ላንቃው የተነሳው በእርሾ ነው የሚባል ሰው እንደዚያ የሚባለው ንግግር የማይችል፣ ንግግሩ የማያስደስት፣ ወዘተ ሆኖ እንጂ በባህሉ ላንቃ በእርሾ የማንሳት ልማድ ኖሮ አይደለም፡፡ ስለዚህ ማር ከላንቃ ማንሻነት ባሻገር ትዕምርታዊነቱ ከጣፋጭነት ባህርዩ ጋር ይያያዛል፡፡ ኮምጣጣ ከሆነው እርሾ በተቃራኒ ማር ለአንደበተ ጣፋጭነት፣ ለአንደበተ ርቱዕነት፣ ለንግግር አዋቂነት የቆመ ትዕምርትና ህፃኑ ሲያድግ እንደዚያ እንዲሆን መመኛና ማምሰያ ነው፡፡

### 5.2.2.8. የደም ዶሮ እርድ

ወላዷና ህፃኑ እንደተኙ ወዲያው ዶሮ ታርዶ አልጋው ስር ጣል ይደረጋል፡፡ የእርዱ ዓላማ ደም እንዲፈስ በማድረግ ወላዷንና ህፃኑን ከእርኩስ መንፈስ መጠበቅ ሲሆን የደም ዶሮ ይባላል፡፡ እርኩስ መንፈስ ደም የፈሰሰበትን ቦታ ይወዳል፣ ደም የፈሰሰውን ሰው ህመም ላይ ይጥላል ተብሎ የሚታመን በመሆኑ ቶሎ ዶሮ አርዶ ደም በማፍሰስ ወላዷ በፈሰሳት ደም ፋንታ እንዲሆን ወይም ጭዳ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ወላዷ በፈሰሳት ደም ምክንያት በእርኩስ መንፈስ ጉዳት እንዳይደርስባት የዶሮው ደም ይከላከልላታል ተብሎ ይታመናል (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 13/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ወላዷ እንደወለደች ወዲያው የእንግዴ ልጁ ሲቀበርና ወላዷና ህፃኑ ሲታጠቡ ሌሎች ሴቶች ገንፎ ያገነፋሉ፡፡ ገንፎ ከተገነፋ በኋላ በሰሊጥ ወይም በቅቤ ማባያ ተደርጐ ለወላዷ ለብቻ፣ ለአዋላጇና አዋላጇን ሲያግዙ ለነበሩት ሴቶች አንድ ላይ ለብቻ ይቀርብና ዱዓ ተደርጐ ይበላል (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 13/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ በቡድን ተኮር ውይይት ጊዜ ወ/ሮ ሶሀሊየት ባቢ በዚህ ጊዜ ይከወናል ያሉትን የሚከተለውን ዱዓ መርተዋል፤ ሌሎች ሴት ተወያዮች ደግሞ "አሜን" እያሉ ተቀብለዋል (30/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቡድን ተኮር ውይይት)፡፡

| <u>ዱዓ አድራጊ</u> | <u>ተቀባዮች</u> |
|---|---|
| በሙሉ ትውረድ | አሜን |
| ምንም ሳይነካት | " |
| ልጁም አድጐ የሚጠቅም ይሁን | " |
| እሷም በሽልም ትውጣ | " |
| ሽፍን ሽፍንፍን ብላ | " |
| እንደው ሳይገልጣት | " |
| ልጁም ይደግ | " |

በጉያዋ አድጐ ”

የሚጠቅም አላህ ያርገው ”

አኋሁ መሰሊ ወሰሊም አላ ሰይድና መሐመድ ወአላ አሊ ሰይድና መሐመድ

ከዚያ በኋላ ወላዷ ተልባ ለብ ባለ ውሃ ተበጥብጦ ይሰጣትና ትጠጣለች፡፡ የደም ተብሎ የታረደው ዶሮ ተሰርቶ ወላዷ ዶሮውን በአሊጣጦ እንድትበላ ይደረጋል፡፡ ይህን የምግብ ዝግጅት አራሷን ለመርዳት የተሰበሰቡ የቤተሰብ አባላት፣ ወይም የቅርብ ዘመዶች ያከናውኑታል (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 13/2/2013፣ ጋቺኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

5.2.2.9. የልጅ ጓሮ ቀበራ

የልጅ ጓሮ የእንግዴ ልጅ ነው፡፡ የእንግዴ ልጅ በቅል ተደርጐ ይቀበራል፡፡ ወላዷ ከወለደች በኋላ እየታጠበችና ከዚያ በኋላ የሚከወነው ነገር እየተከወነ ወንዶች ጉድጓዱን የሚቆፍሩ ሲሆን በወሊድ ጊዜ ሲረዱ ከነበሩ ሴቶች ውስጥ አንዷ እንግዴ ልጁና እትብቱ የተቆረጠበት ምላጭ በተደረገበት ቅል ላይ ትንሽ ጥሬ ጤፍ በማድረግ ወደተቆፈረው ጉድጓድ ትሄዳለች፡፡ ከዚያ በኋላ እንግዴ ልጁን ከነቅሉ በተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ በመድፋት ቅሉ ከላይ በኩል እንደሆነ ወንዶቹ አፈር ያለብሱታል፡፡ እትብቱ የተቆረጠበት ምላጭ ከእንግዴ ልጁ ጋር አብሮ የሚቀበረው የልጁ እትብት እንዳይቆስልና ቶሎ እንዲደርቅ ያደርገዋል፤ ጥሬ ጤፉም ለህፃኑ በሽታ ይከላከልለታል ተብሎ ስለሚታመን ነው (ወ/ሮ ኢና ሙጋ፣ 10/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የእንግዴ ልጁ መቀበሩና ሲቀበርም በቅል መሆኑ የእንግዴ ልጅ ክብር የሚሰጠው በመሆኑ ምክንያት ነው፡፡ የእንግዴ ልጅ ህፃኑ ከመወለዱ በፊት ህይወት የሚያገኝበት፣ ነፍስና እንቅስቃሴ የነበረው ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ ምክንያት እትብት ተቆርጦ ቀሪው የእንግዴ ልጅ እስኪወጣ ድረስ በወላዷ ጭን ላይ የሚታሰረው እንግዴ ልጁ ህይወትና እንቅስቃሴ ስላለው ወደታች መውረድ ሲገባው ወደላይ እንዳይወጣ ነው፡፡ በመሆኑም ከህፃኑ ጋር የነበረ ነፍስ የነበረው ነገር እንዲሁ በአፈር ላይ አይጣልም፤ ህፃኑ በጨርቅ ሲነሳ የእንግዴ ልጁ በቅል ተደርጐ ይቀበራል (ወ/ሮ ኢና ሙጋ፣ 10/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የእንግዴ ልጅ የሚቀበረው የተወለደው ህፃን ወንድ ከሆነ በቤት ውስጥ፣ ሴት ከሆነች ደግሞ ከቤት ውጭ ሲሆን (ወ/ሮ ኢና ሙጋ፣ 10/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) ይህም ድርጊት ትዕምርታዊ ነው፡፡ በአርጐባ ባህል ወንድ ልጅ አድጐ ትዳር ሲይዝ ኑሮውን የሚያደርገው በቤተሰቡ መኖሪያ ቅጥር ግቢ መኖሪያውን በመስራት ሲሆን ሴት ልጅ አድጋ ስታገባ ግን የምትኖረው ወደ ባሏ አካባቢ በመሄድ ነው፡፡ በመሆኑም ወንድ ልጅ ሲወለድ የእንግዴ ልጁ በቤት ውስጥ የሚቀበረው ህፃኑ አድጐ በትክክልም ኑሮውን በቤተሰቡ አካባቢ እንዲያደርግ፣ የቤተሰቡን አካባቢ ይዞና አስከብሮ እንዲኖር ማምሰል ሲሆን ሴት ልጅ ስትወለድ የእንግዴ ልጁ ከቤት ውጭ የሚቀበረው ህፃኗ አድጋ ቶሎ ትዳር እንድታገኝና ወደ ባሏ አካባቢ እንድትሄድ ማምሰያ ነው፡፡

በወሊድ ጊዜ የባል ሚና የደጅ የሚባሉና ጉልበት የሚጠይቁ ስራዎችን ለምሳሌ፣ ውሃ ቀድቶ ማምጣትና የማገዶ እንጨት ፈልጦ ማቅረብን የመሰሉትን ስራዎች ማከናወን ነው፡፡ የሀይማኖት አባቶች በምጥ ጊዜ ዱዓ ያደርጋሉ (አቶ ኢብራሂም አህመድ፣ 26/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

### 5.2.2.10. የአራስ ቤት ገጽታና እንክብካቤ

አብዛኛውን ጊዜ አንዲት ሴት የመጀመሪያ ልጇን ስትወልድ የምትታረሰው በቤተሰቧ ቤት፤ በእናቷ እጅ ነው፡፡ እናት በህይወት ባትኖር እንኳን እህቶች፣ አክስቶች ወይም የእንጀራ እናት ስለሚኖሩ በቤተሰቧ ቤት ወልዳ ትታረሳለች፡፡ ሁለተኛ እርግዝና ሲሆን ግን እንደ ወላዷ ፍላጐት በቤተሰቧ ቤት አልያም በባሏ ቤት ትወልዳለች (ወ/ሮ ሶህሊየት ኑሬ፣ 7/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በአራስ ቤት አራሷን የሚንከባከቡ የአራሷ እናት፣ አማት፣ እህቶች ወይም አክስቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ አራሷን የሚንከባከቡ ሁለት ሴቶች ናቸው፡፡ አንደኛዋ ሴት ለአራሷና ለእንግዶች የሚሆን ምግብ በማዘጋጀት፣ አራሷንና ህፃኑን በመመገብ፣ ለአራሷ ጡት ማጥባት እንዴት እንደሆነ በማሳየት፣ አራሷንና ህፃኑን በማጠብ፣ አራሷን ጭስ በማሞቅ፣ የአራሷንና የህፃኑን ልብስ በማጠብና በማሞቅ፣ ህፃኑን በማልበስ፣ ቤቱን በማጽዳትና ጭስ በማጨስ፣ ወዘተ አራሷና ህፃኑ የሚያስፈልጋቸውን እገዛ የምታደርግ ሲሆን ሌላዋ ሴት ደግሞ አራስ ለመጠየቅ የሚመጡ እንግዶችን በመቀበል የምታስተናግድ ናት፡፡ ሁለት ሰው ከሌለ ግን ያለችው አንዷ አራሷን ትንከባከባለች፣ እንግዶችንም ተቀብላ

ታስተናግዳለች፡፡ አራሷን የሚንከባከቧት ሴቶች ወደየቤታቸው የሚመለሱት አራሷ የአራስነት ጊዜዋ በሚያበቃበት አርባኛ ቀን ከታጠበች በኋላ ነው፡፡ ሁለት ሰው እስከዚያ ድረስ መቆየት የማይችል ቢሆን እንኳን አንዷ ሴት ትቆይላታለች (ወ/ሮ ሶህሊየት ኑሬ፣ 7/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

አራስና አዲስ የተወለደ ህፃን ለተለያዩ ህመሞች የተጋለጡ ናቸው ተብሎ የሚታመን በመሆኑ በአራስ ቤት ለሁለቱም እንክብካቤ ይደረጋል፡፡ የሚደረገው እንክብካቤ በሁለት ዋና ጉዳይ ሊከፈል ይችላል፡፡ የመጀመሪያው እናትና ልጅ እንዲጠነክሩ በምግብና በንጽህና መንከባከብ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ለተለያዩ ህመሞች እንዳይጋለጡ የሚከናወኑ ተግባራትን ማከናወን ነው፡፡

**የአራስና የህፃን ምግብና ንጽህና አጠባበቅ፣**

አራስ በአራስነት ጊዜዋ ጥሩ ጥሩ ምግቦች እየተዘጋጁላት እንድትመገብ ትደረጋለች፡፡ ለአራስ የሚዘጋጁ ዋና ዋና ምግቦች ዶሮ፣ አሊጣጦ፣ በቅቤ የታሸ ቂጣ፣ ገንፎ፣ አጥሚትና ተልባ ናቸው፡፡ አራስ በአርባ ቀን የአራስነት ጊዜዋ በብዛት ከዶሮ የሚዘጋጅ ምግብ ይዘጋጅላታል፡፡ አራስ ቢያንስ በቀን አንድ ዶሮ የሚታረድላት ሲሆን ጥሩ የኢኮኖሚ አቅም ባለው ቤተሰብ ውስጥ ያለች አራስ ደግሞ በቀን ሁለት ዶሮ፣ በአርባ ቀን ሰማንያ ዶሮ ታርዶላት እንድትመገብ ይደረጋል፡፡ አራሷ በነፍሰጡርነት ጊዜዋ በርካታ ዶሮዎችን ለመታረሻዋ እንዲሆን ታረባለች ወይም ከገበያ በመግዛት ታዘጋጃለች፣ ከዚያ በተረፈ በአራስነት ጊዜዋ ሊጠይቋት የሚመጡ ሰዎች ዶሮ ይዘው የሚመጡ በመሆኑ ለመታረሻዋ ይሆናል (ወ/ሮ ሶህሊየት ኑሬ፣ 7/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

አራስ በቀን አምስት ጊዜ የምትመገብ ሲሆን መጀመሪያ ጠዋት ገንፎ ተገንፍቶ ትመገባለች፣ ረፋድ ሲል ዶሮ ይታረድና እስኪዘጋጅ ቂጣ ተጋግሮና በቅቤ ታሽቶ ቀርቦላት ትመገባለች፣ ምሳ፣ መክሰስና እራት የተዘጋጀውን ዶሮ በአሊጣጦ ወይም በእንጀራ ትመገባለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አጥሚት ተሰርቶላት ትጠጣለች፣ ተልባ ተሞቆ ወይም ለብ ባለ ውሃ ተበጥብጦ በእስቤዛ ይቀመጥና በመሀል በመሀል ትጠጣለች (ወ/ሮ ሶህሊየት ኑሬ፣ 7/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ወ/ሮ ጦይባ ይማም በመስክ ስራ ወቅት በአራስ ቤታቸው ተገኝቼ ቃለ መጠይቅ ያደረግሁላቸው አራስ ናቸው፡፡ በአራስነት ጊዜያቸው እየታረሱ ያሉበትን ሁኔታ በሚከተለው መልኩ ገልፀዋል፡፡

ጠዋት ላይ ገንፎ ወይም ቂጣ ፍርፍር እበላለሁ፡፡ አጥሚት ተሰርቶ ይመጣል፡፡ ዶሮ እስኪደርስ ድረስ ያንን እጠጣለሁ፡፡ ከዚያ ዶሮ ይደርሳል ያንን እበላለሁ፡፡ ሆድ መጉደል የለበትም፡፡ በተገኘ ሰዓት መብላት ብቻ ነው፡፡ ምሳና እራት ዶሮ ይበላል፡፡ በመሀል በመሀል የሚያስፈልግ ነገር ሲኖር ይሰራል፡፡ … የሚያርሱኝ የእሱ [የባለቤታቸው] እናት፣ የእኔ እናትና እህቶቻችንም አሉ፡፡ እነሱ ናቸው የሚያርሱኝ (5/10/2012፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

አራስ ሰው ያየውን ምግብ አትመገብም፡፡ ይህ የሆነው ምግቡን አይቶ የጓጓ ሰው ቢኖር አራሷ ምግቡን ስትበላ ትታመማለች በሚል እምነት ምክንያት ነው፡፡ የአራሷን ምግብ የሚያዘጋጁም የአራሷ ወይም የአራሷ ባለቤት እናት ወይም እህቶችን የመሰሉ የቤተሰብ አባላት ብቻ ሲሆኑ ምግቡ ሲሰራ ብዙ ሰው በሌለበት ቦታ ደበቅ ተደርጐ፤ ሲመጣም ተከድኖ ነው (ወ/ሮ ሶሀሊየት ኑሬ፣ 7/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

አራስ የምትመገበው ለብቻዋ ነው፡፡ የባል አብሮ መመገብ ክልክል የሌለው ቢሆንም አራሷ በደንብ በልታ ቶሎ እንድትጠነክር ስለሚፈለግ ምግቧ ለብቻዋ ይሰጣታል፡፡ አስፈላጊ ከሆነ የሚሰራው ምግብ ለሁለት ሰው እንዲበቃ ተደርጐ ይሰራና ለባል ለብቻው ተቀንሶ ይሰጠዋል (ወ/ሮ ሶሀሊየት ኑሬ፣ 7/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

አራስ በአራስነት ጊዜዋ እንዳትመገባቸው የሚከለከሉ ምግቦችም አሉ፡፡ እነዚህ ምግቦች ጥራጥሬ፣ ጐመን፣ ቃሪያ፣ እንዲሁም ረጃ (ሁለተኛ ቡና) እና ጀሚ (ሶስተኛ ቡና) ናቸው፡፡ ጥራጥሬና ጐመን ጡት ለሚጠባው ህፃን ቁርጠት ያመጣበታል፤ ቃሪያ ህፃኑን ያቃጥለዋል፤ ረጃና ጀሚ መጠጣት ደግሞ ህፃኑ ለመሽናት እንዲቸገር ያደርገዋል የሚሉ ምክንያቶች የክልከላዎቹ መነሻዎች ናቸው (ወ/ሮ ሶሀሊየት ኑሬ፣ 7/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የህፃኑን ምግብ በተመለከተ ህፃኑ ጡት ይጠባል፡፡ ሰውነቱ ይጠነክራል፤ ከሆዱ ውስጥ ያለ ቆሻሻም ይወጣል በሚል ምክንያት ለጋ ቅቤም እንዲውጥ ይደረጋል፡፡ አራስ ጡቷ በቂ ወተት እንዲኖረው የተለያዩ ምግቦች ተዘጋጅተውላት እንድትበላ ትደረጋለች፡፡ እነዚህ ምግቦች በጣም ሳይበስል የተቀቀለ ማሽላ እና የሽንብራና የሱፍ ቆሎ ናቸው፡፡ እነዚህ ምግቦች አራሷ ውሀ እንድትጠጣና ጡቷ በቂ ወተት እንዲኖረው የሚያደርጉ ናቸው፡፡

ከዚያ ባለፈ ጡቷ በቂ ወተት ከሌለው በርበሬ ሳይበዛበት የተሰራ የዶሮ መረቅ፣ አጥሚትና ተልባ ትኩስ ትኩሱን እንድትጠጣ ይደረጋል (ወ/ሮ ፋጡማ ቡሴሂሪ፣ 13/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

አንዳንድ ጊዜ የእናት ጡት ወተት ሊቀንስ ወይም ከመጀመሪያውም መጠኑ ትንሽ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ህፃኑ ከሚውጠው ቅቤ በተጨማሪ የላም ወተት ሁለት እጅ ውሃ እየተጨመረበት እንዲጠጣ ይደረጋል፤ የፍየል ወተት ይሰጠዋል፡፡ ህፃኑ አራት ወር ሲሆነው ተጨማሪ ምግብ ይጀመርለታል፡፡ ይኸውም ተልባ ተንተክትኮ ሲበርድ ይሰጠዋል፤ አብሽ ተቀቅሎ የመጀመሪያው ውሃ ከተደፋ በኋላ እንደገና ውሃ ተጨምሮና ተንተክትኮ፣ ትንሽ ስኳርና ለጋ ቅቤ ተጨምሮበት እንዲጠጣ ይደረጋል (ወ/ሮ ፋጡማ ቡሴሂሪ፣ 13/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

አራስ የምትተኛበት ድንክ አልጋ ጠፍሩ ላይ ለሷ እስከ እግሯ የሚደርስ የሚነጠፍ ነገር ተነጥፎላት፤ ለህፃኑ ደግሞ እስከ ወገቡ ድረስ ተነጥፎለት ይተኛሉ፡፡ ህፃኑ ከወገቡ በታች ያለምንጣፍ እንዲተኛ የሚደረገው ሽንት ሲሸና በጠፍሩ በኩል ወደታች እንዲፈስ ታስቦ ነው፡፡ ህፃኑ ገላውን ሲታጠብም አልጋው ላይ በመሆኑ ውሃው እዚያው አልጋው ስር ይፈሳል፡፡ በመሆኑም ሽንቱ እንዳይሸት አራሷ ጠዋት ጠዋት በአልጋው ስር ፍግ ትነሰንስና አዝጋሮና ሽታ በጋቻ በማድረግ አልጋው ስር ታጨሳለች፡፡ በማግስቱ ጠዋት ደግሞ የተነሰነሰውን ፍግ ፍቃና ጠርጋ በማውጣት እንደገና ፍግ ነስንሳ አዝጋሮና ሽታ ታጨሳለች (ወ/ሮ መርሻዬ አሕመድ፣ 14/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

አራስና አካባቢዋ ንፁህና ጥሩ መዓዛ እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ በመሆኑም አራስ በቀን አንድ ወይም ሁለት ጊዜ ገላዋን ታጥባ አዝጋሮና ሽታ ትሞቃለች፤ ልብሷ በየጊዜው እየታጠበ በአዝጋሮና በሽታ ይሞቃል፡፡ የአራስ ቤትና አራስ የምትተኛበት አልጋ ስር ሁሉ አዝጋሮና ሽታ ይጨስበታል፡፡ ህፃኑ በቀን አንድ ጊዜ ወይም ጠዋትና ማታ ሁለት ጊዜ ገላው ታጥቦ ለጋ ቅቤ ጭንቅላቱንና ገላውን ይቀባል (ወ/ሮ መርሻዬ አሕመድ፣ 14/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

አራስ በተቻለ መጠን እንድትተኛና እረፍት እንድታደርግ ይደረጋል፡፡ ነገር ግን አጠገቧ ማንም ሰው በሌለ ጊዜ እንዳትተኛ ትመከራለች፡፡ ይህ የሚሆነው ምናልባት ብትደነግጥ

ብቻዋን ስለሆነች እርኩስ መንፈስ እንዳይቀርባትና ለህመም እንዳትዳረግ ተብሎ ነው (ወ/ሮ መርሻዬ አሕመድ፣ 14/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

**የአራስና የህፃን ጤና አጠባበቅ፣**

አራስና ጨቅላ ህፃን ለሰው ዓይን ህመም ተጋላጭ ናቸው ተብሎ የሚታመን በመሆኑ በአራስ ቤት አራሷን ከሚንከባከቧት የቅርብ የቤተሰብ አባላት ውጭ ሌሎች ሰዎች አራሷንም ሆነ ህፃኑን እንዲያዩዋቸው አይፈለግም፡፡ ሁለቱንም ከሰው ዕይታና ከነፋስም ለመጠበቅ ሲባል የወይባ ዛፍ ቅርንጫፉ ከነቅጠሉ ተቆርጦ አራሷ በምትተኛበት አልጋ ዙሪያ ተገድግዶ ትንሽ በር ብቻ ይተዋል፡፡ አራሷን ለመጠየቅ የሚሄዱ ሰዎች አራሷንና ህፃኑን ሳያዩ በተረፈው በር በኩል እጃቸውን እየዘረጉ ብቻ እጇን በመጨበጥ ሰላምታ ይሰጧታል፣ ይጠይቋታል፡፡ የወይባ ግርዶሽ ቢኖርም እንኳን የሰው ዓይን አለባቸው ተብለው የሚጠረጠሩ ሰዎች አራሷን ለመጠየቅ ሲመጡ ድምፃቸው እንደተሰማ አራሷ ጋር እንዳይደርሱ ለማድረግ አራሿ ሴት ከቤት በመውጣት በደጅ ቁጭ ትልና እዚያው አነጋግራ ትሸኛቸዋለች፤ ወደ ወላዷ ቤት ከገቡም ምክንያት ተሰጥቷቸው (ለምሳሌ፣ አራሷ ተኝታለች የሚል) አራሿን ሴት ብቻ አነጋግረው እንዲመለሱ ይደረጋል (ወ/ሮ መርሻዬ አሕመድ፣ 14/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ነፍሰጡር አምስት ወር ሲሆናት ለሰው ዓይን መከላከያ የሚሆን ጽህፈት ተጽፎ በወገቧ ላይ ይታሰርላትና ስትወልድ ደግሞ ለህፃኑ የሰው ዓይን መከላከያ እንዲሆንለት በአንገቱ ላይ ይታሰርለታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ህፃን ልጅ ገና ሲወለድም ለሰው ዓይን መከላከያ እንዲሆነው ባህላዊ መድኃኒት እንዲቀምስ ይደረጋል፡፡ የሚቀምሰው አንደኛው መከላከያ ሬት፣ ሁለተኛው የድንጋይ ሙጫ የሚባል በዱር ድንጋይ ላይ የሚገኝ ፈሳሽ ሲሆን ሶስተኛው ተጨቅጭቆ በውሀ የተበጠበጠ የተከዜ ዛፍ ስር ነው፡፡ ህፃን እንደተወለደ እነዚህን ከቀመሰ ለሰው ዓይን ህመም አይጋለጥም ተብሎ ይታመናል፡፡ አንድ ህፃን በሰው ዓይን እንደታመመ የሚያስጠረጥሩ ህፃኑ የሚያሳያቸው ምልክቶች አዘውትሮ ማልቀስ፣ ተረጋግቶ አለመተኛት፣ ጡት አለመጥባት፣ ወዘተ ናቸው፡፡ ህፃኑ በሰው ዓይን እንደታመመ ከተጠረጠረ ደግሞ መድኃኒት የሚሆን ጽህፈት በአንገቱ ላይ ይታሰርለታል፤ ህሞ በሚባል ቅጠል ሰውነቱን ማጠብም ህፃኑ ተረጋግቶ እንዲተኛ ያደርገዋል (አቶ አደም መሐመድ፣ 4/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

አራስና ጨቅላ ህፃን ከሰው ዓይን በተጨማሪ ለእርኩስ መንፈስ ጥቃት የተጋለጡ ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ በተለይ አራስ ደም ስለሚፈሳት ፈላጊና ተፈታታኝ እርኩስ መንፈስ አለባት ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ ምክንያትም አራስ መቃብሯ ክፍት ነው ይባላል፡፡ ይህ ማለት በሚፈታተናት እርኩስ መንፈስ ምክንያት በቀላሉ ለጉዳት የተጋለጠች ነች ማለት ነው፡፡ አቶ ኑርዬ በሺር እንደገለፁት (16/7/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቡድን ተኮር ውይይት) በነፋስ ውስጥ የሚገኙና በዓይን የማይታዩ እርኩስ መናፍስት ወይም ጂኒዎች ደም ስለሚወዱ በጥይት የተመታ ሰው እንኳን ጥይቱ ሳይጎዳው ደሙን ብለው የሚመጡ እርኩስ መንፈሶች የሚያደርሱበት ህመም ይጎዳዋል፡፡ ይህ እንዳይሆን በጥይት ተመትቶ የወደቀ ሰው ከወደቀበት ሳይነሳ ነጭ ዶሮ ቦታው ላይ ታርዶ ከዚያ በኋላ እንዲነሳ ይደረጋል፡፡ ወድቆ ተፈንክቶ ለደማ ሰው እንኳን በወደቀበት ቦታ ላይ እንቁላል ይፈረጣል፡፡ በመሆኑም እርኩስ መንፈሶች ደም የፈሰሳትን አራስ ይጠጋሉ፤ ለበሽታም ያጋልጣሉ፡፡ በእርኩስ መንፈስ የመያዝ ምልክቶች ዓይንን ማጉረጥረጥ፣ የቁጣ አስተያየት ማየት፣ መቁነጥነጥ፣ መንጠራራት፣ ማዛጋት፣ ከንፈርን በጥርስ መቦጨቅ፣ የወለዱትን ልጅ መጥላት፣ ወዘተ ናቸው፡፡ ህመሙ በህፃን ላይ ሲሆን ህፃኑ አዘውትሮ ያለቅሳል፣ ትኩሳት ይኖርበታል፣ ይነጫነጫል፣ እንቅልፍ አይተኛም፣ ያንቀጠቅጠዋል፣ አይኑን ያፈጥጣል፡፡

አራሷም ሆነች ህፃኑ በእርኩስ መንፈስ ምክንያት ለህመም እንዳይጋለጡ ጥንቃቄ ይደረግላቸዋል፡፡ እርኩስ መንፈስ ብረት አይወድም፣ ይሸሻል ተብሎ ስለሚታመን እርኩስ መንፈስን ለመከላከል በአራስ መኝታ ላይ ከራስጌዋ ብረት ወይም መሳሪያ ይቀመጣል፣ ለሽንት ስትወጣም ብረት ትይዛለች፡፡ በአራሷ መኝታ ራስጌ የሚቀመጠው ብረት የማይነሳ ሲሆን አራሷ ለሽንት ስትወጣ በበር አካባቢ ግድግዳ ስር የሚቀመጥ ብረት ይዛ ትወጣና ስትመለስም እዚያው ታስቀምጠዋለች፡፡ ፀጉሯ ላይ መርፌ ቁልፍ ወይም ቀለበት፣ በጆሮዋ ላይም ከብር የተሰራ ጌጥ ታደርጋለች (ወ/ሮ ከድጃ መሐመድ ሰዒድ፣ 4/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

አራስና ህፃኑ ታጥቦ የተሰጣ ልብስ ከደጅ እንደገባ አይለብሱም፡፡ ልብሱን የሚለብሱት ከደጅ ገብቶ ከበረደና በአጎበር ተደርጐ አዝጋሮና ሽታ ከተሞቀ በኋላ ነው፡፡ ይህ የሚደረገው ልብሱ ደጅ ተሰጥቶ ድንገት በዓይን የማይታዩ እርኩሳን መናፍስት ነክተውት ከሆነ አራሷና ህፃኑ ሲለብሱት ይታመማሉ ተብሎ ስለሚታመንና ጭሱ ንክኪውን

ያከሽፈዋል ተብሎ ስለሚታመን ነው (ወ/ሮ ከድጃ መሐመድ ሰዒድ፣ 4/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

አራስ ለሽንት የምትወጣው ጠዋት ፀሀይ ከመውጣቱ በፊትና ማታ ጀምበር ከገባች በኋላ ብቻ ሲሆን በቀትርና ፀሀይ በሚኖርበት ጊዜ አትወጣም፡፡ የዚህ ዋና ምክንያት ሁለት ሲሆን አንደኛው አራሷን እርኩስ መንፈስ እንዳይጠጋትና ለህመም እንዳይዳርጋት ሲሆን ሁለተኛው አራሷና የመኝታ አካባቢዋ ሽታ ስለሚሞቁ ምች እንዳይመታት ተብሎ ነው፡፡ አራስ ለሽንት ወጥታ ስትመለስ ልብሷን በምድጃ እሳት ላይ ሶስት ጊዜ አራግፋ ወደ አልጋዋ ትሄዳለች፡፡ ይህን የምታደርገው ስትወጣ ለበሽታ የሚያጋልጥ እርኩስ መንፈስ ልብሷን ነክቶት ከሆነ መንፈሱን ከላይዋ ለማላቀቅ፣ ለማቃጠል ነው (ወ/ሮ ከድጃ መሐመድ ሰዒድ፣ 4/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

አራስ በአራስነት ጊዜዋ ጮክ ብሎ ማውራት አይፈቀድላትም፡፡ አራስ ከጮኸች እርኩስ መንፈስ ይጠጋትና በዚያው ህመምተኛ ሆና ትቀራለች ተብሎ ስለሚታመን አራስ የምታወራው ድምጿን ዝቅ አድርጋ ነው (ወ/ሮ ከድጃ መሐመድ ሰዒድ፣ 4/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ምልከታ ባደረግሁባቸው የአራስ ቤቶችም ይህን ለመገንዘብ ችያለሁ፡፡

አራስ ሁልጊዜ አጠገቧ ሰው እንዲኖር ማስለመድ የለባትም ተብሎ ይታሰባል፡፡ የዚህ እሳቤ ምክንያት አራስ ሁልጊዜ አጠገቧ ሰው እንዲኖር ካደረገችና ካስለመደች በአጋጣሚ ሰው አጠገቧ በማይኖር ጊዜ እርኩስ መንፈስ ይጠጋታል፤ ትታመማለች የሚል እምነት ነው፡፡ በአንፃሩ ከመጀመሪያ ወሊድ ጀምሮ ብቻዋን መሆንና ወደ ሽንት ቤት ስትሄድም ብረት ብቻ በመያዝ ብቻዋን መሄድንና ራስጌ ብረት በማድረግ ብቻ ህፃኑንም ብቻውን አድርጋ መሄድን ካስለመደች ችግር አይኖረውም፤ ስለምትለማመደው ብቻዋን በመሆንዋ ምክንያት እርኩስ መንፈስ ቀርቧት ልትታመም የምትችልበት ሁኔታ አይኖርባትም ተብሎ ይታመናል (ወ/ሮ ከድጃ መሐመድ ሰዒድ፣ 4/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

### 5.2.2.11. አራስ ጠያቂዎች

አራስን ዘመድ አዝማድ፣ ወዳጅና ጐረቤቶች የአራስ መጠየቂያ በመያዝ ይጠይቋታል፡፡ የአራስ መጠየቂያ ዶሮ፣ እንቁላል፣ ለጋ ቅቤ፣ ወይባ፣ አዝጋሮ፣ ሽቶ፣ ሳሙናና ገንዘብ ናቸው፡፡ ለአራስ የበሰለ ምግብ አይወሰድም፤ አራስም ከውጭ በስሎ የመጣ ምግብ

አትመገብም፡፡ የዚህ ምክንያቱ ምግቡ የሰው ዓይን ያረፈበት ስለሚሆን አራሷን ለህመም ይዳርጋል የሚል እምነት ነው (ወ/ሮ ፋጡማ ሁሴን፣ 8/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

አራስ የሚጠይቁ ሰዎች ወደ አራስ ቤት ሲገቡ "እንኳን ደስ አለሽ" እያሉ ይገባሉ፡፡ ከዚያ በኋላ የያዙትን የአራስ መጠየቂያ ለአራሿ ሰጥተው ይቀመጡና ስለ አራሷና ስለ ህፃኑ ደህንነት "በሰላም ተገላገለች ወይ?" "ምጡስ ጠናባት ወይ?" "ህፃኑስ እንዴት ነው?" ብለው በመጠየቅ ከአራሿ ጋር ይወያያሉ፡፡ ጠያቂዎቹ የቤተሰብ አባላት፣ ከቅርብ ዘመዶች ወይም ጓደኞች ከሆኑ ትንሽ ቆየት ብለው ከደጅ የመታቸውን ፀሀይ ካበረዱ በኋላ ወደ አራሷ በመሄድ፤ በወይባው ግርዶሽ እጃቸውን በማሾለክ እጇን ጨብጠው ሰላምታ ከሰጧት በኋላ እንደቆሙ ያወያዩዋትና ተመልሰው ወደነበሩበት በመሄድ ቁጭ ይላሉ፡፡ ከዚያ በኋላ በማር የታሸ የገብስ ቆሎ ይቀርብላቸዋል፤ ትንሽ ቆይቶ እንጀራ በወጥ ቀርቦላቸው ይስተናገዳሉ፤ በመጨረሻ ቡና ተፈልቶ ይጠጣሉ፡፡ ጠያቂዎች ከአራስ ቤት ሲወጡ አራሷን "በሙሉ አላህ ያውጣሽ" ብለው ይሄዳሉ (ወ/ሮ ፋጡማ ሁሴን፣ 8/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ የአራስነት ጊዜ እጅግ በጣም ጥንቃቄን የሚሻ፣ አራሷ በቀላሉ ለህመምና ከዛም በላይ ለሆነ ጉዳት ልትጋለጥበት የምትችልበት ጊዜ እንደሆነ የሚታሰብ በመሆኑ ጠያቂዎች "በሙሉ አላህ ያውጣሽ" ሲሉ ሙሉ የሚለው ቃል ከጤና አለመጉደልን፤ መውጣት ደግሞ የአራስነት ጊዜን በሰላም ማለፍን፣ መሻገርን፣ መቀላቀልን ይወክላሉ፡፡

### 5.2.2.12. የሰባት ቀን እጥበት ስነ ስርዓት

ሰባተኛው ቀን አራሷ የምትታጠብበት፣ አቂቃ[21] የሚወጣበት፣ ለህፃኑ ስም የሚወጣበትና ህፃኑ ወንድ ከሆነ ምናልባትም ግርዛት የሚከናወንበት ቀን ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ከሰባተኛው ቀን እጥበት ጋር አቂቃ የሚደረግ ሲሆን አልፎ አልፎ ግን በተለያዩ ምክንያቶች አቂቃው ከሰባተኛው ቀን በኋላ ይደረጋል፡፡ በሰባተኛው ቀን አቂቃ የሚደረግ ከሆነ አባት ወንድ ዘመድ ወዳጆቹንና ዱዓ እንዲያደርጉ ደረሳዎችን ይጠራል፤ አቂቃ የማይደረግ ከሆነ ግን በእለቱ በአራሷ ቤት የሚገኙት አብዛኛዎቹ ሴት ጠያቂዎች ብቻ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ ለወንዶች ጥሪ የሚደረገው አቂቃ የሚደረግ ከሆነ ብቻ ሲሆን አቂቃ ኖረም አልኖረም ሴት ጠያቂዎች የአራሷን የመታጠቢያ ቀን ቆጥረው ያለጥሪ በአራሷ ቤት

[21] የህፃኑ አባት ልጅ ማግኘቱን የሚመሰክርበት ሀይማኖታዊ ስነ ስርዓት

ይገኛሉ፡፡ አራሷን ያልጠየቁ ሰዎችም ለአራሷ የአራስ መጠየቂያ ይዘው ይሄዳሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሴት ጠያቂዎች ለአራሷ መታጠቢያ ብለው ውሀ ይዘው ይሄዳሉ፤ አራሷ ቤት አንድ መገልበጫ ይቀመጥና እዚያ ውሀውን ይገለብጣሉ፡፡ በእለቱ አቂቃ የሚደረግ ከሆነ እርድ ማድረግ ግዴታ በመሆኑ በዚያ ምግብ ተዘጋጅቶ የሄዱ ሰዎች ይጋበዛሉ፡፡ አቂቃ ከሌለ ግን እርድ ማድረግ ግዴታ አይደለም፤ እርድ ሊከናወንም ላይከናወንም ይችላል፡፡ በመሆኑም ለጥየቃ የሄዱ ሰዎች ቤት ባፈራው ምግብ ይጋበዛሉ (አቶ መሐመድ ሲራጅ፣ 8/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

**እጥበት፣**

አራስ ከወለደችበት ቀን ጀምሮ ገላዋን በቀን አንድ ወይም ሁለት ጊዜ ትታጠባለች፡፡ ነገር ግን በወለደች በሰባተኛው ቀን ከሌላው ቀን እጥበት በተለየ በቅጠላ ቅጠል ትታጠባለች፡፡ መጀመሪያ ህፃኑ በውሀና በሳሙና ከታጠበ በኋላ ልብሱን አልብሰውት ጡት ከጠባ በኋላ አስተኝተውት የአራሷ እጥበት ይከናወናል፡፡ አራሷ የምትታጠበው መጀመሪያ በተቀቀለ ቅጠላ ቅጠል በመሆኑ የተለያዩ ቅጠሎች ማለትም ወይባ፣ ጋሜ፣ ህሞ፣ ሰንሰል፣ ትግሪና ጨጮ ቅጠሎች ይሰበሰቡና ውሀው ቢጫ ቀለም እስኪያመጣ ድረስ አንድ ላይ ይቀቀላሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ያዋለደቻት ሴት ወይም ሌላ የቤተሰቧ አባል የሆነች ሴት ውሃ ከምታቀብል ሌላ ሴት የቤተሰብ አባል ጋር በመሆን አራሷ እዚያው የተኛችበት ድንክ አልጋ ላይ ቁጭ እንዳለች መጀመሪያ በተቀቀለው ቅጠላ ቅጠልና በውሀው እያሹ ያጥቧታል፤ በመቀጠል በውሀና በሳሙና ብቻ ያጥቧታል፡፡ አራሷ ታጥባ ሲበቃት ሰውነቷን ሁሉ ቅቤ ቀብተው ያሿታል፡፡ ከዚያ በኋላ ታጥቦ የተሞቀ ልብስ ያለብሷትና የተኛችበት አልጋ ደጅ ወጥቶ ስለሚታጠብ ልጇን ይዛ በሌላ አልጋ ላይ ትሆናለች፡፡ ከዚያ በኋላ ገንፎ በቅቤ፣ በቅቤ የታሸ የጤፍ ቂጣ ወይም ቅቤ የተቀባ አነባበሮ ይቀርብላትና ትመገባለች፤ እንደሌላው ቀን ዶሮ ተሰርቶ ለምሳ ይቀርብላትና ትመገባለች (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 13/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ከዚያ በኋላ አራሷ የተኛችበት አልጋ ወደ ደጅ ወጥቶ በሙቅ ውሃና በተቀቀለው ቅጠላ ቅጠል ከታጠበ በኋላ ለፀሀይ ተሰጥቶ እንዲደርቅ ይደረጋል፡፡ አልጋው ደርቆ ከገባ በኋላ የተወለደው ወንድ ልጅ ከሆነ ወንድ ዶሮ፣ ሴት ከሆነች ደግሞ ሴት ዶሮ ታርዶ አልጋው ስር ይጣልና እዚያ እንዲንደፋደፍ ይደረጋል፡፡ ወንድ ዶሮ ለወንድ ልጅ፣ ሴት ዶሮ ደግሞ ለሴት ልጅ የሚታረደው ህፃኑ ወይም ህፃኗ ለሀጭ እንዳይበዛባቸው ያደርጋል በሚል

እምነት ምክንያት ነው፡፡ ዶሮው ከተነሳ በኋላ አልጋው ስር አዝጋሮና ሽታ ይጨስና አራሷ ከመተኛቷ በፊት የአራሷ እናት፣ እህት ወይም ሌላ የቤተሰብ አባል አስቀድመው አልጋው ላይ በመውጣት ጋደም ብለው ከተነሱ በኋላ አራሷ ከነልጇ አልጋው ላይ ወጥታ ትተኛለች፡፡ ደጅ የቆየና ፀሀይ የመታው ነገር እርኩስ መንፈስ ሊነካው እንደሚችል ይታመናል፡፡ በዚያ እቃ ላይ ያረፈ እርኩስ መንፈስ ደግሞ የነካውን ሰው ለበሽታ ይዳርጋል ተብሎም ይታመናል፡፡ በመሆኑም አራስ ከሌላው ሰው በተለየ እርኩስ መንፈስ ይከታተላታል፤ ለበሽታ ተጋላጭ ነች ተብሎ ስለሚታመን አስቀድሞ ሌላ ሴት አልጋው ላይ ጋደም ብላ እንድትነሳ የሚደረገው ድርጊቱ ሊከሰት የሚችልን በሽታ ማክሸፊያ ተደርጎ በመታመኑ ምክንያት ነው፡፡ ከዚያ በኋላ የአራሷ ልብስ ታጥቦ ሲደርቅ በአጎበር ተደርጎ አዝጋሮና ሽታ ይሞቃል፡፡ በዚህ እለት ቀን ቆጥረው የመጡ ሰዎች ምግብና መጠጥ ይጋበዛሉ፤ ቡና ተፈልቶ ዱዓ ይደረግና ቡና ይጠጣል (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 13/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

አራስ ከሰባተኛ ቀን እጥበቷ ጀምሮ በቀን አንድ ወይም ሁለት ጊዜ ቀለል ካለ ጭስ እንድትጀምር ተደርጎ ቅቤ እየተቀባች የወይባ ጭስ እንድትሞቅ ይደረጋል፡፡ የወይባ ጭስ ሰውነትን ያጠብቃል፣ ያጠነክራል፣ አራስ ነፋስ እንዳይገባት ይከላከላል፣ ከሞቁት በኋላ እንቅልፍ ያስወስዳል፣ እረፍት ይሰጣል፣ ከውበት አንፃርም ሆድን ይሰበስባል፣ ቆዳ ያሳምራል፣ ቆዳ እንዳይሸበሸብ ያደርጋል ተብሎ ስለሚታመንበት አራስ በተደጋጋሚ እንድትሞቅ ይደረጋል፡፡ ከወይባው በኋላ ገላዋን ታጥባ ታጥቦ የተሞቀ ልብስ በመልበስ ጥሩ መዓዛ እንዲኖራት አዝጋሮና ሽታ ትሞቃለች (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 13/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ጭስ ሶስት አይነት ሲሆን አንደኛው የወይባ ጭስ፣ ሁለተኛው አዝጋሮ እና ሶስተኛው ሽታ ናቸው፡፡ የወይባ ጭስ የወይባ ግንድ ተፈልጦ የሚሞቅ ጭስ ነው፡፡ የወይባ ጭስ መሞቂያ ትንሽ ጉድጓድ በክቡ ይቆፈርና ከላይ አለፍ አለፍ ተደርጎ እንጨት ይረበረባል፡፡ ከዚያ በኋላ መሞቅ ሲያስፈልግ በጉድጓዱ ውስጥ ፍም ተደርጎ በላዩ ላይ የተፈለጠው የወይባ ግንድ ይደረግና ሲጨስ የምትሞቀው ሴት ፀጉሯንና ሰውነቷን ቅቤ ተቀብታ ቀደም ባለው ጊዜ ቁርበት፤ በአሁኑ ጊዜ ግን ጉንደሬ ቀሚስ ወይም ብርድ ልብስ ለብሳ በጉድጓዱ ላይ ትንሽ በርጩማ አድርጋ እዚያ ላይ ትቀመጣለች፡፡ በደንብ ከሞቀች በኋላ በተቀቀለ የወይባ ቅጠል እየታሸች በውሀው ትታጠባለች፡፡ ከዚያ በኋላ በውሀና በሳሙና ታጥባ ታጥቦ የተሞቀ

ጉንደሬ ቀሚስ ለብሳ ጥሩ መዓዛ እንዲኖራት አዝጋሮ በጋቻ ተደርጐ ትሞቃለች፡፡ ከአዝጋሮው በኋላ ደግሞ ሽታ ትሞቃለች፡፡ የሚከተሉት ምሳሌያዊ አ.ጋገሮች ጭስ የመሞቅ ልማድን የሚመለከቱ ናቸው፡፡

- ሴት ያለጭስ፣ ቡና ያለቁርስ አላህ አያድርስ (አቶ አብዱልቃድር ቃሲም፣ 6/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡
- አይጥና ድመት ታርቀዋል፣ ሴትና ሙቀት ተጣልተዋል (አቶ አብዱልቃድር መሐመድ ሰዒድ፣ 9/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡
- አዝጋሮና ሴት ከተጣሉ ቆይተዋል፤ የሚያስታርቃቸው ቢገኝ እኔ ካሳውን እከፍል ነበር አለ ሰውዬው (አቶ አብዱልቃድር መሐመድ ሰዒድ፣ 9/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ጭስ በአራስነት ጊዜ እንደሚያስገኝ ከሚታመንበት ጥቅም በተጨማሪ ማንኛዋም ትዳር ያላት ሴት እንድታዘወትረው ይጠበቅባታል፡፡ በየጊዜው ጭስ የምትሞቅና ልብሷንም የምታሞቅ ሴት ጉበዝና ራሷን የምትንከባከብ ሴት እንደሆነች የሚታሰብና የትዳር አጋሯንም ደስ የሚያሰኘው ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም የመጀመሪያው ምሳሌያዊ አነጋገር ሴት ጭስ ከመሞቅ መለየቷ አግባብ አለመሆኑን የሚገልጽ በመሆኑ ጭስ የመሞቅን ባህል ቀጣይነት የሚያስረግጥ ነው፡፡ ነገር ግን የጭስ መሞቅ ክዋኔ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መጥቷል፡፡ ከላይ በሁለተኛነትና በሶስተኛነት የቀረቡት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ይህን የሚገልፁ ናቸው፡፡ በሁለተኛነት የቀረበው ምሳሌያዊ አነጋገር አጥፊና ጠፊ የሆኑት ድመትና አይጥ ታርቀው ጠላትነታቸው ቀርቷል፤ ወዳጅ የነበሩት ሴትና ጭስ ደግሞ ተጣልተዋል በማለት ጭስ የመሞቅ ባህል በከፍተኛ ሁኔታ እየቀረ መምጣቱን ይገልፃል፡፡ በሶስተኛነት የቀረበው ምሳሌያዊ አነጋገር ደግሞ ሁለቱን ለሚያስታርቅ ማለትም ጭስ የመሞቅ ባህልን ለሚመልስ ካሳ እከፍላለሁ አለ ሰውዬው በማለት ጭስ የመሞቅ ባህል እየቀረ መምጣቱ አባወራዎችን ቅር ማሰኘቱን በመጠቆም የጭስ ባህል መቅረት የለበትም የሚል ሀሳብን ይገልፃል፡፡ ምሳሌያዊ አነጋገሮቹ በተለይም በሁለተኛነትና በሶስተኛነት የቀረቡት ጭስ የመሞቅ ባህል ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል የሚል ሀሳብን የያዙ ናቸው፡፡

አራሷን የምታሞቃትና የምታጥባት በቅርብ ሆና የምትንከባከባት ሴት ናት፡፡ አራሷ ከሰባት ቀን እጥበቷ በኋላ ጓዳ መከተቷ ቀርቶ ቤት ለቤት መንቀሳቀስ ትጀምራለች፣ ሰው ከሌለና

ከተቸገረች ቀለል ቀለል ያሉ ስራዎችን ትሰራለች (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 13/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በቅዳሜና ረቡዕ ቀኖች ገላን መታጠብ ትኩሳት ያመጣል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከመታጠብ በተጨማሪ በእነዚህ ቀናት ልብስ ማጠብና ፀጉር መላጨትም ይከለከላል፡፡ ከሰዓትም አንፃር ገላን መታጠብ የሚመከረው ጠዋትና ረፋድ ላይ ሲሆን በቀትርና ከቀትር በኋላ መታጠብ እንዲሁ ትኩሳትና ድባቴ ያስከትላል ተብሎ ይታመናል፡፡ የሚከተለው ምሳሌያዊ አጋገር የእጥበት ሰዓትን በተመለከተ የሚያስተላልፈው መልዕክት አለ፡፡

- የጠዋት እጥበት አርባ ዓይነት በሽታ ይነቅላል፣ የከሰዓት በኋላ እጥበት አርባ ዓይነት በሽታ ይተክላል (ወ/ሮ እመይ መሐመድ ነጋሽ፣ 18/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር አራስ ሴት በወለደች ሰባተኛና አርባ ቀን ላይ የምታደርጋቸውን እጥበቶች የሚመለከት ሲሆን በጠዋት የሚደረግ እጥበት ጤናን የሚያስገኝ፤ በአንፃሩ ከቀትር በኋላ የሚደረግ እጥበት ደግሞ ጤናን የሚነሳ መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡ ምሳሌያዊ አነጋገሩ ብሄረሰቡ ለሰዓት ያለውን ግንዛቤና እምነት የሚገልጽና ከወሊድ ስነ ስርዓት አንዱ ክዋኔ የሆነው የእጥበት ስነ ስርዓት የሚከወንበትን ሰዓት የሚወስን ነው፡፡ በመሆኑም ምሳሌያዊ አነጋገሩ እምነትንና ክዋኔን በማጽናት ቀጣይነት እንዲኖረው የማድረግ ተግባር አለው ለማለት ይቻላል፡፡

በመሆኑም አራስ ሰባቷ በቅዳሜ ወይም በረቡዕ ቀን ከዋለ እጥበቱ ለማግስቱ ይተላለፍና በስምንተኛው ቀን እንዲከወን ይደረጋል፤ በምትታጠብበት ቀንም የምትታጠበው በጠዋት ነው፡፡ በዚያ ቀን አራሷ እንቅልፍ ከወሰዳት አራስ ለሚከታተል እርኩስ መንፈስ ትጋለጣለች ተብሎ ስለሚታመን ጋደም እንድትል እንጂ በቀን ተኝታ እንቅልፍ እንዲወስዳት አይፈለግም (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 13/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

**አቂቃ፣**

አቂቃ የህፃኑ አባት ልጅ ማግኘቱን የሚመሰክርበት ሀይማኖታዊ መሰረት ያለው የግዴታ ስነ ስርዓት ነው (Ismaiel num.[22] 5049)፡፡ በእስልምና ሀይማኖት አስተምህሮ መሰረት አንድ ልጅ ተወልዶ 15 ዓመት ሳይሞላው ከሞተና አቂቃ ተደርጐለት የነበረ ከሆነ በወዲያኛው ዓለም ለእናትና ለአባቱ ምስክር ሆኖ ያስምራቸዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ልጅ ተወልዶ ወዲያው ቢጠፋ እንኳን አቂቃ ይደረግለታል፡፡ ይህ ስነ ስርዓት በአብዛኛው ልጅ ተወልዶ በሰባተኛው ቀን ይከወናል፡፡ አቂቃው በሰባተኛው ቀን የሚደረግ ከሆነ ደግሞ አባት ደረሳዎችን በመጥራት ይጋብዝና ዱዓ ይደረጋል (አቶ ኢብራሂም ይርጉ፣ 22/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የስነ ስርዓቱ ክዋኔ ዋና መገለጫ የእርድ ስነ ስርዓት የሚከወን መሆኑ ነው፡፡ ሀይማኖታዊ በሆነ ደንብ (Abu Dawud num. 2842) ህፃኑ ወንድ ከሆነ ሁለት ፍየል ወይም በግ፣ ሴት ከሆነች ደግሞ አንድ ፍየል ወይም በግ ይታረዳል፤ የሚታረደው ፍየል ሁለት ዓመት እድሜ የሆነው፣ በግ ከሆነ ደግሞ አንድ ዓመት የሆነው መሆን አለበት፡፡ የሚታረደው ፍየል ወይም በግ በእድሜው ይታወቃል ወይም በዚህ እድሜ ላይ የሚገኝ ለመሆኑ ሁለት ጥርስ የሸረፈ መሆኑ ታይቶ ይለያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የሚታረደው ፍየልም ሆነ በግ አካሉ ያልጐደለ ማለትም ጆሮው ያልተቆረጠ፣ አይኑ ያልጠፋ፣ እግሩ ያልተሰበረ ወይም የማያነክስ፣ ወዘተ መሆን አለበት፡፡ አቶ ኢብራሂም ይርጉ (22/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) እንደገለፁት እርድ ከተከናወነ በኋላ ስጋው አጥንቱ ሳይሰበር ወይም ሳይከሰከስ መለያያ መለያያው ላይ ብቻ ተቆርጦ ይቀቀላል፡፡ ሲበላም ስጋው ከላዩ ላይ እየተላጠ ተበልቶ አጥንቱ አንድም ሳይቀር ተመልሶ ይሰበሰብና በንፁህ ጨርቅ ተቋጥሮ ይቀበራል፡፡ የተጠሩ ደረሳዎችና ሌሎች ወንዶች ምግብ ከበሉና ዱዓ አድርገው ቡና ከጠጡ በኋላ ሰለዋት ያደርጋሉ፡፡

**ስም ማውጣት፣**

ስም የሚወጣውም በዚሁ ቀን ነው፡፡ በአርጐባዎች ዘንድ ስም በዋናነት በአራት መንገድ ይወጣል፡፡ አንደኛው የህፃኑ ወላጆች የወላጆቻቸውን ወይም የሌላ ቤተሰባቸውን አባል ስም

---

[22] የMLA ምንጭ አጠቃቀስ ዘዴ ሀዲስ መጻሕፍት በቁጥር ሲጠቀሱ ከቁጥሩ አስቀድሞ num. የሚል (number የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል አጥሮ) መግለጫ እንዲኖር የሚያዝዝ በመሆኑ ጥቅም ላይ የዋለ ነው፡፡

ለልጃቸው የሚሰጡበት፣ ሁለተኛው መጽሐፍን መነሻ በማድረግ ስም የሚወጣበት፣ ሶስተኛው በአካባቢ የነበሩ ወልዮችን መጠሪያ ለልጅ የሚሰጥበት መንገድ ሲሆን አራተኛውና አልፎ አልፎ የሚታየው ህፃኑ በማህፀን በነበረ ጊዜ ያጋጠሙ ግላዊም ሆነ ማህበራዊ ገጠመኞችን መሰረት በማድረግ ስም ማውጣት ነው፡፡ የህፃኑ ወላጆች ከእነዚህ ከስም ማውጫ አማራጮች መካከል የትኛውን መጠቀም እንዳለባቸው ተመካክረው ይወስናሉ (አቶ መሐመድ ሲራጅ፣ 8/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የመጀመሪያውን አማራጭ በመጠቀም ከወሰኑ በማናቸው ወላጅ፣ እህት፣ ወንድም፣ አጐት ወይም አክስት ስም እንደሚጠሩ በመለየት ህፃኑ ወንድ ከሆነ የአንዳቸውን አባት፣ ወንድም ወይም አጐት ስም፣ ሴት ከሆነች ደግሞ የአንዳቸውን እናት፣ እህት ወይም አክስት ስም ይሰጣሉ፡፡ የቤተሰብ አባል በሆነ ሰው ስም የተጠራ ልጅ በተለየ በእንክብካቤ ይያዛል፣ ቢያጠፋ እንኳን ይገሰፃል እንጂ ከበድ ያለ ግርፊያ አይገረፍም፡፡ በቤተሰብ አባል ስም ስለተጠራ እንደተጠራበት ቤተሰብ አባል ስለሚመሰል በተለየ ሁኔታ ያድጋል፡፡ ስያሜው በወላጆች ስም ከተደረገና ሴት ልጅ በእናት ስም የተሰየመች “ይና ሙጋ”፤ ወንድ ልጅ በአባት ስም የተሰየመ ከሆነ ደግሞ “አባ ሙጋ” እየተባለ ይጠራል እንጂ በተሰጠው የወላጅ ስም በቀጥታ አይጠራም፡፡ “ይና ሙጋ” እና “አባ ሙጋ” ቃላቱ አፋርኛ ሲሆኑ በቅደም ተከተል የእናቴ ሞክሼ እና የአባቴ ሞክሼ የሚል ትርጉም አላቸው፡፡ ልጅ በስማቸው የተጠራላቸው የቤተሰብ አባላት ለልጁ ፍየል ወይም ጥጃ በስጦታ ይሰጣሉ፡፡ ይህን የስያሜ መንገድ የመረጡ ወላጆች ስያሜው በማናቸው ቤተሰብ ስም እንደሚሰየም በመወያየት በስምምነት ይወስናሉ (አቶ መሐመድ ሲራጅ፣ 8/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ሁለተኛው ስም የማውጫ መንገድ ቁርዓንን መነሻ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም መጽሐፍ ታይቶ ስማቸው በመጽሐፍ ተጠቅሶ የሚገኝ ነቢዩና ነቢዩን የተከተሉ ሰዎች የተወለዱበት እለት ይታያል፡፡ ህፃኑ በተወለደበት ቀን የተወለደ ካለ የህፃኑ ስም በዚያ ሰው ስም እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ይህም ለምሳሌ ነቢዩ መሐመድ የተወለዱት ሰኞ እለት በመሆኑ ሰኞ ለተወለዱ ወንድ ልጆች መሐመድ የሚል ስም መስጠት፣ የነቢዩ መሐመድ እናት የተወለዱት ሀሙስ እለት በመሆኑ ሀሙስ ለተወለዱ ሴት ልጆች አሚና የሚል ስም መስጠት ማለት ነው፡፡ በአንድ እለት የተወለዱ ከአንድ በላይ ሰዎች በመጽሐፍ ተጠቅሰው የሚገኙ ከሆነ እጣ ይወጣና በወጣው እጣ መሰረት ስም ይሰየማል (አቶ መሐመድ ሲራጅ፣ 8/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ሶስተኛው መንገድ በአካባቢው የሚከበሩ ያለፉ ወልዮችን ስም አዲስ ለተወለደ ህፃን መጠሪያነት መጠቀም ሲሆን አልፎ አልፎ የሚታየው አራተኛው የስም አወጣጥ መንገድ ልጁ በማህፀን ሳለ ወይም በተወለደ ጊዜ ወላጆች ያጋጠሟቸውን ነገሮች መሰረት በማድረግ ስም የማውጣት ልማድ ነው፡፡ ለምሳሌ ወላጆች በዚህ ጊዜ ሀብት ቢያገኙና ኑሯቸው በበጐ ቢለወጥ የተወለደውን ልጅ ወንድ ከሆነ ሀብታሙ፣ ሴት ከሆነችም ሀብታም ብሎ መሰየም ማለት ነው (አቶ መሐመድ ሲራጅ፣ 8/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በማህበረሰቡ በተለያዩ ምክንያቶች ከእነዚህ የስም ማውጫ መንገዶች ውጭ ስም የተሰጣቸው ልጆች አጋጥመውኛል፡፡ ከመረጃ ሰጪዎች መካከል አንዱ የነበሩት አቶ ኡመር አሊ የመጀመሪያ ልጃቸውን ስም ያወጡት ከዚህ ልማድ ውጭ ሲሆን የዚህን ምክንያት በሚከተለው መልኩ አስረድተዋል፡፡

> በወላጆቻችን ስም ልጄን ለመጥራት አስቤ ነበር፡፡ ያላደረግሁበት ምክንያቴ የመጀመሪያ ልጄ ስለሆነች ወደፊት እኔም ከፍ እያልኩ ስሄድ፣ ልጅንም ማሳደግ እንዴት እንደሆነ ሳውቀው ነው በእናቴ ወይም በአባቴ፣ በእናትሽ ወይም በአባትሽ ስም የምንጠራው ተባብለን ተመካክረን ነው ሌላ ስም የሰጠናት፡፡ በወላጅ ስም ጠርቶ መግረፍም መቆጣትም ያስቸግራል (10/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በመሆኑም አልፎ አልፎም ቢሆን ከተለመደው የስም አወጣጥ ልማድ ውጭ ስም ማውጣት አለ ማለት ነው፡፡

**ግርዛት፣**

የተወለደው ህፃን ወንድ ከሆነ በሰባተኛው ቀን ወይም ከዚያ በኋላ ባሉ ቀናት ይገረዛል፡፡ ግርዛቱን የሚያከናውኑ የተለዩ ባለሙያዎች አሉ፡፡ ግርዛት ከተከናወነ በኋላ ቁስሉ ቶሎ እንዲደርቅ የኮሶ ቅጠል በጨርቅ ተቋጥሮ በቅቤ እየተሞቀ ቁስሉ ይተኮሳል (ወ/ሮ ፋጡማ መሐመድ፣ 9/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የሽግግር ጊዜ የነፍሰጡርነትን ጊዜና ከወሊድ በኋላም የመንፃት ስነ ስርዓት እስከሚከወንበት አርባኛ ቀን ዋዜማ ድረስ ያለውን ጊዜ ይይዛል፡፡ ይህ ጊዜ ነፍሰጡሯ ነፍሰጡር በመሆኗ ምክንያት ቀደም ሲል ከነበረችበት ቡድን የተለየችበት ነገር ግን ብትወልድም የተጣሉባት ማዕቀቦች ተነስተው ወደነበረችበት ቡድን ለመቀላቀል ጊዜው ያልደረሰላት የምትሆንበት ጊዜ ነው፡፡

በሽግግር ጊዜ ነፍሰጡር ነፍሰጡር በመሆኗ ምክንያት በተለየ የአኗኗር ሁኔታ ውስጥ የምትሆንበትና በርካታ ክልከላዎችን የምታስተናግድት ጊዜ ነው፡፡ ነፍሰጡርን የስጋና የጋብቻ ዘመዶቿና ጐረቤቶቿ ከሌላው ሰው በተለየ ያምራታል፣ ይሽታታል በማለት በተለየ ምግብ ይንከባከቧታል፤ የቤት ውስጥ ስራዎቿን እየሰሩ ወይም እያገዙ ይንከባከቧታል፤ ነፍሰጡር ከሌላው ሰው በተለየ በሰው ዓይንና በእርኩስ መንፈስ ምክንያት ለሚመጡ ህመሞች የተጋለጠች ነች ተብሎ የሚታመን በመሆኑ ሰዎች አይናቸውን ሰበር አድርገው እንጂ አተኩረው አያዩዋትም፤ ነፍሰጡር በመንገድ ስታጋጥም "እንትፍ እንትፍ" ይባላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ነፍሰጡር በምግብ፣ በአረማመድ፣ በአቀማመጥ፣ በአተኛኘት፣ በድርጊትና እንቅስቃሴ ክልክሎች ያሉባት መሆኑና እነዚህንም አስመልክቶ ምክር የሚሰጣት መሆኑ በአርጐባዎች ልማድ ነፍሰጡር በሽግግር ላይ መሆኗን የሚያሳዩ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ በወሊድ ጊዜም ወላዷ በምጥና በወሊድ ጭንቅ የምትያዝበትና መስዋዕትነት የምትከፍልበት፣ በነፍሰጡሯ አካባቢ ያሉ ሰዎችም የሚጨነቁበት፣ ነፍሰጡሯ ምጧ እንዲገራና በሰላም እንድትገላገል የምጥ አግሪዎቹ ስም እየተጠራ ልመና የሚደረግበት፣ ዱዓ የሚደረግበት ነው፡፡ ከወሊድ በኋላም ምንም እንኳን ይህን መሰሉ ጭንቀት የቀነሰ ቢሆንም ወላዷ አራስ በመሆኗ ለህመም የተጋለጠች ነች ተብሎ የሚታሰብ በመሆኑ በመኝታዋ አካባቢና ለሽንት በምትወጣ ጊዜ መከላከያ መያዟና ብቻዋን እንዳትሆን መደረጓ፣ እርሷና ህፃኑ በምግብና በንጽህና እንክብካቤ የሚደረግላቸው መሆኑ፣ አራሷ በፈሰሳትና በሚፈሳት ደም ምክንያት ንፁህ እንዳልሆነች ስለሚቆጠር ፆም የማትፆም፣ ስግደት የማትሰግድና ፆታዊ ግንኙነት የማታደርግ መሆኗ፣ የቤት ውስጥ ስራዎችን የማታከናውንና በማህበራዊ ህይወት ውስጥ የማትሳተፍ መሆኗ ይህ ነው በሚባል ደረጃ ላይ አለመሆኗንና በሽግግር ላይ መሆኗን የሚያሳዩ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ይህ ደረጃ ነፍሰጡሯም ሆነ ወላዷ አኗኗሯ የሚለይበት፣ በተጽዕኖና ማዕቀብ ውስጥ የምትቆይበት፣

እርሷና በዙሪያዋ ያሉ ሁሉ የሚጨነቁበት፣ ምጥ ያለበት፣ ከወሊድ በኋላም ወላዷና ህፃኑ በተለየ እንክብካቤና ማዕቀብ ውስጥ የሚያልፉበት ነው፡፡

### 5.2.3. መቀላቀል

ወላዷ በወለደች አርባኛ ቀን በምታደርገው እጥበት ቀደም ሲል ወደነበረው ህይወቷ፣ ወደ ቤተሰቧና ወደ ማህበረሰቡ የምትቀላቀል በመሆኑ ከአርባኛ ቀን እጥበት ጀምሮ ከዚያ በኋላ ያለው ጊዜ የወላዷ መልሶ የመቀላቀያ ጊዜ ነው፡፡ በመሆኑም በዋናነት የአርባ ቀን እጥበት ስነ ስርዓት ክዋኔ እና ከዚያ በኋላ ያሉ የማዘየሪያና የቁንጮ መጣያ ስነ ስርዓቶች የመቀላቀያ መገለጫዎች ናቸው፡፡

#### 5.2.3.1. የአርባ ቀን እጥበት ስነ ስርዓት

የአርባ ቀን እጥበት እንደሌላው ቀን እጥበት የንጽህና ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ከዚያ ከፍ ያለ ትርጉም ያለው የመንፃት፣ የመሻገር እጥበት ነው፡፡ አራስ በወሊድ ጊዜና ከዚያ በኋላ በፈሰሳት ደም ምክንያት ንፁህ እንዳልሆነች የሚታሰብ በመሆኑ በወለደች አርባኛ ቀን የግዴታ እጥበቷን በመታጠብ ንፁህ ካለመሆን ንፁህ ወደመሆን ትሸጋገራለች (አቶ መሐመድ ሰዒድ፣ 8/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በአርባ ቀን እጥበት የሰባት ቀን እጥበት ጊዜ የነበረውን ዓይነት የተስፋፋ ስነ ስርዓትና ብዙ ሰው አይኖርም፡፡ የአራሷን እጥበት አስታውሰው የሚሄዱ በቁጥር ጥቂት የሆኑ ሴቶች ብቻ ሊኖሩ የሚችሉ ሲሆን የሚጋበዙትም ቤት ያፈራውን ነው (ወ/ሮ ጀሚላ አሕመድ፣ 13/7/2013፣ ጉዜ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በእለቱ ቡና ተፈልቶና ዳቦ ተቆርሶ ዱዓ ከተደረገና ቡናው ከተጠጣ በኋላ አራሷ ትታጠባለች፡፡ የአራሷ እጥበት ንይት ያለው የግዴታ እጥበት በመሆኑ ሌሎች ሴቶች ውሃ ያቀራርቡላታል፣ ይረዷታል እንጂ እንደ ሰባት ቀን እጥበት ገላዋን አያጥቧትም፡፡ አራሷ የግዴታ እጥበት ከመታጠቧ በፊት ሰውነቷን መጀመሪያ በተቀቀለ የወይባ ቅጠልና በውሃው፣ ከዚያ በኋላ በውሃና በሳሙና ታጥባ ንፁህ መሆን ይጠበቅባታል፡፡ ከዚያ በኋላ የግዴታ እጥበቱን በንፁህ ውሃ ብቻ ነይታ ትታጠባለች፡፡ አራሷ ገላዋን ታጥባ ከጨረሰች በኋላ ከመውለዷ በፊት የተሰራውን ፀጉሯን ፈትታ እንደገና ትሰራለች፣ ቅቤ ተቀብታ አዝጋሮና ሽታ ትሞቃለች፣ አይኗን ትኩላለች፣ ጌጧን ታደርጋለች፣ እግርና እጇን ሂና

ትታሰራለች፡፡ አራሷ እንደ ሰባት ቀኑ እጥበት በዚህም የእጥበት ቀን በቀን አትተኛም፡፡ አርባ ቀን የአራስነት ማብቂያ በመሆኑ አራሷ የተኛችበት አልጋ ወጥቶ በሰባተኛው ቀን በታጠበበት መንገድ ታጥቦ ለፀሀይ ይሰጣል፤ ልብሷም ይታጠባል (ወ/ሮ ከዲጃ መሐመድ፣ 13/7/2013፣ ጐዜ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ብሂረሰቡ የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ እንደመሆኑ በሀይማኖቱ አስተምህሮ መሰረት (Abu Dawud num. 311) አራስ አርባ ቀን ሆኗት የግዴታ እጥበቷን እስከምትታጠብ ድረስ ንፁህ እንዳልሆነች ስለሚታሰብ ፆም አትፆምም፤ ስግደትም አትሰግድም፤ ከባለቤቷ ጋር ፆታዊ ግንኙነት አታደርግም፡፡ የአራስነት ጊዜዋ ስላላለቀና ሰውነቷም ያልበረታ ስለሆነ የቤት ውስጥ ከባድ ስራዎችን አትሰራም፤ ወደ ውጭ ወጥታ በማህበራዊ ኑሮ እንቅስቃሴ ውስጥ አትሳተፍም፤ አራስ በመሆኗ መከላከያ የሚሆናት ብረት አይለያትም፡፡ ነገር ግን ከእጥበቱ በኋላ አራሷ የአራስነት ጊዜዋ ያበቃል፤ ፆም መፆምና ስግደት መስገድ፣ ፆታዊ ግንኙነት ማድረግ፣ አብዛኛዎቹን የቤት ስራዎችን መስራት፣ ቀስ በቀስ በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ መሳተፍና የበሽታ መከላከያ ብረት መተው ወይም አለመያዝ ትጀምራለች (ወ/ሮ እሙ መነልከሪም፣ 14/7/2013፣ ጐዜ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

አብዛኛዎቹን የቤት ስራዎች ትሰራለች የተባለው ከባድና ሩቅ መሄድን የሚጠይቁ ስራዎችን የምትሰራው ከአርባ ቀን በኋላ በአንድ ጊዜ ሳይሆን በሂደት ስለሆነ ነው፡፡ እንደ ገበያ መሄድና ሌሎች ከበድ ያሉ ስራዎችን ጐረቤቶቿ እያገዟት እርሷ በሂደት የምታከናውናቸው ናቸው፡፡ ከዚያ በኋላ ወደ ቀደመው የእለት ተእለት እንቅስቃሴዎቿ ትመለሳለች፡፡ በዚህ መልኩ ቀደም ወዳለው ህይወቷ ትመለሳለች፤ ነገር ግን ስትመለስ ቀደም ሲል የነበራት ማንነት በተወሰነ መጠን ይቀየራል፤ የምትመለሰው በተለየ የእናትነት ገጽታ ይሆናል፡፡

### 5.2.3.2. የማዘየሪያ ስነ ስርዓት

ማዘየሪያ ከአርባ ቀን በኋላ ባለ በማንኛውም ጊዜ፣ ወላጇና ባለቤቷ የሚመቻቸውን ቀን መርጠው ህፃኑን በመያዝ ወደ ወላጆቻቸው ወይም ወደ ሌላ በእድሜ ታላቅ ወደሆነ የቤተሰባቸው አባል በመሄድ የሚያደርጉት ጥየቃ ነው፡፡ ተጠያቂዎቹ የህፃኑ አያቶች፣ የወላጆቹ አክስቶች ወይም አጐቶች፣ እነዚህ የቤተሰብ አባላት በህይወት ከሌሉ ደግሞ በዝምድና ሀረግ ቀረብ የሚሉና በእድሜ ታላቅ የሆነ የቤተሰብ አባል ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ከዚህ ውጭ ደግሞ ጥየቃ በመንፈሳዊነታቸው ትልቅ ቦታ ወደሚሰጣቸው የሃይማኖት አባቶች ዘንድ በመሄድ ይከወናል (አቶ ኢብራሂም ወርቁ፣ 9/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ጥየቃ በዋናነት ህፃኑን በማሳየት እንዲመረቅ የማድረግ ዓላማ ያለው ሲሆን ዘር መገኘቱን በማሳየት ተጠያቂዎቹን ማስደሰት ሌላው ዓላማ ነው፡፡ ተጠያቂዎቹ ዘር በዛልን ብለው መደሰታቸውና አምላክን ማመስገናቸው ለህፃኑ መልካም ነገር ያስገኛል ተብሎም ይታመናል (አቶ ኑሩ መሐመድ፣ 13/7/2013፣ ጐዜ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የህፃኑ ወላጆች ለጥየቃ ለሚሄዱበት ቤተሰብ የሚሄዱበትን ቀን አስቀድመው ያሳውቃሉ፡፡ በዚያ ቀን ተጠያቂዎቹ መጠነኛ ድግስ በማዘጋጀት ጐረቤት ጠርተው ጠያቂዎቹን ይቀበላሉ፡፡ ጠያቂዎቹ እንደ አቅማቸው ለተጠያቂዎቹ ፍየልና ልብስ ይዘው ይሄዳሉ፡፡ በእለቱ ተዘያሪው ወይም ተዘያሪዎቹ ህፃኑን አቅፈው "እንትፍ እንትፍ" ብለው ዱዓ የሚያደርጉለት ሲሆን የህፃኑ ወላጆች "አሚን" በማለት ዱዓውን ይቀበላሉ፡፡ ዱዓው ህፃኑ በሰላም እንዲያድግ፣ ለወግ ማዕረግ እንዲበቃና ወላጆቹን ጧሪ እንዲሆን የሚደረግ ነው (ወ/ሮ ጀሚላዬ ሼህ ይማም፣ 14/7/2013፣ ጐዜ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

### 5.2.3.3. የቁንጮ መጣያ

የመጀመሪያ ፀጉር ለሰው ዓይን መከላከያ ነው ተብሎ ስለሚታመን ህፃኑ ወንድ ከሆነ ፀጉሩ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲላጭ ተቋጥሮ በህፃኑ አንገት ላይ ይታሰራል፡፡ ፀጉሩ ሲላጭ ግን ትንሽ ቁንጮ ይተውለታል፡፡ ቁንጮ የሚተውለት የሰው ዓይን መከላከያ ይሆነዋል፤ በእርግብግቢቱ ንፋስ እንዳይገባም ይከላከልለታል በሚል ምክንያት ነው፡፡ ከዚያ በኋላም ቁንጮ እየቀረለት ሲላጭ ይቆይና ከፍ ሲል ለመጀመሪያ ጊዜ ቁንጮው ሲላጭ አያቱ፣ አባቱ፣ አክስቱ ወይም አጐቱ የቁንጮ መጣያ ብለው አንድ ሴት ፍየል ወይም ጥጃ ይሰጡታል፡፡ የተላጨው ፀጉር ተቋጥሮ በስጦታው ፍየል ወይም ጥጃ ላይ ይጣልና ፍየሉ ወይም ጥጃው የቁንጮ መጣያው ነው ተብሎ ይረባለታል፡፡ ቁንጮ የሚጣልበት ውሱን ጊዜ የለውም፤ የህፃኑ ቁንጮ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲላጭ የሚከወን ነው (ወ/ሮ ሞሚና ሰኢድ፣ 9/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በመቀላቀል ጊዜ በተለይ የመጀመሪያ ወሊድ ሲሆን ወላዷ በተለየ የእናትነት ገጽታ ወደ ማህበረሰቡ ትቀላቀላለች፡፡ ወላዷ ቀደም ሲል ታከናውናቸው የነበሩ ጉዳዮችን ማለትም ፆም መፆም፣ ስግደት መስገድ፣ የታዊ ግንኙነት ማድረግ፣ የቤት ውስጥ ስራዎችን በሙሉ

መስራት፣ ከአራስነት ወጥታ በተለያዩ ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች መሳተፍ፣ የአራስነት የህመም መከላከያዎችን መጠቀም ማቆም ትጀምራለች፡፡

እነዚህ የመዋቅር ደረጃዎች ከህፃኑ አንፃር ሲታዩ ህፃኑ የሚነጠለው በወሊድ ጊዜ እትብት ሲቆረጥ ነው፡፡ ህፃኑ ከሚያውቀው የቀደመ ዓለም፣ ከእናቱ ማህፀን ወጥቶ አዲስ ዓለምን የሚቀላቀልበትና ከእናቱ የሚለይበት ነው፡፡ የሽግግር ጊዜው ደግሞ ተወልዶ እትብቱ ከተቆረጠበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሰባተኛው ቀን እጥበት ዋዜማ ድረስ የሚቆይ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ህፃኑ አዲስ ወደሆነ ዓለም ይምጣ እንጂ ወደ ማህበረሰቡ ያልተቀላቀለበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ህፃኑ በምግብ፣ በንጽህናና ጤንነቱን በተመለከተ እንክብካቤ እየተደረገለት ይቆያል፡፡ የህፃኑ የመቀላቀያ ጊዜ ከሰባተኛው ቀን እጥበት ጀምሮ እስከ ቁንጮ መጣያ ክዋኔ ድረስ ያለው ነው፡፡ የሰባተኛ ቀን እጥበት ቀን የህፃኑ አባት አቂቃ በማድረግ ልጅ ማግኘቱን በይፋ የሚያሳውቅበትና ለህፃኑም ስም የሚወጣበት ቀን በመሆኑ ህፃኑ ለማህበረሰቡ የሚተዋወቅበትና የሚቀላቀልበት ነው፡፡ አዲስ ህፃን ወደ ምድር መምጣቱን በመመስከርና መጠሪያ የሚሆነውን ስም በመሰየም ህፃኑ ለማህበረሰቡ ይተዋወቃል፡፡ በማዘየሪያ ስነ ስርዓት ህፃኑን ለቤተሰብ አባላት ወይም ለታላላቅ ሰዎች ማሳየትና ማስተዋወቅ እንዲሁም በቁንጮ መጣያ ለልጁ ስጦታ በመስጠት በልጁና በስጦታ ሰጪው መካከል ቅርበት እንዲኖር ማድረግ ልጁ ከቤተሰብና ከማህበረሰብ ጋር እንዲቀላቀል የሚያደርጉ ክዋኔዎች ናቸው፡፡

## 5.3. የአርጎባ ብሄረሰብ የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ ፋይዳ

የአርጎባ ብሄረሰብ የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ ለከዋኞቹ ማህበራዊ ኑሮን ከማጠናከር፣ ስነ ልቡናን ከማረጋጋት፣ እሴቶችን ከመትከልና ጤናን ከመጠበቅ አንፃር የሚያስገኘው ጠቀሜታ አለው፡፡

### ማህበራዊ ፋይዳ፣

ከወሊድ በፊት፣ በወሊድ ጊዜና ከወሊድም በኋላ ወላዷን በጉልበት ማገዝ፣ በምግብ መንከባከብ፣ አራስን መጠየቅ፣ በጋራ መመገብ፣ ወዘተ የሰዎችን ማህበራዊ ኑሮ ያጠናክራል፡፡ ሰዎች ነፍሰጡርንና አራስን በስራ ማገዛቸው፣ በምግብ መንከባከባቸውና መጎብኘታቸው ፍቅራቸውን፣ አብሮነታቸውን መግለፃቸው ነው፡፡ በአንድ ገበታ ቀርቦ በጋራ መመገብ ማህበራዊ ጥምረትን፣ ህብረትን የሚያስገኝ ልማድ ነው፡፡

**ከአደጋ የመጠበቅ ስሜትን የመስጠት ፋይዳ (ስነ ልቡናዊ ፋይዳ)፣**

እዚህ ሁለት ጉዳዮችን ማንሳት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ጉዳይ ባህላዊ ህክምና ሲሆን ሁለተኛው የአምሮት ስነ ስርዓት ነው፡፡ ነፍሰጡርና አራስ በሰው ዓይንና በእርኩስ መንፈስ ለሚመጣ ህመም የተጋለጡ ናቸው ተብሎ የሚታመን በመሆኑ ህመም ከመምጣቱ በፊት በባህላዊ የህክምና ዘዴ መከላከያ ይሰራል፤ ህመሙ ከመጣም በኋላ መድኃኒት ይዘጋጃል፡፡ ከወሊድ ጋር የተገናኘ እክል ሲያጋጥምም ባህላዊ ህክምናው ዋነኛ የመሻር አማራጭ ነው፡፡ የአምሮት ስነ ስርዓት የሚከወንበት ዋነኛ ዓላማ ነፍሰጡሯ በሰላም እንድትወልድ ለማስቻል ዱዓ እንዲደረግላት ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም የባህል ህክምናው ለነፍሰጡሯ ወይም ለአራሷ ከክፉ መንፈስና ከህመም ተጠብቄያለሁ፣ ተከልያለሁ የሚል አእምሯዊ እረፍት ያስገኝላታል፤ በአምሮት ላይ የሚደረገውም ዱዓ ቀሪ የነፍሰጡርነት እና የወሊድ ጊዜዋን ቀና እንደሚያደርግላት ስለምታምን ሰላምን ያስገኝላታል፡፡

**እሴቶችን የመትከል ፋይዳ፣**

በወሊድ ስነ ስርዓት ውስጥ ያሉ እምነቶችና ሌሎች የፎክሎር አህዶች ከቀዳሚ ትውልድ የተወረሱና የሚተገበሩ ብሎም እየተተገበሩ ለመጪ ትውልድ የሚተላለፉ በመሆናቸው ስነ ስርዓቱ ነባር እሴቶችን መትከያም ነው፡፡ ወሊድን በተመለከተ የሚተገበር የባህል ህክምናና እምነቶች ተተግባሪነታቸው እስካለ ቀጣይነታቸውም ይረጋገጣል፡፡

**ጤና የማስገኘት ፋይዳ፣**

ነፍሰጡር ሴት ከመውለዷ በፊት የምትወልድበትን ቤትና አካባቢ በንጽህና መያዟ፣ ከወለደችም በኋላ የሚያርሷት ሴቶች አራሷን፣ ልብሷንና መኝታዋን በንጽህና መያዛቸው ለወላዷ ጤና መጠበቅ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ከወሊድ በፊትና ከወሊድም በኋላ ወላድ ሴትን በጥሩ ምግብ መንከባከብ ወላዷ የተመጣጠነ ምግብ እንድታገኝና ጤናዋ እንዲጠበቅ ያግዛል፡፡ ነፍሰጡር ሴት የሚሰጣት ምክርም ከጤና አንፃር ጠቀሜታን ያስገኝላታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ባህላዊና መንፈሳዊ ህክምናዎች ነፍሰጡርና አራስ ሴትን እንዲሁም ጨቅላ ህፃንን ከህመም ለመጠበቅና ለማከምም ጥቅም ላይ የሚውሉ መሆናቸው ከጤና አንፃር የሚያስገኘው ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

### 5.4. የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ ለውጥና ቀጣይነት

ስነ ስርዓቶች አንድ ዓይነት በሆነ ክዋኔ የማይፀኑና ለለውጥ የተጋለጡ ናቸው፡፡ በየጊዜው በሚደርስባቸው ውስጣዊና ውጫዊ ጫናዎች ምክንያት ለውጥን ያስተናግዳሉ፡፡ በምዕራፍ ሁለት ለለውጥ ምክንያት ሊሆኑ እንደሚችሉ የቀረቡ ጉዳዮች በአርጐባዎች የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ ላይ ለውጦችን ከስተዋል፡፡ ከዚህ በታች በስነ ስርዓቱ ላይ የተከሰቱ ለውጦች ከለውጥ ምክንያቶቻቸው አንፃር እና ያልተለወጡ የስነ ስርዓቱ ገጽታዎች ይቀርባሉ፡፡

#### 5.4.1. የተከሰቱ ለውጦች ከለውጥ ምክንያቶቻቸው አንፃር

በስነ ስርዓቱ ውስጥ የተከሰቱ ለውጦች ዘመናዊነትና የኢኮኖሚ ጫና ያስከተሏቸው ለውጦች ናቸው፡፡

##### 5.4.1.1. ዘመናዊነት ያስከተለው ለውጥ

ዘመናዊ የአኗኗር ዘይቤ መስፋፋት በባህላዊ ክዋኔዎች የተለያየ ገጽታ ላይ ለውጥ ያስከትላል፡፡ ይህም በአርጐባዎች የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔና በክዋኔው ቁሳዊ ባህል ላይ ለውጥ አስከትሏል፡፡

**ዘመናዊነት በወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ ላይ ያስከተለው ለውጥ፣**

ዘመናዊ የህክምና አገልግሎት መስፋፋቱን ተከትሎ በአርጐባ ልዩ ወረዳ ውስጥ ሁለት ጤና ጣቢያዎችና አስራ ሁለት ጤና ኬላዎች ተቋቁመው አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ ጤና ጣቢያዎቹ የሚገኙት በጋቺኔና በላይ መጠቅለያ ቀበሌዎች ውስጥ ሲሆን ጤና ኬላዎቹ ከጋቺኔ ውጭ ባሉ አስራ ሁለቱ ቀበሌዎች ውስጥ የሚገኙ ናቸው (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 2/2/2013፣ ጋቺኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የጤና ተቋማቱ ከሚሰጧቸው አገልግሎቶች መካከል የእናቶችና ህፃናት ጤና እንክብካቤ አገልግሎት አንዱ ነው፡፡ ጤና ጣቢያዎቹ የቅድመ ወሊድ፣ የወሊድና የድህረ ወሊድ አገልግሎት የሚሰጡ ሲሆን (ሲስተር አይሻ በድሩ፣ 23/2/2013፣ ጋቺኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) (ሲስተር አሚና በድሩ፣ 24/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) ጤና ኬላዎቹ በዋናነት የማመቻቸት ስራ ይሰራሉ፤ የድንገተኛ አደጋ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ በጤና ኬላ የሚሰሩ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ነፍሰጡሮችን ከወረዳ ጤና

ባለሙያዎች ጋር ያገናኛሉ፣ ለወሊድ የደረሱትንም ወደዚያ ይልካሉ እንጂ የነፍሰጡር ክትትል አያደርጉም፤ አያዋልዱምም፡፡ ነገር ግን አጣዳፊ ምጥሲያጋጥምና ወላዷ የወሊድ ችግር በሌለበት ሁኔታ መውለድ የምትችል ሲሆን ብቻ ከልምድ አዋላጆች ጋር በመሆን ያዋልዳሉ (ወ/ት እታገኝ ግርማ፣ 23/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ባለሙያዎቹ እንደገለፁት በጤና ተቋማቱ ውስጥ ነፍሰጡሮችና ወላድ ሴቶች በጤና ተቋማት ክትትል እንዲያደርጉና እንዲወልዱ ለማድረግ የማስተማርና የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ ይከናወናል፡፡ በዚህ ምክንያት ቀደም ሲል ሙሉ በሙሉ በቤት ውስጥ ይከወን የነበረው የወሊድ ስነ ስርዓት በአሁኑ ጊዜ በተወሰነ ደረጃ በጤና ተቋማት በሚደረግ ወሊድ ተተክቷል፡፡ ባለሙያዎቹ እንደሚሉት በዚህ ረገድ የታሰበውን ያህል ባይሆንም፤ አሁንም ክትትል የማያደርጉ ነፍሰጡሮችና በቤት ውስጥ መውለድን የሚመርጡ እናቶች ብዙ ቢሆኑም ለውጥ ግን አለ (ሲስተር አይሻ በድሩ፣ 23/2/2013፣ ጋቺኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) (ሲ/ር አሚና በድሩ፣ 24/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በጋቺኔና ላይ መጠቅለያ ቀበሌዎች ባሉ ጤና ጣቢያዎች ነፍሰጡሮች ክትትል ለማድረግና ለወሊድ በተቋማቱ ተገኝተውም ተመልክቻለሁ (21/2/2013፣ ጋቺኔ ቀበሌ፣ ምልከታ) (24/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡ በመሆኑም በዘመናዊ የህክምና መስፋፋትና በጤና ተቋማት በየጊዜው በሚሰጠው ትምህርት ነፍሰጡሮችና ወላድ ሴቶች ወደ ጤና ተቋማት መሄዱን እየለመዱ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በልማዳዊው የቅድመ ወሊድ፣ ወሊድና ድህረ ወሊድ ስነ ስርዓቶች ላይ ለውጥ አምጥቷል፡፡

ቅድመ ወሊድ የተከሰቱ ለውጦችን ስንመለከት ነፍሰጡሮች በልማድ እንዳይመገቧቸው የሚከለከሉ ምግቦችን መመገብ ጀምረዋል፡፡ በጤና ጣቢያ ያገኘኋቸው ነፍሰጡር በእርግዝናቸው ጊዜ የማይበሉ የተባሉትን ምግቦች ከግምት ባለማስገባት ያማራቸውን ምግብ እንደበሉ ነግረውኛል (ወ/ሮ አሚና ዝይን፣ 21/2/2013፣ ጋቺኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በወሊድ ጊዜ በባህላዊው የወሊድ ስነ ስርዓት ወላዷ በጐኗ በመተኛት ወይም በመቀመጥ የምትወልድ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ከዘመናዊ የማዋለድ አገልግሎት መስፋፋት ጋር በተያያዘ የልምድ አዋላጆች በቤት ውስጥ በሚያዋልዱበት ጊዜ በዘመናዊ የህክምና ተቋማት እንደሚተገበረው ወላዷን በጀርባዋ በማስተኛት ማዋለድን እየተገበሩት ነው፡፡

ወሊድ በጤና ተቋማት መደረጉ በድህረ ወሊድ የሚደረጉ ክዋኔዎችም ላይ ለውጥ አስከትሏል፡፡ ወሊድ በቤት ውስጥ ሲከናወን ይደረጉ የነበሩ የህፃኑን ገላ ማጠብ፣ ላንቃ ማንሳትና ቅቤ ማዋጥ ወሊድ በጤና ተቋም ሲደረግ አይከወኑም ወይም ከወሊዱ በኋላ ወላዷ ወደ ቤቷ ስትገባ ከመከወኛ ጊዜያቸው ዘግይተው ይከወናሉ፤ አራሶች በልማድ ይከለከሏቸው የነበሩ ምግቦችን መመገብ ጀምረዋል፡፡

**ዘመናዊነት በወሊድ ስነ ስርዓት ቁሳዊ ባህል ላይ ያስከተለው ለውጥ፣**

የዘመናዊነት መስፋፋት ከወሊድ ጋር የተያያዘ የቁሳዊ ባህል ለውጥን አስከትሏል፡፡ ከተከሰቱ የቁሳዊ ባህል ለውጦች መካከል አንዱ መገለጫ በምግብና መጠጦች ላይ የተከሰተው ለውጥ ነው፡፡ ለአምሮትና ለሌሎች ስነ ስርዓቶች የሚዘጋጁ ምግቦች ግብዓት ላይ፣ በህፃን ምግብና በአራስ ጠያቂዎች የማስተናገጃ ምግብ ላይ ለውጥ ተከስቷል፡፡ በአምሮት ስነ ስርዓትና በሌላም ጊዜ የሚዘጋጀው አነባበሮ፣ ዳቦና አሊጣ የሚዘጋጀው በድንጋይ ወፍጮ ወይም በወፍጮ ቤት ከተፈጨ የስንዴ ዱቄት የነበረ ሲሆን አሁን ግን በፋብሪካ ተዘጋጅቶ ከገበያ ከሚገዛ የስንዴ ዱቄት ይዘጋጃል፡፡ የገንፎ እህሉም አልፎ አልፎ በፋብሪካ የተዘጋጀ የስንዴ ዱቄት ይሆናል፡፡ የህፃን ምግብን በተመለከተ የእናት ጡት ወተት ሲቀንስ በፋብሪካ የተመረተ የህፃናት ወተት መስጠትና ውሃ በስኳር እያፈሉ ለህፃን መስጠት ተለምዷል፡፡ በአራስ ቤት ጠያቂ እንግዶች ሲመጡ ይስተናገዱበት የነበረው ምግብ እንጀራና ወጥ፣ የገብስ ቆሎና ቡና ቢሆንም በአሁኑ ግዜ ግን ይህ ቀርቶ እንግዶች የሚስተናገዱት በብስኩት፣ በዳቦ ቆሎና በሻይ ሆኗል፡፡ ምልከታ ባደረግሁባቸው የአራስ ቤቶች ሁሉ እነዚህ ምግቦች ቀርበውልኝ ቀምሻለሁ፡፡



ፎቶግራፍ 13. የአራስ ቤት እንግዶችን የማስተናገጃ ምግብ በዚህ መልኩ ተለውጧል፡፡

በማዋለጃ ቁሳቁሶች ላይም ለውጥ ተከስቷል፡፡ ማተቢያ ማግና መቁረጫ ምላጭ በዘመናዊ የኘላስቲክ ክርና መቀስ ተለውጠዋል፡፡ የተለያዩ ግብረ ሰናይ ድርጅቶችና የመንግስት የጤና ተቋማት የልምድ አዋላጆችን በዘመናዊ የማዋለድ ስራ አሰልጥነው የማዋለጃ ቁሳቁሶችንም የሰጧቸው በመሆኑ የልምድ አዋላጆች በቤት ውስጥ ሲያዋልዱ እንኳን በማግ ፋንታ ዘመናዊ የእትብት መቋጠሪያ ክር፣ በምላጭ ፋንታም መቀስ መጠቀም ጀምረዋል፤ ቀደም ሲል በባዶ እጃቸው የሚያዋልዱትም አሁን የእጅ ጓንት መጠቀም ለምደዋል፡፡

ለመኝታነት ጥቅም ላይ ይውል የነበረው የጠፍር አልጋ በዘመናዊ የእንጨት አልጋ እየተቀየረ መምጣቱ በቅድመ ወሊድ፣ በወሊድና በድህረ ወሊድ ስነ ስርዓቶች መከወኛ ቁሶች ላይ ለውጥ አስከትሏል፡፡ የተከሰተው የቁስ ለውጥ ደግሞ በወሊድ ስነ ስርዓቱ ላይ የክዋኔ ለውጥ አስከትሏል፡፡ በአምሮት ስነ ስርዓት ላይ የተጠሩ ሴቶች ገበታው ሲነሳ እጃቸውን ታጥበው አልጋ ስር የሚረጩት ውሀ በአልጋው ድፍን መሆን ምክንያት አልጋው ስር መረጨቱ ቀርቶ ወደ ጓዳ ውስጥ ብቻ ይረጫል፡፡ በወሊድ ጊዜ ወላዷ በጠፍር አልጋ ላይ መውለዷ ቀርቶ በዘመናዊ የእንጨት አልጋ ላይ ላስቲክና ከላይ ብርድ ልብስ ተነጥፎ እዚያ ላይ ትወልዳለች፡፡ ከወሊድ በኋላ ብርድ ልብሱ ከነላስቲኩ ተነስቶ ይወጣና ይታጠባል፡፡ ወላድ እንደወለደች ታርዶ በአራሷ አልጋ ስር እንዲንደፋደፍ የሚደረገው የደም ዶሮ አልጋው ድፍን ስለሆነ በአልጋ ስር መጣሉ ቀርቶ እዚያው አልጋው አካባቢ ይታረዳል፡፡ አራሷና ህፃኑ የሚተኙት በጠፍር አልጋ ላይ ሆኖ የልጁ ሽንት ወደታች ስለሚወርድ የቤቱን ንጽህና ለመጠበቅ አልጋ ስሩ እየተጠረገ ፍግ ይነሰነስበትና ጭስ ይጨስበት ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን አራስ በዘመናዊ አልጋ የምትተኛ በመሆኑ ይህ አይነቱ ነገር የለም፤ ለህፃኑም የሽንት ጨርቅ ይደረግለታል፡፡ ከወሊድ በኋላም በሰባትና በአርባ ቀን እጥበት ስነ ስርዓቶች ላይ አልጋ ደጅ አውጥቶ ማጠብና ለፀሐይ ማስጣት የለም፡፡ ከወሊድ በኋላ አራሷና ህፃኑ ገላቸውን የሚታጠቡት በጠፍር አልጋው ላይ መሆኑ ቀርቶ በሳፋ ላይ ሆኗል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የእንግዴ ልጅ ይቀበርበት የነበረው ቅል ተቀይሮ ጨርቅ ሆኗል፤ የአራስ ቤትን የከብት አዛባ ለቅልቆ ማዘጋጀቱ ቀርቶ ቀለም መቀባት ተለምዷል፣ አራስ ቤት የሚገደገደው ወይባ ቀርቶ መጋረጃ መጋረድ ተለምዷል፤ የምግብ ማብሰያና መመገቢያ እቃዎች ዘመናዊ የፋብሪካ ምርት በሆኑ ቁሶች ተተክተዋል፤ ለምሳሌ፣ ዳቦ

ሲጋገር ጥቅም ላይ ይውል የነበረው የሸክላ አክንባሎ ቀርቶ በዘመናዊ የብረት አክንባሎ መጠቀም ተለምዷል፣ የመመገቢያ ጣባ በትሪና በብረት ሰሀኖች ተቀይሯል፡፡

5.4.1.2. የኢኮኖሚ ጫና ያስከተለው ለውጥ

ኢኮኖሚያዊ ጫና በወሊድ ስነ ስርዓት ላይ ለውጥ አስከትሏል፡፡ በአምሮት ስነ ስርዓት ላይ የሚጠሩ ሰዎች ቁጥራቸው ብዙ የነበረ ሲሆን አሁን ግን የሚጠሩ ሰዎች ከቤተሰቡ ጋር የተለየ ቅርበት ያላቸው ብቻ ተመርጠው ነው፡፡ ለአራስ ሴት በቀን አንድ ወይም ሁለት ጊዜ ዶሮ ይታረድ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ግን ይህን ያህል ዶሮ ማረድ እየቀረ መጥቷል፡፡ ሰዎች ለአራስ መጠየቂያ የሚወስዱት ዶሮ፣ እንቁላልና ለጋ ቅቤ ዋጋ እየተወደደ በመምጣቱ ሰዎች እነዚህን ስጦታዎች በመተው ስኳር፣ ሳሙና፣ ለስላሳ መጠጦችንና ገንዘብ ይወስዳሉ፡፡ የአብሽ ውሀ የሚዘጋጅበት ማር አሁን ስኳር ሆኗል፡፡

5.4.2. ያልተለወጡ ጉዳዮች

ለውጥ የክዋኔ አንዱ መገለጫ ቢሆንም ለውጥን ተቋቁሞ የሚቀጥል የክዋኔ ክፍል ደግሞ ይኖራል፡፡ በመሆኑም በአርጐባዎች የወሊድ ስነ ስርዓት ቅድመና ድህረ ወሊድ ነፍሰጡርንና አራስን በምግብ መንከባከብ፣ በጉልበት ማገዝ፣ የቅምሻና የአምሮት ስነ ስርዓት ማከናወን፣ የወሊድ ዝግጅት ማድረግ፣ አራስን ስጦታ ይዞ በመሄድ መጠየቅ፣ የሰባት እና የአርባ ቀን እጥበት ስነ ስርዓቶችንና የማዘየሪያ ስነ ስርዓትን ማከናወን አሁንም ያሉ የክዋኔው ገጽታዎች ናቸው፡፡ የኮሮና ወረርሽኝ በስነ ስርዓቱ ክዋኔ ላይ ምንም ለውጥ አላስከተለም[23]፡፡

በዚህ ምዕራፍ የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ ስነ ስርዓት ከክዋኔ፣ ከመዋቅር፣ ከትዕምርት፣ ከፋይዳና ከለውጥና ቀጣይነት አንፃር ቀርቧል፡፡ በሚቀጥለው ምዕራፍ የብሄረሰቡ የጋብቻ ስነ ስርዓት ቀርቧል፡፡

---

[23] አብዛኛው የመስክ ስራ የተከናወነው የኮሮና ወረርሽኝ በሀገሪቱ መሰራጨት በጀመረበት፣ በየመገናኛ ብዙኃኑ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ በሚሰራበትና ጥንቃቄ የማድረጊያ መንገዶችም በስፋት ይተገበሩ በነበረበት ጊዜ ነው፡፡ ዋና የሚባሉ የመስክ ስራዎች ከ1/10/2012 እስከ 30/12/2012 እና ከ1/2/2013 እስከ 30/7/2013 በመመላለስ የተከናወኑ ናቸው፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

## የአርጎባ ብሄረሰብ የጋብቻ ስነ ስርዓት

ይህ ምዕራፍ የአርጎባ ብሄረሰብን የጋብቻ ስነ ስርዓት የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ በዋናነት የብሄረሰቡ የጋብቻ ስነ ስርዓት ክዋኔ፣ የክዋኔው መዋቅር፣ ትዕምርት፣ ፋይዳ እና ለውጥና ቀጣይነት ቀርበዋል፡፡

### 6.1. የጋብቻ እሳቤ በአርጎባ

በአርጎባዎች ዘንድ ጋብቻ የሰው ልጅ በህይወት እስካለ ድረስ ሊያደርገው የሚገባ አስፈላጊና መሰረታዊ ጉዳይ እንደሆነ ይታሰባል፡፡ ጋብቻ ዘርን የማስቀጠያ ጥምረት በመሆኑ ሴትም ሆነች ወንድ ያለትዳር እንዲኖሩ አይፈለግም፡፡ ይህን አስመልክተው አቶ አደም መሐመድ (5/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) "ኑሮማ ያስከብራል፡፡ ብቻነት የወደቀ ዛፍ ነው፡፡ የወደቀ ዛፍ አፈር ነው የሚሆነው፡፡ ኑሮስ መያዝ? ልጅ ይወለዳል፣ በአባቱ ቦታ ይተካል፡፡ ሴትም ቢወለድ የእናቷን ባህል ይዛ ትኖራለች" ብለዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ትዳር መያዝ ለሀላፊነት የመብቃት ደረጃ ተደርጐ ይታሰባል፡፡ ትዳር ያለው ሰው ሀላፊነትን የሚቀበል፣ የተሰጠውን ኃላፊነትም መወጣት የሚችል፣ ራሱን የገዛ ተደርጐ ይታሰባል (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 4/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ፍቺ እጅጉን የተጠላ በመሆኑ ባለትዳሮች ለፍቺ ወደ ሼሪያ ፍ/ቤት ሲሄዱ እንኳን ተደጋጋሚ ቀጠሮ እየተሰጠ ጉዳዩን እንዲያስቡበት ይደረጋል፡፡ ፍቺ ሲፈፀም ግን በሼሪያው ደንብ መሰረት የሚከናወን ሲሆን ፍቺው በሼሪያ ፍ/ቤት ሲፀድቅ የጋብቻ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ተመልሶ ፍ/ቤቱ የፍቺ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 4/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች በአርጎባዎች ዘንድ ትዳር ትልቅ ዋጋ የሚሰጠው ተቋም መሆኑን የሚገልፁ ናቸው፡፡

- ባል የሌላት ሴትና ሰው የሌለበት ቤት ቶሎ ይወድቃል (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 29/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ መደበኛ ያልሆነ ቡድን ተኮር ውይይት)፡፡
- ሴት የሌለበት ቤት ቤት አይሆንም (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 29/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ መደበኛ ያልሆነ ቡድን ተኮር ውይይት)፡፡

የመጀመሪያውን ምሳሌያዊ አነጋገር በተመለከተ ትዳር ያላት ሴት አጋዥ እንዳላት፣ የህይወት አጋር ያላት በመሆኑ ስትታመም የሚረዳት፣ ሲደክማት የምታርፍበት ሰው እንዳላት ይታመናል፡፡ ሰው የማይኖርበት ቤት ደግሞ ቶሎ ያረጃል፣ ይፈርሳል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም በምሳሌያዊ አነጋገሩ ለመግለጽ የተሞከረው በአንፃሩ ባል የሌላት ሴትና ሰው የሌለበት ቤት ሁለቱም ተጐጂዎች ናቸው የሚለው ሀሳብ ነው፡፡ በሁለተኛው ምሳሌያዊ አነጋገር ለመግለጽ የተሞከረውም ሴት ጐጆን ወይም ትዳርን ለማቆም ካላት ሀላፊነት አንፃር ሴት ወይም ሚስት የሌለችበት ቤት ተጐጂ ነው፣ ወይም ትዳር የሌለው ወንድ ተጐጂ ነው የሚል ሀሳብ ነው፡፡

## 6.2. የጋብቻ ዓይነቶችና የጋብቻ እድሜ

በእስልምና ሀይማኖት አንድ ወንድ እስከ አራት ሚስቶች ማግባት የሚፈቀድለት ቢሆንም (*The Quran,* Al-Nisa' 4:3) በአርጐባዎች ዘንድ የተለመደ አይደለም፡፡ ሁለተኛ ሚስት ለማግባት በተደረገ ሙከራ ብዙ ትዳሮች እንደፈረሱ መረጃ ሰጪዎች (ወ/ሮ እመይ መሐመድ ነጋሽ፣ አቶ አሕመድ ሲራጅ፣ 30/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቡድን ተኮር ውይይት) ምሳሌ በመጥቀስ ገልፀዋል፡፡ በመስክ ቆይታዬም ይህ አይነት ትዳር ያለበት ቤተሰብ አልገጠመኝም፡፡ ከዚህ በታች በባህሉ ተቀባይነት ያለው የተጋቢዎች ቤተሰቦች ተነጋግረው የሚከናወነው ጋብቻ ስነ ስርዓት በዝርዝር ይቀርባል፡፡

በአርጐባዎች ዘንድ የወንዱ አግቢ ቤተሰብ ለታጨችው ልጅ ቤተሰብ ሽማግሌ በመላክ "ልጃችሁን ለልጃችን" ተብሎ የሚፈፀም ጋብቻ በዋናነት የሚከናወን ሲሆን አልፎ አልፎ ግን ጠለፋና በስምምነት ጠፍቶ በመሄድ ኑሮን መጀመር ይተገበራል፡፡ ጠለፋና በስምምነት ጠፍቶ ሄዶ ኑሮን መጀመር የሚከናወነው በብሄረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለውንና በስፋት የሚተገበረውን "ልጃችሁን ለልጃችን" ተብሎ የሚከናወነውን የጋብቻ ዓይነት ማከናወን ሳይቻል ሲቀር ነው፡፡ ለማሳያነትም በባህሉ መሰረት የወንዱ አግቢ ቤተሰብ ወደ ሴቷ ቤተሰብ ሽማግሌ ልኮ በተለያዩ ምክንያቶች በሴቷ ቤተሰብ በኩል ጋብቻው ተቀባይነት ሳያገኝ ሲቀር በወንዱ በኩል ይህን ውሳኔ ለመቀበል ዝግጁ ባለመሆን ጠለፋን አማራጭ ያደርጋል፡፡ በሌላ በኩል በባህሉ መሰረት ሽማግሌ ተልኮና እሺታ ተሰጥቶ ነገር ግን ልጅቷ እድሜዋ አልደረሰም በሚል ወይም በሌላ ምክንያት የሰርጉ ቀን ተራዝሞ ሲቀጠር፣ ጥሎሽ ለመክፈል አቅም ሲያንስ፣ ወዘተ በመካከል ተጋቢዎቹ ተላምደው በመጥፋት ኑሮን በጋራ ይጀምራሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ አማራጮች በባህሉ ተቀባይነት

የሌላቸው ናቸው (አቶ አሕመድ ሲራጅ፣ 28/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በብሂረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ባለው "ልጃችሁን ለልጃችን" ተብሎ በሚፈፀም ጋብቻ ስነ ስርዓት ላይ ነው፡፡

ወንድ ልጅ ለጋብቻ ደርሷል የሚባልበት እድሜ 18 (አስራ ስምንት) ሲሆን ሴት ልጅ ለጋብቻ ደርሳለች የምትባልበት የተወሰነ እድሜ የለም፡፡ ሴት ልጅ እንደ አስተዳደጓ በሰውነት ቶሎ ልትፋፋና የወር አበባ ልታይም ትችላለች[24]፣ ይህ ሲሆን ደግሞ ልጅቷ ለአካለ መጠን ደርሳለች ተብሎ ለጋብቻ ልትታጭ ትችላለች፡፡ ሴት ልጅ በዚህ መልኩ ብትታጭም ጋብቻ ከመደረጉ በፊት ትጠንክር ተብሎ በእናትና አባቷ ቤት አንድም ሁለትም ዓመት እንድትቆይ ይደረጋል፡፡ በዕድሜ ምክንያት አለመከልከሏ ወይም መታጨቷ የሰው እጮኛ ናት ተብላ እንድትከበርና ለጠለፋ እንዳትዳረግ ሲባል የሚደረግ ነው (አቶ አብዱልቃድር ቃሲም፣ 6/3/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

## 6.3. የትዳር አጋርን የመምረጫ መስፈርቶች

በጋብቻ ዝምድናን ለመፍጠር እንደ መሰረት የሚሆኑ የትዳር አጋርን መምረጫ መስፈርቶች አሉ፡፡ በአርጐባዎች ዘንድ ዋና ዋና የትዳር መስፈርቶች አርጐባ መሆን፣ የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ መሆን፣ የጥሩ ባህርይ ባለቤት መሆን፣ የተማረ መሆንና ባለሙያነት ናቸው (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 5/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው በአርጐባዎች ዘንድ የመጀመሪያው የጋብቻ መስፈርት አርጐባ መሆን ነው፡፡ በብሄረሰቡ ከአርጐባ ውጭ ከሆነ ሰው ጋር ጋብቻን መፈፀም ተቀባይነት የለውም፡፡ ነገሩ እያደር እየላላ ቢመጣም ከአርባ ዓመት በፊት ባለው ጊዜ ግን አንድ ሰው ከብሄረሰቡ ውጭ ለሆነ ሰው ልጁን ከዳረ እንደሞተ ይቆጠር ነበር፡፡ ይህን አስመልክተው አቶ መሐመድ አቡበከር (5/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) "ከቆራሬ ወደ ጨኖ በትዳር የሄደች ሴት ነበረች፡፡ ኤኑር ትባላለች፡፡ ልጆቿን ለአርጐባ ድራ ሶስተኛዋን ከአርጐባ ውጭ ላለ ሰው ዳረች፡፡ በዚህ ጊዜ ዘመዶቿ ከቆራሬ ጨኖ ድረስ ሄዱና እንዴት መጣችሁ ሲባሉ ልጅሽን ከአርጐባ ውጭ ዳርሽ፣ ሀዘን ልንደርስሽ ነው የመጣነው አሏት" በማለት ሲነገር የሰሙትን ታሪክ ነግረውኛል፡፡ ከአርጐባነት በተጨማሪ ዝምድና ኖሯቸው ቀድመው የሚተዋወቁ ካልሆኑ በስተቀር ለልጁ ሚስት የሚፈልግ ቤተሰብም ሆነ ሽማግሌ

[24] [እድሜዋ ከ 12-14 ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡]

የሚላክበት የሴቷ ቤተሰብ ውሳኔ ላይ የሚደርሱት አንዳቸው የሌላቸውን የዘር ሀረግ ካጠኑ በኋላ ነው፡፡

በብሄረሰቡ ዘንድ ከአርጐባነትም ባሻገር ቁርዓኑ በሚፈቅደው ልክ የደም ዝምድና ለጋብቻ መምረጫ መስፈርትነት ይውላል፡፡ የሚከተለውን ምሳሌያዊ አነጋገር እንመልከት፡፡

- እንጀራችንን በወጣችን (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 4/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የአርጐባ ብሄረሰብ የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ በመሆኑና በእስልምና ሀይማኖት ደግሞ ጡት መጣባት በሌለበት ሁኔታ ከአክስት ወይም ከአጐት ልጅ ጀምሮ ጋብቻን ማድረግ የተፈቀደ በመሆኑ (*The Quran*, Al-Nisa' 4:24) በብሄረሰቡ የጋብቻ ባህል ይተገበራል፡፡ እንጀራችንን በወጣችን የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር "የራሳችንን በራሳችን" የሚል ሀሳብን የሚፈጥርና ብሄረሰቡ በዘመዳሞች መካከል የሚደረግን ጋብቻ ከሩቅ ከሚመጣው ጋብቻ ይልቅ የሚመርጠው፣ የሚያበልጠው መሆኑን የገለፀበት ነው፡፡

ሁለተኛው የጋብቻ መስፈርት የእስልምና ሀይማኖትን መከተል ነው፡፡ በብሄረሰቡ ዘንድ እስልምናን ከማይከተል ሰው ጋር ጋብቻን መፈፀም ተቀባይነት የለውም፡፡ በጋብቻ ጉዳይ ከዘር ቆጠራው በላይ ሀይማኖት ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል (አቶ አሕመድ ሲራጅ፣ 28/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ በመስክ ስራ ወቅት በሙስሊም አርጐባዎችና ከጊዜ በኋላ በሰለሙ ሰዎች መካከል እንጂ በሙስሊም አርጐባዎችና ከእስልምና ሀይማኖት ውጭ ባሉ ሰዎች መካከል የተከናወነ አንድም ጋብቻ አልገጠመኝም፡፡

ባህርይ ሌላው መስፈርት ነው፡፡ ለጋብቻ የጠየቀው አግቢም ሆነ ለጋብቻ የተመረጠችው ልጅ ቤተሰብና ተጋቢዎቹ ማን ናቸው? ባህርያቸውስ ምን ይመስላል? ተብሎ ጥናት ይደረጋል፡፡ ቤተሰቡም ሆኑ ለጋብቻ የሚተጫጩት ልጆች ጨዋ፣ የሰው ንብረት የማይፈልጉ፣ ታታሪ ወይም ራሳቸውን በስራ ለመለወጥ ጥረት የሚያደርጉ፣ "ትክሻ" ያላቸው፣ ወዘተ እንዲሆኑ ይፈለጋል፡፡ ልጆቻቸውን የሚድሩ ቤተሰቦች አንዳቸው የሌላቸውን እና የተጋቢዎቹንም ልጆች ጨዋነት ይመረምራሉ፡፡ ቤተሰብ በድህነት የሚኖር ቢሆን እንኳን ራሱን ለመለወጥ የሚተጋ ከሆነ ድህነት መመዘኛ ሆኖ ጋብቻን አያስቀርም (አቶ አሕመድ ሲራጅ፣ 28/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ብሄረሰቡ "ወንድ ልጅና ደረቅ ፈጫ አንድ ናቸው" የሚል ምሳሌያዊ አነጋገር ያለው መሆኑ (ወ/ሮ ሷቢራ

ኡመር፣ 26/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) በአስረጅነት መቅረብ የሚችል ነው፡፡ ምሳሌያዊ አነጋገሩ ወንድ ልጅ ከሰራ ገንዘብ ያገኛል፣ እጁ ይረጥባል፤ የደረቀ የውሃ መንገድም ሲዘንብ ይሞላል የሚል መልዕክት የያዘ ነው፡፡ አቶ አሕመድ ሲራጅ እንደገለፁት ደግሞ "ትከሻ" ማለት እድል፣ ገድ ማለት ነው፡፡ "ትከሻ" ያለው ቤተሰብ አርሶ ብዙ የሚያመርት፣ ነግዶ የሚያተርፍ፣ ሰርቶ የሚለወጥ፣ ደሀም ቢሆን ከድህነት የሚወጣ፣ ወልዶ ልጆች የሚያድጉለት፣ ወጥቶ በሰላም የሚገባ፣ ወዘተ ነው፡፡ "ትከሻ" የሌለው ቤተሰብ ደግሞ በአንፃሩ ምንም ቢተጋ ኑሮ የማይሆንለትና የማይሳካለት እንዲሁም ብዙ እንቅፋቶች የሚጋረጡበት ነው (28/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ በመሆኑም ለጋብቻ የምትታጭ ልጅ፣ የሚያጨውም ወንድ ቢሆን "ከባለትከሻ" ቤተሰብ የተገኘ እንዲሆን በእጅጉ ይፈለጋል፤ በአንፃሩ ትከሻ ከሌለው ቤተሰብ መገኘት ደግሞ ጋብቻን የሚያስቀር ወይም የሚያደናቅፍ ጉዳይ ነው፡፡

ሌላው የትምህርትና ሙያ ጉዳይ ነው፡፡ ልጁን ለጋብቻ የሚጠየቅ ቤተሰብ ጠያቂው የተማረ ወይም ቁርዓን የቀራ እንዲሆን ይፈልጋል፤ በተለይ ቁርዓን የቀራች ልጁን ላልተማረ ሰው መዳር አይፈልግም፡፡ የወንዱ ቤተሰብም ለልጁ የሚያጯት ልጅ የቤት ውስጥ ሙያ ያላት እንድትሆን ይመርጣል (ወ/ሮ እመይ መሐመድ ነጋሽ፣ 22/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

## 6.4. የአርጐባ ብሄረሰብ የጋብቻ ስነ ስርዓት፤ ክዋኔው፣ መዋቅሩና ትዕምርቱ

በዚህ ክፍል የአርጐባ ብሄረሰብ የጋብቻ ስነ ስርዓት ክዋኔ ከመለየት፣ ከሽግግርና ከመቀላቀል ደረጃዎች አንፃር እና በክዋኔው ውስጥ ያሉ ትዕምርታዊ ጉዳዮችና ፍካሬዎቻቸው ቀርበዋል፡፡ በብሄረሰቡ የጋብቻ ስነ ስርዓት የመለየት ጊዜ የቆዳ ማንጠፊያ ስነ ስርዓት ተከውኖ ጋብቻው ተቀባይነት ባገኘ ጊዜ የሚጀምር በመሆኑ ከቆዳ ማንጠፊያ ስነ ስርዓት ክዋኔ አስቀድሞ ያሉ ክዋኔዎች ቅድመ መለየት ክዋኔዎች በሚል ንዑስ ርዕስ ስር በቅድሚያ ቀርበዋል፡፡

### 6.4.1. ቅድመ መለየት ክዋኔዎች

በዚህ ክፍል ከመለየት ደረጃ በፊት ያሉ የማጨት ሂደትና የስለላ ስነ ስርዓት ክዋኔዎች ቀርበዋል፡፡

### 6.4.1.1. የማጨት ሂደት

በአርጐባዎች ዘንድ ለጋብቻ የምትታጭ ልጅ የምትገኘው በሁለት መንገድ ነው፡፡ አንደኛው በልጁ ቤተሰብ ፈላጊነት ሲሆን ሁለተኛው በልጁ በራሱ ፈላጊነት ነው፡፡ በመጀመሪያው ሁኔታ ለጋብቻ እድሜ ለደረሰ ልጅ ሚስት የሚፈልግለት የልጁ አባት፤ አባቱ በህይወት ከሌለ ደግሞ አጐቱ፣ ታላቅ ወንድሙ፣ የአክስቱ ወይም የአጐቱ ልጆች፣ የአባቱ የቅርብ ጓደኞች ወይም ሌላ የቤተሰቡ ወዳጅ የሆነ ሰው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በእስልምና ሀይማኖት ከአክስት ወይም ከአጐት ልጆች ጀምሮ ከዚያ የራቀ ዝምድና ባላቸው ሰዎች መካከል ጋብቻ ሊከናወን የሚችል በመሆኑ ለጋብቻ የምትታጨው ልጅ በዚያ ትውውቅ ውስጥ ያለች ከሆነች ፍለጋው አጭር ይሆናል ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ከዚያ ውጭ ከሆነ ለጋብቻ የደረሰ ወንድ ልጅ ያለው ቤተሰብ ለልጁ ሚስት የምትሆንን ልጅ ይፈልጋል ማለት ነው (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 5/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ለልጃቸው ሚስት የሚፈልጉ የቤተሰብ አባላት ለልጃቸው ትመጥናለች ያሏትን ሴት ሲያገኙ አግቢውን ልጃቸውን "እከሊትን ልንድርህ አስበናል ትስማማለህ ወይ?" ብለው ይጠይቁታል፡፡ ልጅቷን አውቆ ከወደደ ወይም ቤተሰቡን አክብሮ ከቤተሰቤ ሀሳብ አልወጣም ካለ ወደ ቀጣዩ ስነ ስርዓት ይኬዳል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ እንዲህ የተባለ ልጅ ከቤተሰብ ቃል አይወጣም፡፡ አግቢው ራሱ በተለያዩ አጋጣሚዎች አይቶ የወደዳት ልጅ ካለች እርሷን ለማግባት እንዳሰበ ለቤተሰቡ በመንገር የቤተሰቡን ስምምነት ይጠይቃል፡፡ የቤተሰቡ አባላት የልጅቷን ማንነት ከልጃቸው በተሻለ ካጣሩና ከመዘኑ በኋላ በጋብቻው መስማማት አለመስማማታቸውን ይገልፁለታል፡፡ ቤተሰብ ከተስማማ ወደሚቀጥለው ስነ ስርዓት ይኬዳል፤ ነገር ግን ከቤተሰብ ፈቃድ ውጭ የሚደረግ ነገር ሁሉ መጥፎ ነገር ያስከትላል ተብሎ ስለሚታመን አብዛኛውን ጊዜ ቤተሰብ ባልፈቀደው ትዳር ውስጥ አይገባም፡፡ በሁለተኛው መንገድ አግቢው ራሱ የትዳር አጋሩን ሲመርጥ ልጅቷን የሚያገኝባቸው የተለያዩ ቦታዎችና አጋጣሚዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል በአረፋ ጊዜ የሚከናወን የሴቶች የሺሎ ጨዋታ፣ የገበያ ቦታና የሰርግ ስነ ስርዓት ዋናዎቹ ናቸው (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 5/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የሺሎ ጨዋታ ከአረፋ በዓል ጀምሮ ለአስር ቀናት ያህል የሚቆይ የሴቶች የኸሮዋኸሮዌ ጨዋታ ነው፡፡ ጨዋታው ሴቶች ልጆች ብቻ የሚጫወቱት ቢሆንም ወንዶች ልጆች

በሺሎው አካባቢ በመገኘት ጨዋታውን ይመለከታሉ፤ ጨዋታው የመተጫጫ አጋጣሚ ነው፡፡ አንድ ወንድ ልጅ በጨዋታው ላይ ተመልክቶ የወደዳትን ልጅ "ስትሾል" ጠብቆ ሳታየው ዛፉ ላይ በመውጣት በገመዱ ላይ ተንጠልጥሎ ወደ ታች ይመጣባታል፤ ይህ ልጁ ልጅቷን መውደዱንና ለጋብቻ መመኘቱን የመግለጫ መንገድ ሲሆን ልጅቱ ከጮኸችና ከሺሎው ወርዳ ለመሮጥ ከሞከረች ፈቃደኛ አለመሆኗን መግለጿ እንደሆነ የሚቆጠር ሲሆን በድርጊቱ ሳትደነግጥ ዝም ካለች ግን እርሷም እንደፈቀደችው መግለጿ እንደሆነ ይታሰባል (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 5/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በዚህ መልኩ ለጋብቻ የተመረጠች ልጅ ከተገኘች በኋላ የሚቀጥለው ስነ ስርዓት የስለላ ስነ ስርዓት ይሆናል፡፡

### 6.4.1.2. የስለላ ስነ ስርዓት

ስለላ የሚደረግበት ዋና ዓላማ ልጅቷ ያልታጨች መሆኑን ማረጋገጥና የልጅቷ ቤተሰብ በተለይ እናቷ ወደፊት የታሰበውን ጋብቻ በተመለከተ ያላቸውን አመለካከት መለየት ነው፡፡ ይህ መረጃ የሚገኘው ከእናት በመሆኑ የምትላከው ሰላይም ሴት ናት፡፡ በመሆኑም የቤተሰቡ የቅርብ ዘመድ ወይም ወዳጅ የሆነች በእድሜ ገፋ ያለች ሴት ትላካለች፡፡ በቃለመጠይቅ ጊዜ በመረጃ ሰጪዎች መካከል ወንድ ሰላይ ተደርጐ ይላካል፤ አይላክም የሚል የሀሳብ ልዩነት ተፈጥሮ ነበር፡፡ በመሆኑም ጉዳዩን በቡድን ተኮር ውይይት በማንሳትና በማወያየት በስተመጨረሻ የውይይቱ ተሳታፊ የነበሩት አቶ አብዱልቃድር መሐመድ ሰዒድ ተሰላይዋ በዋናነት የልጅቷ እናት በመሆኗ ሰላይዋም ሴት ናት፤ ወንድ አይሰልልም ብለው በማስረዳታቸውና ሌሎቹም የውይይቱ ተሳታፊዎች ይህንኑ የተስማሙበት በመሆኑ (16/7/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቡድን ተኮር ውይይት) ለስለላ የምትሄደው ሴት ነች የሚለው መረጃ ፀንቷል፡፡

ሰላይዋ ለስለላ ወደ ልጅቷ ቤተሰብ ቤት በምትሄድበት ቀን ከልጅቷ እናት ጋር ከተጨዋወተች በኋላ በጨዋታ መካከል የልጅቷን ጉዳይ ታነሳለች፤ ልጅቷ ለመታጨት መድረስ አለመድረሷን በመጠየቅ ልጅቷ ያልተዳረች ከሆነ ቤተሰቡ ልጅቷን ለመዳር ያለውን ፍላጐት ለመለየት ትጥራለች፤ ልጅቷ ታጭታ ከሆነም ይህንኑ ትረዳለች፡፡ ልጅቷ ያልታጨች ከሆነችና የልጅቷ እናት ልጇን ለመዳር ፍላጐት ያላት መሆኑን ከተረዳች ደግሞ የላካትን ቤተሰብ በመጥቀስ ቤተሰቡ ለልጁ ሚስት እየፈለገ መሆኑን በመግለጽ

የልጅቷ እናት ከዚያ ቤተሰብ ጋር በጋብቻ ለመዛመድ ፍላጎት ያላት ወይም የሌላት መሆኑን ለማጣራት ትሞክራለች፡፡ የልጅቷ እናት ስለ ልጁ ቤተሰብ ጥሩ አመለካከት እንዳላት ከገለፀችላት ሽምግልና ቢላክ ጥሩ መልስ እንደሚገኝ በመገመት፤ በተቃራኒው እናት ለቤተሰቡ ወይም ለልጁ ጥሩ አመለካከት የሌላት መሆኑን በሁኔታዋ በመረዳት ወደ ወንዱ ቤተሰብ በመሄድ የተገነዘበችውን ነገር ትገልፃለች፡፡ ሰላይዋ ልጅቷ አለመታጨቷን ካወቀችና ከእናቲቱ ጥሩ ፊትና ጥሩ መልስ ካገኘች ምግብና ቡና ቢቀርብላት ተስተናግዳና ተጫውታ፤ ጥሩ መልስ ካላገኘች ግን መስተንግዶውን ሳትቀበል ትመለሳለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የልጁ እናት መክረን እናሳውቅሻለን ካለች ሰላይዋ መልሱን ለማወቅ በሌላ ቀን ልትመለስም ትችላለች (ወ/ሮ እመይ መሐመድ ነጋሽ፣ 22/2/2013፣ ጋቺኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በመሆኑም የስለላ ስነ ስርዓት የሴቷ ቤተሰብ ጋብቻውን የሚቀበለው መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል፣ በተወሰነ መልኩም የሽምግልና ዓይነት ሚናም ያለበት መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡ የወንዱ ቤተሰብ ልጅቷ አለመታጨቷን ካረጋገጠ በኋላ በሌላ ጉዳይ የልጅቷ እናት በእነርሱ ላይ ያላትን ቅሬታ ገልፃ ቢሆን እንኳን ሽማግሌ ነገሩን አለዝቦ ስምምነትን ሊያስገኝ ይችላል በሚል እሳቤ ወደ ልጅቷ ቤተሰብ ሽማግሌ ይልካል፡፡ የሽምግልናው ስነ ስርዓት የቆዳ ማንጠፊያ ስነ ስርዓት ይባላል፡፡

### 6.4.2. መለየት

በአርጎባ የጋብቻ ስነ ስርዓት ክዋኔ የመለየት ደረጃ የቆዳ ማንጠፊያ ስነ ስርዓት ተከውኖ ጋብቻው እሺታን ባገኘ ጊዜ የሚጀምርና የነገር መፍጃ ስነ ስርዓት በሚከወንበት ቀን ዋዜማ የሚጠናቀቅ ነው፡፡ ከዚህ በታች የመለየት ጊዜ መነሻ የሚሆነው የቆዳ ማንጠፊያ ስነ ስርዓት ክዋኔ ቀርቧል፡፡

#### የቆዳ ማንጠፊያ ስነ ስርዓት

የቆዳ ማንጠፊያ ስነ ስርዓት የሽምግልና ስነ ስርዓት ሲሆን ከስለላው ስነ ስርዓት በኋላ የሚከወን ነው፡፡ የሽምግልና ስነ ስርዓት ቆዳ ማንጠፊያ ተብሎ የሚጠራው በስነ ስርዓቱ ላይ የሴቷ ቤተሰብ በጋብቻው መስማማቱን ወይም አለመስማማቱን ሽማግሌዎችን አንጥፎ በሚጠብቃቸው የፍየል ቆዳ ቀለም የመግለጽ ልማድ ያለ በመሆኑ ነው፡፡

ሽማግሌዎችን መርጦ የሚልከው የወንዱ ልጅ ወንድ የቤተሰብ አባል ማለትም አባት፤ አባት በህይወት ከሌለ ደግሞ አጎት፣ ታላቅ ወንድም፣ የአባት የቅርብ ጓደኞች ወይም ሌላ የቤተሰቡ ወዳጅ የሆነ ሰው ነው (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 5/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ሽማግሌዎች የሚመረጡት በእድሜ አንጋፋ በመሆናቸው፣ በጥሩ ንግግር አዋቂነታቸውና ተናግረው በማሳመን አቅማቸው ነው፡፡ ይህን በተመለከተ አቶ አህመድ ሲራጅ (28/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> ሽምግልና የሚላኩት ሽምግልና ከሚላክበት ሰው ጋር አግባብ ያላቸው፣ ማውራት የሚችሉ፣ ሰውየውን ማሳመን የሚችሉ፣ ነገር የማያቆረፍዱ ሰዎች ናቸው የሚላኩት፡፡ የማይሆን ሰው ከተላከማ ጥሩ ነገሩን ቁርፍድፍድ ያደርገውና አጣልቶ ይሄዳል፡፡ … ዘመድ ቢሆኑ ይመረጣል ካልሆነ ግን እውቀት ያለው ባዳ እንዲሰምር ያደርገዋል፡፡ … እንደ ብቃቱ ነው የሚሄደው፡፡

የሚላኩ ሽማግሌዎች ቁጥር ቢያንስ ሶስት መሆን አለበት፡፡ አንድ ሰው ብቻውን ምስክር ሊሆን አይችልም፤ ሁለት ሰዎች በጥሩውም ሆነ ጥሩ ባልሆነው ሊስማሙ ይችላሉ፤ ሶስት ከሆኑ ግን ለመጥፎ ጉዳይ አይስማሙም፣ አንዱ ሊያፋነግጥ ይችላል የሚል አመለካከት ያለ በመሆኑ ሽምግልናና ምስክርነትን በመሰለ ትልቅ ሀላፊነት የሚታጩ ሰዎች ቁጥር ሶስት ነው (አቶ አህመድ ሲራጅ፣ 28/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ሽማግሌዎችን የሚልከው ሰው ሽማግሌዎችን ከመረጠ በኋላ ልጄን ልድር ነውና ሽምግልና ሂዱልኝ ብሎ ይጠይቃል፡፡ ሽማግሌዎች እርስ በርስ ተነጋግረው የሚመቻቸውን ቀን በመምረጥ ለሽምግልናው የሚሄዱበትን ቀን ይወስናሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ለጋብቻ ከተመረጠችው ልጅ ቤተሰብ ጋር የሚግባባ ወይም ቤተኛ የሆነን ሰው በመምረጥ በተወሰነው ቀን ሽማግሌ ወደ ቤታቸው እንደሚሄድ ሹክ እንዲላቸው ወይም ሰላይዋ እንድትነግራቸው ያደርጋሉ፡፡ በመሆኑም የሴቷ ቤተሰብ ሽማግሌዎች በዚያ ቀን እንደሚመጡበት አውቆና ተዘጋጅቶ ይጠብቃል ማለት ነው፡፡ ከሳምንቱ ቀናት ውስጥ ሀሙስና ሰኞ ቀናት ሽምግልና ለመሄድ የሚመረጡ ቀናት ሲሆኑ ረቡዕ፣ አርብና ቅዳሜ

የጁዓ ቀናት በመሆናቸው ለሽምግልና አይኬድባቸውም (አቶ አብዱልቃድር ቃሲም፣ 6/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ሽምግልና በሚኬድበት የሴቷ ቤተሰብ ቤት ሽማግሌዎችን የሚቀበሉ ሰዎች የልጅቷ ወላጆች፣ አያቶች፣ አጎቶች፣ አክስቶች፣ ታላላቅ ወንድሞችና ሌሎች የቤተሰቡ ወዳጆች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሽማግሌዎቹ ሲመጡ ከሽማግሌዎቹ ጋር የሚነጋገሩት ግን ከመካከላቸው የልጅቷ አባት፤ አባት በህይወት ከሌለ ደግሞ አጎቶች ወይም ሌሎች በእድሜ አንጋፋ የሆኑ ወንዶች ናቸው፡፡ ጋብቻውን የመፍቀድም ሆነ ያለመፍቀድ መብት የአባት ሲሆን አባት በህይወት ከሌለ ደግሞ አጎቶች ወይም በእድሜ አንጋፋ የሆነ የቤተሰቡ ወንድ አባል ይወስናል፡፡ አባት በጋብቻው ባይስማማ እናትና ሌሎች የቤተሰቡ አባላት ጋብቻውን ከፈለጉ አባትን ሊያግባቡና ሀሳቡን እንዲቀይር ሊጥሩ ይችላሉ እንጂ ሀሳባቸው ከአባት ውሳኔ በላይ አይሆንም፡፡ በአንፃሩ አባት ጋብቻውን ቢፈልግና እናትን ጨምሮ ሌሎች የቤተሰቡ አባላት በጋብቻው ባይስማሙ አሁንም የመጨረሻ የሚሆነው የአባት ውሳኔ ነው (አቶ አብዱልቃድር ቃሲም፣ 6/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ለሽምግልና የተመረጡ ሰዎች ለሽምግልና በቆረጡት ቀን ጠዋት በየቤታቸው ቁርስ ቀምሰውና ቡና ጠጥተው አማካይ ቦታ ላይ ተገናኝተው ለሽምግልና ወደሚሄዱበት ቤት ያመራሉ፡፡ በአርጐባዎች ዘንድ ጠዋት በባዶ አፍ መውጣት ጥሩ አይደለም፣ የሚሄዱበትን ጉዳይ ያስተጓጉላል፣ በአንፃሩ ቁርስ ቀምሶ መውጣት ስኬታማነትን ያስገኛል የሚል እምነት በመኖሩ ምክንያት ለሽምግልና የሚሄዱ ሰዎች ቁርስ ቀምሰውና ቡና ጠጥተው የሚወጡት የሚሄዱበት ጉዳይ እንዲሳካላቸው፣ ለሽምግልና በሚሄዱበት ቤተሰብ ዘንድ ተቀባይነትንና እሺታን እንዲያገኙ በማሰብ ነው፡፡ እዚያ እንደደረሱ ከደጅ በመሆን ሰዎቹን ጠርተውና ሰላምታ ሰጥተው ወደ ቤት እንዲገቡ ሲጋበዙ ገብተው አረፍ ይላሉ፡፡ የሴቷ ቤተሰብ ቀድሞ በተዘጋጀው መሰረት ሀሳቡን የሚጠቁመው ቤት ውስጥ፤ በመግቢያ በር ፊት ለፊት በእንግዳ መቀበያ ቦታ ላይ ሽማግሌዎቹን አንጥፎ በሚጠብቃቸው ወይደል ቀለም ነው (አቶ አብዱልቃድር ቃሲም፣ 6/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ወይደል የፍየል ቆዳ ሲሆን በአብዛኛው አርጐባ ቤት ውስጥ ይገኛል፡፡ ቆዳ ማንጠፉ ሽማግሌዎችን በክብር ከመቀበል በላይ መልዕክት ማስተላለፊያ ነው፡፡ ቆዳ ማንጠፉ እንደሚነጠፈው ቆዳ ቀለም ዓይነት የተለያየ መልዕክት ያስተላልፋል፡፡ ሽማግሌዎች ለጋብቻ ጥየቃ በሚሄዱበት ጊዜ የሚነጠፍ ቆዳ ቀለም ሶስት አይነት ነው፡፡ አንደኛው ነጭ፣

ሁለተኛው ዥንጉርጉርና ሶስተኛው ሙሉ ጥቁር ቀለም ነው፡፡ ሽማግሌዎች በሚመጡ ጊዜ ተነጥፎ በሚያገኙት ወይደል ቀለም የጋብቻ ጥያቄው መልስ ምን እንደሚሆን ይረዳሉ፡፡ በመሆኑም ነጭ ወይደል ማንጠፍ ጋብቻውን ወድደናል ተቀብለናል፣ የሚቀረው የሰርጉን ቀን መወሰን ነው የሚል መልዕክት ያስተላልፋል፤ ዥንጉርጉር ወይደል ማንጠፍ ጉዳዩን እንመክርበታለን፣ ቁርጥ መልስ የለንም የሚል መልዕክት የሚያስተላልፍ ሲሆን ጥቁር ወይደል ማንጠፍ ደግሞ በጋብቻው በፍፁም አልተስማማንበትም የሚል መልዕክት ያስተላልፋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ወይደሉን ገልብጦ ማንጠፍም በጋብቻው ያለመስማማትን መልዕክት ይወክላል (አቶ አብዱልቃድር መሐመድ ሰዒድ፣ 9/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡



ፎቶግራፍ 14. ነጭ ወይደል



ፎቶግራፍ 15. ዥንጉርጉር ወይደል

ሀሳብን በቆዳ ቀለማት ለመግለጽ የተቻለው ለቀለማቱ የተሰጣቸው ትዕምርታዊ ዋጋ ያለ በመሆኑ ነው፡፡ በአርጐባዎች ዘንድ ነጭ ቀለም መልካም ነገርን፣ አዎንታዊ ነገርን፣ ጥሩ እድልን፣ ኑሮን፣ ደስታን፣ ወዘተ የሚገልጽ ሲሆን በአንፃሩ ጥቁር ቀለም መጥፎ ነገርን፣ አሉታዊ ነገርን፣ መጥፎ እድልን፣ ሀዘንን፣ ወዘተ ይገልፃል፡፡ የነጭና ጥቁር ቀለማት ድብልቅ የሆነው ዥንጉርጉር ቀለም በሁለቱም ቀለማት የሚገለፀውን ሀሳብ በመያዝ አሻሚነትን ይገልፃል በሚል እሳቤ የተወሰነ ነገር አለመኖሩን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ በመሆኑም በአርጐባዎች የቆዳ ማንጠፊያ ስነ ስርዓት ክዋኔ ላይ እነዚህን ትዕምርታዊ ቀለማት በማሳየት ሀሳብ ይገለፃል ማለት ነው፡፡

ሽማግሌዎችም ተነጥፎ እንደሚጠብቃቸው ወይደል ቀለም ምላሻቸው ይለያያል፡፡ ነጭ ወይደል ተነጥፎ ከጠበቃቸው ተረጋግተው ቁጭ በማለት ግብዣ ይቀበላሉ፤ እንጀራ ቀርቦ ማርና ቅቤ ተቀድቶ በደንብ ይጋበዛሉ፡፡ ነገር ግን ጥቁር ወይደል ተነጥፎ ከጠበቃቸው ለመጋበዝ ፈቃደኛ አይሆኑም፤ በልተናል፣ ጠግበናል ብለው ለወጉ ያህል ቁጭ ብለው ይወያዩና እንደማይሆን ተረድተነዋል ብለው ወጥተው ይሄዳሉ (አቶ አብዱልቃድር መሐመድ ሰዒድ፣ 9/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

እሺታንና እምቢታን በሚነጠፍ ወይደል ቀለም መጠቆም ቢኖርም ግን አንጥፎ ዝም አይባልም፡፡ በንግግር እሺታና እምቢታ ይገለፃል፡፡ ነጭ ወይደል አንጥፎ የጠበቀ ቤተሰብ በንግግር እሺታውን የሚገልጽ ሲሆን ጥቁር አንጥፎ የጠበቀውም ቤተሰብ እንዲሁ በጋብቻው አለመስማማቱን ይገልፃል፡፡ ቤተሰቡ ጋብቻውን ያልተቀበለበት ምክንያት ቢኖርም በግልጽ ግን ምክንያቱ ይህ ነው ብሎ አይናገርም፤ ልጅቷ እድሜዋ አልደረሰም በማለት፣ ወይም ሌላ ምክንያት በመስጠት አድበስብሰው ጋብቻውን አለመፍቀዳቸውን ይገልፃሉ፡፡ ዥንጉርጉር ቀለም ያለው ወይደል አንጥፎ የጠበቀ ቤተሰብም ጉዳዩን ከዘመድ ጋር መክረን መልሰን እንነግራችኋለን ብሎ ይመልሳቸዋል (አቶ አብዱልቃድር መሐመድ ሰዒድ፣ 9/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ከዘመድ ጋር እንማከር የሚባለው አንድም እንደተባለው ከዘመድ ለመምከር፣ አንድም ደግሞ ሙሽራውንና ቤተሰቡን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለመሰብሰብ እንዲቻል ጊዜ ለማግኘት ሲባል ነው፡፡ ይህ ሲሆን ሽማግሌዎቹ በአማካይ ከአንድ ሳምንት እስከ ሁለት ሳምንት ከቆዩ በኋላ ተመልሰው የሚሄዱበትን ቀን ተነጋግረው በመወሰን ይሄዳሉ፡፡ ሽማግሌዎቹ የሴቷ ቤተሰብ የሚሄዱበትን ቀን እንዲያውቅና እንዲጠብቃቸው እንደቀደመው ጊዜ ቤተሰቡን የሚግባባ ሰው ሂዶ እንዲነግራቸው ያደርጋሉ እንጂ ሽምግልና በሁለቱ ቤተሰብ ቀጠሮ አይከናወንም (አቶ አብዱልቃድር መሐመድ ሰዒድ፣ 9/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ሽማግሌዎቹ በሚሄዱበት ቀን ሶስት አይነት መልስ ሊጠብቃቸው ይችላል፡፡ አንደኛው ከዘመድ ተማክረን በጋብቻው ተስማምተናል የሚል የይሁንታ መልስ፣ ሁለተኛው ተማክረን ጋብቻው አይሆንም ብለናል የሚልና ሶስተኛው ከዘመድ ጋር አልተገናኘንም፣ አልመከርንምና በሌላ ቀን ተመለሱ የሚል ሊሆን ይችላል፡፡ ሽማግሌዎቹ የመጀመሪያውን ዓይነት መልስ ካገኙ ተደስተው ሲጋበዙም በሙሉ ፈቃደኝነት ተጋብዘውና ተጫውተው

ይመለሳሉ፡፡ ሁለተኛውን ዓይነት መልስ ካገኙ ግን እባካችሁ ተጋበዙ፣ ቡና ጠጡ ቢባሉም አሁን በልተናል፣ ጠጥተናል በማለት ያለግብዣ ይመለሳሉ፡፡ ሶስተኛው ዓይነት መልስ ከተሰጣቸው ደግሞ ያላቸው አማራጭ በሌላ ቀን ተመልሶ መልስ ማግኘት ስለሆነ በሌላ ቀን በተመሳሳይ መንገድ የሚመጡበትን ቀን ካሳወቁ በኋላ የቤተሰቡን ምላሽ ለማግኘት ለሶስተኛ ጊዜ ይሄዳሉ፡፡ በዚያ ቀን አሁንም የሴቷ ቤተሰብ ጋብቻውን ተቀብለናል ወይም አልተቀበልንም የሚል መልስ ሊሰጥ ይችላል፡፡ መልሱ የይሁንታ ከሆነ ከላይ እንደተገለፀው ሽማግሌዎች የተዘጋጀላቸውን ግብዣ ተቀብለው ተጋብዘውና ተጫውተው ይመለሳሉ፡፡ መልሱ ጋብቻውን አልተቀበልነውም የሚል ከሆነ ግን ቢለምኑ እንኳን ሳይበሉና ሳይጠጡ ይመለሳሉ፡፡ በዚህ መልኩ ሽማግሌዎች የተሰጣቸውን ምላሽ ሽምግልና ለላካቸው ቤተሰብ ያሳውቃሉ (አቶ አብዱልቃድር መሐመድ ሰዒድ፣ 9/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ከላይ ለመመልከት እንደሚቻለው የቆዳ ማንጠፊያ ስነ ስርዓት የሚላኩ ሽማግሌዎችን ምልልስ የሚጠይቅ ነው፡፡ የሚተለውን ምሳሌያዊ አነጋገር እንመልከት፡፡

- ሴትና ጫት ሳያደገድጉ አይገኝም (አቶ አሕመድ ሲራጅ፣ 27/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በዚህ ምሳሌያዊ አነጋገር ሴት የተባለችው ሚስት ነች፡፡ በግልጽ እንደሚታየው ምሳሌያዊ አነጋገሩ ሚስት ጠያቂና ጫት በጋራ በሚቃምበት ቦታ ላይ የራሱን ጫት ይዞ ያልቀረበ ሰው ሁለቱም ማደግደግ፣ መለመን፣ ዝቅ ማለት ይጠበቅባቸዋል የሚል ሀሳብ የያዘ ነው፡፡ ምሳሌያዊ አነጋገሩ በብሂረሰቡ የጋብቻ ስነ ስርዓት ያለን የሽማግሌዎች ምልልስ፣ የአግቢውንና የቤተሰቡንም ደጅ ጥናት የሚያሳይ ነው፡፡ ብሂረሰቡ ይህን መሰሉ ምልልስ ተገቢ እንደሆነና ሴት ልጅን ለመዳር የጋብቻ ጥያቄን ቶሎ መቀበል አግባብ አለመሆኑን የሚያምንበት በመሆኑ ነው ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር በስነቃል ሀብቱ ውስጥ የተገኘው፡፡

ሽምግልናው በእሺታ የተጠናቀቀ ከሆነ ከዚያ በኋላ ተጋቢዎቹ ቀደም ሲል ከነበራቸው ህይወት ይለያሉ፤ ቀደም ካለው የኑሮ ዘይቤያቸውና ጓደኞቻቸው ይለያሉ፡፡ ሴቷ ልጅ ቀደም ሲል ከጓደኞቿ ጋር ታሳልፍ የነበረውን ያህል ጊዜ አታሳልፍም፤ ከቤት ወጣ ወጣ ማለት አይፈቀድላትም፤ ጨዋታ አታበዛም፤ ደበቅ ትላለች፤ አብዛኛውን ጊዜ ከቀድሞ ጓደኞቿ ትለያለች፤ ከሌሎች ልጃገረዶች ተለይታ ትታያለች፤ ከሌሎች እኩዮቿ በተለየ

ትከበራለች፡፡ ይህን አስመልክተው አቶ አብዱልቃድር መሐመድ ሰዒድ (9/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) እንዲህ ብለዋል፡፡

> ከዚያ በኋላ ተሰጥታለች ማለት ነው፡፡ የትም የትም መታየት አይፈቀድላትም፡፡ ጨዋ እንድትሆን፣ ጭምት እንድትሆን ይፈለጋል፡፡ ረገብ እንድትል ይፈለጋል፡፡ … ሁሉ ቦታ ላይ አትሄድም፡፡ ያ የምትወደው ሺሎ እንኳን ሀላፊነቱ የእናትና አባት ስለሆነ እዚያ እንኳን አይልኳትም፡፡ ሺሎ አካባቢ ፈጽሞ አትሄድም፡፡ የባል መፍቀድ መብት ነው፡፡ ባሏ አግብታ ከጓደኞቿ ጋር ሊልካት ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ግን እናትና አባት ለሰው ሚስት ፈቃድ መስጠታቸው ስህተት ስለሆነ የተበላሸ ነገር ሲኖር የልጁ ወንድሞችና የአባቱ ጓደኞች ካዩ ስማችንን መሸፈን አለብን ብለው ይመጣሉ፡፡ … ያልተፈቀደላት ቦታ መሄድና ከማንም ጋር መዋል አይፈቀድላትም፡፡ የምታደርገው ነገር በቤት ውስጥ እናቷን ማገዝ ነው፡፡ እናቷ ከሷ በላይ እንድትሆን ትፈልጋለች፡፡

ሴቷ ልጅ ከዚህ ጊዜ በኋላ ለጋብቻ የተሰጠች በመሆኗ ሌሎች ቤተሰቦች ለጋብቻ አያስቧትም፤ ለመጥለፍ የሚደፍርም አይኖርም፡፡ የተሰጠችን ልጃገረድ መጥለፍ የሰው ሚስት እንደመጥለፍ የሚቆጠርና ህይወት እስከመጠፋፋት የሚያደርስ ጉዳይ ነው፡፡ መረጃ ሰጪዎች (አቶ መሐመድ አቡበከር እና አቶ አሕመድ ሲራጅ፣ 30/2/2013፣ ጋቺኔ ቀበሌ፣ ቡድን ተኮር ውይይት) የተሰጠችን ልጅ ጠልፈው ሲሄዱ የጋብቻ ጠያቂው ወንድሞች ተከታትለው ጥይት በመተኮስ የጠላፊውን ወንድም እንደመቱትና ህይወቱ እንዳለፈ ያጋጠማቸውን ገልፀዋል፡፡

ወንዱ ልጅም ቀደም ሲል ከነበረው ጊዜ በተለየ ጥሩ ባልሆነ ቦታ እንዳይታይና ተገቢነት የለውም የሚባል ባህርይ እንዳያሳይ ይጠነቀቃል፡፡ ይህን አስመልክተው አቶ መሐመድ ሀሰን (16/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) የሚከተለውን ብለዋል፡፡

እሱ ገበያ አይከለከልም፡፡ እንቅስቃሴ አይከለከልም፡፡ አልባሌ ቦታ ላይ ስሙን የሚያጠፋ ቦታ ላይ መገኘት የለበትም፡፡ ቤተሰብ ልጃችን ጥሩ ነው ብሎ ነው የጠየቀው፣ ያም ቤተሰብ ባለው መረጃ ጨዋ ነው ብሎ ነው የሰጠው፡፡ ጨዋነቱን ሲያጓድል ቤተሰቡ ክብሩ ስለሚነካ ጥሩ ያልሆነ ቦታ አይፈቀድለትም፡፡

የጋብቻ ጥያቄው እሺታን ካገኘ በኋላ ተጋቢዎቹ ቀደም ሲል ከነበሩበት ቡድንና የኑሮ ዘይቤ ይለያሉ፡፡ ለጋብቻ የተሰጠች ልጅ ከቀድሞ ጓደኞቿ መለየቷ፤ ጓደኞቿ ቀደም ሲል በሚያዩዋት መንገድ አለማየታቸው፤ ጓደኞቿ የእድሜ እኩዮቿ ቢሆኑም እንኳን ለጋብቻ የተሰጠች በመሆኗ በመካከላቸው ልዩነት መፈጠሩ፤ ልጅቷ እንደቀደመው ጊዜ ያህል ከጓደኞቿ ጋር የምታሳልፈው ጊዜ አለመኖሩ፤ ጨዋታ አለማብዛቷ፣ ሌሎች ቤተሰቦች ለጋብቻ የሚያስቧት አለመሆኗ፤ ሊጠልፉት የሚደፍር አለመኖሩ፣ ወንዱ አግቢም ጋብቻ እንደተጠየቀለት ልጅ ተገቢ ካልሆነ ባህርይና ስፍራ የሚርቅ መሆኑ የመለየት መገለጫዎች ናቸው፡፡ የጋብቻ ጥያቄ በእሺታ ከተጠናቀቀ በኋላ የሚከወነው ስነ ስርዓት የነገር መፍጃ ስነ ስርዓት ይሆናል፡፡

### 6.4.3. ሽግግር

የሽግግር ጊዜ ከነገር መፍጃ ስነ ስርዓት ክዋኔ ጀምሮ የሰርግ ስነ ስርዓት እስከሚከወንበት ቀን ዋዜማ ድረስ ያለውን ጊዜ ይይዛል፡፡ ይህ ጊዜ የነገር መፍጃ ስነ ስርዓትና የሰርግ ስነ ስርዓት ዝግጅት የሚከወኑበት ነው፡፡

#### 6.4.3.1. የነገር መፍጃ ስነ ስርዓት

የነገር መፍጃ ስነ ስርዓት በሽምግልና ጊዜ እሺታን ላገኘ ጋብቻ ቃል የሚታሰርበትና የሰርግ ቀን የሚቆረጥበት ነው፡፡ የነገር መፍጃው ስነ ስርዓት የሚከወንበትን ቀን ሽማግሌ ላኪው ቤተሰብና ሽማግሌዎቹ ተማክረው ከወሰኑ በኋላ የሴቷ ቤተሰብ ቀኑን እንዲያውቅ ቤተሰቡን የሚግባባ ሰው ሄዶ እንዲያሳውቅ ይደረጋል፡፡ በቃለመጠይቅ ጊዜ በመረጃ ሰጪዎች መካከል የነገር መፍጃ ቀን የቆዳ ማንጠፊያ ስነ ስርዓት ሲከወን ከሴቷ ቤተሰብ እሺታ በተገኘ ቀን ይደረጋል እና ነገር መፍጃ ራሱን በቻለ ሌላ ቀን የሚከወን ነው የሚሉ ሁለት የተለያዩ ሀሳቦች ተነስተው የነበረ ሲሆን በቡድን ተኮር ውይይት ጊዜ ጉዳዩ ተነስቶ የቡድኑ ተወያይ የነበሩት አቶ አብዱልቃድር ቃሲም ሁኔታውን በማስረዳታቸው ብዙዎቹ

ተሳታፊዎች ነገር መፍጃ ከቆዳ ማንጠፊያው በኋላ በሌላ ቀን ይከወናል በሚለው ሀሳብ ተስማምተዋል (16/7/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቡድን ተኮር ውይይት)፡፡

በነገር መፍጃው ቀን የሴቷ ቤተሰብ አርዶና ደግሶ፣ ቅቤና ማር ቀድቶ፣ ምስክር የሚሆኑ ሽማግሌዎችን አቅርቦ ከወንሰዱ በኩል የሚመጡትን ሰዎች ይጠብቃል፡፡ ከሽማግሌ ላኪው ቤተሰብ ሽማግሌዎቹ የተወሰኑ ሰዎችን ጨምረው ይሄዳሉ፡፡ በእለቱ ከወንዱ በኩል የሆኑ ሰዎች እንደመጡ ምግብ ቀርቦ ይጋበዛሉ፣ ቡና ተፈልቶ ይጠጣሉ፡፡ ከዚያ በኋላ በቅደም ተከተል ቃል አስረው የሰርጉን ቀን ይወስናሉ (አቶ ሁሴን ጢኖ፣ 9/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ቃል የሚታሰረው መጀመሪያ ከሴቷ ቤተሰብ የሆነ ሰው ጉዳዩን ለመጀመር ያህል[25] ሽማግሌዎቹን "ለምን መጣችሁብን?" ብሎ ይጠይቃል፡፡ ከሽማግሌዎቹ አንዱ "ልጃችሁን እከሊትን ለወካዬ ለእከሌ ለእከሌ ልጅ እንድትሰጡን ለመጠየቅ ነው የመጣነው" ይላል፡፡ የሴቷ ቤተሰብ የሆነው ሰውም በሽምግልና ጊዜ በጋብቻ መስማማታቸውን በመግለጽ "አሁንም ልጃችንን እከሊትን ሰጥተንሀል" ይለዋል፤ ሽማግሌውም "ተቀብያለሁ" ይላል፡፡ ይህ ምልልስ ቃልኪዳን ማሰሪያ ቃል ነው፤ የሴት ቤተሰብ ልጁን መስጠቱን፣ የወንድ ሽማግሌዎች መረከባቸውን በመግለጽ በቃል የሚተሳሰሩበት ነው (አቶ ሁሴን ጢኖ፣ 9/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ምንም እንኳን በሽምግልና ጊዜ በጋብቻ ለመዛመድ ስምምነት ላይ ቢደረስም የተጋቢዎቹ ይፋ የእጮኝነት ጊዜ የሚጀምረው ግን ከዚህ "የሰጠሁህና የተቀበልኩ" ቃልና ትጭጭት ጀምሮ ነው፡፡

ከ"ሰጠሁህ - ተቀበልኩ" ቃል በኋላ የሰርጉ ቀን መቼ መሆን እንዳለበት ይወሰናል፡፡ ሁለቱ ቤተሰቦች የሰርጉን ቀን የሚወስኑት በውይይት ተስማምተው ቢሆንም ቀኑን የመወሰን ትልቅ ድርሻ ያለው የሴቷ ቤተሰብ ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ሽምግልና የመጣው ወገን የሰርጉ ቀን በአጭሩ እንዲወሰንለት ቢፈልግም ሽማግሌዎቹን የተቀበለው ወገን ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች የሰርጉ ቀን ይራዘምልን ይላል (አቶ ሁሴን ጢኖ፣ 9/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ የሆነው ሆኖ የሰርግ ቀንን ለመወሰን የተለያዩ ጉዳዮች ከግምት ይገባሉ፡፡

[25] በቆዳ ማንጠፊያ ጊዜ ተነጋግረው ከውሳኔ ላይ የደረሱ ቢሆንም ንግግሩን አዋዝቶ ለመጀመር ሲባል

የሰርግ ቀን የሚወሰነው በዋናነት የምትዳረውን ልጅ ከግምት በማስገባት፣ እህል የሚደርስበትን ወቅት በማስታከክና ድግስ ለመደገስ ከሚያስፈልገው ዝግጅት አንፃር በቂ ጊዜ እንዲኖር በማድረግና ገድ አለው የሚባል ወቅትን በመምረጥ ሲሆን ሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮችም ታስበው ሰርጉ ነፃ በሆነና በሚመች ቀን እንዲሆን ይወሰናል (አቶ ሁሴን ጢኖ፣ 9/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የምትዳረው ልጅ በእድሜ ትንሽ ከሆነች ከፍ እስክትል ድረስ ጠብቁ ተብሎ የሰርጉ ቀን ሊረዝም ይችላል፡፡ ሽማግሌ የተላከበት ጊዜ ምርት ከሚደርስበት ጊዜ ጋር የተራራቀ ከሆነና በዚያ ጊዜ ድግስ ለመደገስ አስቸጋሪ ከሆነ በአካባቢው የእርሻ ምርት እስኪደርስ ድረስ እንዲጠበቅና ሰርጉ በዚያ ጊዜ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ድንገት የታሰበ ሰርግ (ለምሳሌ፣ ለሁለተኛ ጋብቻ የሚደረግ) ካልሆነ በስተቀር በሰኔና በሐምሌ ወራት የታሰበበት ሰርግ አይደረግም፤ ወቅቱ እህል የሚያልቅበትና የእርሻ ስራ የሚከናወንበት ነው፡፡ ገድ ያላቸውና የሌላቸው ወቅቶች አሉ በሚል እምነት መነሻነትም የሰርግ ቀን ጥሩ ገድ ያስገኛሉ በሚባሉ ወቅቶች እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ለምሳሌ ከወራት ጥርና የካቲት ሰርግ የሚደረግባቸው ወቅቶች ናቸው፡፡ በግንቦት ወር፣ በጨረቃ አቆጣጠር መሰረት የሶፈር[26] ጨረቃ በሚታይበት ጊዜና በአረፋና ኢድ መካከል ባለ ጊዜ ሰርግ አይደገስም፡፡ በአርጐባዎች ዘንድ በግንቦት የተቆረጠ ዛፍ እንኳን አይለመልምም፤ ይደርቃል፤ ዝናብ ቢዘንብ እንኳን ትል ያመጣል እንጂ አይጠቅምም የሚል እሳቤ አለ፡፡ በብሄረሰቡ እርጥብና ልምላሜ ከመልካም እድል፣ ከገድ ጋር የተገናኘ ትርጓሜ የሚሰጠው በመሆኑ ይህ የማይሆንበት የግንቦት ወር ገድ የማይገኝበት ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ ምክንያት ግንቦት ወር ሰርግ አይደገስበትም፡፡ ሶፈር ጨረቃ የሚወጣበት ጊዜም ገደ ቢስ እንደሆነ ይታመናል (አቶ ሁሴን ጢኖ፣ 9/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በአካባቢው መንፈሳዊና ሌሎች ማህበራዊ ስነ ስርዓቶች መኖራቸው የሰርግ ቀን ውሳኔን የሚነኩ ጉዳዮች በመሆናቸው የሰርግ ቀን ሲወሰን ቀኑ እነዚህን አይነት ሌሎች ስነ ስርዓቶች የማይከናወኑበት ቀን ተመርጦ ነው (አቶ ሁሴን ጢኖ፣ 9/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ በመስክ ቆይታዬ፣ በተለይም በገበሮች ቀበሌ በርካታ ሰኞ ቀን የተከወኑ የሰርግ ስነ ስርዓቶች አጋጥመውኛል፡፡ ከእሁድ ይልቅ ሰኞ ሰርግ የመደረጉን ምክንያት ጠይቄ እሁድ በአካባቢው የዱዓ ቀን መሆኑን፣ በዚያ ቀን ሁሉም ሰው ወደ መስጊድ

[26] የወር ስያሜ

የሚሄድበትና ዱዓ የሚያደርግበት እንጂ ሰርግ የሚታሰብበት አለመሆኑ ተገልፆልኛል (አቶ አቡበከር መሐመድ ኑር፣ 24/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የነገር መፍጃ ስነ ስርዓት ቃል የሚታሰርበትና የሰርግ ቀን የሚወሰንበት ከመሆኑ በተጨማሪ አግቢው ልጅ ለልጅቷ ቤተሰብ የሰርግ መደገሻ ገንዘብና ለልጅቷ ልብስ የሚሰጥበት ቀን ነው፡፡ የሚሰጠው ገንዘብ መጠን ሙሽራው የሚያመጣውን አጃቢ ሊጋብዝ የሚችል በመሆኑ መጠኑ እንደሚያመጣው አጃቢ ቁጥር ይወሰናል፡፡ ነገር ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚሰጠው የገንዘብ መጠን ከፍ እያለ በመምጣቱና በሰዎች መካከል ፉክክር በማስከተሉ የኢኮኖሚ አቅማቸው አነስተኛ በሆነ ሰዎች ላይ ጫና አስከትሏል፡፡ በዚህ ምክንያት የሼሪያው ፍ/ቤትና የሀገር ሽማግሌዎች መክረው ለመደገሻ የሚሰጥን ገንዘብ መጠን ወስነዋል፡፡ በመሆኑም ለመደገሻ የሚሰጠው ገንዘብ ከ3,000.00 (ሶስት ሺህ) ብር እንዳያልፍ የወሰኑ ቢሆንም ሰዎች ገንዘቡ ለፍየል መግዣ እንኳን አይበቃም በሚል ምክንያት የሚሰጠውን የገንዘብ መጠን እስከ 10,000.00 (አስር ሺህ) ብር ድረስ እንዲደርስ እያደረጉት በመሆኑ አብዛኛው ሰርግ ላይ ለመደገሻ የሚሰጠው ብር ከ10,000.00 (አስር ሺህ) ብር ያነሰ አይደለም፡፡ ከሰርግ መደገሻ ገንዘብ በተጨማሪ ወንዱ አግቢ ለአግቢዋ ልጅ ልብስ የሚልክ ሲሆን ቃል ከተግባቡና የሰርግ ቀን ከቆረጡ በኋላ ሽማግሌዎቹ ከመደገሻ ገንዘቡ ጋር ለሴቷ ቤተሰብ ያስረክባሉ፡፡ ነገር ግን ልጅቷ ልብሱን ሳትለብስ እስከ ሰርጉ ድረስ በማቆየት በሰርጉ ቀን ወደ ባሏ ቤት ይዛው ትሄዳለች እንጂ አትለብሰውም፡፡ ጋብቻው ይፋ ያልተደረገ በመሆኑ ምክንያት ሰርግ ተደግሶ አንድ ቤት መኖር ሳይጀመር አግቢው የገዛውን ልብስ ለብሶ መታየት እንደ ነውር ይቆጠራል (አቶ አህመድ ሲራጅ፣ 28/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በብሄረሰቡ ዘንድ የሚተገበር ፆታን መሰረት ያደረገ የስራ ክፍፍል ወንድና ሴት ያሉባቸውን ሚናዎች የሚሰጥ ነው፡፡ የሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ብሄረሰቡ የሚመራበትን ስርዓተ ፆታን መሰረት ያደረገ የስራ ክፍፍል የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡

- ሴት ባል የለም ብላ ከቤት መውጣት፣ ደረሳ ሼህ የለም ብሎ ከመስጊድ መውጣት አይሆንም (አቶ አሕመድ ሲራጅ፣ 27/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡
- ወንድና ማረሻ ይዋልልን በእርሻ (አቶ አሕመድ ሲራጅ፣ 27/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የመጀመሪያው ምሳሌያዊ አነጋገር ሚስትን ወይም ሴትን የቤት፣ ደረሳን ደግሞ የመስጊድ ብቻ የሚያደርግ ሲሆን ሚስት በማንኛውም ጊዜ የቤት ውስጥ ስራዎችን በማከናወን ጊዜዋን በቤት ውስጥ ማሳለፍ ይኖርባታል የሚል ሀሳብን የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ በአንፃሩ ሁለተኛው ምሳሌያዊ አነጋገር ወንድ ወይም ባል በእርሻ ስራ እንዲውል መመኘትን በመግለጽ የባል ሚና የእርሻ ስራዎችን ማከናወን ነው የሚልን የብሂረሰቡን እውነታ ይገልፃል፡፡ የመጀመሪያው ምሳሌያዊ አነጋገር በብሂረሰቡ ተቀባይነት የሌለውን ተግባር በመቃወም፣ ሁለተኛው ደግሞ እንዲሆን የሚፈለግን በመመኘት በብሂረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ተግባራት ብቻ እየተከወኑ እንዲቀጥሉ ያፀናል፡፡ ከነገር መፍጃ ስነ ስርዓት በኋላ እጮኛሞቹ የሚያደርጉት የጋብቻ ዝግጅትም በዚሁ አግባብ የተቃኘ ነው፡፡

የነገር መፍጃ ስነ ስርዓት ከተከናወነ በኋላ እጮኛሞቹ ለጋብቻ የሚያበቃቸውን የየራሳቸውን ዝግጅት ያደርጋሉ፡፡ ሴቷ ከምታደርጋቸው ዝግጅቶች መካከል አንዱ የቁስ ዝግጅት ሲሆን ወደፊት የሚጠቅሟትን እንደ መሶብ፣ ሰፌድና ወንፊት ያሉ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶችን ሰፍታ ታዘጋጃለች፤ የጭስ መሞቂያዋን ጉንደሬ ቀሚስ ፈትላ ታሰራለች፣ በሙያ ረገድም እናቷ፣ አክስቷ፣ አያቷ ወይም ሌላ ሴት አጠገቧ በመሆን ምግብ ማዘጋጀትን፣ ቤት አያያዝን፣ እንግዳ አቀባበልን፣ ወዘተ በተመለከተ እውቀት እንዲኖራት ታሰለጥናታለች፡፡ ወንዱ አግቢም ለቀጣይ የትዳር ህይወቱ ይዘጋጃል፡፡ በመሆኑም የእርሻ ስራን፣ ከብት አርዶ መበለትን የመሰሉ የወንድ ተብለው የተለዩ ስራዎችን በአግባቡ እንዲያውቅና ያለማንም እርዳታ በራሱ ማከናወን እንዲችል ይማራል፤ የራሱን ጐጆ በቤተሰቡ ግቢ ውስጥ ከቤተሰቡ ቤት በስተጀርባ ይቀልሳል (ወ/ሮ ከድጀሺ ከማል፣ 20/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የሰርጋቸው ቀን የተቆረጠ እጮኛሞች ክልክሎች አሉባቸው፡፡ ይህም እርኩስ መንፈስ ደስታቸውን ስለማይወድ ይፈታተናቸዋል፤ በዚህ ምክንያትም እስከ ሞት የሚደርስ አደጋ ሊያደርስባቸው ይችላል ተብሎ ስለሚታመን ለጋብቻ የሚዘጋጁ ወጣቶች ብቻቸውን እንዳይጓዙ፣ ረዥም መንገድ እንዳይጓዙ፣ ቢቻል በመኪና እንዳይሳፈሩ፤ ብረት እርኩስ መንፈስን ያሸሻል ተብሎ ስለሚታመን ወንዱ አግቢ ብረት ይዞ እንዲንቀሳቀስ ይመከራሉ (ወ/ት ፈቲያ አንበርብር፣ 24/2/2013፣ ጋቺኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ከነገር መፍጃ ስነ ስርዓት በኋላ እጮኛሞቹ እርስ በርስ፣ አንዳቸው ከሌላቸው ቤተሰብ ጋር እና ቤተሰቦቻቸው እርስ በርስ የሚኖራቸው ግንኙነት በተለየ መንገድ የተቃኘ ይሆናል፡፡

እጮኛሞቹ እጮኛሞች መሆናቸውን ካወቁ በኋላ ቀደም ሲል ቢተዋወቁ እንኳን መተፋፈር ይጀምራሉ፤ በመንገድ ቢገናኙ እንዳላየ ይተላለፋሉ፤ ዘመዳሞች ወይም የአንድ አያት ልጆች ሆነው በየበዓሉ በዘመድ ወይም በአያት ቤት ሲገናኙም ከመጫወት ይልቅ ይተፋፈራሉ፡፡ እጮኛሞቹ አንዳቸው ከሌላቸው ቤተሰብ ጋር የተለየ አክብሮትና መፍራት ይኖራቸዋል፤ በአጋጣሚ መንገድ ላይ ቢያዩዋቸው እንኳን መንገድ አሳብረው ይሸሻሉ እንጂ ፊት ለፊት እንዲገናኙ አይፈልጉም፡፡ የእጮኛሞቹ ቤተሰቦችም ዝምድናና ማህበራዊ ግንኙነት የሌላቸው ከነበሩ ከትጭጭቱ በኋላ በደስታና በሀዘን ጊዜ የሚገናኙ ይሆናሉ፤ ነገር ግን ዘመዳሞች ከነበሩ ወይም ቀደም ሲል የጠነከረ ማህበራዊ ግንኙነት የነበራቸው ከሆኑ ከትጭጭቱ በኋላ ግንኙነታቸው ይቆጠብና በዋና ዋና የደስታና የሀዘን ጊዜዎች ብቻ ይገናኛሉ (ወ/ት ራዲ ቡሴሪ፣ 15/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ በሁለቱ ቤተሰቦች መካከል የተለየ መከባበርና የራስንም ክብር የመጠበቅ ፍላጐት ይፈጠርና ግንኙነታቸውን የተለየ መልክ ያስይዘዋል፡፡

ከነገር መፍጃው ጀምሮ ሰርጉ ምንም ያህል ይርዘም የወንዱ ቤተሰብ ለሴቷ ቤተሰብ ጥቅምት ሲደርስ እሸትና አገዳ፤ መውሊድ በሚደረግበት ወር ደግሞ ቅቤና ዳቦ ይልካል፡፡ አግቢውም በአረፋና በኢድ ፍየልና ለተሰጠችው ልጅ ልብስ ይልካል፡፡ “ሰጠሁህ - ተቀበልኩ” ቃል ትልቅ ቦታ የሚሰጠውና እንደ ኒካህ የሚታይ በመሆኑ ወንዱ እጮኛውን መቀበሉንና የራሴ ነች ማለቱን፣ ግዴታውን ማወቁንና እየተወጣ መሆኑን፣ ጋብቻውን መፈለጉን የሚያሳየው ከቃል ትስስሩ በኋላ በሚያደርገው ስጦታ ነው፡፡ ስጦታ አለመላኩ ጋብቻውን አለመፈለጉን መግለፁ እንደሆነ ስለሚታሰብ የሴቷ ቤተሰብ ጋብቻውን ካልፈለገ ለምን አለፋን እንዲሉ የሚያደርግ ነው፡፡ ስጦታውን የሚያደርሰው ወደፊትም ለሰርጉ ሚዜ የሚሆነው የልጁ አብሮ አደግ ጓደኛው ወይም ዘመዱ ነው (ወ/ሮ መራኢና መሐመዴ፣ 23/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

#### 6.4.3.2. የሰርግ ስነ ስርዓት ዝግጅት

የነገር መፍጃ ስነ ስርዓት ከተከናወነ በኋላ የሚጠበቀው የሰርግ ስነ ስርዓት በመሆኑ ከነገር መፍጃው በኋላ እስከ ሰርጉ ቀን ድረስ የሰርግ ዝግጅቶች ይደረጋሉ፡፡ ከዚህ በታች በቅደም ተከተል ከሰርጉ ቀን ቀደም ተብሎና የሰርጉ ቀን ሲቀርብ የሚደረጉ ዝግጅቶች ይቀርባሉ፡፡

### ሀ. ከሰርጉ ቀን ቀደም ተብሎ የሚደረጉ ዝግጅቶች

በነገር መፍጀ ስነ ስርዓት የሰርግ ቀን ከተቆረጠ በኋላ ሙሽሮች ሚዜና አጀቢዎቻቸውን ይለያሉ፤ ሙሽራዋ ይዛው የምትሄደውን የቤት እቃ ታዘጋጃለች፤ ሰርግ የሚደገስባቸው ቤቶችና አጥሮቻቸው ይታደሳሉ፤ እህልና የማገዶ እንጨት ይዘጋጃል እንዲሁም የሰርግ ጥሪ ይደረጋል፡፡

**ሚዜና አጃቢን መለየት፣**

በአርጐባዎች ዘንድ ሚዜነት ትልቅ ዋጋ ይሰጠዋል፡፡ ዝምድና፣ መዋደድ፣ ወንድማማችነት ወይም እህትማማችነት፣ ታማኝነት፣ ጨዋነት፣ ሚስጥር ጠባቂነት የሚዜ መምረጫ መስፈርቶች ናቸው፡፡ ሚዜ የሚሆኑ ተዋደው ሲያጠፉም ሲያለሙም አብረው ያደጉ ጓደኞችና ዘመዶች ናቸው፡፡ ቤተሰብ ከልጅነት ጊዜያቸው ጀምሮ አንተና አንተ፣ አንቺና አንቺ ሚዜ ናችሁ እያላቸው ያድጋሉ፡፡ በየሰርጋቸውም ጊዜ ማን የማን ሚዜ እንደሆነ ወይም እንደሆነች ይታወቃል (አቶ አቡበከር መሐመድ ኑር፣ 28/6/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ በዚህ መሰረት የሚመረጡ ሚዜዎችን ለሚዜነት ማሳሰብ ከነገር መፍጀው በኋላ ይደረጋል፡፡

ሙሽሮች ሁለት ሁለት ሚዜዎች አሏቸው፡፡ የሁለቱም ሙሽሮች የመጀመሪያ ሚዜዎች ዋና ሙሽራ ይባላሉ፡፡ ሁለተኛ ሚዜዎች ደግሞ ግልገል ሙሽራ ይባላሉ፡፡ ዋናም ሆነ ግልገል ሙሽራዎች የየራሳቸው ሀላፊነቶች አሉባቸው፡፡ ዋና ሙሽሮች የሰርጉ እለት በየቤታቸው ደግሰው ምሳ ያበላሉ፡፡ የሙሽራው ዋና ሙሽራ ቤቱ ደግሶ ሙሽራውን እስከ አጃቢዎቹ ምሳ የሚያበላ ሲሆን የሙሽራዋ ዋና ሙሽራም እንዲሁ በቤቷ ደግሳ ሙሽሪትንና አጃቢዎቿን ምሳ ታበላለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሰርጉ ቀን ዋናው ሙሽራ ለሙሽራዋ የሚሄድን ጥሎሽ አቅርቦ ለሽማግሌዎች ያሳያል፣ የሰርጉ ቀን ማታ ሙሽራውን ወደ ጫጉላ ቤት ይወስዳል፣ የምስራቹንም ያበስራል፣ በሙሽራዋ ቤት ሙሽሮች ሲወጡ ሙሽራዋን አዝሎ በቅሎ ድረስ ይወስዳል፡፡ ግልገል ሙሽራው ሙሽራውን ያለብሳል፣ ያስተካክላል፣ በስራ የጐደለ ሲኖር ያሟላል፣ ያስተናግዳል፣ ሽቶና ከረሜላ ይገዛል፣ ሙሽራዋ በምትወጣበት ጊዜ ሽቶ ይረጫል፣ ከረሜላ ይበትናል፡፡ የሴቷ ግልገል ሙሽራ ደግሞ ሙሽራዋን የማስዋብ ሀላፊነት አለባት፡፡ በመሆኑም ሰርጉ ሲደርስ ሙሽራዋን ደጋግማ ጭስ ታሞቃታለች፣ ልብሷን ታሞቃለች፣ በሰርጉ ሰሞን ሁሉ ከሙሽራዋ ሳትለይ

ሙሽራዋን ትንከባከባለች (አቶ ሰማን አሊ፣ 12/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የሙሽራ አጃቢዎችን የመምረጫ መስፈርት ዝምድናና ቅርበት ነው፡፡ የሙሽሮች ቤተሰቦች አጃቢዎችን በመምረጥ ትልቅ ቦታ አላቸው፡፡ ቤተሰቦች የዝምድና ሀረግን በመከተልና በወዳጅነት ባለ ቀረቤታ እያስታወሱ አጃቢዎችን በመለየት ሙሽሮችን ያሳስባሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሙሽሮች አብሮ አደጎቻቸውንና ጓደኞቻቸውን ለአጃቢነት ይጠራሉ፡፡ የአጃቢዎች ቁጥር ሙሽሮቹ እንዳላቸው ማህበራዊ ግንኙነት ሁኔታ ይወሰናል፡፡ ሙሽሮቹ በማህበራዊ ኑሯቸው ከሰዎች ጋር ጠንካራ ግንኙነት ያላቸውና ዘመደ ብዙ ከሆኑ በርካታ አጃቢዎች የሚያጅቧቸው ሲሆን (የአጃቢዎች ቁጥር የተወሰነ አይደለም) የሙሽራው አጃቢዎች እንደየአቅማቸው ለሙሽራው የገንዘብ ስጦታ ያደርጋሉ (አቶ ኡስማን አደም፣ 15/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ለአጃቢዎች አጅቡኝ ተብሎ የሚነገረው ከነገር መፍጃ በኋላ ነው፡፡

**ኢኮኖሚያዊ ዝግጅት፣**

በወረዳው ከተማ ጋቸኔ አብዛኛው ነዋሪ ከግብርና ስራ ውጭ ባለ መተዳደሪያ የሚተዳደር በመሆኑ የግብርና ስራ ውጤቶችን የሚያገኘው ከገበያ በመግዛት ነው፡፡ በመሆኑም በከተማዋ ሰርግ ለመደገስ የሚነሳ ቤተሰብ በተለየ መልክ የግብርና ስራን የሚያከናውን ወይም የግብርና ውጤቶችን ዘመድ በስጦታ የሚያመጣለት ካልሆነ በስተቀር አብዛኛዎቹን የግብርና ውጤቶች ከገበያ ይገዛል፡፡ በመሆኑም እህል፣ ለእርድ የሚሆን ፍየል፣ ቅቤና ማር፣ ቅመማ ቅመም፣ ወዘተ ከገበያ ይገዛል ማለት ነው፡፡ በዚህ ምክንያት አንድ መካከለኛ ሰርግ ለመደገስ እስከ 50,000.00 (ሀምሳ ሺህ) ብር፣ ትልቅ ሰርግ ለመደገስ ደግሞ እስከ 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ) ብር ድረስ ሊያስፈልግ ይችላል (አቶ አህመድ ሲራጅ፣ 28/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ከጋቸኔ ውጭ ያሉ የገጠር ቀበሌዎች ውስጥ የሚኖሩ ነዋሪዎች ደግሞ በአብዛኛው የእርሻ ማሳ ያላቸውና በግብርና ስራ የሚተዳደሩ በመሆናቸው ሰርግ የሚደግስ ቤተሰብ ከገበያ የሚገዛቸው የምግብ ሸቀጦች ውሱን ናቸው፡፡ በመሆኑም ከገበያ የሚገዙ ሸቀጦች በአብዛኛው ጨው፣ ዘይትና ስኳር ናቸው፡፡ ስለዚህ በገንዘብ ደረጃ ከጋቸኔ አንፃር ሲታይ ወጪው አነስተኛ ነው ማለት ነው (ወ/ሮ አይኔ

ይማሙ፣ 5/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ በዚህ ረገድ ሰርግ የሚደግስ ቤተሰብ ሰርጉ ከመድረሱ አስቀድሞ ራሱን በኢኮኖሚ ያጠናክራል፡፡

## የሙሽራ እቃዎች ዝግጅት፣

የሰርጉ ቀን ከመድረሱ አስቀድሞ ከሚከናወኑ የተለያዩ ዝግጅቶች ውስጥ የመጀመሪያው ሙሽራዋ ከነገር መፍጃው ስነ ስርዓት ጀምራ ስታበጃቸው የነበሩ በሰርጉ ቀን ወደ ባሏ ቤት ስትሄድ ይዛቸው የምትሄደውን እንደ ስፌትና ዳንቴልን የመሰሉ የእጅ ስራ ቁሶች አዘጋጅታ ማጠናቀቅ ነው፡፡ ሙሽራዋ የሚያስፈልጓትን የእጅ ስራ ቁሶች አበጅታና አስጊጣ ታዘጋጃለች (ወ/ሮ አይኔ ይማሙ፣ 5/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡



ፎቶግራፍ 16. ሙሽራ የምትወስዳቸው የስፌት ስራዎች



ፎቶግራፍ 17. ሙሽራ የምትወስደው ጋቢ

## ቤትና አጥርን ማደስ፣

የሰርጉ ቀን ሲደርስ ቤትን የማዘጋጀት ስራ ይከናወናል፡፡ የተለያየ ቀለም ያላቸው የአፈር ዓይነቶች በውሀ ተበጥብጠው የቤት ግድግዳ ይቀባል፤ ወለሉ በከብት እበት ይለቀለቃል፤ ልብስ ይታጠባል፡፡ የክትክታ ዛፍ ቅርንጫፍ ተቆርጦ በዚያ እየተሸመጠጠ አጥር ይታደሳል፤ ይጠብቃል፡፡ ቤቱን የማዘጋጀት ስራውን ሴቶች የሚያከናውኑት ሲሆን አጥሩን በሽምጥ ማጥበቁን ደግሞ የቤተሰቡ ወንድ አባላት ከወንድ ጐረቤቶቻቸው ጋር በመሆን ያከናውኑታል፡፡ ለአጥር የሚሆነውን ሽምጥ ከፊሉን የቤተሰቡ ወንድ አባላት የሚያቀርቡ ሲሆን ጐረቤቶቻቸውን ለአጥር የሚሆን ሽምጥ ይዘው እንዲመጡ በማሳሰብ ከፊሉን ጐረቤቶቻቸው ያመጡላቸዋል (አቶ አደም መሐመድ፣ 5/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

**እህል ማበጃ፣**

እህል ማበጃ በሰርግ ስነ ስርዓት ላይ ለሚቀርብ ምግብ ዝግጅት የሚሆን እህል የማዘጋጀት ስራ ነው፡፡ ለሰርጉ ምግብና መጠጥ ማዘጋጃ የሚሆን እህል ለፀሀይ ተሰጥቶ፣ ተበጥሮ፣ ተለቅሞና ተፈጭቶ ይቀመጣል፡፡ ይህን ስራ የሚያከናውኑት ጐረቤትና ዘመዶች የሆኑ ሴቶች ሲሆኑ ለእህል ማበጃ በተቆረጠው ቀን ሁሉ በሰርጉ ቤት እየተገኙ እህሉን ያዘጋጃሉ፡፡ የጉልበት እገዛ የሚያደርጉ ሴቶች በእህል ማበጃው ቀን በሰርጉ ቤት እንዲገኙ አንድ ጐረቤት የሆነች ሴት በየመንደሩ እየዞረች "እከሊት የእህል ማበጃው ቀን በዚህ ቀን ነውና መጥታችሁ አግዙኝ ብላለች" በማለት ትጠራለች፡፡ በእህል ማበጃው ቀን ሁሉ ስራ ለማገዝ ወደ ሰርጉ ቤት የሚሄዱ ሴቶች ስራውን ካከናወኑ በኋላ ቤት ባፈራው ይስተናገዳሉ፡፡ እህሉ ከተዘጋጀ በኋላም ዝግጅታቸው ቀደም ተደርጐ የሚጀመረውን የእልበት፣ የቀሪቦና የአብሽ ውሃ ዝግጅትንም በጋራ በመሆን ያከናውኑታል (ወ/ሮ አይኔ ይማሙ፣ 5/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

**እንጨት ሰበራ፣**

እንጨት ሰበራ ለሰርጉ ምግብ ማብሰያ የሚሆን የማገዶ እንጨት ከጫካ ተቆርጦ በሰርጉ ቤት የሚቀርብበት ስራ ነው፡፡ የሙሽራ አጃቢና ጐረቤት የሆኑ ወጣት ወንዶች ለእንጨት መስበሪያ በተቀጠረበት ቀን በመሰባሰብ ከጫካ እንጨት ሰብረው በትከሻቸው ተሸክመው ወይም በግመል ጭነው በማምጣት በሰርጉ ቤት ግቢ ውስጥ ይከምራሉ፡፡ እንጨት ሰበራ ሰርጉ አንድ ወር ሲቀረው ጀምሮ ይከናወናል፡፡ እንጨት ሰበራውን የሚያስተባብሩ ራሳቸው የጐረቤት ወጣቶች ሲሆኑ ስራቸውን ካጠናቀቁ በኋላ በሰርጉ ቤት ቤት ያፈራው ቀርቦላቸውና ቡና ተፈልቶላቸው ይስተናገዳሉ (አቶ ኢብራሂም አወል፣ 11/7/2013፣ ጐዜ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

**የሰርግ ጥሪ፣**

የሰርግ ጥሪ ሰርጉ አስራ አምስት ቀን ሲቀረው የሚደረግ ሲሆን ሩቅ ላሉ ዘመዶችና ወዳጆች ደብዳቤ ጽፎ በመላክ ይደረጋል፡፡ ከሩቅ ቦታ በደብዳቤ የሚጠራው ወዳጅ ዘመድ ከሰርጉ ቀን ቀድሞ የሚገኝና ከሰርጉም በኋላ የሚቆይ በመሆኑ ሁሉንም ስነ ስርዓት የሚታደም ይሆናል (ወ/ሮ አይኔ ይማሙ፣ 12/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በአካባቢ ላሉ ጐረቤቶች ጥሪውን ለማድረስ ደግሞ የሰርጉ ቤት አባወራ ወንድ፤ እማወራዋ ደግሞ ሴት ጠሪዎችን በመምረጥ ወንዶችን ወንዱ፣ ሴቶችን ደግሞ ሴቷ ይጠራሉ፡፡ ለጐረቤት ሰዎች የሚደረጉ የጥሪ አይነቶች አራት ናቸው፡፡ እነዚህ የጥሪ አይነቶች አንደኛው "ሙሽራ ሸኙልኝ"፣ ሁለተኛው "ልጄ ጉፍታ ስለምትጭን እዩልኝ"፣ ሶስተኛው "ሙሽራ ተቀበሉልኝ" እና አራተኛው "ሙሽራ ሸኙልኝም ተቀበሉልኝም" በማለት የሚደረጉ ጥሪዎች ናቸው፡፡ አንደኛው ጥሪ ለሙሽራው ቤት ተጠሪዎች የሚደረግ ከሆነ ተጠሪዎች በምሳ ሰዓት ወደ ሰርጉ ቤት በመሄድ ተጋብዘውና ሙሽራውን ሸኝተው ወደ ቤታቸው የሚመለሱ ሲሆን በሙሽራዋ ቤት ከሆነ ደግሞ ተጠሪዎች ከምሳ በኋላ ወደ ሰርጉ ቤት በመሄድ የእራት ግብዣ ተደርጐላቸውና ሙሽራዋን ሸኝተው ይመለሳሉ፡፡ ሁለተኛው ጥሪ ለሙሽራዋ ቤት ተጠሪዎች የሚደረግና የሙሽራዋ እናት የምታደርገው ሲሆን ጥሪው በእድሜ አንጋፋ ለሆኑና ዱዓ በማድረግ ለሚታወቁ ሴቶች የሚደረግ ነው፡፡ ይህ አይነቱ ጥሪ የሚደረገው ሴቶቹ በተለይ በጉፍታ ስነ ስርዓቱ ላይ ተገኝተው ስነ ስርዓቱን እንዲከዉኑና እንዲጋበዙ ነው፡፡ ሶስተኛውና አራተኛው ጥሪዎች ለሙሽራው ቤት ተጠሪዎች የሚደረጉ ሲሆን በቀዳሚው ጥሪ ተጠሪዎች አመሻሽ ላይ ወደ ሰርጉ ቤት በመሄድ እራት የሚጋበዙና ሙሽራው ሲመጣ የሚቀበሉ ሲሆን ሙሽራ ሸኙልኝም ተቀበሉልኝም ተብሎ የሚጠሩ ተጠሪዎች ደግሞ በሰርጉ ቤት ከምሳ በፊት ቀድመው በመገኘት ምሳ ተጋብዘውና ሙሽራውን ሸኝተው እዚያው በመዋል ማታም ሙሽራውን ይቀበላሉ (ወ/ሮ አይኔ ይማሙ፣ 12/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

### ለ. ሰርጉ ሲቀርብ የሚደረጉ ዝግጅቶች

የሰርጉ ቀን ሲቀርብ ሙሽራዋ ጭስ በመሞቅ፣ ልብሷን በማሞቅና ፀጉሯን ተሰርታ ቅቤ በመቀባት ራሷን ታስውባለች፤ የምግብ ዝግጅቱ በከፊል ይደረጋል፤ ዳስ ይጣላል፣ የሽድር ስነ ስርዓት ይከናወናል፡፡

**ራስን ማስዋብ፣**

የሰርጉ ቀን ሲቃረብ ሙሽራዋ ራስዋን መንከባከብና ማስዋብ ትጀምራለች፡፡ ውበቷን ከምትጠብቅባቸው ልማዶች መካከል ጭስ መሞቅ፣ ገላዋን በተቀቀለ የወይባ ቅጠል መታጠብ፣ ልብሷን ማሞቅ፣ ፀጉሯን መሰራትና ቅቤ መቀባት ዋና ዋናዎቹ ናቸው (ወ/ሮ አይኔ ይማሙ፣ 12/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ጭስ መሞቅ፣ ጭስ የመሞቅ ልማድ ያላት የአርጎባ ሴት ንፁህና ጥሩ መዓዛ ያላት በመሆኗ በየሄደችበት አካባቢዋን በጥሩ መዓዛዋ ታውዳለች፤ ይህም በሰዎች ዘንድ አድናቆትን ያስቸራታል (ወ/ሮ አይኔ ይማሙ፣ 12/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ከዚህ በታች የቀረበው የአርጎባዎች መንቶ ግጥም አቶ መሐመድ አቡበከር (5/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) የነገሩኝ ሲሆን ጭስ መሞቅንና የተሞቀ ልብስን መልበስ የምታዘወትር ባለሙያ ሴት ልብሷ የነካው ድንጋይ እንኳን ጥሩ መዓዛ አለው የሚል ሆኖ ጭስ የምትሞቅን ሴት የማሞገስ፣ የማድነቅ ይዘት ያለው ነው፡፡

እንዴት ነው በሉልኝ ጨኖ ድንጋዩን[27]

የቀሚሷ ዳር ዳር የነካካውን፡፡

በአርጎባዎች ዘንድ ጭስ እንዲሞቁ የሚፈቀድላቸው ለሰርጓ የምትዘጋጅ ልጃገረድና ያገባች ሴት ሲሆኑ ለጋብቻ ያልተዘጋጀች ወይም ያላገባች ልጃገረድ ጭስ አትሞቅም፡፡ ትዳር ያላት ሴት በትዳር የምትኖር በመሆኗ ባለ መልካም መዓዛ መሆኗ ባሏን ያስደስተዋል፤ ነገር ግን ያላገባች ልጃገረድ ጭስ መሞቋ በዙሪያዋ ያሉ ወንዶችን ፆታዊ ፍላጎት ይቀሰቅሳል ተብሎ ስለሚታሰብ አዝጋሮ በምድጃ ላይ በማድረግ ጐንበስ ብላ ፀጉሯን በግራና በቀኝ በኩል በማድረግ ታሞቃለች እንጂ ገላዋን ጭስ እንድትሞቅ አይፈቀድላትም (ወ/ሮ አይኔ ይማሙ፣ 12/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ሙሽራ ሰርጓ አንድ ወር ገደማ ሲቀረው ጭስ መሞቅ ትጀምራለች፡፡ ፀጉሯንና ገላዋን ቅቤ እየተቀባች ወይባ ትሞቃለች፤ ሞቃ ስትጨርስ በተቀቀለ የወይባ ቅጠል እየታሸች ገላዋን ትታጠባለች፤ ከዚያ በኋላ የተሞቀ ጐንደሬ ቀሚስ በመልበስ አዝጋሮና ሽታ ሞቃ ስታበቃ ጥሩ ጥሩ ምግብ ይቀርብላታል፡፡ ሙሽራ ጭስ መሞቋና በተቀቀለ ወይባ ቅጠል መታጠቧ ገላዋ ንፁህ እንዲሆን፣ እንዲለሰልስና እንዲያምር ያደርጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለሰውነቷና ለልብሷ ጥሩ መዓዛ ይሰጥላታል (ወ/ሮ አይኔ ይማሙ፣ 12/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ የጭስን ጥቅም በተመለከተ ወ/ሮ ሷቢራ ኡመር (26/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) "ዘመን አመጣሹ መኳኳያ ቀባ ቀባ ተደርጐ ለጊዜው ፏ ያደርጋል፡፡ የታጠበ ጊዜ ውልቅ ይላል፡፡ ጭሱ ግን እየበለጠ ነው የሚሄደው፡፡ ሰውነት

[27] ጨኖ በልዩ ወረዳው የሚገኝ አንድ ቀበሌ ነው፡፡ ጨኖ ድንጋዩን የተባለው በጨኖ የሚገኝን ድንጋይ ወይም የጨኖን ድንጋይ ለማለት ነው፡፡

ሁሉ እንደ መብራት ያበራል፤ ያጠራል፡፡ ጭሱ ደግሞ ወደ ውስጥ ይገባል፡፡ ሽታውም ጥሩ መዓዛ ይሰጣል፡፡ ልብስ ሁሉ ነው የሚሸተው" በማለት ገልፀዋል፡፡

ልብስ ማሞቅ፣ ሰርጉ ሰባት ቀን ገደማ ሲቀረው የሙሽራዋ ልብስ ታጥቦ ጥሩ መዓዛ እንዲኖረው ሁልጊዜ ማታ ማታ በአጐበር ላይ እየተደረገ ሽታ ይሞቃል፡፡ ከዚያ በኋላ ሽቶ እየተረጨበትና እየታጠፈ ለብቻው ይቀመጣል (ወ/ሮ አይኔ ይማሙ፣ 12/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ፀጉር መሰራት፣ የአርጐባ ሴቶች የፀጉር አሰራር ሁለት አይነት ነው፡፡ አንደኛው ያላገቡ ልጃገረዶች የሚሰሩት ባህላዊ የፀጉር አሰራር ሲሆን "ረፍረፎ" ይባላል፡፡ ሁለተኛው ያገባች ሴት የምትሰራው የፀጉር አሰራር ሲሆን "ስጥቂት" ይባላል፡፡ ረፍረፎ መሀሉ ከግንባር ጀምሮ ወደ ኋላ በሚሰራ ሁለት ረድፍ ሹሩባ ተደፍኖ ከግራና ከቀኝ ወደ ታች ሹሩባ የሚሰራ የፀጉር አሰራር ሲሆን ስጥቂት ግን መሀሉ እስከመጨረሻው ተከፍሎ ከግራና ከቀኝ እንደ ረፍረፎ ወደ ታች የሚሰራ የፀጉር አሰራር ነው፡፡ ያላገባች ልጃገረድና ያገባች ሴት የሚሰሩት የፀጉር አሰራር ዋነኛ ልዩነት የልጃገረዷ መሀሉ ተደፍኖ የሚሰራ መሆኑና ያገባች ሴት ግን መሀሉ ተከፍሎ የሚሰራ መሆኑ ነው (ወ/ሮ አይኔ ይማሙ፣ 12/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ለሰርጓ የምትዘጋጅ ልጃገረድ የምትሰራው ስጥቂት ነው፡፡ በሰርጉ ዋዜማ የፀጉር ስራ በደንብ የምትችል ሴት ተመርጣ ትመጣለች፡፡ ቡና ተፈልቶ ጀባ ከተባለ በኋላ ዱዓ ተደርጐ ሙሽራዋ ፀጉሯን ትሰራለች፡፡ ከዚያ በኋላ ቅቤ ትቀባና ፀጉሯ ጥሩ መዓዛ እንዲኖረው ማታ ፀጉሯን በአዝጋሮና በሽታ ያሞቋታል (ወ/ሮ አይኔ ይማሙ፣ 12/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

**ምግብ ማዘጋጀት፣**

ለእርድ የሚሆን ፍየል ቁጥሩ እንደ ደጋሹ ሰው አቅም ሆኖ ይዘጋጃል፡፡ ከገበያ የሚገዛ ከሆነ ይገዛል፣ ከቤት ፍየል የሚረባም ከሆነ ተመርጦ ይዘጋጃል (ወ/ሮ ሷቢራ ኡመር፣ 26/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የአብሽ ውሀ፣ ቀሪቦና እልበት ይዘጋጃሉ፡፡ የአብሽ ውሃና እልበት "ጥላ አይወጹም" ተብሎ ይታመናል፡፡ ጥላ አይወጹም ማለት ምግቦቹ የሚዘጋጁት ብዙ ሰው በሚገባ በሚወጣበት

ወይም በሚረማመድበት አካባቢ ከሆነ ይበላሻሉ ወይም ጥሩ አይሆኑም የሚል እምነት ነው፡፡ በዚህ እምነት ምክንያት ሁለቱ ምግቦች ሰዎች በብዛት በማይተላለፉበት ቦታ ይዘጋጃሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ምግቦቹ ይበላሻሉ በሚል ምክንያት "ንፁህ የሆነች" ሴት እንጂ የወር አበባ በምታይባቸው ቀናት የሆነች ሴት በዝግጅቱ ላይ አትሳተፍም (ወ/ሮ ሷቢራ ኡመር፣ 26/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ሰርጉ ሁለት ቀን ሲቀረው እንጀራ የሚጋገርበት ዱቄት ይቦካል፡፡ በማቡኪያው ቀን የጐረቤት ሴቶች ተሰብስበው ስራውን በመረዳዳት ያከናውኑታል፡፡ በሰርጉ ዋዜማ እንጀራው ይጋገራል፤ ሊጡ እየተቀነሰ ለየጐረቤቱ ይከፋፈልና ጐረቤት በየቤቱ እንጀራውን ጋግሮ ወደ ሰርጉ ቤት ያመጣል፡፡ ዳቦና አነባበሮም ይጋገራል፡፡ ከዚህ ውጭ የወጥ ስራ የሚከናወነው በሰርጉ ቀን ጠዋት ነው (ወ/ሮ ሷቢራ ኡመር፣ 26/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

**ዳስ መጣል፣**

በሰርጉ ዋዜማ ዳስ ይጣላል፡፡ ዳስ የሚጣለው እንደሚያስፈልገው የዳስ ስፋት አራት፣ ስድስት ወይም ከዚያ በላይ ቋሚዎች በመትከል፤ ከላይም አግድም ቋሚዎቹን የሚያያይዝና ወራጅ የሚሆን እንጨት ከቋሚዎቹ ጋር በልጥ እየታሰረ፤ ከዚያ በኋላ ከላይ የወይባ ቅጠል እየተረበረበ ነው፡፡ የወይባ ቅጠል የተመረጠው ቅጠሉ ሰፋፊና ጥላ የሚሰጥ በመሆኑ ነው፡፡ ዳሱ በሚዘጋጅ ጊዜ በሰፊው ተሰርቶ በማግስቱ ምግብ ለማዘጋጃነትና ማሳረፊያነት ካገለገለ በኋላ የተለያዩ ተጠሪ ቡድኖችን ማስተናገጃ እንዲሆን ክፍል ተበጅቶለት መቀመጫ ይዘጋጃል፤ ይህ ስራ የሚከናወነው ግን የሰርጉ ቀን ጠዋት ነው፡፡ (አቶ ኢብራሂም አወል፣ 11/7/2013፣ ጐዜ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ከወረዳው ከተማ ጋቺኔ ውጭ ያሉ የገጠር ቀበሌዎች በአብዛኛው ለእንግዳ ማስተናገጃና ለምግብ ማዘጋጃ ይህ አይነቱን ዳስ ሲጠቀሙና አልፎ አልፎ በተለይም እድር ያቋቋሙ አካባቢዎች ለእንግዳ ማስተናገጃ እንዲሆናቸው ዘመናዊ የሸራ ድንኳን ሲጠቀሙ ተመልክቻለሁ፡፡ በጋቺኔ ቀበሌ ግን የቅጠል ዳስ አልተመለከትኩም፡፡ በጋቺኔ ቀበሌ ለሰዎች ማስተናገጃ የሸራ ድንኳን የሚጣል ሲሆን ለምግብ ማዘጋጃ ደግሞ እንጨት በማቆምና ከላይ ኘላስቲክ በመወጠር ዳስ ይበጃል፡፡ ይህ ልዩነት የጋቺኔ ቀበሌ አካባቢ

ከከተማነቱ አንፃር ለዳስ መጣያ የሚሆን ቅጠል በበቂ ሁኔታ ባለመኖሩና ድንኳን የሚሰጥ እድር የተቋቋመ በመሆኑ ምክንያት የሆነ ይመስላል፡፡

ዳስ የሚጥሉ አቅምና እውቀት ያላቸው ወንድ ዘመዶችና ጐረቤቶች ሲሆኑ የሰርጉ ቤት አባወራ ወይም ታላቅ ወንድ ሰው የማስተባበርና የመስራት ሀላፊነት አለበት፡፡ በሙሽራው ቤት ዳስ የሚፈርሰው እንግዳው እንደተሸኘ ሲሆን በሙሽራዋ ቤተሰብ ቤት ግን የመልስ ስነ ስርዓት ከተጠናቀቀ በኋላ ነው (አቶ ኢብራሂም አወል፣ 11/7/2013፣ ጐዜ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

**የኸድር ስነ ስርዓት ማከናወን፣**

ኸድር አውሊያ ነው፡፡ ኸድር ሲሳይን የሚያስገኝ እንደሆነ ስለሚታመንበት ሰርግ ሲታሰብ ጋብቻውን እንዲባርክ በማስብ በሰርጉ ዋዜማ በስሙ የዋዜማ ስነ ስርዓት ይከናወናል፡፡ እርድ ተደርጐና ምግብ ተሰርቶ ዳስ ለመጣልና ለመጋገር የመጡ ጐረቤቶች ይጋበዙና ሰለዋት ተደርጐ ወደየቤታቸው ይሄዳሉ (አቶ አደም መሐመድ፣ 5/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በዚህ የሽግግር ጊዜ የመለየት መገለጫዎች የሚቀጥሉ ቢሆንም የሽግግር መገለጫ ባህርያት ጐልተው የሚወጡበት ነው፡፡ ይህ ጊዜ በዋናነት ቃል ታስሮ የተጋቢዎቹ ትጭጭት የሚደረግበት ወይም ተጋቢዎቹ እጮኛሞች የሚሆኑበት፤ ነገር ግን ጋብቻ የሚፈጽሙበትና በአንድ ላይ መኖር የሚጀምሩበት ቀን ያልደረሰ በመሆኑ ተጋቢዎቹ ቀደም ሲል ከነበራቸው ደረጃ ተለይተው ነገር ግን ባለመጋባታቸው የሚቀጥለውን ደረጃ ያላገኙበት ጊዜ ነው፡፡

በአርጐባዎች ዘንድ ይህ የሽግግር ጊዜ የነገር መፍጃ ስነ ስርዓት ተከውኖ ቃል የሚታሰርበት፣ የሰርግ ቀን የሚወሰንበት፣ ድግስ ተደግሶ ሽማግሌዎች የሚጋበዙበት፣ አግቢው ልጅ ለልጅቷ ቤተሰብ የሰርግ መደገሻ ገንዘብና ለልጅቷ ልብስ የሚሰጥበት ነው፡፡ ነገር ግን የታጨችው ልጅ አግቢው የሚልክላትን ልብስ ሰርግ ተደግሶ አብረው መኖር ከመጀመራቸው በፊት አትለብሰውም፡፡ ይህም ተጋቢዎቹ ይህ ነው ተብሎ በተለየ ደረጃ ላይ ባለመሆናቸውና ወደሚቀጥለው ደረጃ ያልተሸጋገሩ በመሆናቸው እጮኛዋ የላከላትን ልብስ መልበስ እንደ ነውር ስለሚታሰብ ነው፡፡

በዚህ ጊዜ እጮኛሞች ለሚቀጥለው ደረጃ የሚያበቃቸውን ዝግጅት ያደርጋሉ፤ ሴቷ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶችን ታበጃለች፣ የቤት አስተዳደርንና ሙያን ትማራለች፤ ወንዱ ደግሞ የወንድ ተብለው የተለዩ ስራዎችን ያለ ማንም እርዳታ መስራትን ይማራል፣ በትዳር የሚኖርበትን ጎጆ በቤተሰቡ መኖሪያ ግቢ ውስጥ ይቀልሳል፡፡

በዚህ ጊዜ እጮኛሞች እርስ በርስና አንዳቸው ከሌላቸው ቤተሰብ ጋር ያላቸው ግንኙነት እና ቤተሰቦቻቸው እርስ በርስ ያላቸው ግንኙነት በተለየ መንገድ የተቃኘ ይሆናል፡፡ እጮኛሞቹ የሚተፋፈሩበት፣ በመንገድ ቢገናኙ እንኳን እንዳላየ የሚተላለፉበትና አንዳቸው የሌላቸውን ቤተሰብ በተለየ መንገድ የሚፈሩበት ይሆናል፡፡ የቤተሰቦቻቸው ግንኙነትም የተለየ ይሆንና በቀደመው ጊዜ የማይተዋወቁ ከነበሩ በደስታና በሀዘን ጊዜ የሚገናኙበት፤ ዝምድና የነበራቸው ወይም ቀደም ሲል የጠነከረ ግንኙነት የነበራቸው ከሆነም ግንኙነታቸው የሚቆጠብበትና በዋና ዋና የደስታና የሀዘን ጊዜዎች ብቻ የሚገናኙበት ይሆናል፡፡

በዚህ ጊዜ የወንዱ ቤተሰብና አግቢው ልጅ ለሴቷ ቤተሰብና ለልጅቷ ስጦታ የሚሰጥ ሲሆን ይህም ቤተሰቡም ሆነ አግቢው ልጅ ለጋብቻው መጓጓታቸውን የሚገልፁበት ነው፡፡

### 6.4.4. መቀላቀል

የመቀላቀል ደረጃ ከሰርግ ስነ ስርዓት ክዋኔ ጀምሮ እስከ ጎጆ መውጫ ስነ ስርዓት ክዋኔ ማጠቃለያ ድረስ የሚቆይ ነው፡፡ የሰርግ፣ የባዷሼህ፣ የደመቅሁ፣ የመልስና የጎጆ መውጫ ስነ ስርዓቶች ክዋኔዎች የመቀላቀል ጊዜ መገለጫዎች ናቸው፡፡

#### 6.4.4.1 የሰርግ ስነ ስርዓት

ሰርግ በአርጎባዎች ዘንድ ማቀባይ ወይም መቅጠሪያ ይባላል፡፡ ማቀባይ ሙሽራዋን ማቀበያ፣ መስጫ ማለት ሲሆን በአብዛኛው ለመጀመሪያ ጋብቻ ለሚደረግ የሰርግ ስነ ስርዓት መጥሪያነት ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ መቅጠሪያ የሚለው ስያሜ ደግሞ እጅግም ላልታሰበበት አነስተኛ ሰርግ በተለይ ለሁለተኛ ጋብቻ ለሚደረግ የሰርግ ስነ ስርዓት መጥሪያነት ይውላል (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 4/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በመጀመሪያው ዓይነት የሰርግ ስነ ስርዓት ክዋኔ ላይ ነው፡፡

በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት የነበረው የጋብቻ ስነ ስርዓት ሙሽራዋ ከሰርጓ በኋላ አንድ አመት ለሚሆን ጊዜ በቤተሰቧ ቤት የምትቆይበት፤ ሙሽራው እህል፣ ፍየል፣ ማርና ቅቤ በመያዝ ከሰርጉ ቀን ጀምሮ ለአስር ቀናት ያህል ከሚዜና አጃቢዎቹ ጋር በአማቾቹ ቤት የሚከርምበት፤ ሙሽራው ሙሽራዋን ከወሰዳትም በኋላ ሙሽሮች በራሳቸው ጐጆ ኑሮ ሳይጀምሩ በሙሽራው ቤተሰብ ቤት አንድ አመት ለሚሆን ጊዜ የሚከርሙበትና ከዚያ በኋላ ጐጆ የሚወጡበት ነበር፡፡ ሙሽራው በአማቾቹ ቤት ከአጃቢዎቹ ጋር ለአምስት ቀን፤ ከሚዜዎቹ ጋር ደግሞ ለአስር ቀን ያህል የሚቆይበት ጊዜ አስርቲ ይባላል፡፡ ይህ አስርቲ ያለው የሰርግ ስነ ስርዓት በሀይማኖት አባቶች ውሳኔ እንዲቀር የተደረገ በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ ሙሽራው ከሚዜዎቹና ከአጃቢዎቹ ጋር በሙሽራዋ ቤተሰብ ቤት ለአስር ቀን መክረሙ ቀርቷል፤ ሙሽራው ሙሽራዋን በሰርጉ እለት ይወስዳል፤ ጥንዶቹ በሙሽራው ቤተሰብ ቤት ሳይቆዩ ወዲያው ኑሮ ይጀምራሉ (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 4/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ በመሆኑም የዚህ የጋብቻ ስነ ስርዓት ክዋኔ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 6.4.4.1.1. የሰርግ ስነ ስርዓት ክዋኔ[28]

የምግብ ዝግጅትና እንግዶችን የማስተናገጃ ቦታ የማዘጋጀት ስራ፣ የተጠሪዎች አለባበስና መስተንግዶ እንዲሁም የሀላፊነትና የመተጋገዝ ሁኔታ በሁለቱም ሙሽሮች ቤት በተመሳሳይ መንገድ የሚከወን ነው፡፡

**የምግብ ዝግጅት፣**

በሰርጉ ቀን ጠዋት በሰርጉ ቤት እርድ ተከናውኖ ወጥ ይሰራል፡፡ ይህን ስራ ለማከናወን የቅርብ ጐረቤቶችና ወዳጆች በጠዋት ወደ ሰርጉ ቤት ይሄዳሉ፡፡ ወንዶች ከወንድ የሰርጉ ቤት የቤተሰብ አባላት ጋር በመሆን እርድ ያከናውናሉ፤ ስጋውን ቆራርጠው ለሴቶች ያስረክባሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ሴቶቹ በተጣለው ዳስ ውስጥ ወጥ ይሰራሉ፡፡ ለሰርግ ስነ ስርዓት የሚዘጋጁ ዋና ምግቦች የዶሮ ወጥ፣ ቀይ ወጥ፣ ስቅስቆሽ፣ ዝልዝል ወይም ንፍር ስጋ፣ ወቃሊሞ፣ ቅቤና ማር፣ እልበት፣ እንጀራ፣ ዳቦና አነባበሮ ሲሆኑ መጠጦቹ ደግሞ የአብሽ ውሀና ቀሪቦ ናቸው (ወ/ሮ ሳሱየ አሊየ፣ 7/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

[28] በሁለቱም ሙሽሮች ቤተሰቦች ቤቶች



ፎቶግራፍ 18. ወቃሊሞ



ፎቶግራፍ 19. የተቀዳ ቅቤ

ቅቤና ማር የወግ ምግቦች ናቸው፡፡ ቅቤና ማር የቀረበለት ተጋባዥ ከቅቤውም ከማሩም ፈትፍቶ በልቶ እንዲጠግብ በማሰብ የሚቀርቡ ምግቦች ሳይሆኑ ጋባዥ ያለውን ማህበራዊ ደረጃና ለተጋባዥ ያለውን አክብሮት የሚገልጽባቸው ምግቦች ናቸው፡፡ እከሌ እንግዶቹን ቅቤና ማር ቀድቶ ጋበዘ መባሉ የጋባዡንና የተጋባዡን የማህበራዊ ደረጃ እርከንና የግብዣውንም ትልቅነት የሚያሳይ ነው፡፡ በሰርግ ቀን በሙሽሮች ቤተሰብ ቤት ሙሽራው ከሚዜዎቹና ከአጃቢዎቹ ጋር በሚቀርብበት ገበታ ላይ እነዚህ የወግ ምግቦች ከሌላው ተጠሪ ገበታ በተለየ በመጠናቸው በርከት ተደርገው ይቀርባሉ (ወ/ሮ ሳሱየ አሊየ፣ 7/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

## እንግዶችን የማስተናገጃ ቦታ ማዘጋጀት፣

በሰርጉ ቀን ጠዋት ወጥ ከተሰራ በኋላ አካባቢው ተፀድቶ ዳሱ ለእንግዶች ማረፊያ እንዲሆን ይዘጋጃል፡፡ በቅድሚያ ዳሱ ይከፋፈልና ከዚያ በኋላ መቀመጫ ይዘጋጃል፡፡ የሰርጉ ዋና ቤት ለእንግዶች ማስተናገጃ እንዲሆን በአማራጭነት ጥቅም ላይ ካልዋለ በስተቀር በሙሽራውም ሆነ በሙሽራዋ ቤት የሚጣለው ዳስ ተከፋፍሎ የተለያዩ የተጠሪ ቡድኖችን ማስተናገጃ ይሆናል (አቶ ፋንታዬ መሐመድ ኑር፣ 12/7/2013፣ ጐዜ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በሙሽራው ቤት ዳሱ አራት ቦታ የሚከፋፈል ወይም የሚቀየድ ሲሆን እነዚህ አራት ክፍሎች ሙሽራው ከሚዜዎቹና ከአጃቢዎቹ ጋር የሚያርፍበትና ገበታ የሚቀርብበት፣ ቤተሰብና ዘመድ የሆኑ ሴቶች የሚያርፉበትና የሚስተናገዱበት ክፍል እና ወንድና ሴት

ተጠሪዎች በተናጥል የሚያርፉባቸውና የሚስተናገዱባቸው ሁለት ክፍሎች ሲሆኑ ወንዶች ቁርዓን ስለሚቀሩ ወንድ የቤተሰቡ አባላትና ዘመዶች ከተጠሪ ወንዶች ጋር አንድ ላይ ይሆናሉ፡፡ በሙሽራዋ ቤት የሚዘጋጀው ዳስ ደግሞ ስድስት ክፍሎች እንዲኖሩት ይደረጋል፡፡ እነዚህ ስድስት ክፍሎች ኒካህ አሳሪ የሀይማኖት አባቶች፣ ሽማግሌዎችና የሙሽራዋ በእድሜ ታላላቅ የሆኑ ወንድ የቤተሰብ አባላት የሚያርፉበት፣ የሙሽራዋ የቅርብ የሆኑ ሴት ዘመዶችና ጐረቤቶች የሚያርፉበት፣ ሙሽራው ሲገባ ከሚዜና አጃቢዎቹ ጋር ሆኖ የሚስተናገድበት፣ ሙሽራዋ ከሚዜዎቿና አጃቢዎቿ ጋር የምትቆይበት፣ ወንድ ተጠሪዎች የሚስተናገዱበት ክፍልና ሴት ተጠሪዎች የሚስተናገዱበት ክፍል ናቸው (አቶ ፋንታዬ መሐመድ ኑር፣ 12/7/2013፣ ጐዜ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የተጣለው ዳስ ተከፋፍሎ ከተዘጋጀ በኋላ የእንግዶች መቀመጫ ይዘጋጃል፡፡ በዳስ ውስጥ መቀመጫ በሁለት መንገድ ይዘጋጃል፡፡ አንደኛው መቀመጫ ሙሽራው ከሚዜዎቹና ከአጃቢዎቹ ጋር በመሆን የሚያርፍበት ሲሆን ሁለተኛው የሰርጉ ታዳሚ የሚያርፍበት ነው፡፡ በሁለቱም ሙሽሮች ቤት ወንዱ ሙሽራ ከሚዜዎቹና ከአጃቢዎቹ ጋር በመሆን የሚቀርብበት ገበታ በወንዱ ሙሽራ ቤት የሙሽራ ገበታ የሚባል ሲሆን በሴቷ ሙሽራ ቤት ደግሞ የአማች ገበታ ይባላል፡፡ ይህ ገበታ በልዩ መንገድ የሚዘጋጅ በመሆኑ መቀመጫውም ከሌላው ታዳሚ በተለየ መንገድ ይዘጋጃል፡፡ ይህም ለሙሽራው፣ ለሚዜዎቹ፣ ለጥቂት አጃቢዎቹና ጋባዥ ለሆኑ የሙሽራዋ ቤተሰብ የቀደሙ ወንድ አማቾች መቀመጫው በግራና በቀኝ ፊት ለፊት ድንክ አልጋ ተደርጎ በመካከል ከመቃ የሚሰራ ረዥም ገበታ ተደርጎ ይዘጋጃል፡፡ ይህ ቦታ ደግሞ በመጠኑ ተከልሎ ከብዙሀኑ አጃቢ መቀመጫ እንዲለይ ይደረግና ለወንዱ ቀሪ አጃቢዎች በተመሳሳይ መንገድ ገበታ ይዘጋጃል፡፡ በተዘጋጀው ገበታ ላይ ምግብ የሚደረገው በሙሽራው ቤት ሙሽራው ሙሽራዋን ለማምጣት የመሄጃ ሰዓቱ ደርሶ ሙሽራው እስከ አጃቢዎቹ በቤተሰቡ ቤት ሲጋበዝ ሲሆን በሙሽራዋ ቤት ደግሞ የአማች መምጫ ሰዓት ሲደርስ ነው (አቶ ፋንታዬ መሐመድ ኑር፣ 12/7/2013፣ ጐዜ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡



ፎቶግራፍ 20. የሙሽራ/ አማች ገበታ

ሴትና ወንድ ለየብቻ ሆኖ መቀመጡ ሀይማኖታዊ መሰረት ያለው ሲሆን (*The Quran*, Al-Ahzab 33:53) ሌላው የማህበራዊ ደረጃ ጉዳይ ነው፡፡ የሀይማኖት አባቶችና ሽማግሌዎች፣ የሙሽራና የአማች ቦታዎች መለየታቸው ለእነዚህ ቡድኖች ከሚሰጥ ክብር ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የሀይማኖት አባቶችና ሽማግሌዎች ኒካሁን የሚያስሩና የተለየ ክብር የሚሰጣቸው በመሆኑ፣ ሙሽራ ተከባሪና ብርቅ በመሆኗ እና አማች ከሚሰጠው ክብር አንፃር ከሌላው ተጠሪ ጋር ተቀላቅሎ እንዲቀመጥ ስለማይፈለግ በየብቻ ቦታዎቻቸው ሆነው ይስተናገዳሉ፡፡ ሙሽራዋ እንደ ሙሽራው ሁሉ ሌሎች ሰዎች ባሉበት ቦታ ሄዳ አትደባለቅም፣ ሚዜዎቿና አጃቢዎቿ ሙሽራዋን በማልበስ፣ በማስዋብና በመዝፈን አብረዋት ይቆያሉ፡፡ ሁለተኛው የሌላው የሰርግ ታዳሚ መቀመጫ በመሬት ላይ የወይባ ቅጠል በመጐዝጐዝ የሚዘጋጅ ነው፡፡

**ተጠሪዎችና አስተናጋጆች፣**

ሴት ተጠሪዎች ጐንደሬ ቀሚስና ጉፍታ፣ ወንድ ተጠሪዎች ደግሞ ወንበርቲ ሱሪና ጥልቆሽ እንዲሁም ጥምጣም የሚለብሱ ሲሆን ስጦታ በመያዝ እንደየጥሪያቸው አይነት በተለያየ ሰዓት ወደ ሰርጉ ቤት ይሄዳሉ፡፡ ተጠሪዎች የሚሰጡት ስጦታ አብዛኛውን ጊዜ ለሰርግ ቤቱ አባወራና እማወራ የሚሰጥ ገንዘብ ሲሆን እንደቅርበታቸው ሁኔታ ለሙሽራ ልብስ ገዝተው ሊሰጡም ይችላሉ፡፡ ሰርጉ ቤት ይዘው የሄዱትን ስጦታ ወንዶች ለሰርጉ ቤት አባወራ፣ ሴቶች ደግሞ ለቤቱ እማወራ በመስጠት ሴቶች ለብቻ፣ ወንዶች ለብቻ በተዘጋጀላቸው ቦታ ላይ አረፍ አረፍ ይሉና ገበታ ይቀርብላቸዋል፡፡ ለተጠሪዎች ምግብ የሚቀርበው ከሳጠራ

በተሰራ ገበታ ሲሆን ገበታ አጣጣሉም እንጀራ እየታጠፈ ዙሪያውን ይደረግና ማባያዎች በጣባ ተደርገው በመሀል ይቀመጣሉ፡፡ ተጠሪዎች በአንድ ገበታ በቡድን እየሆኑ በክብ ተቀምጠው የሚመገቡ ሲሆን ሁሉም ተጠሪዎች እንደ አመጣጣቸው ገበታ ይቀርብላቸዋል፡፡ በሙሽራው ቤት ከምግብ ግብዣው በኋላ ወንድ ተጠሪዎች ቁርዓን እየቀሩ የሚቆዩ ሲሆን ተጠሪዎች እንደየተጠሩበት አግባብ ሙሽራ ይሸኛሉ፣ ይቀበላሉ ወይም ሸኝተው ይቀበላሉ፤ በሙሽራዋ ቤት ደግሞ ተጠሪዎች እንደጥሪያቸው ዓይነት በጉፍታ ስነ ስርዓት ላይ ይታደማሉ ወይም ሙሽራዋን ይሸኛሉ (ወ/ሮ ከድጃሺ በሽር፣ 5/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ወንድ ተስተናጋጆችን ወንዶች፣ ሴት ተስተናጋጆችን ደግሞ ሴቶች ያስተናግዳሉ፡፡ የማስተናገድ ስራውን በቅልጥፍናና ጉብዝናቸው የተመረጡ ሰዎች ያከናውኑታል፡፡ ምግብ በመስራት የታወቁ ባለሙያዎች፣ ዱዓ በማድረግ የታወቁ፣ በማስተባበር ስራ የታወቁ፣ ወዘተ እንዳሉ ሁሉ አስተናጋጆችም እንዲሁ ይመረጣሉ (ወ/ሮ ከድጃሺ በሽር፣ 5/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

***ሀላፊነትና መተጋገዝ፣***

በሰርግ ስነ ስርዓት ዝግጅት፣ በሰርጉ ቀንና ከሰርጉ በኋላም የሰርጉ ቤት አባወራና እማወራ የየራሳቸው ሀላፊነቶች አሉባቸው፡፡ አባወራው ዘመዶቹንና ጐረቤቶቹን በማስተባበር የቤቱን አጥር ያድሳል፣ ዳስ ይጥላል፣ የአማችና የተጠሪ ማረፊያዎችን ያዘጋጃል፣ የእርድ ስራውን ያከናውናል፣ በምግብ ዝግጅት ጊዜ የማገዶ እንጨትና ውሃ ያቀርባል፣ ወንድ ተስተናጋጆችን ያስተናግዳል፡፡ ከእነዚህ የጉልበት ስራ ሀላፊነቶች በተጨማሪ ከገበያ ተገዝቶ ለሚመጣው ነገር ሁሉ ገንዘብ በመስጠት እንዲገዛ ያደርጋል (አቶ ሙሳ አሕመድ፣ 18/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ እማወራዋ ደግሞ ከሚረዷት ሰዎች ጋር በመሆን ምግቡን የማዘጋጀት ትልቅ ሀላፊነት አለባት፡፡ የሴቷን ሀላፊነት በተመለከተ ወ/ሮ ሳሱየ አሊየ (7/7/2013 ዓ.ም.፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> *አንድ ጊዜ ብቻ አብልቶ መቀመጥ የለም፡፡ ቁርስም፣ ምሳም፣ እራትም ይዘጋጃል፡፡ ማቡካት ነው፣ ወጥ መስራት ነው፣ ማብላት ማጠጣት ነው፡፡ ሰሞኑን ሁሉ እንግዳ ይመጣል፤ ሶስት አራት ቀን ሲቀረው ከሩቅ የሚመጣ ዘመድ አለ፡፡ ቀረብ ቀረብ*

የሚል ደግሞ ተያያዘልሽ? ተሳካልሽ? ብሎ የሚጠይቅ አለ፤ እቃ ይዞ የሚመጣ አለ፡፡ ለሱ ሁሉ ገበታ እየተቀረበ ይጋበዛል፡፡ የእናት ተአቡ ብዙ ነው፡፡

ዘመዶችና ጐረቤቶችም ሰርገኛውን ቤተሰብ በተለያየ መንገድ ያግዛሉ፡፡ የሚደረገው እገዛ የዓይነት፣ የገንዘብ፣ የሀሳብና የጉልበት እገዛ ነው፡፡ ለሰርጉ ተጠርተው ከሩቅም ሆነ ከቅርብ የሚመጡ ዘመዶች ከሰርጉ ቀን ቀድመው በሰርጉ ቤት የሚገኙ ሲሆን ሰርጉ ካበቃ በኋላም ወደየቤታቸው የሚመለሱት ከቀናት በኋላ ነው፡፡ ወደ ሰርጉ ቤት ሲሄዱ እንደየአቅማቸው እህል ጭነው፣ ፍየል ስበው፣ ማርና ቅቤ፣ ልብስ፣ ወዘተ ይዘው ይሄዳሉ፤ ዝምድናቸው የሙሽራዋ ከሆነም ሙሽራዋ ወደ ባሏ ስትሄድ ይዛቸው የምትሄዳቸውን ቁሳቁሶች በስጦታ መልክ ይዘው ይሄዳሉ፡፡ በሰርጉ ቤት ቆይታቸውም ሰርገኛውን ቤተሰብ በሀሳብ ያግዛሉ፡፡ ከዚያም ባለፈ ወንዶች ዳስ በመጣል፣ ቤትና አጥር በማስተካከል፣ እርድ በማከናወን፣ በማስተናገድ፣ ወዘተ፤ ሴቶች ደግሞ በአብዛኛው በምግብ ዝግጅቱና በመስተንግዶው ላይ ተሳትፎ በማድረግ እገዛ ያደርጋሉ (አቶ ሙሳ አሕመድ፣ 18/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ጐረቤቶችም በተለያየ መልክ እገዛ ያደርጋሉ፡፡ በሰርጉ ቀን ለሙሽራ ልብስ ገዝተው ይሰጣሉ፤ ጉርብትናቸው ለሙሽራዋ ከሆነ ሙሽሪት ይዛው የምትሄደውን የቤት ቁሳቁስ በስጦታ መልክ ይወስዳሉ፤ የገንዘብ ስጦታ ይሰጣሉ፡፡ በሀሳብ ደረጃም ሰርጉ ከታሰበ ጊዜ ጀምሮ እንዴት ሆነላችሁ? እያሉ፣ ከሰርጉ በኋላም እንግዳ በሰላም ተሸኘላችሁ ወይ? እያሉ ያወያያሉ፡፡ የጉልበት ስራውን በተመለከተም በአብዛኛው ሰርገኛው ቤተሰብ እንዲህ አድርጉ ብሎ አያዝዝም፤ ጐረቤቶች የሚሰራውን ስራ በቅርበት ሆነው በመከታተል እራሳቸው አውቀው ይሰራሉ (አቶ ሙሳ አሕመድ፣ 18/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

#### 6.4.4.1.2. የሰርግ ስነ ስርዓት ክዋኔ በሙሽራው ቤተሰብ ቤት

ሙሽራ እጀ ጠባብ፣ ወንበርቲ ሱሪና ጥምጣም ያደርግና የታጠፈ ጋቢ ትከሻው ላይ ጣል ያደርጋል፡፡ የሰርጉ ቀን በሙሽራው ቤተሰብ ቤት ዝግጅቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ሙሽራው፣ ሚዜዎች፣ አጃቢዎች፣ የሙሽራው ቤተሰብና ቀድመው ለሰርጉ የመጡ ወዳጅ ዘመዶች ቁርስ ይበላሉ፡፡ ለሰርጉ ስነ ስርዓት ቀድመው ከሩቅ ቦታ የሚመጡ ወዳጅና ዘመዶች

በሰርጉ ሰሞን የሚከርሙና ከሰርጉ በኋላም ዳስ አፍርሰው የሚሄዱ በመሆኑ በሰርጉ ቤት በቁርስ፣ በምሳና በእራት ጊዜ በአግባቡ ይስተናገዳሉ፡፡ አንደኛ ሚዜ ደግሶ የማብላት ሀላፊነት ያለበት በመሆኑ ምሳ ሲደርስ ሙሽራውና የተወሰኑ አጃቢዎቹ በሚዜው ቤት ምሳ ይጋበዛሉ፡፡ ሙሽራው ከሚዜና አጃቢዎቹ ጋር ሚዜው ቤት ምሳ በልተው እንደተመለሱ ቡና ተፈልቶ የተዘጋጀውን ጥሎሽ ለባልቴቶች ያሳያሉ፡፡ ዱዓ ተደርጐ ቡናው ተጠጥቶ የታየው ጥሎሽ ተመልሶ በሻንጣ ይገባል፡፡ ሙሽራው ወደ ሙሽሪት የሚሄድበት ሰዓት ሲደርስ የሙሽራው ቤተሰብ መሸኛ ያበላል (አቶ አሕመድ መሐመድ፣ 10/7/2013፣ ጐዜ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ሙሽራው ሙሽሪትን ለማምጣት ጉዞ የሚጀምርበት ሰዓት ከቀትር በኋላ ሲሆን የሙሽራዋ ቤት ሩቅ ከሆነ ከምሳ ሰዓት በኋላ ብዙም ሳይቆይ ይነሳል፤ ቅርብ ከሆነ ግን ወደ ጀምበር መጥለቂያ አቅራቢያ ይነሳል፡፡ ሙሽራው የሚሄድበት ሰዓት ሲደርስ ጉዞ ከመጀመሩ በፊት ቤተሰቡን ዘይሮ ዱዓ ይደረግለታል (አቶ አሕመድ መሐመድ፣ 10/7/2013፣ ጐዜ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ምልከታ ባደረግሁበት የሰርግ ስነ ስርዓት ላይ ሙሽራው አቶ አህመድ አቡበከር ቤተሰቡን ሲዘይር አያቱ ወ/ሮ ፋጡማ ኢብራሂም ዱዓ አድርገውለታል (9/5/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡ ዱዓው ተጋቢዎቹ እንዲዋደዱ፣ ጥሩ ኑሮ እንዲኖራቸው፣ ልጆች እየወለዱና ሀብት እያፈሩ የሚኖሩ እንዲሆኑ፣ የሰርግ ስነ ስርዓቱ በሰላም እንዲጠናቀቅ፣ ሙሽራውና ሚዜዎቹ ፍቅራቸው እንዲጠብቅ የተደረገ ነው፡፡

ሙሽራው ሙሽሪትን ለማምጣት ሲነሳ የሚያጅቡት በዋናነት ሚዜዎቹና አጃቢዎቹ ሲሆኑ የሙሽራው ተወካይ በመሆን ኒካሁን የሚያስር ሰው የሀይማኖት ትምህርት ያለው መሆን ስላለበት ከቤተሰቡ መካከል የሀይማኖት እውቀት ያለው ሰው አብሯቸው ይሄዳል፡፡ ይህ ሰው ኒካሁን ከማሰር ሀላፊነት በተጨማሪ አጃቢዎችን ያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል፡፡ ከቤተሰብ፣ ከዘመድና ወዳጅ የሀይማኖት ትምህርት ያለው ሰው ከሌለ ግን ቃዲ አብሯቸው ይሄዳል፡፡ ቃዲ የእስልምና ሀይማኖት ስነ ስርዓቶችን ከማስፈፀም በተጨማሪ በቁርዓን መንፈሳዊ መጽሐፍ በተደነገገው መሰረት የጋብቻ ውል የሚያስፈጽም፣ አባት ሲሞት ሀብቱን ለልጆቹ የሚያከፋፍል፣ ማናቸውንም ወንጀል ነክ ያልሆኑ ጉዳዮችን በሸሪያ ህግ መሰረት በዳኝነት የሚያይና ውሳኔ የሚሰጥ የሀይማኖት ትምህርት አዋቂ ሰው ነው፡፡

ከነውር የሚቆጠር በመሆኑ የሙሽራው ሴት የቤተሰብ አባላትም ሆኑ ዘመዶች ሙሽራውን አጅበው አይሄዱም (አቶ አሕመድ መሐመድ፣ 10/7/2013፣ ጉዜ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የአጃቢዎችን ቁጥር በተመለከተ ቀደም ባለው ጊዜ የሙሽራዋ ቤተሰብ የመጣውን የወንድ አጃቢ በሙሉ ተቀብሎ ያስተናግድ ነበር፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ በኑሮ ውድነት ምክንያት በሙሽሮቹ ቤተሰቦች መካከል ባለ ሰው አማካይነት የአጃቢዎችን ቁጥር በመወሰን ይህን ያህል ሆነው ይምጡ የሚል መልዕክት ማስተላለፍ ተለምዷል፡፡ ስለዚህ ሙሽራውን ማጀብ የፈለገ በመንገድ ያጅብና ሙሽራዋ ቤት ሲደረስ አጃቢዎች ተመርጠው ወይም የሚገቡ አጃቢዎች ስማቸው ተመዝግቦ ስማቸው እየተጠራ የተወሰኑ አጃቢዎች ብቻ እንዲገቡና ሌሎቹ እዚያ እንዲቀሩ የማድረጉ ነገር ተለምዷል፡፡ ሙሽራው ሙሽሪትን ይዞ ሲወጣ ደግሞ የቀሩት አጃቢዎች ጠብቀው አጅበው ይመልሱታል (አቶ አሕመድ መሐመድ፣ 10/7/2013፣ ጉዜ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ምልከታ ባደረግሁበት የሰርግ ስነ ስርዓት ላይ ሙሽራውን ለማጀብ በርካታ ወጣቶች በመነሳታቸው ሙሽራውና የሙሽራው ሁለት ዘመዶች አጃቢዎች ቁጥራቸውን እንዲቀንሱ ሲለምኑ፤ የሙሽራው አባት ደግሞ "አባትየው አርባ ሆኖ ይምጣ ነው ያለኝ፣ እባካችሁ ከዚያ በላይ አትሁኑ እሱንም አታሳዝኑት፡፡ እዚህ ሁሉንም አሟልቻለሁ፣ ሁሉንም አቅርቤያለሁ፡፡ ሁሉም አለ፡፡ እባካችሁ ወንድማችሁንም አታሳዝኑት?!" በማለት አስተዛዝነው ሲለምኑ ተመልክቻለሁ፡፡ ይህም በብዙዎቹ አጃቢዎች ዘንድ ቅሬታን የፈጠረና ጉምጉምታን ያስነሳ ቢሆንም ተከትዬ በሄድኩበት የሙሽራዋ ቤት በቁጥር በውል ያልተለዩ ሰዎች ሰርጉ ቤት አለመግባታቸውንና ሙሽራው ሲመለስ አጅበውት መመለሳቸውን ተመልክቻለሁ (9/5/2013፣ ጋቼኔ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

#### 6.4.4.1.3. የሰርግ ስነ ስርዓት ክዋኔ በሙሽራዋ ቤተሰብ ቤት

ከዚህ በታች በሰርጉ ቀን በሙሽራዋ ቤተሰብ ቤት ከጠዋት ጀምሮ ሙሽራው ገብቶ ሙሽራዋን ይዞ እስኪወጣ ድረስ ያለው የሰርግ ስነ ስርዓት ክዋኔ ይቀርባል፡፡

#### ሀ. የሙሽራዋ፣ የሚዜዎቿና የአጃቢዎቿ የጋራ ቆይታ

ሙሽራዋ ጐንደሬ ቀሚስ የሚባለውን የብሄረሰቡን ባህላዊ ልብስና ጉፍታ ታደርጋለች፤ በጭልጭሌ፣ በላዚም፣ በእጅ ካቴና፣ በአልቦና በእግር ጣት ቀለበት ታጌጣለች፡፡ ሙሽራዋ

ከሚዜዎቿና አጃቢዎቿ ጋር ለብቻ በተዘጋጀላቸው ቦታ ይሆናሉ፡፡ ምሳ ሰዓት ሲደርስ በዋና ሚዜዋ ቤት በመሄድ ምሳ ይበሉና ይመለሳሉ፡፡ ከዚያ በኋላ የሙሽራዋ ሚዜዎችና አጃቢዎች ኒካህ ሲታሰር፣ ሙሽራው ሲገባና ሲጋበዝ ሁሉ የተለያዩ ዘፈኖችን እየዘፈኑ ይጫወታሉ (ወ/ት ከድጃ አሕመድ፣ 25/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡



ፎቶግራፍ 21. ላዚም፣ ጭልጭሌ፣ የእጅ ካቴና፣ የእግር ጣት ቀለበት

የሚከተለው ምልከታ ባደረግሁባቸው የሰርግ ስነ ስርዓቶች ላይ ለተዘፈኑ የሰርግ ዘፈን ግጥሞች ማሳያ እንዲሆን የተመረጠ ነው፡፡

| <u>አውራጅ</u> | <u>ተቀባዮች</u> |
|---|---|
| ኧረ ነይ እቴ ኧረ ነይ | ኧረ ነይ እቴ ኧረ ነይ |
| ኧረ ነይ ቶሎ ነይ | ኧረ ነይ ቶሎ ነይ |
| የድንጋይ ላይ ንፍሮ | ኧኸ |
| አይበስል አይከስል | ኧኸ |
| ምነው ሰዉ ሁሉ | ኧኸ |
| ፈቲያን [የሙሽራዋ ስም] አይመስል | ኧኸ |
| ኧረ ነይ እቴ ኧረ ነይ | ኧረ ነይ እቴ ኧረ ነይ |

(3/5/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

ይህ የሰርግ ዘፈን ግጥም በዋናነት ሙሽራዋ የተሞገሰችበት ነው፡፡ በግጥሙ ለመመልከት እንደሚቻለው የሙሽራዋ ስም እየተነሳና ምነው ሰው ሁሉ እርሷን አይመስል እየተባለ ሙሽራዋ ከሌሎች ሰዎች የተለየ ማንነት ያላት መሆኑ ተገልፇል፡፡ ሙሽራዋ የሚመስላት የለም በሚለው ሀሳብ ውስጥ ደግሞ ቁልፍ የሆነው ጉዳይ መምሰል ነው፡፡ መምሰል በብዙ ሊሆን ይችላል፡፡ መምሰል በመልክ፣ በቁመና፣ በአጠቃላይ በቁንጅና ወይም በላይ ውበት ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህ እልፍ ሲልም መምሰል በባህርይ፣ በትህትና፣ በሰው አክባሪነት፣ በእውቀት፣ በሙያ፣ ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡ በዘፈን ግጥሙ ላይ ሙሽራዋ የሚመስላት ጠፋ ሲባልም በእነዚህ ሁሉ መሳይ የሌላት፣ የተሻለች፣ የበለጠች መሆኗ እየተመሰከረና ሙሽራዋ እየተሞገሰች ነው፡፡ በምልከታ የተሰሙ የሰርግ ዘፈን ግጥሞች መልዕክት የተላለፈባቸው ቢሆኑም ሰርግን ማድመቂያና መዝናኛም ናቸው፡፡

## ለ. የጉፍታ መጫን ስነ ስርዓት

ጉፍታ በደማቅ ክሮች የተጠለፈ ሻሽ ሲሆን አንዲት ሴት ጉፍታ ማድረጓ ያገባች ሴት የመሆኗ ማሳያ ምልክት ነው፡፡ ጉፍታ የሚደረገው ወይም የሚጫነው በሰርጉ ቀን ሙሽራው ከመምጣቱ በፊት ነው፡፡ ጉፍታ የሚጫንላት ሙሽራ ሴት የቤተሰቧ አባላትና ሌሎች በእድሜ የገፉ ሴት ጐረቤቶችና ዘመዶች በሚቀመጡበት የብቻ ክፍል ወይም ዳስ በመሄድ የጉፍታ ስነ ስርዓቱ ይከናወንላታል፡፡ ጉፍታውን የምትጭንላት ሴት አግብታ ያልፈታች፣ በአንድ ትዳር ለረዥም ጊዜ የቆየችና ብዙ የወለደች ሴት ተመርጣ ነው (ወ/ሮ አይኔ ይማሙ፣ 12/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ይህም ትዕምርታዊ ድርጊት ሲሆን ሙሽራዋ የጉፍታ ጫኝዋ ሴትን ትዳር የመሰለ ትዳር እንዲገጥማት በመመኘት ለማምሰል የሚደረግ ነው፡፡

የጉፍታ መጫን ስነ ስርዓት ሲከናወን መጀመሪያ ስነ ስርዓቱን እንዲታደሙ የተጠሩ ባልቴቶች ባሉበት ክፍል ቡና ተፈልቶ ይቀርባል፣ ድፎ ዳቦና የማሽላ ቆሎም ይቀርባል፡፡ ሙሽራዋ እንደተሸፈነች ከሚዜና አጃቢዎቿ ጋር በመሆን ወደ ባልቴቶቹ ሄዳ ታጅባ ትቀመጥና ጉፍታው ይጫንላታል፡፡ ጉፍታው ሲጫን ከሙሽራዋ በላይ ነጠላ ተወጥሮና ዙሪያው ተይዞ ሙሽራዋ ከተሸፈነች በኋላ ጉፍታ የምትጭነው ሴት ጉፍታውን በሙሽራዋ ራስ ላይ ሁለት ጊዜ እንደማሰር አድርጋ በማውለቅ በሶስተኛው አስቀምጣ ትተወውና ሙሽራዋን ነጠላ ታለብሳታለች፡፡ ጉፍታው እየተጫነ የተሰበሰቡ ሴቶች እያጨበጨቡ ሶስት ጊዜ "አጢሾ አጢሾ አጢሾ…"፣ "አጢሾ አጢሾ አጢሾ…"፣ "አጢሾ አጢሾ አጢሾ…"

ይላሉ፡፡ የሙሽራዋ ወንድ የቤተሰብ አባላት ወይም ዘመዶች ጥይት ይተኩሳሉ፡፡ ዱዓ ከተደረገ በኋላ ዳቦው ተቆርሶ ከቆሎው ጋር ለሁሉም ሰው ይታደልና ቡናው ይጠጣል (ወ/ሮ አይኔ ይማሙ፣ 12/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ በአርጐባዎች ዘንድ ነገር በሶስት ይፀናል ተብሎ ስለሚታመንና የሙሽራዋ ጉፍታ የትዳሯ ምልክት በመሆኑ ሶስት ጊዜ መደረጉ ትዳሯ እንዲፀና የማምሰል ድርጊት ነው፡፡



ፎቶግራፍ 22. ጉፍታ



ፎቶግራፍ 23. ጉፍታ ሲጫን

የሚከተለው ዱዓ ምልከታ ባደረግሁበት የወ/ት ሩቅያ መሐመድ የጉፍታ ስነ ስርዓት ላይ በወ/ሮ ብርቄ መሪነትና በተሰበሰቡ ሴቶች ተቀባይነት የተደረገ ነው (23/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

| ዱዓ አድራጊ | ተቀባዮች |
|---|---|
| ቢስሚላሂ ራህማን ራሂም | አሜን |
| ሀጃዋን አላህ ያውጣው | ” |
| ሙራዷን አላህ ይሙላው | ” |
| አማን በአማን አላህ ይበለን | ” |
| ንግግራችንን ጣፋጭ አላህ ያርገው | ” |
| መገናኘታችንን ለኸይር አላህ ያርገው | ” |
| ለመሻር አላህ ያርገው | ” |

ልጃገረዱ የሚዳር አላህ ያርገው ”

የወንድ ልጅ እናት አላህ ያርጋት ”

ሹሙም በወንበሩ አላህ ያኑረው ”

ክርስቲያን በታቦቱ እስላም በመስጊዱ መርሀባ አላህ ይበለን ”

አላህ ይውደደን “

ኣ'ሏሁ መሰሊ ወሰሊም አላ ሰይድና መሐመድ ወአላ አሊ ሰይድና መሐመድ

በዚህ ዱዓ የተነሱ አራት አንኳር ሀሳቦችን ማንሳት ይቻላል፡፡ አንደኛው ጉዳይ ለሙሽራዋና ለመሰል ልጃገረዶች የተደረገ ምኞት ነው፡፡ “ሀጃዋን አላህ ያውጣው”፣ “ሙራዷን አላህ ይሙላው” እና “መገናኘታችንን ለኸይር አላህ ያርገው” የሚሉ የዱዓ ክፍሎች ሙሽራዋ በጐ እንዲሆንላት፣ መልካም እንዲገጥማት፣ የተደረገው የጉፍታ ስነ ስርዓት ጥሩ ነገርን የሚያስከትል እንዲሆን በመመኘት የተደረጉ ናቸው፡፡ “ልጃገረዱ የሚዳር አላህ ያርገው” የሚለው ዱዓም የሙሽራዋ ዕድል ለሌሎቹም ልጃገረዶች እንዲገጥም በመመኘት የተደረገ ሲሆን ማህበረሰቡ ለጋብቻ የሚሰጠውን ትልቅ ቦታ የሚያሳይ ነው፡፡ ሁለተኛው ጉዳይ “ሹሙም በወንበሩ አላህ ያኑረው” በሚለው የዱዓ ክፍል የተገለፀ ነው፡፡ በእስልምና ሀይማኖት አስተምህሮ መሰረት መሪ የሚሾመው በአላህ ምርጫ እንደሆነ ይታመናል (*The Quran,* Al-Baqara 2:247)፡፡ ይህ በመሆኑ ደግሞ በሹመት ላይ ያለ ሰው በሹመቱ እንዲረጋ ይፈለጋል፡፡ በዱዓው የታየው ምኞትም የቁርዓን ቃልን መነሻ ያደረገና ሹመት እንዲፀና የተደረገ ነው፡፡ ሶስተኛው ጉዳይ “ክርስቲያን በታቦቱ እስላም በመስጊዱ መርሀባ አላህ ይበለን” በሚለው የዱዓ ክፍል የተገለፀ ሲሆን በብሄረሰቡ አባላት ዘንድ የሀይማኖት ልዩነት አብሮ መኖርን እና መከባበርን ያላፋለሰ መሆኑን፣ የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ የሆነው አርጐባ ለክርስትና ሀይማኖት ተከታዮች መልካም መመኘቱን የሚያሳይ ነው፡፡ የመጨረሻው የብሄረሰቡ የፆታ ምርጫ ጉዳይ ሲሆን “የወንድ ልጅ እናት አላህ ያርጋት” በሚለው የዱዓ ክፍል ወንድ ልጅ እንዲወለድ ዱዓ መደረጉን መመልከት ይቻላል፡፡ ከዱዓ በኋላ ዝኪር ተደርጐ ስነ ስርዓቱ ይጠናቀቃል፡፡ በጉፍታ መጫን ስነ ስርዓት ላይ የሚከወኑ ዝኪሮች በአምሮት ስነ ስርዓት ላይ የሚከወኑ ዝኪሮች ናቸው፡፡

የሙሽራው መምጫ ሰዓት ሲቃረብ በተዘጋጀው ገበታ ላይ የተዘጋጀው ምግብ ይደረደራል፡፡ እንጀራው እየታጠፈ ከዳርና ከዳር ይጣልና በመካከል ማባያው በጣባ ተደርጎ ይደረደራል፤ ዝልዝል ስጋው በእንጀራው ላይ እየተደረገ ስጋውን መቁረጫ ቢላዋም አጠገቡ ይደረጋል፡፡ ከዚያ በኋላ ከላይ መቃ ጣል ጣል ተደርጎበት በነጠላ ጨርቅ ሙሉ በሙሉ ይሸፈናል፡፡ ገበታውን የሚያዘጋጁ ወንድ አስተናጋጆች ሲሆኑ ሙሽራው ከሚዜዎቹና ከአጀቢዎቹ ጋር ገብቶ ቦታውን ሲይዝ ምግቡ የተሸፈነበትን ጨርቅ በመግለጥ የሚጋብዙ ገበታ ከፋች ተብለው የተለዩ ሽማግሌዎች ናቸው (አቶ ታቢቶ መሐመድ፣ 5/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ሙሽራው ሙሽራዋ ቤት አቅራቢያ ሲደርስ ወካዩን ማለትም እርሱን ወክሎ ኒካሁን የሚያስረውን ሰው፣ ጥሎሽ የሚያሳይ ሚዜውን እና እንደ አስፈላጊነቱ ሌላ አንድ ወይም ሁለት ሰው ጨምሮ ወደ ሰርጉ ቤት በመላክ ከአጀቢዎቹ ጋር እዚያው አካባቢ ይቆያል፡፡ የተላኩ ሰዎች በቀጥታ ኒካሁን ለማሰር በአንድ ቤት ተሰብስበው ወደሚጠብቋቸው የሙሽራዋ ተወካይ፣ የሀይማኖት አባቶችና ሽማግሌዎች ዘንድ ይሄዳሉ፡፡ የተላኩ ሰዎች እንደደረሱ ቡና ቀርቦ ዱዓ ይደረጋል፡፡ የሙሽራው ተወካይ ዱዓ በሚያደርጉ ሽማግሌዎች ፊት በመቆም "አሜን" እያለ ምርቃቱን ይቀበላል፡፡ ከዚያ በኋላ ዳቦው ተቆርሶና ታድሎ ቡናው ከተጠጣ በኋላ ኒካህ ወደማሰር ስነ ስርዓት ይገባል (አቶ ታቢቶ መሐመድ፣ 5/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

### ሐ. የኒካህ ማሰር ስነ ስርዓት

ኒካህ የቃል[29] ማሰሪያ ስነ ስርዓት ሲሆን የሚከወነው በሰርጉ ቀን ነው፡፡ ሼህ ጧሂር ኑሬ (22/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) እንደገለፁት ግን አጋጣሚ ሆኖ ሰርጉ ገድ የላቸውም በሚባሉ ወቅቶች ላይ ከወደቀ ኒካሁን በማስቀደም ሰርጉ በተቀጠረው ቀን ይደረጋል፡፡

---

[29]የወረዳው የሼሪያ ፍ/ቤት ከ1990 ዓ.ም. ጀምሮ የጋብቻ የምስክር ወረቀት እየሰጠ ይገኛል፡፡ የምስክር ወረቀቱ በሁለት ቋንቋዎች ማለትም በአማርኛና በአረብኛ የተዘጋጀ ሲሆን የተጋቢዎች ፎቶግራፍ፣ የተጋቢዎች ስምና አድራሻ፣ የወኪልና የምስክሮች ስምና አድራሻ፣ ተጋቢዎቹ የተስማሙበት የመኸር መጠን፣ የተጋቡበት ቀን እና የቃዲ ስም እንዲሰፍርበት ሆኖ የተዘጋጀ ነው፡፡ ከጋብቻ ቀን በኋላ ተጋቢዎቹ ሼሪያ ፍ/ቤት በመሄድ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ይዘጋጅላቸውና ይወስዳሉ፡፡

ኒካህ የሚታሰረው በተጋቢዎቹ ተወካዮች በኩል ሲሆን ተወካዮቹ የሀይማኖት እውቀት እንዲኖራቸው ይጠበቃል፡፡ በሁለቱም ተጋቢዎች በኩል ተወካዮች ሆነው የሚቀርቡ ሰዎች የሙሽሮቹ አባቶች ወይም በአባት በኩል ያሉ ወንድ ዘመዶች ማለትም አጐቶች፣ ወንድሞች፣ የአጐት ወይም የአክስት ልጆች ወይም ሌሎች የቤተሰብ አባላት ሊሆኑ የሚችሉ ቢሆኑም ሀይማኖታዊ እውቀት ከሌላቸው ግን ቃዲ ይወክላሉ፡፡ በሙሽራዋ በኩል ያለ ተወካይ ውክልናውን ለቃዲ ሲያስተላልፍ ቃዲውን "ልጄን፣ እህቴን፣ ወዘተ እከሊትን በዚህ ያህል መኸሯ [የመኸሩ መጠን ተጠቅሶ] እንድታጋባልኝ ወከልኩህ" በማለት ያስተላልፋል፡፡ ቃዲውም "መወከልህን ተቀበልኩ" በማለት ውክልናውን ይቀበላል፡፡ ሙሽራው ለተወካዩ ውክልና የሚሰጠው "እከሊትን የእከሌን ልጅ ኒካህ ልትቀበልልኝ ወከልኩህ" በማለት ሲሆን ተወካዩም "ተቀበልኩ" በማለት ውክልናውን ይቀበላል (ሼህ ጧሂር ኑሬ፣ 22/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በሰርጉ ቀን የሙሽራዋ ተወካይ ሙሽራው ከመምጣቱ በፊት ተዘጋጅቶ የሚጠብቅ ሲሆን ከተወካዩ በተጨማሪ ሶስት ሸሪያን የሚያውቁ የሀይማኖት አባቶች እንዲገኙ ይደረጋል፡፡ እነዚህ ሰዎች ኒካሁ ለመታሰሩ ምስክር የሚሆኑና ተወካዮች ኒካሁን ሲያስሩ ከተሳሳቱ ስህተቱን የሚያርሙ ወይም የሚመልሱ፣ ሳይጠቀስ የተዘለለ ነገር ካለ እንዲሟላ የሚያደርጉ፣ ወዘተ ናቸው (ሼህ ጧሂር ኑሬ፣ 22/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ኒካህ የሚታሰረው መጀመሪያ በሙሽራዋ በኩል ሲጠብቁ የነበሩ ሽማግሌዎች የወንዱ ተወካይ ማን እንደሆነ ይጠይቃሉ፡፡ ተወካዩም "እኔ ነኝ" ብሎ ይቀርባል፡፡ የሙሽራዋና የሙሽራው ተወካዮች ፊት ለፊት እየተያዩ ይቆሙና የሙሽራዋ ተወካይ የቤተሰቧ አባል የሆነ ሰው ከሆነ "ልጄን፣ እህቴን፣ ወዘተ እከሊትን፣ የእከሌን ልጅ ባልከው መኸር [ወይም የመኸሩ መጠን ተጠቅሶ] ለወኪልህ ለእከሌ፣ ለእከሌ ልጅ አጋባሁ" ይላል፡፡ የሙሽራዋ ወኪል ሶስተኛ ሰው ከሆነ ተወካዩ ሰው "በውክልናዬ መሰረት እከሊትን፣ የእከሌን ልጅ ባልከው መኸር [ወይም የመኸሩ መጠን ተጠቅሶ] ለወኪልህ ለእከሌ፣ ለእከሌ ልጅ አጋባሁ" ይላል፡፡ ተወካዩ የስም፣ የመኸር መጠን፣ የአባባል፣ ወዘተ ስህተት አለመፈፀሙንና ቃል አለማጉደሉን ምስክሮችን ይጠይቃል፤ ተሳስቶ ከሆነ ስህተቱን ይነግሩትና ስህተቱን አስተካክሎ በድጋሚ እንዲለው፣ ያልተሟላ ነገር ካለም እንዲያሟላ ይደረጋል፡፡ በተደጋጋሚ ስህተት ከሰራ አርሞ ለተደጋጋሚ ጊዜ እንዲደግመው ይደረጋል፡፡ የሙሽራው ተወካይም "እርሷን ለእርሱ በጠራኸው መኸር ማጋባትህን በውክልናዬ መሰረት ተቀበልኩ" ይልና

ኒካሁ ይታሰራል (ሼህ ጧሂር ኑሬ፣ 22/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ በዚህ መልኩ ኒካህ ከታሰረ በኋላ መኽር ይሰጣል፡፡

መኽር ሀይማኖታዊ መነሻ ያለው ሙሽራው ለሙሽራዋ በገንዘብ ወይም በዓይነት የሚሰጠው ስጦታ ነው (*The Quran*, Al-Nisa' 4:4)፡፡ ቀደም ባለው ጊዜ የመኽር ገንዘብ መጠን እንደ ሙሽራዋ ቤተሰብ ማህበራዊ ደረጃ ከፍና ዝቅ ይል ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን ማህበራዊ ደረጃ የመኽር ገንዘብ መጠን ላይ ምንም ተጽዕኖ የለውም፡፡ በእስልምና ሀይማኖት የመኽር ገንዘብ መጠን የተወሰነ ባለመሆኑ (*The Quran*, Al-Nisa' 4:24) መጠኑ የሚወሰነው በተጋቢዎቹና በሴቷ ሙሽራ ቤተሰብ መካከል በሚኖር ስምምነት ነው፡፡ የሴቷ ቤተሰብ የመጣውን የመኽር ገንዘብ ይበቃል ብሎ ከተስማማና ከተቀበለ፣ ሙሽራው ሙሽራዋ ደስ ይበላት ብሎ ብዙ መኽር ካመጣ፣ ሙሽራዋ አስቀድማ "በመጣው መኽር እስማማለሁ" ካለች ወይም "ምንም መኽር አልፈልግም፤ ለወጉ ግን ይህን ይስጠኝ" ብላ ትንሽ ነገር ከጠየቀች ጉዳዩ በስምምነት ያልቃል፡፡ ልጃችን በዚህ ያህል መኽር አትሄድም ብለው የሙሽራዋ ቤተሰብ አባላት ስምምነት ከሌላቸው የሙሽራው ተወካይ ከሙሽራው ተማክሮም ቢሆን ነገሩን ማስተካከል ይጠበቅበታል፡፡ ይህን አይነቱ ችግር እንዲቀረፍ በማሰብ የሀገር ሽማግሌዎች ተሰብስበው የመኽር ገንዘብ ለልጃገረድ 1,000.00 (አንድ ሺህ) ብር፣ ለፈታች ሴት ደግሞ 500.00 (አምስት መቶ) ብር ይሁን ብለው ደንብ አውጥተው ነበር፡፡ ነገር ግን በድሮ ጊዜ 20.00 (ሀያ) ወይም 30.00 (ሰላሳ) ብር የነበረው የመኽር ገንዘብ መጠን አሁን አልፎ አልፎ እስከ 10,000.00 (አስር ሺህ) ብር ድረስ እየተከፈለ ነው (አቶ አህመድ ሲራጅ፣ 28/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ በመሆኑም ኒካህ ሲታሰር የሀይማኖት አባቶቹ የመኽር ገንዘቡን እንዲሰጥ የሙሽራውን ወኪል ይጠይቃሉ፡፡ ወኪሉ የመኽሩን ገንዘብ ሲያስረክብ የሀይማኖት አባቶቹ "ለልጅህ ስጥ" ብለው በሙሽራዋ በኩል ላለ ተወካይ ይሰጣሉ፡፡ የመኽር ገንዘብ ከተሰጠ በኋላ ወግ የማሳየትና የማስረከብ ስነ ስርዓት ይከናወናል፡፡

### መ. የወግ ማስረከብ ስነ ስርዓት

ወግ ሙሽራው ለሙሽራዋ፣ ለቤተሰቧና ለዋና ሚዜዋ የሚሰጠው ጥሎሽ ነው፡፡ በአርጐባዎች ዘንድ በአቅም ልክ ጥሎሽ መጣል እንደ ግዴታ ይታሰባል፡፡ በመሆኑም ሙሽራው ለሙሽራዋ ቀሚስ፣ ሻሽ፣ ሽቶ፣ ዣንጥላ፣ መስተዋት፣ ጫማ፤ ለሙሽራዋ እናት ቀሚስ፣ ሻሽና ሽቶ፤ ለሙሽራዋ አባት ሸሚዝ፣ ሽርጥና ጥምጣም ይጥላል፡፡ አያት በቅርብ

ካሉ ወይም ሙሽራዋ በአያት እጅ ያደገች ከሆነች ለአያትም እንዲሁ ይጣላል፡፡ ለሙሽራዋ የመጀመሪያ ሚዜ ደግሞ አንድ ቀሚስ ወይም ሻሽ ከሳሙና ወይም ከሳሙናና ከሽቶ ጋር ይዋላል (ወ/ሮ እሙዬ መሐመድ፣ 6/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ምልከታ ባደረግሁበት የሰርግ ስነ ስርዓት ክዋኔ ላይ የሙሽራዋ ሚዜ የነበረችው ወ/ት አይሻ መሐመድ ሰኢድ አንድ ቀሚስ ከገላ ሳሙና ጋር እንደመጣላት ነግራኛለች (2/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ወጉን መርጦ የሚገዛው ሙሽራው ነው፡፡

በመሆኑም ከተወካዩ ጋር ወግ ይዞ የመጣው ሚዜ ሻንጣውን ከፍቶ የመጣውን የወግ እቃ አንድ በአንድ ለሽማግሌዎቹ ያሳያል፡፡ ለሙሽራዋ አባት የመጣውን "ይኸ የአባታችን ነው"፣ ለሙሽራዋ እናት የመጣውን "ይኸ የእናታችን ነው"፣ ለሙሽራዋ የመጣውን "ይኸ የልጃችን ነው"፣ ለሚዜዋ የመጣውን "ይኸ የእህታችን ነው" በማለት በተነጠፈ ቁርበት ላይ ያስቀምጣል፡፡ ሚዜው አሳይቶ እንደጨረሰ ሽማግሌዎቹ ሰለዋት ያደርጉና ከተዘያየሩ በኋላ ሚዜው ከሙሽራዋ እናት በስተቀር በእድሜ ገፋ ያሉ የሙሽራዋ ሴት ዘመዶች ወደሚገኙበት ክፍል በመሄድ ለእነርሱም እንደገና የመጣውን ወግ ያሳያል (ሼህ ጧሂር ኑሬ፣ 22/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

እንደ ነውር ስለሚታሰብ የሙሽራዋ እናት ወግ ሲቀርብ ገብታ አታይም፡፡ ወጉን የሚያዩ ሴቶች የጐደለ ነገር አለ ብለው ካሰቡ "ይኸ ለምን አልተሟላም?" ብለው ይጠይቃሉ፡፡ ነገር ግን ጥያቄውን የሚያቀርቡት ለመጠየቅ ያህል ነው እንጂ በአብዛኛው አሟሉ ብለው አያስገድዱም፡፡ ወጉ ከታየ በኋላ ሴቶቹ ዱዓ ያደርጋሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ሚዜው የሙሽራዋ የሆነውን መርጦ በመጣበት ሻንጣ ይከትና ሌላውን ሲተው ሴቶቹ ለሚዜዋ የመጣውን በማስቀረት ለእናትና ለአባት የመጣውን አጣጥፈው በመጣበት ሻንጣ እንዲገባና ተመልሶ እንዲወሰድ ያደርጋሉ፡፡ ይህ የሚሆነው ለእናትና ለአባት የመጣው ስጦታ የሚሰጠው ሙሽሮች ለመልስ ሲመጡ በመሆኑ በሰርጉ ቀን ልብሱ ከተሰጠ ሙሽራው ለመልስ ደግሞ ሌላ ልብስ ለመግዛት እንዳያስብ ነው፡፡ የሚዜዋ ስጦታ ለሚዜዋ ይሰጣል (ወ/ሮ እሙዬ መሐመድ፣ 6/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የሚከተለው ዱዓ ምልከታ ባደረግሁበት የሰርግ ስነ ስርዓት ላይ ወግ ከታየ በኋላ በወ/ሮ ብርቄ መሪነትና በተሰበሰቡት ሴቶች ተቀባይነት የተደረገ ነው (24/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

| ዱዓ አድራጊ | ተቀባዮች |
|---|---|
| ቢስሚላሂ | አሜን |
| የፋጢማን ኑሮ | ” |
| አላህ ያርግላቸው | ” |
| አማናቸውን ሙሉ | ” |
| ርዚቃቸውን ሰፊ | ” |
| ኸቲማቸውን ደማቅ | ” |
| አላህ ያርገው | ” |
| አኋሁ መሰሊ | ወሰሊም አላ ሰይድና መሐመድ ወአላ አሊ ሰይድና መሐመድ |

አማን፣ ርዚቅ እና ኸቲማ የሚሉት በዱዓው ውስጥ ያሉ ዋና ዋና ቃላት ናቸው፡፡ ዱዓው ሙሽሮቹ ሰላም እንዲሆኑ፣ ሀብት እንዲያፈሩ፣ መጨረሻቸው እንዲያምር በመመኘት የተከናወነ ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ ለሙሽራ የሚሰጥ ወግ እየበዛና ዓይነቱም በውድ የሚገዙ ቁሶችን እየጨመረ መምጣቱ በሰዎች መካከል ፉክክር እያመጣና በኢኮኖሚ አቅሙ ደከም የሚል ሰው በዚህ ምክንያት ከጋብቻ እየዘገየ በመሆኑ እንዲሁም ወግ የመክፈል አቅም አለመኖር ከነገር መፍጃው በኋላ ለሰርግ ቀን ተቆርጦ እያለ ተጋቢዎች ተስማምተው በመጥፋት ከኒካህ በፊት አብሮ ኑሮን መጀመር እየተለመደ በመሆኑ የሀይማኖት አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎች ደንብ አውጥተዋል፡፡ ደንቡ የሚሰጥ የወግ መጠን ይቀንስ፣ የወግ ሻንጣም ሳይከፈት መምጣቱ ብቻ ታይቶ እንዲሁ ይመለስ እንጂ የመጣ ወግ አንድ በአንድ አይታይ የሚል ሲሆን እንደዚያ የተደረገባቸው የተወሰኑ ክዋኔዎች ቢኖሩም አብዛኛውን ጊዜ ግን ከፍተኛ ወግ እየተሰጠ፤ ሻንጣም ተከፍቶ ለሽማግሌዎች እየታየ ነው (ሼህ ጧሂር ኑሬ፣ 22/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ በአይነትና በመጠን ከፍ

እያለ የመጣውን ወግ ጉዳይ በተመለከተ ወ/ሮ እመይ መሐመድ ነጋሽ (22/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> *በእኛ ጊዜ ለእናትና ለአባት የለም፡፡ ለልጅቱ ብቻ ሁለት ሙሉ ልብስ፣ ዣንጥላ፣ ጫማ፣ መስታወት እነኚህ ነገሮች አይቀሩም፡፡ ቅምብቻና ሙዳይም ከነሽታው ይመጣ ነበር፡፡ ከእኛም ጊዜ በኋላ መካከሉን በጣም የተንዛዛ ነበር፡፡ የናረ ነበር፡፡ ልብስ እስከ አስራ አምስት የሚጣልበት፣ ለአያት፣ ለእናት፣ ለአባት፣ ለአክስት፣ ለአጐት ሙሉ ልብስ ከነጫማው ይመጣ ነበር፡፡ ከባድ ነበር ጥሎሹ፡፡ በአሁን ጊዜ ግን በወንዶች ላይ ጫና ስለፈጠረ በእነርሱ አማካይነት ይቅር ተባለ፤ ልጃገረዶች ሳያገቡ ቀሩ፣ ወንዶችም በፍርሀት ቀሩ ስንት ደሀ ትንሽ ነገር አድርጐ ማግባት ሲገባው አንደገና ለአያት ለአክስት የሚባለው ነገር ይቅር ተብሏል፡፡*

የኒካሁና የወግ ማሳየቱ ስነ ስርዓት ከተከወነ በኋላ የሙሽራው ተወካይ፣ ሚዜና ምናልባትም ሌሎች አብረው የመጡ አንድ ወይም ሁለት አጃቢዎች ወደ ሙሽራው ሄደው ይቀላቀላሉ፡፡ ሙሽራውን አጅበው የቆዩት አጃቢዎች የላኳቸው ሰዎች ከሰርጉ ቤት መውጣታቸውን ሲያዩ ጥይት በመተኮስ ደስታቸውን ይገልፃሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ሙሽራው ከሚዜዎቹና ከአጃቢዎቹ ጋር በመሆን ወደ ሰርጉ ቤት ይገባል፡፡ ሙሽራ የሚገባበት ሰዓት የሰርጉ ቤት ሞቅ የሚልበት ነው፡፡ የሙሽራው ሚዜዎችና አጃቢዎች ጥይት ይተኩሳሉ፤ የሙሽራዋ ሚዜዎችና አጃቢዎች ዘፈኖችን በመዝፈን ይቀበላሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ኒካሁን ያሰሩ የሀይማኖት አባቶችና ሽማግሌዎች ምግብ ቀርቦላቸው ከተመገቡ በኋላ ቁርዓን ሲቀሩ ሙሽራው፣ ሚዜዎቹና አጃቢዎቹ በተለየ በተዘጋጀላቸው የአማች ቦታ ይገቡና ገበታ ይቀርባሉ (ሼህ ጧሂር ኑሬ፣ 22/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ሙሽራው በቤተሰቡ ቤትም ሆነ በሙሽራዋ ቤተሰብ ቤት በተለየ ቦታ የሚያርፍና የሚመገበውም በተለየ መንገድ በተሰናዳ ገበታ መሆኑ እንዲሁም ሙሽራ ሲገባና ሲወጣ ጥይት የሚተኮስ መሆኑ ለሙሽራ የሚሰጥን ክብር የሚያሳይ ነው፡፡

## ሠ. የገበታ ስነ ስርዓት

ሙሽራው ከሚዜዎቹና ከአንድ ወይም ከሁለት አጃቢዎቹ ጋር በአንድ ላይ ገበታ ይቀርባል፡፡ ከሙሽራዋ ወገን ቀደም ብለው በጋብቻ ቤተሰቡን የተቀላቀሉ ወንድ አማቾች ማለትም የአክስት ባሎች፣ የእህት ባሎች፣ የእህትና የወንድም ልጆች ባሎች፣ ወዘተ እንዲጋብዙ ከአዲሱ አማች ጋር አብረው ገበታ ይቀርባሉ፡፡ ቀሪዎቹ የሙሽራው አጃቢዎች ደግሞ በአንድ ላይ በሌላ ገበታ ይቀርባሉ (አቶ ሙሳ ሲራጅ፣ 25/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ማህበራዊ ደረጃን መሰረት በማድረግ በአማች ገበታ ላይ በቅደም ተከተል የሚቀርቡ ቡድኖች በመኖራቸው ምክንያት የአመጋገብ ስነ ስርዓቱም እያንዳንዱ ተመጋቢ ቡድን ቀጥሎ የሚመገበውን ቡድን በማያስቀይም መልኩ ይሆናል፡፡ አዲሱ አማች አብረውት ገበታ የቀረቡ ሚዜዎቹና ጥቂት አጃቢዎቹ ከቀረበላቸው ገበታ ከእንጀራና ወጡ በመጠኑና በአግባቡ ይመገባሉ፡፡ ለወግ ከቀረቡ ምግቦች ማለትም ከቅቤው፣ ከማሩና ከዝልዝሉ በትንሹ ተመግበው ሳይጨርሱ ይተዋሉ፤ ሲመገቡም አንዱን ከአንዱ ሳያነካኩና ሳያንጠባጥቡ፣ ለሰው እይታ እንዳያስቀይም አድርገው ይመገባሉ፡፡ በዚህ መልኩ ከበሉ ጨዋ ናቸው ይባላሉ፤ ጨርሰውና አነካክተው ከበሉ ግን እንጨት ሰባሪዎች “ጅብ አዝለው ነው የመጡት” እያሉ ይተቿቸዋል፡፡ አማች በልቶ እንዳበቃ በቀረበው ገበታ ላይ ያነሱ ምግቦች ላይ ተጨምሮ ገበታ ከፋች ሽማግሌዎች ለሁለተኛ ዙር ይቀርቡበታል፡፡ ሽማግሌዎች ከላይ በተገለፀው መንገድ በልተው እንዳበቁና እንደተነሱ በዚያው ገበታ ላይ ምግብ ተጨምሮ እንጨት ከጫካ በመስበር ያመጣውና አጥር ሲያጥር የነበረው እንጨት ሰባሪ የወጣት ቡድን ይቀርብና ይመገባል (አቶ ሙሳ ሲራጅ፣ 25/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

አማች ከሌላው የሰርጉ ተሳታፊ ሰው ተለይቶ በተከለለ ቦታ እንዲያርፍና እንዲመገብ ማድረግ፣ ለአማች የተለየ ረዥም ገበታ ማዘጋጀት፣ አማች ከብዙሀኑ አጃቢው ተለይቶ በተዘጋጀለት ገበታ ከሚዜዎቹና ጥቂት አጃቢዎቹ ጋር ብቻ ገበታ እንዲቀርብ መደረጉ፣ ከአጃቢ የተለየ የተከተረ ቦታ መሰጠቱና አዲሱን አማች እንዲያባሉና እንዲጋብዙ ቀደም ሲል ከሙሽራዋ ቤተሰብ ጋር በጋብቻ የተዛመዱ አማቾች መመደባቸው በባህሉ ለአማች የሚሰጥን ከፍ ያለ ቦታና ክብር የሚያሳይ ነው፡፡

## ረ. የሙሽሮች አወጣጥ ስነ ስርዓት

የሙሽሮች መውጫ ሰዓት ሲደርስ የሙሽራዋ ሴት የቤተሰብ አባላት ሙሽራዋ የምትወስዳቸውን እቃዎች ከቤት በማውጣት ደጅ በሰፌ ምንጣፍ ላይ በመደርደር ለተከታዩዋ ሴት እያሳዩና እያስቆጠሩ ተከታዩዋ በሀላፊነት ከተረከበች በኋላ አሳስረው ወንድ የቤተሰብ አባላትና የሙሽራው አጃቢዎች እየተሸከሙ በአህያ ላይ ይጭናሉ፡፡ ሙሽራዋ ወደ ባሏ ቤት ስትሄድ የምትወስዳቸው እቃዎች መሶብ፣ ሰፌድ፣ ወንፊት፣ የበርበሬና የሽሮ ቅል፣ የሽታ ቅል፣ ደጋንና እንዝርት፣ ጀበናና ስኒ፣ ጣባ፣ ምድጃ፣ ለመኝታ የሚሆን ቁርበት፣ ቡልኮ፣ የጭስ መሞቂያ፣ ለባለቤቷ እናትና አባት ጋቢ፣ እና ለሴት የቤተሰቡ አባላት ማለትም ለእህቶቹ፣ ለወንድሞቹ ባለቤቶች፣ ለአጎቶቹ ባለቤቶች፣ ወዘተ ልብስ ወይም ሳሙና ናቸው፡፡ እነዚህን እቃዎች ከነገር መፍጃው በኋላ ከፊሉን ሙሽራዋ አበጅታ ታዘጋጃለች፤ ከፊሉን ደግሞ ቤተሰብና ዘመድ ያሟላላታል፡፡ በተጨማሪም ለባዲሼህ መደገሻ የሚሆን እህል፣ ለእርድ የሚሆን ፍየልና ማጣፈጫም ይጫናል (ወ/ሮ እሙዬ መሐመድ፣ 6/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡



ፎቶግራፍ 24. የሙሽራዋ እቃ ሲዘጋጅ

አስርቲ በመቅረቱ ምክንያት የተጋቢዎች ወገኖች በሆኑ ወጣቶች ዘንድ የነበረው መተቻቸት ቢቀርም አሁንም ሙሽራ ሲወጣ የሚደረጉ ትንኮሳዎች አልቀሩም፡፡ አቶ መሐመድ ሲራጅ (14/7/2013፣ ጉዜ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) ከሴት ወገን እንጨት ሰባሪ በነበሩበት የሰርግ ስነ ስርዓት ላይ ሙሽራ ሲወጣና የሙሽራዋ እቃ ሲጫን ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ያደረጉትን እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡

መጀመሪያ በጋብቻው ቅሬታ ነበረን፡፡ ሁላችንም ቅሬታ ነበረን፡፡ ሽማግሌ ግን ተዉ አትረብሹ፤ የመጣው አማች እንጂ ጠላት አይደለም፤ ምንም ነገር ብታደርጉ ጠባችሁ ከእኛ ነው አሉ፡፡ እኛ ግን ሄደን ብዙ የወፍ ዘር፣ ገበሎና እባብ ሳይቀር ገድለን አመጣንና አማች በሚወጣበት ጠባብ መንገድ ላይ በእንጨት አንጠለጠልናቸው፡፡ ሽማግሌዎቹ ፈልገው አግኝተው አንስተው ወረወሩብን፡፡ ከወደቁበት አንስተን አመጣንና አማች ሲወጣ ጠብቀን የሙሽራዋን እቃ ስንጭን በቅሎው ላይ ከእቃው በታች እያደረግን የገደልናቸውን ሁሉ አብረን ጫንናቸው፡፡ ሲራገፍ ሲታይ ለአማች ውርደት ነው፡፡

ሙሽራዋ የምትወጣበት ሰዓት ሲደርስ ሙሽራውና ሚዜዎቹ ሙሽራዋ ወዳለችበት ቤት ይሄዳሉ፡፡ ይህ ጊዜ እንደ ሙሽራ መግቢያ ሁሉ የሰርጉ ቤት ሞቅ የሚልበት ነው፡፡ የሙሽራው ወገኖች ጥይት ይተኩሳሉ፤ የሙሽራዋ ሚዜዎችና አጃቢዎችም ይዘፍናሉ፡፡ ሙሽራው፣ ሚዜዎቹና አጃቢዎቹ ሙሽራዋን ለመውሰድ ሙሽራዋ ባለችበት ዳስ ወይም ቤት በር ላይ እንደደረሱ የሙሽራዋ ሚዜዎችና አጃቢዎች እጅብ ብለው እየዘፈኑ በሩን ይይዙባቸዋል፡፡ የዘፈኖቹ ግጥሞች ሙሽራውንና ሚዜዎቹን የሚሰድቡ ናቸው 9/5/2013፣ ጋቻኔ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

የሚከተለው ግጥም ምልከታ ባደረግሁበት የወ/ት ሸምስያ ሰዒድ የሰርግ ስነ ስርዓት ላይ ሙሽራው አቶ አባኢዚድ አቡበከር ሙሽራዋን ለመውሰድ ከሚዜና አጃቢዎቹ ጋር በመሆን ሙሽራዋ ወዳለችበት ከፍል ሲቀርብ የሙሽራዋ ሚዜዎችና አጃቢዎች በር በመያዝ ከዘፈኗቸው ዘፈኖች ግጥሞች ውስጥ በማሳያነት የተመረጠ ነው (9/5/2013፣ ጋቻኔ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

| <u>አውራጅ</u> | <u>ተቀባዮች</u> |
|---|---|
| ሲጥ ሲጥ አለ ጐፍ ጫማዋ ደረሰ መሄጃዋ | ሲጥ ሲጥ አለ ጐፍ ጫማዋ ደረሰ መሄጃዋ |
| እሷ አትሄድም ባጋስስ አምጡላት አውቶቡስ | እሷ አትሄድም ባጋስስ አምጡላት አውቶቡስ |
| እሷ አትሄድም ባጋስስ አምጡላት ሚኒባስ | እሷ አትሄድም ባጋስስ አምጡላት ሚኒባስ |

የዘፈን ግጥሙ ዘመናዊነት በማህበረሰቡ ዘንድ ያመጣውን ለውጥ የሚያሳይና ለሙሽራ መጓጓዣነት የሚውለው የጋማ ከብት በዘመናዊ ተሽከርካሪ፣ የሙሽራዋ ልብስም በዘመናዊ ነጭ የሙሽራ ቀሚስ እንዲቀየር መሻትን የሚያሳይ በመሆኑ በባህል ላይ ለውጥ መከሰቱን ያሳያል፡፡

የሙሽራዋ ሚዜዎች ሙሽራዋን ደብቀው የወንድ ሚዜዎች ሽቶ ሳይረጩ፣ ከረሜላ ሳይበትኑ ሙሽራዋን መውሰድ እንደማይችሉ የሚገልፁ ግጥሞች ያሏቸውን ዘፈኖች ሲዘፍኑ የሙሽራው ሚዜዎች ከያዙት ሽቶ ይረጫኑ፣ ከረሜላውንም ይበትናሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ሚዜው ይገባና ሙሽራዋን ተሸክሞ በሌላ በር ይወጣል፡፡ አማች በገባበት በር አይወጣም፡፡ የሚገባው በፊት ለፊት በር ስለሆነ ሙሽራዋን ይዞ ሲሄድ ከቤት ውስጥ እቃው ሁሉ ወጥቶ በቤቱ ውስጥ አልፎ በሌላ በር እንዲወጣ ይደረጋል፡፡ ይህ የሚደረገው ሰርገኛ ጥሎት የሚሄደው በረከት አለ ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ሚዜው ሙሽራዋን ተሸክሞ በማውጣት በቅሎ[30] ላይ ይጭናትና እርሱም በቅሎዋ ላይ ተፈናጥጦ ሙሽራዋን በመደገፍ ሰፈሩን ከወጡ በኋላ ይወርድና ሙሽራው ይፈናጠጣል፡፡ ተከታይ ሆና ከሙሽራዋ ጋር ለምትሄደው ሴትም በቅሎ የሚቀርብ ሲሆን ሌላው አጃቢ በእግር ከኋላ ይከተላል፡፡ ጉዞ ሲጀምሩ ለሙሽራዋ ሀዘን ይደረግላታል፡፡ ከዚያ በኋላ የሙሽራዋ ሚዜዎችና አጃቢዎች ዘፈኖችን እየዘፈኑ ሙሽራዋን ይሸኙዋታል (ወ/ሮ አይኔ ይማሙ፣ 13/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የሚከተሉት ግጥሞች ምልከታ ባደረግሁበት የሰርግ ስነ ስርዓት ላይ ሙሽራዋ ስትሸኝ የተከወኑ ዘፈኖች ግጥሞች ናቸው (9/5/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

ግጥም 1፣

| <u>አውራጅ</u> | <u>ተቀባዮች</u> |
|---|---|
| ሄደች አሉ ጋራ ጋራውን ነፋሻውን | ሄደች አሉ ጋራ ጋራውን ነፋሻውን |
| ሄደች አሉ ከቤቱ በላይ አይኗን ሳላይ | ሄደች አሉ ከቤቱ በላይ አይኗን ሳላይ |
| ሄደች አሉ ከቤቱ ስር ስር የኔ ምስር | ሄደች አሉ ከቤቱ ስር ስር የኔ ምስር |

[30] በአካባቢው በስፋት ጥቅም ላይ የሚውለው የጋማ ከብት በቅሎ ነው፡፡

| ሂደች አሉ በጅሩ በይፋት የዳኛ ጥፋት | ሂደች አሉ በጅሩ በይፋት የዳኛ ጥፋት |
|---|---|

ግጥም 2፣

| <u>አውራጅ</u> | <u>ተቀባዮች</u> |
|---|---|
| የሰማይ ኮኮብ ተወረወረ ሙሽሪት | የሰማይ ኮኮብ ተወረወረ ሙሽሪት |
| ደህና እደሪ | ደህና እደሪ |
| ሙሽሪት አይዞሽ አይዞሽ ቤት | ሙሽሪት አይዞሽ አይዞሽ ቤት |
| እሰራለሁ አጠገብሽ | እሰራለሁ አጠገብሽ |

ሙሽራዋን ተከትለው የሚሄዱ አንድ ወንድና አንድ ሴት ተከታዮች ብቻ ናቸው፡፡ እንደ ነውር ስለሚቆጠር ከሙሽራዋ ወገን ከሁለት ተከታዮች ውጭ ሙሽራዋን ተከትሎ የሚሄድ ሰው የለም፡፡ ሙሽራዋ ስትሄድ ሚዜዎቿና አጃቢዎቿ እንኳን ሸኝተዋቸው ይመለሳሉ እንጂ ተከትለው ሙሽሮቹን አጅበው አይሄዱም፡፡ ተከታዮች ከሰርጉ ቀን ጀምሮ ለአራት ቀናት ከሙሽሮቹ ጋር በሙሽራው ቤተሰብ ቤት ይቆያሉ፡፡ በቆይታቸው ተከታይ ለመሆናቸው ምክንያት የሆኑ ሀላፊነቶች አሉባቸው፡፡ ሴቷ ተከታይ በዋናነት ሙሽራዋ በባሏ ቤት ስትደርስ ገላዋን በማጠብ፣ ልብሷን በመቀየር፣ ወደ ጫጉላው ቤት በመውሰድና በሚያስፈልገው ሁሉ አብራት በመሆን ታግዛታለች፤ ከሙሽራዋ ቤተሰብ ቤት የተጫነውን የሙሽራዋን የቤት እቃና ለአማቾች የሚሰጥ ስጦታን በሀላፊነት ተረክባ ታደርሳለች፤ ለባዱሼህ መደገሻ ተጭኖ የሚወሰደውን እህል፣ ፍየልና የመሳሰሉ ነገሮች ተረክባ በሙሽራው ቤተሰብ ቤት ሰዎችን በማስተባበር ደግሳ ታበላለች፡፡ ተከታይ የምትሆን ሴት የሙሽራዋ የቅርብ ዘመድ ስትሆን በአብዛኛው አክስት ወይም የአጎት ሚስት ለተከታይነት ይመረጣሉ፡፡ ወንዱ ተከታይ የወንድ ስራ ተብለው የተለዩ ስራዎችን ይሰራል፡፡ ባዱሼህ ሲደገስ እርድ ያርዳል፣ ስጋውን ይበልታል፣ የሚያስፈልጉ የጉልበት እገዛዎችን ያደርጋል፡፡ ተከታይ የሚሆነው አብዛኛውን ጊዜ የአጎት ወይም የአክስት ልጅ ነው (ወ/ሮ አይኔ ይማሙ፣ 13/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ሙሽራው ሙሽሪትን ይዞ የሚገባው ቤተሰቡ ቤት ነው፡፡ ሙሽሮቹ እንደደረሱ ተከታይዋ ሙሽራዋን ገላዋን አጥባ ልብስ ትቀይርላታለች፡፡ ከዚያ በኋላ እራት ሲቀርብ ሙሽራዋ ከተከታይዋ ጋር ሆና፤ አንድ ከሙሽራው ወገን የሆነች ሴት ተጨምራ በአንድ ገበታ ይቀርባሉ፡፡ ከሙሽራው ወገን የሆነች ሴት የምትጨመረው እንግዶቹን እንድትጋብዝ ነው፡፡ ሙሽራው ከሚዜዎቹና አጀቢዎቹ ጋር ሆኖ ከመቃ በተሰራ ገበታ እራት ቀርቦላቸው ይመገባሉ፤ ከእራት በኋላ ቡና ተፈልቶ እየተጫወቱ ይቆያሉ (ወ/ሮ አይኔ ይማሙ፣ 13/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

6.4.4.1.4. የጫጉላ ቤት ስነ ስርዓትና ለድንግልና የሚሰጥ ዋጋ

የጫጉላ ቤት የሚዘጋጀው በጐረቤት ቤት ሲሆን የት እንደሆነ የሚያውቁት የሙሽራዋ ተከታይና የሙሽራው ሚዜ ብቻ ሲሆኑ ሲገቡና ሲወጡ ሌሎች ሰዎች እንዳያዩዋቸው ተደብቀው በሚስጥር ነው፡፡ ሰዓቱ ሲመሽ የሙሽራዋ ተከታይና ሚዜው ለጫጉላ በተዘጋጀው ቤት ሙሽሮቹ የሚለብሱትን ይዘው በመሄድ ተከታይዋ አንጥፋና መኝታቸውን አስተካክላ ሙሽራዋን ይዛት ትሄዳለች፤ ሙሽራውን ደግሞ ሚዜው ይዞት ይሄዳል፡፡ ከዚያ በኋላ ተከታይዋም ሆነች ሚዜዎቹ በሙሽራው ቤተሰብ ቤት መኝታ ተዘጋጅቶላቸው ያድራሉ፡፡ በማግስቱ ጠዋት ሙሽራዋ ድንግል ሆና ስትገኝ ሚዜው የሙሽራውን ቤተሰብና ዘመዶች "ደስ ብሎናል እንኳን ደስ አላችሁ" በማለት ያበስራል፤ ለተከታይዋም እንዲሁ ይነገራታል፡፡ በዚህ ጊዜ ተከታይዋ ጫጉላው ቤት በመሄድ ሙሽራዋን ገላዋን አጥባና ልብሷን ቀይራላት ከሚዜው ጋር በመሆን ሙሽሮቹን ወደ ሙሽራው ቤተሰብ ቤት ይዘዋቸው ይመለሳሉ፡፡ ሙሽሮቹ ከጫጉላው ቀን በኋላ የሚያድሩት በሙሽራው ቤተሰብ ቤት በሚዘጋጅላቸው ክፍል ይሆናል (ወ/ሮ አይኔ ይማሙ፣ 13/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ በማግስቱ ጠዋት የሙሽራው ሚዜዎች ወደ ሙሽራዋ ቤተሰብ ቤት በመሄድ "ደስ ብሎናል እንኳን ደስ አላችሁ" በማለት የምስራቹን ይነግራሉ፡፡

የሙሽራው ሚዜዎች በሙሽራዋ ቤተሰብ ቤት ቅቤና ማር ተቀድቶ በጥሩ ሁኔታ ከተጋበዙ በኋላ ሽልሙን እያሉ በመዝፈን እየዞሩ ከቤተሰቡ አባላት ብር ይሰበስባሉ፡፡ ሽላሚዎቹ የሙሽራዋ እናትና አባት፣ አያቶች፣ አጐትና አክስቶች፣ የአጐትና አክስት ባለቤቶች፣ ወዘተ ናቸው፡፡ ሚዜዎቹ በሰበሰቡት ብር የቤት እቃ በመግዛት ለሙሽሮቹ ስጦታ ይሰጣሉ (ወ/ሮ አይኔ ይማሙ፣ 13/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በአርጐባዎች ዘንድ የሙሽራዋ ድንግል ሆኖ መገኘት ትልቅ ዋጋ የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ ድንግል ሆና ያልተገኘች ሙሽራ ድንግል ሆና ከተገኘችው እኩል ክብር አይሰጣትም፡፡ የመኽር ገንዘብ ሲወሰን እንኳ ፊት ሴት ስታገባ የሚሰጣት የመኽር ገንዘብ ልጃገረድ ስታገባ ከሚሰጣት የመኽር ገንዘብ በግማሽ ያነሰ ይሁን ተብሎ መወሰኑን ማንሳት ይቻላል፡፡ በተለይ በሙሽራው ቤተሰብ ዘንድ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው በመሆኑ ሙሽራ ድንግል ሆና ስትገኝ በአማቾቿ ዘንድ የተለየ ክብር ይሰጣታል፡፡ ነገር ግን ድንግል ሆና ካልተገኘች በየጊዜው በነገር እየተሸነቆጠች አንገቷን እንድትደፋ ትደረጋለች፡፡ ስለዚህ አንዲት ሙሽራ ድንግል ሆና መገኘቷና አለመገኘቷ ከቀጣይ ኑሮዋ ጋር እጅጉን የተያያዘ ነው፡፡

ሙሽሮች ከሰርጋቸው በኋላ በሙሽራው አካባቢ በቤተሰብ ግቢ ውስጥ ከቤተሰብ ቤት በስተጀርባ በኩል ሙሽራው አስቀድሞ በሰራው ቤት ውስጥ ይኖራሉ፡፡ በአርጐባዎች ዘንድ ወንድ አግብቶ ኑሮውን በሴቷ አካባቢ ማድረጉ አሳፋሪ ነው (ወ/ሮ አይኔ ይማሙ፣ 13/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች እንመልከት፡፡

- የእናትና የአማች ሀገር ሀገር አይባልም (ወ/ሮ ሲቲ ፋጡማ መሐመድ፣ 30/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቡድን ተኮር ውይይት)፡፡
- የሴት ልጅ አባቷ ባሏ ነው (ወ/ሮ አይኔ ይማሙ፣ 30/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቡድን ተኮር ውይይት)፡፡
- የሚስት ሀገሯ የባሏ ሀገር ነው (ወ/ሮ አይኔ ይማሙ፣ 30/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቡድን ተኮር ውይይት)፡፡

የመጀመሪያው ምሳሌያዊ አነጋገር የሙሽራዋ ቤተሰብ ሀገር ለሙሽራው ሀገር፣ መኖሪያ አለመሆኑን በመግለጽ፣ ሁለተኛው ሴቷ የቤተሰቧን አካባቢ በመልቀቅ የምትሄድ በመሆኑ ተጠሪ የሚሆናት ባሏ በመሆኑ ባሏ እንደ አባቷ መሆኑን በመግለጽና ሶስተኛው የሚስት ሀገሯ የባሏ ሀገር መሆኑን በመግለጽ ይህን የሰርግ ስነ ስርዓት ከተከናወነ በኋላ ሙሽራው ሙሽራዋን ወደ እርሱ የመኖሪያ አካባቢ የመውሰድ ባህል ይነግረናል፣ ያጠይቃልም፡፡

አንዲት ሴት ካገባች በኋላ ከማግባቷ በፊት ከነበራት አለባበስ፣ አጊያጌጥና የፀጉር አሰራር ትለያለች፡፡ ጥልፍ ያልበዛበትን ቀሚስ በመተው ባለ ጥልፍ ቀሚስ፣ እጥፍ ካቴና ነጠላን

በመተው ሙሉ ወይም ትልቅ ነጠላ ትለብሳለች፤ ከማግባቷ በፊት የማታጌጥበትን ትልቅ ጭልጭሌ ታደርጋለች፤ ረፍረፎ የፀጉር ሹሩባዋን በመተው ስጥቂት ትሰራለች (ወ/ሮ አይኔ ይማሙ፣ 13/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

### 6.4.4.2. የባዱሼህ ስነ ስርዓት

ባዱሼህ ሙሽራዋ የሰርጉ ቀን ማታ ስትወጣ ተጭኖ በሚወሰድ የምግብ ግብዓት በባሏ ቤት ተደግሶ የሚዘጋጅ ስነ ስርዓት ነው፡፡ ባዱሼህ ተደግሶ ሰዎች የሚጋበዙበት ዋና ዓላማ ሙሽራዋ ዱዓ እንዲደረግላት፣ የሀገሩ ሼህ እንዲቀበላት፣ ይህም በመሆኑ ሀገሩ እንዲስማማትና ኑሮዋ እንዲሰምርላት ለማድረግ ነው፡፡ ድግሱን የመደገስ ሀላፊነት ያለባቸው የሙሽራዋ ሁለት ተከታዮች ናቸው፡፡ ወንዱ ለድግሱ የሚሆን እርድና እንጨት መፍለጥን የመሰሉ የወንድ ተብለው የተለዩ ስራዎችን በሀላፊነት ያከናውናል፤ ሴቷ ደግሞ የሙሽራውን ቤተሰብ በማስተባበርና እርሷም ዋና ተሳታፊ በመሆን ምግብ ታዘጋጃለች (ወ/ሮ ሀይሀሊማ ሱለይማን፣ 17/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በመሆኑም የሰርጉ ቀን ማታ ሙሽራዋ ስትወጣ ለድግሱ ዝግጅት የሚያስፈልግ ጥሬ ነገር በሙሉ ይጫናል፡፡ የሚሄዱ የምግብ ማዘጋጃ ግብዓቶች የተፈጨ የጤፍ ዱቄት፣ ሙክት፣ ሽሮና በርበሬ፣ ቅቤ፣ ዘይት፣ ቅመማ ቅመም፣ ቡና፣ ወዘተ ናቸው፡፡ ተከታዮች ይህን በሀላፊነት በመውሰድ ሴቷ ተከታይ በማግስቱ ሰዎችን አስተባብራ የተወሰደውን ዱቄት ታስቦካለች፡፡ በሚቀጥለው ቀን ጠዋት እንዲሁ የተቦካው ተጋግሮ፣ ሙክቱ ታርዶና ወጥ ተሰርቶ የቅርብ ጎረቤት የሆኑ ባልቴቶች ቡና ጠጡ እየተባለ ይጠሩና ይጋበዛሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ቡና ተፈልቶ ሙሽራዋ ይዛው የሄደችው የቤት እቃና ለአማቾቿ ይዛው የሄደችው ስጦታ ተከፍቶ ተከታይዋ ሴት አንድ በአንድ እያሳየች ታስረክባለች (ወ/ሮ ሀይሀሊማ ሱለይማን፣ 17/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ወ/ሮ አይኔ ይማሙ በ5/24/2013 በተከናወነና ምልከታ ባደረግሁበት የሰርግ ስነ ስርዓት ላይ የሙሽራዋ ተከታይ ሆነው የሄዱ ሴት ናቸው፡፡ ተከታይ ሆነው በሄዱበት የሙሽራው ቤተሰብ ቤት ያከናወኑትን ስራ በሚከተለው መልኩ ገልፀዋል፡፡

> ይገፎ የሄድኩት ዱቄት፣ ሽሮ፣ በርበሬ፣ ፍየል፣ ምን አለፋሽ ብቻ ጨው ሳይቀር፣ ቅመም ሳይቀር በቃ ሁሉን ነገር ይገፎ ነው የሄድኩት፡፡ እዚያ እንደገባን ቡና ቆሉ፣

አሸተቱኝ፡፡ ቡናውን በቆሎ ጠጣን፡፡ ከዚያ በኋላ ዝልዝሉ፣ ስቅስቆሹ፣ ሁሉ ነገር ቀረበ፡፡ ያንን በላን ጠጣን፡፡ ልጅቱን [ሙሽራዋን] አስተኛሁ፡፡ በማግስቱ ጠዋት በተኛሁበት መጡ ነቀነቁኝ [ቀሰቀሱኝ]፡፡ ነይ አሉ፤ ወሰዱኝ፤ የምስራቹን ደስ አለኝ፡፡ ገላዋን አስታጠብኩና ይዣት ወደ በተሰቡ ቤት መጣሁ፡፡ በኛ ባህል የሚተኙት እልፍ ባለ በጐረቤት ቤት ነው፡፡ ከዚያ ቁርስ በላን፡፡ ከበላን በኋላ እቃዬን ፈታታሁና ቡናዬን አውጥቼ ሰጠሁ፡፡ የእኔ ቡና ሲፈላላ ዱቄቱን አወጣሁ፤ ዳቦዬን አወጣሁ፡፡ ዱቄቱን መጀመሪያ አቦኩ፡፡ ካቦኩ በላይ ተጣጥበው ዳቦው ተቆርሶ ተበላ፣ ቡናው ተጠጣ፡፡ በማግስቱ ጠዋት የተቦካው ተጋገረ፡፡ አብሮኝ የሄደው የእኔ ልጅ ነው፡፡ እሱ ደግሞ ፍየሉን አሳረደና ስጋውን ለቀቃይ አስረከበ፡፡ የሙሽራው እናት ጐረቤቶቿን እንደገና ለምሳ ጠራች፡፡ ምግቡ ሁሉ ተዘጋጅቶ ሰው መጣ፤ የኔ ልጅ ከወንዶቹ ጋር ሆኖ ወንዶቹን ሲያስተናግድ እኔ ደግሞ ሴቶቹን አስተናገድሁ፡፡ ብዙ ስራ እነሱ ናቸው የሰሩት፡፡ እኔ አለች ያቻት ለመባል ነው እንጂ የቀረማ ብድግ እንኳን ስትይ ለምን ነው? ይሉኛል፡፡ ቁጭ በይ ነው የሚሉኝ፡፡ ያው ግን ጐርደድ ማለት አይቀርም፡፡ የተጠራው ወንዱም ሴቱም በልቶ ጠጥቶ ሲያበቃ የሄደውን እቃ ሁሉ አሳየሁና መልሶ ታሰረ፡፡ እኔ እቃውን ለማሳየት እንጂ ያወጡትም መልሰው ያሰሩትም እነሱዉ ናቸው፡፡ ከእቃው በኋላ የሄደውን ጋቢ ይሄ የእናታችን፣ ይሄ የአባታችን ብዬ ልብሱን ደግሞ የእህቶቻችን ብዬ እያሳየሁ አስረከብኩ (5/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

እቃውና ለአማቾች የሄደው ስጦታ ታይቶ ሲያበቃ ይነሳና ዱዓ ተደርጐና ተከታይዋ ሴት በዱዓ አድራጊዎች ፊት በመቆም "አሚን" እያለች ዱዓውን ተቀብላ ቡናው ይጠጣል፡፡ የሚከተለው ዱዓ በቡድን ተኮር ውይይት ጊዜ ወ/ሮ አይኔ ይማሙ በባዲሼህ ስነ ስርዓት ላይ ይደረጋል በማለት አስታውሰው ያደረጉትና የውይይቱ ተሳታፊዎች "አሚን" በማለት የተቀበሉት ዱዓ ነው (30/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቡድን ተኮር ውይይት)፡፡

| <u>ዱዓ አድራጊ</u> | <u>ተቀባዮች</u> |
|---|---|
| አላህ ያስደሳት | አሚን |
| ላገሩም ግጥም | ” |

ለሼሁም ግጥም ”

የምትሆን ”

ጭድና ጭቃ ”

ማርና ቅቤ ”

ሰምና ወርቅ ”

አላህ ያድርጋት ”

ደግ ዕጣ የሚያቀናጣ ”

ደግ ዕድል የሚያደላድል ”

ደግ ኑሮ የሌለበት እንጉርጉሮ ”

አላህ ያርግላት ”

አሏሁ መሰሊ ወሰሊም አላ ሰይድና መሐመድ ወአላ አሊ ሰይድና መሐመድ

ዱዓው ሙሽሮቹ እንዲዋደዱ፣ ኑሯቸው ጥሩ እንዲሆን በመመኘት የተደረገ ነው፡፡ በዱዓው ውስጥ ጭድና ጭቃ፣ ማርና ቅቤ እና ሰምና ወርቅ የሚሉት ትዕምርታዊ ቃላት ናቸው፡፡ የትዕምርቶቹ ፍች የሚለየው የትዕምርቶቹን ምንነት በመረዳትና አንዱ ትዕምርት ከሌላው ትዕምርት ጋር ያለውን ግንኙነት በመለየት ነው፡፡ ጭድና ጭቃ አንድነታቸው የሚያስፈልግና በተናጠል ቤት ለመስራት የማያስችሉ ናቸው፡፡ ጭድና ጭቃ በአንድ መሆናቸው የሚጠበቅና አንድነታቸው ጥንካሬ የሚሆናቸው ናቸው፡፡ ማርና ቅቤ የአርጐባዎች የክብር ምግቦች ሲሆኑ ገበታ ሲቀርብ አንዱ ካለ ሌላውም ይኖራል፡፡ በንግግር እንኳን "እከሌ ማርና ቅቤ ቀድቶ እንግዶቹን ጋበዘ" እንጂ "ማር ወይም ቅቤ ቀድቶ እንግዶቹን ጋበዘ" ማለት አልተለመደም፡፡ ስለዚህ እነዚህ ሁለት ምግቦች ሁለት ሆነው እንደ አንድ የሚታዩ ናቸው፡፡ ሰምና ወርቅም አንዳቸው በአንዳቸው ውስጥ የሚገኙ

ናቸው፡፡ በመሆኑም ዱዓው የቁሶቹ አንድነት፣ ጥምረት ለተጋቢዎቹ እንዲሆን በመመኘት የተደረገ ነው፡፡

### 6.4.4.3. የደመቅሁ[31] ስነ ስርዓት

ለባዱሼህ ስነ ስርዓት የተጠራው ሰው ከመበተኑ በፊት ቡና እየተጠጣ የሙሽራው ሚዜዎች አንዱ ሽቶና ከረሜና ይዞ፤ አንዱ ደግሞ አለንጋ ይዞ ወደ ሙሽሮቹ በመሄድ በመጀመሪያ ሙሽራውን "ደመቅሁ ለወ/ሮ እከሊት [ለሙሽራዋ] በል" ይሉታል፡፡ "ደመቅሁ ለወ/ሮ እከሊት" ይላል፡፡ በዚህ ጊዜ እልል ይባላል፤ ይጨበጨባል፤ ሚዜው ሽቶ ያርከፈክፍበታል፤ ከረሜላም ይሰጠዋል፡፡ ሙሽራዋም "ደመቅሁ ለአቶ እከሌ [ለሙሽራው] በይ" ትባላለች፡፡ "ደመቅሁ ለአቶ እከሌ" ስትል ለሙሽራው እንደተደረገው ሁሉ እልል ተብሎ ሚዜው ሽቶ ያረከፈክፍባትና ከረሜላ ይሰጣታል፡፡ ከዚያ በኋላ ሚዜዎቹ በስነ ስርዓቱ ላይ የተገኙ ሰዎች ጋር አንድ በአንድ እየሄዱ ደመቅሁ እንዲሉ ያደርጓቸዋል፡፡ ባለ ትዳር ወደሆኑት ጋር በመሄድ "ደመቅሁ ለአቶ እከሌ [የባል ስም] ወይም ለወ/ሮ እከሌ [የሚስት ስም]" እንዲሉ ያስገድዷቸዋል፡፡ ያላገቡ ልጃገረዶችና ወንድ ልጆች ጋር በመሄድ "ደመቅሁ ለሚመጣው ወይም ለምትመጣው በሉ" እያሉ ያስገድዷቸዋል፡፡ ደመቅሁ ላሉት ሽቶ እያርከፈከፉና ከረሜላ እያደሉ ይሄዳሉ፡፡ ነገር ግን አፍረው ለማለት ፈቃደኛ ያልሆኑትን አለንጋ የያዘው ሚዜ ደመቅሁ እስኪሉ ድረስ ይገርፏቸዋል፡፡ ትዳር ያላት ሴት ሆና አፍራ ደመቅሁ ሳትል ብትቀርና ባል ይህን ቢሰማ ሁኔታው ግጭትን የሚፈጥርና እስከ ፍቺ የሚያደርስ መሆኑን አቶ አደም መሐመድ (5/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) ገልፀዋል፡፡

የሙሽራዋ ተከታዮች የሚመለሱት በሰርጉ አራተኛ ቀን ማለትም ሙሽሮች ምላሽ በሚሄዱበት ቀን ጠዋት ነው፡፡ የሙሽራው ቤተሰብ እነርሱን ጠዋት ከሸኘ በኋላ ምሽት ላይ ሙሽሮቹ ለመልስ ስነ ስርዓት ወደ ሙሽራዋ ቤተሰብ ቤት ይሄዳሉ (ወ/ሮ ሀይሀሊማ ሱለይማን፣ 17/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ምልከታ ባደረግሁበት የመልስ ስነ ስርዓት ላይ ተከታዮቹ ምሽት ላይ ከሙሽሮቹ ጋር አብረው እንደመጡ ተመልክቼ (27/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ምልከታ) ይህ ለምን እንደሆነ ስጠይቅ ሙሽሮቹ የሄዱበት የሙሽራው ቤተሰብ ቤት ሩቅ ስለሆነ ነው አብረው የተመለሱት የሚል ምላሽ አግኝቻለሁ፡፡

---

[31] ደምቄ ታየሁ፣ አማርኩ

የሙሽራዋ ተከታዮች ሲሸኙ የሙሽራው እናት አንድ እግር የፍየል ስጋና በመሶብ ድፎ ዳቦ አድርጋ ለሙሽራዋ ቤተሰብ እንድታደርስላት ለሴቷ ተከታይ ትልካለች፡፡ ለተከታይዋ ለራሷ ደግሞ አንድ ቀሚስና ሳሙና ስጦታ ትሰጣታለች፡፡ ወንዱ ተከታይ ቤቱ ይዞት የሚገባው ዳቦ ተጋግሮ ይቋጠርለታል፡፡ ሴቷ ተከታይ ወደ ሙሽራዋ ቤተሰብ ቤት በመሄድ ይዛ የመጣችውን ታስረክብና በመጣው ስጋ ወጥ ተሰርቶና ቡና ተፈልቶ ምሳ ሰዓት ላይ የሙሽራዋ እናት በሰርጉ ስራ ሲረዱ የነበሩትን የቅርብ ሴት ጐረቤቶቿን "እንግዶቻችን መጥተዋል ቡና ጠጡ" ብላ ትጠራለች፡፡ ምሳ ከተበላ በኋላ ቡና ሲቀርብ ዱዓ ተደርጐ የመጣው ዳቦ ተቆርሶ ከታደለ በኋላ ቡና ይጠጣል (ወ/ሮ ሀይሀሊማ ሱለይማን፣ 17/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የሙሽራው ሚዜዎችና አጃቢዎች ከሰርጉ ቀን ምሽት ጀምሮ ለሶስት ቀናት ያህል በሙሽራው ቤተሰብ ቤት አብረው ከርመው በአራተኛው ቀን ጠዋት ሚዜዎችና የተወሰኑ አጃቢዎች ሲቀሩ ብዙዎቹ አጃቢዎች ይሸኛሉ፡፡ አጃቢዎች በአራተኛው ቀን ጠዋት ወደየቤታቸው ሊሄዱ በሶስተኛው ቀን ማታ የሽኝት ድግስ ይደገስላቸዋል፡፡ ማምሻው ላይ ለሽኝታቸው የሚሆን አሊጣጦ ሲጋገር አጃቢዎች በማግስቱ እንደሚሸኙ ይገባቸዋል፡፡ መለያያቸው መሆኑንም በቀልድ መልክ ይነጋገራሉ፤ ግጥምም ይገጥማሉ፡፡ ሴቶቹ አሊጣጦውን ሲጋግሩ የሚመለከቱ አጃቢዎች ከመካከላቸው አንዱ "ደብዳቤው ምን ይላል" ይላል፤ ሌላኛው አጃቢ ተነስቶ አሊጣጦውን ዘርግቶ በመያዝ "ነገ ጠዋት እዚች ቦታ አንድ ሰው እንዳይገኝ ይላል" በማለት ይመልሳል (አቶ አሕመድ ሲራጅ፣ 28/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ አሊጣጦ የመሸኛ ምግብ በመሆኑ ነው አጃቢዎቹ በጨዋታ መልክ አሊጣጦውን እንደ ደብዳቤ በማድረግ መለያያቸው መድረሱን የሚያነሱት፡፡

አጃቢዎች በጨዋታና በደስታ አብረው ከርመው መለያያቸው ሲደርስ የሚያዝኑ በመሆኑ ይህንኑ ስሜት የሚገልፁባቸውን ግጥሞች ይገጥማሉ፡፡ አቶ አዬ ጦይብ (20/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) ሰማሁት ያሉትን የሚከተለውን ማሳያ ሊሆን የሚችል ግጥም ነግረውኛል፡፡

ይጋግሩ ጀመር ቀጭን ቀጭን ቂጣ

የዛሬን እደሩ የሚል ሰው በመጣ፡፡

የሚጋገረው ቂጣ የመሸኛ መሆኑ የሚታወቅ በመሆኑ አጃቢዎች ጋገራውን ሲያዩ መለያየታቸው ሀዘንን ይፈጥርባቸዋልና የዛሬን እደሩ የሚለን ሰው በተገኘ ብለው ለተጨማሪ ቀናት መክረም መፈለጋቸውን ይገልፃሉ፡፡

በእለቱ ዶሮ ተሰርቶ አጃቢዎች በጥሩ ሁኔታ እራት ከተጋበዙ በኋላ የመውጫ ዳቦ ፊት ፊታቸው ገበታ ላይ ይደረግላቸዋል፡፡ በአራተኛው ቀን ጠዋት ቁርስ ከተበላ በኋላ አብዛኛዎቹ አጃቢዎች ወደየቤታቸው የሚሄዱ ሲሆን ሚዜዎችና ጥቂት አጃቢዎች ብቻ በመቅረት በዚያው እለት ማታ ለመልስ ስነ ስርዓት ወደ ሙሽራዋ ቤተሰብ ቤት ይሄዳሉ (አቶ አሕመድ ሲራጅ፣ 28/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

#### 6.4.4.4. የመልስ ስነ ስርዓት

በሰርጉ አራተኛ ቀን ሙሽሮች ለመልስ ስነ ስርዓት ወደ ሙሽራዋ ቤተሰብ ቤት የሚመለሱ ሲሆን የሚገቡት ምሽት ላይ ነው፡፡ ቤተሰብ፣ ለሰርጉ መጥተው የከረሙ ዘመዶችና ልጆቻችን ይመጣሉና ተቀበሉልን ተብለው የተጠሩ ጐረቤቶች ይቀበሏቸዋል፡፡ ሙሽሮች ለመልስ መጥተው አራት ቀን አድረው የሚሸኙት በአምስተኛው ቀን ጠዋት ነው፡፡ ሙሽራው ለመልስ ይዞ የሚመጣው አጃቢ ቁጥር ተወስኖ አስቀድሞ የሚነገረው ሲሆን ሚዜዎቹን፣ ወንድሞቹን፣ የቅርብ ዘመዶቹንና ጓደኞቹን ይዞ ይመጣል፡፡ ከነውር ስለሚቆጠር የሙሽራው እናትና አባት ለመልስ አይሄዱም (ወ/ሮ ፋጡማ ሁሴን፣ 8/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ለመልስ ስነ ስርዓት መጠኑ አነስ ይበል እንጂ ለሰርግ ስነ ስርዓት የሚዘጋጅ አይነት ምግብ ይዘጋጃል፡፡ ሙሽሮቹ የገቡ እለት እና የመሸኛቸው ቀን ዋዜማ እራት ላይ ዶሮ፣ አሊጣጦና ወቃሊሞ ይቀርብላቸዋል፡፡ እነዚህ ምግቦች የመቀበያና የመሸኛ ምግቦች ናቸው፡፡ ሙሽሮች በገቡ ማግስት ጠዋት ፍየል ይታረዳል፡፡ ከዚያ በኋላ ስጋው ካለቀ እንደ አቅም ተደግሞ እየታረደ ጥሩ ጥሩ ምግብ እየተዘጋጀ ይጋበዛሉ፤ በዶሮ፣ በወቃሊሞ፣ በዝልዝል ስጋ፣ በማርና በቅቤ ይስተናገዳሉ፡፡ ሙሽሮች በገቡ ማግስት ማለትም በሁለተኛው ቀን ጠዋት ለቁርስ ቅቤና በርበሬ የተቀባ አነባበሮና በማር የታሸ የገብስ ቆሎ ይቀርብላቸዋል፡፡ በሶስተኛው ቀን ጠዋት ገንፎ፣ በአራተኛው ቀን ደግሞ ፍርፍር ይቀርብላቸዋል፡፡ በሚሸኙበት በአምስተኛው ቀን ጠዋት ቤት ባፈራው ቁርስ ይሸኛሉ፡፡ ምሳና እራት

በታረደው ፍየል ጥሩ ምግብ እየተሰራ ይጋበዛሉ (ወ/ሮ ፋጡማ ሁሴን፣ 8/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ሙሽራዋ ስትመጣ በመሶብ ድፎ ዳቦ ይዛ የምትመጣ ሲሆን በማግስቱ ቡና ተፈልቶ ዘመዶችና የቅርብ ጐረቤቶች የሆኑ ባልቴቶች ቡና ጠጡ ተብለው ይጠሩና ዱዓ ተደርጐ ሙሽራዋ ያመጣችው ዳቦ ተቆርሶ ቡና ይጠጣል፡፡ በቃለ መጠይቅ ጊዜ በመረጃ ሰጪዎች መካከል ሙሽራ የበሰለ ምግብ ይዛ አትመጣም እና ድፎ ዳቦ ይዛ ትመጣለች የሚል የሀሳብ ልዩነት ተከስቶ የነበረ ሲሆን ጉዳዩን በቡድን ተኮር ውይይት ላይ በማንሳትና በማወያየት ሙሽራ ለመልስ ወደ ቤተሰቦቿ ቤት ስትሄድ ዳቦ መውሰዷን አብዛኛዎቹ የቡድኑ ተወያዮች ተስማምተውበታል (30/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቡድን ተኮር ውይይት)፡፡

የመልሱ ስነ ስርዓት ተጠናቅቆ ሙሽሮች ሲሄዱ ሙሉ ሆኖ የመጣ መሶብ ባዶውን አይመለስም በሚል ልማድ ምክንያት ዳቦ ተጋግሮ ሙሽራዋ ዳቦ ባመጣችበት መሶብ ተደርጐ ይላካል፡፡ ለሙሽራው ሚዜዎችም በመጠኑ ከፍ ከፍ ተደርጐ ዳቦ ይጋገርና ሲሄዱ በልብሳቸው ይቋጠርላቸዋል- የወገብ ዳቦ ይባላል (ወ/ሮ ፋጡማ ሁሴን፣ 8/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ሙሽሮች በገቡ በሶስተኛው ቀን በሰርጉ ቀን ታይቶ የተመለሰው ለሙሽራዋ እናትና አባት የመጣው ጥሎሽ ቀርቦ ይታያል፡፡ በመሆኑም በእለቱ ምሳ ከተበላ በኋላ ቡና ተፈልቶ ዘመዶችና ጐረቤቶች ይሰበሰቡና የሙሽራው ሚዜ ልብሱን አቅርቦ ያሳያል፡፡ ለሙሽራዋ አባት የመጣውን ልብስ “ይህ የአባታችን”፣ ለሙሽራዋ እናት የመጣውንም “ይህ የእናታችን” በማለት አንድ በአንድ ያሳያል፡፡ ከዚያ በኋላ ዱዓ ይደረግና ሚዜው ዱዓውን ከተቀበለ በኋላ ቤተዘመዱ ልብሱን አንስተው ወደ ጓዳ ያስገባሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ቡናው ይጠጣል (ወ/ሮ ፋጡማ ሁሴን፣ 8/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ምልከታ ባደረግሁበት የመልስ ስነ ስርዓት ላይ ለሙሽራዋ አባት ጋቢ፣ ሸርጥ፣ ሸሚዝ፣ ጫማ፣ ኮፍያና ሽቶ፤ ለሙሽራዋ እናት ደግሞ ድሪያና ጉርጉራ፣ ቀሚስ፣ የውስጥ ልብስ፣ ጫማ፣ ሽቶና ሰንደል መጥቶ ሲታይ ተመልክቻለሁ (29/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡



ፎቶግራፍ 25. ለሙሽራ እናትና አባት የመጣ ልብስ ሲታይ

በአራተኛው ቀን ማታ ሙሽራው የሙሽራዋን ቤተሰብ የሚዘይር ሲሆን ይህ ስነ ስርዓት አዲሱ ሙሽራ ከሙሽራዋ ቤተሰብ ጋር የሚቀላቀልበት ዋና ስነ ስርዓት ነው፡፡ በዚህ ቀን ታርዶ የመቀበያውን ያህል የመሸኛ ምግብ ይዘጋጅና ማታ ሙሽሮቹ እስከ ሚዜዎቻቸውና አጃቢዎቻቸው እራት ይጋበዛሉ፡፡ ከዚያ በኋላ የሙሽራዋ እናትና አባት፣ አያቶች፣ አክስቶች፣ አጎቶች፣ እና ሌሎች የቅርብ ዘመዶች በተወሰነ ቦታ ይቀመጡና አንድ ሚዜ ቀድሞ፣ ከዚያም ሙሽራውና ሙሽራዋ ተከትለው፤ አንድ በአንድ እየሄዱ ጉንበስ ብለው ጉልበት እየሳሙ ይዘይራሉ፤ ዱዓም ይደረግላቸዋል (ወ/ሮ ፋጡማ ሁሴን፣ 8/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የሚከተለው ዱዓ ምልከታ ባደረግሁበት የመልስ ስነ ስርዓት ላይ በወ/ሮ አሚና መሐመድ መሪነትና በሙሽራውና በተሰበሰቡ ሰዎች ተቀባይነት ለሙሽራው የተደረገ ዱዓ ነው (30/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

| <u>ዱዓ አድራጊ</u> | <u>ተቀባዮች (ሙሽራውና ሌሎች የተሰበሰቡ ሁሉ)</u> |
|---|---|
| ያብጅልህ | አሚን |
| ተዋደዱ | ” |
| ውለዱ | ” |
| ክበዱ | ” |

ክበሩ ”

አግኙ ”

አትገኙ ”

ስጡ ”

አትሰጡ ”

አላህ ያዋድዳችሁ ”

ያንድ ዱር እሸት ”

ያንድ ላም ወተት ”

አላህ ያርጋችሁ ”

እንደ ባህር ማሽላ ”

በሽፍን ”

እንደ እንቁላል ”

በድፍን ”

ምንም ሳያገኛችሁ ”

ኑሮ የምትይዙ “

አላህ ያርጋችሁ ”

አሏሁ መሰሊ ወሰሊም አላ ሰይድና መሐመድ ወአላ አሊ ሰይድና መሐመድ

በዱዓው ውስጥ የአንድ ዱር እሸት፣ የአንድ ላም ወተት የሚሉ ትዕምርታዊ ቃላት ይገኛሉ፡፡ ባንድ ዱር እሸትነት እና በአንድ ላም ወተትነት መካከልም ልዩነት የለም፡፡ በመሆኑም ዱዓው በእነዚህ ቁሶች መካከል ያለው የግንኙነት መልክ ለተጋቢዎቹ እንዲሆን

በመመኘት የተደረገ ነው፡፡ "እንደ ባህር ማሽላ በሽፍን እንደ እንቁላል በድፍን ምንም [አያገኛችሁ]" የሚለው የዱዓ ክፍልም ሙሽሮች ለአደጋ ሳይጋለጡ ተከልለው፣ ተሸፍነው፣ ተጠብቀው እንዲቆዩ በመመኘት የተደረገ ነው፡፡

ሙሽራው የሙሽራዋን እናት ጉልበት ሲስም ተቋጭቶ የተሰፋ ጋቢ ትከሻው ላይ ጣል ታደርግለታለች፡፡ በዚህ መልኩ ሙሽሮች ከአጃቢዎቻቸው ጋር በሙሽራዋ ቤተሰብ ቤት ለአራት ቀናት ያህል ከቆዩ በኋላ በአምስተኛው ቀን ጠዋት ቁርስ ይጋበዙና ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ (ወ/ሮ ፋጡማ ሁሴን፣ 8/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

### 6.4.4.5. የጉጆ መውጫ ስነ ስርዓት

የጉጆ መውጫ ስነ ስርዓት ከመልስ ስነ ስርዓት በኋላ የሙሽራዋ ቤተሰብ ዝግጁ በሚሆንበት ጊዜ የሚያከናውነውና የሙሽራው ቤተሰብም የሚሳተፍበት፤ የሙሽሮቹ ጉረቤቶች ተጠርተው ለአዲሶቹ ተጋቢዎች ዱዓ የሚያደርጉበት ስነ ስርዓት ነው፡፡ የሙሽራዋ ቤተሰብ ለጉጆ መውጫ ወደ ሙሽራዋ ቤት ሲሄድ የሙሽራዋ አጎቶችና አክስቶች ለሙሽራዋ የሚሰጥ ልብስ፣ ብር፣ ጭነት እህል ይዘው ቤተሰቡን ተከትለው ይሄዳሉ (ወ/ሮ ፋጡማ መሐመድ፣ 9/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የሙሽራዋ ቤተሰብ አባላት የጉጆ መውጫ ስነ ስርዓቱን የሚያከናውኑት በጥንዶቹ ቤት ሲሆን የሚሄዱት ስነ ስርዓቱ በሚከናወንበት ቀን ዋዜማ ምሽት ላይ ነው፡፡ ሲሄዱም ለስነ ስርዓቱ ምግብ ማዘጋጃ የሚሆን የተፈጨ የእንጀራ እህል፣ የተፈጨ ሽሮና በርበሬ፣ ድልህ፣ ቅቤ፣ ዘይትና ቅመማ ቅመም፣ ሙክት እና ድሮ ዳቦ ይዘው ይሄዳሉ፡፡ ማታውኑ በማግስቱ ለሚከወነው ስነ ስርዓት የሚጠሩ ጉረቤቶች ይጠራሉ፡፡ የተወሰደው ዳቦ በሚጠራው ጉረቤት መጠን ተቆራርሶ፤ ለእያንዳንዱ የጉረቤት ቤት ዳቦ፣ ድልህና ሽሮ በጨርቅ ተቋጥሮ እየተሰጠ በማግስቱ ምሳ ሰዓት እንዲገኙ ይነገራል፡፡ እራት ተበልቶ ካበቃ በኋላ የመጣው አህል ይቦካል፡፡ በማግስቱ ጠዋት የተቦካው ሊጥ ይጋገራል፡፡ ወንዶች የመጣውን ሙክት አርደው ምግብ ይዘጋጅና የተጠሩ እንግዶች ይስተናገዳሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ቡና ተፈልቶ ዱዓ ይደረግና ይጠጣል (ወ/ሮ ፋጡማ መሐመድ፣ 9/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡



ፎቶግራፍ 26. ለጐጆ መውጫ ዳቦ ሲጋገር



ፎቶግራፍ 27. ዳቦው በተጠሪዎች ቁጥር ልክ ሲቆረስ

የሚከተለው ዱዓ ምልከታ ባደረግሁበት የጐጆ መውጫ ስነ ስርዓት ላይ ከተደረጉ ዱዓዎች መካከል አንዱ ሲሆን በወ/ሮ ሀሊም ሁጤል መሪነት የተደረገ ነው (7/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

| ዱዓ አድራጊ | ተቀባዮች |
| --- | --- |
| ያአላህ ጌታዬ | አሜን |
| አላህ ያስደሳት | ” |
| አባቷንም እናቷንም አላህ ያቆይላት | ” |
| ደግሞ በደንብ የሚያዩዋት፣ የሚጫንላት፣ የሚደለደልላት አላህ ያርግላት | ” |
| ነቢይ መጀን ረሱል መጀን ጌታዬ | ” |
| የአማን ሰው ይበለን ጌታዬ | ” |
| እሷም ተደስታ | ” |
| እናቷም ተደስታ | ” |
| አባቷም ተደስቶ | ” |

ሀጃቸውን አላህ ያውጣው ”

የሚጠቃቀሙ ጌታዬ ”

የሚከባበዱ ”

አላህ ያርጋቸው ”

ፍሬ ትሁን ጌታዬ ”

አሏሁ መሰሊ ወሰሊም አላ ሰይድና መሐመድ ወአላ አሊ ሰይድና መሐመድ

በዱዓው ላይ "ደግሞ በደንብ የሚያዩዋት፣ የሚጫንላት፣ የሚደለደልላት አላህ ያርግላት" ተብሏል፡፡ ከጐጆ መውጫ በኋላ የሙሽራዋ ቤተሰብ ሙሽሪትን የሚያይበት ዋና ስነ ስርዓት የአምሮት ስነ ስርዓት ነው፡፡ ሙሽራዋ የሚያዩዋት፣ የሚጫንላት፣ የሚደለደልላት ትሁን ተብሎ ዱዓ የተደረገው ሙሽራዋን ለአምሮት ስነ ስርዓት ያብቃት፣ ልጅ ታግኝ የሚል ትርጉም አለው፡፡

ከሰርግ በኋላ የጐጆ መውጫ ስነ ስርዓት የሚከናወንበትን ጊዜ የሚያረዝሙ ምክንያቶች ወቅቱ የእርሻ ስራ የሚከናወንበት ወቅት መሆን፣ በአካባቢ የተለያዩ ማህበራዊ ስነ ስርዓቶች ክዋኔ መደራረብ፣ ሙሽራዋ የሄደችበት ቦታ ሩቅ መሆን፣ የአቅም አለመኖርና አቅም ለማግኘት የሚያስፈልግ ጊዜ፣ ወዘተ ናቸው፡፡ እነዚህ እንቅፋቶች በሌሉበት ሁኔታ የጐጆ መውጫ ስነ ስርዓት የሰርጉ ስነ ስርዓት በተከናወነ አጭር ጊዜ ውስጥ ሊከናወን ይችላል፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች የጐጆ መውጫ ስነ ስርዓት ሳይከወን ሙሽራዋ ካረገዘች የአምሮት ስነ ስርዓት የሚከወንበት ጊዜ ተጠብቆ በአምሮቱ ክዋኔ ማግስት የጐጆ መውጫ ስነ ስርዓቱ ይከወናል፡፡ ለአምሮቱ የተጠሩ ሰዎች ተጋብዘው ሲሄዱ ነገ ምሳ እንድትመጡ እየተባሉ ይጠራሉ፡፡ የምሳ ግብዣው የጐጆ መውጫ ግብዣ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህ የሚሆነው የሙሽራዋ ቤተሰብ ሁለት ጊዜ ወደ ሙሽሮቹ ቤት እንዳይመላለስና በአንድ ጊዜ ሁለቱንም ለማጠናቀቅ ሲባል ነው (ወ/ሮ ፋጡማ መሐመድ፣ 9/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በመቀላቀል ጊዜ የሰርግ ስነ ስርዓት ዋናውና ቀዳሚው የመቀላቀል ጊዜ መገለጫ ነው፡፡ የሰርግ ስነ ስርዓት እጮኛሞች ወደ አንድነት መምጣታቸውንና መጣመራቸውን ይፋ ማድረጊያና ማክበሪያ ስነ ስርዓት ነው፡፡ ጉፍታ መጫን ሙሽራዋ ካለፈ ደረጃዋ መለየቷን፣ ከልጃገረድነት ወደ ባለትዳርነት፣ ከአንድነት ወይም ከብቸኛነት ወደ ሁለትነት መሻገሯን ለመግለጽ የሚደረግ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው፡፡ የኒካህ ማሰር ስነ ስርዓት ተጋቢዎች በቃል የሚታሰሩበትና አንድነታቸው የሚፀናበት ስነ ስርዓት ነው፡፡ ሙሽራው ለሙሽሪትና ለቤተሰቧ አባላት ጥሎሽ መክፈሉና የሙሽራዋ ቤተሰብ መቀበሉ የመቀላቀል መገለጫ ነው፡፡ በሰርጉ ቀን ምሽት ሙሽራዋ የቤተሰቧን አካባቢ በመልቀቅ ኑሮን ለመጀመር ወደ ሙሽራው ቤተሰብና አካባቢ መሄዷና ከዚያ በኋላም በሄደችበት አካባቢ አዲስ ማህበራዊ ግንኙነትን መመስረቷ የመቀላቀል መገለጫ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሰርጉ ስነ ስርዓት ክዋኔ ያሉ በጋራ መመገብ፣ መዝፈንና የሙሽሮች ቤተሰቦች፣ ወዳጅ ዘመዶችና የአካባቢው ማህበረሰብም ሙሽሮቹን የክዋኔው ማዕከል በማድረግ መሳተፋቸውና ስጦታ መስጠታቸው የመቀላቀል መገለጫዎች ናቸው፡፡

ድህረ ሰርግ የሚከወኑ ስነ ስርዓቶች የባዲሼህ፣ የደመቅሁ፣ የመልስና የጉጆ መውጫ ስነ ስርዓቶች ሲሆኑ የመቀላቀያ ስነ ስርዓቶች ናቸው፡፡ የባዲሼህ ስነ ስርዓትን የመከወን ዋና ዓላማ ሙሽራዋ በሄደችበት የሙሽራው አካባቢ የሀገሩ አምላክ ይቀበላትና ኑሮዋ ይሰምር ዘንድ ዱዓ እንዲደረግላት ማስቻል ነው፡፡ ሙሽራዋ በሄደችበት አካባቢ አምላክ ተቀብሏት፣ ከባሏ፣ ከባሏ ቤተሰብና ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ተስማምታና ተዋድዳ መኖሯ ደግሞ የመቀላቀል መገለጫ ነው፡፡ የደመቅሁ ስነ ስርዓት በጨዋታ መልክ ጥምረትን፣ ውህደትን መግለጫ ስነ ስርዓት ነው፡፡ የመልስ ስነ ስርዓት ሙሽራው ከሙሽራዋ ቤተሰብ ጋር የሚቀላቀልበት የመጀመሪያ ስነ ስርዓት ነው፡፡ ሙሽሮቹ ለመልስ በሙሽራዋ ቤተሰብ ቤት በገቡ በአራተኛው ቀን ማታ ሙሽራው የሙሽራዋን ቤተሰብ የሚዘይርበት ስነ ስርዓት ቤተሰቡን በይፋ የሚቀላቀልበት ነው፡፡ በስነ ስርዓቱ ክዋኔ ላይ የሙሽራዋ እናት ለሙሽራው የጋቢ ስጦታ ማድረጓና ሙሽራው መቀበሉ መቀላቀልን መግለጫ ነው፡፡ የጉጆ መውጫ ስነ ስርዓት የተጋቢዎቹ ቤተሰቦች የሚቀላቀሉበት መሆኑና የተጋቢዎች ኑሮ እንዲጠነክር፣ እንዲሰምርና ተጋቢዎቹ ልጅ እንዲወልዱ ዱዓ የሚደረግበት መሆኑ ስነ ስርዓቱን የመቀላቀል መገለጫ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

ከሚከወኑ ስነ ስርዓቶች በተጨማሪ ሙሽራዋ በነገር መፍጃ ስነ ስርዓት ጊዜ የተላከላትን ልብስ የምትለብሰው ከሰርጉ ስነ ስርዓት ክዋኔ በኋላ መሆኑ ተጋቢዎች ወደ አንድነት መምጣታቸውን፣ በተለየ ደረጃ ላይ መሆናቸውንና በአዲስ ማንነት መገለጣቸውን ይገልፃል፡፡

ከሰርግ ስነ ስርዓት ክዋኔ በኋላ ሙሽሮች በአዲስ ማንነት ይገለጣሉ፡፡ ወንዱ በአባወራነት፣ ሴቷ ደግሞ በእማወራነት ሚና ወደ ማህበረሰቡ ይቀላቀላሉ፡፡ ሙሽራዋ ከሰርጓ ስነ ስርዓት በኋላ ከማግባቷ በፊት ከነበራት አለባበስ በተለየ ትለብሳለች፡፡ በመሆኑም ከማግባቷ በፊት ጥልፍ ያልበዛበት ቀሚስ የምትለብስ ሲሆን ካገባች በኋላ ባለ ጥልፍ ቀሚስ ትለብሳለች፤ ከማግባቷ በፊት የምትለብሰውን እጥፍ ካቴና ነጠላ በመተው ትልቅ ነጠላ ትለብሳለች፤ ከማግባቷ በፊት የማታጌጥበትን ትልቅ ጭልጭሌ ታደርጋለች፤ ፀጉሯንም ከማግባቷ በፊት የምትሰራውን ረፍረፎ የፀጉር ሹሩባ በመተው ስጥቂት ትሰራለች፡፡ ከሰርጉ በኋላ ያለ እርግዝናና ወሊድም የመቀላቀያ መገለጫዎች ናቸው፡፡



ፎቶግራፍ 28. የልጃገረድ አለባበስ



ፎቶግራፍ 29. ያገባች ሴት አለባበስ

## 6.5. የአርጐባ ብሄረሰብ የጋብቻ ስነ ስርዓት ክዋኔ ፋይዳ

የአርጐባ ብሄረሰብ የጋብቻ ስነ ስርዓት ክዋኔ ለከዋኞቹ የአሻጋሪነት፣ ማህበራዊ ኑሮንና የኢኮኖሚ አቅምን የማጠናከር፣ ስነ ልቡናን የማረጋጋት፣ የማስተማር፣ የተግባቦት፣ የማዝናናትና የማሞገስ ፋይዳዎች አሉት፡፡

**አሻጋሪነት፣**

የሰርግ ስነ ስርዓት ትዳር የሌለውን ሰው ወደ ባለትዳርነት ያሻግራል፣ መሻገርን ይፋ ያደርጋል፣ ትዳር ከመያዝ በፊት የነበረን ሚና ይቀይራል፡፡ የሰርግ ስነ ስርዓት ካለው የአሻጋሪነት ሚና አንፃር ዘርን ማስቀጠያም ነው፡፡

**ማህበራዊ ፋይዳ፣**

የሰርግ ስነ ስርዓት ለከዋኞቹ ከፍተኛ ማህበራዊ ፋይዳ አለው፡፡ የጋብቻ ስነ ስርዓት ሰዎችን በአንድ ያገናኛል፤ ዘመድ ወዳጆች ግንኙነታቸውን ያጠናክሩበታል፤ የማይተዋወቁ ይተዋወቁበታል፡፡ በየስነ ስርዓቱ ላይ በጋራ አብሮ መመገቡ የሚያስገኘው ማህበራዊ አንድነት አለው፡፡ በተጨማሪም ሚዜና አጃቢ መሆኑ፣ የሰርጉን ቤትና አጥር ማደሱን፣ እህል ማበጀቱን፣ እንጨት መስበሩን፣ ምግብ ማዘጋጀቱን፣ ዳስ መጣሉን፣ የሰርጉ ቀን እድምተኛውን ማስተናገዱን፣ ወዘተ በጋራ ማከናወኑ የማህበረሰቡን ማህበራዊ አንድነት ያጠናክራል፡፡

**ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ፣**

የሰርግ ስነ ስርዓትን እህል በሚደርስበት ጊዜ ማድረጉ፣ ሚዜዎችና አጃቢዎች ለሙሽሮች ስጦታ ማድረጋቸው፣ ተጠሪዎች ለሙሽራና ለሰርግ ደጋሾች የገንዘብና የዓይነት ስጦታ ማድረጋቸው፣ ሙሽራ ለመደገሻ የሚሆን ገንዘብ ለሙሽራዋ ቤተሰብ መስጠቱ፣ ወዘተ ለሰርግ ደጋሾችና ስጦታውን ለሚቀበሉ ሰዎች ኢኰኖሚያዊ ጠቀሜታን ያስገኛል፡፡

**ከአደጋ የመጠበቅ ስሜትን የመስጠት ፋይዳ (ስነ ልቡናዊ ፋይዳ)፣**

የሰው ልጅ በተፈጥሮው ከአደጋ መጠበቅን ይፈልጋል፡፡ በአርጐባ ባህል ሰዎች ከአደጋ የተጠበቁ እንዲሆኑ ማድረጊያ ዋና መንገድ ዱዓ ነው፡፡ የባዲሼህ ስነ ስርዓት ደግሞ ዱዓ እንዲደረግ ሲባል ብቻ የሚከወን ስነ ስርዓት ሲሆን ሙሽራዋ በሄደችበት የባሏ አካባቢ የሀገሩ ሼህ እንዲቀበላት፣ በዚህ ምክንያትም ኑሮዋ እንዲሰምር፣ አደጋ እንዳያገኛት፣ ፍቅር እንዳታጣ ዱዓ የሚደረግበት ነው፡፡ ይህ እና መሰል ስነ ስርዓቶች መከወናቸው ሙሽራዋ ከአደጋ የመጠበቅ ስሜት እንዲያድርባት ያደርጋሉ፡፡

**የማስተማር ፋይዳ፣**

የቆዳ ማንጠፊያ ስነ ስርዓት ተከናውኖ ከሴቷ ቤተሰቦች የእሺታ መልስ ከተገኘ በኋላ የሰርጉ ስነ ስርዓት የሚከናወንበትን ቀን ረዘም አድርጐ መቅጠሩ የታጨችው ልጅ እወቀትና የህይወት ስልጠና እንድታገኝ ያስችላታል፡፡

**የተግባቦት፣ የማዝናናትና የማሞገስ ፋይዳ፣**

በሰርግ ስነ ስርዓት ላይ የሚከወኑ ዘፈኖች ከአንድ የህይወት ደረጃ ወደ ሌላው መሸጋገርን፣ የተሻለ ስጦታ መጠየቅንና ጥልቅ ፍቅርን እንዲሁም ዘመናዊነት በማህበረሰቡ ዘንድ ያመጣውን የባህል ለውጥ በመግለጽ መልዕክት ማስተላለፊያ፣ ሙሽሮችን ማሞገሻ፣ ሰርግን ማድመቂያና መዝናኛም ናቸው፡፡

## 6.6. የአርጐባ ብሄረሰብ የጋብቻ ስነ ስርዓት ክዋኔ ለውጥና ቀጣይነት

በአርጐባ ብሄረሰብ የጋብቻ ስነ ስርዓት የክዋኔና የመዋቅር ለውጦች ተከስተዋል፡፡ በዚህ ክፍል በስነ ስርዓቱ ላይ የተከሰቱ የክዋኔና የመዋቅር ለውጦች እና ያልተለወጡ ጉዳዮች ምንነት ይቀርባሉ፡፡

### 6.6.1. የክዋኔ ለውጦች

በስነ ስርዓቱ ውስጥ የተከሰቱ ለውጦች በቀጥተኛ ምክንያት ማለትም ባህል በራሱ ሂደት በመሆኑ ምክንያት፣ በዘመናዊነት፣ የሌላን ባህል በመቀበልና በመከወን፣ በኢኮኖሚ ጫና እና ሆን ተብሎ በሚደረግ ለውጥ ምክንያት የተከሰቱ ናቸው፡፡

#### 6.6.1.1. ቀጥተኛ ለውጦች

ባህል ሂደት በመሆኑ ምክንያት በብሄረሰቡ የጋብቻ ስነ ስርዓት ክዋኔ ላይ በጋብቻ ዓይነትና መስፈርት፣ በእጮኝነት ጊዜ ባለ የግንኙነት መልክ፣ በሚዜ መረጣ፣ ሚናና ቁጥር፣ በወግ ዓይነትና መጠን እና በክዋኔ ጊዜና ቦታ ላይ ለውጥ ተከስቷል፡፡

**በጋብቻ ዓይነት ላይ የተከሰተ ለውጥ፣**

በአርጐባ ብሄረሰብ ዘንድ በአሁኑ ጊዜ በዋናነት በሶስት መንገድ ጋብቻ ይከናወናል፡፡ የመጀመሪያው የተጋቢ ቤተሰቦች ልጅህን ለልጄ ተባብለው ልጆቻቸውን የሚድሩበት

መንገድ ሲሆን ነባሩና አሁንም የሚተገበር የጋብቻ አይነት ነው፡፡ ሁለተኛና ሶስተኛው መንገዶች ከጊዜ በኋላ የመጡ ሲሆኑ ተጋቢዎች በራሳቸው ተዋድደው ወንዱ አግቢ በራሱ ላጫት ልጅ ቤተሰብ ሽማግሌ ልኮ ጋብቻ የሚመሰረትበት እና ተዋድደው በፈቃደኝነት የስምምነት ጠለፋ ተደርጎ አብረው መኖር የሚጀምሩበትና በኋላም በሴቷ ቤተሰብ መልስ የሚጠሩበት መንገዶች ናቸው፡፡ ጠለፋ አልፎ አልፎ ብቻ ይከሰታል፡፡

ተጋቢዎች በትምህርት፣ በስራ ቦታና በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ተዋውቀው ለጋብቻ የመስማማቱ ሁኔታ እየሰፋ በመምጣቱ ከፍ ሲል በሁለተኛነት በተጠቀሰው የጋብቻ ዓይነት መሰረት ወንዱ በራሱ ሽማግሌዎችን መርጦ መላክ የተለመደ ጉዳይ ሆኗል፡፡ ከዚህ በታች ጋብቻቸው በቅርብ ጊዜ የተከናወነና በራሳቸው ተዋውቀውና ወንዱ በራሱ ሽማግሌ በመላክ ጋብቻ የመሰረቱ ሰዎች ምስክርነት ቀርቧል፡፡

> የተዋወቅነው መጀመሪያ እዚሁ አየኋት፡፡ የማን ልጅ ናት እያልኩ ሳጠያይቅ ባጋጣሚ አጎቷ ጓደኛዬ ነበር፡፡ ከእሱ ጋር ያለውን ሁኔታ አወራን፡፡ ስለሷ ጠየቅሁት አወራኝ፡፡ ግን ሳንተዋወቅ ወደ አረብ ሀገር ሄደች፡፡ እዚያ ሆና በፌስ ቡክ አወራን፡፡ ተግባባን፡፡ ከሁለት ዓመት በኋላ እኔ ቤተሰቦች ጋር ተደገሰና ደረሶች ተወክለው እዚያ ኒካሁ ታሰረ፡፡ ስትመጣም የተቀበልኳት እኔ ነኝ፡፡ ከዚያ በኋላ በአስራ አምስተኛው ቀን ሽማግሌ ተልኮ ከወር በኋላ ሰርግ ተደገሰና አብረን መኖር ጀመርን (አቶ ዩሱፍ ኢብራሂም፣ 26/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

> ዘመዳሞች ነበርን፡፡ በዝምድና ቀድመን እንተዋወቅ ነበር፡፡ የአክስቴ አብሱማ ነች፡፡ እኔ የእናቷ የአጎት ልጅ ነኝ፡፡ በዚህ ዝምድናችን ምክንያት አልፎ አልፎ እንጠያየቅ ነበር፡፡ አየኋትና ይህችን ልጅ ባገባ ያዋጣኛል ብዬ አሰብኩ፡፡ ተፈላለግንና በስልክ እየተገናኘን አወራን፡፡ ከተግባባን በኋላ ሽማግሌ ላክሁኝና ለመጋባት በቃን፡፡ … ሁለታችን መግባባታችንን ስላወቁ ሁለቱ ከተግባቡ ብለው ተስማሙ፡፡ ነገር ከተፈጀ በኋላ አልፎ አልፎ እንገናኝ ነበር፡፡ ዘመዳሞች ስለሆንን በእህቴ ቤት እንገናኝ ነበር፡፡ ስንወጣ ተራ በተራ እንወጣለን ሰው እንዳያየን (አቶ አሊ መሐመድ፣ 21/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ቀደም ባለው ጊዜ ሴት ልጅ የምታገባውን ሰው የመምረጥ እድሏ በጣም ጠባብ ነበር፡፡ በስለላ ጊዜ የእርሷ ስሜት ምን እንደሆነ የሚታይ ቢሆንም በቤተሰብ ጫና ወይም ከቤተሰብ ምርጫ መውጣት እንደ ትልቅ ነውር የሚቆጠር በመሆኑ ምክንያት አብዛኛውን ጊዜ ቤተሰቧ የመረጠላትን ሰው ታገባለች፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን ከላይ በተገለፀው መንገድ ይህ አይነቱ ጋብቻ ሲከወን ተጋቢዎች በራሳቸው የመተዋወቅ እድሉን እያገኙት በመሆኑ ሴቷ የወደደችውንና የፈቀደችውን ወንድ የማግባት ሰፊ እድል አላት፡፡ የምታገባውን ወንድ ከስራው፣ ካለው ሀብትና ከመልከ መልካምነቱ አንፃር መዝና ለጋብቻ ትመርጣለች፡፡ ይህን አይነቱን የጋብቻ ሁኔታና ሴቷ የምታገባውን ሰው መምረጧን በተመለከተ አቶ አብዱልቃድር መሐመድ ሰዒድ (9/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) ያላቸውን ሀሳብ በሚከተለው መልኩ ገልፀዋል፡፡

> የዱሮ ልጅ አባቱ ሲያጋባው እከሊትን እፈልጋለሁ እከሊትን አልፈልግም የለም፡፡ የተደረገለትን እሺ ብሎ ማግባት ነው፡፡ እኔ ራሴ ሳገባ የሰርጌ ቀን ነው ያየኋት፡፡ ያሁኑ ሴቷም እገሌን ነው የምፈልገው አለች፡፡ እናትና አባትኮ እሷ እምቢ አለች እያለ እንደ ትንሽ ልጅ እየሆነ ነው፡፡ የወለድኳት ልጅ ከኔ በላይ አትሆንም፡፡ ሰዉ ነው ያባለገው ነው የምለው እንጂ ከጊዜው ነው አልልም፡፡ የወለድኳት ልጅ እኔ ካልሰጠኋት የት ታውቀዋለች ደህናና መጥፎውን? እኔ ብዙ ጠለቅ ብዬ የማስበው አለ፡፡ የቤተሰቡ ዘር ምንድን ነው? በኋላ ምን ጥግስ አላት? አንሺስ ማን አለ? ብትወልድ? ከዘርም ከሁሉም እመርጣለሁ፡፡ እሷ በገበያም በምንም ያየችው ሰውነቱን ብቻ ነው፤ እሱም ቁመናዋን ነው ያየው፡፡ ምን እንደሆነች አያውቅም፡፡ ተጋቡ፡፡ ያገኘሁሽ ከንዲህ ቦታ ነው ሂጂ ቢላትም ምን አለ? ብትወድቅ አንሺ የላትም፡፡ እየመሰላቸው ነው፡፡ ዞሮ ዞሮ አባት አይጨክንም እንጂ፡፡ እሱ ማንን አይቶ ይፈራል፡፡ ለማንኛውም መወቀሻ መኖር አለበት፡፡

በስምምነት ጠፍቶ አብሮ መኖር መጀመርም በቅርብ ጊዜ መከወን የጀመረ ሲሆን የሴቷን ቤተሰብ የሚያስቆጣና ግጭት የሚያስነሳ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ሁኔታ ሲፈጠር የወረዳው የሸሪያ ፍ/ቤት ቃዲ ወደ ሴቷ ቤተሰብ በመሄድ በአስቸኳይ ኒካህ እንዲታሰር ይመክራሉ፡፡

ከጋብቻ በፊት የሚደረግ ያታዊ ግንኙነት ንጽህና የጐደለው "ሀራም" እንደሆነ ስለሚታመን ይህ እየታወቀ ጊዜ ከማሳለፍ በፍጥነት ኑካሁ እንዲታሰር ይፈለጋል፡፡ ምንም እንኳን በሴቷ ቤተሰብ ዘንድ ቅሬታን የሚፈጥር ቢሆንም የሀይማኖት አባቶችና ሽማግሌዎች በመካከል ገብተው ነገሩን በማርገብና ቤተሰቡን በማግባባት ኒካሁን ተጋቢዎቹ በሌሉበት በወኪል እንዲታሰር ያደርጋሉ፡፡ ቤተሰብ አሻፈረኝ ቢልና በዚህ ባይስማማ የሀይማኖት አባቶች ሶስት ጊዜ እየተመላለሱ ከጠየቁ በኋላ በራሳቸው ኃላፊነት ኒካሁን የሚያስሩበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ከጊዜ በኋላ የሴቷ ቤተሰብ ደግሶ መልስ ይጠራና እርቅ እንዲሆን ይደረጋል (ሼህ ጧሂር ኑሬ፣ 22/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ በመሆኑም ቤተሰብ የሚደግሰው ድግስ የመልስ ዓይነት በመሆኑ በዚህ መልኩ ጋብቻ ሲከናወን የሰርግ ስነ ስርዓት ቀረ፤ በዚህ ምክንያትም ቅድመ ሰርግ የሚከወኑ ስነ ስርዓቶችም ቀሩ ማለት ነው፡፡

### በጋብቻ መስፈርት ላይ የተከሰተ ለውጥ፣

አርጐባነት ዋና የጋብቻ መስፈርት ሆኖ መቅረቡ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መጥቶ የብሂረሰቡ አባላት በጉርብትና አብረዋቸው ከሚኖሩና በትምህርትና በሌሎች ምክንያቶች ወደ አካባቢው ከሚመጡ አርጐባ ያልሆኑ ሰዎች ጋር በጋብቻ መዛመድ ጀምረዋል፡፡ በመስክ ቆይታዬ ይህን ዓይነቱን ጥምረት ለመመልከት ችያለሁ፡፡ ይህ ዓይነቱ ጋብቻ ሲከናወን ሴቷ ከአርጐባ ውጭ አግብታ ወደ ባሏ አካባቢ ከምትሄድ ይልቅ ወንዱ አግብቶ ቢያመጣ ይመረጣል፡፡ የመጣችው ሴት ወደ አርጐባዎች አካባቢ መምጣቷ በሂደት በባህሉ ታንፃ አርጐባ ትሆናለች ተብሎ ይታመናል፡፡ የሴት የጋብቻ እድሜም አስራ ስምንት ሆኗል፡፡

### በእጮኝነት ጊዜ ያለ የግንኙነት መልክ ላይ የተከሰተ ለውጥ፣

ቀደም ባለው ጊዜ እጮኛሞች የሚገናኙበትና አብረው የሚሆኑበት መንገድ አልነበረም፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን ትጭጭት የተካሄደው በቤተሰብ ሆኖ ተጋቢዎቹ ቀደም ሲል የማይተዋወቁ ቢሆኑ እንኳን ከሰርጉ ቀን በፊት ተገናኝተው ይተዋወቃሉ፡፡ ኒካህ የሚታሰረው የኤች. አይ. ቪ. ምርመራ ውጤት ከታየ በኋላ በመሆኑም ምርመራውን ለማድረግ ተደዋውለው ይገናኛሉ፡፡ በራሳቸው የተገናኙ ሲሆኑም በእጮኝነት ጊዜያቸው ተገናኝተው የሰርጋቸውን ሁኔታ ተወያይተው የሚያስተካክሉት ራሳቸው ናቸው፡፡

### የሚዜ መረጣ፣ የሚዜና የአጃቢ ሚናና የሚዜ ቁጥር ላይ የተከሰተ ለውጥ፣

ቀደም ባለው ጊዜ ሚዜ የሚመረጥበት መስፈርት መዋደድና አብሮ ማደግ ነበር፡፡ ይህ መስፈርት አሁንም ጥቅም ላይ እየዋለ ቢሆንም ነገር ግን በአብዛኛው የሚዜ መረጣ የሚደረገው የቅርብ ጊዜ ትውውቅንና ጓደኛነትን መሰረት በማድረግ ሆኗል፡፡ የመልክና የቁመና ሁኔታ ሚዜን ለመምረጥ መመዘኛ ሆኖ ጥቅም ላይ እየዋለ ሲሆን ሚዜ የሚመረጠውም ሰርጉ ሲደርስ ነው፡፡ የሚዜዎች ሚና ላይም ለውጥ የተከሰተ በመሆኑ በየጊዜው ከፍ እያለ በመጣው የኑሮ ውድነት ምክንያት ሚዜዎች ድግስ ደግሰው ማብላታቸውና ድርጊቱን እንደ ኋላ ቀርነት መገለጫ በመውሰድ የወንዱ ሚዜ ሙሽራዋን ተሸክሞ መውሰዱ ቀርቷል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የወንድም ሆነ የሴት ሚዜዎች ለሙሽሮቹ የገንዘብ ወይም የዓይነት ስጦታ ያደርጋሉ፡፡ የሙሽራው ሚዜዎች በሙሽራዋ ቤተሰብ ቤት ሽልሙን ብለው ያገኙትን ብር ለሙሽራዎቹ የሚሆን ስጦታ ይገዙበት የነበረ ሲሆን አሁን ግን ለራሳቸው ለስላሳ መጠጥና ጫት ይገዙበታል፡፡ በተጨማሪም የሚዜዎች ቁጥር በከተሞች እንደሚደረገው ከሁለት ወደ አራትና ስድስት ከፍ ብሏል፡፡ አጃቢዎች የገንዘብ ስጦታ ለሙሽራው ያደርጉ ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን ብሩን አዋጥተው ለራሳቸው ጫትና ለስላሳ መጠጥ ገዝተው ከምሳ በኋላ ሙሽራው እስኪወጣ ድረስ ባለው ጊዜ ጫት ይቅማሉ፡፡ የሴት ሚዜዎች በሰርግ ቀን ማታ ሙሽሮቹን ተከትለው መሄዳቸው እንደ ነውር የሚታይ ቢሆንም አጥኚዋ ምልከታ ባደረገችበት የሰርግ ስነ ስርዓት ላይ ግን ተከትለው መሄዳቸውን ተመልክቻለሁ (24/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

### ወግ ላይ የተከሰተ ለውጥ፣

የወግ ዓይነትና መጠን ጨምሯል፤ ሙሽራው ከሙሽራዋ ውጪ ለሙሽሪት ወላጆች፣ አያቶችና ለሚዜዋ ከሚሰጠው ወግ በተጨማሪ በአሁን ጊዜ ስጦታው ለሙሽራዋ ሴት የቤተሰብ አባላትና ዘመዶችም ጭምር ማለትም ለእህቶች፣ ለአክስቶች፣ ለአጐትና ለወንድም ሚስቶች፣ ወዘተ ሆኗል፡፡ በተጨማሪም ወግ የሚገዛው ሙሽራው ራሱ መርጦ መሆኑ ቀርቶ ሙሽሮቹ ተገናኝተው ይገዙና ሙሽራው ይዞ ይሄዳል ወይም ብሩን ይልክና ሙሽራዋ ከጓደኞቿ ጋር መርጣ ገዝታ ወደ እርሱ ትልካለች፡፡

**የክዋኔ ጊዜና ቦታ ላይ የተከሰተ ለውጥ፣**

በአሁኑ ጊዜ በሰርጉ ቀን የሚከወነውን የጉፍታ ስነ ስርዓት በሰርጉ ቀን ጊዜ ይጣበባል በሚል ምክንያት በሰርጉ ዋዜማ መከወን፣ ሙሽራው ሙሽራዋ ቤት የሚደርስበትን የጀምበር መጥለቂያ ሰዓት ቀደም በማድረግ ዘጠኝና አስር ሰዓት መድረስና (በመንገድ ላይ የፎቶግራፍና የሽርሽር ስነ ስርዓት ማድረግ እየተለመደ በመምጣቱ ጊዜ ለማግኘት ሙሽራ በምሳ ሰዓትም ሊገባ ይችላል) በሰርጉ ሶስተኛ ቀን ይከወን የነበረውን የባዱሼህ ስነ ስርዓት በሰርጉ ማግስት መከወን የተለመደ ሲሆን በጐረቤት ቤት ይዘጋጅ የነበረው የጫጉላ ቤት አሁን በሙሽራው ቤተሰብ ቤት ሆኗል፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩ ለውጦች በተጨማሪ በአካባቢው የሚሰሩ ቤቶች ባለሁለት ደጅ አፍ መሆናቸው እየቀረ መምጣቱን ተከትሎ አማች በአንድ በር ገብቶ በሌላው መውጣቱ ቀርቷል፤ የቆዳ ማንጠፍ ስነ ስርዓት በአብዛኛው ወይደል የማይነጠፍበት ሆኗል፡፡

6.6.1.2. ዘመናዊነት ያስከተለው ለውጥ

በብሄረሰቡ የጋብቻ ስነ ስርዓት ክዋኔ ላይ ዘመናዊነት በክዋኔ፣ በቁሳዊ ባህልና ምግቦች ዓይነት ላይ ለውጥ አስከትሏል፡፡

**ዘመናዊነት በክዋኔ ላይ ያስከተለው ለውጥ፣**

በአሁኑ ጊዜ የሰርግ ጥሪ ዘመናዊ የጥሪ ወረቀት በማሳተምና በመበተን፣ ወረቀት መስጠት ያልተቻለውን ወይም ሩቅ የሆነውን ደግሞ ስልክ ደውሎ በመጥራት እየተከናወነ ይገኛል፡፡ ቤት የሚዋበው አፈርና የከብት አዛባ በመለቅለቅ መሆኑ ቀርቶ ቀለም በመቀባት ሆኗል፡፡ ወለሉም ኘላስቲክ ምንጣፍ ይነጠፍበታል፡፡

ዘመናዊ መዋቢያዎችን የመጠቀሙ ልማድ በአካባቢው እየተስፋፋ በመምጣቱ ምክንያት ብቸኛ የሴቶች ውበትን የመጠበቂያ መንገድ የነበረው የወይባ ጭስ ተተግባሪነቱ እየቀነሰ ይገኛል፡፡ በዚህ ምክንያት በአብዛኛው የአርጐባ ቤት ይገኝ የነበረው የመሞቂያ ጉድጓድ፣ አጐበርና መሞቂያ ጐንደሬ እየጠፉ ነው፡፡

በጋቸኔ ዘመናዊ የሙዚቃ ማጫወቻ ቴኘ ሪከርደሮች በአካባቢው ከመስፋፋታቸው ጋር በተያያዘ በሰርግ ቀን ሙሽራ ከመምጣቱ በፊት የሙሽራዋ አጃቢዎች ሙሽራዋን በመያዝ

የሚከውኗቸው ዘፈኖች ቀርተው በቦታቸው በቴፕ ሪከርደር የሚከፈቱ ዘፈኖች፣ ነሺዳና መንዙማዎች ተተክተዋል፡፡ ዘፈኖቹ የመከወን እድል የሚያገኙት መብራት ሲጠፋና ቴፕ ሪከርደር ማጫወት ሳይቻል ሲቀር ነው፡፡ በመሆኑም በመስክ የሰበሰብኳቸው የሰርግ ዘፈን ግጥሞች በገጠር ቀበሌዎች ሲከወኑ ያገኘኋቸውና በጋቸኔ ደግሞ መብራት ጠፍቶ በነበረበት ጥቂት ጊዜ ሲከወኑ ያገኘኋቸው ናቸው፡፡ ሙሽራ ከመጣ በኋላ የሙሽራዋ መውጫ ሰዓት ሲደርስ የሚከወኑ የሰርግ ዘፈኖች አልፎ አልፎ ይከወናሉ፡፡

ለሙሽራዋና ለተከታዮቿ በቅሎ ማቅረብ ቀርቶ ሰርገኞች በመኪና፣ በሞተር ሳይክልና በባጃጅ ዘመናዊ መጓጓዣዎች ይጓጓዛሉ፡፡

ቀደም ባለው ጊዜ ሙሽራው ሙሽሪትን ይዞ በሚመለስበት ጊዜ በመንገዳቸው ምንም የሚከውኑት ስነ ስርዓት አልነበረም፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን  በተለይ የሙሽራው ቤት ከወረዳው ውጭ ሆኖ ሙሽሮችና አጃቢዎቻቸው ሩቅ የሚጓዙ ከሆኑ በመንገዳቸው የመዝናኛና የፎቶግራፍ መነሳት ስነ ስርዓቶችን ማካሄድ ተጀምሯል፡፡ እነዚህን ስነ ስርዓቶች ለማከናወን የሚያስችሉ ቤቶች በአካባቢው መከፈታቸው የሌላን አካባቢ ልማድ ወደ ባህሉ እንዲቀላቀል በማድረግ ለክዋኔው መጨመር ምክንያት ሆነዋል፡፡ በተጨማሪም የወንድ አጃቢዎችም በመንገድ ላይ ድቤ እየመቱ ነሺዳ ይላሉ፡፡

የሙሽራው ሚዜዎች በሰርጉ ማግስት ጠዋት የምስራች ለማለት በሙሽራዋ ቤተሰብ ቤት እንዲገኙ የሚጠበቅ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ሙሽራዋ የተወሰደችው ሩቅ ቦታ ከሆነ ሚዜዎች ስልክ ደውለው የምስራቹን መንገር ተለምዷል፡፡

**ዘመናዊነት በቁሳዊ ባህል ላይ ያስከተለው ለውጥ፣**

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከዘመናዊነት ጋር ተያይዞ ሙሽራ ይዛቸው በምትሄደው ቁሶች ውስጥ ተጨማሪ ዘመናዊ የቤት ቁሳቁሶች ተካትተዋል፡፡ ከእነዚህ ዘመናዊ የቤት ቁሳቁሶች መካከል የስጋና የቡና መፍጫ ማሽኖች፣ የፍራፍሬ መጭመቂያ ማሽኖች፣ ፔርሙስ፣ ዘመናዊ የቡና ስኒዎች፣ ረከቦትና ጀበና፣ የውሀ ማቅረቢያ የጠርሙስ ጆግና ብርጭቆዎች፣ የሻይ ስኒዎች፣ የፕላስቲክ ሰሀኖች፣ የትራስና የአልጋ ልብሶች፣ ትራሶች፣ ወዘተ ይገኙበታል፡፡ በመሆኑም በቤተሰብ ደረጃ የሚገዙ እቃዎችን ለማሟላት በአማካይ ከአስራ አምስት እስከ ሀያ ሺህ ብር እንደሚያስፈልግ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ለወግ የሚሰጡ እቃዎች ዓይነትና መጠን ላይ ለውጥ ተከስቷል፡፡ ቀደም ባለው ጊዜ ለሙሽራ ከሚሰጥ ወግ በተጨማሪ ሞባይል ስልክ፣ የጆሮ፣ የአንገትና የጣት የወርቅ ጌጣጌጥ፣ ድሪያና ጉርጉራ፣ የእጅ ሰዓት፣ ሻምፖና ኮንዲሽነር፣ ወዘተ የወግ እቃዎች ሆነዋል፡፡ በአቅም ማነስ ምክንያት የወርቅ ጌጣጌጥ ቢቀር እንኳን ከብር የተሰራ ጌጣጌጥ ይመጣል፡፡ የመጠን ልዩነቱን በተመለከተም የሚመጣው ልብስ ቁጥር እስከ አስራ አምስት ደርሷል፤ የሚመጣው ጫማ ቁጥርም እንዲሁ ከፍ ብሏል፡፡

የሰርግ ቀን አለባበስና አጋጌጥ ላይም ከፍተኛ ለውጥ ተከስቷል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ሴት ሙሽሮች ባህላዊ ቀሚስ መልበሳቸው ቀርቶ ዘመናዊ የሰርግ ቀሚስ ይለብሳሉ፡፡ በመስክ ቆይታዬ ባህላዊ የአርጎባ ልብስ ተለብሶ የተከወነ አንድ የጉፍታ ስነ ስርዓት ብቻ ያጋጠመኝ ሲሆን (2/5/2013፣ ጋቻኔ ቀበሌ፣ ምልከታ) ከዚያ ውጭ የተመለከትኳቸው የጋብቻ ስነ ስርዓቶች ላይ የባህል ልብስ ተለብሶ አልተመለከትኩም፡፡ በአሁኑ ጊዜ ባህላዊው ቀሚስ ቀርቶ የሴት ሙሽራ ቀሚስ ቬሎ ሆኗል፡፡ የሙሽራዋ ሚዜዎች በከተማው አይነት ቀለሙ ተመሳሳይ የሆነ ቀሚስና ሂጃብ ያደርጋሉ፤ እንደ ላዚምና ጭልጭሌ ያሉ ባህላዊ ጌጦችን የማይጠቀሙ ሲሆን በዘመናዊ ጌጦች ያጌጣሉ፤ በዘመናዊ መዋቢያዎችም ይዋባሉ፡፡ ሙሽራውና ሚዜዎቹም ዘመናዊ ሱፍና ሸሚዝ የሚለብሱ ሲሆን የሚዜዎቹ ልብስ ተመሳሳይ ቀለም ያለው ነው፡፡ የተጠሪዎች አለባበስም ዘመናዊነት ቀይሮታል፤ የሴቶች ጉንደሬ ቀሚስ በሺቲ ቀሚስ፣ የወንዶች ወንበርቲና ጥልቆሽ በሸርጥና በሸሚዝ ተተክቷል፡፡







ፎቶግራፍ 30፣ 31 እና 32. የአለባበስ ለውጥ ፎቶግራፍ 31 ፎቶግራፍ 32

በወይባ ቅጠል የሚሰራው ዳስ በተለይ በጋቾኔ አካባቢ በዘመናዊ የሸራ ድንኳንና የፕላስቲክ ዳስ እየተተካ መጥቷል፡፡ ማረፊያ እንዲሆን ውስጡ በቅጠል ተጐዝጉዞ ይዘጋጅ የነበረው የፕላስቲክ ምንጣፍ በማንጠፍ እየተቀየረ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በጋቾኔ አካባቢ ድንኳኑን በዘመናዊ ማስዋቢያ መንገድ ማስዋብ እየተለመደ መጥቷል፡፡

የምግብ መመገቢያ ባህላዊ ቁሶች የፋብሪካ ምርት በሆኑ ዘመናዊ ቁሶች እየተተኩ ይገኛሉ፡፡ በሰርግ ቀን ሙሽራው በቤተሰቡና በሙሽራዋ ቤተሰብ ቤት የሚቀርብበት ረዥም የመቃ ገበታ ቀርቶ በትሪ ተቀይሯል፤ አማች ገበታ ሲቀርብ የሚቀመጥበት ድንክ ቀርቶ መቀመጫው ፍራሽና ምንጣፍ ሆኗል፤ ሰርገኞች የሚመገቡበት የሳጠራ ገበታም በትሪ ተቀይሯል፤ ማባያ ማቅረቢያ ጣባ በጐድጓዳ የብረት ሰሀን ተቀይሯል፡፡



ፎቶግራፍ 33. የሙሽራ ገበታ ለውጥ



ፎቶግራፍ 34. የመመገቢያ ቁሳቁስ ለውጥ

### ዘመናዊነት በሚቀርቡ ምግቦች ዓይነት ላይ ያስከተለው ለውጥ፤

በሰርግ ላይ የሚቀርቡ ብዙዎቹ ባህላዊ ምግቦች እንዳሉ ሆነው አንዳንዶቹ ግን በአሰራር ተቀይረዋል፤ ዘመናዊ ምግቦችም ተጨምረዋል፡፡ ዝልዝል ስጋ አሰራሩ ስጋውን በውሀና በጨው መቀቀል ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ አልፎ አልፎ የተቀቀለውን ስጋ እንደገና በዘይት በመጥበስና መጠሪያውን “ሀኒድ” በማለት ማቅረብ ተጀምሯል፡፡ ሀኒድ የአረቦች ባህላዊ ምግብ ሲሆን ዝልዝሉን ስጋ ወደዚያ በመውሰድ መቀየሩ እየታየ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሩዝና ሰላጣ ምግቦች በሰርግ ገበታ ላይ የሚቀርቡ ምግቦች ሆነዋል፡፡ ጋቾኔ የወረዳው ከተማ በመሆኑ ከሌሎቹ ቀበሌዎች በተለየ የዘመናዊነትና ከተማነት ጥላ

ያጠላበት በመሆኑ ብዙዎቹ ከዘመናዊነት ጋር የተያያዙ ለውጦች በጋቾኔ ጐልተው ይታያሉ፡፡

### 6.6.1.3. የሌላን ባህል ተቀብሎ በመከወን ምክንያት የተከሰቱ ለውጦች

እዚህ በዋናነት ሁለት ከሌላ ባህል መጥተው ወደ አርጐባዎች ባህል የተጨመሩ ክዋኔዎች ይቀርባሉ፡፡ አንደኛው በሰርግ ቀን ሙሽራው ሙሽሪትን ለመውሰድ በሚዘጋጅበት ጊዜ የሙሽራዋ ሚዜዎችና አጃቢዎች የ"ደምባችንን" ብለው ከሙሽራው በኩል ገንዘብ መጠየቃቸው ሲሆን ሌላው የሙሽራዋ ያላገቡ ወንድ የአጐት ወይም የአክስት ልጆች ወይም ከዚያ በሚርቅ የሚዛመዱ ወጣት ወንዶች የ"አብሱማችንን" ብለው አሁንም ገንዘብ መጠየቃቸው ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ልማዶች ከብሄረሰቡ ጋር በጉርብትና ከሚኖረው የአፋር ብሄረሰብ ባህል የመጡ ናቸው፡፡

የሙሽራዋ ሚዜዎችና አጃቢዎች የደምባችንን በማለት የደምብ በሚባለው ገንዘብ መጠን ላይ ጭቅጭቅ ያነሳሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የሙሽራው ሚዜዎች ከሙሽራው ጋር ተመካክረው የሚሰጡት የገንዘብ መጠን የሴት ሚዜዎችን አያስደስትም፡፡ ሴት ሚዜዎች የተሰጣቸውን ገንዘብ ይሁን ብለው ከመቀበል ይልቅ ገንዘቡ በቂ አይደለም ጨምራችሁ አምጡ የሚል ሀሳብ ስለሚያነሱ፣ በወንድ ሚዜዎች በኩል ደግሞ የማሳመን ጥረት ስለሚደረግ ጉዳዩ እየተባባሰ ክርክርና ጭቅጭቅን ይፈጥራል፡፡ በዚህ ጊዜ በሙሽራዋ ወገን ያለ አንድ ሰው በመካከል ገብቶ በማስማማት ሴት ሚዜዎች ገንዘቡን እንዲቀበሉና ሙሽራው ሙሽሪትን ይዞ እንዲሄድ ያደርጋሉ፡፡ የሙሽራዋ ሚዜዎች የደምባችንን ብለው በመጠየቅ በተሰጣቸው ገንዘብ ለመልስ በሙሽራዋ ቤተሰብ ቤት በሚቆይበት ጊዜ ብስኩትና ለስላሳ በመግዛት ታዳሚውን ይጋብዙበታል፡፡ በመሆኑም በውሰት የመጣው ልማድ በመልስ ስነ ስርዓት ላይ ተጨማሪ ስነ ስርዓትን በመፍጠር የክዋኔ ለውጥም አምጥቷል ማለት ነው፡፡

የሙሽራዋ ወንድ ዘመዶች የ"አብሱማችንን" ስጡን ብለው ሙሽራውን መያዛቸው ልጅቷን የማግባት ፈቃድ ያለን በመሆናችን አንዳችን ልናገባት የምንችላትን ልጅ በመውሰድህ ለእኛ ካሳ ልትከፍል ይገባል የሚል የመብት ጥያቄ ነው፡፡ ምልከታ ባደረግሁባቸው የሰርግ ስነ ስርዓቶች ላይ የ"ደምባችንን" እና የ"አብሱማችንን" በሚል የገንዘብ ጥያቄ ምክንያት ከፍተኛ ክርክርና ውዝግብ ተነስቶ አደራዳሪዎች በመካከል ገብተው ነገሩን በማርገብ ስምምነት እንዲፈጠር ሲያደርጉ ተመልክቻለሁ (3/5/2013 እና 9/5/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣

ምልከታ)፡፡ ሌላው በሰርግ ቀን ጐረቤቶች ወደ ሰርጉ ቤት ይዘው የሚሄዱትን ስጦታ ዓይነትና መጠን በሰርጉ ቤት በር ላይ ሆኖ በመዝገብ የመመዝገብ አዲስ ልማድ መጥቶ እየተከወነ ይገኛል፡፡

የአርጐባዎች ቋንቋ አርጐብኛ ነው፡፡ ነገር ግን በጊዜ ሂደት አርጐብኛው በአርጐባዎች የቀን ተቀን ህይወት ውስጥ ለመግባቢያነት መዋሉ እየቀነሰ መጥቶ በአሁኑ ጊዜ ቋንቋውን መናገር የሚችሉ ሰዎች ቁጥር በጣም ጥቂት ሆኗል፡፡ በዚህ ምክንያት በአሁኑ ጊዜ በቋንቋው ይከወኑ የነበሩ ዱዓዎች፣ ዝኪሮችና ዘፈኖች የሉም፤ እነዚህ ትውፊቶች የሚከወኑት በአማርኛ ቋንቋ ነው፡፡ ቀደም ያለውን የአርጐብኛውን ስነቃሎች ለማግኘትና ለመመዝገብ ጥረት ቢደረግም አውቃለሁ የሚል ሰው ባለመገኘቱ ምክንያት ጥረቱ ሊሳካ አልቻለም፡፡

### 6.6.1.4. ኢኰኖሚያዊ ጫና ያስከተለው ለውጥ

ከመስክ በቃለመጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ቀደም ባለው ጊዜ ለመደገሻ የሚሰጥን ገንዘብ መጠን በተመለከተ በሙሽራዋ ቤተሰብ በኩል ትኩረት አይደረግበትም ነበር፤ መጠኑ ምንም ይሁን ምን አክብሮ የተላከውን ገንዘብ መቀበል እንጂ መቁጠር እንኳን እንደ ነውር ይቆጠር ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን ገንዘቡን መቁጠር፣ በመጠኑ ላይ መነጋገር፣ መከራከርና አንሷል ማለት እየተለመደ መጥቷል፡፡ በተላከው ገንዘብ መጠን ባለመስማማትም በሰርጉ ቀን የሚመጣውን አጀቢ ቁጥር በመወሰን የተወሰኑ አጀቢዎችን የመመለስ ልማድ መጥቷል፡፡

ለጐጆ መውጫ ጥሪ ሲደረግ የተወሰደው ዳቦ በሚጠራው አባወራ ቁጥር ያህል ተቆራርሶ፣ ከዳቦው ጋር ድልህና ሽሮ ተደርጐ በየቤቱ እየተዞረ ይታደልና በማግስቱ ምሳ ሰዓት እንዲገኙ እየተነገረ ይጠራ ነበር፤ ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ለመጥሪያ የሚታደለው ዳቦ ብቻ ሆኗል፡፡ የአብሽ ውሀ የሚሰራው በማር ሲሆን ማር በመወደዱ ምክንያት መጠጡ የሚሰራው በስኳር ሆኗል፡፡

### 6.6.1.5. ሆን ተብሎ የተደረጉ ለውጦች

ተተግባሪነቱ ወጥነት ባይኖረውም በሰዎች መካከል ፉክክር እንዳይኖርና ይህም በሙሽራው ላይ ጫና እንዳያስከትል ሲባል የሀይማኖት አባቶችና ሽማግሌዎች በመመካከር በተወሰኑ

ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ወይም ገደብ አስቀምጠዋል፡፡ በውሳኔያቸው ለመደገሻና ለመኸር ክፍያ የሚሰጥን ገንዘብ መጠን ገድበዋል፤ የወግ መጠንንና የሚሰጣቸው የሙሽራዋ ቤተሰብ አባላትን ቁጥር ቀንሰዋል፤ ወግ ተከፍቶ እንዳይታይም ከልክለዋል፡፡ የደምቅሁ ስነ ስርዓት በተደጋጋሚ ጊዜ በባለትዳሮች መካከል ጠብን በማስከተሉ ምክንያት የሀይማኖት አባቶች ይቅር በማለታቸው ክዋኔው እየተከወነ አይደለም፡፡

### 6.6.2. የመዋቅር ለውጥ

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በብሄረሰቡ ባህላዊ የጋብቻ ስነ ስርዓት ክዋኔ መዋቅር ላይ ለውጥ ተከስቷል፡፡ በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት የነበረው የጋብቻ ስነ ስርዓት ሙሽራዋ ከሰርጓ ቀን ጀምሮ አንድ አመት ለሚሆን ጊዜ በቤተሰቧ ቤት የምትቆይበት፤ ሙሽራው ከወሰዳትም በኋላ በሙሽራው ቤተሰብ ቤት አንድ አመት ያህል የሚከርሙበትና ከዚያ በኋላ ጎጆ የሚወጡበት በመሆኑ እና ከዚያ በኋላ የሚከወነው የሰርግ ስነ ስርዓት ከላይ በሰፊው የቀረበው በመሆኑ የመለየት ደረጃው ተመሳሳይ ቢሆንም የሽግግር ደረጃው ቀደም ባለው ጊዜ ከነገር መፍጃው ጀምሮ እስከ ጎጆ መውጫ ቀን ዋዜማ ድረስ የሚቆይና የመቀላቀያ ደረጃውም ከጎጆ መውጫ ስነ ስርዓት ክዋኔ የሚጀምር ነበር፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ሙሽሮች ከሰርጋቸው ቀን ጀምረው አብረው የሚኖሩ በመሆኑ የሽግግር ደረጃው ከነገር መፍጃ ስነ ስርዓት ክዋኔ ጀምሮ እስከ ሰርግ ዋዜማ ብቻ የሚቆይና የመቀላቀያ ጊዜው ከሰርግ ስነ ስርዓት ክዋኔ የሚጀምር ሆኗል፡፡

### 6.6.3. ያልተለወጡ ጉዳዮች

ለውጥ ካሳዩ የጋብቻ መስፈርቶች ውጭ ያሉ ሌሎች መስፈርቶች፣ የስለላ ስነ ስርዓት፣ የቆዳ ማንጠፊያና የነገር መፍጃ ስነ ስርዓት ክዋኔዎች፣ ከነገር መፍጃ በኋላ ወንዱ አግቢ ወደ እጮኛውና ቤተሰቧ የሚልከው ስጦታ፣ ከሰርግ ስነ ስርዓት አስቀድሞ የሚከወኑ ስነ ስርዓቶችና የሰርግ ስነ ስርዓት፣ አማች ከሌላው የሰርጉ ተሳታፊ ተለይቶ በተከለለ ቦታ እንዲያርፍና እንዲመገብ ማድረግ፣ የጉፍታ ስነ ስርዓት ክዋኔ፣ ወግ ማቅረብ፣ አንድ ሴትና አንድ ወንድ የሙሽራዋ ተከታዮች አብሮ መሄድ፣ ለድንግልና የሚሰጠው ዋጋ፣ የባዱሼህ ስነ ስርዓት ክዋኔ፣ የመልስ ስነ ስርዓት ክዋኔና ለመልሱ ሙሽሮች ከሚዜዎቻቸው ጋር በሙሽራዋ ቤተሰብ ቤት መክረማቸው እና የጎጆ መውጫ ስነ ስርዓት ክዋኔ ያልተለወጡ ጉዳዮች ናቸው፡፡ የኮሮና ወረርሽኝ ምንም አይነት ለውጥ አላስከተለም፡፡

በዚህ ምዕራፍ የአርጐባ ብሄረሰብ የጋብቻ ስነ ስርዓት ከክዋኔ፣ ከመዋቅር፣ ከትዕምርት፣ ከፋይዳና ከለውጥና ቀጣይነት አንፃር የቀረበ ሲሆን በሚቀጥለው ምዕራፍ የብሄረሰቡ የሀዘን ስነ ስርዓት ቀርቧል፡፡

# ምዕራፍ ሰባት

## የአርጐባ ብሄረሰብ የሀዘን ስነ ስርዓት

ይህ ምዕራፍ የአርጐባ ብሄረሰብን የሀዘን ስነ ስርዓት የሚመለከት ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ምዕራፍ በዋናነት የብሄረሰቡ የሀዘን ስነ ስርዓት ክዋኔ፣ የክዋኔው መዋቅር፣ ትዕምርት፣ ፋይዳና ለውጥና ቀጣይነት ቀርበዋል፡፡

### 7.1. የሞት እሳቤ በአርጐባ

በአርጐባዎች ዘንድ ሞት የሰው ልጅ መጨረሻ አይደለም፤ ከሞት በኋላም ህይወት አለ፡፡ ሞት የሰውን ልጅ ከሚታየውና ከኖረበት ዓለም ወደማይታየው አዲስ ዓለም የሚያሻግርና የሟች ነፍስ በዚያ አዲስ ዓይነት ኑሮ እንድትጀምር የሚያደርግ ክስተት ነው፡፡ ይህን አስመልክተው አቶ አህመድ ሲራጅ (28/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) እና ሼህ ጧሂር ኑሬ (24/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) በቅደም ተከተል የሚከተሉትን ብለዋል፡፡

> በአርጐባ ሞት በዚህ ዓለም ፍፃሜ ነው፡፡ ከሞት በኋላ ከዚህ ዓለም በላይ የሰፋ ህይወት እንዳለ እናምናለን፡፡ ሞቶ መነሳት በጣም የሚታመን ነው፡፡ ይህን ያላመነ የተሟላ ህይወት ኖረ አይባልም፡፡ … በሰማይ ቤት ትርፍ የሚተረፍባትም ይሁን የሚከሰርባት ይህቺ ምድር ናት፡፡ መጥፎ ስራ ሰርቶ እሳት መግቢያም ሆነ ጥሩ ስራ ሰርቶ ጀነት መግቢያ ይህቺ ዓለም ነች፡፡
>
> ሞት በምድር ላይ የመጨረሻ ፍፃሜያችን ነው፡፡ ለምድራዊ ኑሮ መሰናበቻ ነው፡፡ ከሞቱ በኋላ ደግሞ በመጨረሻ ቀን ትቀሰቀሳላችሁ ይለናል፤ በምድር ለሰራናት ሁሉ ጥያቄ ይመጣብናል፡፡ በአላህ ትዕዛዝ እንነሳለን፡፡ መጥፎም የሰራው መጥፎ ስራው ይቀርብለታል፤ ጥሩ ስራም የሰራው ጥሩ ስራው ይቀርብለታል፡፡

አብዛኛውን ጊዜ የአርጐባዎች ልማድ በሀይማኖታዊ መሰረት ላይ የቆመ ነው፡፡ በተለይ ከገሀዱ ዓለም ባሻገር በመሄድ የማይታየውን ዓለም በተመለከተ ያለው እምነት ሀይማኖታዊ

መሰረት አለው፡፡ ይህን መነሻ በማድረግ የብሄረሰቡ አባላት ከሞት በኋላ ስላለው ህይወት ያላቸውን እምነት እንመልከት፡፡

በብሄረሰቡ እምነት መሰረት ከሞት በኋላ ነፍስ በማይታየው ዓለም ያሉ ሁለት ዋና መዳረሻዎች ያሏት ሲሆን እነዚህም ጀነትና ጀሀነም ናቸው፡፡ ጀነት በህይወት ዘመኑ በሀይማኖት ከተከለከሉ ተግባራት የተቆጠበና መልካም ስራ ሲሰራ የኖረ ሰው ሲሞት ነፍሱ የምታርፍበት ቦታ ሲሆን በአንፃሩ ጀሀነም ከዚህ በተቃራኒው የፈጣሪውን ትዕዛዝ ሲጥስና እኩይ ተግባራትን ሲያከናውን የኖረ ሰው ሲሞት ነፍሱ የምታርፍበት ዘለዓለማዊ ስፍራ ነው፡፡ በአርጐባዎች እምነት መሰረት የጀነት መገኛ ከምድር በላይ፣ በሰማይ ላይ ሲሆን የጀሀነም መገኛ ከምድር በታች ነው፡፡ ጀነት ብርሀን ያለው፣ ወንዞች የሚፈሱበት፣ ዛፎች ያሉበትና ለምለም እንዲሁም መልካም ሽታ የሚያውድበት ስፍራ ነው፡፡ ጀሀነም ደግሞ በሚንቀለቀል እሳትና በጋለ ድንጋይ የተሞላ ነው (ሼህ ጧሂር ኑሬ፣ 24/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) (አቶ አሕመድ መሐመድ፣ 10/7/2013፣ ጐዜ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በአርጐባ ብሄረሰብ ሞት የሟች ማንነትንና የአሟሟት ሁኔታን መሰረት በማድረግ የተለያዩ ትርጉሞች ይሰጡታል፡፡ ሟች አዋቂና ጠቃሚ ሆኖ ሲሞት ትልቅ ሀዘን ይሆናል፡፡ “የአሊም ሞት የዓለም ሞት” የሚለው የአርጐባዎች ምሳሌያዊ አነጋገር (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 6/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) የአዋቂ ሰው ሞት ዓለም የሞተ ያህል ትልቅ ሀዘንን ይፈጥራል የሚል ሀሳብን የሚገልጽ ነው፡፡ ልጆች ወልዶ፣ በህመም ብዙ ጊዜ ቆይቶ፣ ሰውነቱ ወፍራም ከነበረ ከስቶ እና እዳ ካለበት እሱን ተናግሮ የሞተ ሰው ሞት ከሞት አይቆጠርም ተብሎ ይታመናል፡፡ በብሄረሰቡ ዘንድ ወልዶ፣ ዘሩን አብዝቶ የሞተ ሰው ሞት እንደማይባል ሁሉ ለስም መጠሪያ የሚሆንና መታሰቢያ የሚያደርግ ልጅ ሳይወልድ የሞተ ሰው ሞት ደግሞ ከፍተኛ ሀዘንን የሚፈጥር ነው፡፡ በወጣትነት እድሜ ሞት ሲከሰትም ሀዘኑ የከፋ ይሆናል፡፡ በሰው እጅ የሞተ ሰው መስዋዕት በመሆኑ በፈጣሪ ዘንድ ዋጋ ያገኛል ተብሎ የሚታመን ሲሆን በአንፃሩ አእምሮው ጤነኛ ሆኖ፣ እያወቀ ራሱን ያጠፋ ሰው ነፍሱ ምህረትን አታገኝም ተብሎ ይታመናል፡፡ በድንገተኛ አደጋና በወሊድ ምክንያት ሞት ሲከሰት ሀዘኑ ከሌላው ዓይነት ሞት የከበደ ይሆናል (ወ/ሮ ሲቲ ፋጡማ መሐመድ፣ 10/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ለሁሉም የሞት አይነት የሚደረገው የሀዘን ስነ ስርዓት ተመሳሳይ ነው፡፡ ሟች ማንም ይሁን፣ በምንም አይነት ምክንያት ይሙት፣ በብሄረሰቡ የሚደረገው የሀዘን ስነ ስርዓት ቅደም ተከተሉን ጠብቆ ይከወናል፡፡ ህፃን ሲሞት ወዳጅ ዘመድ "ተውት ተውት" ብሎ ስነ ስርዓቱ ቀለል ብሎ እንዲታለፍ የሚፈለግ ቢሆንም እንደማንኛውም ተገንዞና ስግደት ተደርጎለት ይቀበራል፤ ሶደቃም ይደረግለታል (ወ/ሮ ሲቲ ፋጡማ መሐመድ፣ 10/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

### 7.2. የአርጎባ ብሄረሰብ የሀዘን ስነ ስርዓት፤ ክዋኔው፣ መዋቅሩና ትዕምርቱ

በዚህ ክፍል የአርጎባ ብሄረሰብ የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ Gennep የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች ያልፉባቸዋል ካሏቸው የመለየት፣ የሽግግርና የመቀላቀል ደረጃዎች አንፃር እና በክዋኔው ውስጥ ያሉ ትዕምርታዊ ጉዳዮችና ፍካሬዎቻቸው ይቀርባሉ፡፡

#### 7.2.1. መለየት

በአርጎባ የሀዘን ስነ ስርዓት ክዋኔ የመለየት ደረጃ ሰው በጠና ሲታመም ጀምሮ ሞት እስኪከሰት ድረስ ያለውን ጊዜ ይይዛል፡፡ የህመም መከሰት ለመለየት ደረጃ መነሻ ሲሆን ሞት የመለየት ደረጃ መጨረሻና የሽግግር ደረጃ መጀመሪያ ወይም መግቢያ ነው፡፡ ከህመም እስከ ሞት ባለ ጊዜ የሚከወኑ ስነ ስርዓቶች የመለየት ጊዜ መገለጫዎች ናቸው፡፡

በአርጎባ ብሄረሰብ አንድ ሰው ሲታመም ቤተሰቡ፣ ዘመዶቹና ጎረቤቶቹ ሁሉ እንደየቅርበታቸው ሁኔታ ያስታምሙታል፤ ይረዱታል፡፡ ህመምተኛው የሚያምረውና የሚፈልገው ምግብ እየተጠየቀ ይዘጋጅለታል፡፡ ህመምተኛው እየደከመ ሄዶ ምግብ መብላት የሚያቅተው ደረጃ ከደረሰ ደግሞ ውሃ በስኒ ተደርጎ በንድፍ ጥጥ እየተነከረ አፉ ላይ እየተጨመቀለትና ከንፈሩ እየተጠራረገለት ይቆያል (ወ/ሮ ከድጃ መሐመድ ሰዒድ፣ 4/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ሰው ሲታመም ጭዳ እንዲሆንለት አካሉ ሙሉ የሆነ ፍየል ይታረዳል፡፡ ጭዳ ማለት መስዋዕት ማድረግ ወይም ደም ማፍሰስ ነው፡፡ ለእርድ የሚቀርበው ፍየል ሙሉ አካል እንዲኖረው የሚፈለገው ፍየሉ እያንዳንዱ አካሉ ለህመምተኛው እያንዳንዱ አካል ጭዳ እንዲሆንለትና ህመምተኛው ከህመሙ እንዲድን የሚታረድ በመሆኑ ነው (ወ/ሮ እመይ መሐመድ ነጋሽ፣ 22/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ህመምተኛው ህመሙ ሲፀናም በቀኝ ጐኑ እንዲተኛ ይደረጋል (ወ/ሮ እመይ መሐመድ ነጋሽ፣ 22/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ በብሄረሰቡ ዘንድ ቀኝ የገድ ተምሳሌት፣ የመልካም ዕድል፣ የሰማያዊ ሀሳብ ተምሳሌትና ብሩህ የሆነ መፃዒ ጊዜን መመኛ ሲሆን በአንፃሩ ግራ የአንጋዳ፣ የመጥፎ እድልና የእርኩስ መንፈስ መገኛ ተደርጐና ከሞት በኋላም ጀነት የቀኝ፣ ጀሀነም ደግሞ የግራ እንደሆኑ ስለሚታመን የታመመን በቀኝ ጐኑ የማስተኛት ድርጊት ታማሚው ከህመሙ እንዲድን፣ መልካም እንዲሆንለት፣ ቢሞት እንኳን የጀነት እንዲሆን ማምሰያ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው፡፡

ሰው ታሞ ህመሙ ለሞት ያሰጋዋል ተብሎ ሲታሰብ ሰው ተጠርቶ ዱዓ ይደረግለታል፡፡ ዱዓው ምህረትን ያስገኝለታል ወይም ጣሩን ያሳጥርለታል ተብሎ ይታመናል፡፡ ህመምተኛው ለሞት የሚያሰጋው መሆኑን የሚጠቁሙ ምልክቶች በዋናነት የሰውነት መዛል፣ መናገር አለመቻል ወይም የአንደበት መያዝ፣ በትኩረት ማየት አለመቻል ወይም ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ መመልከት፣ ራስን መሳትና የሰውነት ከእግር ጀምሮ ወደ ላይ እየቀዘቀዘ መሄድ ናቸው፡፡ የህመምተኛው የአተነፋፈስ ሁኔታም ህመምተኛው ያለበትን ሁኔታ ይጠቁማል፡፡ በአርጐባዎች እምነት መሰረት ሰው ሲሞት ነፍሱ ከሆድ ተነስታ ወደ ደረት፣ ከዚያም ወደ ጉሮሮ ከፍ በማለት በመጨረሻም በአፍንጫ ትወጣለች፡፡ ነፍስ ከሆድ ተነስታ ወደ ደረትና ጉሮሮ መሄዷ በየቦታው በሚሰማው የኩርፍርፍታ ድምጽና የአተነፋፈስ ሁኔታ ይለያል፡፡ ሰው ጣር ላይ ሆኖ አይኑ ትክል የሚለው ነፍሱ የምትደርስበት ቦታ እየታየው ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ነፍሱ የምትሄደው ወደ ጀነት ወይም ወደ ጀሀነም መሆኑ አስቀድሞ ይታየዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከሞት በኋላም ነፍሱ ወደ ጀነት የምትሄድ ከሆነ ፊቱ ያምራል፣ ወዝ ያመጣል፤ ወደ ጀሀነም የምትሄድ ከሆነ ደግሞ ፊቱ ይጠቁራል ተብሎ ይታመናል፡፡ የታመመ ሰው እነዚህ ምልክቶች ሲታዩበት ነፍስ የምትወጣበት ጊዜ ስለማይታወቅ ቤተሰብ የሆነና የቅርብ ሰው አጠገቡ ቁጭ ብሎ ይጠብቀዋል፤ የፈጣሪን አንድነት፣ የመሐመድን መላዕክተኛነት፣ ወደ ፈጣሪ ብቻ ማሰብ እንደሚያስፈልግ፣ ቤት፣ ልጅ፣ ገንዘብ፣ ዓለም ቀሪ መሆኑን፣ ወዘተ እየነገረ ታማሚው እንዲያስበው ያደርጋል፡፡ ይህ ተግባር ታማሚው ቢሞት እንኳን ከሞት በኋላ ጥሩ መንገድን ያስገኝለታል ተብሎ ይታመናል (ወ/ሮ እመይ መሐመድ ነጋሽ፣ 22/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

አንድ ሰው ነፍሱ እንደወጣችና እንደሞተ ሲረጋገጥ አጠገቡ ያለ ሰው ያካትመዋል፡፡ ማካተም የሟችን ዓይንና አፍ በመዳፍ በመያዝ እንዲዘጋ ማድረግ ነው፡፡ ነፍስ የምትወጣበትን ሁኔታ በተመለከተ ወ/ሮ ሏቢራ ኡመር (26/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> ሩህ የምትወጣው በአፍንጫ ነው ይባላል፡፡ ሩህ ስትወጣ መጀመሪያ አጥር ወይም እጣሪያ ላይ ትቀመጣለች፡፡ የቀብር ሰዓት ሲደርስ ሰዎች አስከሬን ተሸክመው ሲሄዱ ሩህ እያኮበኮበች እያኮበኮበች ቀድማ እጉድጓድ ትገባለች ይላሉ፡፡ ሲቀበር ሩህ አውጡኝ አውጡኝ እያለች ትጮሃለች፡፡ ለዚያ ነው እንዳትሰማ የሚቀራው የሚባለው፡፡

ብሄረሰቡ የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ ስለሆነ ከሞት በኋላ ያለ የንብረት ጉዳይ መልክ የሚይዘው በሸሪያ ህግ መሰረት ነው፡፡ በሸሪያ ህግ መሰረት አንድ ሰው ከሞተ በኋላ ንብረቱ የወራሾች በመሆኑ የራሱ ሆኖ ሲያስተዳድረውና ሲወስንበት የኖረው ሀብትና ንብረት ሞቱን ተከትሎ ወዲያውኑ የወራሾቹ ሀቅ ይሆናል፡፡ ሟች እድሜያቸው ከአስራ አምስት ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ካሉት ደግሞ ከዚያ ንብረት ተቀንሶ ለሶደቃ ማዋል አይፈቀድም፤ ከሚያስፈልገው ሶስት የከፈን ጨርቅም የሚፈቀደው አንድ ብቻ ይሆናል (አቶ አሕመድ መሐመድ፣ 16/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ አቶ መሐመድ አቡበከር (6/2/2013 ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) በወረዳው ሸሪያ ፍ/ቤት በሚሰሩበት ጊዜ ያጋጠማቸውን እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡

> አንድ ሰው ድንገት ሞተ፡፡ ወስያ የለውም፡፡ ከፈኑን ሲያወጡ አትችሉም አልናቸው፡፡ እያለ? አሉ፤ ተከራከሩ፡፡ ኖረ አልኖረ ወስያ የለውም፤ አንድ ብቻ ነው መልሱት አልናቸው፡፡ እንዴት አሉ፡፡ እንዲህ አይነት ቀልድ የለም አልናቸው፡፡ ተጣላን፡፡ ከዚያ ትልቁን ልጅ ጠራሁትና አንተ እከፍላለሁ ካልክ ፈርምልን፤ ከራስህ ድርሻ ላይ የከፈኑን እችላለሁ ካልክ አንተ ትችላለህ አለዛ ከእነርሱ ድርሻ

ላይ አይነካም፤ ሁለቱ ነጠላ የእነሱ ነው፤ አንዱ ብቻ ነች የእሱ አልነውና በዚያ ተስማማን፡፡

ነገር ግን ለሞት በዳረገ ህመም ላይ ተሆኖ የተደረገ ኑዛዜ ተቀባይነት ስለሌለው ሟች ለሞት ከዳረገው ህመም አስቀድሞ ጤነኛ በነበረበት ጊዜ ወይም ታሞም ቢሆን በዳነበት ህመም ላይ ሆኖ ኑዛዜ ሊያስቀምጥ የሚችል ሲሆን መጠኑን ጠቅሶ ከንብረቱ ላይ ተቀንሶ ለዚህ አይነቱ ጉዳይ እንዲውል ኑዛዜ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ሟች ኑዛዜ ከሌለው ዘመድና ጐረቤቶች አዋጥተው ሶደቃውን ያደርጋሉ፤ የቀረውን ሁለት የከፈን ጨርቅም ይገዙለታል እንጂ ከንብረቱ አይነሳም (አቶ አሕመድ መሐመድ፣ 16/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የንብረት ውርስ ጉዳይ የሚታየውም በዋናነት የሸሪያውን ህግ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ነገር ግን በሸሪያው ህግ የመውረስ መብታቸው የተረጋገጠላቸው ሰዎች ተቃውሞ የሌላቸውና የሚቀበሉት ከሆነ በሶስት ምስክሮች ፊት የተደረገ ኑዛዜ በውርስ ክፍፍል ዓይነትና መጠን ላይ ልዩነት ሊፈጥር ይችላል፡፡ ንብረት በዚህ መልኩ በስጦታ ሲሰጥ ስጦታው ከራስ ቀሪ ንብረት ተለይቶ ለሶስት ቀን ያህል በሌላ ቦታ እንዲቀመጥ የሚደረግ ሲሆን (አቶ አሕመድ መሐመድ፣ 16/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) ይህም በስጦታ የተሰጠው ንብረት የራስ ሀቅ መሆን ማቆሙን፣ ከራስ ንብረት የተለየ መሆኑን፤ ንብረቱን ማውጣትን፣ ስጦታ ማድረግንና ማጽናትን መግለጫ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው፡፡

ይህን የመለየትን ጊዜ ከሟችና ከሟች ቤተሰብ አንፃር መመልከት ይቻላል፡፡ ከሟች አንፃር ሲታይ ሟች ከመሞቱ በፊት በጠና ሲታመም ከሌላው ሰው ተለይቶ ይታያል፡፡ በመሆኑም ሰዎች የቅርበታቸውን ያህል ያስታምሙታል፣ ይንከባከቡታል፣ የሚያምረውን ምግብ እየጠየቁ ያዘጋጁለታል፣ ጭዳ እንዲሆንለት ፍየል ያርዱለታል፣ ዱዓ ያደርጉለታል፣ አንድ ሰው ከራስጌው ቁጭ ብሎ የፈጣሪን አንድነትና የዓለምን ጠፊነት እየነገረ በልቦናው እንዲያሳድር ይረዳዋል፡፡ ታማሚው ሰው ሲሞትም ከገሀዱ ዓለም ኑሮ ይለያል፡፡ ይህ ደረጃ ከሟች ቤተሰብ አንፃር ሲታይ የሟች ቤተሰብ አባላት ሀዘንተኞች በመሆናቸው ከቀን ተቀን የህይወት እንቅስቃሴያቸውና ከማህበራዊ ኑሯቸው የሚለዩበት ነው፡፡

### 7.2.2. ሽግግር

በአርጐባ የሀዘን ስነ ስርዓት የሽግግር ደረጃ ሞት ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ የቆዳ ማጠፊያ ስነ ስርዓት እስከሚከወንበት ቀን ዋዜማ ድረስ ያለውን ሰፊ ጊዜ ይሸፍናል፡፡ ሞት የሽግግር ደረጃ መግቢያ ሲሆን የቆዳ ማጠፊያ ስነ ስርዓት የመቀላቀል ደረጃ መግቢያ በመሆኑ የሽግግር ደረጃ በቆዳ ማጠፊያ ዋዜማ የሚጠናቀቅ ይሆናል፡፡

የሽግግር ጊዜ መገለጫዎች ከሞት በኋላ ጥሪ ከማድረግ ጀምሮ የዳስ መጣል፣ የመሸኛ ማዘጋጀት፣ የመቃብር ጉድጓድ የመቆፈር፣ አስከሬን የማለስለስ፣ አስከሬን የማጠብና የመገነዝ፣ በጋራ የማልቀስ፣ በቀብሩ ቀን በሀዘኑ ቤት በጋራ የመመገብ፣ አስከሬን የማጓጓዝ እንዲሁም የቀብርና የሀፈሻ[32] ስነ ስርዓት ክዋኔዎች ናቸው፡፡

#### ሀ. ጥሪ ማድረግ

በአርጐባዎች ዘንድ አንድ ሰው ሲሞት ሩቅ ያሉ ዘመድና ወዳጆች እንዲሰሙ ይደረጋል፡፡ በጣም የቅርብ የሆኑ ለምሳሌ፣ የቤተሰብ አባላት ሩቅ ከሆኑ እነርሱ ሳይመጡ አይቀበርም ተብሎ የቀብርና የመቃብር ቁፋሮ ሰዓት እንዲዘገይ ይደረጋል (ወ/ሮ ሶህሊየት ባቢ፣ 29/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)

የሀዘን መልዕክትና ጥሪ ሩቅ ላለ ዘመድና ወዳጅ የሚነገረው በሁለት መንገድ ነው፡፡ አንደኛው መንገድ "ኸረን" ሲሆን ሰዎች ከፍ ያለ ቦታ ላይ በመሆን ራቅ ያለ አካባቢ ላሉ ሰዎች ጮክ ብለው ጥሪ በማድረግ ሀዘን መድረሱን መልዕክት የሚነግሩበት መንገድ ነው፡፡ ጥሪው የሚደረገው መጀመሪያ ሀዘኑን የሚነግረው ሰው በአካባቢው ከፍ ያለ ቦታ ላይ ይሆንና መልዕክቱን የሚያስተላልፍበትን ቦታ በመጥቀስ "እዚህ ቦታ (ለምሳሌ ገበሮች) ያለህ ማንሂ (ማን ነህ)?!" ብሎ ጮሆ ይጣራል፡፡ ስሙ የተጠራበት ቦታ ያለ ማንም ሰው ጥሪው የመርዶ ጥሪ መሆኑን ይረዳና ጥሪውን መስማቱን ለመግለጽ "ኢ.ኢ.ኢ. ..." በማለት መልስ ይሰጣል፡፡ በዚህ ጊዜ መልዕክቱን የሚያስተላልፈው ሰው ሀዘን የደረሰበትን ሰው ስም በመግለጽ "እከሌ እናት/ አባት/ ወንድም ወዘተ (የሟች ዝምድና ተገልፆ) ሞቶብኛል ብለዋል፣ ወደዚህም ወደዚህም ቦታ (ጥሪው እንዲደርስ የሚፈለግበት ቦታ እየተጠቀሰ ለምሳሌ፣ ወደ ኸይራምባም፣ ወደ አማን አምባም፣ ወደ አዋዲም፣ ወዘተ) ጥሩና ንገሩ"

[32] ጐረቤቶች ከቀብር ቀን በኋላ ባሉ ስድስት ቀናት ማታ ማታ ምግብ ይዘው ወደ ሀዘኑ ቤት በመሄድ ሀዘንተኞችን የሚያስተዛዝኑበት ስነ ስርዓት

ይላል፡፡ ቦታውን በመግለጽ እዚህ እዚህ ቦታ ዘመድ አለኝ ይጠራልኝ የሚለው ሀዘን የደረሰበት ቤተሰብ ሲሆን ጥሪውን የሚያደርገው የጐረቤት ሰው ወይም ከሀዘኑ ቤተሰብ ውጭ ያለ ሌላ ሰው ነው (ወ/ሮ ሶሀሊየት ባቢ፣ 29/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)

የሟች ዘመዶች ያሉበት አካባቢ ሩቅ ሆኖ በቀጥታ ጥሪውን ለማድረግ የማይሰማ ቢሆን እንኳን በዚሁ መልኩ የሰማ የቅርብ አካባቢ ሰው ራቅ ላለው እያስተላለፈ፣ ሌላውም እንዲሁ እየነገረ መርዶው ሩቅ ለተባለው አካባቢ ይደርሳል፡፡ ለቅሶውን የሰሙ ተጠሪዎችም እንደ ሁኔታው በበቅሎ ሆነው ወይም በእግራቸው ወደ ሀዘኑ ቤት ይጓዛሉ፣ ቦታው ሩቅ ቢሆንም ከሟች ጋር ባላቸው የዝምድና ቅርበት መጠን ለቀብር ሰዓትም ሊደርሱ ይችላሉ፡፡ ሁለተኛው መንገድ ሰዎች በቅሎ ተጭኖላቸው በቦታው ሄደው የሚነግሩበት መንገድ ነው (ወ/ሮ ሶሀሊየት ባቢ፣ 29/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)

ሰው ሲሞት ቤተሰቡና አብሮ የነበረ ወዳጅ ዘመድ ወጥቶ በደጅ ስለሚያለቅስ በቅርብ ያለ ሰው ሲለቀስ በመስማትና እርስ በእርሱ በመነጋገር ሀዘኑን ሰምቶ ወደ ሀዘኑ ቤት በመሄድ እርሙን ያወጣል፡፡ ሞት የተከሰተው በቀን ከሆነ ጐረቤቶች ሀዘኑን ላልሰሙ ሌሎች የአካባቢው ሰዎችና እድር ያለበት አካባቢ ከሆነ ለእድር ይነግራሉ፡፡ ሞት የተከሰተበት ሰዓት ምሽትና ሌሊት ከሆነ ግን የሰማው ሰው ብቻ ያለቅስና የሞቱን ዜና ለሌሎች የማድረስና ለእድር የመንገር ስራ የሚከናወነው ሲነጋ ተጠብቆ በማለዳ ነው (ወ/ሮ ሶሀሊየት ባቢ፣ 29/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)

አርጐባዎች በዋናነት ሀዘንም ሆነ ደስታ በደረሰበት ቤት በመረዳዳት ሀዘኑንም ደስታውንም በጋራ ይወጡታል፡፡ በአርጐባዎች አካባቢ ለሀዘን ጊዜ መረዳጃ ተብሎ እድር የማቋቋም ልማድ እምብዛም ነው፡፡ ከገጠር ቀበሌዎች በተሻለ እድር ተቋቁሞ የሰዎችን ትግግዝ ለማቀናጀት የተሞከረው በወረዳው ከተማ በጋቸኔ ቀበሌ ነው፡፡ በቀበሌው የሴት ባልትና በማለት የሚጠሩት አንድ የሴት እድርና ሌላ የወንድ እድር ተቋቁመዋል፡፡ የሴት እድሩ ሰብሳቢ ወ/ሮ ሲቲ ፋጡማ መሐመድ (10/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) በሀዘን ጊዜ የሴት እድሩ የምግብ ግብዓቶችን፣ የወንድ እድሩ ደግሞ የማብሰያ ቁሳቁሶችን፣ ድንኳንና ገንዘብ እንደሚሰጥ ገልፀዋል፡፡

### ለ. ዳስ መጣል

በቀብሩ እለት ጠዋት ወንዶች ለእንግዳ መቀበያና ለምግብ ማዘጋጃ የሚሆን ዳስ ይጥላሉ፡፡ መቀመጫ እንዲሆን በዳስ ውስጥ ዳሱ የተሰራበት ዛፍ ቅጠል የሚጐዘጐዝ ሲሆን በሀዘኑ ቤት ውስጥ መዋስ ይነጠፋል፡፡ ዳሱ የሚዘጋጀው ከወይባና ከደደሆ ዛፍ እንጨትና ቅጠል ነው፡፡ በጋቸኔ ቀበሌ ለለቅሶ ደራሽ መስተናገጃ ድንኳን ተጥሎ ተመልክቻለሁ፤ ምግብ ሲዘጋጅ የተመለከትኩትም ኘላስቲክ ተወጥሮ በተዘጋጀ ዳስ ውስጥ ነው (17/11/2012 እና 20/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡ በገበሮች ቀበሌ ግን እንግዶች የሚስተናገዱበትና ምግብ የሚዘጋጅበት የቅጠል ዳስ ተጥሎ ተመልክቻለሁ (3/10/2012፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡ ይህ የሆነው ጋቸኔ የወረዳው ከተማ በመሆኑና ከሌሎቹ የወረዳው ቀበሌዎች አንፃር በመጠኑ የከተማነት መልክ ያለው በመሆኑ ነው፡፡

በለቅሶ ስነ ስርዓት ላይ ዳስ መጣል ሞት ምን ያህል ሰዎችን የሚያሰባስብና የማህበረሰብን አንድነት የሚያጠብቅ መሆኑን የሚያሳይ ትዕምርት ነው፡፡ ሰዎች በለቅሶ ጊዜ በአንድ ዳስ ውስጥ በአንድ ላይ መሰብሰባቸው የተከሰተው ሞት ያስከተለባቸውን የጋራ የሀዘን ስሜት በጋራ ሆነው ለመቋቋም መነሳታቸውን ያሳያል፡፡ መዋስ በተነጠፈበት ቤት ውስጥ ሞት መከሰቱንና ለቅሶ መሆኑን የሚገልጽ ትዕምርታዊ ቁስ ነው፡፡ በብሂረሰቡ ዘንድ "መዋስ ዘርግታለች" ማለት ለቅሶ ተቀምጣለች የሚል መልዕክትን ያስተላልፋል፡፡

### ሐ. መሸኘ ማዘጋጀት

መሸኘ በቀብሩ እለት ለቀባሪና ለለቅሶ ደራሽ የሚዘጋጅ ምግብና መጠጥ ነው፡፡ ሞት የተከሰተው በምሽት ከሆነና በሌሎችም ምክንያቶች ቀብሩ በማግስቱ እንዲሆን ከተወሰነ በዚያ ቀን ወይም በቀብሩ ዋዜማ ምንም ዝግጅት አይደረግም፡፡ በዚህ ሁኔታ ጐረቤቶችና በቅርብ ያሉ የሟች ዘመዶች በሀዘኑ ቤት ተገኝተው ከሀዘንተኞች ጋር ያድራሉ፡፡ በማግስቱ ሰው ሳይሰበሰብ ሴቶቹ ማልደው ይነሱና በተገኘው ነገር ምግብ አዘጋጅተው ሀዘንተኞችን ያበላሉ፤ ቡና አፍልተው ያጠጣሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ከሀዘንተኞች ጋር በመሆን የሚያላቅሱ የተወሰኑ ሴቶች ብቻ ይቀሩና ሌሎቹ ከሚመጡት ተጨማሪ ሰዎች ጋር በመሆን የመሸኘ ዝግጅቱን ይጀምራሉ፡፡ ሞት የተከሰተው በቀን ሆኖ ቀብሩም በዚያው ቀን የሚፈፀም ከሆነ ጐረቤቶች በሀዘኑ ቤት ተገኝተው የመሸኘ ዝግጅቶችን ያደርጋሉ፡፡ ስለዚህ የመሸኘ ዝግጅት

የሚደረገው በቀብሩ ቀን ነው ማለት ነው (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 14/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በመሆኑም ለቀባሪ መሸኛ የሚሆን ምግብ ለማዘጋጀት የሚውል ግብዓት ከሌለ ይዘጋጃል ወይም ሴት ጐረቤቶች ከቤታቸው ከተቦካው እህል እየቆነጠሩ አምጥተው በሀዘኑ ቤት በአንድ ላይ ተደርጐ እንጀራ ይጋገራል፤ ወጥ ይሰራል፣ ንፍሮ ይቀቀላል፤ ቡናና ሻይ ይፈላል፡፡ ሴቶች ጋገራውን፣ ወጥ መስራቱንና ቡናና ሻይ ማፍላቱን የሚያከናውኑ ሲሆን ወንዶች እርድ የሚደረግ ከሆነ እርዱን በማከናወን ስጋውን ቆራርጠው ወጡን ለሚሰሩ ሴቶች ያስረክባሉ፣ ንፍሮ ይቀቅላሉ፣ ለጋገራና ለወጥ መስሪያ የሚሆን ማገዶ ያቀርባሉ (17/11/2012 እና 20/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

ከመሸኛው አንዱ “ቦላ” ነው፡፡ “ቦላ” በቀብር እለት ለቀባሪው የሚታደል ጥሬ ስጋ ነው፡፡ ሟች አርዳችሁ ሶድቁልኝ ብሎ ከተናዘዘ፣ ሟች ትልቅ ሰው ነው በእርድ ይሸኝ ተብሎ የሀገር ሰው አዋጥቶ ፍየል ከገዛ ወይም ዘመድ ፍየል ስቦ ከመጣ ለ”ቦላ” ተብሎ የእርድ ስነ ስርዓት ይከናወናል፡፡ እርዱ ከተከናወነ በኋላ ስጋው ለቀብር በመጣው ሰው ቁጥር ልክ እንዲሆን ተገምቶ በትንንሹ ይቆራረጣል፡፡ ከዚያ በኋላ ስጋው በእቃ ይደረግና ስጋውን የያዙ ሰዎች በመስጊድ በር ላይና በቀብር ስፍራ አመቺ በሆነ ቦታ ላይ በመሆን ከመስጊድና ከቀብር ቦታ ለሚመለሱ ሰዎች በእጅ በእጃቸው በመስጠት ያድላሉ፡፡ “ቦላ”ው የታደላቸው ሰዎች ስጋውን ወደየቤታቸው በመውሰድ ተቀቅሎ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ይመገቡታል፡፡ ይህ የሚደረገው ሶደቃውን የሚያገኘው ሰው ቁጥር እንዲበዛ ሲባል ነው (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 14/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

### መ. የመቃብር ጉድጓድ መቆፈር

ሰው የማይኖርበት ዱር፣ ሜዳማና አፈር ቦታ ሆኖ ለመቆፈር የሚመች መሬት ለመቃብር ስፍራነት ይመረጣል፡፡ በአፄ ሀይለስላሴ ዘመነ መንግስት በነበረው የመሬት አስተዳደር ስርዓት በየአካባቢው የነበረው የመሬት ባለቤት በመሬቱ ላይ ለቤተሰቡ ብቻ የሚሆን የመቃብር ስፍራ ይከልል ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት በየጐጡ ከነበረው የመቃብር ቦታ በተለየ የቤተሰብ የመቃብር ቦታዎች ነበሩ፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ይህ አይነቱ የቤተሰብ ቀብር ቦታ ቀርቶ የቀብር ስነ ስርዓት የሚከናወነው በጋራ የመቃብር ቦታዎች ሆኗል (አቶ ኑርዬ በሺር፣ 4/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ሰው ሞቶ የቀብር ስነ ስርዓቱን ሊያዘገይ የሚችል ምክንያት ከሌለ በተቻለ ፍጥነት የቀብር ጉድጓድ ቁፋሮው ይጀመራል፡፡ በዚህ ሁኔታ የቀብር ስነ ስርዓቱን ለማከናወን የሚጠበቀው የመቃብር ጉድጓዱ ቁፋሮ መጠናቀቅ በመሆኑ ቁፋሮው እንደተጠናቀቀ የቀብር ስነ ስርዓቱ ይከናወናል፡፡ ነገር ግን ዘመድ አዝማድ የሚጠበቅበት ሁኔታ ኖሮ ወይም ሌላ የዝግጅት አለመድረስ ኖሮ የቀብር ስነ ስርዓቱ የሚራዘም ከሆነ ሞት ይጠራል በሚል እምነት ምክንያት ጉድጓዱ ተቆፍሮ አልቆ እንዲጠበቅ አይደረግም፡፡ በመሆኑም የቀብር ጉድጓድ የሚቆፈረው ቁፋሮው እንደተጠናቀቀ ወዲያው የቀብር ስነ ስርዓት የሚከናወን ሲሆን ብቻ ነው (አቶ ኑርዬ በሺር፣ 4/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የቀብር ጉድጓድ የሚቆፈረው መጀመሪያ ከምስራቅ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ሶስት ክንድ ቁመት፣ ከሰሜን ወደ ደቡብ ደግሞ ሁለት ክንድ ጎን እንዲኖረው ተደርጐ በዶማ ወደ ታች ይቆፈራል፡፡ ወደ ታች የሚቆፈረው መጠን መካከለኛ ቁመት ያለው ሰው ቆሞና እጁን ወደ ላይ ዘርግቶ የጉድጓዱን አፍ መንካት እስኪችል ድረስ የሚሆን ጥልቀት እንዲኖረው ተደርጐ ነው፡፡ ይህን ያህል ጥልቀት ከተቆፈረ በኋላ በስተ ሰሜን አቅጣጫ ለአስከሬኑ መቅበሪያ የሚሆን ለኸድ ወደ ጐን ይቆፈራል፡፡ ይህ ጉድጓድ በሩ አስከሬን ለማስገባት የሚያስችል፣ ጐኑ አስከሬን ለማስተኛት የሚያስችልና ቁመቱም ሰው ሊያስቀምጥ የሚችል ተደርጐ ይቆፈራል፡፡ ጉድጓዱ ይህን መጠን እንደያዘና እንዳልያዘ ጉድጓድ ቆፋሪዎች እየገቡና ተኝተው እያዩ፣ ቁጭ ብለውም ቁመቱ ለመቀመጥ የሚያስችል መሆኑን እያዩ ያስተካክላሉ፡፡ ቁመቱና ጐኑ ልክ ሲሆን ውስጡን ጥሩ አድርገው በመጥረቢያ ያለሰልሱታል (አቶ አብዱልቃድር ቃሲም፣ 7/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ጉድጓድ ቆፋሪዎቹ ጉድጓዱን በሚቆፍሩበት ሰዓት የተወሰኑ ሌሎች ደግሞ ለኸዱ የሚዘጋበትን ድንጋይ ከሚገኝበት ቦታ በመሄድ ፈንቅለውና አስተካክለው ተሸክመው ያመጣሉ፡፡ ለመዝጊያነት የሚሆነው ድንጋይ ጠፍጣፋና ከቁመቱ ረዘም፣ ከጐኑም ሰፋ ያለ በሀ ድንጋይ ሲሆን በአካባቢው በስፋት የሚገኝ ነው፡፡ ሞት ይጠራል በሚል እምነት ምክንያት ድንጋዩ ሞት ሲከሰት ይዘጋጃል እንጂ ተዘጋጅቶ አይቀመጥም፡፡ ለአንድ መቃብር መዝጊያ የሚሆን ድንጋይ ቁጥር እንደ ድንጋዩ መጠን አንድ፣ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሊሆን ይችላል፡፡ ድንጋዩ ከመጣ በኋላ የለኸዱን በር በትክክል ሊዘጋ የሚችል መሆኑ እየተዘጋ ከታየና ያልተስተካከለ ነገር ካለውም ከተስተካከለ በኋላ ለመምረጊያ

የሚሆን ጭቃ ተቦክቶ ይዘጋጃል (አቶ አብዱልቃድር ቃሲም፣ 7/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በአንድ አካባቢ ሰው ሞቶ ቀብሩ እየተቆፈረ ደግሞ ሌላ ሰው ቢሞት በዚያው ጉድጓድ ውስጥ ለቀደመው አስከሬን በተቆፈረው ሰሜን አቅጣጫ ትይዩ በስተ ደቡብ በኩል ሌላ ለኸድ ተቆፍሮ ሁለተኛው አስከሬን በዚያ ሊቀበር ይችላል፣ ሌላ ሞት ቢያጋጥም እንኳን በዚያው ጉድጓድ ወደታች ተቆፍሮ ሶስተኛ አስከሬን በዚያ ሊቀበር ይችላል፡፡ በአርጐባዎች ዘንድ እኔ ያስቆፈርኩት ጉድጓድ ነው ሌላ ጉድጓድ አስቆፍሩ የሚባል ነገር የለም፡፡ ድንገተኛ አደጋ አጋጥሞ ብዙ ሰዎች በአንድ ጊዜ ቢሞቱ በአንድ ጉድጓድ ለኸድ እየተበጀ እስከ አራት የሚደርስ አስከሬን ይቀበራል፡፡ የቀብር ጉድጓድ እጥረት ሲያጋጥምም የቆየ ቀብር ተከፍቶ ይቀበርበታል (አቶ ኑርዬ በሺር፣ 4/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ጉድጓዱን የሚቆፍሩ ሰዎች የሟች ወዳጅ ዘመዶችና ጐረቤቶች የሆኑ ወንዶች ናቸው፡፡ በአካባቢው ሞት ሲከሰት በእድሜ ከፍ ከፍ ብለው ጉድጓድ የመቆፈር አቅም ያላቸው ወንዶች ሁሉ የቀብር ጉድጓድ የመቆፈር ግዴታ እንዳለባቸው ይታመናል፡፡ የቀብር ጉድጓድ በሚቆፈር ጊዜ ምንም ችግር ሳያጋጥመው በቁፋሮው ላይ ያልተገኘ ወንድ ከባድ ስህተት እንደፈፀመ ይቆጠራል፡፡ ከቀብሩ ስነ ስርዓት በፊትና በስነ ስርዓቱ ላይ ተገኝቶ ከቁፋሮና አፈር ከመመለስ ገሸሽ የሚል ሰውም ማህበራዊ መገለል ይደርስበታል፡፡ በመሆኑም ጉድጓድ ሲቆፈር አቅም ያላቸው ወንዶች ሁሉ የስራ ክፍፍል በማድረግ መቃብሩን የሚቆፍሩ፣ የመቃብር መዝጊያ ድንጋይ ፈልገው የሚያመጡ፣ ጭቃ የሚያቦኩ፣ ውሃ የሚያቀርቡ ሆነው የስራ ድርሻ በመከፋፈል ስራውን በመተካካትና በሽሚያ ያከናውናሉ (አቶ አብዱልቃድር ቃሲም፣ 7/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ከመቃብር ስፍራዎች ላይ ዛፍ መቁረጥ ክልክል ሲሆን የመቃብር ስፍራዎች ዙሪያቸው በካብ ይታጠራል (አቶ ኑርዬ በሺር፣ 4/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ከመቃብር ስፍራዎች ላይ ዛፍ መቁረጥ ክልክል መሆኑ ምድራዊ ዛፎችን የሙታን ነፍስ ማረፊያ ለሆነው ሰማያዊው የጀነት ዛፍ ውክልና ማቆም ያስከተለው ውጤት ነው፡፡ ሰማያዊው ጀነት ለምለምና በተክሎች የተሞላ፣ ቀዝቃዛና ነፋሻማ አየር ያለው እንደሆነ ይታመናል፡፡ በዚህ ምክንያት የመቃብር ስፍራዎች አረንጓዴና ቀዝቃዛ እንዲሆኑ

ተደርገው ሙታንን ለምለም ወደ ሆነው ጀነትም እንዲመሯቸው በማሰብና ለማምሰል የተደረገ ነው፡፡

በብሄረሰቡ ለመቃብር ቦታዎች የተለየ ክብርም ይሰጣል፡፡ በህይወት የነበሩ፣ በህይወት ዘመናቸው በርካታ ተግባራትን ሲያከናውኑ የነበሩ፣ የሀይማኖት አባቶች የነበሩ፣ የተከበሩ የሀገር ሽማግሌዎች የነበሩ፣ ወዘተ ህይወታቸው አልፎ ያረፉበት በመሆኑ ለእነርሱ በሚሰጥ ከበሬታ ምክንያት ስፍራውም ትልቅ ክብር እንዲሰጠው ሆኗል፡፡ ይህ ክብር ደግሞ በተለያዩ ነገሮች ይገለፃል፡፡ አንደኛው መገለጫ በመቃብር ስፍራዎች የተደረመሰ ወይም የተከፈተ የመቃብር ጉድጓድ መኖር በአካባቢው የዝናብ እጥረት ከፍ ሲልም ድርቅ ያስከትላል ተብሎ የሚታመን መሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም በክረምት ጊዜና በአካባቢው የዝናብ እጥረት ሲያጋጥም የሀይማኖት አባቶች ዱዓ ካደረጉ በኋላ በአካባቢው የሚገኙ የመቃብር ስፍራዎችን በማሰስ የተደረመሰ መቃብር ካለ ያንን መቃብር የመድፈን፣ የተጋለጠ የሰው አጽምም ካለ ያንን ሰብስቦ የመቅበር ስራ እንዲሰሩ ወጣቶችን ያዝዛሉ፡፡ ወጣቶችም በዘመቻ መልክ ይህንኑ ስራ ይሰራሉ (አቶ አብዱልቃድር ቃሲም፣ 7/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ለመቃብር ስፍራዎች የሚሰጠውን ክብር የሚያሳይ አጋጣሚ አጋጥሞኛል፡፡ በመስክ ስራ ወቅት ላይ መጠቅለያ ቀበሌ የነበረኝን ስራ ጨርሼ የወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት በፈቀደልኝ መኪና ወደ ሌላ የገጠር ቀበሌ ስጓዝ ሹፌሩ አቶ ኻሊድ በድሩ በመንገድ ላይ በሚያጋጥሙን የመቃብር ስፍራዎች ሁሉ ስንደርስ የመኪናውን ፍጥነት ዝግ ያደርጋል፤ በመኪና ውስጥ የከፈተውን ሙዚቃ ድምጽም በጣም ይቀንሳል፡፡ በተደጋጋሚ እንዲህ ሲያደርግ በመመልከቴ ምክንያቱን ስጠይቀው የመቃብር ስፍራ በህይወት ዘመናቸው ትልቅ ስራ ሲሰሩ የነበሩ ሰዎች ያረፉበት በመሆኑ ይከበራል፣ በተመጣበት ፍጥነት ከሚጮህ ሙዚቃ ጋር ማለፍ ሙታኑን መረበሽና ቦታውንም አለማክበር ነው የሚል ሀሳቡን በመግለጽ ምክንያቱን አስረድቶኛል (1/4/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ እና አባሊ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

### ሠ. አስከሬን ማለስለስ

ሞት ሲከሰት መጀመሪያ አስከሬኑ በንፁህና ቀዝቃዛ ውሀ ይታጠባል፡፡ ይህ አስከሬን ሲገነዝ ከሚደረገው ዋና የአስከሬን እጥበት አስቀድሞ ሰው እንደሞተ የሚደረገው እጥበት ሚች

ነፍሱ ስትወጣ በሰውነቱ እሾህ ገብቶ የመውጣትን ህመም ያህል ህመም ይሰማዋል ተብሎ ስለሚታመንና ቀዝቃዛ ውሀ የሚያበርድ፣ የሚያቀዘቅዝ በመሆኑ የሟችን ህመም ለማብረድ በማሰብ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ በጠፍር አልጋ ላይ የእጣን ዛፍ ቅጠል ተጎዝጉዞ አስከሬኑን እዚያ ላይ በማስተኛት ከላይ ጨርቅ ይሸፈንና አስከሬኑን የማለስለስ ስራ ይከናወናል፡፡

አስከሬን የሚቀበረው ፊቱ ወደ ሰሜን አቅጣጫ እንዲዞር ተደርጎ በቀኝ ጎኑ ነው፡፡ አስከሬን በሚቀበርበት ጊዜም ወደ ሌላ አቅጣጫ እንዳይዞር ወይም በጀርባው እንዳይገለበጥ ለማድረግ የቀኝ እግር በመጠኑ አጠፍ ይደረጋል (አቶ አሕመድ ሲራጅ፣ 28/2/2013፣ ጋቺኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ አስከሬኑን እንዲህ ለመቅበር ደግሞ አስከሬኑ መድረቅ የለበትም፡፡ ሌላው ጉዳይ ደግሞ አስከሬን ሲታጠብ ዉዱእ እንደሚደረግ እጁ ላይ ውሃ እየተደረገና ከፍ ተደርጎ ውሃው ወደ ክርኑ እንዲፈስ እየተደረገ በመሆኑ (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 6/2/2013፣ ጋቺኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) ሰው ሲሞት አስከሬኑ እንዲደርቅ አይፈለግም፡፡ አስከሬን ለስልሶ ቆይቶ በአጠባና በቀብር ጊዜ የገራ እንዲሆን ይፈለጋል፡፡ በመሆኑም አስከሬን እስኪገነዝ ድረስ ባለው ሰዓት ሁሉ አስከሬን የማለስለስ ስራ ይሰራል፡፡

የመጀመሪያው የማለስለሻ መንገድ የቀብሩ ሰዓት ደርሶ አስከሬኑ እስኪገነዝ ድረስ የእጣን ዛፍ ቅጠል ጎዝጉዞ አስከሬኑን እዚያ ላይ ማስተኛትና ጭንቅላቱን ወደ ቀኝና ወደ ግራ እያንቀሳቀሱና የእጅና የእግር መገጣጠሚያውን እያጠፉና እየዘረጉ መቆየት ነው፡፡ ዋናው መንገድ አስከሬኑ እስኪታጠብ ድረስ ያለመታከት አጠገቡ ሆኖ መገጣጠሚያውን ሁሉ እያጠፉና እየዘረጉ መቆየት ሲሆን የእጣን ዛፍ ቅጠሉ የማለስለስ ባህርይ ስላለው አስከሬኑ በቀላሉ እንዳይደርቅ ያደርገዋል ተብሎም ይታመናል፡፡ ነገር ግን ይህን የሚያደርግ ጠፍቶ በአጋጣሚ አስከሬኑ ቢጠነክር አብሽ፣ የእምቧይ ስር፣ የጥድ ዛፍ እንጨት ወይም የባህር ዛፍ ቅጠል አስከሬኑ ካለበት አልጋ ስር ተደርጎ ይጨሳል፡፡ እነዚህ ጭሶች አስከሬን የማለስለስ ባህርይ እንዳላቸው ይታመናል፡፡ ከዚያ በኋላ መገጣጠሚያዎችን በተደጋጋሚ በማጠፍና በመዘርጋት አስከሬኑን ለማለስለስ ጥረት ይደረጋል፡፡ ሟቹ ወንድ ከሆነ አስከሬኑን የሚያለሰልሰው ወንድ ሰው ሲሆን ሟቿ ሴት ከሆነች ደግሞ የማለስለስ ስራ የምትሰራ ሴት ነች፡፡ ነገር ግን አስገዳጅ ሁኔታ ሲፈጠርና ሰዎች እስኪመጡ ድረስ ወንዱ የሴት ቤተሰቡን አስከሬን፣ ሴቷም የወንድ ቤተሰቧን አስከሬን ማለስለስ ይችላሉ (አቶ አብዱልቃድር ቃሲም፣ 7/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

### ረ. አስከሬን ማጠብና መገነዝ

አስከሬን የሚገነዘው የመቃብር ጉድጓድ ቆፋሪዎች ቁፋሮው ሊያልቅላቸው የሚችልበትን ሰዓት በመገመት አስከሬኑን አስተካክላችሁ ለዚህ ሰዓት አድርሱልን ብለው በሚልኩት መልዕክት መሰረት ነው፡፡ መልዕክቱ እስኪላክ ድረስ አስከሬኑን ለማጠብና ለመገነዝ የሚያስፈልጉ ነገሮች ተዘጋጅተው አስከሬኑ እየተለሰለሰ የሚቆይ ሲሆን መልዕክቱን የሚነግር ሰው ሲላክ አስከሬኑ በአግባቡ ታጥቦ ይገነዛል (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 6/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

**አስከሬን ማጠብ፣**

አስከሬን ለማጠብ የሚያስፈልጉ የቁርቁራ ውሃ፣ ንፁህ ውሀና ሳሙና ናቸው፡፡ የቁርቁራ ውሃ የሚዘጋጀው መጀመሪያ የቁርቁራ ዛፍ ቅጠሉ እየተለቀመ በሳፋ ላይ በተደረገ ውሃ ውስጥ ይጨመርና ይታሻል፡፡ ቅጠሉ እየታሸ በቆየ መጠን አረፋ እያመጣና ውሃውም አረንጓዴ ቀለም እየያዘ ይሄዳል፡፡ ቅጠሉ ታሽቶ ሲበቃ ውሃው በንፁህ ወንፊት ይጠለልና በንፁህ እቃ ውስጥ ተደርጎና ተከድኖ ይቀመጣል፡፡ አስከሬን ማጠቢያ ውሃ ንፁህ መሆን ስላለበት የቁርቁራ ውሃ ሲዘጋጅ የማዘጋጃ ቁሳቁሶቹ በሙሉ በአግባቡ የታጠቡ መሆን አለባቸው (20/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡



ፎቶግራፍ 35. የቁርቁራ ቅጠል

አስከሬን የሚታጠበው መጀመሪያ አስከሬኑ በሚታጠብበት ቦታ ላይ፤ አብዛኛውን ጊዜ በሀዘኑ ቤት ሁለተኛ ክፍል ወይም ጓዳ ውስጥ ጉድጓድ ይቆፈርና በጉድጓዱ ላይ ሁለት

ትልልቅ እንጨት ወይም ጣውላ ተጋድሞ አስከሬኑ ሳይጋለጥ እስከተሸፈነበት ጨርቅ ከቆየበት አልጋ ላይ ተነስቶ እዚያ ላይ ይደረጋል፡፡ ጉድጓዱ የሚቆፈረው አስከሬኑ እየታጠበበት የሚፈሰው ውሀ የትም እንዳይሄድና በጉድጓዱ ውስጥ ገብቶ እንዲሰርግ ለማድረግ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ አስከሬኑን ቁጭ በማድረግ ሁለት ሰው ትከሻውንና አንድ ሰው ጭንቅላቱን ደግፎ በመያዝ ሌላ ሰው ደግሞ የአስከሬኑን ሆድ ጫን ጫን በማድረግና በማሸት በሆድ ዕቃው ውስጥ ቆሻሻ ካለ እንዲወጣና ሆድ ዕቃው ንፁህ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡ ከዚያ በኋላ እጃቸውን በሸማ ጠቅልለው አካባቢውን በውሃ ካፀዱ በኋላ አስከሬኑን አስተኝተውና እጃቸውን ታጥበው ከላይ የተሸፈነበት ጨርቅ ሳይነሳ አስከሬኑን ማጠብ ይጀምራሉ (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 6/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

መጀመሪያ አስከሬኑ በውሀና በሳሙና ይታጠብና ሲያበቃ በቅደም ተከተል ተዘጋጅቶ በተቀመጠው የቁርቁራ ውሃና በንፁህ ውሃ ይታጠባል፡፡ በዚህ ጊዜ አስከሬኑ በዉዱእ መልክ ይታጠባል፡፡ አስከሬኑ ሲታጠብ መጀመሪያ ከቀኝ ጐን ያሉት ቀኝ ጐኑን፣ ቀኝ እጁንና ቀኝ እግሩን ያጥባሉ፣ ከዚያ በኋላ ደግሞ በተመሳሳይ መንገድ በስተግራ ያሉት ሰዎች የበስተግራ በኩሉን ያጥባሉ (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 6/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ በብሄረሰቡ ዘንድ ቀኝ የመልካም እድል፤ ግራ ደግሞ የመጥፎ እድል ምሳሌ ተደርጐ የሚታመን በመሆኑ እጥበቱን ከቀኝ በኩል የመጀመር ድርጊት ሟች በዚያኛው ዓለም መልካም ነገር እንዲገጥመውና ነፍሱ የጀነት እንድትሆን ማምሰያ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው፡፡

**አስከሬን መገነዝ፣**

አስከሬን ለመገነዝ የከፈን ጨርቅ፣ ማግ፣ ጥጥ፣ ቀጭኔና ሽቶ ያስፈልጋሉ፡፡ የከፈን ጨርቅ አስከሬኑ የሚለብሰው ልብስ ሲሆን ሟች በህይወት ዘመኑ ይጠቀምበት ከነበረው ከጥጥ ፈትል የተሰራ ልብስ መካከል የሚመረጥ ነው (20/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

የሴቶች ከፈን በቁጥር አምስት ሲሆኑ እነዚህም ጉፍታ፣ ሽርጥ፣ ጥልቆሽ እና ሁለት ነጠላ ጋቢዎች ናቸው፡፡ ጉፍታ ጭንቀላት የሚሸፈንበት ሻሽ ሲሆን ሽርጥ ከወገብ በታች የሚለበስ ጨርቅ ነው፡፡ ጥልቆሽ የሚባለው የአርጐባ ሴቶች ባህላዊ ቀሚስ ነው፡፡ ቀሚሱ ተጠልፎ የሚለበስ አርጐባዎች ጐንደሬ ብለው የሚጠሩት ቀሚስ ሲሆን ለከፈን የሚሆነው ግን ጥልፍ ያልተጠለፈበት ቀሚስ ነው፡፡ ሟች ካሏት ጐንደሬዎች ውስጥ ያልተጠለፈና

ምናልባትም ስሞት ለከፈኔ ይሆናል በማለት ያስቀመጠችው ካለ ይመረጣል፣ ነገር ግን ሁሉም ጥልፍ ከሆኑ ወይም ያላት አንዱ ባለ ጥልፍ ከሆነ ጥልፉ ሙሉ በሙሉ ተተርትሮ ለከፈንነት ይውላል፡፡ ለሁለት የተነጠለው ጋቢ በቁጥር እንደ ሁለት የሚቆጠር ሲሆን መካከሉ ይሰፋና የአስከሬን መጠቅለያ እንዲሆን ይዘጋጃል (ወ/ሮ ሀይሀሊማ ሱለይማን፣ 19/5/2013 ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ጥልፍ መተርተሩ ማጌጥ ዓለማዊ ብቻ በመሆኑ ለሙታን የሚፈለግ አለመሆኑንና ሞት ከሚጌጥበት ዓለም የስጋዊ መገለጫ የሆነ ጌጥ ወደማያስፈልግበት ዓለም የሚደረግ ሽግግር መሆኑን የሚያሳይ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው፡፡



ፎቶግራፍ 36. ጥልፍ የሌለው ጉንደሬ ቀሚስ

የወንድ ከፈን በቁጥር ሶስት ሲሆኑ እነዚህም ሁለት ነጠላ ጋቢና አንድ ሸርጥ ናቸው፡፡ አቶ መሐመድ አቡበከር (6/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) የሴት ከፈን አምስት፣ የወንዱ ደግሞ ሶስት ብቻ የሆነበትን ምክንያት በሚከተለው መልኩ አስረድተዋል፡፡

> ሴት ስትኖርም ውበቷ መሸፈኗ ነው፡፡ የፈረንጅ ባህል ካልሆነ በስተቀር ሴት ልጅ መራቆቷ አይፈለግም፡፡ ሴት በቁሚም ከወንድ በተለይ ፀጉሯንና ሌላ አካሏን ትሸፍናለች፡፡ ጭማሪውም ይኸው ነው፡፡ አንደኛው ጉፍታው ነው፡፡ ሁለተኛው ጥልቆው ነው፡፡ ወንድ ግን ሸረጥ አድርጎ ቢሄድም ብዙ ችግር የለበትም በቁሙም ቢሆን፡፡ ስለዚህ ሴቷ መሸፈኗ ውበቷ ስለሆነ ጨመር ይላል፡፡

ከጥጥ ተፈትሎ የሚዘጋጅ ማግ አስከሬን ተከፍኖ ካለቀ በኋላ አምስት ቦታ ላይ ለመቋጠር የሚጠቀሙበት ነው፡፡ ብዙ አርጐባዎች በቤታቸው ውስጥ ለአስከሬን መገነዣ ብለው ማግ ያስቀምጣሉ፡፡ ከመረጃ ሰጪዎች መካከል አንዷ የነበሩት ወ/ሮ ሞሚና መሐመድ ስለዚሁ ጉዳይ አንስተን ስንነጋገር "የምጠራበት ቀን አይታወቅም" ብለው መገነዣቸውን ማግ፣ ጥጥና ቀጭኔ በቤታቸው በሳጥናቸው ውስጥ እንዳስቀመጡ ነግረውኝ (18/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ መደበኛ ያልሆነ ቡድን ተኮር ውይይት) በማግስቱ አዘጋጅተው ያስቀመጡትን በላስቲክ የተቋጠረ አንድ ልቃቂት፣ ያልተፈለቀቀ ጥጥና በላስቲክ የተቋጠረ ቀጭኔ አምጥተው አሳይተውኛል (19/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡ ነገር ግን በአጋጣሚ ማግ ካልተገኘ ከመከፈኛው ጨርቅ ተቆርጦ እንደ ማግ መጠቀም እንደሚቻል ወ/ሮ ሞሚና መሐመድ (19/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) ገልፀዋል፡፡ ቀጭኔ መልካም መዓዛ ያለው ቅጠል ሲሆን ደርቆና ታሽቶ ሲደቅ በተነደፈ ጥጥ ላይ እየተነሰነሰ በአስከሬን የተለያዩ ቦታዎች ላይ ይደረጋል፡፡ አስከሬኑ ተከፍኖ ካበቃ በኋላ ሽቶ የሚርከፈከፍበት በመሆኑ ሽቶም ያስፈልጋል፡፡



ፎቶግራፍ 37. ቀጭኔ፣ ማግና ጥጥ

አስከሬን የሚገነዘው ድንክ አልጋ ላይ በመሆኑ አስከሬኑ በሚታጠብበት ጊዜ ጐን ለጐን አስከሬኑ የሚያርፍበትና ቀሪው የግነዛ ስራ የሚሰራበት አልጋ ይዘጋጃል፡፡ ድንክ አልጋው አራቱም እግሮቹ ከታች በላስቲክ ተጠቅልለው ይታሰራሉ፡፡ ይህም አልጋው የሚቀመጥበት ቦታ "ጡሀራ" ወይም ንፁህ ባይሆን፣ በንክኪ ምክንያት አልጋውም "ጡሀራ" ሳይሆን ቀርቶ

የአስከሬኑ “ጡሀራ”ነት ሳይጠበቅ እንዳይቀር ነው፡፡ ከዚያ በኋላ አልጋው ላይ ቅጠል ይረበረብና እዚያ ላይ የተዘጋጀው ማግ እጥፍ እጥፍ እየተደረገና ለማሰር በሚያስችል ቁመት እየተቆረጠ አስከሬኑን ጭንቅላት፣ ትከሻ፣ ወገብ፣ ጉልበትና ቁርጭምጭሚት አካባቢ ለማሰር በሚያስችል መልኩ አምስት ቦታ ላይ ይጣላል፡፡ ከዚያ በላይ ነጠላ ጋቢው በስተግራ ያለው ተረፍ እንዲል ተደርጎ ይዘረጋል (20/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

አስከሬኑ ታጥቦ እንዳበቃ ሽርጡ ይሸረጥበትና አስከሬኑ የተሸፈነበት ጨርቅ ይነሳል፡፡ ከዚያ በኋላ አስከሬኑን ከታጠበበት ጣውላ ላይ በትብብር በማንሳት አልጋው ላይ በጀርባው ይደረግና የመገነዝ ስራው ይቀጥላል፡፡ ሟቿ ሴት ከሆነች ከሽርጡ በኋላ ጥልቆሹ ይጠለቅና እስከ እግር ድረስ ይለበሳል፡፡ ጉፍታው ይለበስና ጠበቅ ተደርጎ አገጭ ስር በመርፌ ተሰፍቶ ይያያዛል (ወ/ሮ መራኢና መሐመዱ፣ 23/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ሟቹ ወንድ ከሆነ ሽርጥ ብቻ ይሸረጥለታል (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 6/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ከዚያ በኋላ አስከሬኑ በነጠላ ጋቢው ከመጠቅለሉ በፊት ንድፍ ጥጥ እየተቦጨቀና ቀጭኔ እየተነሰነሰበት እርጥበት ሊኖር ይችላል ተብሎ በሚታሰብበት የሰውነት ክፍል ላይ ሁሉ ይደረጋል፡፡ በመሆኑም ሟቿ ሴት ከሆነች ሀያ አራት ቦታ ላይ ማለትም በእጅና በእግር ጣቶች መካከል ላይ፣ በአፍንጫና በጆሮ ቀዳዳዎች ላይ፣ ከተደረገ በኋላ በመጨረሻ የሚቦጨቀውን ንድፍ ጥጥ መጠን ከፍ በማድረግና አሁንም ቀጭኔ በመነስነስ በአስከሬኑ ፊት ላይ ሙሉ በሙሉ፣ በብብትና በብብት ውስጥና በብልት ላይ ይደረጋል (ወ/ሮ መራኢና መሐመዱ፣ 23/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ሟቹ ወንድ ከሆነም በብልት ላይ ከሚደረገው ጥጥ ውጭ በተመሳሳይ መንገድ በሁሉም ቦታ ላይ ጥጥ ይደረጋል፡፡ እነዚህ የሰውነት ክፍሎች ላይ ንድፍ ጥጥ የሚደረገው ቦታዎቹ ላይ እርጥበት ሊኖር ይችላል ተብሎ ስለሚገመትና ምናልባት ፈሳሽ ካለ ጥጡ እንዲመጠውና አስከሬኑ እንዳይበላሽ በማሰብ ነው (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 6/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ከዚያ በኋላ ሽቶ ይርከፈከፍና ነጠላ ጋቢው መጀመሪያ ከቀኝ በኩል፣ በመቀጠል ከግራ በኩል መለስ መለስ ተደርጎ አስከሬኑ ይሸፈንበታል፡፡ ከዚያ በኋላ ነጠላ ጋቢው ከእግር ተረፍ ተደርጎ በደንብ እየተለበሰና ከስር በተዘረጋው ማግ እየታሰረ ጭንቅላት ጋር ሲደርስ ነጠላ ጋቢው ከጭንቅላት በላይ በደንብ ተለብሶና ተጠቅልሎ በማጉ ይታሰራል፡፡ ከዚያ በኋላ እንደገና ሽቶ ይርከፈከፍና በነጠላ ይሸፈናል፡፡ በየትኛውም ዓይነት አሟሟት የሞተ እና በየትኛውም

ማህበራዊ ደረጃና እድሜ ላይ ያለ ሰው ሲሞት የአስከሬን እጥበትና አገናነዙ ተመሳሳይ ነው፣ ተወልዶ ተንፍሶ ወዲያው የጠፋ ጨቅላ እንኳን ቢሆን በተመሳሳይ መንገድ ይገነዛል (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 6/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

መልካም መዓዛ ያለውን ቀጭኔ በጥጥ እያደረጉ በተለያዩ የአስከሬኑ ክፍሎች ላይ ማድረግና ሽቶ ማርከፍከፍ ለአስከሬኑ ጥሩ መዓዛ ለመስጠት ዓላማ (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 6/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) ከመደረጉ ባሻገር ትዕምርታዊነት ያለው ድርጊት ነው፡፡ አርጐባዎች ከጀነት መገለጫዎች መካከል አንዱ መልካም መዓዛ እንደሆነ የሚያምኑ በመሆኑ ይህን ማድረጋቸው የሟች ነፍስ የጀነት እንዲሆን በመመኘት ለማምሰልም ነው፡፡

አስከሬን የሚታጠበውና የሚገነዘው ከአጣቢና ገናዦቹ ውጭ ሌላ ሰው በሌለበት ቦታ ነው፡፡ የሀዘኑ ቤት ከአንድ በላይ ክፍል ካለው ሰው በሌለበት በአንዱ ክፍል ውስጥ፣ የሀዘኑ ቤት አንድ ክፍል ብቻ ከሆነ ግን ሰዎች ከክፍሉ እንዲወጡ ተደርጐ ስራው ይከናወናል (20/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለፀውም አስከሬን የሚታጠበው በጨርቅ እንደተሸፈነ ሲሆን ጨርቁ የሚነሳውም በቅድሚያ አስከሬኑ ሽርጥ ከተሸረጠበት በኋላ ነው፡፡ አቶ መሐመድ ሀሰን (20/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) እንደገለፁት አስከሬን የሚያጥብ ሰው በተቻለ መጠን የሟች ዘመድ ወይም ቅርብ የሆነ ወዳጅ ቢሆን ይመረጣል፡፡

> ሰውየው ከሞተ ጀምሮ ባለ በማንኛውም ስራ የሚሳተፍ ዘመድ ቢሆን ይመረጣል፡፡ የሚወደውና ቀረብ ያለ ሰው ቢሆን ይመረጣል፡፡ የማይሆን ሰው መጥፎ ነገርም ቢያይ ሄዶ ማውራቱ አይቀርም፡፡ ጥሩውን ነገር ማውራት ነው ኪታቡ ያዘዘው፡፡ እከሌ እኮ ሲያጥቡት ፊቱ ያበራ ነበር፣ ሰውነቱም ልስልስ ያለ ነው፣ ስናጥብ አላስቸገረንም ማለት ነው ጥሩ፡፡ ግን ባዳ ሄዶ ሄዶ መተንፈሱ ስለማይቀር ዘመድ ቢሆን ይመረጣል፡፡ ሰውየው በቁሙም ቢሆን እኮ ለሚወደውና ለቅርቡ ሰው ነው እንጂ ለማንም ሚስጥሩን አይናገርም፣ ስለዚህ ዘመድ ቢሆን ይመረጣል፡፡

ሟቹ ወንድ ከሆነ አስከሬኑን የሚያጥቡና የሚገንዙ ወንዶች ሲሆኑ ሴት ከሆነች ደግሞ አጥበው የሚገንዙ ሴቶች ናቸው፡፡ ነገር ግን ወንድ ሰው ሲሞት ሴቶች ንድፍ ጥጥና ቀጭኔ በማዘጋጀት ወንዶቹን ሊረዷቸው ይችላሉ (20/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

ሰ. የአለቃቀስ ስነ ስርዓት፣ ለቅሶ የመድረስና የመረዳዳት ልማድ

ከዚህ በታች በአርጐባዎች ዘንድ ሞት ሲከሰት የሚከወነው የአለቃቀስ ስነ ስርዓትና በማህበረሰቡ ዘንድ ያለው ሀዘን የመድረስና በሀዘን ጊዜ የመረዳዳት ልማድ ቀርበዋል፡፡

**የአለቃቀስ ስነ ስርዓት፣**

በአርጐባዎች ዘንድ ሀዘንን የማጥበቅና ምርር ብሎ የማልቀስ ልማድ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ግን የሀይማኖት አባቶች እየከለከሉ ይህን አይነት የሀዘን ሁኔታ እየቀረ መጥቷል፡፡ በመሆኑም ለቅሶ ሲለቀስ ቁጭ ተብሎ በለሆሳስ ነው፡፡ ሰዉ ቁጭ ብሎ እያለቀሰ ሀዘኑን ይገልፃል እንጂ ምርር ብሎ ማልቀስ፣ መጮህ፣ ማርገድ፣ መዝለል፣ ደረት መምታት፣ ራስን መጉዳት፣ እየተንጐራደዱ፣ ግጥም እየገጠሙና ዜማ እየቆረጡ ማልቀስ፣ ሟችን በግጥም ማወደስ፣ የተለየ መልበስ፣ ወዘተ በአርጐባ የሚታሰብ አይደለም (17/11/2012 እና 20/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡ ይህን በተመለከተ ወ/ሮ መራኢና መሐመዴ (23/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) "ሲለቀስ መገጣጠም ነውር ነው፡፡ የለቅሶው እምባ በዋንጫ ተጠራቅሞ ለሟች ይጠብቀዋል፡፡ እንደ እሬት የሚመር ሆኖ ነው የሚጠብቀው፡፡ ሟችን በሰማይ ቤት ይኸው ዘመዶችህ ያስቀመጡልህ ጠጣው ይባላል፡፡ ስለዚህ ለሟች እዳ ነው የሚቀመጥለትና ምርር ተብሎ አይለቀስም" ብለዋል፡፡

ቁጭ ተብሎ ሲለቀስ ሟችን እያነሱና በባህርዩና በመልኩ እያወደሱ ማልቀስ የተለመደ ነው፡፡ ሟች በህይወት በነበረች ጊዜ ጐረቤቶቿን የምትጠቀም፣ የምትረዳ፣ የምታበላና የምታጠጣ ከሆነች ይህንኑ ደግነቷን እያነሱ ያለቅሳሉ፡፡ ሟች ጐበዝ ገበሬ ከነበረ ይኸው ጉብዝናው እየተነሳና እየተሞካሸ ይለቀሳል፡፡ ሟች ቆንጆ ከነበረች ወይም መልከ መልካም ከነበረ ቁንጅናና ቁመና እየተነሳ፤ የኔ ብርሌ፣ የኔ ቆንጆ እየተባለ ይለቀሳል (17/11/2012 እና 20/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

ሞት ሲከሰት የሚለቀሰው በዋናነት ሁለት ጊዜ ሲሆን አንደኛው ነፍስ ስትወጣ፤ ሁለተኛው ደግሞ አስከሬን ከቤት ሲወጣ ነው፡፡ ሞት ሲከሰት በአካባቢው ያሉ የቤተሰብ አባላትና

ዘመዶች፣ ምናልባትም ጐረቤቶች ያለቅሳሉ፡፡ አስከሬን ከቤት ሲወጣ ደግሞ ሴቶች ቆመው እያለቀሱ ይሸኛሉ (17/11/2012 እና 20/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡ ወንዶች አስከሬን ይዘውና አጅበው ወደ ቀብር ቦታ ሲሄዱ በመንገድ ላይ ምንም የለቅሶ ድምጽ አይሰማም፤ ምንም ንግግር አይኖርም፤ ጉዞው የሚደረገው በፀጥታ ነው፡፡ የቀብር ቦታ ተደርሶ የቀብሩ ስነ ስርዓት ሲፈፀምም ለቅሶ የለም፤ ቀባሪው ቁርዓን በመቅራት ሀይማኖታዊ ግዴታውን ይወጣል እንጂ አያለቅስም፡፡ የሟች የቤተሰብ አባላት እንኳን ማልቀስ አይፈቀድላቸውም፡፡ የሚያለቅስና የሚያስቸግር የቤተሰብ አባል ቀድሞውኑም ወደ ቀብር እንዳይሄድ ይከለከላል (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 6/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ከዚህ ውጭ ባለ ጊዜ የመጣ ሰው ቁጭ ብሎ ያለቅሳል፡፡ ከቀብር በኋላም ሀዘኑን የሰማና ሩቅ ሆኖ ለቀብር መድረስ ያልቻለ ሀዘን ደራሽ በመጣ ጊዜ ቁጭ ብሎ በማልቀስ እርሙን ያወጣል፡፡ ይህንን አስመልክተው ወ/ሮ ሲቲ ፋጡማ መሐመድ (10/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) "ሸሪያው ደረት ላንመታ፣ ፀጉር ላንበጥስ፣ ሸማ ላንቀድድ ይከለክለናል፡፡ ከዚያ ውጭ ግን ያም ሲመጣ ያም ሲመጣ ያለቅሳል፡፡ ውሏችንን እሬሳ እስኪወጣ ድረስ እናለቅሳለን፡፡ ለቅሶው ለየት ያለ ከሆነ ግን ምነው በጥይት የሞተውን አታይም? አንቺ አስታመሽ ቀብረሽ እንዴት ይኸን መሳይ ለቅሶ ታለቅሻለሽ? ብለን እንቆጣለን" ብለዋል፡፡

በእስልምና አስተምህሮ መሰረት ሰዎች በሚሰበሰቡባቸው ስነ ስርዓቶች ሁሉ ወንዶችና ሴቶች አንድ ላይ ተደባልቀው አይቀመጡም፡፡ በመሆኑም በሀዘን ስነ ስርዓት ጊዜም ሴትና ወንድ ለቅሶ ደራሾች የሚቀመጡት ለየብቻ ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ሴቶች በሀዘኑ ቤት ውስጥና በደጅ በየጥላው ስር ሲሆኑ ወንዶች ደግሞ በዳስ ውስጥ ይሆናሉ (17/11/2012 እና 20/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

### ሀዘን የመድረስና የመረዳዳት ልማድ፣

በአርጐባዎች ዘንድ ለቅሶ አለመድረስ ወዳጅነትንና አንድነትን የሚያሳጣ፣ ቂም የሚያያይዝ፣ ለቅሶዬን በልቶ/በልታ ቀረ/ቀረች የሚያባብል ከባድ ጉዳይ ነው፡፡ በአንድ አካባቢ ያሉ ሰዎች ለቅሶ መድረስ ምንም ጥያቄ የሌለው ሆኖ ሩቅ ቦታ የሚኖሩ ሰዎች በእግር ተጉዘው ለቅሶ ይደርሳሉ (ወ/ሮ ሀይሀሊማ ሱለይማን፣ 21/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የአርጐባዎች የመኖሪያ መልክዓ ምድር ዳገትና ቁልቁለት የበዛበት፣ መንገዱ በጣም አስቸጋሪና ትልልቅ አለቶች የበዙበት ነው፡፡ የአየር ጠባዩም ቆላማ በመሆኑ ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ በቀላሉ ለመንቀሳቀስ አይቻልም፡፡ የወረዳውን ከተማ ጋቻኔን ከሌሎቹ ቀበሌዎች፣ ሌሎቹንም የገጠር ቀበሌዎች እርስ በርስ የሚያገናኙ አልፎ አልፎ ከሚታዩ ሞተር ሳይክሎች ውጭ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የለም፡፡ ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች ከአንድ ቀበሌ ወደ ሌላው ለመሄድ በእግር ከመጓዝ ውጭ ሌላ አማራጭ የላቸውም፡፡ በእድሜ የገፉአዛውንቶች ጭምር በበረሀማው የሚያቃጥል የአየር ጠባይ ለሰዓታት ተጉዘው ያሰቡበት ይደርሳሉ፡፡ ለመስክ ስራ በአካባቢው በቆየሁባቸው ጊዜያት ይህንን ለመረዳት ችያለሁ፡፡ በዚህ ተጨባጭ ሁኔታ ሰዎች በዋናነት ለቅሶ ለመድረስ ሩቅ ከሆኑ ቀበሌዎች ተጉዘው፣ በብዙ ድካምና ጉስቁልና በሀዘን ቤት ይገኛሉ፡፡ ለቅሶ ባለመድረስ የሚመጣን መቀያየም ለማስቀረት መስዋዕትነት ይከፍላሉ፡፡

በተደጋጋሚ ለቅሶ የማይደርሱ ሰዎች ማህበራዊ መገለል ይደርስባቸዋል፡፡ ሀዘን ሲያጋጥማቸው የአስተዛዛኞች፣ የምግብ አዘጋጆች፣ የዳስ ጣዮች፣ የቀብር ጉድጓድ ቆፋሪዎች፣ ወዘተ ቁጥር አነስተኛ ይሆናል፤ አንዳንድ ጊዜም ሰዎች ቀብሩን ቆፍረውና ቀብረው የሚበላውን ሳይበሉ ሊበተኑበት ይችላሉ፡፡ ነገር ግን በህመም ምክንያት በሀዘን ቤት መገኘት የማይችሉና አቅመ ደካማ የሆኑ አዛውንቶች ሀዘን አልደረሱም ተብለው ቂምና መገለል አይደርስባቸውም (ወ/ሮ ሀይሀሊማ ሱለይማን፣ 21/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ይህን ልማድ የሚመለከት የሚከተለው የብሂረሰቡ ምሳሌያዊ አነጋገር በማሳያነት ቀርቧል፡፡

- ቀብር የሀገር ነው፣ ቆዳ የነፍስ ነው (ወ/ሮ ሳሱየ አሊየ፣ 5/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ መደበኛ ያልሆነ ቡድን ተኮር ውይይት)፡፡

ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር ቆዳ የነፍስ ቢሆንም፤ ማለትም ቆዳ ማንጠፍ ወይም ሀዘን መቀመጥ የሀዘንተኞች ቢሆንም ቀብር የመቅበር፣ ሀዘን የመድረስ ሀላፊነት የሀገር - የሁሉም ሰው ሀላፊነት ነው በማለት በብሂረሰቡ ዘንድ ያለውን ሀዘን የመድረስን የጠነከረ ልማድ ይገልፃል፡፡

ዘመድና ጐረቤቶች በሀዘኑ ቤት እየተመላለሱ ከማጽናናት በተጨማሪ ለሀዘንተኞች የጉልበት፣ የዓይነትና የገንዘብ እገዛ ያደርጋሉ፡፡ ሞት በደረሰበት ቤት ሀዘንተኛው እድር

ኖረውም አልኖረውም ዘመድ አዝማድና ጐረቤቶች በመሰባሰብ መሰራት ያለበትን ስራ ይሰራሉ፡፡ ሴቶች ምግብ በማዘጋጀትና በማቅረብ ስራ እገዛ የሚያደርጉ ሲሆን ወንዶች ዳስ ወይም ድንኳን በመጣል፣ የማገዶ እንጨት በማቅረብ፣ ንፍሮ በመቀቀል፣ እርድ ካለ የእርድ ስነ ስርዓቱን በማከናወን፣ የመቃብር ጉድጓድ በመቆፈርና ለመቃብር የሚሆን ድንጋይ ከሩቅ ሄዶ በማምጣት፣ የቀብር ስነ ስርዓቱን በማከናወን እገዛ ያደርጋሉ፡፡ ሞት ሲያጋጥም የጐረቤት ሴቶች ካቦኩት የእንጀራ ሊጥ ቀንሰው ወደ ሀዘኑ ቤት በመውሰድ በአንድ ላይ አድርገው እንጀራ ይጋግራሉ፡፡ ዘመድ የሆነ ወይም ከሟችና ከቤተሰቡ ጋር ጥሩ ወዳጅነት ያለው ሰው ወደ ሀዘኑ ቤት ሲሄድ ለእርድ የሚሆን ፍየል፣ እህል፣ የተፈጨ በርበሬና ሽሮ፣ ወዘተ ይዞ ይሄዳል፡፡ ሟች ዘመደ ብዙ ከሆነ ለሀዘን ስነ ስርዓቱ የሚዘጋጀው ምግብ የተትረፈረፈ ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ዘመዶችም ሆኑ ጐረቤቶች ለሀዘንተኞች የገንዘብ እገዛ ያደርጉላቸዋል (ወ/ሮ ሀይሀሊማ ሱለይማን፣ 21/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

## ሸ. ሀዘን ደራሾችን በምግብ ማስተናገድ

በቀብሩ ቀን የቀብር ስነ ስርዓቱ ከመከናወኑ በፊት በሀዘኑ ቤት የሚገኙት በብዛት ሴቶች ሲሆኑ ብዙ ወንድ በዚያ ሰዓት እዚያ አይገኝም፡፡ ምግብና መጠጥ የሚያዘጋጁም ሆነ ሀዘን ለመድረስ የመጡ ሴቶች የሚቆዩት በሀዘኑ ቤት ነው፡፡ ንፍሮ የሚቀቅሉና ሌሎች ስራዎችን የሚያከናውኑ እንዲሁም ሟቹ ወንድ ከሆነ አስከሬን የሚገንዙ ጥቂት ወንዶች ቢኖሩም ብዙዎቹ ወንዶች የቀብር ጉድጓድ ቁፋሮ ለማከናወን በመቃብር ስፍራው ይቆያሉ፤ ሌሎች ወንዶችም በተለይ ሀይማኖታዊ እውቀት ያላቸው ሰለዋት ጂናዛ በሚደረግበት መስጊድ ወይም የመቃብር ስፍራ በመሆን አስከሬኑን ይጠብቃሉ (አቶ አቡበከር ኑር፣ 28/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በሀዘኑ ቤት የምግብና መጠጥ ስራው እየተከናወነ ከሩቅም ይሁን ከቅርብ የመጡ የሟች ዘመዶችና ወዳጆች እንዲሁም ጐረቤቶች በሀዘኑ ቤት ይሰበሰባሉ፡፡ የምግብ ዝግጅቱ እንዳበቃ ምግብ ይቀርብና ከሩቅ የመጡ እንግዶችን በማስቀደም ሀዘን ደራሾች በሙሉ ይስተናገዳሉ፡፡ ምግቡ ተበልቶ ካበቃ በኋላ ንፍሮ፣ ቡናና ሻይ ይቀርባል፡፡ ለቀብር ቆፋሪዎችና ንፍሮ፤ በመስጊድ ሰለዋት ጂናዛ ለሚሰግዱ የሀይማኖት መምህርና ደረሶች እንጀራ ተፈትፍቶ ይላካል፡፡ በዚያ ቀን በተጣለው ዳስ ውስጥ ወንዶችና ከሩቅ ቦታ የመጡ

ሴቶች ይስተናገዱበታል፡፡ ከቀብር በኋላ ግን በዳሱ ውስጥ የሚያርፉትና የሚስተናገዱት ወንዶች ብቻ ይሆናሉ (17/11/2012 እና 20/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

ወንዶችን የሚያስተናግዱ ወንዶች ሲሆኑ ሴቶችን የሚያስተናግዱ ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡ ወንድ አስተናጋጆች ሴቶች የሚያዘጋጁትን ገበታ፣ ቡናና ሻይ በመውሰድ ወንዶችን ያስተናግዳሉ፡፡ የማስተናገዱን ስራ የሚሰሩት ከሁለቱም ፆታዎች በእድሜ አነስ ያሉ ወጣቶችና በእድሜ ከፍ ያሉ ቢሆኑም ቀልጠፍ ብለው ማስተናገድ የሚችሉ ናቸው፡፡ አስተናጋጆች አስተናግደው ከጨረሱና የተበላበትን እቃ ሁሉ ከመለሱ በኋላ ምግብ የሚመገቡ ሲሆን እርስ በራሳቸው ይስተናገዳሉ (17/11/2012 እና 20/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

### ቀ. አስከሬን ከቤት ሲወጣ የሚከወን ስነ ስርዓት

አስከሬን ወደ መስጊድ ወይም/እና ወደ ቀብር ስፍራ የሚወሰደው አስከሬኑን እስከተገነዘበት አልጋ በመሸከም ሲሆን እድሜ ሳይለይ አቅም ያላቸው ወንዶች በሙሉ እየተጋገዙ ይሸከማሉ፡፡ በቀብር ጉድጓድ ቁፋሮ ላይ የሚሳተፉ ሰዎች በርካታ ስለሚሆኑና ቆፋሪዎቹ ጉድጓዱን ቆፍረው እዚያው ሆነው አስከሬን ስለሚጠብቁ፤ አብዛኛዎቹ ቀባሪዎችም በመስጊድ ወይም በቀብሩ ቦታ ሆነው የሚጠብቁ በመሆኑ አስከሬን ከቤት አውጥተው ወደ መስጊድ ወይም/እና ወደ ቀብር ቦታ የሚወስዱ ሰዎች ለዚሁ ስራ የተመደቡ ብቻ ስለሚሆኑ ቁጥራቸው አነስተኛ ይሆናል፡፡ በጉዞው ላይ አስከሬኑን ያልተሸከሙ ሰዎች ቀድመው፤ ከዚያ በኋላ አስከሬኑን ተሸክመው የሚጓዙ ሰዎች ይከተላሉ፡፡ የቀብር ስነ ስርዓቱ ከተከናወነ በኋላ በዚያው ለሚሄዱ ቀባሪዎች የሚቀምሱት ንፍሮና የቦላ ስጋም ይላካል (17/11/2012 እና 20/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

አስከሬን ከቤት ሲወጣ በሀዘኑ ቤት የተሰበሰቡ ሴቶች እያለቀሱ አስከሬን ይሸኛሉ፡፡ ሴቶች አስከሬኑን እያለቀሱ ይሸኛሉ እንጂ አስከሬን ለመቅበር አይሄዱም፤ የሚሸኙትም እስከ አጥር በር ድረስ ብቻ እንጂ ከአጥር ውጭ አይወጡም (17/11/2012 እና 20/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡ ለዚህ ከሚሰጠው ሀይማኖታዊ ምክንያት (Ismaiel num. 1278) ባሻገር ሴቶች ለቀብር የማይሄዱት ሩህሩህ ስለሆኑና የቀብር ስነ ስርዓቱን ያውካሉ ተብሎ ስለሚታሰብ ነው የሚል ምክንያት ይሰጣል፡፡ ይህን በተመለከተ አቶ ሁሴን ጢኖ (9/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) በድሮ ጊዜ ሴቶች ለቀብር ሄደው አስከሬኑ

ከተቀበረ በኋላ ተመልሰው አስከሬኑን እናውጣ አሉ የሚባል ተረት መኖሩን እንደ ምሳሌ በማንሳት ሴቶች ሩህሩህ፣ ሆደ ቡቡና መቁረጥ የማይችሉ በመሆናቸው ለቀብር አይሄዱም ብለዋል፡፡

አስከሬን ከቤት ከወጣ በኋላ አብዛኛዎቹ ሀዘን ለመድረስ በሀዘኑ ቤት የተገኙ ሴቶች ሀዘንተኞችን ተሰናብተው ወደየቤታቸው ይሄዳሉ፡፡ የሚሰናበቱት ሴት ሀዘንተኞችን ሲሆን ወደ ሀዘንተኞች ቀርበውና የሀዘንተኞቹን እጅ ይዘው ሟች አዋቂ ሰው ከሆነ "እናንተንም አላህ ይሶብራችሁ፤ ሟቹንም/ሟቿንም አላህ ይማረው/ይማራት" በማለት፤ ሟች ህፃን ከሆነ ደግሞ "እናንተንም አላህ ይሶብራችሁ፤ እሱንም/እሷንም ሸፍዓ ያድርገው/ያድርጋት" በማለት ነው፡፡ ህፃን የጀነት ነው ተብሎ ስለሚታመን ይማረው አይባልም፡፡ ከዚያ በኋላ ሀዘን ደራሾች እንደ አቅምና ከሀዘንተኞች ጋር እንዳላቸው ቀረቤታ መጠኑ ሊለያይ የሚችል ገንዘብ ለሀዘንተኞች በማስጨበጥ ይሰጧቸዋል (17/11/2012 እና 20/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

አስከሬን በመንገድ ሲያልፍ መንገድ ላይ ያለ ሰው ከተቀመጠበት ተነስቶ ይሸኛል፡፡ አስከሬን ሲያልፍ ቆሞ የታየ ወይም ያልሸኘ ሰው ነውር ይሆንበታል፤ ቅሬታን ይፈጥራል፤ ይወገዛል፡፡ አስከሬን መሸኘት መተዋወቅን አይጠይቅም፡፡ አስከሬን ለቀብር ሲወሰድ ያጋጠመው ሰው ሟችን ወይም የሟችን ቤተሰብ አወቀም አላወቀም መሸኘት እንደ ግዴታ ይቆጠራል፡፡ አስቸኳይ ጉዳይ ያጋጠመው ሰው እንኳን ቢሆን ትንሽ ሸኝቶ ጉዳዩን ተናግሮ ይመለሳል እንጂ ባለበት ቦታ ቆሞ አስከሬን አያሳልፍም፡፡ አስከሬን መስጊድ ሲገባም ቁጭ ያለው ሰው ሁሉ ብድግ ብሎ አስከሬኑን ያሳልፋል (አቶ አቡበከር ኑር፣ 28/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

አስከሬን ከቤት ከወጣ በኋላ ሰለዋት ጀናዛ ይደረጋል፡፡ የሰለዋቱን ምንነትና ዓላማ በተመለከተ አቶ አቡበከር ኑር (28/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> ወንዶቹ ሰለዋት እንላለን፡፡ ይማረው እየተባለ የሚደረግለት ዱዓ አለ፡፡ ሰለዋት የምንለው አንድ ማለት የሚችል መሪ ካለ ለመከተል ትምህርት የሌለውም መከተል ይችላል፡፡ ውዳሴ ነው የምናደርገው፡፡ ጌታችንን ነው የምናወድሰው፡፡ በነቢያችን

ላይ ራህመት ይውረድ ነው የምንለው፡፡ ያ የምንለው ነገር ጥቅም አለው፡፡ በአምላክ ዘንድ ምንዳ አለው ብለን እናምናለን፡፡ ያ ምንዳ እኛ እያልነው ለእሱ [ለሟች] እንዲደርስለት ነው የምንለው፡፡ ስጦታ እንዲሆንለት ነው፡፡

ሰለዋት የሚደረግበት ቦታ ከቦታ ቦታ ይለያያል፡፡ አንደኛው ቦታ የመስጊድ ቅጥር ግቢ ሲሆን ሁለተኛው ቦታ የቀብር ስፍራ ነው፡፡ አስከሬንን ወደ መስጊድ ወስዶ ሰለዋት ማድረግ አብዛኛውን ጊዜ የከተማነት ባህርይ ባለው በጋቸኔ አካባቢ የሚከናወን ሲሆን በሌሎቹ የገጠር ቀበሌዎች ግን በአብዛኛው ሰለዋት ጀናዛ የሚደረገው አስከሬኑን ወደ ቀብሩ ስፍራ በመውሰድ እዚያው ነው (አቶ አቡበከር ኑር፣ 28/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ሰለዋቱ ሲደረግ አስከሬኑ "ጡሀራ" በሆነና ጥላ ባለው ቦታ ላይ ከሰጋጆቹ ፊት ይደረጋል፡፡ ሰለዋት ጀናዛ በፈጣሪ ዘንድ ተቀባይነት የሚኖረው በእድሜ ገፋ ያሉ ሰዎች ሲመሩት ነው ተብሎ ስለሚታመን ለሰለዋት ጀናዛ መሪ ወይም አሰጋጅ የሚሆን ሰው በእድሜ ገፋ ያለ አዛውንት እንዲሆን ይመረጣል፡፡ ሌሎች በእውቀት የሚበልጡ ቢኖሩ እንኳን እውቀት ለዚህ አይነቱ ሰለዋት መሪነት መመዘኛ አይሆንም፡፡ ተከታይ ሰጋጆች በመስጊዱ የሀይማኖት ትምህርት የሚማሩ ደረሶች፣ አስከሬኑን ከሀዘኑ ቤት ይዘው የሄዱ ሰዎችና አስከሬኑን ቀድመው በመስገጃው ቦታ ሲጠብቁ የቆዩ ሰዎች ናቸው (አቶ አቡበከር ኑር፣ 28/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ሰለዋቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ሰጋጆች የሟች ቤተሰብ አባልን ወይም አባላትን፣ ሟች ቤተሰብ ከሌለው ደግሞ ቀረብ የሚለውን ዘመድ ከብበው በመቀመጥ ቁርዓን ከቀሩ በኋላ የቀብር ጉድጓድ ቁፋሮው ካልተጠናቀቀ በሁለቱም ቦታ አስከሬኑ እዚያው በጥላ ስር እንዲቆይ ይደረጋል (አቶ አቡበከር ኑር፣ 28/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የቀብር ስነ ሰርዓቱ የሚከናወነው መደበኛ ስግደት በሚደረግበት ሰዓት አካባቢ ከሆነ የሰዓቱ ስግደት ይደረግና ስግደቱ መስጊድ ውስጥ የተከናወነ ከሆነ አስከሬኑ ተይዞ ወደ ቀብር ቦታ ይኬዳል፤ ስግደቱ የተከናወነው በቀብር ቦታው ከሆነ ከስግደቱ በኋላ የቀብር ስነ ስርዓቱን ማከናወን ይጀመራል፡፡ ሰለዋቱ የሚባለው በመስጊድ ከሆነና ሰግደው ወደ ቀብር ሳይሄዱ በዚያው የሚሄዱ ሰዎች ካሉ በመስጊዱ መውጫ በር ላይ ንፍሮና ቦላ ስጋ የያዙ ሁለት

ሰዎች በመቆም ከሁለቱም በእጅ በእጃቸው ያድሏቸዋል (አቶ አቡበከር ኑር፣ 28/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

### በ. የቀብር ስነ ስርዓት

የቀብር ስነ ስርዓት በተቻለ መጠን በቶሎ እንዲከናወን ይፈለጋል፡፡ በተለይ ሟች በአደጋ ሞቶ ደሙ መቆም ካልቻለ፣ እብጠት ካለ፣ ወይም ሌላ አስከሬን ሊበላሽ የሚችልባቸው አስገዳጅ ምክንያቶች ካሉ የቀብር ስነ ስርዓት በቶሎ ይከወናል፡፡ ነገር ግን የቀብር ሰዓት እንዲራዘም የሚያደርጉ ምክንያቶች አሉ፡፡ ከእነዚህ ምክንያቶች መካከል ዋናዎቹ ሁለት ሲሆኑ እነዚህም ሩቅ ያለ የቤተሰብ አባል ወይም ዘመድ ይድረስ ተብሎ መጠበቁ እና የቀብር ጉድጓድ ቆፍሮ ለማዘጋጀት ረዘም ያለ ሰዓት የሚወስድ መሆኑ ናቸው (አቶ አሕመድ ሲራጅ፣ 28/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በምዕራፍ አራት እንደተገለፀው በወረዳው ይኖሩ የነበሩ በርካታ አርጐባዎች በተለያዩ ምክንያቶች አካባቢውን በመልቀቅ ኑሯቸውን በተለያዩ የክልል ከተማዎች አድርገዋል፡፡ ለምሳሌ፣ በርካቶች ኑሯቸውን በአዋሽ ሰባት ኪሎ፣ በደብረ ብርሃን፣ በሚኤሶ፣ በአስበ ተፈሪ፣ በመተሀራ፣ በናዝሬት፣ በአዲስ አበባና በሌሎች አካባቢዎች መስርተዋል፡፡ እነዚህ ተራርቀው የሚኖሩ አርጐባዎች ታዲያ በደስታም ሆነ በሀዘን ይገናኛሉ፡፡ ሞት ሲከሰት በርካታ ኪሎ ሜትሮችን አቋርጠው ሀዘን ይደርሳሉ፡፡ በመሆኑም በወረዳው ሰው ሲሞት በተጠቀሱና በሌሎችም አካባቢዎች ለሚኖር ዘመድ አዝማድ ይነገራል፡፡ ርቀው ከሚኖሩ ሰዎች መካከልም የሟች ቤተሰብ አባላት ወይም በጣም የቅርብ ሰዎች ካሉ እነርሱ ሳይመጡ የቀብር ስነ ስርዓት አይከናወንም ተብሎ የቀብሩ ሰዓት እንዲራዘም ይደረጋል፡፡ አሊም ሲሞትም በተለያዩ አካባቢዎች የሚኖሩ የሀይማኖት አባቶች ለቀብሩ ይድረሱ ሲባል የቀብሩ ሰዓት እንዲሁ እንዲራዘም ይደረጋል፡፡ በዚህ ምክንያት አስከሬን ሳይቀበር እንዲቆይ ይሆናል፡፡

ሌላው ጉዳይ የቀብር ጉድጓዱን ቆፍሮ ለመጨረስ የሚወስደው ሰዓት ነው፡፡ የመቃብር ጉድጓድ ሲቆፈር ወደታች ጥልቀት እንዲኖረው ተደርጐ፣ ወደ ጐን ለኸድ ተበጅቶና ለስልሶ ነው፡፡ ጉድጓዱ የሚቆፈረው በርከት ባሉ ሰዎች ቢሆንም ይህን አይነቱን ጉዳጓድ ቆፍሮ ለማዘጋጀት ረዘም ያለ ጊዜ ይፈልጋል፡፡ በተለይ የመሬቱ ዓይነት ድንጋያማ ወይም ጥብቅ ሆኖ ለመቆፈር የማይገራ ሲሆን ተጨማሪ ሰዓቶችን ይወስዳል፡፡ እነዚህ ምክንያቶች

በሌሉበት ሁኔታ የቀብር ስነ ስርዓት ቶሎ የሚከናወን ሲሆን የቀብር ሰዓትም በአብዛኛው ከቀትር በኋላ ፀሀይ በረድ ሲል፣ ከአሱር ስግደት በኋላ ይሆናል፡፡ አስከሬን የመቅበሪያ ሰዓት ፀሀይ በረድ ሲል እንዲሆን የሚፈለገው ቀትር ላይ መሬቱ ስለሚግልና በብሄረሰቡ አባላት ዘንድ ደግሞ በጋለ መሬት አስከሬን መቅበር ከስነ ምግባር አንፃር አግባብ አይደለም ተብሎ ስለሚታሰብ ነው (አቶ አሕመድ ሲራጅ፣ 28/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የቀብሩ ስነ ስርዓት ሰለዋት ጀናዛ የተደረገው በመስጊድ ከሆነ ሰለዋቱ ሲያልቅ ቀባሪዎች አስከሬኑን ይዘው ወደ ቀብር ስፍራ በመሄድ፤ ሰለዋቱ የተደረገው በቀብሩ ስፍራ ከሆነ ሰለዋቱ እንዳበቃ ሊከናወን ይችላል፡፡ በቀብር ስፍራው የቀብሩ ጉድጓድ ተስተካክሎ አልቆ ከሆነ የቀብር ስነ ስርዓቱን ወዲያው ማከናወን የሚቻል ሲሆን ጥቂት ስራዎች ከቀሩ አስከሬኑን በጥላ ስር በማድረግ ይጠበቃል፡፡ ስራው ሲጠናቀቅ የቀብር ስነ ስርዓቱ ይከወናል (አቶ አሕመድ ሲራጅ፣ 28/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

አስከሬን የሚቀበረው በቀኝ ጐኑ ፊቱ ወደ ሰሜን አቅጣጫ፣ ጭንቅላቱ ወደ ምስራቅና እግሩ ወደ ምዕራብ ተደርጐ፤ አስከሬኑ በጀርባው እንዳይገለበጥ እግሩ በመጠኑ አጠፍ ተደርጐና አስከሬኑ የሚሸፈንበት ነጠላ ጋቢ በፊቱ በኩል ገለጥ ተደርጐ ፊቱ በግማሽ አፈር እንዲነካው መሬቱ ላይ ተደርጐ ነው (አቶ አሕመድ ሲራጅ፣ 28/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ በእስልምና ሀይማኖት ስግደት፣ ዝኪርና ሌላውም ሀይማኖታዊ ስነ ስርዓት የሚደረገው ፊትን ወደ ሰሜን አቅጣጫ (ቂብላ) በማድረግ በመሆኑ (*The Quran,* Al-Baqara 2:144) እዚህም የአስከሬን ፊትን ወደ ሰሜን አቅጣጫ አድርጐ መቅበሩ ሀይማኖታዊ መሰረት ያለው ድርጊት ነው፡፡

በመሆኑም ቀባሪዎች አስከሬኑን በመሸከም በቀብር ጉድጓዱ ውስጥ ላሉ ቀባሪዎች ሲያቀብሏቸው ጉድጓዱ ውስጥ ያሉ ቀባሪዎች አስከሬኑን ተቀብለው ከላይ በተገለፀው መልኩ አስተካክለው አስከሬኑን በለኸዱ ውስጥ ያስተኛሉ፡፡ ቀባሪዎቹ አስከሬኑን በአግባቡ ማስተኛታቸውን ሲገልፁ እነርሱን በመከተል ቀባሪዎች ቁርዓን መቅራት ይጀምራሉ (አቶ አሕመድ ሲራጅ፣ 28/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ሟች ከተቀበረ ጊዜ ጀምሮ ለሰባት ቀናት ያህል የመጠየቂያው ጊዜ ነው፡፡ መላዒካዎች በመቃብር እየቀረቡ ጌታው ማን እንደሆነና ሌሎችም ጥያቄዎችን ያቀርቡለታል፣ እርሱም

ለሚቀርቡለት ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል፡፡ ሰባቱ ቀን ሟች በጥያቄ የሚያዝበት የጭንቅና የፍርሀት ጊዜ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ይህን በተመለከተ አቶ አሕመድ መሐመድ (16/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> ይሄ የቀብር ኑሮ ፍርድ ያልተሰጠውን እስረኛ ኑሮ ይመስላል፡፡ እንደ እስር ቤት መቆያ ነው፡፡ ተጠርጣሪ ሆኖ የታሰረ ሰው ወንጀሉን እስኪያምን ድረስ ይጠየቃል፡፡ ልክ እንደዚያ በቀብር የሚያስቀጣ ያስቀጣዋል፡፡ በህይወት ዘመኑ ጥሩ የሰራ ከሆነ ወደ ፊት የሚገባበት ጀነት እየተገለጠለት አብሽር እየተባለ፣ ወደ ፊት በዚህ ነው የምትገባው እየተባለ እየተበሸረ ይቆያል፣ መጥፎ ስራ የሰራ ደግሞ ጀሀነም እየተገለጠለት ማስፈራሪያ ይደረግበታል፡፡ ከሰባት ቀን በኋላ ሁሉም እንደ ስራው ጀነትና ጀሀነብ ይገባል፡፡

በመሆኑም ቀብር እንደተከናወነ ሟች በመቃብሩ ውስጥ ሆኖ እንደሚሰማ ስለሚታመን ለሚመጣበት ጥያቄ መስጠት ያለበት መልስ ቁርዓን እየተቀራ ይነገረዋል (አቶ አሕመድ ሲራጅ፣ 28/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ቁርዓኑ እየተቀራ ለኸዱ በድንጋይ ተዘግቶ፣ ዙሪያውንና በመሀል በመሀል ክፍተት ያለበት ቦታ በትንንሽ ድንጋዮች እየተሞላ በጭቃ ይመረግና አስከሬኑን ያስተኙና ድንጋዩን የዘጉ ሰዎች ከጉድጓዱ ወጥተው አፈር ተመልሶ የፊት ለፊቱ ጉድጓድ ይሞላል፡፡ ለኸዱን የመዝጋትና አፈር የመመለስ ስራው በህብረት የሚከናወን ሲሆን ቀባሪዎቹ ስራውን እየሰሩ በተመሳሳይ ሰዓት ቁርዓኑንም እየቀሩ በእኩል ሰዓት ያጠናቅቃሉ፡፡ ከዚያ በኋላ በመቃብሩ ላይ ውሃ ተርከፍክፎና እርጥብ ቅጠልም ተጐዝጉዞ ምልክት የሚሆን ትልቅ ድንጋይ በመቃብሩ መካከል ላይ ይተከላል፡፡ በብሂረሰቡ ዘንድ ጀነት ቀዝቃዛ፣ ወንዞችና ጅረቶች የበዙበት፣ እርጥብ ቅጠሎች ባሏቸው ዛፎች የተሞላ እንደሆነ የሚታመን በመሆኑ ውሀ ማርከፍከፍና እርጥብ ቅጠል መጐዝጐዝ የሟች ነፍስ የጀነት እንዲሆን መመኛና ማምሰያ ድርጊት ነው (አቶ አሕመድ ሲራጅ፣ 28/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የቀብር ስነ ስርዓት ከተከናወነ በኋላ በአብዛኛው ሩቅ ከሆነ አካባቢ የመጡና የማያድሩ ቀባሪዎች በዚያው ወደየቤታቸው ይሄዳሉ፡፡ ሀዘንተኞች በዚያው የሚሄዱ ቀባሪዎችን

ለማሰናበት ጥላ ስር ቁጭ ይላሉ፡፡ ቀባሪዎቹም ወደ ሀዘንተኞቹ ጠጋ ብለው እጃቸውን በመጨበጥ ሟች አዋቂ ሰው ከሆነ “እናንተንም አላህ ይሶብራችሁ፤ ሟቹንም/ሟቿንም አላህ ይማረው/ይማራት” በማለት፤ ሟች ህፃን ከሆነ ደግሞ “እናንተንም አላህ ይሶብራችሁ፤ እሱንም/እሷንም ሸፍዓ ያድርገው/ያድርጋት” በማለት ይሰናበታሉ፡፡ ቀባሪዎቹ በሌላ ቀን የማይመለሱ ከሆነ እንደ አቅማቸውና ለሀዘንተኞች እንዳላቸው ቅርበት መጠን መቶም ሀምሳም ብር ጨበጥ አድርገው ለሀዘንተኞች ይሰጧቸዋል፡፡ ቀባሪዎች ተሰናብተው ሊሄዱ ሲሉ የተላከውን ንፍሮና ቦላ የሚያድሉ ሁለት ሁለት ሰዎች በመሆን ቀባሪዎች በሚሄዱባቸው መንገዶችና አቅጣጫዎች ሁሉ በመቆም ለቀባሪዎች ከንፍሮውና ከቦላ ስጋው በእኩል መጠን በእጅ በእጃቸው ያድሏቸዋል (አቶ አሕመድ ሲራጅ፣ 28/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በአርጐባዎች ዘንድ የቀብር ስነ ስርዓት ከተፈፀመበት ቀን ጀምሮ እስከ ሰባት ቀን ድረስ ነፍስ ወደ ዘላቂ ማረፊያዋ እንደማትሄድና ከአስከሬኑ ጋር በመቃብር እንደምትቆይ ይታመናል፡፡ ይህ የመቃብር ቆይታ ደግሞ ድቅድቅ ጨለማ የዋጠው፣ ጭንቅ ያለበት፣ ሟች አስጨናቂ ጥያቄ የሚጠየቅበት እንደሆነ ይታመናል፡፡ የሚከተለው ምሳሌያዊ አነጋገር ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው፡፡

- በቀብር ውስጥ የዱንያ ሀገር ንፋስ አይገኝም (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 29/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ መደበኛ ያልሆነ ቡድን ተኮር ውይይት)፡፡

በዚህ ምሳሌያዊ አነጋገር በገሀዱ ዓለም ያለው አኗኗር ንፋስ ተብሎ ተገልፆ በሙታን ዓለም፣ በመቃብር ውስጥ የሌለ መሆኑንና መቃብር አስጨናቂ መሆኑ ተገልጿል፡፡

### ተ. በቀብር ቀን ከቀብር መልስ የሚከወን ስነ ስርዓት

የቀብር ስነ ስርዓት ከተከናወነ በኋላ በዚያው ተሰናብቶ የሄደ ሰው ሄዶ ጐረቤትና ከሩቅ ቦታ መጥቶ የሚያድር ወይም ሀዘንተኞችን አጅቦ ቤት አስገብቶ ለመሄድ ያሰበ ወዳጅ ዘመድ የሆነ ቀባሪ ወደ ሀዘኑ ቤት ይመለሳል፡፡ ቀባሪዎቹ እንደተመለሱ በሀዘኑ ቤት ሲደርሱ ውሀ ይዘው የሚጠብቋቸው ሰዎች እያስታጠቧቸው ሁሉም እጃቸውን እየታጠቡ ወደ ዳሱ ይገባሉ፡፡ እጅን በውሀ መታጠብ ከንጽህና ዓላማ ባሻገር የሆነ ትርጉምን የያዘ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው፡፡ ውሀ ህይወትን፣ መንፃትንና ተስፋንና መሻገርን ይወክላል፡፡

ከቀብር የሚመለሱ ሰዎች እጃቸውን መታጠባቸው ከገጠማቸው ሞት ባሻገር ህይወትን መሻታቸውን ወይም መናፈቃቸውን፣ ከደረሰው ሀዘን ወደ ህይወት መሻገር መፈለጋቸውንና መመኘታቸውን፣ ከደረሰው የሀዘን ስሜት መውጣትንና ህይወትን፣ ተስፋን መመኘታቸውን ይገልፃል፡፡ ከዚያ በኋላ ንፍሮ በትሪ እየተደረገ በቡድን በቡድን ይቀርብላቸዋል፤ ቡናና ሻይም ይቀርባል፡፡ ከዚያ በኋላ ሰለዋት ይጀመራል፡፡ የሰለዋት መጽሐፍ ባለ ብዙ ገጽ በመሆኑ በአንድ ጊዜ ቁጭታ አይጨረስም፡፡ በመሆኑም ከቀብር መልስ ይጀመርና ወንዶች ሲሰባሰቡ እያሉት እስከ ሰባተኛው ቀን ድረስ ያልቃል፡፡ ሲጠናቀቅም የማክተሚያ ተብሎ ጣፋጭ ምግብ ተዘጋጅቶና ቡና ተፈልቶ ሰለዋቱን ሲያደርጉ ለነበሩ ሰዎች ይቀርባል፡፡ በመሆኑም በቀብሩ ቀን አንድ ምዕራፍ ብቻ ያልቅና ሰዎች ደክሟቸው ውለው ሊሆን ይችላል ተብሎ በይደር ይቀመጣል፡፡ ከዚያ በኋላ ምሽት ድረስ ሀዘንተኞችን ሲያጽናኑና ሲጫወቱ ይቆያሉ፡፡ ከሩቅ ቦታ የመጡ ሀዘን ደራሾች ሀዘንተኞችን አስተዛዝነው ሲሄዱ ተሰናብተው የሚሄዱ ሲሆን በሀዘኑ ቤት ወንድ ሀዘን ደራሾች ወንድ ሀዘንተኞችን፣ ሴት ሀዘን ደራሾች ደግሞ ሴት ሀዘንተኞችን ይሰናበታሉ፡፡ የአካባቢ ሰው ግን በጉርብትናው መሰረት ተመላልሶ ሀዘንተኞችን ስለሚያጽናና አይሰናበትም (አቶ ኢብራሂም መሐመድ፣ 27/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

## ቸ. የሀፈሻ ስነ ስርዓት

ከቀብሩ ቀን በኋላ ያሉት ስድስት ቀናት ሀዘንተኞች ቁጭ ብለው እንግዶቻቸውን የሚቀበሉበት፣ ጎረቤቶች ቤቶቻቸውን እየተዉ በሀዘኑ ቤት ከሀዘንተኞች ጋር እየዋሉና እያደሩ፣ የሀዘንተኞችን ስራ እያከናወኑ፣ ምግብ ከቤታቸው እየወሰዱና ዱዓ እያደረጉ ሀዘንተኞችን የሚያስተዛዝኑባቸው የሀዘን ቀናት ናቸው፡፡ በእነዚህ ቀናት ሀዘን ያልደረሱ ሰዎች ይደርሳሉ፤ ሀዘን የደረሱም እየተመላለሱ ሀዘንተኞችን ያጽናናሉ፤ ይደግፋሉ (አቶ ኢብራሂም መሐመድ፣ 27/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ሀዘንተኞች ከሚደገፉባቸው መንገዶች አንዱ ደግሞ የሀፈሻ ስነ ስርዓት ነው፡፡

የሀፈሻ ስነ ስርዓት ከቀብሩ ቀን ምሽት ጀምሮ ጎረቤቶች ምግብ ይዘው ወደ ሀዘኑ ቤት በመሄድ ሀዘንተኞችን የሚያስተዛዝኑበት ስነ ስርዓት ነው፡፡ በሀዘኑ ጊዜ ሀዘንተኞች፣ ጎረቤቶችና ከሩቅ የሚመጡ ሀዘን ደራሾች የሚስተናገዱት ጎረቤቶች ባመጡት ምግብ

ሲሆን በሀዘኑ ቤት የሚዘጋጅ ምግብ አይኖርም[33] (3/10/2012፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ምልከታ) (አቶ ኢብራሂም መሐመድ፣ 27/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ሼህ ጧሂር ኑሬ (24/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) የሀዘንተኞችን ምግብ ያለመብላት ልምድና ሀፊሻ የጀመረበትን ሁኔታ በሚከተለው መልኩ አስረድተዋል፡፡

> ጃዕፈር የነቢያችን የአጐታቸው ልጅ ነው፡፡ በመጀመሪያው ስደት መጥቶ ከነጃሺ ጋር የተገናኘ ነው፡፡ ከዚህ እንደተመለሰ ለጦርነት ተልኮ እዚያ ነው የሞተው፡፡ የሞተው ሩቅ ቦታ ነው ግን ነቢያችን መልዕክቱ እስከሚመጣ አልጠበቁም፣ እዚሁ ሆነው ጃዕፈር ተሰዋ፣ እኔንም ታዕዚያ አድርጉኝ፣ ቤተሰቦቹንም አስተዛዝኗቸው፣ ምግብ እየያዛችሁ ሂዱ ብለው አዘዙ፣ ለጃዕፋር ልጆችና ሚስት ማለት ነው፡፡ ለሚች ቤተሰብ ምግብ ይዞ መሄድ የተጀመረው ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ ስለዚህ ሴቶች እንጀራ ይወስዳሉ፣ ወንዶቹ ስኳርም፣ ጫትም እንወስዳለን፡፡

ጐረቤቶች ይዘው የሚሄዱት ምግብ እንደየአቅማቸው ሁለትም ሶስትም እንጀራ ከወጥ ጋር፣ ቡና፣ ሻይና ቆሎ ነው፡፡ እንጀራና ወጡ የሚወሰደው ለየብቻ ሆኖ ሲሆን በሀዘኑ ቤት ከሁሉም ቤት የሚሄደው እንጀራና ወጥ በአንድ ላይ ተቀይጦ በየመመገቢያ ሰዓት ከዚያ እየተቀነሰ ይቀርባል፡፡ ለደረሰ ሁሉ ቁርስ፣ ምሳና እራት፤ ከቁርስ፣ ምሳና እራት ሰዓት ውጭ ለሚመጣ ሻይ፣ ቡናና የማሽላ ቆሎ ይቀርባል፤ ወንዶቹ የሱቢህና የአሱር ሰለዋት ሰግደው ሲጨርሱም ምግብ ይቀርባል (3/10/2012፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ምልከታ) (አቶ ኢብራሂም መሐመድ፣ 27/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ለሀዘን ቤቱ ከሚመጡ የበሰሉ ምግቦች በተጨማሪ ሰዎች ለሀዘንተኞች እንዳላቸው ቅርበትና ወዳጅነት ማሽላ ወይም ጤፍ ጭነው፣ ፍየል ስበው፣ ሽሮና በርበሬ አስፈጭተው ይዘው ሊሄዱ ይችላሉ፡፡ ይህ በሚሆን ጊዜ በሀዘኑ ቤት እህሉ ተፈጭቶ ይጋገራል፣ ፍየሉም ታርዶ ወጥ ይሰራበታል፡፡ ከሚች ወይም ከሀዘንተኞች ንብረት ውጭ ያለ በመሆኑ ሰዎች በዚያ ይስተናገዳሉ፡፡ የምግብ ማዘጋጀቱን ስራም ጐረቤት የሆኑ ሴቶች ይወጡታል (3/10/2012፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

[33] እድር በተቋቋመባቸው አካባቢዎችም ቢሆን

በእነዚህ ቀናት ሴት ሀዘንተኞች በተነጠፈ መዋስ ላይ ቁጭ በማለት ሴት ሀዘን ደራሾችን ይቀበላሉ፡፡ ወንድ ሀዘንተኞች ደግሞ በተጣለው ዳስ ውስጥ በተጉዘጉዘ ቅጠል ላይ ቁጭ ብለው ወንድ ሀዘን ደራሾችን ይቀበላሉ፡፡ የሚመጡ ወንድ ሀዘን ደራሾች ፋቲሃ ይላሉ፡፡ ሀዘን ለመድረስ የሚመጣ ወንድ ወደ ዳሱ ሲገባ ቀድመውት በዳሱ ውስጥ የነበሩ ወንዶችን እየዞረ አንድ በአንድ ሁሉንም ዘይሮ ይቀመጣል፡፡ ከዚያ በኋላ ፋቲሃ አባብሉኝ ብሎ በጋራ ፋቲሃውን ይላሉ፡፡ ፋቲሃ ለሀዘንተኞች መጽናናት፣ ለሟች ደግሞ ምህረት እንዲሆን የሚደረግ መማፀኛ ነው፡፡ በቀብሩ ቀን የተወሰነ ክፍል የተባለው ሰለዋትም ከቆመበት እየተቀጠለ ይባላል (አቶ ኢብራሂም መሐመድ፣ 27/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ይህንን የሽግግር ጊዜም ከሟችና ከሟች ቤተሰብ አንፃር መመልከት ይቻላል፡፡ ከሟች አንፃር ይህ ጊዜ ሟች ከገሀዱ ዓለም የተነጠለበት ነገር ግን ነፍሱ ወደ ዘላቂው የሙታን ዓለም ያልተቀላቀለችበት፣ በመቃብር ሆኖ ጥያቄ የሚጠየቅበት፣ የሚጨነቅበት፣ የነፍሱ መዳረሻ ገና ያልተለየበት ጊዜ ነው፡፡ ከሟች ቤተሰብ አንፃር ሲታይም ይህ ጊዜ የሟች ቤተሰብ አባላት ሀዘንተኞች በመሆናቸው ቀደም ሲል ከነበራቸው የቀን ተቀን እንቅስቃሴ የተነጠሉበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ቤተሰቡ በተከሰተው ሀዘን መረበሽና መጨነቅ የሚደርስበት፣ ማህበራዊ ኑሮውን የማይጀምርበት፣ የቤት ውስጥ ስራዎችን የማያከናውንበትና ከሌላው ቀን በተለየ አብሮ የሚመገበው ጎረቤቶች አዘጋጅተው የሚያመጡለትን ምግብ የሚሆንበት ጊዜ ነው፡፡

### 7.2.3. መቀላቀል

የመቀላቀል ደረጃ ከቆዳ ማጠፊያ ስነ ስርዓት ክዋኔ ጀምሮ ከዚያ በኋላ ያሉ የሙት መታሰቢያ ስነ ስርዓቶች የሚከወኑበትን ጊዜ በሙሉ ያጠቃልላል፡፡ ቆዳ ማጠፊያ የመጀመሪያው የመታሰቢያ ስነ ስርዓት ሲሆን የሟች ነፍስ ወደማይታየው ዓለም እንደምትቀላቀል የሚታመንበት፤ ሀዘንተኞችም በመጠኑ ወደቀደመው የቀን ተቀን የህይወት እንቅስቃሴያቸው የሚመለሱበት በመሆኑ የመቀላቀል ደረጃ የሚጀምርበት መነሻ ነው፡፡

የመቀላቀል ጊዜ ዋና መገለጫዎች የሆኑት የመታሰቢያ ስነ ስርዓቶች በብሄረሰቡ ዘንድ ባሉ ሞት የመጨረሻ ጉዳይ ሳይሆን አሻጋሪ ነው፤ የሟች ነፍስ ከሞት በኋላ ከገሀዱ ዓለም

ተነስታ ወደማይታየው ዓለም ትደርሳለች፤ አንድ ጊዜ ከገሀዱ ዓለም የተለየች ነፍስ ደግሞ መንገዱ እንዲስተካከል፣ ከፈጣሪ ምህረት እንድታገኝና በዚያኛው ዓለም እንድትደላደል የመታሰቢያ ስነ ስርዓቶች ተደርገው ሶደቃና ዱዓ ማድረግ ያስፈልጋል የሚሉ እምነቶች መሰረትነት የሚከወኑ ናቸው፡፡

ሶደቃ የሚቀርብ ምግብና መጠጥ ነው፡፡ ሶደቃ የሚደረገው የሟች ነፍስ ወደ ወዲያኛው ዓለም የምታደርገውን ጉዞና በዚያ የሚኖራትን ቆይታ ጥሩ ያደርጋል፤ ከፈጣሪ ምህረትን እንድታገኝና የጀነት እንድትሆን ያደርጋል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ሰው ተመግቦ ደስ መሰኘቱና የተራበም መብላቱ ዋጋ ሆኖ ለሟች ነፍስና ለሌሎች ነፍሳትም ምህረት ያስገኛል ተብሎ ይታመናል፡፡ በየጊዜው የሚደረገው ሶደቃም ሟች በህይወት ዘመኑ የሰራውን ሀጢያት እየሸረፈ፣ እየቀነሰ በመሄድ ነፃ ያደርገዋል ተብሎ ይታመናል (አቶ መሐመድ ሱፌማን፣ 4/4/2013፣ ጩኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ይህን በተመለከተ በቅደም ተከተል አቶ ኢብራሂም ወርቄ (9/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) እና አቶ ኑሩ መሐመድ ሰኢድ (13/7/2013፣ አባሊ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) የሚከተሉትን ብለዋል፡፡

> ሰው ሲወልድም ስጦታ ይሰጣል፤ ሲያገባም ይሰጣል፤ በሞተ ጊዜ ለሀዘንተኛው ሀፈሻ ይወሰዳል፣ ለሟች ደግሞ ሶደቃ ይደረግለታል፡፡ ለሟች የምንሰጠው ስጦታ ሶደቃ ነው እንጂ ሌላ ምን ይሰጠዋል? ለእሱ ደንቡ ነው፡፡ በመቃብር የሚቀጡ አሉ፡፡ እንዳይቀጣ፣ በሰላም እንዲሄድ ባለ አቅም ሶደቃ ይሰጠዋል፡፡ ለእሱ ይጠቅመዋል፡፡
>
> ሟች ያለበትን አናውቀውም፡፡ በሞቃት ይሁን በቀዝቃዛ ያለው አናውቀውም፡፡ ላይመቸው ይችላል የሚለውን ነው መያዝ ያለብን፡፡ ተመችቶታል ብለን መዝናናት የለብንም፡፡ ሩቅ ሀገር የላክሽው እንኳን ዘመድ አግኝቶ ወይም ተርፎት ይሆናል፡፡ ካላገኘ አንድ ነገር እንላክለት ይባላል፡፡ አይደለም እንዴ? የሞተን ሰው የምትጠይቂው ደግሞ በዚህ መልኩ ነው፡፡ ሰላምታው ጥየቃው ይሄ ነው በቃ! በሰባቱም፣ በወሩም፣ በሌላም ቀን የሚደረገው ለሱ መግሪያ ነው፡፡

ሶደቃ ማድረግ ለቋሚም ዋጋ እንደሚያስገኝ ይታመናል፡፡ ይህን በተመለከተ አቶ አሕመድ ሲራጅ (28/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) "በመጀመሪያ ሰው ስታበዪ ምንዳ አለሽ

ከፈጣሪ፡፡ ስታመሰግኝም፣ የፈጣሪን ጥሩነት ስትናገሪም ምንዳ አለው፡፡ ዋጋው ለሟች ይሁን ነው የምንለው፡፡ ለሱም ስንል ለእኛም ደግሞ አይቀርም፡፡ ለቋሚውም ይመዘገብለታል፡፡ ለሟች በማሰባችን ለእኛም አለን" ብለዋል፡፡ በአንፃሩ ለሙታን የሚደረግ ሶደቃና ዱዓ መጓደል በቋሚዎች ላይ ችግር እንደሚያስከትል ይታመናል፡፡ ሶደቃ ቢጓደል የሟች ነፍስ ወደ ሟች ቤተሰብና ዘመዶች በመመለስ ቋሚን ትረብሻለች ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህን በተመለከተ ወ/ሮ ሲቲ ፋጡማ መሐመድ (10/2/2013፣ ጋቾኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) "ያ ባይደረግ በህልምም ታይዋለሽ፣ መጨነቅ፣ መረበሽ አለ፡፡ በእኛ አዳ ሟች በህልም የሚመጣውና የሚረብሸው ሶደቃ ሲያጣ ነው፤ ሲከጅል ነው፡፡ በእኛ ስጡ ይባላል" ብለዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የሶደቃ መጓደል በአካባቢው ድርቅ ወይም የዝናብ እጥረትን እንደሚያስከትል ይታመናል፡፡ በመሆኑም ሶደቃ የሟች ነፍስ ጥሩ መንገድ እንደምታገኝና ቋሚም ከሞት በፊትም ሆነ ከሞት በኋላ መልካም ነገር እንደሚያገኝ በማመን የሚደረግ ነው፡፡

በመታሰቢያ ስነ ስርዓቶች ላይ የሚደረገው ዱዓም ፈጣሪ የተበላውንና የተጠጣውን አድርስለት የሚል ክፍል ያለው በመሆኑ ሶደቃው ለሟች ነፍስ መልካም መንገድና ማረፊያ እንደሚያስገኝ ይታመናል (አቶ ኡመር አሊ፣ 10/4/2013፣ ጨኖ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በአርጐባዎች ዘንድ መታሰቢያዎችን ማድረግና መሶደቅ የሟች የቅርብ ሰዎች ግዴታ እንደሆነ ይታሰባል፡፡ ሙታን ለአንዱ የሚደረገውን የሶደቃ ዋጋ ይካፈላሉ ተብሎ ስለሚታመን ሙታን የሌላውን እየተካፈሉ ቆይተው የራሳቸው ሳይላክላቸው መቅረቱ ሶደቃ የማድረግ ሀላፊነት ላለበት ሰው እንደ እርግማን ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም የሟች ቤተሰብ ገንዘብ ባይኖረው ተበድሮ ሶደቃውን ያበላል እንጂ አያስቀርም፡፡ ለሟች ቤተሰቡ አባል ሶደቃውን ተግቶ የሚያደርግ ሰው በማህበረሰቡ ዘንድ ምስጋናና ክብርን ያገኛል (አቶ መሐመድ ሰዒድ ያሲን፣ 6/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡



ፎቶግራፍ 38. ሶደቃ ሲደረግ

ቀብር በሚከናወንበት እለት አስከሬን ከቤት ሲወጣ ሸኝተው የሚሄዱ፣ ከመስጊድ ሰለዋት ጂናዛ ሰግደው የሚሄዱ፣ በቀብር ቦታ ቀብረው ወደ ሀዘኑ ቤት ሳይመለሱ በዚያው የሚሄዱና ከቀብር ስነ ስርዓት በኋላ ከሀዘንተኛው ጋር አብረው ወደ ሀዘኑ ቤት የሚመለሱ ሀዘን ደራሾች፣ በመስጊድ ሰለዋት ጂናዛ የሚያደርጉ ደረሳዎችና መቃብር የሚቆፍሩ ሰዎች አሉ፡፡ አስከሬን ከቤት ሲወጣ ሸኝተው የሚሄዱ ሰዎች ከመሄዳቸው በፊት በተዘጋጀው ምግብና መጠጥ ይስተናገዳሉ፡፡ ከመስጊድና ከቀብር ቦታ በዚያው የሚሄዱ ንፍሮና ቦላ ይታደላቸዋል፡፡ ሀዘንተኛውን አጅበው ወደ ሀዘኑ ቤት የሚመለሱ ሰዎች በሀዘኑ ቤት ሲደርሱ ንፍሮ፣ ቡናና ሻይ ይቀርብላቸዋል፡፡ ለደረሳዎቹ ፍትፍት፤ ለመቃብር ቆፋሪዎቹ ደግሞ ንፍሮ ይላክላቸዋል፡፡ በዚህ መልኩ በቀብሩ እለት የነበሩ ሰዎች ሁሉ ከተዘጋጀው ምግብ እንዲቀምሱ ይደረጋል፡፡ በቀብር ስነ ስርዓቱ ላይ የነበሩ ሁሉ እህልና ውሀ እንዲቀምሱ ማድረግ፣ ቦላ ስጋ አድሎ ስጋውን የወሰደው ሰው ቤቱ ወስዶ ከእርሱ በተጨማሪ ቤተሰቡም ከስጋው እንዲቀምስ ማስቻል ሶደቃን ማብዛት ነው፡፡ ወ/ሮ ከዲጃ መሐመድ ሰኢድ (16/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) እንደገለፁት ደግሞ ሶደቃ ለብዙ ሰው ሲዳረስ ለሟች ነፍስ በፈጣሪ ዘንድ የበዛ ዋጋ ያስገኝላታል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሟች ከሞተ ጀምሮ እስከ ስድስተኛው ቀን ድረስ ወዳጅና ጉረቤት በሀዘኑ ቤት የሚቆየው ከራሱ ቤት በመጣ እህልና ውሀ እየተስተናገደ ነው፡፡ ይህ ደግሞ አንድም ለሟች ከሶደቃ እንዲቆጠርለትና ምህረት እንዲያገኝ ማድረጊያ፣ አንድም ሀዘንተኞችን ማገገሚያ ነው፡፡ ከሰባተኛው ቀን ጀምሮ በሀዘኑ ቤት በሚከናወኑ የሙት

መታሰቢያ ስነ ስርዓቶች ላይ የሚደረገው የምግብና መጠጥ ግብዣም ሶደቃ ነው፡፡ ከዚህ በታች የሙት መታሰቢያ ስነ ስርዓቶች ክዋኔ ቀርቧል፡፡

### 7.2.3.1. የቆዳ ማጠፊያ ስነ ስርዓት

ሞት ከተከሰተ ጊዜ ጀምሮ እስከ ቆዳ ማጠፊያ ቀን ድረስ ያለው ዋና የሀዘን ጊዜ ሲሆን ሀዘንተኞች የእለት ተእለት ስራቸውን የማያከናውኑበትና ሀዘንተኞች በመሆናቸው ቁጭ ብለው ሀዘን የሚደርሱ ሰዎችን የሚቀበሉበት ነው፡፡ የቆዳ ማጠፊያ ስነ ስርዓት ሀዘንተኞች ይህን ዋናውን የሀዘን ጊዜ ጨርሰው ቀለል ያሉና ከቤት የማያርቋቸውን ስራዎች መስራት የሚጀምሩበት ነው፡፡ ስነ ስርዓቱ ቆዳ ማጠፊያ የተባለው ሴት ሀዘንተኞች ሀዘን የሚቀመጡት መዋስ በማንጠፍ በመሆኑና ይህ ስነ ሰርዓት የሀዘን ጊዜ ማብቂያ ሆኖ የተነጠፈው መዋስ ስለሚነሳ ነው፡፡ በቆዳ ማጠፊያው ቀን ሚች ያስቀመጠው ኑዛዜ ካለ በዚያ መሰረት እርድ ተከናውኖ ይሶደቅለታል፡፡ ኑዛዜ ከሌለውም ሰው አዋጥቶ ይሶድቅለታል (ወ/ሮ አሚናየ መሐመድ፣ 17/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የቆዳ ማጠፊያ በሚከወንበት እለት ሰዎች ቀኑን ቆጥረውና አስበው ወደ ሀዘኑ ቤት ይሄዳሉ እንጂ ምንም አይነት ጥሪ አይደረግም፡፡ በመሆኑም በቆዳ ማጠፊያው ቀን ጠዋት ሴት ዘመዶችና የቅርብ ጐረቤቶች በሀዘኑ ቤት በመገኘት ሴት ሀዘንተኞችን በቃችሁ በማለት ለሀዘን የተዘረጋው መዋስ ላይ ውሀ አርከፍክፈው በማጠፍ ያነሱታል፡፡ ቆዳው ሲታጠፍ እንደ አዲስ ይለቀሳል፡፡ ሁሉም ሴቶች እጃቸውንና ፊታቸውን በውሃ ከታጠቡ በኋላ ቡና ተፈልቶ ቁርስ ይቀርብና ዱዓ ተደርጐ ቡናው ይጠጣል (ወ/ሮ አሚናየ መሐመድ፣ 17/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

መዋስ ለቅሶ መኖሩን የሚገልጽ ትዕምርታዊ ቁስ ነው፡፡ በአንድ ቤት ውስጥ የተነጠፈ መዋስ  መኖሩ በዚያ ቤት ለቅሶ መኖሩን ገላጭ ነው፡፡ መዋስ የመዘርጋትና የማጠፍ ድርጊቶችም ትዕምርታዊ ናቸው፡፡ መዋስ መዘርጋት የሞት መከሰትን፣ ሰዎች በአዲስ፣ በትኩስ ለቅሶ ላይ መሆናቸውን፣ ቀጣይ ቀናቶች ሞት በተከሰተበት ቤት የሚታወቅ የለቅሶ ጊዜ መሆኑን የሚያሳይ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው፡፡ በአንፃሩ መዋስ ማጠፍ የለቅሶ በቃ ማለትን፣ ሞት ካስከተለው የሀዘን ስሜት መውጣትን፣ ተፈጥሮ ከነበረው የስነ ልቡና ቀውስ ማገገምን፣ መሻገርን፣ መውጣትን የሚወክል ትዕምርታዊ ድርጊት ነው፡፡

መዋሱ የሚታጠፈው ጠዋት መሆኑ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው፡፡ የንጋት ጊዜ ወፎች መዘመር የሚጀምሩበት፣ አበባዎች የሚፈኩበትና የሌሊት ፍጥረታት ወደ ቦታቸው የሚያፈገፍጉበት ሰዓት ነው። ንጋት አዲስ ቀንን፣ እንደገና መወለድን፣ ተስፋን፣ ብሩህ ነገርንና ለውጥን ይወክላል። በመሆኑም ቆዳ የሚታጠፈው በጠዋት መሆኑ በአስጨናቂው ጊዜ ውስጥ እንኳን ሁልጊዜ አዲስ ጅምርና ለውጥ ሊኖር እንደሚችል የሚያሳይ፣ የተከሰተውን ሞትና ያለፉትን የሀዘን ቀናት ወደኋላ ትቶ ወደ አዲስ ቀን ብርሀን መግባት የሚገልጽ፣ ሞት ካስከተለው የሀዘን ስሜት በመሻገር ብሩህ የወደፊት ተስፋን፣ ህይወትን፣ አዲስ እድሎችን ማሰብ እንደሚያስፈልግ የሚገልጽ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው፡፡

ቆዳው የሚታጠፈው ውሀ ተርከፍክፎበት መሆኑና ከተለቀሰም በኋላ በሀዘኑ ቤት የተሰበሰቡ ሴቶች በሙሉ እጃቸውንና ፊታቸውን በውሃ መታጠባቸው ትዕምርታዊ ድርጊት ነው፡፡ ውሀ ህይወትን፣ ተስፋን ይወክላል፡፡ ሴቶቹ ውሀ ማርከፍከፋቸውና በውሀ መታጠባቸው የደረሰውን ሀዘን ወደ ኋላ በመተው ተስፋ መናፈቃቸውን፣ ህይወትን መሻታቸውን፣ ውሀን ማብረጃና ማርከሻ ትዕምርታዊ ቁስ በማድረግ ሀዘን እንዲበርድ፣ ሀዘን እንዲበቃና እንዳይደገም መመኘታቸውንና ማምሰላቸውን የሚገልጽ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው፡፡

ቆዳ ማንጠፍ ሀዘንን፣ በአንፃሩ ቆዳ ማጠፍ የሀዘን ቀናት ማብቃትን የሚገልፁ ትዕምርቶች እንደመሆናቸው ቆዳ ሲታጠፍ እንደ አዲስ ማልቀስም ከዚሁ ጋር የሚተያይ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው፡፡ ቆዳ ማጠፍ ከሀዘን ቀናቶችና ሀዘንተኞች የዕለት ተዕለት የኑሮ እንቅስቃሴዎቻቸውን ከሚከውኑባቸው ቀናት መካከል ያለ አሻጋሪ ድርጊት እንደመሆኑ በዚህ ጊዜ እንደ አዲስ ማልቀስ ሀዘኑ ዳርቻ፣ የመጨረሻ እንዲሆን ማዕኛና መመኛ፣ ቀኑም የሀዘን ጊዜን መዝጊያና ስለወደፊቱ ህይወት ማሰቢያ እንዲሆን ማዕኛም ነው፡፡

በአርጐባዎች የለቅሶ ስነ ስርዓት ክዋኔ ተደጋግሞ የሚመጣው ውሃ አርጐባዎች ስለሞትና ህይወት ያላቸውን ግንዛቤ የሚነግር ትዕምርት ነው፡፡ ውሃ የህይወት ምልክት ሲሆን አርጐባዎች ውሃን የሚያርከፈክፉበትና የሚታጠቡበት ቦታና ጊዜ ከሞት በኋላ ህይወት አለ ብለው ማመናቸውን የሚገልጽ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው፡፡ የብሄረሰቡ አባላት ከሞት በኋላ ያለን ህይወት የሚረዱበት መልክ ደግሞ ሁለት ዓይነት ሲሆን አንደኛው ሰማያዊ ህይወት ሲሆን ሁለተኛው ምድራዊ ነው፡፡ ሰማያዊውን ህይወት በተመለከተ በመቃብር ላይ ቀዝቃዛ ውሃ ማርከፍከፋቸው ሞት የመጨረሻ ሳይሆን ከገሀዱ ዓለም ወደማይታየው ዓለም የሚያሻግር ድልድይ ብቻ መሆኑንና ሟች ከሞት በኋላ የሚሄድበት ዓለም መኖሩን፣

በዚያም ህይወት በሞላው ጀነት እንዲኖር መመኘታቸውን ያሳያል፡፡ ከለቅሶ ቀናት በኋላ እጅና ፊትን በቀዝቃዛ ውሃ መታጠብ ደግሞ በምድራዊው ዓለም ያሉ የሟች ቤተሰብና ዘመዶች ህይወት ቀጣይ መሆኑን እንዲገነዘቡ፣ ከደረሰባቸው ሀዘን ተሻግረውና ሀዘኑን ወደ ኋላ ትተው ህይወታቸውን እንዲኖሩ ማምሰያ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው፡፡

በእለቱ ጠዋት የሟች ወይም የቤተሰቡ ቅርብ የሆኑ ወንዶች ያለማንም አስታዋሽና ያለምንም ጥሪ ተሰብስበው በጠዋት ወደ ቀብሩ ቦታ በመሄድ በቀብሩ ጊዜ የተተከለውን ድንጋይ ምልክት በማድረግ የመቃብሩን ቦታ ዙሪያውን በድንጋይ ይከባሉ፡፡ ካቢዎቹ ከበው ሲጨርሱ ወደ ሀዘኑ ቤት በመምጣት ቁርስ ይበላሉ፤ የሚቀርብላቸው ገበታም የካቢ ገበታ ይባላል፡፡ ከዚያ በኋላ እርድ የሚታረድ ከሆነ እርዱን ያከናውናሉ፡፡ በዚህ ቀን ሩቅ ቦታ የሚኖሩና ሀዘኑን የደረሱና ያልደረሱም የሟች ዘመዶችና ወዳጆች ቀኑን ቆጥረው ወደ ሀዘኑ ቤት ይሄዳሉ፣ በስራም ያግዛሉ (አቶ ያሲን ቢሆን፣ 9/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ድንጋይ ከመትከልና ዙሪያውን ከመካብ ውጭ በመቃብር ላይ የሚደረግ ሌላ ምልክት አይኖርም፤ ነገር ግን በሀይማኖት በቅተው ለሞቱ አባቶች መቃብሮቻቸው ላይ ቤት ይሰራል፡፡ የሚሰራው ቤት ከላይ ጣሪያ ይኑረው እንጂ ግድግዳው በእንጨት ወይም በካብ ይሰራል፤ አምሮና የመኖሪያ ቤት መስሎ አይሰራም፡፡ የመቃብር ቤቱ ሄደው ለሚዘይሩ ሰዎች ማረፊያ ይሆናቸዋል (አቶ ያሲን ቢሆን፣ 9/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ የመቃብር ቤቱ አምሮ የማይሰራው ማማር የገሀዱ ዓለም መገለጫ እንጂ የሙታን ዓለም መገለጫ አይደለም፤ ለሙታን ዓለም ጌጥ አያስፈልግም በሚል እምነት ምክንያት ነው፡፡

በቆዳ ማጠፊያው ቀን ሴቶች በሀዘኑ ቤት ይሰበሰቡና ምግብና መጠጥ ያዘጋጃሉ፡፡ ሞት በተከሰተ ጊዜ የተበጀውና ምግብና መጠጥ ሲዘጋጅበት የነበረው ዳስ ሳይፈርስ የሚቆይ በመሆኑ በሰባቱ ቀን ምግብ ማዘጋጃ ዳስ ማዘጋጀት ሳያስፈልግ ስራው በዚያ ዳስ ስር ይከናወናል፡፡ የምሳ ሰዓት ሲሆን ሰዎች ወደ ሀዘኑ ቤት ይሰበሰቡና ወንዶች ሞት ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ ተጥሎ በቆየው ዳስ ውስጥ፣ ሴቶች ደግሞ በሀዘኑ ዋና ቤት ይቀመጣሉ (26/2/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡

የምግብ መስተንግዶውን ለመጀመር በተሰራው ምግብ ገበታ ይዘጋጃል፡፡ ቅድሚያ የሚስተናገዱት ወንዶች በመሆናቸው[34] አስተናጋጅ ወንዶች የተሰራውን ገበታ ወደ ዳስ እየወሰዱ ያቀርባሉ፣ የሚጨመር ሲኖርና አዲስ ለመጣ ሰው አዲስ ገበታ ሲያስፈልግ እየተመላለሱ ወስደው የመጣውን ሁሉ ያስተናግዳሉ፡፡ እንግዶች በቡድን በቡድን ሆነው ከተመገቡ በኋላ ድፎ ዳቦ፣ የማሽላ ቆሎ፣ ቡናና ሻይ ይቀርብላቸውና በዚያ ይስተናገዳሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ቁርዓን መቅራት ይጀምራሉ፡፡ መስተንግዶውን ሲያከናውኑ የነበሩ ወንዶችም እርስ በርስ እየተስተናገዱ ምግብ ከበሉ፤ ቡናና ሻይ ከጠጡ በኋላ ቁርዓን የሚቀሩትን ወንዶች ይቀላቀላሉ፡፡ ከዚያ በኋላ የሴቶች መስተንግዶ ይጀመርና በቅደም ተከተል ሰባት ሰዓትን ጠብቀው የመጡ እንግዶችና ምግብና መጠጥ ሲያዘጋጁ የቆዩ ሴቶች በሴቶች አስተናጋጅነት በተመሳሳይ መንገድ ይስተናገዳሉ፡፡ ሴቶች ከመስተንግዶ በኋላ ቀስ በቀስ ወደየቤታቸው የሚሄዱ ሲሆን ቁርዓኑ ተቀርቶ እንዳለቀ የስነ ስርዓቱ ማብቂያ ሆኖ ወንዶችም ወደየቤታቸው ይሄዳሉ፡፡ ከዚያ በኋላ የቅርብ ወንዶች ብቻ ይቀሩና ዳሱን ያፈርሳሉ (26/2/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ምልከታ)፡፡



ፎቶግራፍ 39. ለቆዳ ማጠፊያ የተዘጋጀ ምግብ

የቆዳ ማጠፊያ ስነ ስርዓት ከተከወነ በኋላ የሚከወነው የወር መታሰቢያ ስነ ስርዓት ነው፡፡ ከስምንተኛው ቀን ጀምሮ እስከ ወር ድረስ ባለው ጊዜ እስከ ሰባት ቀን እንዳለው ጊዜ ብዙ ሰውና የሰፋ ስነ ስርዓት ባይኖርም ቅርብ የሆኑ ሰዎች ሀዘንተኞችን አይለዩዋቸውም፤ ጠዋትም ሆነ ማታ እንዳመቻቸው እየተመላለሱ ሀዘንተኞችን ይጐበኟዋቸዋል፡፡ ሀዘኑን ሳይሰማ የቆየ ሰውም ሀዘን ይደርሳል፡፡

[34] በአርጐባዎች ዘንድ ለወንዶች ቅድሚያ መስጠት የአክብሮት መገለጫ ተደርጐ ይታሰባል፡፡

### 7.2.3.2. የወር መታሰቢያ ስነ ስርዓት

የወር መታሰቢያ ስነ ስርዓት ሞት በተከሰተ በወሩ የሚከወን ስነ ስርዓት ሲሆን ለሀዘንተኞች የሀዘን ጊዜ ማብቂያ፣ ከሀዘን መነሻና የእለት ተእለት የኑሮ እንቅስቃሴን መጀመሪያ ነው፡፡ ሟቹ ባለትዳር ወንድ ከሆነ ግን የባለቤቱ ሀዘን መቋጫ የዓግል መፍቻ[35]ዋ ቀን ነው (አቶ አብዱሰላም አሊ፣ 10/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ሀዘንተኞች ከቆዳ ማጠፊያው ቀን በኋላ ወዲያው የእለት ተእለት የኑሮ እንቅስቃሴያቸውን አይጀምሩም፡፡ የቤት ውስጥ ስራዎችን ጐረቤቶቻቸው የሚያከናውኑላቸው ሲሆን እነርሱ ቁይቶ የመጣን ሀዘን ደራሽ ይቀበላሉ፡፡ ከወር መታሰቢያ ስነ ስርዓት በኋላ ግን ከሀዘን ተነስተው የእለት ተእለት የህይወት እንቅስቃሴያቸውን ይጀምራሉ፡፡ (አቶ አብዱሰላም አሊ፣ 10/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የወር መታሰቢያ ስነ ስርዓት የቆዳ ማጠፊያ ስነ ስርዓትን ያህል አይደምቅም፤ ጥሪ ካልተደረገ በስተቀር ብዙ ሰው አይገኝበትም፤ የቆዳ ማጠፊያ ስነ ስርዓቱን ያህልም ድግስ አይደገስበትም፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ለተወሰኑ ሰዎች እንደ አቅም ሁኔታ ምግብ ተዘጋጅቶ ዱዓ ይደረጋል፡፡ የወር መታሰቢያ ስነ ስርዓት በሚከወንበት እለት ጠዋት ወንዶች ለሰው ማረፊያ የሚሆን ዳስ ይጥላሉ፤ ውስጡን በቅጠል ይጐዘጉዛሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ረፋድ ላይ ወንዶች በተጣለው ዳስ ውስጥ ሲሰበሰቡ ለቁርዓን መክፈቻ ተብሎ ዳቦ፣ አነባበሮ፣ ቡናና ሻይ ይቀርብላቸውና ከተመገቡ በኋላ ቁርዓን መቅራት ይጀምራሉ፡፡ የምሳ ሰዓት ሲደርስ ምሳ ይቀርብላቸውና ከበሉ በኋላ ቁርዓን መቅራቱ ይቀጥላል፡፡ ከዚያ በኋላ ወንዶች የተጣለውን ዳስ አፍርሰው ወደየቤታቸው ይሄዳሉ (አቶ አብዱሰላም አሊ፣ 10/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

### 7.2.3.3. የዓግል መፍቻ ስነ ስርዓት

ባለቤቷ የሞተባት ሴት ሀይማኖታዊ በሆነ ምክንያት ሟቹ ከሞተበት እለት ጀምሮ ለአራት ወር ከአስር ቀን ያህል ቅባትና ሽቶ እንዳትቀባ የምትከለከል ሲሆን (Ismaiel num. 313) ዓግል በክልክል የምትቆይበት የሀዘን ጊዜ ነው፡፡ ይህ ክልክል ሀይማኖታዊ መሰረት ያለው ቢሆንም ክልክሉን ማንሳትን ተከትሎ የሚከወን ስነ ስርዓት ግን አለ፡፡ ስነ ስርዓቱ ዓግል

[35] ምንነቱ ወደፊት በሰፊው ይቀርባል፡፡

መፍቻ የሚባል ሲሆን የሚከወነው በሀይማኖታዊ ትዕዛዝ ምክንያት የተጣለው ክልክል መነሳቱን ለመግለጽና ፈጣሪ ሀዘንን በቃ እንዲል ዱዓ ለማድረግ ነው፡፡

በአርጐባዎች ዘንድ የሀዘን ጊዜ አንድ ወር፣ ባለቤቷ ለሞተባት ሴት ደግሞ አራት ወር ከአስር ቀን ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ሀዘንተኛ የሆኑ ሴቶች ከቤታቸው ራቅ ብለው አይሄዱም፤ ውሀ አይቀዱም፣ ወደ ወፍጮ አይሄዱም፣ ቅባት አይቀቡም፡፡ የቤት ውስጥ ስራዎቻቸውን ጐረቤቶች ያከናውኑላቸዋል፡፡ ነገር ግን ለሚች ባለቤት የዓግል መፍቻ ቀን የሀዘን ጊዜዋ የሚያበቃበት፣ ከዚያ በኋላ አስተዛዛኝና ለቅሶ ደራሽ ይመጣብኛል የማትልበትና ከሀዘኗ በፊት የምታከናውናቸውን የእለት ተእለት የህይወት እንቅስቃሴዎቿን ማከናወን የምትጀምርበት ቀን ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ርቃ መሄድ፣ ገበያ መገበያየት፣ ከሰዎች ጋር ያላትን ማህበራዊ ኑሮ መቀጠል፣ ለአራት ወር ከአስር ቀን ያህል የደረቀ ሰውነቷን በቅባት ማለስለስ፣ ወዘተ ትችላለች (ወ/ሮ አሚና ዝይን፣ 21/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ "እከሌ ዓግሏን ፈትታለች" የምትባለው ከነበረችበት የአራት ወር ከአስር ቀን የሀዘንተኛነት መልክ ወጥታ ከባለቤቷ ሞት በፊት የምታደርጋቸውን የእለት ተእለት የኑሮ እንቅስቃሴዎች ማድረግ ስለምትጀምር ነው፡፡ "መፍታት" የሚለው ቃል በራሱ የታሰረንና የጠበቀን ማላላት፣ የተከለከለን መሻር፣ ይደረግ ያልነበረን ማድረግ ማለት ነው፡፡

በዓግል መፍቻው ቀን የሚች ዘመዶች የሆኑ ሴቶች የሚች ሚስት የምትቀባውን ለጋ ቅቤ፣ የምትለብሰውን አዲስ ቀሚስና ሻሽ፣ ድፎ ዳቦና ቆሎ ይዘው ወደ ሀዘኑ ቤት ይመጣሉ፡፡ ሚች የሞተበትን ሰዓት ጠብቀው የሚችን ሚስት ገላዋን አጥበው ያመጡትን ቅቤ ለሶስት በመክፈል አንድ እጁን ከራስዋ ጀምረው ገላዋን ሁሉ ቀብተዋት ያመጡትን አዲስ ልብስ ያለብሷታል፡፡ በዚህ ጊዜ ይለቀሳል፡፡ ለቅሶው ሲያበቃ አዝጋሮና ሽታ በጋቻ በማድረግ ያሞቋትና በተቀባችው ቅቤ ለሰው አይን እንዳትጋለጥ ተብሎ ደበቅ ያለ ቦታ ትቀመጣለች፡፡ ከዚያ በኋላ ቡና ተፈልቶ የሚች ዘመዶች ይዘውት የመጡት ዳቦ ቀርቦ ለሚቹና ለዓግል ፈቺዋ ዱዓ ከተደረገ በኋላ ዳቦው ተቆርሶ ከቆሎው ጋር እየተሰጠ ቡናው ይጠጣል፡፡ የተረፈውን ሁለት እጅ ቅቤ በማግስቱና በሶስተኛው ቀን ይቀቧትና ከዚያ በኋላ ገላዋን ያጥቧታል (ወ/ሮ አሚና ዝይን፣ 21/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የሚችን ሚስት በዚህ መልኩ ቅቤ መቀባት አንድም ሀይማኖታዊ መሰረት ያለው የቅባት ክልከላ ጊዜው ሲደርስ በመሻር ሀይማኖታዊ ትዕዛዝን መፈፀም ሲሆን አንድም ደግሞ የሚች ሚስትን ለአዲስ ኑሮ ማዘጋጀት ነው፡፡ የሚች ዘመዶች የሚችን ሚስት ሰውነቷን

በሙሉ ቅቤ መቀባታቸው ግዴታሽን ተወጥተሻል፣ ከታሰርሽበት ተፈትተሻል፣ ነፃ ሰው ነሽ ስለዚህ ከዚህ በኋላ ማግባትና ኑሮሽን መቀጠል ትችያለሽ፣ ቅሬታ የለንም የሚል መልዕክታቸውን የሚያስተላልፉበት ትዕምርታዊ ድርጊት ነው፡፡ ቅቤ ከቀቧት በኋላ የሚያለብሷት አዲስ ቀሚስ መሆኑም መጪው ጊዜ ሀዘኗን የምትረሳበት፣ ስለራሷ አዲስ ህይወት የምታስብበት፣ ወደራሷ የምትመለከትበት፣ አዲስ ኑሮን የምትይዝበትና በአዲስ ማንነት የምትገለጽበት እንዲሆንላት ማምሰያ ነው፡፡

ባለቤቷ የሞተባት ሴት ዓግል በምትፈታበት ቀን ቤተሰቧ ማለትም አባቷ፣ አጐቷ ወይም ሌላ የቅርብ ሰው ፍየል አርዶ ይደግሳል፡፡ ዓግሏ ነው ተብሎ ዘመድ ጐረቤት ይጠራል፡፡ ቅቤ የመቀባት ስነ ስርዓቱ የሚከናወነው ሟች በሞተበት ሰዓት በመሆኑ ጠዋት የሚከወን ከሆነ ታርዶ የተዘጋጀው ድግስ የሚበላው ከዚያ በኋላ ይሆናል፤ ምሽት የሚከወን ከሆነ ደግሞ ድግሱ በቅድሚያ ይበላል፡፡ ድግሱና ሀዘንተኛዋን ቅቤ የመቀባቱ ስነ ስርዓት ከተከናወነ በኋላ ወንዶች ቁርዓን ይቀራሉ፤ ሴቶች ደግሞ ለዓግል ፈቺዋ እንደ አቅማቸው የገንዘብ ስጦታ በመስጠት "አላህ ይጠግንሽ፤ ነገ ደግሞ ቅቤውን በዓለም የምትቀቢና የምትወጪ አላህ ያርግሽ" እያሏት ወደየቤታቸው ይሄዳሉ (ወ/ሮ አሚና ዝይን፣ 21/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

### 7.2.3.4. ጠም ቆሎ

ጠም ቆሎ በረመዳን ፆም ወር የሚደረግ የሙት መታሰቢያ ስነ ስርዓት ነው፡፡ የስነ ስርዓቱ ክዋኔ ዓላማ በቆሎ ወይም በተገኘው ነገር ሙታንን ማሰብ ነው፡፡ በረመዳን የፆም ወቅት የሟች ቤተሰብ አባላት ለሞተ የቤተሰባቸው አባል ዱዓ እንዲደረግ ሰዎችን ቀድመው በማሳወቅ በማፍጠሪያ ሰዓት እንዲገኙላቸው ያደርጋሉ፡፡ በዚህ ምክንያት በረመዳን ወር በቤቱ የሚያፈጥር ሰው ቁጥር ትንሽ ይሆናል፡፡ ሁሉም የረመዳን ቀኖች ጠም ቆሎ በሚያደርጉ ቤተሰቦች ጥሪ የሚያዙ በመሆናቸው አንድ ቀን አንዱ ጋር፣ ሌላ ቀን ሌላው ጋር እየተኬደ ይፈጠርና ለሟች ዱዓ ይደረጋል፡፡ አቶ ኢብራሂም ይርጉ እንደገለፁት የሌላ ሀይማኖት ተከታይ ሆነው ነገር ግን የሞተ ቤተሰባቸው አባል የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ የነበረ ከሆነ ምግብ ሰርተው በማፍጠሪያ ሰዓት መስጊድ ድረስ ይዘው በመምጣትና ለሟች ዱዓ አድርጉልን ብለው በመጥራት ጠም ቆሎውን ያደርጋሉ (22/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ጠም ቆሎ በረመዳን ወር ቀኖቹን በመሻማት የሚከወነው በፆም ጊዜ የሚደረግ መልካም ስራ በሌላ ቀን ከሚደረግ መልካም ስራ የበለጠ ዋጋን ከፈጣሪ

ዘንድ ያስገኛል ተብሎ ስለሚታመን ነው፤ በየም ወቅት በመደረጉ ፈጣሪ የሚችን ሀጥያት በብዙ ይሽራል ተብሎ ይታመናል (አቶ መሐመድ ጀማል በሽር፣ 11/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

### 7.2.3.5. የክረምት ዚያራ

በአርጎባዎች ዘንድ ያልተሰደቀላቸው ሙታን፣ የተከፈተ ወይም የተደረመሰ መቃብርና የተጋለጠ የሰው አጽም መኖር በክረምት ወቅት የዝናብ እጥረት ወይም ከባድ ዝናብ እንዲኖር ያደርጋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህንን ለማስቀረትና ጥሩ የክረምት ወቅት እንዲመጣ የክረምት ዚያራ ይደረጋል፡፡ በመሆኑም በክረምት መግቢያ ሰኔ ወር ላይ ይህን የሚያስተባብሩ ሰዎች በየቤቱ በመሄድ ገንዘብ ይሰበስቡና በተሰበሰበው ገንዘብ ምግብ ተዘጋጅቶ ይሶደቃል፤ ወንዶች በቡድን እየሆኑ በየመቃብሩ ስፍራ ሁሉ እየሄዱ ዚያራ ያደርጋሉ፤ የተከፈተ መቃብር አስሰው ይደፍናሉ፤ የተጋለጠ የሰው አጽም ካለም ሰብስበው ይቀብራሉ፡፡ ዱዓውና ሶደቃው የሚደረገው በመቃብር ስፍራዎች በመሆኑ ጊዜያዊ ዳስ ተደርጐ እዚያ ዱዓ ከተደረገ በኋላ የተዘጋጀው ምግብ ይበላል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ሰኞ ሰኞ ቀን ቀጠሮ እየተያዘ በየመቃብር ስፍራዎቹ ሁሉ እየተሄደ ይህ ይከናወናል፡፡ ለሙታን ዚያራ ሲደረግ ፈጣሪ በመቃብር ውስጥ በጭንቅ የሚገኙ ሙታንን ይምራል፣ ከጭንቅ ያስጥላቸዋል፣ ዚያራውን ላደረጉ ሰዎችም አዘኔታ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል (አቶ መሐመድ ጀማል በሽር፣ 11/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ አቶ መሐመድ አቡበከር (6/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) የክረምት ዚያራን ጥቅም በተመለከተ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> ራህመት ስናደርግ ፈጣሪም ለእኛ ያስብልናል፡፡ በመቃብር በእዳ የተጠየቀውም ወንጀሉ የሚሻረው በኸይር ስራ ነው፡፡ ከዚህ የሚደረገው የኸይር ስራ ነው፡፡ ለሞተው ሁሉ ስናደርግ በቀብር ላሉ ማዘናችንኮ ነው፡፡ በቀብር ለሚጨነቁት ስናዝን ፈጣሪ ለእኛም ያዝናል፡፡ ዝናቡም ይስተካከላል፡፡ አደጋ የሚያደርስ ዝናብ አይዘንብም፤ ጐርፍ አይኖርም፡፡ ያንን ሳናደርግ ንፋሱም ዝናቡም ጥሩ አይሆንም፡፡

በአቶ መሐመድ አቡበከር የተገለፀው ሀሳብ ሙታንን ማሰብ ለሙታን እረፍትን፣ ይቅር መባልን የሚያስገኝ መልካም ተግባር ነው፡፡ ለሙታን የሚደረግ መልካም ተግባር ደግሞ ለመልካም አድራጊውም ጥሩ ነገርን ያስገኛል፡፡ በተደረገው መልካም ተግባር የሙታን ጭንቅ ሲነሳ ተግባሩን የሚያይ ፈጣሪ ደግሞ ለመልካም አድራጊዎቹም መልካምን ያስገኛል የሚል ነው፡፡ ይህ ሀሳብ ለሙታን የሚደረግ መታሰቢያ ከሙታን አልፎ ለቋሚም ይጠቅማል የሚለውን በብሄረሰቡ ያለ እምነት ማሳያ ነው፡፡

የክረምት ዚያራ የሚያስገኘውን ተጨማሪ ጥቅም በተመለከተ አቶ አሕመድ ሲራጅ (28/2/2013፣ ጋቸኔ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ) "በተጨማሪ ደግሞ አንድ ነገር አለ፡፡ ሰው እዚያ ቦታ መሄዱ ሞትን እንዲያስታውስ ያደርገዋል፡፡ እነዚያ ሰዎች እዚህ ቦታ ላይ በስርዓቱ ተቀበሩ፤ እኔ ስሞት ምን እሆን ይሆን ብሎ እንዲያስብ ያደርገዋል፡፡ ሞትን ካሰበ ደግሞ ጥሩ ነገር ያስባል" ብለዋል፡፡ ከዚህ ለመረዳት እንደሚቻለው ይህን አይነቱን ዚያራ ማድረጉ የሞራል ትምህርትንም የሚያስገኝ መሆኑንም ነው፡፡ የክረምት ዚያራ የሙት መታሰቢያዎች የሚዘጋጁት ለቋሚ ሰላምና መረጋጋት ሲባልም ለመሆኑ ትልቅ ማሳያ ነው፡፡

### 7.2.3.6. ዚያራ

ዚያራ በመንፈሳዊ ህይወታቸው የበቁ ሼሆች ከሞቱ በኋላ የአካባቢው ሰው ተሰብስቦ የሚያደረግላቸው መታሰቢያ ነው፡፡ ዚያራን የመከወኑ ዋና ዓላማ እንደሌላው የሙታን መታሰቢያ የሟች ነፍስ ምህረት እንድታገኝ ተማፅኖ ማድረግ አይደለም፡፡ ዚያራው የሚደረግላቸው ሰዎች የበቁና የተመረጡ በመሆናቸው ነፍሳቸው በፈጣሪ ዘንድ መልካም ቦታ የምታገኝና ሰዎችም በህይወታቸው መልካም እንዲሆንላቸው ፈጣሪን የምትለምን እንደሆነች ይታመናል፡፡ ስለዚህ ሰዎች ለዚያራ የሚመጡት በረከት ለማግኘት፣ በህይወታቸው የጐደለ ነገር እንዲሟላላቸው ለመማፀንና ስዕለት ለማድረግ፣ ስዕለታቸውን ለማስገባት፣ ሟቾችን ለመዘከርና ለማሞገስ ነው (ወ/ሮ ዘምዘም መሐመድ፣ 18/5/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በአርጐባ ዚያራ የሚከናወነው ገበሬው የግብርና ስራውን አከናውኖ፣ አዝመራውን አጭዶና ወቅቶ ጐተራ የሚከትበትን ወር በማስታከክ ሲሆን ይህም ከታህሳስ ወር መጨረሻ ጀምሮ እስከ ጥር ወር መጨረሻ ድረስ ይሆናል፡፡ የዚያራው ቀን ተወስኖ ሲነገር ሰዎች ከዚያራው

ቀን አስቀድመው ዚያራው በሚደረግበት ቤት ይሰባሰባሉ፡፡ በመቃብር ቦታ በመሄድ ዘይረው ከተመለሱ በኋላ ስነ ስርዓቱ በሽሊፋው ቤት የሚከወን ይሆናል፡፡ ሰዎች በረከት ለማግኘት የዓይነትና (ለምሳሌ፣ እህል፣ ሙክት) የገንዘብ ስጦታ ያደርጋሉ፤ እህል ማሰናዳቱን፣ እንጨት መስበሩን፣ ዳስ መጣሉን፣ ጋገራውን፣ ወዘተ ሁሉ ተረዳድተው ያከናውናሉ፡፡ ድግስ ተደግሶ ስነ ስርዓቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ ሰው ሁሉ ይጋበዛል፡፡ ከእነዚህ የሙታን መታሰቢያ ስነ ስርዓቶች በተጨማሪ ሰዎች የሞተ ቤተሰባቸውን አባል መታሰቢያ በተመቻቸውና ማድረግ በሚፈልጉ ጊዜ ሁሉ ያደርጋሉ (አቶ መሐመድ ኑርሁሴን፣ 21/6/2013፣ ገበሮች ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ይህ ጊዜ ከሟች አንፃር የሟች ነፍስ ወደ ዘላቂ ማረፊያዋ የምትቀላቀልበት፤ ከሀዘንተኞች አንፃር ደግሞ ሀዘንተኞች ዋናውን የለቅሶ ጊዜ ጨርሰው ቀስ በቀስ ወደቀደመው የህይወት እንቅስቃሴያቸው የሚመለሱበትና ወደ ማህበረሰቡ ተመልሰው የሚቀላቀሉበት ነው፡፡ የዚህ መቀላቀል መሰረት እንደሆኑ የሚታመንባቸው የመታሰቢያ ስነ ስርዓቶች በዚህ ጊዜ በዋናነት የሚነሱ ናቸው፡፡ እነዚህ መታሰቢያዎች የሟች ነፍስን መንገድና ማረፊያ ያስተካክላሉ፣ ምህረት ያስገኛሉ፣ በተከወኑ ቁጥር የሟችን ሀጢያት እየሸራረፉ የሟች ነፍስን ወደ ጥሩ ማረፊያ ያደርሳሉ በሚል እምነት የሚከወኑና ቋሚም ከሟች ነፍስ ጋር ያለውን ግንኙነት መልክ የሚያስይዝባቸው ናቸው፡፡ የሟች ቤተሰብ በቆዳ ማጠፊያ ስነ ስርዓት ላይ በመሰደቅ፣ የወር መታሰቢያ ስነ ስርዓትና ጦም ቆሎ በማድረግ የሟች ነፍስ ወደ ማረፊያዋ እንድትሄድ የሚያግዝ ሲሆን ስነ ስርዓቱን ባለመከወኑ በሟች ነፍስ ከሚደርስበት ችግርና መረበሽም ይጠበቃል፡፡ በእነዚህ የመታሰቢያ ስነ ስርዓቶች በጋራ ሆኖ መመገብ መኖሩም የመቀላቀል መገለጫ ነው፡፡

ሀዘንተኞች ከቆዳ ማጠፊያ ስነ ስርዓት ክዋኔ በኋላ ቀስ በቀስ ቀደም ሲል ወደነበረው ህይወታቸው ይመለሳሉ፡፡ የቤት ውስጥ ስራዎቻቸውን ማከናወንና በመጠኑ በማህበራዊ ህይወት ውስጥ መሳተፍ ይጀምራሉ፡፡ ሟች ትዳር ያለው ወንድ ከነበረ ግን የሟች ሚስት የመቀላቀያ ጊዜዋ የሚጀምረው የዓግል መፍቻ ስነ ስርዓት ከተከወነ በኋላ ይሆናል፡፡ ከስነ ስርዓቱ ስያሜ መፍታት የሚለው ቃል መውጣት፣ ከተለየ፣ ከታገደ፣ ከተከለከለ ነገር ነፃ መሆን የሚል ትርጉም ያለው ነው፡፡ የሟች ሚስት ወደ ማህበረሰቡ መልሳ የምትቀላቀለው ግን በአዲስ ማንነት ነው፤ ሞት ከመከሰቱ በፊት ባለትዳር ሴት የነበረች ሲሆን ሞት ከተከሰተ በኋላ ግን ባሏን በሞት ያጣች ሴት ትሆናለች፡፡

## 7.3. የአርጐባ ብሄረሰብ የሀዘን ስነ ስርዓት ክዋኔ ፋይዳ

የአርጐባ ብሄረሰብ የሀዘን ስነ ስርዓት ክዋኔ ለከዋኞቹ ተግባቦታዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኰኖሚያዊና ስነ ልቡናዊ ፋይዳዎች አሉት፡፡

**ተግባቦታዊና ማህበራዊ ግንኙነትን የማጠናከር ፋይዳ፣**

በአርጐባዎች ዘንድ ያለው ጠንካራ ሀዘን የመድረስ ልማድ የተግባቦት መንገድ ነው፡፡ ሰዎች በሀዘን ቤት መገኘታቸውና በሚከወኑ ስነ ስርዓቶች ላይ መሳተፋቸው ለሀዘንተኞች ያላቸውን ቀረቤታና አጋርነት ማሳየታቸው ነው፡፡ ሰዎች ወደ ሀዘን ቤት በመሄድ ከሀዘንተኞች ጋር አብረው ሲሆኑ፣ አብረው ሲያለቅሱ፣ ቤቶቻቸውን ትተው ከሀዘንተኞች ጋር ሲውሉና ሲያድሩ፣ ሀዘንተኞችን ሲረዱ፣ የተፈጠሩ ችግሮችን ሲቀርፉ፣ ሀዘንተኞች ቁጭ ብለው ጐረቤቶች የቤቱን ስራ ሲያከናውኑ፣ ምግብ ከየቤታቸው በመውሰድ መሸኛና ማምሻ ሲያዘጋጁ፣ ሰው ሲያስተናግዱ፣ የመቃብር ጉድጓድ ሲቆፍሩ፣ አስከሬን አጥበው ሲገንዙ፣ አስከሬን ወስደው ሲቀብሩ፣ ወዘተ ሰዎቹ ሀዘንን እየተጋሩ መሆኑን እየገለፁ፣ ለሀዘንተኞቹ ያላቸውን ቅርበት፣ ፍቅርና አጋርነት እያሳዩ ነው፡፡

ሰዎች ከሀዘንተኞች ጋር ባላቸው ግለሰባዊ ግንኙነት ምክንያት በሀዘን ስነ ስርዓቶች ላይ በመሳተፍ ማህበራዊ አንድነታቸውን ያስጠብቃሉ፡፡ ሰዎች ባለመነጣጠላቸውና የሀዘን ስነ ስርዓትን በመሰለው አጋጣሚ በመገኘታቸው ቅርበታቸውን ያስመሰክራሉ፤ አንድነታቸውን ያጠናክራሉ፡፡ በቀብር ቀንና በመታሰቢያ ስነ ስርዓቶች ላይ በጋራ መመገብም ማህበራዊ ግንኙነትን ያጠናክራል፡፡

**ኢኰኖሚያዊ ፋይዳ፣**

ሀዘን ደራሾች ለሀዘንተኞች የሚያደርጉት የገንዘብና የዓይነት ስጦታ ለሀዘንተኞች ኢኰኖሚያዊ ፋይዳን ያስገኛል፡፡ ለዚህ ዋና መገለጫው የሀፈሻ ስነ ስርዓት ነው፡፡ ጐረቤቶች በሀዘን ቤት ሀዘንተኞችን እያጽናኑ ሲያመሹ የሚስተናገዱትና ከሩቅ የመጡ ሀዘን ደራሾችን የሚያስተናግዱትም ከየቤታቸው በሚያመጡት ምግብና መጠጥ ነው፡፡ ሀዘንተኞች ለእንግዶች ብለው የሚያዘጋጁት ምግብ አይኖርም፡፡ ይህ ልማድ ደግሞ ለሀዘንተኞች የኢኰኖሚ ድጋፍን ያስገኛል፡፡ ከዚህ ውጭ ሀዘን ደራሾች ለሀዘንተኞች የሚያደርጉት የገንዘብና የዓይነት ስጦታ ለሀዘንተኞች የኢኰኖሚ እገዛ ነው፡፡

**ስነ ልቡናዊ ፋይዳ፣**

ሀዘንተኞች በሽግግር ጊዜ ሀዘንና የመንፈስ መረበሽ ያጋጥማቸዋል፡፡ ሀዘን የመድረስ ልማድ ደግሞ ሀዘንተኞች የሚከሰትባቸውን መረበሽ በመቀነስ ረገድ ለሀዘንተኞች ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡ ሀዘንተኞች በዙሪያቸው በተገኙ ሰዎች ምክንያት የሚያጋጥማቸው የሀዘን ስሜት እንዲቀንስ፣ እንዲረሳሱ፣ እንዲበረቱ፣ ስሜታቸው እንዲስተካከል ይሆናሉ፡፡ በአንድነት ተሰብስቦ ማልቀስ በራሱ ከዚያ በኋላ መመለስን፣ መበርታትን፣ ስነ ልቡናዊ እፎይታን፣ እረፍትን ያስገኛል፡፡ በመሆኑም እነዚህ ክዋኔዎች ሀዘንተኞች የሚደርስባቸውን ሀዘንና እምቅ ስሜት በማቅለል ስነ ልቡናዊ ፋይዳ ያስገኛሉ ማለት ነው፡፡

ከሞት በኋላ የሚደረጉ መታሰቢያዎችና ሶደቃም የሟችን ነፍስና የቋሚንም ህይወት መልክ የሚያስይዝ ነው፡፡ የሚደረገው ሶደቃ የሟችን ነፍስ መንገድ ያቀናል፣ ነፍስን ወደ መዳረሻዋ ያደርሳል፣ የሟች ነፍስ በዚያኛው ዓለም ተቀባይነት እንድታገኝ ይረዳል በሚል እምነት ምክንያት ይከወናል፡፡ ሶደቃ አለማድረግ ቋሚን ይረብሻል ተብሎም ይታመናል፡፡ ለሟች አለመሶደቅ የሟች ቤተሰብ መንፈስ እንዲረበሽ ያደርጋል፤ በሀገርም ላይ ድርቅን ወይም የበዛ ዝናብን ያስከትላል ተብሎ ይታመናል፡፡ በአንፃሩ ሶደቃን ማድረግ ለቋሚ ወይም ለቤተሰብ መረጋጋትን፣ ለሀገርም የተስተካከለ ዝናብን ያስገኛል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ቋሚ ሶደቃን በማድረግ ባለመሶደቁ ምክንያት ሊደርስበት የሚችልን መረበሽ ይከላከላል፤ ስነ ልቡናዊ እፎይታን ያገኛል፡፡

## 7.4. የአርጐባ ብሄረሰብ የሀዘን ስነ ስርዓት ክዋኔ ለውጥና ቀጣይነት

በአርጐባ ብሄረሰብ የሀዘን ስነ ስርዓት ክዋኔ ላይ የተለያዩ ለውጦች ተከስተዋል፡፡ በዚህ ክፍል በስነ ስርዓቱ ክዋኔ ላይ የተከሰቱ ለውጦች ለለውጦቹ መንስኤ ከሆኑ ምክንያቶች አንፃር እና ያልተለወጡ ጉዳዮች ምንነት ይቀርባሉ፡፡

### 7.4.1. የተከሰቱ ለውጦች ከለውጥ ምክንያቶቻቸው አንፃር

በስነ ስርዓቱ ውስጥ የተከሰቱ ለውጦች በቀጥተኛ ምክንያት፣ በዘመናዊነትና በውሳኔ የተከሰቱ ናቸው፡፡

### 7.4.1.1. ቀጥተኛ ለውጦች

በቀብር ቀንና ከቀብር ቀን በኋላ ባሉ ምሽቶች ወንዶች ሀዘንተኞችን የሚያጽናኑት እንዲሁ በመጫወት ነበር፤ በአሁኑ ጊዜ[36] ግን ጫት እየቃሙ መጫወት ተለምዷል፡፡

ቀደም ሲል በሀፈሻ ስነ ስርዓት ወደ ሀዘኑ ቤት የሚወሰደው እንጀራና ወጥ፣ ሻይ፣ ቡናና የማሽላ ቆሎ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ግን ስኳርና ጫት መውሰድም እየተለመደ መጥቷል፡፡

በአሁን ጊዜ የቀብር ስነ ስርዓትን ቶሎ ማከናወን እየተለመደ መጥቷል፡፡ የቀብር ስነ ስርዓት አብዛኛውን ጊዜ የመቃብር ጉድጓድ ቁፋሮ እንዳለቀ ወዲያው በሰባት ሰዓት፣ ካልደረሰላቸው ደግሞ በአስር ሰዓት የሚከናወን እንጂ ሩቅ ቦታ ያለ ዘመድ አዝማድ ይሰብሰብ ብሎ አስከሬን አልብሶ መጠበቅ እየቀረ መጥቷል፡፡

በመቃብር ላይ በሚተከለው ድንጋይ ላይ የሟችን ስም በመቅረጽ ምልክት ማኖር እየተለመደ መጥቷል፡፡

እነዚህ ለውጦች ባህል ባለበት የሚቆይ ባለመሆኑ ምክንያት፣ ከዚህ ከታች ለለውጥ ምክንያት ሆነው ከቀረቡ ጉዳዮች በተለየ ሁኔታ የተከሰቱ ናቸው፡፡

### 7.4.1.2. ዘመናዊነት ያስከተለው ለውጥ

በአሁኑ ጊዜ የሀዘን ጥሪ በቀላሉ ስልክ ተደውሎ ይነገራል፡፡ ከዚያም ቢያልፍ በአካባቢው አልፎ አልፎ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ጥቂት ሞተር ሳይክሎች ስላሉ ለዚህ አይነቱ ድንገተኛ ጥሪ አማራጭ መጓጓዣዎች ሆነዋል፡፡

ከሌሎቹ ቀበሌዎች ይልቅ ጋቸኔ የከተማነት ጠባይ የሚታይበት በመሆኑ ለሀዘን ስነ ስርዓት ማከናወኛ የሚጣለው ዳስ በዘመናዊ ድንኳን እየተቀየረና የቅጠል ጉዝጓዙም እየቀረ በዘመናዊ ምንጣፍ ወይም ፕላስቲክ እየተቀየረ መጥቷል፡፡

ለሀዘን መቀመጫ እንዲሆን የሚነጠፈው መዋስ እየቀረ መጥቶ ሴት ሀዘንተኞች የሚቀመጡት ፍራሽ ላይ ሆኗል፡፡

---

[36] አቶ ኢብራሂም መሐመድ ከአስር አመት ወዲህ ብለዋል (27/3/2013፣ ላይ መጠቅለያ ቀበሌ፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በቀብር ቦታ የሚታደለው ንፍሮ የሚሰጠው በእጅ በእጅ እየተዘገነ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ግን በፌስታል እየቋጠሩ መስጠት ተጀምሯል፡፡

አስከሬን የሚያጥቡ ሰዎች አስከሬን የሚያጥቡት ሽማ በእጃቸው ላይ በመጠምጠም ነበር፤ በአሁኑ ጊዜ ግን ጓንት መጠቀም እየተለመደ ነው፡፡

### 7.4.1.3. ሆን ተብሎ የተደረጉ ለውጦች

ቀደም ባለው ጊዜ በብሄረሰቡ ሞት ሲያጋጥም ከባድ ሀዘን ይደረግ ነበር፡፡ ሩቅ ቦታ የሚኖር ዘመድ አዝማድ ሁሉ እስኪሰበሰብ ድረስ የቀብር ስነ ስርዓት አይከወንም፣ አልጋ ተለቅቆ መሬት ይተኛል፣ ሴቶች መቀነታቸው አጥብቀው ይሰነብታሉ፣ ያለ ጫማ በባዶ እግራቸው ይሄዳሉ፣ ከብዙ ጊዜ በኋላ በሰማ ጊዜ የመጣ ሀዘን ደራሽ ሲያለቅስ እንደ አዲስ ያለቅሳሉ፡፡ ይህ የሀዘን መግለጫ ሀዘንተኞች ላይ ጉዳት ያስከትላል በሚል ምክንያት የሀይማኖት አባቶች እየከለከሉ ይህ አይነቱ ድርጊት እየቀረ መጥቷል፡፡

## 7.4.2. ያልተለወጡ ጉዳዮች

የታመመ ሰውን ተረዳድቶ ማስታመም፣ ሰው ሲሞት ጥሪ ማድረግ፣ ዳስ መጣል፣ መሸኛ ማዘጋጀት፣ አስከሬን ማለስለስ፣ አስከሬን ማጠብና በልማዱ መሰረት መገነዝ፣ ራስን ሳይጎዱና ግጥም ሳይገጥሙ ማልቀስ፣ ሀዘን የመድረስ ጠንካራ ልማድ፣ በሀዘን ጊዜ በሀሳብ፣ በጉልበት፣ በገንዘብና በዓይነት መረዳዳት፣ ሀዘንተኞችን ማጽናናት፣ የሀፊሻ ስነ ስርዓት ማከናወንና የዓግል መፍቻ ስነ ስርዓትን ጨምሮ የመታሰቢያ ስነ ስርዓቶችን ማድረግ ያልተለወጡ ልማዶች ናቸው፡፡ የኮሮና ወረርሽኝ በሀዘን ስነ ስርዓት ክዋኔ ላይ ምንም አይነት ለውጥ አላስከተለም፡፡

## ምዕራፍ ስምንት

## ማጠቃለያ፣ ግኝት እና ይሁንታ

ይህ ጥናት "የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓቶች ክዋኔ ትንተና፣ በአፋር ክልል፣ ዞን ሶስት፣ አርጐባ ልዩ ወረዳ" የሚል ርዕስ ያለው ሲሆን የጥናቱ ዋና ዓላማ በአፋር ክልል ከሚኖረው የአርጐባ ብሄረሰብ የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች መካከል የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓቶችን ክዋኔ መተንተን ነው፡፡ በጥናቱ በአፋር ክልል የሚኖረው የአርጐባ ብሄረሰብ በወሊድ፣ በጋብቻና በሀዘን ጊዜ የሚከውናቸው ስነ ስርዓቶች ምን ምን ናቸው? እንዴትስ ይከወናሉ? የክዋኔዎቹ መዋቅር ምን መልክ አለው? በክዋኔዎቹ ውስጥ ያሉ ሌሎች የፎክሎር ዓይነቶች ምን ምን ናቸው? በስነ ስርዓቶቹ ውስጥ ያሉ ትዕምርቶች ምን ምን ናቸው? ፍካሬያዊ ትርጉማቸውስ ምንድን ነው? ስነ ስርዓቶቹ ለከዋኞቻቸው የሚሰጡት ግለሰባዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ምንድን ነው? የስነ ስርዓቶቹ ክዋኔ ቀደም ካለው ጊዜ ክዋኔ ጋር ያለው ልዩነትና ተመሳስሎ ምንድን ነው? መነሻቸው ወሊድ፣ ጋብቻና ሞት እንዲሁም የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶቹ የሆኑ ስነቃሎች የትኞቹ ናቸው? የሚያስተላልፏቸው መልዕክቶች ምንድን ናቸው? የሚሉ ጥያቄዎች መልስ አግኝተዋል፡፡

የጥናቱን ዓላማ ለማሳካትና የጥናት ጥያቄዎቹን ለመመለስ ቀዳማይና ካልዓይ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ካልዓይ መረጃን በተመለከተ ቀደም ሲል በጥናት ርዕሰ ጉዳዩና በአካባቢው የተሰሩ ጥናቶችና መጻሕፍትን፣ እንዲሁም የጽንሰ ሀሳብና የንድፈ ሀሳብ ትንታኔን የያዙ መጻሕፍትን በማንበብ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ቀዳማይ መረጃ ለመሰብሰብ የመስክ ስራ የተከናወነ ሲሆን በመስክ መረጃ ለመሰብሰብ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይት ዘዴዎች በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ የጥናቱ ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የወሊድ ስነ ስርዓት፣

በጥናቱ የአርጐባ ብሄረሰብ ባህላዊ የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ፣ መዋቅር ትዕምርትና ፋይዳ ቀርቧል፡፡ በብሄረሰቡ አንዲት ሴት ነፍሰጡር መሆኗን ካወቀችበት ጊዜ ጀምሮ ያሉ የቅምሻ ስነ ስርዓት፣ ለነፍሰጡር የሚደረግ እንክብካቤ፣ የነፍሰጡር ክልክሎችና ምክር፣ የአምሮት ስነ ስርዓት፣ የወሊድ ዝግጅት፣ የወሊድ ስነ ስርዓት፣ ላንቃ ማንሳት፣ የደም ዶሮ እርድ፣ የልጅ ኋሮ ቀበራ፣ የአራስ ቤት ገጽታና እንክብካቤ፣ የአራስ ጥየቃ፣ የሰባት ቀን

እጥበት ስነ ስርዓት፣ የአርባ ቀን እጥበት ስነ ስርዓት፣ የማዘየሪያና የቁንጮ መጣያ ስነ ስርዓቶች ዋና ዋና ስነ ስርዓቶች ናቸው፡፡

የእነዚህ ስነ ስርዓቶች ድምር የሆነው የብሂረሰቡ የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ መዋቅሩ ከ Gennep የሶስት ደረጃ ሞዴል አንፃር ለሶስት (መለየት፣ ሽግግርና መቀላቀል) ሊከፈል የሚችል ነው፡፡ ይህም አንዲት ሴት ነፍሰጡር መሆኗ ከታወቀ በኋላ የቅምሻ ስነ ስርዓት ሲከወን ነፍሰጡሯ ከነበረችበት ማህበረሰብና ከቤተሰቧ አባላት ትለያለች፡፡ የሽግግር ጊዜ ከቅምሻ ስነ ስርዓት ክዋኔ ጀምሮ ከወሊድ በኋላ እናቲቱ የአራስነት ጊዜዋ እስከሚያበቃበት የአርባኛ ቀን እጥበት ዋዜማ ድረስ ያለውን ጊዜ ይይዛል፡፡ በዚህ ጊዜ የሚከወኑ ለነፍሰጡሯ የሚደረግ እንክብካቤ፣ የሚጣሉባት ክልክሎችና የሚሰጣት ምክር ነፍሰጡሯ ላይ ማእቀብ የሚጥሉ ናቸው፡፡ ይህ ደረጃ ነፍሰጡሯ አዲስ ማንነትን ለማግኘት ጊዜው ያልደረሰላት፣ በምጥና በጭንቅ የምትያዝበት፣ በዙሪያዋ ያሉ ሰዎች የሚጨነቁበትና ዱዓ የሚደረግበት ጊዜ ነው፡፡ ከወሊድ በኋላም በአራስነቷ ምክንያት ለህመም የተጋለጠች ተደርጋ የምትታሰብበት በመሆኑ አራሷንና ልጇን ከህመም ለመጠበቅ የተለየ እንክብካቤ የሚደረግላቸው፣ አራሷም ለህመም መከላከያ እንዲሆናት በራስጌዋ ብረት የምታስቀምጥበት፣ ለሽንት ስትወጣም እንዲሁ ብረት የምትይዝበትና በፀጉሯ ላይም የምታደርግበት፣ በወሊድ ምክንያት ንፁህ እንዳልሆነች የሚታሰብ በመሆኑ ቀደም ሲል ታከናውናቸው የነበሩ ተግባራትን የማታከናውንበት ጊዜ መሆኑ አራሷ በሽግግር ውስጥ ያለች መሆኗን የሚያሳይ ነው፡፡ የመቀላቀል ደረጃ ከአርባኛው የእጥበት ቀን የሚጀምር ሲሆን ከዚያ በኋላ አራሷ ቀደም ሲል ወደተነጠለችው ማህበረሰብ፣ የፆታ አቻዎቿና የቤተሰቧ አባላት በተለየ ማንነት ትቀላቀላለች፤ አራስ ልትጋለጥባቸው ትችላለች ተብለው ለሚታሰቡ ህመሞች መከላከያ እንዲሆናት ትይዛቸው የነበሩ ቁሶችን በመተው መንቀሳቀስ ትጀምራለች፤ በአራስነት ጊዜዋ ንፁህ እንዳልሆነች በመታሰቡ ምክንያት እንዳታደርግ ትከለከላቸው የነበሩ ተግባራትንም ማከናወን ትጀምራለች፡፡

በጥናቱ በብሂረሰቡ የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ ውስጥ ያሉ የፎክሎር አይነቶች የተለዩ ሲሆን እነርሱም ስነቃሎች (ዱዓዎች፣ ዝኪሮች፣ መማፀኛዎች፣ መልካም ምኞትን መግለጫዎች፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ ዝየራዎች)፣ ቁሳዊ ባህሎች (ባህላዊ ምግብና መጠጥ፣ ሽታ፣ አዝጋሮ፣ ወይባ፣ ገላ መታጠቢያ ቅጠላ ቅጠል፣ አልባሳት፣ የማዋለጃ ቁሳቁሶች፣ የልጅ ጓሮ መቅበሪያ ቁስ) እና ሀገረሰባዊ ልማዶች (እምነቶች፣ ባህላዊ ሕክምና (መንፈሳዊና የእጽዋት ሕክምና)፣

የፀጉር አሰራር፣ ጭስ መሞቅ፤ ስም አወጣጥ) ናቸው፡፡ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት በክዋኔው ውስጥ አልተገኙም፡፡

በጥናቱ በብሄረሰቡ የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ ውስጥ ያሉ ቃላዊ፣ ቁሳዊና ድርጊታዊ ትዕምርቶች ተለይተው ፍቺዎቻቸውም የቀረቡ ሲሆን ክዋኔው ማህበራዊ፣ ስነ ልቡናዊ፣ እሴቶችን የመትከልና ጤና የማስገኘት ፋይዳ ያለው መሆኑ በጥናቱ ተለይቷል፡፡

በጥናቱ የብሄረሰቡ የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ ከለውጥና ቀጣይነት አንፃርም ታይቷል፡፡ በክዋኔው ላይ ለውጥ ያስከተሉ ዋና ጉዳዮች ዘመናዊነትና የኢኮኖሚ ጫና ናቸው፡፡ ዘመናዊ ህክምና እየተስፋፋ በመምጣቱ ምክንያት እናቶች በጤና ተቋማት መውለድን እየለመዱ ይገኛሉ፡፡ በዚህ ምክንያትም በቅድመና ድህረ ወሊድ ስነ ስርዓቶች ክዋኔ ላይ ለውጥ ተከስቷል፡፡ በሌላ መንገድ ዘመናዊነት የወሊድ ስነ ስርዓት መከወኛ በሆኑ ቁሶች ላይ ለውጥ አስከትሏል፡፡ ለውጥን ተቋቁመው የሚከወኑ የስነ ስርዓቱ ክዋኔዎች መኖራቸውም በጥናቱ ተመላክቷል፡፡

- የጋብቻ ስነ ስርዓት፣

በዚህ ጥናት የአርጎባ የጋብቻ ስነ ስርዓት ከክዋኔ፣ መዋቅር፣ ትዕምርትና ፋይዳ አንፃር ቀርቧል፡፡ በዚህም መሰረት በጥናቱ የማጨት ሂደት፣ የስለላ ስነ ስርዓት፣ የቆዳ ማንጠፊያ ስነ ስርዓት፣ የነገር መፍጃ ስነ ስርዓት፣ የሰርግ ስነ ስርዓት ዝግጅት፣ የሰርግ ስነ ስርዓት (የጉፍታ መጫን፣ የኒካህ ማሰር፣ የወግ ማስረከብ፣ የገበታና የባዷሼህ ስነ ስርዓቶች)፣ የደመቅሁ፣ የመልስና የጎጆ መውጫ ስነ ስርዓቶች ክዋኔ ቀርቧል፡፡ ክዋኔው ከስነ ስርዓቶች ሶስት ደረጃ አንፃር ሲታይ ከመለየት ደረጃ ቀድመው የመጡ ክዋኔዎች ተለይተዋል፡፡ እነዚህ ክዋኔዎች የማጨት ሂደትና የስለላ ስነ ስርዓት ሲሆኑ ቅድመ መለየት ክዋኔዎች በሚል ርዕስ ስር ቀርበዋል፡፡ በመሆኑም በዚህ የአርጎባ ብሄረሰብ የጋብቻ ስነ ስርዓት ጥናት ሞዴሉ ባለ ሶስት ደረጃ መሆኑ ቀርቶ ባለ አራት ሆነ ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ይህን የጥናቱን ግኝት መነሻ በማድረግ ስነ ስርዓቶች በሶስት ደረጃዎች ያልፋሉ የሚለው እሳቤ አንዳንድ ጊዜም ከዚያ ደረጃ በላይ ሊያልፉ የሚችሉ ስነ ስርዓቶች ለመኖራቸው ፍንጭ ነው ማለት ነው፡፡ በብሄረሰቡ የጋብቻ ስነ ስርዓት የመለየት ደረጃ የሚጀምረው የቆዳ ማንጠፊያ ስነ ስርዓት ተከውኖ ጋብቻው እሺታን ባገኘ ጊዜ ነው፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ተጋቢዎቹ ቀደም ሲል ከነበራቸው የአኗኗር ዘይቤ ይለያሉ፣ በእድሜ እኩዮቻቸውና

በአጠቃላይ በማህበረሰቡም በተለየ ሁኔታ ይታያሉ፡፡ የሽግግር ጊዜ ከነገር መፍጃ ስነ ስርዓት ክዋኔ ጀምሮ እስከ ሰርግ ቀን ዋዜማ ድረስ የሚቆይ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ተጋቢዎቹ ቀደም ሲል ከነበራቸው ማንነት ተለይተዋል ነገር ግን ሽግግር ላይ በመሆናቸው የተለየ ማንነት ያላገኙበት ጊዜ ነው፡፡ ይህ ጊዜ ቃል የሚታሰርበት፣ የሰርግ ቀን የሚቆረጥበት፣ የሰርግ መደገሻ ገንዘብ ለሴቷ ቤተሰብ የሚሰጥበት፣ ለልጅቷ ልብስ የሚሰጥበትና እስከ ሰርጉ ቀን ድረስ ባሉ በዓላትና የእሸት ወቅቶች ሁሉ የወንዱ ቤተሰብ ለሴቷ ቤተሰብ ስጦታ የሚልክበት የተጋቢዎቹ የእጮኝነት ጊዜ ነው፡፡ ይህ ጊዜ ተጋቢዎቹ ለኑሮ የሚዘጋጁበት፣ እርስ በርስ፣ አንዳቸው ከሌላቸው ቤተሰብ አባላትና ቤተሰቦቻቸው እርስ በርስ የሚኖራቸው ግንኙነት በተለየ ሁኔታ የሚቃኝበትና የሰርግ ዝግጅት የሚደረግበት ነው፡፡ የመቀላቀል ጊዜ ከሰርግ ስነ ስርዓት ክዋኔ የሚጀምር ሲሆን የሰርግ ስነ ስርዓትን ጨምሮ ከዚያ በኋላ የሚከወኑ የመልስና የጉጆ መውጫ ስነ ስርዓቶች የመቀላቀያ መገለጫ የሆኑ ክዋኔዎችን የያዙ ናቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ተጋቢዎች በአዲስ ማንነት፤ ወንዱ በአባወራነትና ሴቷ በእማወራነት ወደ ማህበረሰቡ ይቀላቀላሉ፡፡ ሴቷ በተለየ አለባበስና አጋጌጥ እንዲሁም የፀጉር አሰራር ትቀላቀላለች፡፡

በጥናቱ በብሄረሰቡ የጋብቻ ስነ ስርዓት ክዋኔ ውስጥ ያሉ የፎክሎር ቅንጣቶች ተለይተዋል፡፡ እነርሱም ስነቃሎች (ቃል ማሰሪያዎች፣ የዘፈን ግጥሞች፣ መወከያዎች፣ ዱዓዎች፣ መልካም ምኞት መግለጫዎች፣ የቃላት ምልልሶች፣ መንቶ ግጥም፣ ዝየራዎች)፣ ቁሳዊ ባህሎች (ምግብና መጠጥ፣ ወይደል (የፍየል ቆዳ)፣ የሙሽራ ጉጆ መውጫ ቁሳቁሶች፣ ለወግ የሚሰጡ ቁሶች፣ ወይባ፣ አዝጋሮ፣ ሽታ፣ አልባሳት፣ ጉፍታ፣ ጌጣጌጥ፣ ዳስ)፣ ሀገረሰባዊ ልማዶች (ጨዋታዎች (ሺሎ፣ ደመቅሁ)፣ እምነቶች፣ የጊዜ አረዳድ፣ ጭስ መሞቅ፣ የፀጉር አሰራር) እና ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት (ዘፈኖች) ናቸው፡፡

በጥናቱ እንደተለየው በዚህ ክዋኔ ቃላዊ፣ ቁሳዊና ድርጊታዊ ትዕምርቶች ተገኝተው ተፈክረዋል፡፡ ክዋኔው ለብሄረሰቡ አባላት በአጠቃላይ የአሻጋሪነት፣ ማህበራዊ ኑሮን የማጠናከር፣ የማስተማር፣ የተግባቦት፣ የማዝናናት፣ የማሞገስ ፋይዳዎች እንዲሁም ኢኮኖሚያዊና ስነ ልቡናዊ ፋይዳዎች ያሉት መሆኑም በጥናቱ ተገልጿል፡፡

በጥናቱ የብሄረሰቡ የጋብቻ ስነ ስርዓት ክዋኔ ከለውጥና ቀጣይነት አንፃር የታየ ሲሆን የስነ ስርዓቱ የክዋኔና የመዋቅር ለውጦች ተለይተዋል፡፡ የክዋኔ ለውጡን በተመለከተ ቀጥተኛ ለውጦች፣ ዘመናዊነት፣ የሌላን ባህል ተቀብሎ መከወን፣ ኢኮኖሚያዊ ጫናና ውሳኔዎች

ለተከሰቱ ለውጦች ዋና ምክንያቶች መሆናቸው ተገልጿል፡፡ ቀጥተኛ ለውጦች በጋብቻ ዓይነትና መስፈርት ላይ፣ በእጮኝነት ጊዜ ባለ የግንኙነት መልክ ላይ፣ በሚዜ መረጣ፣ ሚናና ቁጥር ላይ፣ በወግ ዓይነትና መጠን ላይ እና በክዋኔ ጊዜና ቦታ ላይ ተከስተዋል፡፡ በዘመናዊነት ምክንያት በክዋኔና በክዋኔ ቁሶች ላይ በተለይም በአልባሳትና በምግብ ማቅረቢያ ቁሶች ላይ ለውጦች ተከስተዋል፡፡ የሌላን ባህል በማምጣትና በመከወን የክዋኔ ለውጦች የተስተዋሉ ሲሆን በዋናነት የ"ደምባችንን" እና የ"አብሱማችንን" ክዋኔዎች ተገልፀዋል፡፡ በጥናቱ በኢኮኖሚ ጫና እና በሀይማኖት አባቶችና በሀገር ሽማግሌዎች ውሳኔ የተከሰቱ ለውጦች መኖራቸውም ተገልጿል፡፡ የተከሰተ የመዋቅር ለውጥና ለውጥን ተቋቁመው የቀጠሉ ክዋኔዎች መኖራቸውም ተገልጿል፡፡

- የሀዘን ስነ ስርዓት፣

የአርጎባ ብሄረሰብ የሀዘን ስነ ስርዓት የመለየት ደረጃ አንድ ሰው በጽኑ ታምሞ በህይወት እስኪያልፍ ድረስ ያለው ጊዜ መሆኑና በህመም ጊዜ የሚከወኑ ስነ ስርዓቶች የዚህ ጊዜ መገለጫዎች መሆናቸው በጥናቱ ተገልጿል፡፡ ይህ ጊዜ ከሟች አንፃር ሲታይ ሟች በጠና ሲታመም ከሌላው ሰው ተለይቶ ይታያል፤ ቤተሰቡና የቅርብ የሆኑ ሰዎች ያስታምሙታል፤ የተለየ ምግብ ያዘጋጁለታል፤ ጭዳ ያደርጉለታል፤ ዱዓ ያደርጉለታል፡፡ ታማሚው ሲሞት ደግሞ ከዓለም ኑሮ ይለያል፡፡ ይህ ደረጃ የሟች ቤተሰብ አባላት ሀዘንተኞች በመሆናቸው ከቀን ተቀን የህይወት እንቅስቃሴያቸው የሚለዩበት ነው፡፡ የስነ ስርዓቱ የሽግግር ጊዜም ሞት ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ የቆዳ ማጠፊያ ስነ ስርዓት እስከሚከወንበት ቀን ዋዜማ ድረስ ያለውን ጊዜ ይይዛል፡፡ ጥሪ ማድረግ፣ ዳስ መጣል፣ መሸኛ ማዘጋጀት፣ የመቃብር ጉድጓድ መቆፈር፣ አስከሬን ማለስለስ፣ አስከሬን ማጠብና መገነዝ፣ በጋራ ማልቀስ፣ በቀብሩ ቀን በሀዘኑ ቤት በጋራ መመገብ፣ አስከሬን ማጓጓዝ እና የቀብርና የሀፈሻ ስነ ስርዓት ክዋኔዎች የሽግግር ጊዜ መገለጫዎች መሆናቸውም በጥናቱ ተገልጿል፡፡ ይህ የሽግግር ጊዜ ዋናው የሀዘን ጊዜ ሲሆን ሽግግሩን ከሟችና ከሟች ቤተሰብ አንፃር መመልከት ይቻላል፡፡ ከሟች አንፃር ሲታይ ሟች ከተቀበረ ጊዜ ጀምሮ እስከ ሰባት ቀን ድረስ ነፍሱ ወደ ዘላቂ ማረፊያዋ እንደማትደርስ ይታመናል፤ በሌላ መንገድ ሀዘንተኞች በሀዘንተኛነታቸው ምክንያት ቀደም ሲል ከነበራቸው ህይወት ተለይተው ሀዘን የሚደርሱ ሰዎችን ብቻ እየተቀበሉ የሚቆዩበትና የመቀላቀያ ጊዜያቸው ገና የሆነባቸው ሆነው ይቆያሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ሁለቱም በሽግግር ደረጃ ላይ ይሆናሉ፡፡ የመቀላቀል ደረጃ ከቆዳ ማጠፊያ ስነ

ስርዓት ክዋኔ ጀምሮ ከዚያ በኋላ ያሉ የሙት መታሰቢያ ስነ ስርዓቶች የሚከወኑበትን ጊዜ በሙሉ ያጠቃልላል፡፡ ቆዳ ማጠፊያ የመጀመሪያው የሙት መታሰቢያ ስነ ስርዓት ሲሆን የሟችን ነፍስ ወደ ዘላቂ ማረፊያዋ የሚያደርስ፣ ሀዘንተኞችንም በመጠኑ ቀደም ሲል ወደነበራቸው የእለት ተእለት እንቅስቃሴ የሚመልስ ነው፡፡ ከቆዳ ማጠፊያ ስነ ስርዓት በኋላ የሚከወኑ የሙት መታሰቢያ ስነ ስርዓቶች የሟችን ነፍስ ወደተሻለ ማረፊያ ያደርሳሉ ተብለው ታምኖባቸው የሚከወኑና ሀዘንተኞችም እያንዳንዳቸውን መታሰቢያዎች ተከትለው ቀደም ሲል ወደነበራቸው ህይወት በተሻለ የሚመለሱባቸው በመሆናቸው ዋነኛ የመቀላቀል ደረጃ መገለጫዎች ናቸው፡፡

በጥናቱ በብሂረሰቡ የሀዘን ስነ ስርዓት ክዋኔ ውስጥ ያሉ ሌሎች የፎክሎር አይነቶች የተለዩ ሲሆን እነርሱም ስነቃሎች (ዱዓ፣ መርዶ መንገሪያ ጥሪ፣ ማጽናኛዎች፣ መሰናበቻዎች) ቁሳዊ ባህሎች (ምግብና መጠጥ፣ የከፈን ጨርቅ፣ አዲስ ልብስ፣ ማግ፣ ጥጥ፣ ቀጭኔ፣ አዝጋሮ፣ ድንክ አልጋ፣ መዋስ (የተለፋ ቆዳ)፣ ለኸድ መዝጊያ ድንጋይ፣ የመቃብር ላይ ድንጋይ፣ የመቃብር ላይ ካብ፣ የመቃብር ቤት፣ ዳስ) ሀገረሰባዊ ልማዶች (ባህላዊ ህክምና፣ እምነት) ናቸው፡፡ በክዋኔው ውስጥ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት አልተገኙም፡፡

በጥናቱ በክዋኔው ውስጥ ያሉ ድርጊታዊ ትዕምርቶችና ፍቺዎቻቸው የቀረቡ ሲሆን ክዋኔው በአጠቃላይ ተግባቦታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ስነ ልቡናዊና ማህበራዊ ግንኙነትን የማጠናከር ፋይዳዎች ያሉት መሆኑ በጥናቱ ተገልጿል፡፡

በጥናቱ በብሂረሰቡ የሀዘን ስነ ስርዓት ክዋኔ ላይ ቀጥተኛ ለውጦችና በዘመናዊነትና በውሳኔ ምክንያት የተከሰቱ ለውጦች መኖራቸው የተገለፀ ሲሆን ያልተለወጡ ጉዳዮች መኖራቸውም ተረጋግጧል፡፡

ትኩረታቸው ወሊድ፣ ጋብቻና ሞት እንዲሁም እነዚህን የህይወት ሽግግሮች ተከትለው የሚከወኑ ስነ ስርዓቶች የሆኑ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ተለይተው የይዘት ምርመራ ተደርጐባቸዋል፡፡ የተመረመሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች የከዋኞቻቸውን ሀሳብ የሚያንፀባርቁ ሲሆኑ በብሂረሰቡ ተቀባይነት ያላቸውን እሴቶች በማሞገስ፣ ተቀባይነት የሌላቸውን ደግሞ በመንቀፍ ተቀባይነት ያላቸው እሴቶችን የመትከል ፋይዳ አላቸው የሚል መደምደሚያ ላይ ተደርሷል፡፡

የጥናቱን ግኝቶች መሰረት በማድረግ የሚከተሉት የይሁንታ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

- ዘመናዊ የህክምና ተቋማት ባህላዊውን የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ ግብዓት በማድረግ የነፍሰጡር ማረፊያዎቻቸውንና ማዋለጃዎቻቸውን ሁኔታ በብሄረሰቡ ባህል መሰረት ማስተካከል ቢችሉ ግባቸውን ማሳካት ይችላሉ፤ የባህላዊውን ስነ ስርዓት ቀጣይነትንም ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ በጋቾኔ ቀበሌ ጤና ጣቢያ ውስጥ ለወላዶች ማረፊያ ተብሎ የተሰራው ባህላዊ ጐጆ ለታሰበለት ዓላማ እንዲውል የማመቻቸት ስራ ቢሰራ፣
- ነፍሰጡር ያሉባት የምግብ ክልክሎች ነፍሰጡሯ ከምግብ ልታገኝ ከሚገባው ንጥረ ነገር አንፃር የሚያሳጣት ነገር መኖር አለመኖሩ በወረዳው የጤና ጽ/ቤት ጥናት ተደርጐ ቢለይ፣
- ነፍሰጡር ሴት ያምራታል በሚል ጐረቤቶች እንድትመገብ የሚወስዱላት ዋና ምግብ ጥሬ ወይም ያልበሰለ የከብት ጨጓራና ጉበት ነው፡፡ ይህ እና በወሊድ ጊዜ የሚከወኑ አንዳንድ ክዋኔዎች ለምሳሌ፣ መነቅነቅ፣ ሆድ ማሸት፣ ወላድን በጭንቅላት መዘቅዘቅና የመሳሰሉት ከጤና አንፃር ነፍሰጡርና ወላድ ላይ የሚያስከትሏቸው የጤና ጉዳቶች ካሉ ይኸው ሁኔታ በወረዳው የጤና ጽ/ቤት ጥናት ተከናውኖ ጉዳቱ ቢለይ፣
- ከባህሉ ውጭ በየጊዜው እየጨመረ የመጣው የጥሎሽ መጠን በየጊዜው ከሚታየው የኑሮ መወደድ ጋር ተደምሮ ወጣት ወንዶችን አላስፈላጊ ጭንቀትና ወጪ ውስጥ እየከተታቸው ይገኛል፡፡ በባህል ዘርፍና በሌሎች ተመሳሳይ ሙያዎች የሚሰሩ አካላት ይህ ዓይነቱ ልማድ የሚያስከትለውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግር ማጥናት ቢችሉ፣
- መጠኑ ከፍ እያለ የመጣውን ጥሎሽ ለመክፈል አለመቻል ለስምምነት ጠለፋ መለመድ ምክንያት ሆኗል፡፡ ይህም በተጋቢዎች ላይ የስነልቡና ጫናን እና በቤተሰቦቻቸው ላይም ቅሬታንና ቁጣን የሚፈጥር በመሆኑ የወረዳው የሴቶችና ህፃናት ጽ/ቤትና ሌላውም የሚመለከተው አካል ትምህርት በመስጠት የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ ቢሰሩ፣
- “የደንባችንን” እና “የአብሱማችንን” የሚባሉ ከሌላ አካባቢ የተወረሱ ልማዶች በሰዎች መካከል ግጭትን የሚያስነሱና የደንብና የአብሱማ በሚጠየቀው አካል

በኩል ኢኮኖሚያዊ ጫናን የሚፈጥር በመሆኑ የወረዳው የባህል ጽ/ቤት በዚህ ረገድ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ ቢሰራ፣

- በሀዘን ጊዜ በብሄረሰቡ ዘንድ ያለ የመተጋገዝና የመረዳዳት ጠንካራ ልማድ የእርስ በርስ ግንኙነትን የሚያጠናክርና በሀዘንተኞች ዘንድ የሚኖርን ጫና የሚቀንስ ነው፡፡ ሀፊሻን የመሰለ የብሄረሰቡን እሴት ከዘመናዊ የመረዳጃ ተቋማት ጋር ማስተሳሰር ለቀጣይነቱ አስተዋጽኦ የሚያደርግ በመሆኑ የወረዳው ባህል ጽ/ቤት በዚህ ጉዳይ ቢሰራ፣
- ዚያራ ለበርካታ ቀናት የሚከወንና ዝርዝር ክዋኔዎችንም የያዘ የሙት መታሰቢያ ስነ ስርዓት ነው፡፡ በመሆኑም በፎክሎር እና አንትሮፖሎጂ የጥናት መስክ ያሉ ተመራማሪዎች ክዋኔውን በዝርዝር ቢያጠኑት፡፡

# የዋቢ መጻሕፍትና ጽሁፎች ዝርዝር


ለማ ንጋቱ፡፡ "የለቅሶ ሥርዓት ክወና በደቡብ ጎንደር ዞን"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ በፎክሎር የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት፡፡ 2006፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ስራዬ እንዳለው፡፡ "የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ስርዓት ክዋኔ በፍኖተ ሰላም አካባቢ ከፎክሎር ክዋኔ ንድፈ ሀሳብ አንፃር"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር መርሀ ግብር የኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት፡፡ 2005፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ረጅብ መሐመድ ዓብዱልሐሊም፡፡ *የሐበሾችና የዘይላዕ ሙስሊሞች የመካከለኛው ዘመን መንግሥታት ፖለቲካዊ ግንኙነት ታሪክ*፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ድሬ ማተሚያ ድርጅት፣ 2001፡፡

አህመድ መሀመድ ኢብራሂም፡፡ *በኢትዮጵያ የማክዙማይትና የሃሺማይት ወላስማ ስርወ-መንግስት ስልጣኔና ታሪክ የአርጐባ ሕዝብ የመነሻና የማንነት ግንዛቤ*፡፡ 1999፡፡

አለቃ ታየ፡፡ *የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ*፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ ማተሚያ ቤት፣ 1958፡፡

አበባ አማረ፣ ደስታ አማረ እና ፍሬህይወት ባዩ፡፡ "የሕይወት ኡደት ባህላዊ ክዋኔና ሥርዓት በስልጤ"፡፡ *Some Features of Diversity of Ethiopian Languages and Cultures.* Vol. 2, Addis Ababa University, Addis Ababa University Business Enterprise Printing Press. 2015, ገጽ 2-115.

አዲሱ ጴጥሮስ፡፡ "የአርጐባ ማህበረሰብ የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ትንተና"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር የኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት፡፡ 2000፡፡ (ያልታተመ)፡፡

አፀደ ተፈራ፡፡ "የዋግኽምራ የወሊድ የጋብቻ እና የሞት ሥነ-ሥርዓት ፋይዳ ትንተና"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በፎክሎር መርሃ ግብር የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት፡፡ 2007፡፡ (ያልታተመ)፡፡

እታገኘሁ አስረስ፡፡ "የአርጐባ ብሄረሰብ አፋዊ ትውፊቶችና መገለጫዎች ጥበቃ ጥናት"፡፡ *የአራተኛው አገር አቀፍ የባህል አውደ ጥናት መድበል፡፡* ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ፡፡ 2010፣ ገጽ 143-173፡፡

ከሣቴ ብርሃን ተሰማ፡፡ *የዐማርኛ መዝገበ ቃላት*፡፡ 2005፡፡

0ቢዪ አስማማው፡፡ “የአርጎባ ብሄረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች፣ በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን፣ አርጎባ ልዩ ወረዳ”፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር መርሀ ግብር ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ 2005፡፡ (ያልታተመ)፡፡

የአርጎባ ልዩ ወረዳ የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት፡፡ *በአፋር ብ/ክ/መንግስት የአርጎባ ልዩ ወረዳ*፡፡ SSB ማተሚያ ቤት፣ 2010፡፡

“የአርጎባ ልዩ ወረዳ ገጽታ”፡፡ *ሲፋኖ ጥር*፣ 2000፣ ገጽ 21-22፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ፡፡ *ኣማርኛ መዝገበ ቃላት*፡፡ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማተሚያ ቤት፣ 2006፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ *የምርምር መሠረታዊ መርሆችና አተገባበር*፡፡ አልፋ አታሚዎች፣ 1998፡፡

ደስታ አማረ፡፡ “የህይወት ኡደት (የወሊድ፣ የጋብቻና የሞት) ስርዓቶች ክዋኔ ትንተና በወሊሶ ሊበን ኦሮሞ”፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በፎክሎር መርሃ ግብር የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት፡፡ 2007፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ደስታ ተ/ወልድ፡፡ *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት*፡፡ አዲስ አበባ፡፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1970፡፡

ድርብወርቅ ብፁ፡፡ “የጉምዝ ብሄረሰብ ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ኡደት ሽግግር ደረጃዎች ሥርዓት በማንዱራ ወረዳ”፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት፡፡ 2007፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ግርማ አውግቸው ደመቀ፡፡ *አርጎብኛ - አማርኛ መዝገበ ቃላት*፡፡ አዲስ አበባ፡፡ መርዋ ሶ. አታሚዎች፣ 2003፡፡

ፈቃደ አዘዘ፣ *የሥነቃል መምሪያ*፣ አዲስ አበባ፣ 1991፡፡

Abbink, J. "An Historical-Anthropological Approach to Islam in Ethiopa: Issues of Identity and Politics". *Journal of African Cultural Studies*. Vol. 11, no. 2, 1998, pp. 109-124.

Abebe Kifleyesus. "Food Familiarity and Novelity in a Condition of Socio-Economic Transformation in North-Central Ethiopia". *Journal of Eastern African Studies*. Vol. 1, No. 3, 2007, pp. 449-465.

__________. "The Argobba of Ethiopia are not the Languages They Speak". *Aethiopica*. Vol. 09, 2006, pp. 7-22.

__________. "The Dynamics of Ethnicity in a Plural Polity: Transformation of Argobba Social Identity". Northwestern University. A Dissertation submitted to the Graduate School in Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree of Doctor of Philosophy in the Field of Anthropology. 1992.

Abu Dawud, I. H. *Sunan Abu Dawud*. Translated by Al-Khattab, Nasiruddin. Vol. 3. Darussalam, 2008.

___________. *Sunan Abu Dawud*. Translated by Qadhi, Yaser. Vol. 1. Darussalam, 2008.

Aklilu Asfaw. "A Short History of the Argobba". *Annals d´Éthiopie*. Vol. XVI, 2000, pp. 173-183.

Al-Krenawi A. and John R. Graham. "Conflict Resolution Through a Traditional Ritual Among the Bedouin Arabs of the Negev" *Ethnology*, vol. 38, no. 2, 1999, pp. 163-174.

Barnard, A. *History and Theory in Anthropology*. Cambridge, Cambridge University Press. 2004.

Barnard, A. and Jonathan Spencer. "Rite of passage" *Encyclopedia of Social and Cultural Anthropology*. London, Routledge, 1996, pp. 737-738.

Bascom, W. R. "Four Functions of Folklore". *The Journal of American Folklore*, vol. 67, no. 266, 1954, pp. 333-349.

Bauman, R. "Performance". *A Companion to Folklore*, edited by Regina F. Bendix and Galit Hasan-Rokem. Blackwell Publishing Ltd, 2012, pp 94-118.

___________. editor. *Folklore, Cultural Performances, and Popular Entertainments A Communications-Centered Handbook*. New York. Oxford University Press, 1992.

___________. "Verbal Art as Performance". *American Anthropologist*. Vol. 77, no. 2, 1975, pp. 290-311.

Bechhofer, F. and Lindsay Paterson. *Principles of Research Design in the Social Sciences.* London. Routledge. 2000.

Bell. C. *RITUAL Perspectives and Dimensions*. Oxford: Oxford University Press, 1997.

__________. *Ritual Theory, Ritual Practice*. Oxford, Oxford University Press, 1992.

Ben-Amos, D. "Performance". *FOLKLORE: An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music, and Art*. Santa Barbara, ABC-CLIO, Inc., 1997, pp. 630-634.

___________. “"Context" in Context”. *Western Folklore*, vol. 52, no. 2/4 1993, pp. 209-226.

___________. "Toward a Definition of Folklore in Context". *The Journal of American Folklore*. Vol. 84, no. 331, 1971, pp. 3-15.

Bender, M. L., et al. editors, *Language in Ethiopia*. London. Oxford university press. 1976.

Bernard, H. R. *Research Methods in Anthropology*. Oxford. AltaMira Press, 2006.

Brana-Shute, R. and Gary Brana-Shute. "Death in the Family: Ritual Theraphy in a Creole Community". *Anthropologica*. Vol. XXI. 1979, pp. 59-83.

Briggs, Charles L. "Since I Am a Woman, I Will Chastise My Relatives": Gender, Reported Speech, and the (Re)Production of Social Relations in Warao Ritual Wailing". *American Ethnologist*. Vol. 19, no. 2, 1992, pp. 337-361.

Bronner, S. J. editor, *The Meaning of Folklore the Analytical Essays of Alan Dundes*. Utah, Utah State University press. 2007.

Brown, G. "Theorizing Ritual as Performance: Explorations of Ritual Indeterminacy". *Journal of Ritual Studies*. Vol. 17, no. 1, 2003, pp. 3-18.

Collier, J, J. and Malcolm Collier. *Visual Anthropology: Photography as a Research Method*. Mexico. University of New Mexico Press, 1986.

Cooke, B. and Gary Macy. *CHRISTIAN SYMBOL AND RITUAL An Introduction*. Oxford, Oxford University Press, 2005.

Creswell, J. W. *Research Design Qualitative, Quantitative, and Mixed Methods Approaches*. California. SAGE Publications, Inc. 2014.

Daniel, K. "An Analysis of the Rites of Passage and Their Relation to Christianity". *International Journal of Sociology and Anthropology* vol. 1, no. 8, 2009, pp. 156-166.

Davis, K. "The Myth of Functional Analysis as a Special Method in Sociology and Anthropology". *American Sociological Review*.vol. 24, no. 6, 1959, pp. 757-772.

Dissanayake, E. "Ritual and Ritualization: Musical Means of Conveying and Shaping Emotion in “Humans and Other Animals". *Music and Manipulation: on the Social Uses and Social Control of Musi,* edited by Steven Brown and Ulrich Voglsten. Oxford, Berghahn Books. 2006, pp. 1-23.

Eller, J. D. *Cultural Anthropology Global Forces, Local Lives*. New York. Routledge. 2009.

Eriksen, T. H. *Small Places, Large Issues An Introduction to Social and Cultural Anthropology*. London. Pluto Press, 2011.

Farbod, M. S. "An Anthropological Study of Death and Funeral Ceremony with Focus in Gilan Province". *International Journal of Social Sciences*. Vol. 6, no. 4, 2016, pp. 55-61.

Federal Democratic Republic of Ethiopia Population Census Commission. *Summary and Statistical Report of the 2007 Population and Housing Census*. Addis Ababa፡ CSA Printing Press, 2008.

Fetterman, D. M. *Ethnography step-by-step*. California. SAGE Publications, Inc., 2010.

________________. "Emic/Etic Distinction". *The SAGE Encyclopedia of Qualitative Research Methods*. California, SAGE Publications, Inc. 2008, pp. 249.

Fife, W. *Doing Fieldwork Ethnographic Methods for Research in Developing Countries and Beyond*. U.S.A., Palgrave Macmillan, 2005.

Finnegan, R. *Oral Traditions and The Verbal Arts a Guide to Research Practices*. London, Routledge, 1992.

Flick, U. *An Introduction to Qualitative Research*. London, SAGE Publications: 2006.

Frobish, T. S. "Ritual as Communication". *Encyclopedia of Religious Rites, Rituals, and Festivals*. New York. Routledge, 2004, pp. 361-362.

Gennep, A. V. *The Rites of Passage*. Chicago: University of Chicago Press. 1960.

Gerhart, k. M. *The Material Culture of Death in Medieval Japan*. U.S.A. University of Hawaii press, 2009.

Getahun Amare. ″Definiteness in Argobba NPs″. *Nordic Journal of African Studies*. Vol. 23, no. 4, 2014, pp. 201-218.

________. "Argobba Verb Morphology and Syntax: A Documentation with Head-Driven Phrase Structure Grammar as Analytic Framework". Norwegian University of Science. Thesis for the Degree of Philosophy of Doctor. 2009.

Girma A. Demeke. ″The Ethio-Semetic Languages (Re-examining the Classification)″. *Journal of Ethiopian Studies*. Vol. 34, no. 2, 2001, pp. 57-93.

Gray, D. E. *Doing Research in the Real World*. London. SAGE publications, 2004.

Grimes, R. L. *Deeply into the Bone Re-inventing Rites of Passage*. London, University of California Press. 2000.

Gruenwald, I. *Rituals and Ritual Theory in Ancient Israel*. Netherlands. Brill, 2003.

Goldstein, K. S. *A Guide for Field Workers in Folklore*. Pennsylvania. Folklore Associates, Inc., 1964.

Gordon-Lennox, J. editor, *Emerging Rtual in Secular Societies A Transdisciplinary Conversation*. London. Jessica Kingsley Publishers, 2017.

Han, J. H. "Birth Rituals". *Encyclopedia of Religious Rites, Rituals, and Festivals*. New York. Routledge, 2004, pp. 48-52.

Harris S. N. "Ritual: Communication and Meaning". *Journal of Ritual Studies*, vol. 11 no. 1, 1997, pp. 35-44.

Hufford. M. "Context" *The Journal of American Folklore*, vol. 108, no. 430, 1995, pp. 528-549.

Ismaiel, M.I. *Sahîh Al- Bukhâri*. Translated by Khan, Muhammad Muhsin. Vol. 1. Darussalam, 1997.

_________. *Sahîh Al- Bukhâri*. Translated by Khan, Muhammad Muhsin. Vol. 2. Darussalam, 1997.

_________. *Sahîh Al- Bukhâri*. Translated by Khan, Muhammad Muhsin. Vol. 6. Darussalam, 1997.

Kalmijn, M. "Marriage Rituals as Reinforcers of Role Transitions: An Analysis of Weddings in the Netherlands". *Journal of Marriage and the Family*. Vol. 66, 2004, pp. 582-594.

Kleinig, J. W. *The Lord's Song. The Basic, Function and Significance of Choral Music in Chronicles*. Sheffeld, Sheffeld Academic Press, 1993.

Koster, J. "Ritual Performance and the Politics of Identity on the Functions and Uses of Ritual". *Journal of Historic Pragmatics*. Vol. 4, no. 2, 2003, pp. 211-248.

Kowalzig, B. *Singing for the Gods Performances of Myth and Ritual in Archaic and Classical Greece*. Oxford, Oxford University Press. 2007.

Kumar, R. *Research Methodology a step – by – step Guide for Beginners*. Los Angeles, SAGE. 2011.

Lan, Q. "Does Ritual Exist? Defining and Classifying Ritual Based on Belief Theory". *The Journal of Chinese Sociology*.vol. 5, no.5, 2018, pp. 1-14.

Langer, R. et al. "Transfer of Ritual". *Journal of Ritual Studies*. Vol. 20 no. 1, 2006, pp. 1-10.

Leslau, W. *Argobba Vocabulary*. Roma. Instituto per L'orente VIA A. Caroncini, 19. 1978.

____________. *English-Amharic Context Dictionary*. Otto Harrassowitz. Wiesbaden, 1973.

____________. ″Classification of the Semitic Languages of Ethiopia″. *Proceedings of the Third International Conference of Ethiopian Studies. Addis Ababa, 1966*. Addis Ababa, 1970, pp. 5-22.

Lobar, S. L. et al. "Cross-Cultural Beliefs, Ceremonies, and Rituals Surrounding Death of a Loved One". *Pediatric nursing*. Vol. 32, no.1, 2006, pp. 44-50.

Longhurst, R. “Pregnant Bodies, Public Scrutiny ‘Giving’ Advice to Pregnant Women.” *EMBODIED GEOGRAPHIES Spaces, Bodies and Rites of Passage*, edited by Elizabeth Kenworthy Teather. London. Routledge. 1999, pp. 77-88.

Malinowski, B. *A Scientific Theory of Culture and Other Essays*. The University of North Carolina Press.

McClymond, K. *Beyond Sacred Violence A Comparative Study of Sacrifice*. Baltimore. The Johns Hopkins University Press, 2008.

McWhorter, L. "Rites of Passing: Foucault, Power, and Same-Sex Commitment Ceremonies". *Thinking Through Rituals Philosophical perspective*, edited by Kevin Schilbrack, New York. Routledge, 2004, pp. 72-98.

Mohammed, H. et al. ″Sociolinguistic Survey among Ethnically Argobba Communities″. *ELRC Working Papers*. Vol. 2, no. 4, 2006, pp. 415-454.

Morris, M. W. et al. “Views from Inside and Outside: Integrating Emic and Etic Insignts About Culture and Justice judgment.” *Academy of Management Review*. Vol. 24, no. 4, 1999, pp. 781-796.

Mwandayi, C. *Death and After-Life Rituals in the Eyes of the Shona Dialogue with Shona Customs in the Quest for Authentic Inculturation*. University of Bamberg press, 2011.

Naidoo, L. "Ethnography: An introduction to Definition and Method". *An Ethnography of Global landscapes and corridors*, pp. 1-8.

Navon, L. "From Wordless Ritual to Ritual Words. An Analysis of the Ritualized Contact with Leprosy in Thailand". *Anthropos*. Vol. 4, no. 6, 1995, pp. 511-524.

Oring, E. "Three Functions of Folklore: Traditional Functionalism as Explanation in Folkloristics". *The Journal of American folklore*. Vol. 89, no. 351, 1976, pp. 67-80.

Pentikäinen, J. "Ritual". *FOLKLORE: An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music, and Art*. Santa Barbara, ABC-CLIO, LLC, 2011, pp. 1104-1110.

Pickering, W. S. F. "The Persistence of Rites of Passage: Towards an Explanation". *The British Journal of Sociology*. vol. 25, no.1, 1974, pp. 63-78.

Price, S. R. F. *Rituals and Power the Roman Imperial Cult in Asia Minor*. Cambridge. Cambridge University Press, 1986.

Radcleffe-Brown, A. R. *Structure and Function in Primitive Society*. Glencoe. The Free Press, 1952.

Rappaport R. A. *Ritual and Religion in the Making of Humanity*. Cambridge. Cambridge University Press, 1999.

______________. "Ritual". *Folklore, Cultural Performances, and Popular Entertainments*, edited by Richard Bauman. Oxford, Oxford University Press, 1992, pp. 249-260.

Reimers, E. "Death and Identity: Graves and Funerals as Cultural Communication". *Mortality*. Vol. 4, no.2, 1999, pp. 147-166.

Sax, W. S. "Ritual and the Problem of Efficacy". *The Problem of Ritual Efficacy*, edited by William S. Sax, Johannes Quack and Jan Weinhold. New York, Oxford University Press, 2010.

Schechner, R. *Performance Theory*. New York, Routledge. 1988.

Schensul, J. J. et al. *Enhanced Ethnographic Methods*. U.S.A., ALTAMIRA Press. 1999.

Seid Muhie. ″Documentation and Description of the Rekebot Traditional Conflict Resolution System of the Argoba Community″. Addis Ababa University. Presented in Partial Fulfillment for the Requirements for the Degree of Master of Arts in Documentary Linguistics and Culture. 2015. (Unpublished).

Seligman, A. B. et al. *Ritual and Its Consequences An Essay on the Limits of Sincerity*. Oxford, Oxford University Press. 2008.

Shenhar, A. "Metafolkloristic Additions to Stories by the Artistic Narrator". *Folklore*. Vol. 98, no.1, 1987, pp. 53-56.

Shujaa, M. J. "Rituals". *Encyclopedia of African Religion*. California, SAGE Publications, Inc., 2009, pp. 575-579.

Sims, M. C. and Martine Stephens. *Living Folklore An Introduction to the Study of People and Their Traditions*. Utah. Utah State University Press, 2005.

Simpson, J. and Steve Roud. *A Dictionary of English Folklore*. New York. Oxford University Press, 2000.

Srivastava, V. K. "Functionalism, Structural-Functionalism and Neo Functionalism" *MAN-001 Social Anthropology*. New Delhi. Graphic Printers, 2011.

Stitz, V. "The Western Argobba of Yifat, Central Ethiopia". *Proceedings of the first United States Conference on Ethiopian Studies. Michigan, 2-5 may 1973*, edited by Harold G. Marcus, East Lansing: Michigan, 1975, pp. 185-192.

Storey, J. *Cultural Theory and Popular Culture An Introduction*. London. Pearson Longman.

Sutlive V. "Ritual Control". *Encyclopedia of Religious Rites, Rituals, and Festivals*. New York. Routledge, 2004, pp. 362-366.

Tesfaye Hailu. "History and Culture of the Argobba." *Annales d'Ethiopie*.vol. XVI, 2000, pp. 195-206.

*The Quran*. Translated by M.A.S. Abdel Haleem, Oxford University Press, 2005.

Thomassen, B. "The Uses and Meaning of Liminality". *International Political Anthropology*, vol. 2, no. 1, 2009, pp. 5-28.

Toit, B. M. D. "Religion, Ritual, and Healing Among Urban Black South Africans". *Urban Anthropology,* vol. 9, no. 1, 1980, pp. 21-49.

Trimingham, J. Spencer. *Islam in Ethiopia*. FRANK CASS and CO. LTD.. 1965

Turner E. "Anthropology, Symbolic". *FOLKLORE: An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music, and Art*. Santa Barbara, ABC-CLIO, Inc., 1997, pp. 25-29.

Turner, V. *From Ritual to Theatre The Human Seriousness of Play*. New York. PAJ Publications. 1982.

________. "Symbolic Studies". *Annual Review of Anthropology*, vol. 4, 1975, pp. 145-161.

________. "Liminal to Liminoid, in Play, Flow, and Ritual: An Essay in Comparative Symbology". *Rice Institute Pamphlet*. Rice University Studies, vol. 60, no. 3, 1974, pp. 53-92.

________. "Symbols in African Ritual". *Science*, vol.179, no. 4078, 1973, pp. 1100-1105.

________. *The Ritual Process: Structure and Anti-Structure*. New York: Cornell University press, 1969.

Underberg N. M. “Virtual and Reciprocal Ethnography on the Internet: The East Mims Oral History Project Website.” *The Journal of American Folklore*, vol. 119, 2006, pp. 301-311.

Voigt, R. ″Argobba Language″. *Encyclopedia Aethiopica*. Harrassowitz Verlag. Wiesbaden, 2014, pp. 331.

Waldron, S. R. ″Argobba″. *Muslim Peoples : A World Ethnographic Survey*, edited by Richard V. Weekes. Greenwood Press. 1984, pp. 49-54.

Walliman, Nicholas. *Research Methods: The Basics*. London. Routledge, 2011.

Watts, J. W. *Ritual and Rhetoric in LEVITICUS from Sacrifice to Scripture*. Cambridge, Cambridge University Press. 2007.

Wetter, A. ″The Argobba of Tollaha - a Comparative Overview″. *Proceedings of 15th International Conference of Ethiopian Studies* edited by S. Uhlig. Verlag: Harrassowitz Verlag, 2006, pp. 899-907.

Wimalasena, N. A. "An Analytical Study of Definitions of the Term "Marriage". *International Journal of Humanities and Social Science*. Vol. 6, no. 1, 2016, pp. 166-174.

Zelealem Leyew. ″Argobba, the People and the Language″. *Sociolinguistic Survey Report of the Argobba Language of Ethiopia*. SIL International. 2001, pp. 4-27.

# አባሪ

## አባሪ 1. መሰረታዊ የምልከታ ጥያቄዎች

- የክዋኔው ቦታ የት ነው?
- የክዋኔው ቦታ ገጽታ ምን መልክ አለው? በአካባቢው ያለ ድምጽ፣ ሽታ፣ የአየር ሁኔታ ምን ይመስላል?
- ክዋኔው እንዴት ተጀመረ?
- የክዋኔው ሂደት ወይም ቅደም ተከተል ምን ይመስላል?
- የከዋኞች የአከዋወን ስልት ምን ገጽታ አለው? (አካላዊ እንቅስቃሴ፣ ድግግሞሽ፣ የድምጽ ምት)
- ሰዎች ምን ያከናውናሉ? በአውዱ ያላቸው ተግባር ወይም ሚና ምንድን ነው? እንዴትስ ያከናውኑታል?
- ከዋኞች እነማን ናቸው? (ስማቸው፣ ቁጥራቸው፣ ፆታቸው፣ እድሜያቸው፣ ማህበራዊ ደረጃቸው)
- ሰዎች እርስ በርስ ያላቸው ግንኙነት ምን ይመስላል? የግንኙነታቸው ስርዓት ምን ይመስላል?
- ሰዎች በአውዱ ያላቸው አካላዊ ቦታ የት ነው? ምክንያቱስ?
- የሰዎች አለባበስና አጋጌጥ ምን ይመስላል?
- በአውዱ ላይ ምግብና መጠጥ አለ? ምን ምን?
- በክዋኔው ጥቅም ላይ የዋሉ ሌሎች ቁሳዊ ነገሮች ምን ምን ናቸው?
- ክዋኔው ለከዋኞቹ ምንድን ነው? ምን ስሜት አሳደረባቸው?
- የሰዎች ስሜት ምን ይመስላል?
- ሰዎች ስሜታቸውን ይገልፃሉ? እንዴት? ይስቃሉ? ያለቅሳሉ?
- ሰዎች ድጋፋቸውንና ነቀፌታቸውን ይገልፃሉ? እንዴት?
- ሰዎች ክዋኔውን በተመለከተ ያላቸውን ስሜት ይገልፃሉ? እንዴት?
- የክዋኔው መዝጊያ ምን መልክ አለው? (አካላዊ ቦታ፣ ቁሳቁሶች)
- ክዋኔው መቼ ተጀመረ? መቼስ ተጠናቀቀ?
- ክዋኔው የቆየበት ጊዜ ምን ያህል ነው?
- አዲስ ወይም እንግዳ ክስተት ተከስቷል?
- የክዋኔው ምክንያት ምንድን ነው?

አባሪ 2. ምልከታ የተከናወነባቸው ስነ ስርዓቶች

| ተራ ቁጥር | የስነ ስርዓቱ ዓይነት | ምልከታ የተደረገበት ቀን | ምልከታ የተደረገበት ቦታ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የወሊድ ስነ ስርዓት | 5/10/2012 | ጋቾኔ | የአራስ ቤት ምልከታ |
| 2 | የወሊድ ስነ ስርዓት | 7/10/2012 | ጋቾኔ | የሰባት ቀን እጥበት |
| 3 | የወሊድ ስነ ስርዓት | 18/11/2012 | ጋቾኔ | የአርባ ቀን እጥበት |
| 4 | የወሊድ ስነ ስርዓት | 16/2/2013 | ጋቾኔ | የአምሮት ዋዜማ ዝግጅት |
| 5 | የወሊድ ስነ ስርዓት | 17/2/2013 | ጋቾኔ | የአምሮት ስነ ስርዓት |
| 6 | የወሊድ ስነ ስርዓት | 11/3/2013 | ላይ መጠቅለያ | የአምሮት ስነ ስርዓት |
| 7 | የወሊድ ስነ ስርዓት | 25/3/2013 | ላይ መጠቅለያ | የአምሮት ስነ ስርዓት |
| 8 | የወሊድ ስነ ስርዓት | 12/4/2013 | ጨኖ | የአራስ ቤት ምልከታ |
| 9 | የወሊድ ስነ ስርዓት | 17/4/2013 | ጨኖ | የአምሮት ስነ ስርዓት |
| 10 | ዘመናዊ የህክምና ተቋም | 23/2/2013 | ጋቾኔ | የሚሰጠውን ዘመናዊ የእርግዝና ክትትልና የወሊድ አገልግሎትን በተመለከተ |
| 11 | ዘመናዊ የህክምና ተቋም | 24/3/2013 | ላይ መጠቅለያ | የሚሰጠውን ዘመናዊ የእርግዝና ክትትልና የወሊድ አገልግሎትን በተመለከተ |
| 12 | የጋብቻ ስነ ስርዓት | 2/5/2013 | ጋቾኔ | የጉፍታ ስነ ስርዓት |
| 13 | የጋብቻ ስነ ስርዓት | 3/5/2013 | ጋቾኔ | የሰርግ ስነ ስርዓት |
| 14 | የጋብቻ ስነ ስርዓት | 9/5/2013 | ጋቾኔ | የሰርግ ስነ ስርዓት |
| 15 | የጋብቻ ስነ ስርዓት | 12/5/2013 | ላይ መጠቅለያ | የጐጆ መውጫ ስነ ስርዓት ዝግጅት |
| 16 | የጋብቻ ስነ ስርዓት | 13/5/2013 | ላይ መጠቅለያ | የሰርግ ስነ ስርዓትና የጐጆ መውጫ ስነ ስርዓት ዋዜማ |
| 17 | የጋብቻ ስነ ስርዓት | 14/5/2013 | ላይ መጠቅለያ | የጐጆ መውጫ ስነ ስርዓት |
| 18 | የጋብቻ ስነ ስርዓት | 23/5/2013 | ገበሮች | የጉፍታ ስነ ስርዓት |
| 19 | የጋብቻ ስነ ስርዓት | 24/5/2013 | ገበሮች | የሰርግ ስነ ስርዓት |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 20 | የጋብቻ ስነ ስርዓት | 27/5/2013-30/5/2013 | ገበሮች | የመልስ ስነ ስርዓት |
| 21 | የጋብቻ ስነ ስርዓት | 1/6/2013 | ገበሮች | የሰርግ ስነ ስርዓት |
| 22 | የጋብቻ ስነ ስርዓት | 7/6/2013 | ገበሮች | የጉጆ መውጫ ስነ ስርዓት |
| 23 | የጋብቻ ስነ ስርዓት | 8/6/2013 | ገበሮች | የሰርግ ስነ ስርዓት |
| 24 | የጋብቻ ስነ ስርዓት | 15/6/2013 | ገበሮች | የሰርግ ስነ ስርዓት |
| 25 | የጋብቻ ስነ ስርዓት | 18/6/2013 | ጨኖ | የጉፍታ ስነ ስርዓት |
| 26 | የጋብቻ ስነ ስርዓት | 19/6/2013 | ጨኖ | የሰርግ ስነ ስርዓት |
| 27 | የጋብቻ ስነ ስርዓት | 22/6/2013 | ገበሮች | የሰርግ ስነ ስርዓት |
| 28 | የሀዘን ስነ ስርዓት | 3/10/2012 | ገበሮች | የሀፈሻ ስነ ስርዓት |
| 29 | የሀዘን ስነ ስርዓት | 17/11/2012 | ጋቾኔ | የመሸኛ ዝግጅት፣ የአለቃቀስ ስነ ስርዓት፣ መተጋገዝ፣ የስራ ክፍፍል፣ ወዘተ (የቀብር ቀን ስነ ስርዓቶች) |
| 30 | የሀዘን ስነ ስርዓት | 27/12/2012 | ገበሮች | የወር መታሰቢያ ስነ ስርዓት |
| 31 | የሀዘን ስነ ስርዓት | 20/2/2013 | ጋቾኔ | የመሸኛ ዝግጅት፣ የአለቃቀስ ስነ ስርዓት፣ መተጋገዝ፣ የስራ ክፍፍል፣ ወዘተ (የቀብር ቀን ስነ ስርዓቶች) |
| 32 | የሀዘን ስነ ስርዓት | 26/2/2013 | ጋቾኔ | የቆዳ ማጠፊያ ስነ ስርዓት |
| 33 | የሀዘን ስነ ስርዓት | 18/3/2013 | ላይ መጠቅለያ | የዓግል መፍቻ ስነ ስርዓት |

## አባሪ 3. ለመረጃ ሰጪዎች የቀረቡ መሰረታዊ ጥያቄዎች

ሀ/ የወሊድ ስነ ስርዓትን በተመለከተ የሚቀርቡ ጥያቄዎች

- አርጐባ በባህሉ ጽንስ እንዴት ይፈጠራል ብሎ ያምናል/ሳይንሱ ሳይሆን/?
- ወሊድ በአርጐባ ብሄረሰብ ዘንድ ያለው ቦታ ምንድን ነው?
- የአንዲት ሴት እርግዝና እንዴት ይታወቃል?
- አንዴ እርግዝናዋ ከታወቀ በኋላ ሴቲቱ ከሌላው ሰው በተለየ ምን ይደረግላታል?
  - ነፍሰጡሯ ምክር ይሰጣታል? ማን ይመክራታል? ምን ትመከራለች?
  - ነፍሰጡሯ በተለየ ምን እንድትበላና እንድትጠጣ/እንድታደርግ ትመከራለች? የእያንዳንዱ ምክንያትስ ምንድን ነው?
  - ነፍሰጡሯ ምን እንዳትበላና እንዳትጠጣ/እንዳታደርግ ትመከራለች? የእያንዳንዱ ምክንያትስ ምንድን ነው?
- በነፍሰጡርነት ወቅት የሚከናወኑ ስነ ስርዓቶች ምን ምን ናቸው? እንዴትስ ይከወናሉ?
- ምጥ ሲጠነክር ምን ይደረጋል?
- የወሊድ ስነ ስርዓት የትና እንዴት ይከናወናል?
- ነፍሰጡሯ እንደወለደች የሚደረጉ ነገሮች ምን ምን ናቸው?
- አራሷና ህፃኑ በአራስ ቤት የሚደረግላቸው እንክብካቤ ምን መልክ አለው?
- የአራሷንና የህፃኑን ጤና መጠበቅ የሚደረጉ ልማዶች ምን ምን ናቸው?
- በአራስ ቤት ያሉ ክልክሎች ምን ምን ናቸው የእያንዳንዳቸው ምክንያትስ ምንድን ነው?
- ከወሊድ በኋላ የሚከናወኑ ስነ ስርዓቶች ምን ምን ናቸው? የእያንዳንዳቸውን ምንነትና አከዋወን በዝርዝር ይንገሩኝ?
- በወረዳው ስንት ጤና ተቋማት አሉ? የት የት ቀበሌዎች ውስጥ? ስንቶቻቸው ማዋለጃ አላቸው?
- ወላዶች በጤና ጣቢያ እንዲወልዱ ምን እያደረጋችሁ ነው?
- ብዙ ወላዶችን በጤና ተቋማት እንዲወልዱ አድርገናል ወይም ውጤታማ ነን ብላችሁ ታምናላችሁ? ካላመናችሁስ ምክንያቱ ምንድን ነው?
- በቤት ውስጥ የሚወልዱ አሉ? በምን ምክንያት?

- ሴቶች ክትትል ለማድረግና በጤና ተቋም ለመውለድ ጤና ጣቢያ እየመረጡ ነው ወይስ አይመርጡም? ለምን ይመስላችኋል?
- ለነፍሰ ጡር ሴቶችና /በምክርና ክትትል/ እና ለመውለድ ለሚመጡ በቅደም ተከተል ምን ምን ነገሮችን ታደርጉላቸዋላችሁ?
- በቂ የማዋለጃ ቁሳቁስ፣ ባለሙያና አምቡላንስ አሏችሁ? ምን ምን ችግሮች አሉባችሁ?
- በቅድመ ወሊድ፣ በወሊድና በድህረ ወሊድ ስነ ስርዓቶች ወቅት የተለወጡ ነገሮችና ክዋኔዎች ምን ምን ናቸው የለውጦቹ ምክንያቶችስ ምን ምን ናቸው?
- ትኩረታቸው ወሊድና ወሊድን ተከትለው የሚከወኑ ስነ ስርዓቶች የሆኑ ስነቃሎች የትኞቹ ናቸው?

ለ/ የጋብቻ ስነ ስርዓትን በተመለከተ የሚቀርቡ ጥያቄዎች

- በአርጎባ ጋብቻ ምን ትርጉም ይሰጠዋል?
- በአርጎባ ስንት አይነት የጋብቻ አይነቶች አሉ?
- ጋብቻ የሚፈፀመው በእነማን መካከል ነው ለምን?
- የጋብቻ እድሜ (ለወንዱና ለሴቷ) ስንት ነው?
- ወንዱ ለጋብቻ ሲደርስ የሚያገባትን ሴት የሚያጨው እርሱ ነው ወይስ ሌሎችም ያግዙታል?
- ለጋብቻ የምትሆንን ሴት የመፈለጊያ መቼቶች ምን ምን ናቸው?
- የጥሩ ሚስት መመዘኛ ምንድን ነው? የጥሩ ባልስ?
- ቅድመ ሰርግ የሚከናወኑ ስነ ስርዓቶች ምን ምን ናቸው? እንዴትስ ይከወናሉ?
- የታጨች ሴትና ወንድ ካልታጬት እኩዮቻቸው በተለየ እንዲያደርና እንዳያደርጉ የሚገደዱባቸው ነገሮች አሉ? ካሉ ምን ምን ናቸው? የእያንዳንዳቸውስ ምክንያት ምንድን ነው?
- የእጮኝነት ጊዜ ምን ያህል ነው? ጊዜውን እንዲረዝምም ሆነ እንዲያጥር የሚያደርጉ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?
- በእጮኝነት ጊዜ የእጮኛሞችና የቤተሰቦቻቸው ግንኙነት ምን መልክ አለው?
- የትኛው እለት፣ ቀንና ወር ለሰርግ ይመረጣል? ለምን? ለጋብቻ የማይመረጠውስ እለትና ወር የትኛው ነው? ለምን?

- ለሰርግ ቀን የሚደረጉ ዝግጅቶች ምን ምን ናቸው?
- የሰርግ ስነ ስርዓት እንዴት ይከወናል?
- አርጐባ ለድንግልና ምን አይነት ቦታ ይሰጣል?
- ሙሽራዋ በሙሽርነት ጊዜዋ የሚንከባከባት ማን ነው?
- ከሰርጉ ማግስት ጀምሮ የሚከወኑ ስነ ስርዓቶች ምን ምን ናቸው እንዴትስ ይከወናሉ?
- በቅድመ ሰርግ፣ በሰርግና በድህረ ሰርግ ስነ ስርዓቶች ወቅት የተለወጡ ነገሮችና ክዋኔዎች ምን ምን ናቸው? የለውጦቹ ምክንያቶችስ ምን ምን ናቸው?
- ትኩረታቸው ጋብቻና ጋብቻን ተከትለው የሚከወኑ ስነ ስርዓቶች የሆኑ ስነቃሎች የትኞቹ ናቸው?

ሐ/ የሀዘን ስነ ስርዓትን በተመለከተ የሚቀርቡ ጥያቄዎች

- ለአርጐባ ሞት ምንድን ነው?
- በሟች ማንነትና በአሟሟት ሁኔታ ተመስርቶ ለሞት የተለያየ ብያኔ ይሰጣል? ከተሰጠ እንዴት?
- የሞተ ሰው ነፍሱ ወዴት ትሄዳለች? መድረሻዋ የት ነው?
- ነፍስ ወደ መዳረሻዋ የምትደርሰው መቼ ነው?
- የሙታን አለም ምን መልክ አለው ምን ይመስላል?
- የአሟሟት ሁኔታን እና የሟች ማንነትን መሰረት በማድረግ የሀዘን ስነ ስርዓት ማድረግና አለማድረግ አለ? ካለ እንዴት?
- አንድ ሰው ታሞ ለሞት ያደርሰዋል ተብሎ ስጋት ሲኖር በቤት ውስጥ ምን ምን ዝግጅቶች ይደረጋሉ?
- አንድ ሰው ለሞት የሚያሰጋው ነው ተብሎ የሚታሰበው ህመምተኛው ምን ምልክት ሲያሳይ ነው? መሞቱስ የሚታወቀው እንዴት ነው?
- ከሞት እስከ ቀብር ያሉ ስነ ስርዓቶች ምን ምን ናቸው? እንዴትስ ይከወናሉ? ግንዘት፣ የአለቃቀስ ሁኔታና የጉድጓድ አቆፋፈር ስነ ስርዓቶች እንዴት እንደሚከወኑ አስረዱኝ?
- በቤት ውስጥ ምን ዝግጅቶች ይደረጋሉ?
- በሀዘን ስነ ስርዓት ወቅት ያለ ማህበራዊ ግንኙነት እንዴት ይገለፃል?

- የቀብር ስነ ስርዓት የሚከወነው የት፣ መቼና እንዴት ነው?
- በቀብሩ ቀን የሚከወኑ ዝርዝር ነገሮች ምን ምን ናቸው? እንዴትስ ይከወናሉ?
- የቀብሩ ቀን ከቀብሩ በኋላ ምን ምን ነገሮች እንዴት ይከወናሉ?
- ከቀብር ማግስት ጀምሮ የሚከናወኑ ስነ ስርዓቶች ምን ምን ናቸው? አከዋወናቸውስ እንዴት ነው?
- ሰዎች ሀዘንተኞችን የሚያስተዛዝኑት እንዴት ነው?
- ሀዘንተኞች ሀዘናቸውን ለመግለጽ ምን ምን ነገሮችን ያደርጋሉ?
- የሀዘን ጊዜ በአብዛኛው ስንት ቀን ነው? እንደሟች ማንነትስ ይለያያል?
- የመታሰቢያ ስነ ስርዓቶች ይከወናሉ? የሚከወኑ ከሆነ ስነ ስርዓቶቹ ምን ምን ናቸው? መቼ፣ የትና እንዴትስ ይከወናሉ?
- የመታሰቢያ ስነ ስርዓቶች ለሁሉም አይነት አሟሟትና ለሁሉም ሟች ይከወናሉ ካልተከወኑ ለምን?
- የመታሰቢያ ስነ ስርዓቶች ክዋኔ ዓላማ ምንድን ነው? ስነ ስርዓቶቹ ባይከወኑ ምን ይከሰታል ተብሎ ይታመናል?
- በቅድመ ቀብር፣ በቀብርና በድህረ ቀብር ስነ ስርዓቶች ወቅት የተለወጡ ነገሮችና ክዋኔዎች ምን ምን ናቸው? የለውጦቹ ምክንያቶችስ ምን ምን ናቸው?
- ትኩረታቸው ሞትና ሞትን ተከትለው የሚከወኑ ስነ ስርዓቶች የሆኑ ስነቃሎች የትኞቹ ናቸው?

አባሪ 5. የተደረጉ መደበኛ ቡድን ተኮር ውይይቶች ዝርዝር

| ተራ ቁጥር | የውይይት ርዕሰ ጉዳይ | የውይይት ቦታ | የውይይት ቀን |
|---|---|---|---|
| 1 | የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓት | ጋቸኔ | 30/2/2013 |
| 2 | የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓት | ጨዋ | 27/4/2013 |
| 3 | የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓት | ገበሮች | 30/6/2013 |
| 4 | የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓት | ጐዜ | 15/7/2013 |
| 5 | የአርጐባ ብሄረሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ስርዓት | ላይ መጠቅለያ | 16/7/2013 |

አባሪ 6. የአፋር ክልልና የአርጐባ ልዩ ወረዳ ካርታ

